# ዶክተር አሸብር

## እና ሌሎችም




አሌክስ አብርሃም

10ኛ ዕትም

# ማውጫ


1. አስር የሽቶ ጠርሙሶች በግድግዳ ላይ — 5
2. ተሰቀለ ቢሉኝ 'ባርኔጣው' ነው ብዬ — 15
3. ከሰሀራ ቢታች — 21
4. ትንሽ ወደግራ ዘምበል... — 44
5. አ ገ ዛ ላ ታ ለ ሁ . . . !! — 49
6. የፍርምባ ጦርነት — 54
7. ተ ሸ ከ መ ና ታ ል !! — 57
8. ደወል — 59
9. የአባዬ ስልክ እና ባዮሎጂ — 65
10. ሁለት ብር ስንት ዶላር ነው ? — 72
(አንዱን ወንዝ ሁለት ጊዜ ስንሻገራት)
11. አግዚአአአአአአአአአ — 77
12. ንፋስ ወዴት ነህ ቢሉት ማርና ወተት ወዳለበት — 84
13. 'ቆጠራ ላይ ስለሆንን መግባት ክልክል ነው' ኮሚቴው !! — 88
14. የመግቢያ ፈተና — 92
15. አብድ እና ዘመናይ — 96
16. ከፍሪጅ የተጫረ እሳት — 101
17. የታረሙ ነፍሶች — 112
18. በብረትና ቻፕስቲክ በተከበበ ከተማ እነሆ የመልአክ ድምጽ ተሰማ — 119
19. ዝግመተ ለውጥ — 126
20. ፈንዲሻ ሲቆሉት ድምፅ ሲበሉት ድምፅ — 137
21. "ሸረኛ" "እና" "ደህና" "በአንድ ላይ ሲሄዱ በሸረኛው በኩል ተናደ መንገዱ — 141
22. የመደርደሪያው ጫፍ — 150
23. አለሁላት...!! — 162
24. ትንቢት... — 168
25. ዶክተር አሸብር — 172

# 1 አስር የሽቶ ጠርሙሶች በግድግዳ ላይ

አሸከም...አሸከም...አሸከም (ያዝ እንግዲህ!)

ደግሞ እስከስስስስስስ (አሳየው...ላላየው)

እልልልልልልልልልልልልልልልል...ችቦ አይሞላም ወገቧ (ያዝ እንግዲህ!)

የጎረቤታችን ሰርግ ነው:: የኑአሚን ተፈራ:: ዘፋኝ ስለሆነች ይሆን ዘፈኑ የደመቀው:: ማንትስ ባንድ የሚባል፣ እንደ አንበሳ አዳኝ "ያዝ እንግዲህ" ማለት ከሚያበዛ የባህል ዘፋኝ ጋር ሰርጉን እያደመቁት ነው:: መንደሩ አብዷል:: ቢራ አራት መኪና ሙሉ ተዘርግፎ "ጠጡ!" ተባለ :: ጠጅ፣ ወይን ጠጅ፣ አባይ ቢጫ ልብስ ለብሶ ሰርጉ ላይ የተገኘ እስኪመስል ስክርርር እስኪል አላፊ አግዳሚው::

ከሰርጉ በፊት...፣

"የልጃችን የወይዘሪት ኑአሚን ተፈራ እና የታደለ ግርማ የጋብቻ ሥነሥርዓት የሚፈፀመው እሁድ ከቀኑ 7፡00 ሰዓት 19... ዓ ም ስለሆነ ከባለቤትዎ ጋር ተገኝተው የደስታችን ተካፋይ እንዲሆኑ ተጋብዘዋል::"

ጥቅስን እንደመፈክር፣ "እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ማንም አይለየውም...ምዕራፍ 7፣ ቁጥር 3"፣ ሌላ መፈክር፣ "ከእንግዲህ አንድ ናቸው እንጂ ሁለት አይደሉም:: ...ምእራፍ፣ ...ቁጥር፣ የምር ምስጋና፣ "አድርገህልኛልና ለዘላለም አመሰግንሀለሁ" (እንደገና ስጦታ ካርድ የሚከፋፈተው፣ አብረቅራቂ የጥሪ ወረቀት ላይ በየገፁ ጥቅስ አለ::የሙሽሪት የሕይወት ገፅ ቢገላበጥ፣ እንኳን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ፣ የዘወትሩ "አባታችን ሆይ..." በወጉ አይገኝም:: "የዕለት እንጀራችን..." ላይ ያልቃል እምነቷ!!)

አድራሻችን፣ "ከፊታውራሪ አሰፋ ግዛው ቤት ጎን":: ይሄ የጥሪ ካርድ የተሰጠው ለአባቴ

“ፊታውራሪ አስፋ ግዛው” ነው!! ያውም በወርቃማ ቀለም ተሽሞንሙኖ እንደግቢ በር በትልቁ ግራና ቀኝ ተከፋች ተደርጎ፣ የሙሽራውና የሙሽሪት ፎቶ አስማት በሚመስል ቀለም ተሥሎበት፣ ደግሞ ካርዱ በጨለማ ውስጥ ያበራል:: (እዮብ አንድ ቀን የሚያበራ ፅሁፍ ያለበት እስክርቢቶ ይዞ፣ “እንዴት በጨለማ ያበራል?” አልኩት፤ “በፎስፎረስ ነው ፅሁፉ የተፃፈው” አለኝ::ከዛች ቀን ጀምሮ ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ አብሪ ትል፣ የቤታችን አምፖል ከፎስፎረስ የተሰሩ መሰለኝ::)

አባቴ ተቃጠለ ::ነደደ :: የጥሪ ካርዱን ሲያይ በከዘራው መሬቱን ቀጭ ቀጭ እያደረገ በእግሩም እየተመተመ ዐይኑን የሚያሳርፍበት ቦታ አጥቶ ተንከራተተ:: በሰንሰል ቅጠል፣ በቆርቆሮና በጥሬ ካብ የተቀቀረውን ዘባተሎ የግቢያችንን አጥር፣ ተገንጥሎ ቋሚው ጋር በሽቦ የታሰረውን የግቢውን የቆርቆሮ በር እያ - መዛግ ጀምሯል በሩ:: ሲዝግ ይገነጠላል:: የበሰበሰውን የበረንዳ መደገፊያ ጣውላ ቃኘ፣ “እንዲህ ምልከት አድርጉኝ እንጂ በወግ ማዕረግ ለመዳሩማ አልታደልኩም:: እዎ ከእኔ ቤት ጎን ሰርገኛው ይጉረፍ” አለ::‘ወይኔ አባባ፣ ሊያለቅስ ነው እንዴ’ አልኩ እኔ:: ከምር እንባው በዓይኑ ሞልቷል::

እህቴ እዮብን አፈቀረችው ፤ እዮብም አፈቀራት ፤ በጣም ተፋቀሩ :: (እዮብ ማነው ካላችሁ እዮብ የእህቴ ፍቅረኛ ነው፤ ሌላ መታወቂያም ማንነትም የለውም:: እህቴ የእዮብ ባንዲራ ናት፤ ኢትዮጵያዊያን ሮጡም ተዋጉም ባንዲራው ነው አይደለም ቀድሞ የሚታየው:: እዮብ ይኑርም አይኑርም በእህቴ ነው የሚከበረው (እዮብ ማነው? ይሄ የሳምሪ ጓደኛ?) አይነጣጠሉም ‘ጠይም ባንዲራው’ ናት::)

ሁሉም ሰው እዮብን “እድለኛ ነው” ፤ “አፈሰ” ይለዋል:: ለእህቴ የሚሰጠው አስተያየት ግን ይቀላቀላል:: ፒያሳ ታክሲ እየጠበቀ፣ “የምትገርም አፍቃሪ፣ የእግዜር ሰው፣ ትሁት” ያለው አስተያየት ሰጪ ቁራ ሳይደርስ፣ “ምን ነከቷት ነው እዚህ (ጣሙጋ...ሬሳ...ጣውላ...ቀድረ ቀላል... ጠኔያም...‘ሱሰኛ’...በዘኔ...የቆመ እባብ የመሰለ...እህል አይቶ የማያውቅ የመሰለ) ልጅ ላይ ሙጭጭ ያለችው? እችን የመሰለች (ኬክ...መልአክ...ውብ...መለሎ...ምናሊዛ...ወለላ...የማር ሰፈፍ...ፀሐይ... ፅጌሬዳ...እንቡጥ...ጠይም አሳ መሳይ...‘ሴክሲ’)...” ይላል ፤ በዕርግጥ እዮብ እንዳሉት ነው- ‘ሱሰኛ’ ከሚለው ውጪ፤ እህቴም እንዳሏት ናት ፤‘ሴክሲ’ የምትለዋ ቃል ግን ተናጋሪዎቹ ሲናገሯት ከስሪቷ ታፈነግጣለች:: አርፈው (አማላይ) ቢሉስ !!

ቆንጆ ሴት መውለድን፣ ቤት ውስጥ የነዳጅ ጉድጓድ እንደማግኘት አድርጎ የሚወስደው ‘የአዲስ አበባ’ ህዝብ፣ እህቴን ሲያይ “የብረት መዝጊያ የሚሆን አማች አምጥታ እዚህ እድሜ ልኩን ከፍቱን የኖረ፣ በሩ የዛገ ቤት ላይ ትገጠግጠዋለች” ብሎ በኩራት ይናገር ነበር !!

እህቴ ግን እዚህ ግባ የማይባለውን፣ ለሰው ዐይን እንደፋዬ ገላ የቀለለውን፣ የህይወት ነፋስ ማሳረፊያ አሳጥቶ የሚያንሳፍፈውን እዮብን አፈቀረች :: ያውም በፍፁም ልቧ፣ በፍፁም ነፍሷ እንደእግዜር !! እዮብ የእህቴ እግዜር ነው:: እግዜር በእህቴ አይቀየምም:: እግዜር እንደመንደራችን ጎረምሶች አይደለም:: የፍቅር አምላክ ስለፍቅር እስከጥግ መውረድን መዋረድን ያውቃታል::

እናም እዮብ የእኔ መልአክ፣ የእህቴ እግዜር ነው...!!

"ኧ...ረ እጂ ላይ እንዳይሞት! ይሄ ሞት የጀመረው ልጅ" ይላሉ እህቴን የሚቋምጡ ቁምጥና ልብና ህሊናቸውን ያጠቃው ባለጉንድሽ ልብ ጎረምሶች ፡፡ ጠዋት ሲወጡ ሰባት ልብስ ለከተው ስምንተኛውን መርጠው የሚለብሱ ሴት አውሎች !! እዮቤን ያሙታል (እዮቤ የኔ ሚስኪን በድሪቶ የተጠቀለለ ወርቅ፡፡) እነዚህ የሴት ስም ሲያቆላምጡ የሚውሉ የዘነጡ ቆሻሾች እዮቤን ያሙታል ፡፡

"እዩብዬ ና እኛ ጋር ዋል ዛሬ" ትለዋለች እህቴ ደውላ፡፡

"አባባ አሉ እንዴ ?" በፍርሃት ይጠይቃል፡፡

"ችግር የለውም፡፡ እንደውም 'ያ ልጅ የት ጠፋ?' ሲል ነበር ማታ" ትላለች እህቴ ፤ አባባ ግን ማታ እንደዛ አላለም፡፡ አባቴ እዮብን ለአይኑ ይፀየፈዋል፡፡ ሲያየው ደሙ ይፈላል፡፡ እዮብ ሲመጣ አባቴ ተነስቶ ከቤት ይወጣል፡፡ እየፈራ፣ "አባባ ደህና ዋሉ" ሲለው እንዳልሰማ ያልፈዋል፡፡ እዮብ ዞር ብሎ ሰው ያያል ሃፍረቱን ማን እንደተጋራው ሊቃኝ፡፡ ምንጊዜም እኔን ብቻ ነው ከስሩ የሚያየኝ ፡፡ እኔ የእዮቤ ጋራ ነኝ ፡፡ በሰለለ ህይወቱ፣ ብቸኝነት በሚረጭ አይኑ 'የኔ ጋራ የሚሆን? ሲል፣ 'እኔኔኔኔ' ብዬ ላንቃዬ እስኪሰነጠቅ የጮህኩ ፡፡ እናም ከጎኑ የቆምኩ፡፡ እህቴማ ጎኑ አይደለችም፣ ውስጡ ናት፡፡

"ከምን ተሰራሽ ?" ብትባል፣ "ከስጋ ፤ ከመንፈስና ከእዮብ" የምትል እህቴ !!

ታደለ የሚባል ሰው ወደ ሰፈራችን እህቴን ወደድኩ ብሎ መጣ፡፡ የት እንዳያት አላውቅም፡፡ (በከፉ አይኑ) ቁመቱ የሚያምር፣ ፈገግታው 'ሳቁ እንሳቅ' አዋጅ !! የቀይ ዳማ፣ እንዳች ግርማ ሞገስ ያጎናፀፈው 'ሳድግ እንደሱ ነው የምራመደው' ብያለሁ፡፡ 'ሳድግ እንደሱ ነው እጄን በመስኮት ላይ አስደግፌ መኪና የምነዳው' ብያለሁ፡፡ 'ሳድግ እንደሱ ነው በእርጋታ የታሸገ ውሃ 'ቷ' አድርጌ የምከፍተው' ብያለሁ፡፡ 'ሳድግ አማርኛን በእንግሊዝኛ ላንቃ የምለፋደድባት እንደሱ ነው' ብያለሁ፤ ይሄ ሰው እህቴን ወድዶ ወደ እኛ ሰፈር መጣ፡፡ ያውም በቆመችበት ሰው ሲነካት "ፂው ፂው" የምትል መኪና ይዞ !!

ሰፈሩ ሁሉ የታደለ መሪ ጠቋሚው ሆነ፡፡ አማልዱኝ ሳይል፣ ድፍን አገር አማላጁ ሆነ፡፡ (እንግዳ ተቀባይ...ሂሂሂ)
"አውስትራሊያ ዘጠኝ ዓመት፣ አሜሪካ ሶስት፣ ስዊዲን ሁለት ዓመት ኖሮ የመጣ ዶክተር ነው" አሏት፡፡

"ሁለት ሴቶች በፍቅሩ በረኪና ጠጥተዋል፣ አንዷቷ መኪናው ጎማ ስር ተነጥፋ 'ካላገባኸኝ ጨፍልቀኝ!' ብላው ቀስላ ተርፋለች፣ ሶስት ከህንፃ ዘለው ተፈጥፍጠዋል፣ አስራ ሰባት የት

እንደደረሱ አይታወቅም ! ልብሳቸውን ጥለው ብን ጥን ብለውለታል :: (አምስት ሙት፣ አንድ ቁስለኛ፣ አስራ ሰባቱ የት እንደደረሱ ያልታወቁ...ሂሂሂ)" ለእህቴ ይሄን ዜና አንብበውላታል:: ('ዓለሙን ሁሉ ንቆ ተከተለሽ' ብለው ሴትነቷን ሊለኩሱት)::

"መኪናው ሚሊየን፣ ስልኩ ሃምሳ ሺ ፈሪ ነው፣ ቤቱ ከውበቱና ከታላቅነቱ ብዛት አንድ ቀን ጠቅላይ ሚንስትሩ፣ 'ውይ ዛሬ ከምን ጊዜው ቤተ መንግስት ደረስኩ!' ብለው ዘው ብለዋል እዚህ ፍልውሃ ጋ" አሏት::

እዮቤ አጠገቧ ቆሞ እየሰማ፤ "የወንዶች አውራ ባል መጥቶልሻል፣ አልጋ ሲሉሽ አመድ አትሁኝ!" አሏት::

"ኧረ የወንድ ጡር አለው" እነሄለን፣ እነሜሮንና ገሊላ (የመንደራችን ዘመነኛ ሴቶች ! ባደ ቦርሳቸውን አንጠልጥለው ቦሌ ለቦሌ ሲያቃጥኑ ያጡት 'ዲያስፖራ' መንደራቸው ድረስ ሲከሰት 'አሳዝኗቸው'::)

"የወንድ ጡር አለው ኢታንገላችው" አሏት፤ በወንድ ጡር የተገዛ ቀሚሳቸውን እየነሰነሱ፣ በወንድ ጡር ግብዣ የገዘፈ ዳሌያቸውን እያውረገረጉ:: ('እኔ ብሆን ኖሮ አይነት ቁጭት...') የሰጋ አናከራይም...ሂሂሂ) የኪራይ ቤቶች !! (ባለትዳር

"ወደዛ ቶሎ እንደሚሆን አድርጊውና ሰርጉን አብዪን" ያሉም አሉ:: (አፈር፣ ጠጠር ይብሉ::) አንድ ቀን ሳምሪ ክፍል ውስጥ ቡና ተፈልቶ ክፍሏ በእጣን ታፍና ሳምሪ በቢጃማ ፍራሹ ላይ ተቀምጣ አስቴር እየዘፈነች ('ቁጭ ብለህ አጫውተኝ አትለይ ከጎኔ' እያለች) እንዲህ አለ፣

"ሳምሪ"

"ወይዬ እዩ" በአፏ አቤት ማለቷ አልበቃት ብሏት በእጇ እጁን እየያዘችው:: እዮብ መናገር ይፈራል:: እጁን ይዛ አይን ዐይኑን እያየች ጠበቀችው::

"አንድ ነገር ልነግርሽ ነበር እንዳትቆጭ" እየፈራ ፊቱ በሐዘን ተወርሮ አስፈቀዳት:: እጁን ቀስ ብላ ለቀቀችው፣ ፊቷ ተቀያየረ:: ምን እንደሚል ቀድማ የሰማች ይመስል፣ ሳግ በተናነቀው ድምፅ፣ "ተወው አትንገረኝ ...እ..ን ዳ ት ና ገ ረ ው!" አለች ::

"ታ...ዲያ ከእኔ ጋር እስከመቼ ሳምሪ..." እዮብ በምሬት ተነፈሰ:: "ካልፈለግከኝ ሂድ፣ 'አልፈለግኩሽም ስለቸሽኝ' በል - ሰበብ አታብዛ" እንባዋ ተዘረገፈ::

ዝምምምምምምምምምምምምምምም !! የተጣደው ቡና ይንተከተካል...!! እንባዋ ጠብ ጠብ ጠብ ጠ.ብ ጠ..ብ ጠ....ብ ....ጠ.....ብ ጠ.....ብ! ጠ....

"ልሂድ!" አለና ተነሳ እዮብ:: እጄን ይዞኝ ከእጁ ጋር እየተጫወትኩ ነበር:: እጁ ላይ ባለችው የነሀስ አምባር ('ማን ሰጥቶህ ነው?'...'እናቴ' ብሎኛል አንድ ቀን::) እህቴ ዝም አለች:: እዮብ አፍንጫዋ ጠመም ያለች ቆዳ ጫማውን አጠለቀ:: ጫማውን ሲያጠልቅ ጎንበስ ሲል እየዋለሁ ከኋላው:: ጥቁር ጅንስ ሱሪው የኋላ ኪሱቹ ጠርዝ ላይ በረዶ መስሎ ጨርቷል፣ ሳስቷል፣ ሳውቀው ጀምሮ እችው ናት ሱሪው - ወጥቶ ሄደ::

እህቴና እኔ ተነስተን በሩ ላይ ቆምን:: ከኋላው እያየነው መንገዱን ቀጠለ:: ሲያፍተለትላት የነበረችውን የማስቲካ ልባስ እጁን አወናጭፎ ወረወራት - ወደ አበባው ውስጥ::

ድንገት "እዩዬ" ብላ ተጣራች እህቴ:: ዞረ እዮብ::

"ጠብቀኝ!" ወደ ቤት ገባች:: ለቅቃው የሄደችውን እጄን በአየር ላይ እንዳንከረፈፍኩት አሰብኩ፣ ወደ እዮብ ልሂድ ወይስ...እንደቆምኩ በፌስታል የተጠቀለለ ነገር ይዛ መጣች:: በአጠገቤ ስታልፍ ዱለት ሸተተኝ::አሃ ዛሬ በግ ታርዶ ነበር ለካ!! አቀብላው የሆነ ነገር ተነጋግረው ተመለሰች:: ወደ እኔ ስትቃረብ እዮብ እንዲህ አላት፣

"ሳምሪ፣ የበቀደሙን ሰሀን ሳላየው ቆሜበት ተሰበረ" በይቅርታ ዓይነት...::

"ደንባራ ማሚ እንዳትሰማ ከዚህ ጥፋ" ተሳሳቁ::

ወደ ቤት ስንመለስ "የትኛው ሰሀን ነው የተሰበረው?" አልኳት::

"ዝም በል!"

ዝም!!

ዲያስፖራው ለሰማይ ለምድር የከበዱ ሸማግሌዎች ወደቤታችን ላከ:: አባቴ ፊታውራሪ አሰፋ ግዛው በደስታ አበደ:: እናቴ በፍርሃት ዝም ብላለች:: ጎረቤቱ አሰፍስፎ ሰርጉን ጠበቀ:: ለሰርጉ የሚለብሰውን መረጠ:: "ያው ዲያስፖራ ጠይቆ እንቢ አይባልም፣ ያውም አንዲት ተራ ፀሃፊ የጡረተኛ ልጅ":: ይሁንና መልሱን ለመስማት አሰፈሰፈ፤ የብሔራዊ ቡድን ወሳኝ ጨዋታ ውጤት ለመስማት እንጂ የእህቴን 'እገባለሁ' ፣ 'አላገባም' ምላሽ ለመስማት አይመስልም አሰፋሰፉ - ሰፍሳፋ ሁሉ!!

እህቴ ሳምራዊት ላቧን ጠብ አድርጋ የምትኖር ጨዋ መሆኗን ማንም ያውቃል :: በወር 1600 ብር ደመወዝ እየተከፈላት ቴሌ በኦፕሬተርነት ትሰራለች:: ጥሩ ልብስ አትለብስ፣ አትኳኳል- ጓደኛ የላት:: 1600 ብር ትቀበልና 700 ብር ለእማማ ፣300 ብር ለአባባ ትሰጣለች:: 300 ብር ለይታ ታስቀምጣለች - በቀጣዩ ቀን ሥራ የምትገባ ከሆነ በሚስጥር፣ "እዮብ ሲመጣ ይሄንን ስጠው እሺ እንዳትጥል" ብላ 300 ብሩን ትሰጠኛለች:: እዮብ ሲቀበለኝ ደስ አይለውም:: እኔ ብሆን እጨፍርለት ነበር ይሄን ሁሉ ብር ባገኝ:: አንዳንዴ የታክሲ ብር ስታጣ፣ (ብዙ ጊዜ አታጣም) "ማሚ ትንሽ ከአስቤዛ የተረፈ ብር ይኖርሻል?" ትላለች::

ሥራ ስትሄድ ከመሬት ተነስቼ እናፍቃታለሁ:: ከዛ እደውልላታለሁ:: "ጤና ይስጥልኝ የሰሜን ምስራቅ ሪጅን ቴሌ ኮሚዩኒኬሽን ፅ/ቤት እባክዎ ምን ልርዳዎት ?" ትላለች ሳምሪ:: መንፈስ ትመስለኛለች:: የማላውቃት ደግሞ ፍጥነቷ - ሳምሪ እኮ ስትናገር ቀስ ብላ ነው:: እንዴት ቻለችበት?! እንደትልቅ ሰው ስላናገረችኝ እህቴን እፈራታለሁ:: ቀስ ብዬ ስልኩን እዘጋዋለሁ:: ድምጿን ስሰማ ደስታ በመላ አካላቴ ይፈሳል - እወዳታለሁ :: አንድም ቀን ግን ደውዬላት እንደነበረ ነግሬያት አላውቅም::) በዚች ደመወዝ ቤተሰባችንን ታስተዳድራለች:: የአባባም ጡረታ ተጨምሮበት::

ሽማግሌዎቹ ለሳምንት ተቀጥረው ከሄዱ በኋላ አባባ ምን አለ፣ "እግዜር ቀኝ እግሩን ቤታችን አስገባ::" ሳምሪ ሲነገራት ምንም ሳትደናገጥ፣ "አይ አባባ የማይሆን ነገር ለምን ታስባለህ"

"ምን...? ('ምናልሽ አንቺ ጨምላቃ!' በሚመስል የፊት ገፅታና ድምፅ) ምኑ ነው የማይሆነው ነገር፣ የተከበረ፣ ጨዋ፣ ምራቁን የዋጠ ባል ማግባቱ ነው - የሚሆነውን ንገሪኝ" አለ በደም ፍላት ዐይኑን እያጉረጠረጠባት :: እየው አባቴ ፈታውራሪ አሰፋ ግዛው ባንዴ ፈታውራሪ መሸሻ ሲሆን - ያውም መሐል አዲስ አበባ ላይ !!

"አባባ እኔ አሁን ማግባት አልፈልግም " ትንሽ የፈራች መሰለች::

"ምን ዳር ዳር ትያለሽ! ይሄ እንደተተኮሰባት ሚዳቆ ውቃቢው የተገፈፈ ዱርዬ ጋር ስጃጃል ቆሜ ልቅር አትይም" (የእግዜርን ቀኝ እግር ገፍታ ከቤት ስታስወጣ ምን ያድርጋት::)

ሳምሪ እንባዋ መጣ:: ጭንቅ አትወድም:: አማርኛው ሁሉ ያጥራታል:: ለፍቅር ብቻ ፈጥሯት ለንትርክ የሚሆን ቃል ከየትአባቷ ታምጣ::

አባቴ ቀጠለ፣ "የማንንም ስልክ እየተቀበልሽ 'ሃሎ' ስትይ ከመዋል በክብር ብትንፈላሰሽ አይሻልም?" (አንዳንዴ አዲስ ነገር ሊጭኑብን ሲፈልጉ ያለንን የሚያስጥሉብን ልምጭ ብዛቱ)

"ስራዬን እወደዋለሁ አባባ፣ አንተስ 'በጀግንነት የተዋጋህለትን የቆሰልክለትን' ሕዝብ አይደል 'ሃሎ' እያልኩ ሳገለግል የምውለው" እንዴ ሳምሪ ናት የተናገረችው - ገረመኝ::

"በጀግንነት የተዋጋህለትን" የሚሉት ሁለት ቃላት አባባን ለሁለት ደቂቃ ዝም አስብለውት ቆዩና፣ ወደነበረ ቁጣው ተመለሰ:: "እሱን ተይው፣ ድፍን የኢትጵያን ሕዝብ 'ሃሎ' ከማለት ከአማሪካ የተደወለ አንድ ስልክ ማንሳት ይሻላል:: ደሃ ቢደውልም ቢያነሳም ትርፉ ብር ማስቆጠርና ጆሮ ማደንቆር ነው::"

"አባባ አጭሩ ነገር እኔ አላገባም" ብላ ብድግ ስትል፣

"ተቀመጭ !" ብሎ ጮኸባት:: በድንጋጤ ዘፍ ብላ ተቀመጠች:: የሆነ ሰው ከኋላዋ ፀጉሯን ጎትቶ ያስቀመጣት ነበር የምትመስለው:: እኔ ራሴ ተከትያት ልነሳ ነበር:: ለሷ

የተወረወረው "ተቀመጭ" አስቀመጠኝ:: እንደለማዳ ውሻ ምንጣፉ ላይ ከእግሯ ስር ኩስስ ብዬ ነው ይሄን ሁሉ የምሰማው:: ስታወራ በደመነፍስ ፀጉሬን በጣቶቿ ታበጥርልኛለች::

ከዛን ቀን ጀምሮ በገባች በወጣች ቁጥር ከአባቴ ጋር ዱላ ቀረሽ አምባጓሮ ሆነ:: አባባ የሚናገረው ቃል ሁሉ ያበሳጫል፣

"አንችን ከመውለድ ጦር ሜዳ በሞትኩ:: ለአሞራ እራት በሆንኩ" ይላል::

ሽማግሌዎቹ እንደነገ ወዲያ ሊመጡ እንደዛሬ ሳምሪ ድክም ብሏት ስትገባ ገና ከበረንዳው አባባ ተቀበላት:: እስከ ማታ ሰደባት፣ "የሰው ትንሽ..." አላት:: "ቤቴ ድረስ ወንድ እየጎተትሽ ስትዳሪ ዝም ማለቴ አስናቀኝ" አላት::

ሳምሪ በአንድ ሳምንት የቀኝ ዐይኗ ስር ማዲያት የሚመስል ነገር ወጣባት:: ፊቷ ጠቆረ፣ ስታለቅስ የምታድርበት ዐይኗ ያስታውቃል:: ....

ብዙ ነገር ያየን ሰዎች ነን፣ ማግኘትንም ማጣትንም - ገና ለገና እያመጣሽ የምትወረውሪልንን ደመወዝ ጠባቂ አድርገሽን ናቅሽን - ማን አለብኝ አልሽ::"

"ኧረ ተው እንዲህ አይባልም" አለች ከፉ ደግ ተንፍሳ የማታውቀው እናቴ በቁጣ አይኗ እየተንቀለቀለ:: እንባዋ እየቀደማት:: እናቴ ከተናገረች ጉዳዩ መርሯል ማለት ነው !!

"ዝም በይ! አንች ነሽ የልብ ልብ የሰጠሻት:: እንደሰዎቹ እናቶች ስትንዘላዘል አትመክሪያትም? ጭራሽ ለእርሷ ከማበር:: ለነገሩ አንችስ ማን ሆንሽና - የእናቷ ልጅ!!" ብሎ እናቴን ኩም አደረጋት :: (እናቴን ከቡና ቤት አግኝቶ ነው ያገባት)

ወደ እህቴ ዞሮ፣ "አይንሽን እዚህ ቤት እንዳላየው:: መድሃኒያለም አይለመነኝ:: አንዱ ቦታ ሂጂ አንጥፊ እለምናለሁ እንጂ ያንቺን ገንዘብ ከአንግዲህ አልበላም...!!" አላት እየተንዘፈዘፈ::

"አባባ እኔ ካለ እናንተ ምን መሄጃ አለኝ ?" አለች ሳምሪ:: (ሳግ ባነቀው ድምፅ)

"መሄጃሽንማ ገፋሽ፣ ወርቅሽን ጭቃ ላይ ጣልሽው:: ሂጂ እዛ ከንቱ ጋር፣ አብረሽው በየጎዳናው ዙሪ! አባይ ማደሪያ ሳይኖረው አሉ..."

እህቴ ዝም ብላ ፀጉሬን ታሻሻለች:: አያያዟን ግን እስኪያመኝ ድረስ አጥብቃው ነበር፣ በጣቶቿ መቆፈር ዓይነት::ለአባባ ያላትን ፍቅር እናቴ ላይ ገድላ ልትቀብረው ያሰበች ነው የምትመስለው:: እንደውም በዚህ ሳምንት በጠና ታምሞ ነበር:: ተነስታ ወደክፍሏ ሄደች:: ተከትያት ሄድኩ:: ክፍሏ ውስጥ ገብታ እንደወትሮው ጫማዋን

አልቀየረችም:: ሻንጣዋን አነሳች ከፈተችው፣ አልጋዋ ትራስጌ የነበረውን የእዮብን ፎቶ ስታነሳ አለቀሰች:: በቲሸርት ጠቅልላ ሻንጣዋ ውስጥ አስቀመጠችው:: አንድ የቆየ ባዶ የሽቶ እቃ ወደ ቦርሳዋ ጨመረች::

"ሂድ ወደ ሳሎን" አለችኝ::

"አልሄድም" ብዬ እግሯ ላይ ተጠመጠምኩ:: ብር ብላ የምትሄድብኝ መሰለኝ :: እንቅ ! እጇ እስከደረሰበት አቅፌያት::
እቅፍ አደረገችኝ:: እቅፏ ላይ እንቅልፍ እንደወሰደኝ ትዝ ያለኝ ጠዋት ስነቃ ነበር:: የለችም፣ የእዮብ ፎቶ የለም:: ሻንጣዋ የለም:: ሜማዎቿ የሉም:: ፎጣዋ የለም:: የጥርስ ቡርሽ፣ የጥፍር መቁረጫና መሞረጃዎቿ የሉም:: የእህቴ ትዝታዎች ቤቱ ውስጥ የሉም - ልቤ ውስጥ ብቻ:: ቤቱ ቤት ብቻ ሆኗል:: አይ ቤቱ በረንዳ ሆኗል - እኔ በረንዳ አዳሪ::

ትራሱ ላይ፣ "ይሄን ለእማማ ስጣት፣ ይሄን ለእዮቤ እንዳትጥል!..." ከሚል ማስታወሻ ጋር የመቶ እና የሃምሳ ብር የብር ኖቶች::(የት ሄደች?) በጥድፊያ ሳሎኑን አልፌ ወደ በረንዳው ሄድኩ፣ አባቴ ውዳሴ ማሪያሙን በተመስጦ ይደግማል::

"አባባ ሳምሪስ ?" አልኩት ሳልፈራው::

"ሂድ ወዲያ...!!" አለኝና ወደ ውዳሴው 'አንች የማለዳ ብርሃን ነሽ፣ አንች መጠጊያ ላጡ...' ወደ ቤት ገብቼ...::

"እማማ ሳምሪስ ?" ፀጥ ብላ አየችኝና በማይሰማ ደካማ ድምፅ "ሄደች" ብላኝ ወደ ጓዳ ገባች ::

ተንደርድሬ ወደ ስልኩ ሄድኩ:: አባባ ያየኛል ብዬ ሳልፈራ ደወልኩ፣ "ጤና ይስጥልኝ ቴሌ ነው ምን ልርዳዎት" አለ አንድ ጎርናና ድምፅ ያለው ኦፕሬተር::

"ሳምሪን ነው የምፈልገው፣ ሳምሪ እህቴን - አለች ? ነይ እኔንም ውሰጅኝ ብሎሻል በልልኝ:: 'እኔ እኮ እወድሻለሁ ለምን ትተሽኝ ሄድሽ' በልልኝ - ሳምሪ እህቴን"

"ማሙሽዬ ይሄ እኮ ቴሌ ነው...ሃሃሃሃሃ"

*** *** ***

ዲያስፖራው እዛው ጎረቤታችን ኑአሚን የምትባል የማታ ጭፈራ ቤት የምትሰራ ዘፋኝ አገባ:: አስተማሪ ቦይ ፍሬንዷን 'አፍንጫህን ላስ' ብላው:: ለእህቴ በተተኮሰው የሀብት ጥይት ፍቅሯን ገደለች !!

*** *** ***

ቁራሌ የሚሰራ አንድ የሰፈራችን ልጅ አለ:: ከነስሙ 'ጃምቦ ቁራሌው' አንድ ቀን የሰፈር ልጆች ጋር "ኢላማ ኢላማ" ስንጫወት ደረሰና ኬሻውን አስቀምጦ ተቀላቀለን:: የእኛን ኢላማ ሰብረን ኢላማ የሚሆን ነገር ስናፈላልግ ድንገት ከእቃ ማስቀመጫው ውስጥ አንድ ጠርሙስ አወጣና አስቀምጦ ጠርሙሷን ለመስበር ድንጋይ አነሳን፣ጃምቦ ወረወረ - ሳታት:: ተረኛ እኔ ነኝ አነጣጠርኩ፣ ጠርሙሱን አየሁት:: ልቤ ደነገጠ:: ቀርቤ አየሁት - የሳምሪ የሽቶ ጠርሙስ!! ቢቆሽሽም ራሱ ነው::

"አንተ የት አባህ አገኘሽው ?" አልኩት ግራ ተጋብቼ ፤ እንባዬ መጥቶብኝ:: ሳምሪዬን ያገኟት ነው የመሰለኝ:: ሳምሪዬን ኢላማ አድርገን በድንጋይ ያባረርናት፣ ቤተሰቡ፣ ሰፈሩ፣ ኅብረተሰቡ፣ ዲያስፖራው...ሳምሪን የወገርናት...:: "ከእናንተ ሀጢያት የሌለበት ይውገራት" ሲባል ዘራፍ እኛ፤ሀጢያት የለብንም:: እኛ ቅዱሳን:: እኛ ንፁህን ብለን ሳምሪ ላይ የወረወርን:: መሄጃ የሌላትን ወፍ በድንጋይ ከደሃ ጎጆዋ ያባረርናት::

"ኧረ ማሪያምን ሰርቄው አይደለም፣ እህትህ ሻንጣ ይዛ የሄደች ቀን እዛ ሱቁ አካባቢ አገኘችኝና 'ይሄን ትገዛለህ...?' ስትለኝ ብር ከስሙኒ ገዛኋት:: የሚፈለግ መስሎኝ ነበር:: ግን በቃ አይፈለግም ሲሉኝ ዝም ብዬ አስቀምጬው ነበር::ከፈለግክ ውሰደው" አለ ጃምቦ::

ጠርሙሱን ወሰድኩት :: እቅፍ አድርጌ፣ በቲሸርቴ ስር ሰውነቴ ላይ ለጥፌ:: (ይሄ ጠርሙስ ባዶ የሆነው ምን ሆኖ ነው?ሽቶው ሳምሪ የምትባል ሚስኪን፣ እዮብ የሚባል ፍቅሯ እግር ላይ ደፍታው ነው፣ በቃ እንደዛ ነው:: 'ሽቶውን ስለምን እናባክነዋለን፣ ሽጠን ለድሀ አንመፀውተውምን?' ብለዋት ነበር ጎረቤቶች አባቴን ጨምሮ !!) ከሳምሪ የቀረኝ ነገር አንድ ባዶ የሽቶ ጠርሙስ ብቻ - ከኋላ ጓደኞቼ ሌላ ጠርሙስ ሲሰብሩ ሰማሁ - ከሽሽሽሽ!!

አስር የሽቶ ጠርሙሶች በግድግዳ ላይ - አንዱን ስንከሰክሰው ምንም ይቀራል፣

ምንም ይቀራል...

ምንም ይቀራል...

ምንም ይቀራል...

(ተጠንቀቅ !! ባንዲራውን አውርድ፣ ጠይሙን ባንዲራ - ለሞላ ንፋስ እንዳይውለበለብ የከለከልከው ቆንቋና ሁሉ !! ባወረድከው የክብር ባንዲራ ፋንታ ድሪቶህን ስቀል ! ቀለም አልባ፣ ታሪክ አልባ ድሪቶህን !! ቡቱቷም::)

ሂሳብ ምናባቱ ያገባዋል ስለ ስሜት - ቁጥር አባቱ ይብላና !!

ሌላ ቀን ማታ፣ አባባ አንድ ነገር ጠየቀኝ:: ሰርጉ ባለፈ በስንት ወሩ:: "ይሄ የሰርግ መጥሪያ ሌሊት ሌሊት እንደ አብሪ ትል የሚያበራው ለምንድን ነው ?"

ረጋ ብዬ መለስኩለት - እንደ ሳይንቲስት፣ “ጽሁፉ ከፎስፎረስ ስለተፃፈ ነው::”

አባባ ዝም ብሎ ቆየና፣ “ወደዛ ወስደህ ጣልልኝ !!” አለ

መኝታ ቤቴ ወስጄ የሳምሪ ሽቶ ጠርሙስ ጎን አስቀመጥኩት:: ማታ መብራቱን ሳጠፋ ካርዱ ላይ ያሉት ፅሁፎችና ጌጣጌጦች ተብረቀረቁ:: ግን ‘ፎስፎረስ’ ምንድን ነው:: ካርዱ ያበራል የሳምሪ የሽቶ ጠርሙዝ ግን አያበራም::

ያልታደለ ዘመን ላይ ቅጥፈት ነው የሚያብረቀርቀው ::

ይነጋል ! የሳምሪ ጠርሙስ ያበራል !

ይነጋል - ቀጣፊው ካርድ ይጨልምበታል::

ይነጋል ! የበራው ሁሉ ብርሃን አለመሆኑ የሚገለጥበት ዘመን ይመጣል !

አንስቼ በጨለማው ውስጥ ወረወርኩት:: ራሴ እስኪፈነዳ ጨለማው ላይ አፍጥጬ አሰብኩ::

እህት አለችኝ:: ጥቁር ዘንፋላ ፀጉር ያላት:: ሳቋ ‘እንደ ፎስፎረስ’ በጨለማ የሚያበራ:: እህት አለችኝ እጆቿ ፀጉሬ ላይ ሲርመሰመሱ የሚያስፈነጥዙኝ:: እህት አለችኝ - ሙዚቃ ድምፅ ያላት:: እህት አለችኝ ለተራብ ዱለት የምትሰጥ-ታድዬ !! እህት አለችኝ አንድ ቦታ...ስሟ በከፉ የማይነሳ:: ሴቶች ላይ ከፉ ሊናገር የጀመረ ሁሉ እሷን ሲያይ ዝም የሚልላት ጨዋ እህት አለችኝ::

እህት አለችኝ ሳምሪ የምትባል:: ፍቅሯን ሽጣ በሊሙዚን ከመሄድ የሽቱ ጠርሙስ ለቁራሌ ሽጣ በታክሲ መሄድን የመረጠች:: ያላትን ለእማማ ሰጥታ የዓለምን ችግር በብር ከስሙኒ ልትፋለመው የወጣች::ስሟ ሳምራዊት ነው !! የአባቷን ስም አላውቀውም:: አባት የላትም:: እኔም አባት የለኝም !!

ኃይለኛ ዝናብ ጣለ::

# ተሰቀለ ቢሉኝ 'ባርኔጣው' ነው ብዬ

# 2

የአራተኛ ዓመት ተማሪዎች ሳለን፣ አስቻለው የሚባል ጓደኛችን ለስምንት የምንጋራው ዶርም ውስጥ ራሱን በቀበቶ ሰቅሎ ተገኘ:: አስደንጋጭ፣ አሳዛኝ ጉዳይ !! አስቻለው የለየለት ሱሰኛ ነበር (የሞተ ሰው ወቀስክ አትበሉኝና...):: ያጨሳል፣ ይቅማል፣ ይጠጣል...(ያገኘውን ሁሉ ይጠጣል...በተለይ ጠላ ነፍሱ ነው):: ውሀ እንኳን ሲጠጣ 'ትፍ ትፍ' ይላል፣ በጠላ ገፈት ለምዶበት !! ሀሺሽ ምናምንም ከመውሰድ አልፎ ግቢ ውስጥ ያከፋፍል ነበር:: ኧረ አበዛኸው እንዳትሉኝ እንጂ ሴተኛ አዳሪ ሳይቀር ዶርም ይዞ ይመጣ ነበር (አልፎ አልፎ እንግሊዝኛ ጣል የምታደርግ ሴተኛ አዳሪ ከገጠመቻችሁ፣ ግቢ ጎራ ብላ ልታውቅ ትችላለች ብላችሁ ጠርጥሩ::)

ያው አንዳንዴ ደግሞ ታጥቦ የተሰጣ ልብስ ያነሳ ነበር እየተባለ ይታማል(እኔ 'ንኳ ቲሸርቴን ከወሰደብኝ በኋላ እንዲህ ሲል አስፈቅዶኛል...'አብርሽ...ያንተ መሆኗን ሳላውቅ ያችን ሁልጊዜ የምትለብሳትን ሰማያዊ ቲሸርት ወስጃታለሁ...'):: እና አስቻለው ራሱን ሰቅሎ ሞተ ::

ታዲያ ብዙ ተማሪዎች እኛ ዶርም እየመጡ አስተዛዘኑን፤ "አስቹ አሪፍ ልጅ ነበር...አይዞን.... ወይ አስቺ ሆዱኮ ንፁህ ነው ፤ ላፉ ይናገራል እንጅ...አንዴ ምን አደረገ መሰላችሁ..." እያሉ ስለደግነቱ ስለቸርነቱ እንደጉድ አወሩ ::ሲቆይ ዶርማችን በር ላይ በቀይ ተፅፎ የተገኘው ሙሾ እንዲህ ይል ነበር፣

*ተሰቀለ ቢሉኝ ባርኔጣው ነው ብዬ፣* (የዲግሪው ቆብ)
*ተሰቀለ ቢሉኝ ያ ሱሪው ነው ብዬ* (የነበረው አንድ ያረጀ ጅንስ ሱሪ ብቻ ነበር)
*ተሰቀለ ቢሉኝ 'ግሬዱ' ነው ብዬ*
*ለካስ አስቻለው ነው ትልቁ ዱርዬ !!*

ቢከፋንም ነገሩን በቅሬታ ፈገግታ አለፍነው (ይቅርታ...አላለፍነውም !):: ማታ ግማሹ ተኝቶ አንዳንዶችም አልጋቸውን ጋርደው እያጠኑ...እስናቀ የሚባለው የዶርማችን ልጅ፣ "ግን ምን ለማለት ተፈልጎ ነው ?" አለ ፊቱ ላይ ቁጣ እየተንተገተገ፤ እኔን ነበር የጠየቀኝ::

ጫማዬን እየፈታሁ ነበር ልተኛ::

"ምኑ እስኔ" አልኩት አይኔን ከጫማ ማሰሪያዬ ላይ ሳልነቅል...

በር ላይ የተፃፈው ግጥም ነዋ !!"

"ያው ሙድ ለመያዝ ምናምን ነዋ የሚሆነው...የግቢ ነገር ታውቀው የለ...ያንተ ሀዘን የሌላው ሀዘን ላይሆን ይችላል" አልኩ ቀለል አድርጌ...

"ኖ ኖ...ሙድማ አይደለም...ሆን ተብሎ የጎጃምን ህዝብ ታሪክ ለማጉደፍ የተሰራ ሴራ ነው" ብሎ ጠረጴዛውን በቡጢ ደቃው::

"ኧረ...እስኔ ምን ያገናኘዋል...ጎጃም እዛ ማዶ...ዩኒቨርስቲው እዚህ..."

"ዩኒቨርስቲ እንጂ ስንቱን ታሪክ ኩል የሚኩል...ስንቱን ጥላሸት የሚቀባ የተንኮል ማጀት::"

"ቆይ...እስቻለው የሸሮሜዳ ልጅ...የተፃፈው ስለሱ...እና ጎጃም..." አልኩ ሳቅ እየተናነቀኝ::

*"ተሰቀለ ቢሉኝ ባርኔጣው ነው ብዬ፣*
*ለካስ በላይ ኑሯል ትልቁ ሰውዬ"*

የሚለውን ግጥም እኮ ነው ቀይረው ለማንም ዱርዬ የሚጠቀሙበት..."

"አይ...እስቻለውንማ 'ማንም' አትለውም፣ አይደብርህም ትላንት ተለይቶን ዛሬ..." አንዱን ጫማዬን ፈትቼ አንዱን ሳልፈታ ከርክር...

"አይ ዶን ኬር...የበላይ ክብር በማንም ደደብ አይጎድፍም..." አለ:: እንደዛሬው ሲበሳጭ አይቼው አላውቅም::በጣም እየጮኸ ስለነበር የሚናገረው የዶርም ልጆች ከተኙበት እየበረገጉ ተነሱ:: የሚያጠኑት ግርዶሻቸውን ገለጥ እያደረጉ ብቅ አሉ::

"ምንድን ነው ሰላም አይደላችሁም..." አለ ገብረ መስቀል በአስናቀ ጩኸት ከእንቅልፉ በርግጎ ተነስቶ::

"ማን ጠራህ አንተን ?!" አለ አስናቀ በበለጠ ቁጣ ለነገር ተጋብዞ::
"ኧ..."

"ደንቆሮ"

"ማነው ደንቆሮ" አለ ገብረ መስቀል ሕልም ይሁን እውነት ግራ ገብቶት::
"አንተ ነሃ ! ሴታ ሴት ! በር ላይ እየተደበቅክ የሰው ታሪክ ከማጉደፍ እንደ ወንዶቹ ፊትለፊት አትናገርም..."

"ዋይ...ምን ጉድፍ ታሪክ ነው እሱ...እተ...ግሬድ ተለጠፈ እንዴ ?" አለ ገብረ መስቀል:: የታሪክ ተማሪ ነው፣ ቀልድ መስሎት ነበር::

"በላይ ሀገር አላስገነጠለም ! በላይ ወንዱ በዘር አልከፋፈለንም ! ለአንድ ኢትዮጲያ ሕይወቱን የሰጠ ጀግና ነው::"

"ዋ...ይ ታዲያ በዚህ ሌሊት በላይ በላይ ምትሎው ሙን ሁነ ኖው...?"

"በላይን እንኳን በር ላይ የተፃፈ ዝባዝንኬ፣ ባህር በር ላይ በመርከብ የተዘረገፈ ሰላቶ ጣሊያን ክብሩን አልነጠቀውም::"

"ባክህ አትጨህብን እናጥናበት" አለ ቶሎሳ ከግርዶሹ ብቅ ብሎ::

"ዝም በል ባክህ ! አንተ ላይ ማን ደረሰ..."

"ጩኸትህ ረበሸኝ" (ቶሎሳም የታሪክ ተማሪ ነው::)

"ጩኸቱ ጩኸትህ ነበር ቢገባህ...በላይ ላንተም ክብር ነበር የታገለው...ኢትዮጵያዊነት ስሜት ቢኖርህ ይቆጭህ ነበር..." አለው ሽቅብ ወደ ቶሎሳ አልጋ እየተመለከተ::

"ማነው የኢትዮጵያዊነት ስሜት የሌለው?"
"አንተ ነሃ ! ለስሙ የታሪክ ተማሪ ነህ ! በርህ ላይ ታሪክ ታንክ እንደሄደበት የቤት መኪና ተጨራምቶ እየተጻፈ አንተ ጋርደህ የአውሮፓ ተረት ታነባለህ...'ማንትስ በመርከብ ተጉዞ አሜሪካን አገኘ' በል የራስህ አገር ከእጅህ ላይ እየጠፋች::"

"አብርሃም...ኧረ በክርስቶስ ይሄን ሰው ፀበል ውሰዱት" አለ ዲንሳም እየሳቀ:: ቀልድ ይቀናዋል፣ ሁልጊዜ ሳቂታ ነው::

"ስርዓት ! ፀበል መቀለጃ መሰልህ እንዴ" አልኩት በብስጭት:: ጴንጤ ስለሆነ 'ኦርቶዶክስ እምነቴ ላይ ምናባቱ ያላግጣል' ብዬ ቱግ አልኩ ::

"እንዴ ፀበል ያድናል ትሉ የለ እንዴ ?"

"መቀለድ ሳይሆን ሞክረው...አንተም ከዚህ ዕብደትህ ትፈወሳለህ" አልኩት አፍጥጬበት !በዕምነትና በሚስትማ ቀልድ የለም (ሚስት እንኳን ....)::

"እኔማ ቃሉ እንደሚል፣ 'መዳን በሌላ በማንም የለም ትድኑበት ዘንድ..."
"ዝጋ እዛ !የምትሰብከውን ስበክ...ይሄን ተረትህን..."

"ጌታ ይገስፅህ"

"ማንን ነው የሚገስፀው አንተ ?..." በብስጭት ከአልጋው ላይ ጎትቼ ላወርደው ስንደረደር የጫማ ማሰሪያየ አወላከፈኝና አልጋው ስር ጥቅልል አልኩ::

ዲንሳሞ ጭራሽ መዘመር ጀመረ...
"ነብሱ በትዕቢት ያበጠ...
ጠላቱ ተገለበጠ.... ሃሌ ሉ...ያ"፡፡

ተነስቼ ላጋጨው ስል ሄኖክ ከዛ ተወርውሮ መጥቶ ገላገለን ፡፡

ዲንሳሞ ሊያቀም ነው..."እሽ ካልቻላችሁ ሪፈር ጻፉለት እንፀልይለት...በእየሱስ ስ.....ም!" አለ እጁን ወደ አስናቀ ዘርግቶ እየሳቀ...፡፡

"መናፍቅ ! ዋና ታሪክ አጥፊዎቹ እናንተ ናችሁ...ምን ታሾፋለህ...ዘረኞችን አትገስፅም?!" አለ አስናቀ ወደ ገብረመስቀል በአገጩ እየጠቆመ፡፡

"አተ አትጨሚለቅ...ሞታገስ አታውቅም ? ዙም ብለህ ሰው ጭቅላት ላይ ፉጥ ትላለህ...ጩምላቃ" ብሎ ዘሎ ከመኝታው ወረደ፡፡ ...ዶርሙ...ቀውጢ ሆነ ፡፡

አስናቀ ባለ በሌለ ኃይሉ ገብረ መስቀልን ሲደረግመው ከአልጋው ብረት ጋር ተጋጨ፡፡ ወዲያው የገብረ መስቀል እርግጫ አስናቀን ከፉ ቦታ ላይ አገኘው፡፡ እንደምንም አገላገልናቸውና ገብረ መስቀል ወጥቶ ሄዶ ሌላ ዶርም አደረ፡፡ በቀጣዩ ቀን አስናቀ ከየት እንደተወረወረ ባልታወቀ ድንጋይ ተፈንክቶ ክሊኒክ ዋልን ፡፡ ነጭ ፋሻውን እናቱ ላይ ጠምጥሞ ሲፎክር፣ ቅስናውን የገፈፉት የእግዜርን መንግሥት ይቆየኝ ብሎ ለምድራዊ መንግሥት የዘመተ አርበኛ ቄስ ይመስል ነበር ፡፡ በዚህች መነሻ ሰላም ጠፋ፡፡ ግቢ ውስጥ በአንድ ሳምንት ብቻ አራት ተማሪ ተፈነከተ...ቀላልና ከባድ ጉዳት !

የተፈነከቱ ተማሪዎች ዝርዝር፡-
ሰኞ.... አስናቀ
ማክሰኞ ማታ.... ኃይቶም
እሮብ.... አረጋ
ሐሙስ.... ተከላይ
አርብ.... መላኩ
ቅዳሜ.... ትርሀስ (የሴቶች እኩልነት)
እሁድ.... አትጠገብ (ቤተ-ክርስቲያን ስትሄድ...)
ሰኞ ማታ.... ሚስኪኑ አብርሃም !! ሰምታችሁኛል ? አብርሃም እኮ እኔ ነኝ !!

ስለአፈነካከቴ አጭር ገለፃ...
ሰአቱ ማታ 3፡00 ሰዓት አካባቢ ይሆናል...በግ ተራ...ሂሩት እና እኔ ጨለም ያለ ቦታ መርጠን በነፋሻው አየር እየተሳሳምን ነበር፡፡

ሚ...ሚጿጿጿ..."እስከዘላለሙ እወድሻለሁ ሂሩትዬ"

...ጷጷጷሟ፣ "አ..ብርሽየ ለምን ስልክ ስደውል ትዘጋብኛለህ ?"

..."ላይብረሪ ነበርኩ የኔ ማር...ጷጷጷ"

"አብርሽ ምንም ቢፈጠር እስከዘላለሙ አብሬህ መሆን እፈልጋለሁ"

...ቀኝ እጇ በቲሸርቷ ስር አልፎ የጡት ማስያዣዋን ጠንካራ ከፈፍ መሰርሰር ጀመረ:: (ጡት የላትም ለምንድን ነው የጡት ማስያዣ የምታደርገው ?! አንዳንድ ሴቶች በሌለ ጡት የጡት ማስያዣ ሲያደርጉ ልባቸውን ለመያዝ የሚጠቀሙበት ነው የሚመስለኝ...ታዲያ ጡት ከሌላት እጄ ምን እየፈለገ ነው ? ምን አፈላሰፈኝ ዝም ብዬ አልሰምም ጷጷጷሟ...)

ዓይኖቻችንን ጨፍነን በፍቅር አየር ላይ መንሳፈፍ ጀመርን...ሟፅፅፅፅ...ድንገት ትልቅ '...ጓ...!!!!!':: ከፍቅር ሰማይ የሚያምዘገዝግ የአየር መቃወሚያ !! ከነበርኩበት ከፍታ አምዘግዝጎ እውነተኛው ዓለም ላይ የፈጠፈጠኝ ድንጋይ ከኋላዬ ራስ ቅሌን ነረተኝ !! "ሂሩት ባል አላት እንዴ?..." የሚል ሀሳብ ብልጭ አለብኝና ራሴን ስቼ ወደቅኩ::

ከሊኒክ ውስጥ ስነቃ ግቢው ቀውጢ ሆኗል...ፌዴራል ፖሊስ...የአመፅ መበተኛ መኪና...
የተማሪ አመፅ...ጩኸት... መዝሙር !!
"አስቻለው ለምን ለምን ሞተ ?"
"አብርሃም ለምን ለምን ሞተ...?"

"ምን ? አ ብ ር ሃ ም...?" አይኔን ስገልጥ የዩኒቨርስቲያችን ነርስ (ያምሮት) እና ሦስት ፌዴራል ፖሊሶች ቆመዋል:: "ሲስተር!...አብርሃም ለምን ሞተ ሲሉ ሰማሁ ?..." "አዎ ! እንዴት ነህ አሁን ?" ጣረ ሞት የጠራት ይመስል ደንግጣ::

"አንችኑ ልጠይቅሽ እንጂ ተማሪዎቹ እንደሚሉት ሞቻለሁ ወይስ ....????" ከት ብላ ሳቀች:: እንደምንም ተነስቼ አልጋው ላይ ቁጭ ስል፣

"ስማ..." አለኝ ፌዴራል ፖሊሱ::

"አ...ቤት" አልኩ በድንጋጤ የጨበጠውን ጥቁር ዱላ እያየሁ:: ዱላው አፍ አውጥቶ የጠራኝ ነበር የመሰለኝ፣

"ተሻለህ ?"

ውይ ለዚህ ነው እንዴ..."አዎ አሁንማ..." ብዬ ከአልጋዬ ላይ ወርጄ ወደ በሩ ሳመራ፣

"ወዴት ነው ?" አለኝ በግርምት እያየኝ::

"ወደ ውጭ" መለስኩ::

"ተመለስ !!" 'ዘሩ ቀለጠ' አለ ያ ሰውዬ !! ለካስ ሦስት ፖሊስ ሌኔው ነበር !!

"አብርሽዬ እስኪ ተረጋጋ...ክርስቶስ እንኳን በሦስተኛ ቀኑ ነው ከሞት የተነሳው...ገና ባንድ ቀን የክሊኒክ በር ከፍተህ ሰላም ለእናንተ ይሁን ልትል አማረህ?...ሂሂሂሂ" አለች ነርሷ...::

"ሲስተር ምንድን ነው ?"

"እስረኛ ነህ !!" አለች በሹክሹክታ !!

"እ..."

"ሰ ም ተ ኻ ል"

"...ዩኒቨርስቲው ውስጥ በዘር በተነሳ ግጭት አንተና እስቻለው ባልታወቁ ሰዎች ተገድላችኋል፤ ! አሁን ተማሪው ለምን እንደተገደላችሁ እንዲገለፅለት እየጠየቀ ነው:: እና ደግሞ ግጭቱን ያስነሳችሁት አንተ...አስናቀ እና ...ዲንሳም ናችሁ:: የኃይማኖትም ጉዳይ አለበት...አብርሃም አርፈህ ብትማር ምናለበት..." አለችኝ:: የመጨረሻ ቃሎቿን ኮስተር ብላ ነበር የተናገረቻቸው:: ወዲያው ፌዴራል ፖሊሱ ቆፍጠን ባለ አነጋገር፣

"አልጋህ ላይ ተሰቀል!" ብሎ አዘዘኝ::

"እሺ..." ብዬ ወደ አልጋው ተጠጋሁ:: ድንኩ አልጋ እንደ ቀራኒዮ ራቀብኝ:: በሁለት ጊዜ ሙከራ አልጋው ላይ ተሰቀልኩ::

በሀሳቤ...

*ተሰቀለ ቢሉኝ ባርኔጣው ነው ብዬ (የዲግሪው)*
*ተሰቀለ ቢሉኝ እስቻለው ነው ብዬ*
*አብርሽም ታዘዘ ኧረ እናንተ ሆዬ....*

ብዬ ቀና ስል...ከነርሷ ትልልቅ ጡቶች መሐል መስቀሏ ተንጠልጥሏል:: መስቀሉ ላይ ጌታ እየሱስ ተሰቅሎ አየሁት::

"ሂሩትዬስ..." ብዬ ነርሷን ጠየቅኳት:: ፍቅራችንን ታውቃለች፣ ስንታመም ሁሉ ወደ ክሊኒክ የምንመጣው ከሂሩት ጋር አብረን ነበር::

"ሂሩትዬማ...አንተ ተፈንክተህ እንደወደቅክ ሂሩት ተያዘችና ሦስቱም ፖሊሶች በየተራ 'ታውቂዋለሽ ?' እያሉ ሲጠይቋት፣ ሦስት ጊዜ 'አላውቀውም' ብላ ወደ ቤቷ ሄደች" አለችኝ አሁን መሰቀል ሙሉ ሆነች...ኤሎሄ፣ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ ?

# ከሰሀራ በታች 3

የፍቅርተ ጂንስ ሱሪ ታጥቦ ከተሰጣበት የልብስ ማስጫ ገመድ ላይ ጠፋ:: "የትኛው ሱሪ?" የሚል ይኖራል፤ - ፍቅርተ የነበራት አንድ ሱሪ ነበር:: የጠፋውም ይሄው አንድ ለናቱ የሆነ ሱሪ ነው:: የመንደሩ ሱሰኛ ጎረምሶች ለዕለት ሱሳቸው ማስታገሻ ወስደው ሸጠውት ይሁን አልያም ሞገደኛ ነፋስ እያግለበለበ ወስዶ አንዱ ቁርቁራ ሽጉጦት እግዜር ይወቅ:: ግራም ነፈሰ ቀኝ ከተገዛ ገና ስድስት ወር ብቻ የሆነው፣ ግርጌው ቀበኛ ከብት አኝኮ እንደተወው ጨርቅ የተተፈተፈው የፍቅርተ ጥቁር ጅንስ ሱሪ ታጥቦ ከተሰጣበት ገመድ ላይ ጠፋ:: ትልቅ የአገር ቅርስ የጠፋ ያህል ነበር አንጀቴ ቁርጥ ያለው:: ደምና አጥንት የተከፈለለት የአገር ድንበር የተቀረሰ ያህል ነበር ውስጤ በቁጭት የተንገበገበው::

በእርግጥ ይሄ ሱሪ በመታጠብ ብዛት የልጅነት ጥቁር ቀለሙ ተገፍፎ ግራጫ መሆን ጀምሮ ነበር:: ኸረ እንደውም እንደ ሰው ፀጉር በስተርጅና ነጫጭ ጭረት ጣል ጣል ያደረገበት ሱሪ ነበር:: ቢሆንም እርጅናው ከሱሪው ህያው ዋጋ ላይ ሽራፊ ሳንቲም ሊቀንስ አይቻለውም:: እርጅና የማያደበዝዘው እውነት፣ የዘመን ብዛት የማያጠፋው ሃቅ አለና፤ የዛ እውነት ማህደር ነው የተወሰደው::

የፍቅርተ ሱሪ ጠፋ ማለት የመንደራችን ባንዲራ ጠፋ እንደማለት ነው:: ይሄ ሱሪ ተራ ሱሪ ብቻ አልነበረም፤ የማንነት መቋጠሪያ ጨርቅ፣ የተገፉ ድሆች እንባ ማበሻ መሃረም፣ የፍቅር መከተቻ ከረጢት ነበር:: ምን ያደርጋል ! ታጥቦ ከተሰጣበት ገመድ ላይ ጠፋ ::

አንዳንዱ የደላው መንደርተኛ የፍቅርተ ሱሪ መጥፋቱን ሲሰማ "ይሄ ሁሉ ላይ ታች ማለት ለአንድ አሮጌ ሱሪ ነው ?" እያለ ወደየ ጉዳዩ ይጣደፋል:: "በሰው ቁስል እንጨት ስደድበት" ቢባልም ቅሉ እንዴት ሰው በራሱ ቁስል እንጨት ይሰድዳል? ስለፍቅርተ ሱሪ የማይመለከተው ማነው?

እኔ በበኩሌ የፍቅርተ ሱሪ ከሚጠፋ የወለዱት ይጥፋ ባይ ነኝ:: ስንለው ስንጮኸው የኖርነው ቃል ነበር የፍቅርተ ሱሪ ! አብሮን የኖረ ቃል ጨርቅ ለብሶ የተከሰተው በፍቅርተ ሱሪ ነበር:: ድንገት የቀኝ እጄን ስመለከተው ሁለት ጣቶቼን ከቦታቸው ላይ ባጣቸው እንኳን የዚህን ያህል የምደነግጥ አይመስለኝም:: እዚህ መዲናችን ውስጥ ያለው የአፍሪካ ህብረት ሕንፃ ድንገት ከስሩ ተነቅሎ የደረሰበት

ጠፋ ቢባል የፍቅርተን ሱሪ ያህል አያስደነግጠኝም፤ ኧረ ፍቅርተ ራሷ ብትጠፋ የሱሪዋን ያህል አታስደነግጠኝም:: ስለዚህ ሱሪ የተዳፈነ ተስፋ፤ የተኮላሸ ፍቅር አለና ሱሪው ሱሪ ብቻ አልነበረም::

ሱሪው የጠፋ ቀን ከሰዓት በኋላ ወደ ስምንት ሰዓት አካባቢ ከምማርበት ኮሌጅ ስመለስ እማማ አመለወርቅ በራቸው ስር ሁልጊዜ የሚቀመጡባት ጠፍጣፋ ድንጋይ ላይ ተቀምጠው አገኘኋቸው:: ዓይናቸው ቡዝዝ ብሎ በሀሳብ በመመሰጣቸው እስካናግራቸው ድረስ አጠገባቸው መድረሴንም አላዩም ነበር:: ለወትሮው እዚህች ድንጋይ መቀመጫ ላይ የሚቀመጡት እጃቸው አጠር ሲል ለዕለት ቡና ብር ቢጤ ሲቸግራቸው ነበር:: የድንጋይ ወንበሯ የመተከዣ መድረካቸው ናት::

“ማዘር ምነው ሰላም አይደሉም እንዴ?” አልኳቸው፤

ቀጥ ብለው እንባ በኳተሩ ዐይኖቻቸው ተመለከቱኝና ሳግ በተናነቀው አሳዛኝ ድምፅ ፡ “የፍቅርተን ሱሪ ወሰዱባት አብርሽ!” አሉኝ፤ ሊያናግሩኝ ቀና ሲሉ እያለቀሱ እንደቆዩ ፊታቸው ላይ ዳናውን የተወ እንባቸው ይናገራል::

“እነማን ናቸው የወሰዱት?” አልኳቸው የሰማሁትን ባለማመን፤ ቅስም ከሚሰብር ዜና ኋላ የተከሰተ የጅል የሚመስል ጥያቄ::

“ምናውቄ ብለህ አብርሽ ! ከዚህ ከተሰጣበት ገመድ ላይ አንስተው ወሰዱት” አሉና እንባቸውን ዘረገፉት:: ድህነት እንደ ሸንኮራ መጥጦ ካደረቀው ሰውነት ይሄን ያህል እንባ ይወጣል ብዬ አላሰብኩም ነበር:: ሕይወት ምንጊዜም አዲስ እንባ አላት::ከእንባቸው የበለጠ ፊታቸው ላይ ያረበበው ሐዘንና ምሬት ያሳዝን ነበር::አንጋጥጬ የልብስ ማስጫ ገመዱን ተመለከትኩት:: ወዲህ የኤሌክትሪክ ምሰሶ ላይ ወዲያ ደግሞ የአንዲት ጎረቤት የቤት ጣራ ማገር ላይ የተወጠረው ገመድ የተወረረ ከተማ መስሏል:: ባንዲራውን እንዳወረዱበት የሰንደቅ ምሰሶ ትከሻው ቀሏል:: ባዶ !! ለፍቅርተ፤ ለእኔ፤ ለእማማ ዓመለ፤ ለመንደሩና ለአገሩ ባዶነትን ትቶልን የሄደው ማነው?

ይሄ ገመድ ባዶውን ውሎ አያውቅም ነበር:: ቢጠፋ ቢጠፋ የጉግሳ አውራ ጣቱ የተሸነቆረ ካልሲ ወይም አሁን የጠፋው የፍቅርተ ሱሪ ተሰጥቶበት ነበር የሚውለው:: የፍቅርተ ሱሪና የጉግሳ ካልሲ ሁልጊዜም ገመዱ ላይ ጎን ለጎን ተሰጥተው ስለማያቸው የልብ ወዳጆች ይመስሉኝ ነበር ::የፍቅርተ ሱሪ ከፍ ያሉት ንቀውት ዝቅ ብሎ የካልሲ ጓደኛ የሆነ:: ካልሲውም ቢጤዎቹ ንቀውት ቀን ከገፋው ሱሪ ጋር የዋለ ዓይነት::

አንጋጥጬ ስመለከት ከገመዱ በላይ ጥርት ያለው ሰማይ ተዘርግቷል:: የፍቅርተን ሱሪ የወሰዱት ሌቦች ለወትሮው ሰማዩ ላይ የማይጠፋውን ደመና የወሰዱት ይመስል ነበር:: ሰማዩ ባዶ! የልብስ ማስጫው ገመድ ባዶ!! አይ አይ ሰማዩ እንኳን ባዶ አልነበረም:: ነግቶ የረፈደባት የምትመስል ግማሽ ጨረቃ ትታያለች:: የሱሪ ሌባው ግማሿን ጨረቃ ሸርፎ የወሰዳት ይመስል::

ቆይ ግን ሱሪውን የወሰደው ሌባ ከሆነ ሌባውን ምን ነካው? እንዴት የፍቅርተን ሱሪ ይወስዳል? እሺ ነፋስም ከሆነ ንፋሱን ምን ነካው ? አቧራ ያስነሳ፣ የቤት ጣራ ይገነጣጥል ቢፈልግ ! ያንን ከሰፈራችን ወደታች ያለውን 'የአድባር ዛፍ' ከስሩ ገርስሶ ይጣለው ! ግን እንዴት የፍቅርተን አንድ ለእናቱ የሆነ ሱሪ ይወስዳል ? ምን ቁርጥ አድርጎት የመንደራችንን ባንዲራ ይደፍራል ? በሌባው ተቆጣሁ :: በነፋሱ ተቆጣሁ :: በፈጣሪም ተቆጣሁ :: መምሬ ልሳኑ ታዲያ (የእማማ አመለ ንስሃ አባት) የሱሪውን መጥፋት ሲሰሙ፣ እማማ አመለን ለማፅናናት ብለው ይሁን አልያም አምነውበት እንጃ ብቻ ጥቅስ አጣቀሱ፤ "ላለው ይጨመርለታል፣ ከሌለው ግን ያለውም ይወሰድበታል - ወለተ ኪዳን አይዞሽ" በዚህ ማፅናኛቸው በጣም ተበሳጨሁ፤ እንደውም በፈጣሪ ላይ የተሰማኝ ቅሬታ ተባባሰ::

ፈጣሪ የሌባው እጅ ወደ ፍቅርተ ሱሪ ሲዘረጋ እንደ ደረቅ እንጨት ድርቅ አድርጎ ማስቀረት ይችል ነበር:: ነፋስና ማዕበልን የሚገስጽ ፈጣሪ እንዴት ዝም አለ ? እሳት ከሰማይ የሚያወርድ አምላክ ከዚህ በላይ በደል፣ ከዚህ በላይ ግፍ ምን አለና ታገሰ ? የፍቅርተን ሱሪ የወሰደው ንፋስ ከሆነም መገሰጽ ይችል ነበር፣ ስለምን  ዝም አለ ? እንኳን አጋጣሚውን አገኘሁ እንጂ ፈጣሪ ጋርማ በፍቅርተ ጉዳይ ብዙ ጥያቄ አለኝ ! ብ....ዙ ! ሲጀመር ፍቅርተን ስለምን እንዲህ አድርጎ ፈጠራት...እኮ ለምን !? ለእሱስ ለስሙ ጥሩ ነው ?

**** **** ****

"የእናት ሆድ ዥንጉርጉር ነው" ይሉት ብሂል ስጋ ለብሶ የተገለጠው እማማ አመለ ቤት ነበር:: እማማ አመለ በመልክ ይሁን በባህሪ የማይገናኙ፣ ከፆታቸው በቀር  አንድ የሚያደርጋቸው አንድ ነገር እንኳን ፈልጎ ማግኘት የሚከብድ ሁለት ሴት  ልጆች ያሏቸው፣ እድሜያቸው የገፋ ደግ ሴት ነበሩ :: ከሁለት ክፍል ቤታቸው አንዷን ተከራይቼ ለአራት ዓመታት ቤታቸው ውስጥ ኖሬያለሁ::

ለስሙ ሁለት ክፍል ተባለ እንጂ አብረን በደባልነት እንደኖርን ነበር የሚቆጠረው:: እማማ አመለ ከሁለቱ ልጆቻቸው ጋር የሚኖሩበትን ክፍል ረግጬ የእኔ ክፍል ወደሆነችው ጓዳ አልፋለሁ፤ አንዳንዴ ታዲያ ወደ እኔ ክፍል ለማለፍ  የተደረደሩትን እቃዎች መዝለል ይኖርብኛል:: በተለይ ቡና ከቀራረበ ረከቦቱን  መራመድ ግድ ነበር:: የእኔ ክፍል ከእነ እማማ አመለ ክፍል የሚለየው በአንድ ስስ መጋረጃ ነበር :: እኔ ቤት ሆኖ የእነማማ አመለን ቤት አጠቃላይ እንቅስቃሴ መመልከት ይቻላል ፤ ድንበራችን ስስ መጋረጃ ነበርና::

ፍቅርተ የእማማ አመለ ሁለተኛ ልጅ ናት:: ፍቅርን ጨምሮ ሁሉንም ነገር የነሳት፣ የአርባ ቀን እድሏ በየቀኑ አርባ የሰቀቃ ጅራፍ የሚያሳርፍባት መልከጥፉ ወጣት ናት:: ልቅም ያለች መልከ ጥፉ ነበረች:: ቁንጅና እንደተመልካቹ ነው ቢባልም ፍቅርተን "ቆንጆ" የሚል ሰው አጋጥሞኝ አያውቅም፤ ራሷን ፍቅርተን ጨምሮ::

ፍቅርተን ድንገት የተመለከታት ሰው ድንገት የተከሰተ ሰይጣን ፊት የቆመ ሊመስለው ይችላል:: መጀመሪያ ግማሽ ፊቷን የሞላ የሚመስለው ትልልቅ እና የተፍረከረከ ከንፈሯ ድራማ ለመስራት

የተጠለቀ ጭምብል እንጂ በእርግጥም የአንዲት የአስራ ስምንት ዓመት ወጣት ከንፈር አይመስልም፤ ከላይኛው ከንፈሯ የተረፈው ቦታ ላይ ለምልክት የተቀመጠው አፍንጫዋ ወደላይ ቀና ብሎ ሰፋፊ ሽንቁሮቹ ፊት ለፊት የቆመ ተመልካች ላይ የተደገኑ መንታ የከባድ መሳሪያ አፈሙዞች ይመስላሉ::የመርፌ ቀዳዳ የሚያካክሉ ዓይኖቿ ሁሌም ጉሸርጥ መስለው እንደቀሉ ናቸው:: የፀጉሯ ነገር አይነሳ ! የፍቅርተ ፀጉር ቀለም የለውም ፤ የማለዳ ጠል የሰፈረበት የሜዳ ላይ ችፍርግ ! ስታበጥረው አስቃቂ ፉጨት የመሰለ ድምፅ ይወጣል::

ይህን ሁሉ ተፈጥሯዊ በደል የተሸከመችው ፍቅርተ በዚህ በቃሽ ቢላት ጥሩ ነበር፤ ከቁመቷም ከፉኛ በድሏታል:: በእጥረቷ ላይ ሲበዛ ትልልቅ ጡቶቿና አጠቃላይ የሰውነቷ ውፍረት ተዳምሮ በሰቆቃ እንድትኖር ፈርዶባታል:: በእርግጥ ሰዎች "እግዜር የሰጣትን በፀጋ መቀበልና መኖር ነው ለምን ትሳቀቃለች?" የሚል ጉንጭ አልፉ ንግግር ሲናገሩ ይደመጣሉ:: ግን እንደባለቤቷ ሰቆቃው ሊገባቸው አይችልም:: "ምከርና ቡጢ ለሰጪው ቀላል ነው" እንዲሉ :: የልብሳቸው መዛነፍ፣ የከንፈር ቀለማቸው አለመስተካከል የሚያስጨንቃቸው ቆነጃጅት "እግዜር የሰጠውን..." ይሏታል፤ ይሄን ሁሉ ነገር የተሸከመችውን ፍቅርተን !

እንግዲህ የእናት ሆድ ሲዥጎረጎር ፋና ተወለደች ፤ "ያየሽ ይውደድሽ!" የሚል ምርቃት አብሯት የተወለደ:: ከባህሪውም ከቁንጅናውም አትረፍርፎ የሰጣት ውብ የአስራ ዘጠኝ ዓመት ወጣት ነበረች - መልዓክ ! ፋናን ዓይድን ትክ ብዬ ማየት አልችልም:: ርዳለሁ ... እፈራታለሁ:: ቁንጅናዋ ከተለመደው የሴት ልጅ ቁንጅና ያልፋል::

በዕድሜ ከእኔ ብታንስም ሁልጊዜም አጠገቧ ስቆም ትገዝፍብኛለች:: ፋና ለእኔ ቆንጆ ብቻ አልነበረችም፤ የቁንጅና ማነፃፀሪያ ሚዛኔም እንጂ:: ልክ የሌለው ቁንጅና፣ ቃል የማይገልፀው መስህብ ነበራት:: የፊቷ ቆዳ ነፋስ እንደቆለለው የምድረበዳ አሸዋ ለስላሳ ነበር:: እንዲሁ በዓይን ሲመለከቷት በእጅ የዳሰሷት ያህል ልስላሴዋ ይሰማል:: ዓይኖቿ ልብን የሚያስጨንቁ ነገሮች ናቸው:: ፋና በልብ ውስጥ ለዘላለሙ የሚታተም ግን ቃል አውጥተው የማይናገሩት ቁንጅና የነበራት ልጅ ነበረች፤ ህያው ፈተና !

*** *** ***

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ንግድ ስራ ኮሌጅ (ኮሜርስ) ተማሪ ነበርኩ:: ለአንድ የክፍለ ሐገር ልጅ ይቅርና አዲስ አበባ ተወልደው ላደጉ ልጆችም ቢሆን ንግድ ስራ ኮሌጅ መማር ከባድ ነበር፤ የመጀመሪያው ችግር ኮሌጁ ለተመደቡ ተማሪዎች የመኝታም ይሁን የምግብ አገልግሎት ስለማይሰጥ በየወሩ ለተማሪዎች እዚህ ግባ የማይባል የኪስ ገንዘብ እየከፈለ ከግቢ ውጭ እየኖሩ ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ያደርጋል:: ተማሪው በአካባቢው ቤት አፈላልጎ በመከራየት ትምህርቱን ይቀጥላል::

ገና ከጅምሩ እዚህ ኮሌጅ መመደቤን ስሰማ አልቅስ አልቅስ እያለኝ ነበር ከክፍለ ሐገር ወደ አዲስ

አበባ የመጣሁት፡፡ የኮሌጁን ተማሪዎች የማስቃየት ጀብዱ በሩቁ ሰምቻለሁ፡፡ በዛ ላይ ለአዲስ አበባ አዲስ ስለነበርኩና የማውቀው ሰው ስላልነበረኝ እንኳን እየዞርኩ ቤት መፈለግ ቀርቶ አምስት ርምጃ ብራመድ ተመልሼ አልጋ የያዝኩበትን ሆቴል የማገኘው አይመስለኝም ነበር፡፡ በዚህ ግራ በተጋባሁበት ወቅት ነበር ባረፍኩበት ሆቴል አልጋ አንጣፊ በኩል የእማማ አመለን ቤት ለመከራየት የበቃሁት ፡፡

"እንደው መንደሩም ቤቱም ይሆንህ አይመስለኝም እንጂ የሚሆንህ ከሆነ አንዲት ጎረቤታችን አንዲት ከፍል ቤት አለቻቸው" አለችኝ የሆቴሉ አልጋ አንጣፊ፡፡ ቤቱን ልናይ ጎተራ አሁን ቀለበት መንገዱ የተሰራበትን ወደቀኝ ትተን ወሎ ሰፈር የሚባለው አካባቢ ሄድን፤ በመንገዱ ግራና ቀኝ የተሰደሩት ትላልቅና ውብ ሕንፃዎች ጀርባ ውስጥ ለውስጥ ሂደን እዚህ አካባቢ ይኖራል ተብሎ የማይታሰብ ጭርንቁስ መንደር ውስጥ ገባን፡፡ እርስ በርስ ተደጋግፈው የቆሙት ቤቶች ግድግዳ ላይ ተለጥፈው የተሰሩ የውሻ ቤቶች እንጂ የሰው ቤት አይመስሉም፡፡ "ጨረቃ ቤት" እንደሚባሉ በኋላ ሰማሁ፡፡ አፈር አፈር የመሰሉ ሕፃናት መንደሩ ውስጥ ውር ውር ይላሉ፡፡ ትንሽ ተጉዘን ካገኘናቸው መደዳ ቤቶች ያሉበት ቦታ ስንደርስ በአንዱ በር ላይ ቆምን፡፡ ፍቅርተ እና እናቷ እማማ አመለ ነበሩ ያናገሩኝ፡፡

እውነቱን ለመናገር ፍቅርተን ሳያት ላማትብ ቃጥቶኝ ነበር፡፡ በስመአብ በ...፡፡ ድንገት ፍቅርተን የተመለከተ ሰው ሊሰማው የሚችለው ነገር ቢኖር ይሄው ነው፡፡ ለምን እንደሆነ ባላውቅም አዲስ አበባ ውስጥ የዚህ ዓይነት ቤትም፣ የዚህች ዓይነት ልጅም ይኖራሉ ብዬ አስቤውም አልሜውም አላውቅም፡፡እንደውም ያመጣኝ አውቶብስ በትክክል አዲስ አበባ እንደጣለኝ ተጠራጠርኩ፡፡ የእኔ ቤተሰቦች መካከለኛ ኑሮ የሚኖሩ የክፍለ ሐገር ሰዎች ናቸው፡፡ ያደግኩበት ቤትና ግቢ ግን በስፋትም በንፅህናም ከዚህ "ቤት" ጋር ሲወዳደር...ኧረ አይወዳደርም፡፡ ወይ አዲስ አበባ !! "ለጊዜው እዚህ ቤት አረፍ ብዬ አገሩንና ሰዉን ስለምደው የተሻለ ቤት እፈልጋለሁ" ብዬ የ'አዲስ አበባ' የቤት ችግር መፈናፈኛ ያሳጣኝ እኔ ጓዳዋን በሶስት መቶ ብር ለመከራየት ተስማማሁ፡፡

ከሰዓት በኋላ አንዲት የስፖንጅ ፍራሽ ገዝቼ ካረፍኩበት ሆቴል ሻንጣዬን በመያዝ ወደተከራየሁት "ቤት" ስመለስ ያጋጠመኝ ነገር ባንድ ራስ ሁለት አስወራኝ፡፡ "ያመጣኝ አውቶብስ አዲስ አበባ ነው ወይስ ገነት ያወረደኝ?!"፤ ፋና በር ላይ ቆማ ነበር፡፡ ፋና የእኔ የማለዳ ጀምበር...! ፋና የእኔ ደግ ፊት ! ሩህሩህ ፊት፣ የተከሰተች መልአክ...!

ሻንጣዬን ልትቀበለኝ እጇን ዘረጋች፡፡ ለስላሳ ጣቶቿ የእጄን መዳፍ ነኩኝ! የከተማው የኤሌክትሪክ ኃይል ሁሉ በፋና እጅ በኩል አድርጎ ልቤን ቀጥ እስኪያደርገው ነዘረኝ፡፡ አዲስ አበባ በጨለማ ተውጣ በጥቁር አዲስ አበባ ላይ ፋና የምትባል ፀሐይ ፍንትው ብላ ወጣች ! እነሆ ይህቻትና አዲስ አበባ የልዩነት አገር... ሁሉን ቻይ አዲስ አበባ! የሁሉ መኖሪያ አዲስ አበባ! ከትላልቆቹ ሕንፃዎች ኋላ ሲኦልና ገነት በፍቅር በመተሳሰብና በአንድነት ተቃቅፈው የሚኖሩባት አዲስ አበባ! የአዲስ አበባ ልጅ የሆንኩ መሰለኝ፤ አዲስ አበባ ተወልጄ ያደግኩ መሰለኝ፡፡ ፋና ፋና ፋና ፋና ያለችበት ቤት ውስጥ ልኖር ነው፡፡

አ.ዲ.ስ አበባ ዩኒቨርስቲ ንግድ ስራ ኮሌጅ እግዜር ይስጠው፤ አካውንቲንግ ላስተምርህ ብሎ ጠርቶ፣ ከቁጥሮች ክምር ውስጥ እውነትን ማውጣት ላስተምርህ ብሎ ጠርቶ፣ ድህነት ከቀበረው መንደር ውስጥ የወርቅ ፍልቃቂ የመሰለች ልጅ እንዳወጣ የተላከኩ መልአክ አደረገኝ:: እኔክ ቆንጆ ሴት ሲያዩ የሚደነግጡት የፊልም 'አክተሮች' ብቻ ይመስሉኝ ነበር:: ፈዘዝኩ ! ፉናን ስመለከት ፈዘዝኩ::

ከዚች ቤት እንኳን ራሴ ልወጣ ውጣም ቢሉኝ እግሬን እንደማላነሳ የገባኝ ገና ፉናን እንዳየኋት ነበር:: "ለልማት መንደሩ ሊፈርስ ነው መድረሻህን ፈልግ" ቢሉኝም "አብራችሁ አፍርሱኝ" ከማለት ወደኋላ እንደማልል የገባኝ የፉና ጣቶች ሲነኩኝ ነው ::ማን አለ ለርስቱ የማይሞት! ፉና እኮ ርስት ናት፤ከፀሐይ መውጫ እስከ ፀሐይ መግቢያ ከአፅናፍ እስከ አፅናፍ የተዘረጋች:: እግዚዮ ! ፉናን እዚህ መንደር ውስጥ ምን እግር ጣላት ?! መቼም ከዚህ ቤት በሆነ መንገድ አውጥተው ቢጥሉኝ አርቀው እንደጣሉት ውሻ፣ ጫካ ወስደው እንደወረወሩት ድመት የፉናን ኮቴ እያነፈነፍኩ ተመልሼ እዚሁ መገኘቴ አይቀርም::

ማንም 'ችኩል' ቢለኝ ግድ አይሰጠኝም:: ፉናን ገና ስመለከታት ልቤ ውስጥ የማይናወጥ የፍቅር ሐውልት ቆሟል:: ማንም ብትሆን ግድ አይሰጠኝም፤ ቤት ውስጥ ምንሽር የታጠቀ፣ ጓንዴ ትራሱ ስር ያስተኛ ባሏ ቢቀመጥ፣ ሰባት ልጆቿ "እማ እማ!" እያሉ የሚንጫጩ ሴት ብትሆንም ግድ የለኝም:: ፉናን አየኋት፣ ወደድኳት በቃ!! ይሄ ሁሉ ነገር የሆነው አንድ ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ነው:: እና ይሄን ሁሉ ሴኮንድ፣ ዘላለም የሚያህል ደቂቃ ፉናን አይቼ ባፈቅራት "ቸኮልክ" የሚለኝ ማነው?!

***     ***     ***

ቤተሰቦቼ በየወሩ የሚልኩልኝ ብር ከዚህ የተሻለ ቤት እንድከራይ የሚያስችለኝ ቢሆንም ፉና የምትባል የእግር ብረት ተጠናውታኝ በየት በኩል ! ቤቱ ለአንድ የዩኒቨርስቲ ተማሪ ምኑም የሚመች አልነበረም:: ከእኔ ክፍል ኋላ የታወቀ ጠላ ቤት ነበር፤ ጫጫታው፣ ሁካታው፣ ዘፈኑ፣ ፀቡ ሁሉ ይረብሸኛል :: በሳምንት ሦስት ቀን !!

የጠላ ቤቱ ጬኸት ጋብ ሲል ኳስ የሚጫወቱ ልጆች ይተካሉ:: ግድግዳየን በኳስ ሲነርቱት የቤቴ ምርጊት አፈሩ በለጠፍኩት የግድግዳ መሸፈኛ ወረቀት ስር እየተንኮሻኮሸ ሲፈርስ ይሰማኛል:: ይህን ሁሉ ስችለው ደግሞ የጠላ ቤቱ አሻሮ ሲታመስ ፣ የጠላ ቂጣው ሲጋገር አሻሮ አሻሮ የሚሸትት እንኩሮ እንኩሮ የሚተነፍግ ጭስ ጠባብ ክፍሌን ይሞላታል:: ይህ ሁሉ ችግር ግን ቤቱን እንድጠላው አላደረገኝም:: ፉናን ስመለከት ጫጫታው የፍቅር ሙዚቃ፣ ጭሱ ፍቅርን የሚያጥን የገነት ከርቤ እስኪመስለኝ ይስማማኛል::

እዚህ ቤት ውስጥ ለስድስት ወራት ስኖር ከፍቅርተ ጋር ተግባባን፤ እማማ አመለ ጋር የእናትና የልጅ ያህል ተቀራረብን፤ ከፉና ጋር ግን ከሰላምታ ውጭ አንዲት ቃል ተለዋውጠን አናውቅም :: ፉና እዛው ተቀምጣ አንድ ቤት እየኖርን ትናፍቀኛለች ፤ አትናገር አትጋገር ! ዝም:: ፉና

ቤት ውስጥ አለች ማለት ማንም ቤት ውስጥ የለም እንደማለት ነው፤ ዝምታ ይነግሳል:: የፉናን ድምፅ አንዳንዴ ለአራት ለአምስት ቀናት አልሰማውም፤ እዛው እያለች:: አይገርምም ? እኔም በቤተሰቦቼ "እሱ አይናገር አይጋገር ዝም ነው!" እየተባልኩ እሞካሽ ነበር:: ጉዳቸውን ባዩ ! እዚህ ሞት የሚያስንቅ ዝምታ የሰፈረባት ጋግርታም ጋር በፍቅር ወድቄ አንድ ቃል ሲናፍቀኝ::

የፉና ዝምተኝነት የጤና አልመስል ብሎኝ ነበር:: እንጀራ እየበሉ ወጥ ሲያልቅባት እንኳን ወጥ ጨምሩልኝ አትልም:: ደግነቱ እናቷ እማማ አመለ ዓይናቸው ከፉና ላይ ስለማይነቀል ገና ወጡ ሲያልቅባት በላይ በላዩ ይጨምሩላታል:: ፉና በቀን ውስጥ የምትናገራቸው ቃላት ቢደመሩ እህቷ ፍቅርተ በግማሽ ደቂቃ ከምታዘንበው ንግግር እሚበልጡ አይመስለኝም:: ፍቅርተ ሙሉ ቀን ስታወራ፣ ስትስቅ፣ ስትጫወት ነው የምትውለው:: አንዳንዴ ፈገግታ የሚያጭርብኝ ነገር ፉናና ፍቅርተ ሲያወሩ መስማት ነበር:: ፍቅርተ ብቻዋን የምታወራ ነው የምትመስለው:: ፉና አንድ ቃል አትመልስም፤ ፍቅርተም ብትሆን የእህቷን አመል ያወቀች ይመስል መልስ አትጠብቅም፤ ዝም ብላ ታወራለች ::

የፍቅርተን ወሬ መስማት አይሰለችም:: እንደው ፍቅርተን መልኳን ሳይመለከት ድምጿን ብቻ ያደመጠ ሰው በዓለም አንደኛዋ ቆንጆ ሴት እየተናገረች ሊመስለው ይችላል:: በተለይ ሳቋ ! የፍቅርተ ውበት ግን ድምጿ ብቻ ነው:: "ስምን መልአከ ያወጣዋል" የሚባለው ብሂል እውነት ከሆነ የፍቅርተን ስም ያወጣው መልዓከ ድምጿን ብቻ በሆነ መንገድ አድምጦ "ፍቅርተ" ብሎ ሳይሰይማት አልቀረም::

*** **** ****

እማማ አመለወርቅ ብርቱ እናት ነበሩ:: ሁለቱን ሴት ልጆቻቸውን ያሳደጉት ካለ አባት ነው:: ዛፍ ቆራጭ የነበሩ ባለቤታቸው አንድ ቀን ዛፍ ሲቆርጡ የዛፉ ቅርንጫፍ የተላጠ ኤሌክትሪክ መስመር ጋር የተነካካ ሆኖ በአሰቃቂ ሁኔታ ሕይወታቸው አለፈ:: ያኔ ፉና የሶስት፣ ፍቅርተ የሁለት ዓመት ሕፃናት ነበሩ:: እነዚህን ሁለት ልጆች ለማሳደግ ያልፈነቀሉት ድንጋይ የለም:: ያለፉበትን አሰቃቂ የድህነት መንገድ ተመልሰው ሲያስቡት ያንገሸግሻቸዋል:: ታዲያ ከተቀራረብንና እኔም ከቤተሰቡ አባል እንደ አንድ ተቆጥሬ ገመናቸውን ተካፋይ ስሆን ማታ ማታ ቡና ተፈልቶ ታሪካቸውን ያወሩልኝ ነበር:: እማማ አመለ ወሬ ይችላሉ፤ አሁን በሐዘን ዐይናችንን በእንባ ሞልተውት ድንገት ጣል በሚያደርጉት ቀልድ ለሐዘን የኳተረ እንባችን በሳቅ ይፈሳል::

የማታ ቡና አብሬያቸው መጠጣት የጀመርኩበት ቀን ትዝ ይለኛል:: በፊት ቡና ሲያፈሉ ፍቅርተ መጋረጃዬን ገለጥ አድርጋ አንድ ስኒ ታቀብለኝና እጠጣለሁ፤ እጣኑም ቢሆን እየተጥመለመለ መጋረጃዬን አልፎ ከፍሌ ይደርሳል ::

"አብዬ" ይሉኛል እማማ አመለ ሲጠሩኝ እንዲህ ነው፤

"አቤት ማዘር !"

"ሁለተኛ ትጠጣለህ?"

"አይ ይበቃኛል ማዘር" እላለሁ:: እየፈራሁ እንጂ ብጠጣ ደስ ይለኝ ነበር::

አንድ ቀን ታዲያ ቡናው ተፈልቶ፣ እጣኑ ቤቱን ሞልቶት፣ እኔም ነቃ ብዬ ፍቅርተ መጋረጃዬን ገለጥ አድርጋ ቡናዬን እስከታቀብለኝ ስጠብቅ እማማ አመለ ጠሩኝ::

"አብዬ !"

"አቤት ማዘር"

"እንደው ከሰውም አልተፈጠርክ ? ምናለ ወዲህ ወጣ ብለህ ብትጫወት፣...ጀበናውንም እያየህ ቡና ብትጠጣ፣ እኔም እናትህ ነኝ፣ እነፍቅርዬም እህቶችህ ናቸው" አሉኝ:: ይሄ የመለአከት ጥሪ ነው! ልብሴን ቀየርኩ፤ (ምርጥ የምላትን ልብስ ነው የለበስኩት፣ ከዚህች እዚች የመጋረጃ ድንበር ለማለፍ ሸክ!!):: እናም መጋረጃዬን ገለጥ አድርጌ ብቅ አልኩ፤ ሁሉም በአክብሮት ተቀበሉኝ:: የተዘጋጀችልኝ ኩርሲ ላይ ተቀመጥኩ :: እዩት እንግዲህ እግዜር ጨዋታውን ሲያሳምረው! ፋና ፊት ለፊቴ ነው የተቀመጠችው:: ከዚህ በፊት ፊት ለፊቴ ተቀምጦ የሚያውቅ ውብ ነገር ምን ነበር?...ምንም !!

በእኔና በፋና መሃል የሲኒ ረከቦት፣ ሲኒዎቹ ስድስት ጨረቃ መስለው፣ ከረከቦቱ ጎን ማጨሻው እንደ ደመና በቀስታ ሽቅብ ወደ ጠቆረው ጣራ፣ ከሚሳብ የእጣን ጭሱ ጋር:: ከስሱ የእጣን መጋረጃ ባሻገር ፋና አንገቷን ደፍታ መሬት መሬት እየተመለከተች ተቀምጣለች:: አዲስ ሰው ስለተቀላቀልኩ ጨንቋታል:: አቤት እንዲህ ፊቷ ተቀምጠው በእጣኑ ጭስ ውስጥ ሲመለከቷት! "ምነው ባልነቃሁ" በሚባልበት እንቅልፍ ውስጥ የተከሰተች ጣፋጭ ህልም ነው የምትመስለው፤ ፋና የኔ ውብ::

ድህነትን አፈር ድሜ ያስጋጠ ውበት በዚህ ጭርንቁስ ቤት ውስጥ ፊት ለፊቴ በእጣን ደመና ተከብቦ ተቀምጧል፤ እኔም ከእግር ጥፍር እስከራስ ፀጉር በሚነዝር በሚያስረቀርቅ ደስታ ውስጥ ህያውና ዘላለማዊ ሥዕል ላደርጋት እያጠናኋት ነው ::ነፍሱ በፍቅር ፍላፃ እንደተወጋች አፍቃሪ (፡ምድር ላይ ምርጥ ሠዓሊ የለም ::አፍቃሪ እንደፎቶ አንሽ ያፈቀረውን ስጋ ብቻ አይደለም የሚያሳምረው፤ የተፈቃሪውን ነፍስ ይመለከታል፤ ነገን ይመለከታል፤ በዝምታ ውስጥ ያለ ሰላምን የሚቃኙ ዐይኖች ይታደላል:: ኩተከዘ ፊት ፈገግታን ያወጣል:: እውነትን በዓይነ ህሊናው ይቃኛል! አፍቃሪ ሠዓሊ ነው!

ከዛን ቀን ጀምሮ ፋና ጋር በእጣን ጭስ መሃል መተያየት የዘወትር ተግባራችን ነበር:: የእማማ አመለ ጣፋጭ ወግ፣ የፍቅርተ የማያባራ ሳቅና ጨዋታ፣ የፋና የማይገሰስ ዝምታና የዝምታዋ ውበት፣ የውበቷ ግዝፈት እንደ መንፈስ በቤቱ ውስጥ ያረብብ ነበር:: ያችን የድህነት ጎጆ ሙሉ

ያደረገ መልካም ቤተሰባዊ ፍቅራችን ለአራት አመታት አብሮን ኑሯል፡፡

*** *** ***

ድህነት ከፉ ነው፡፡ ድህነት ምኑም አያኮራም፤ ድህነት ያስጠላኛል፡፡ አንድ ቀን ትንሽ ራሴን ስላመመኝ በጊዜ ወደቤት ተመለስኩ፤ ማንም አልነበረም፤ የት እንደሄዱ እኔንጃ፡፡ ወደ ክፍሌ ገብቼ ፍራሽ ላይ በደረቴ ተደፍቼ ተኛሁ፡፡ ብዙ ሳልቆይ ፍቅርተ ከውጭ እየተጣደፈች ገባች፤ መኖሬን አላወቀችም፡፡ እኔም ካለወትሮዬ ዝም ብዬ በመጋረጃው አሻግሬ እመለከታታለሁ፡፡ አለ አይደል አንዳንዴ መናገር የሚታከትብን ጊዜ...

ፍቅርተ የሆነ ቦታ ልትሄድ በጥድፊያ ላይ እንደሆነች ታስታውቃለች፡፡ ከአሮጌው አልጋ ስር ዚፑ የተበላሸ አንድ የልብስ ማስቀመጫ ሻንጣ ጎትታ አወጣች፡፡ ይህ ሻንጣ የቤተሰቡ ብቸኛ የልብስ ማስቀመጫ ነበር፡፡ ከፈተችውና ልብስ መምረጥ ጀመረች፤ ትእይንቱ አሳዛኝ ነበር፡፡ አንዱን ታነሳና በሁለት እጆቿ ራቅ አድርጋ ይዛ እያገላበጠች ትመለከተዋለች፣ አልጋው ላይ ትጥላለች፤ ሌላውን ታነሳለች ትጥላለች፡፡ የእማማ አመለ የከት ቀሚስና ነጠላ፣ የፋና አንድ ሁለት ተራ ቀሚሶች እናም የፍቅርተ በርካታ ነጫጭ ቲሸርቶች...ሻንጣው ውስጥ የነበረው ልብስ በሙሉ አለቀ፡፡ ፍቅርተ ልትሄድ ላሰበችበት ቦታ የሚመጥን አንድም የረባ ልብስ አላገኘችም፡፡ በረዥሙ ተነፈሰችና በአንድ እጇ ወገቧን ይዛ በሌላ እጇ ጠጉሯን እያከከች ግራ ተጋብታ ለብዙ ደቂቃዎች በትካዜ ቆመች፡፡ ከዛም በቁጣ ልብሱን ከአልጋው ላይ ገፍፋ ወደ ሻንጣው ወረወረችውና ሻንጣውን ዘግታ በእርግጫ ወደ አልጋው ስር ገፋችው፡፡ በዚህች ቅፅበት ጓደኞቿ ከውጭ ጠሯት፤

"...ፍቅር ቶሎ በይ እንጂ...ረፈደ እኮ!"

"እናንተ ሂዱ ኤልሲ ! ሌላ ቀጠሮ አለኝ ረስቼው ነበር" አለቻቸው፤ ጓደኞቿ ሄዱ፡፡ ፍቅርተ አልጋው ጫፍ ላይ ተቀምጣ ስቅስቅ ብላ ማልቀስ ጀመረች፡፡

"ኤጭ! ወይ መልክ የለኝ፣ ወይ ደህና ቤተሰብ የለኝ፣ ሰው ጋር መቀላቀያ እንኳን አንዲት ልብስ ያጣል ሰው ?...አንዲት ልብስ...እግዚአብሄር አሁንስ ብትገለኝ ምናለበት ! በስንት ነገር ከሰው በታች ታደርገኛለህ?" አለች በምሬት፡፡ አልቅሳ ሲወጣላት እንባዋን ጠራርጋ አንዲት ትንሽ መስተዋት ወደተሰቀለችበት ጥግ ሄደችና መስተዋቷን አውርዳ አንዴ ከንፈሯን ሰብሰብ አንዴ ለቀቅ እያደረገች መልኳን ስትመለከት ቆየችና መስተዋቱን ወደ ቦታው እየመለሰች "አስቀያሚ!" ብላ በምሬት ተናገረች፡፡ ማታ የተለመደው ቡናችን ላይ ግን ፍቅርተ በሳቅ ስትፍለቀለቅና ምንም ነገር ያልተሰማት ልጅ መስላ አመሸች፡፡ "ሳቅ የደስታ ምልክት ነው" የሚሉ የዋሆችን ታዘብኳቸው፡፡

ከዛን ቀን ጀምሮ የፍቅርተን ልብሶች ማስተዋል ጀመርኩ፡፡ የፍቅርተ የሚበዙት ልብሶቿ ነጫጭ

ቲሸርቶች ነበሩ:: እነዚህ ቲሸርቶች ከተለያዩ ድርጅቶች በነፃ የሚታደሉ የተለያዩ መፈክሮች ደረታቸው እና ጀርባቸው ላይ በተለያዩ ቀለማት የታተሙባቸው ሲሆኑ ብዙዎቹ ለአንድ በዓል ወይም ለሆነ ቀን መታሰቢያነት የተዘጋጁ ናቸው:: አንድ ቀን ታዲያ ፍቅርተ ልብስ አጥባ ቲሸርቶቹ የተሰጡበት ቆሜ ስመለከት ገረመኝ:: የፍቅርተ ቲሸርቶች ታጥበው ሲሰጡ የኢትዮጵያ ችግሮች በሙሉ ታጥበው የተሰጡ ነበር የሚመስሉት::

"የእናቶች እና ህፃናት ሞት ይቁም" በቀይ ቀለም ደረቱ ላይ የተፃፈበት ቲሸርት፤

"ከ ኤች አይ ቪ ኤድስ ራሳችንን እና ቤተሰባችንን እንጠብቅ" በሰማያዊ፤

"ፖሊዮን ከኢትዮጵያ እናጠፋለን" በጥቁር፤

"መስኮት በመክፈት የቲቢ በሽታን እንከላከል" በቀይ፤

"ችግኝ በመትከል አካባቢያችንን ውብና ፅዱ እናድርግ" በአረንጓዴ፤

ከነጫጮቹ ቲሸርቶቹ ለየት ያሉት ደማቅ ቀይና ቢጫ ቲሸርቶች ደግሞ የታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ አርማ የታተመባቸው ነበሩ:: ፍቅርተ ብትበሳጭ እውነት አላት::የዘመኗን ወጣቶች፣ የአዲስ አበባን ቆነጃጅት በእነዚህ ቲሸርቶች መወዳደር ዘበት ነው:: እያንዳንዷ ወጣት ሴት ውስጥ እድሜ የሚያመጣው የቁንጅና ውድድር አለ:: መልክ ያለው በመልኩ፣ የሌለው በዘመናዊና ውብ ልብሶች ውድድሩ ውስጥ አለበት:: በዚህ የታይታ ዘመን ግባቸው መታየት የሆነ እልፍ አእላፍ ወጣቶች የማይታዩ መስዋዕትነቶችን የሚከፍሉት ወደው አይደለም፤ መታየት መኖርን ማረጋገጫ አንድ ምስክርነት ስለሆነባቸው እንጂ:: እናም ለመታየት፣ ዕይታ ውስጥ የሚገባ አልባሳት አንዱ መስፈርት ነው:: በዚህ ውድድር ላለመውደቅ የከፋ አዘቅት ውስጥ የሚወድቁትንም ቤት ይቁጠራቸው::

*** *** ***

ፋና ጋር መቀራረብ በጣም ከባድ ነበረ:: አንዳንዴ ባህሪዋ ያበሳጨኛል:: "ምናይነት የደነዘዘች ልጅ ናት" እልና ለራሴ ቁጣ ቁጣ ይለኛል:: ለምን እንደ ፍቅርተ አታናግረኝም ? ሌላው ቢቀር አንድ ዓመት ሙሉ እዚህ ቤት ስኖር ቤቴን እንኳን ተሳስታ ረግጣው አታውቅም:: ፍቅርተ እኮ እናት ማለት ናት:: ረፍዶብኝ ፍራሼን ሳላነጣጥፍ ከወጣሁ ፍራሼን አነጣጥፋ፣ ያዝረከረኩትን ወረቀት አስተካክላ የሚጠጣ ውሃ ቀድታ አስቀምጣልኝ ነው የማገኘው:: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ምግቤንም የምትሰራልኝ ፍቅርተ ናት:: እች ፋና የሚሏት ዝግ ግን...ዝምታዋ ሰልችቶኝ ነበር::

የሆነ ጊዜ ታዲያ ድንገት ታመምኩ:: ለሳምንት ትምህርት ቤት አልሄድኩም፤ ፍቅርተና እማማ አመለ ተጨንቀው ሲሯሯጡ ሰነበቱ:: ፋና ዝርም ብላ አታውቅም:: ከዛን ጊዜ በኋላ የፋና

ነገር ቢቃኝ፡፡ "እግዜር ይግደልህ !" ማንን ገደለ? አንድ ቀን ሳትጠይቀኝ ቢቃ ድኜ ተነሳሁ፡፡ ፉና የምትባል ልጅ ቢቃ ቢቃችኝ፡፡ ሳልፍ ሳገድም እወረውርላት የነበረውን ሰላምታዬን እኔም አቆምኩ፡፡ ስገባ ብቻዋን ተቀምጣ ባገኘት እንኳን ሰላም አልላትም፡፡ እንደውም ከብስጭቴ ብዛት ቤት ለመቀየር አሰብኩ፡፡ ግን ለእማማ አመለ ምን ሰበብ እንደማቀርብ ጨነቀኝ፡፡ ከእኔ ከሚያገኟት የኪራይ ብር በላይ ለእኔ ያላቸው ቤተሰባዊ ፍቅር ቦታ አለው፤ ለእርሳቸው፡፡ ደግሞም ብቸኛ መተዳደሪያቸው ከእኔ የሚያገኟት የኪራይ ብር ነበረች፡፡ ምን ሆንኩ ብዬ ከዚህ ቤት ልውጣ ? እች ጉልት ስወጣ ስገባ እንደ ግኡዝ ነገር ተጎልታ ማየቴ ያበሳጨኛል፡፡ ማታ ማታ ቡና ሲጠሩኝ በህመሜ አሳብቤ ልቀር ብሞከርም አልተሳካም፡፡

"ቡና ባትጠጣ እንኳን ና እና ተጫወት፤ በሽታውም ለብቻ ሲሆኑ ነው የሚጠናው" አሉኝ እማማ አመለ፡፡ ጨዋታው እንደወትሮው አልጥምህ አለኝ፤ እጣኑ ከነከነኝ፤ ከእጣኑ ወዲያ አቀርቅራ የምትቀመጠው ፉና ሰለቸችኝ፡፡ እወዳታለሁ፤ ግን ግኡዝ ናት ቢቃ ! ወይስ ከራሷ ውበት ጋር በፍቅር ወድቃ ዓለምን ረስታለች ? ምናይነት ድንዛዜ ነው ይሄ ?

ፍቅርተ ጋር ቅርርባችን ተጠናከሮ ነበር፡፡ ማታ ማታ ቡናው እስከሚፈላ ደብተሯን ይዛ ወደ ከፍሌ ትመጣለች፡፡ ግን አታጠናም፤ ቤታቸው ውስጥ ቴፕ ስለሌለ ሁልጊዜ የደብተሯ ቦርሳ ውስጥ የምታኖረውን የአስቴርን ካሴት ይዛ ትመጣና በእኔ ቴፕ ታዳምጣለች፡፡ ግጥሙን ሸምድዳዋለች፤ ጀምሮ እስኪጨርስ በቃሏ ትወጣዋለች፡፡ ሙዚቃውን እንደ ሙዚቃ ሳይሆን እንደ መርዶ ነበር ፊቷን አጨፍግጋ የምታዳምጠው፡፡ አንድ ቀን ሙዚቃውን እያዳመጠች እንባዋ በጉንጯ ላይ ኮለል ብሎ ወረደ፤

"ምን ሆንሽ ፍቅርተ" አልኳት ደንግጬ፤

"ምንም" ብላ ተነስታ ከክፍሌ ወጣች፡፡ከዛን ቀን ጀምሮ ፍቅርተ የወትሮዋ አልነበረችም፤ የሌላትን አመል መነጫነጭ ጀመረች፡፡ ከመሬት ተነስታ ታለቅሳለች፤ በትንሽ ነገር ይከፋታል፡፡ ከወራት ልመና በኋላ ጭንቋን ተነፈሰችው፤ ፍቅርተ ፍቅር ይዧት ነበር፡፡ ፍቅር እንደያዛት ስትነግረኝ "እግዚአብሔር አምላከ ሆይ፣ የነገስታት ንጉስ፣ የዓለም ሁሉ ፈጣሪ ኃያል! እባክህ ይህች ልጅ ፍቅር የያዛት ከእኔ እንዳይሆን እርዳኝ" ብዬ ፀለይኩ፡፡

"ከስምንተኛ ክፍል ጀምሮ አብረን አንድ ክፍል ነው የተማርነው፤ ቶማስ ይባላል" ስትለኝ "ሃሌሉያ!" ብዬ ልጮኽ ቃጥቶኝ ነበር፡፡ ኡፍፍፍፍፍፍ ! አሁን እዳው ገብስ ነው ! ተረጋግቼ አዳምጣት ጀመር፡፡ የክፍሎቿ ልጆች ተሰባስበው የተነሱትን አንድ ፎቶ እየሰጠችኝ ልጁን ጠቆመችኝ፤ ሲበዛ ቆንጆ ልጅ ነበር፡፡ ከግራና ቀኙ ሁለት ቆነጃጅት እንደ መኽገር ተጣብቀውበታል፡፡

"አንቺ የታለሽ ታዲያ!" አልኳት፤

"እኔ ፎቶ መነሳት አልወድም" አለችኝ ትክዝ ብላ፡፡ ለምን ብዬ አልጠየቅኳትም፡፡

"ከወደድሽው ስንት ጊዜ ሆነሽ?" አልኳት ፎቶውን እያየሁ፤

"እኔንጃ ግን ቆይቷል ፤ ሶስት አመት"

"እና ሦስት ዓመት ሙሉ ስታፈቅሪው እርሱ ምን አለ ?"

"አያውቅም፡፡"

"ተነጋግራችሁ አታውቁም"

"አንድ ቀን አናግሮኛል..."

"እና ምን አለሽ?" አልኳት በጉጉት፡፡

"እርሳስ አጥቼ ስጠይቅ ሰጠኝ...ስመልስለት 'ውሰጂው!' አለኝ" አለችና እዛኛው ክፍል ሄዳ አንድ ቢጫ እርሳስ ይዛ ተመለሰች፡፡ እንደ ትልቅ ቅርስ በፍቅር እርሳሱን እየተመለከተች...፣ "አየኸው የእሱ ነው" አለችኝ፡፡ ፊቷ ላይ የነበረው ደስታ... ናፍቆት...ፍቅር ያሳዝን ነበር፡፡ ትቀጥላለች ብዬ ጠበቅኳት፡፡ የተነጋገሩት ግን እችኑ ነበር፡፡ አንድ ቃል "ውሰጅው" አላት፤ በቃ፡፡ ይሄ ቃል ለፍቅርተ "ንግግር" ነበር፡፡

"ለምን አታናግሪውም ታዲያ ? በቀጥታ መናገር እንኳን ባትችይ በሆነ መንገድ እንደወደድሽው አሳውቂው፡፡ እሱም ሊወድሽ ይችላል" አልኳት እንደው ለማፅናናት እንጂ ያልኩትን ለራሴም አላመንኩበትም፡፡ ይሄ ልጅ ፍቅርተን ቢወዳት በሺ ዓመት አንድ ጊዜ የሚከሰት አጋጣሚ አድርጌ ላየው ሁሉ እችላለሁ፡፡

በድንጋጤ አፍጥጣ እያየችኝ፣ "ትቀልዳለህ ?!" አለችኝና አፏን በሁለት እጇቿ አፍና እንደዘገነነው ሰው ሰውነቷ ተንዘረዘረ፤

"በጣም የሃብታም ልጅ ነው፤ በዛ ላይ ከላሳችን ውስጥ ካሉ ሰላሳ ሴቶች ግማሹ በሱ ፍቅር ያበዱ ናቸው፡፡ በእረፍት ሰዓት ጎታቹ ብዙ ነው፤ በዚያ ላይ ጎበዝ ተማሪ፤ ኤጭ" ብላ በምሬት ፊቷን አጨፈገገች፡፡ ዝም ብዬ አየኋት፤ ፍቅርተ ይበልጥ በቀረብኳት ቁጥር ይበልጥ መልከጥፉ የምትሆን ሚስኪን ነበረች፡፡ በቦዙ አይኖቿ ባዶውን እየተመለከተች ምሬቷን አምበለበለችው፡፡ "የሆነ ነገር ያስፈልግሃል፤ ለመፈቀር አንድ የሆነ ነገር ያስፈልግሃል፤ መልክ ወይም ሃብት...ብቻ የሆነ ነገር፤ እኔ ደግሞ ምንም የለኝም፤ መልክ የለኝ፣ ሃብት የለኝ፣ በትምህርት እንኳን እንዳላካክሰው እንደ ትምህርት የሚያስጠላኝ ነገር የለም፤ እማማ እንዳይከፋት ነው የምማረው፤ ችኮኛል፡፡ ከቤት ባልወጣ ደስታዬ ነው፤ ማንንም ባላይ፣ ማንም ባያየኝ ደስታዬ ነው" አለችና እንባዋ ይፈስ ጀመረ፡፡

"ፍቅርተ ለፍቅር ሃብት ፣ መልክ ምናምን ቢያስፈልግ ኖሮ እኮ አታፈቅሪም ነበር" አልኳት፡፡

ከአፌ ነጥቃ በቁጣ መናገር ጀመረች፡፡ንግግሯ በምሬት የተሞላ ነበር፡፡ "እንኳን ለፍቅር ለተራ

ሰላምታም ሀብት ያስፈልጋል ::መልክ ያስፈልጋል :: አንተ አስቀያሚ ወጣት ሆነህ ታውቃለህ ? አስቀያሚ ሴት ሆነህስ ታውቃለህ ? ህመሙ አይገባህም::አብርሽ መገፋቱ ስሜት አይሰጥህም... እየውልህ እንኳን አሁን ሕፃን ሆነን እኔና ፋና መንገድ ላይ ስንሄድ ያገኘን ሁሉ ፋናን አገላብጦ ጉንጯን ይስምና እኔን..." መጨረስ አልቻለችም እንባዋ ቀደማት::

"...አስራ ስምንት ዓመት አልፎኛል:: እስካሁን አንድ ወንድ እንኳን ጠይቆኝ አያውቅም:: እንዳንዴ እንዴት እንደተፋቀሩ ይቅርና ያፈቀሩት ጋር እንዴት እንደተጣሉ ሴቶች ሲያወሩ እቀናለሁ...ከፍቅረኛ ጋር መጣላት በራሱ ያስቀናል፤ ይናፍቅሃል፤ ሰው ሆነህ በፍቅር መጋጨትህ በራሱ ከሰው እኩል ያደርግሃል:: የሚጣላህም የሚወድህም በሌለበት ዓለም መኖር ካለመኖር እኩል ነው" ፍቅርተ ባንዴ ተቀየረችብኝ፤ አስፈሪ ሆነችብኝ:: ንፍጧ በአፍንጫዋ ተዝረከረከ፤ እንባዋ ፊቷን አጨቀየው፤ አስቀያሚነቷ ሙሉ ሆነ:: ስታሳዝን!

"አስራ ስምንት ዓመት እኮ ትንሽ እድሜ ነው...ገና ነሽ ወደፊት የሚያፈቅርሽ የራስሽ ሰው ይመጣል" አልኳት ልክ የሚያፈቅራትን ሰው የቀጠርኩት ይመስል በእርግጠኝነት:: ግን ውስጤ መቼም ቢሆን ፍቅርተን የሚያፈቅር ሰው በምድር ላይ የሚፈጠር አይመስለውም፤ እናገራለሁ፤ ግን የምለውን እኔም አላምንበትም::

በቅሬታ ፈገግ ብላ ልትሄድ ተነሳች:: እስካሁን በስሜት ባወራችኝ ነገር ሃፍረት ተሰምቷት ነበር...ማታ ቡና ላይ ግን ስትስቅ ስትጫወት ዓለም የሞላላት ደስተኛ ወጣት ትመስል ነበር:: ስቃይን አፍኖ እንደፍቅርተ መሳቅ ትልቅ ብቃት ሳይጠይቅ አይቀርም::

*** *** ***

ፋናን እንዳኮረፍኳት አስራ አምስት ቀናት አለፉ:: አስራ አምስት የሚያንገሸግሹ ቀናት:: ወደ ጓዳዬ ስገባ ፋና ያለችበትን ክፍል ማለፍ በሲኦል ውስጥ እንደማለፍ ነበር ለእኔ::የመገፋት ሥሜት ይሰማኝ ነበር ፣ የመናቅ ስሜት ይሰማኝ ነበር:: ልክ በአስራ አምስተኛው ቀን ከትምህርት ቤት ስመለስ ፋና ብቻዋን ቤት ውስጥ ተቀምጣ ነበር:: ሰላም ሳልላት አልፌ ወደ ክፍሌ ገባሁና ደብተሬን ፍራሼ ላይ ወርውሬ እኔም ፍራሼ ላይ በጀርባዬ ተንጋልዬ ተኛሁ::ለምን እንደሆነ እንጃ ፋናና እኔ ብቻችንን ቤት ስንሆን ይጨንቀኛል፣ የማደርገው ሁሉ ግራ ይገባኛል:: እንዳናግራት የሚገፋፋኝ ነገር አለ ግን አፌ አይከፈትም፣ እግሬም ወደ ርሷ ስንዝር መራመድ አይችልም:: ለራሷ ደንዝዛ እኔንም አደንዝዛኛለች::

በጀርባዬ ተኝቼ እያሰብኩ እያለ የበር መጋረጃዬ በቀስታ ሲገለጥ እና የውጪው ብርሃን ያሳደደው የሰው ጥላ ሲያርፍብኝ ታየኝ:: መጀመሪያ ፍቅርተ መስላኝ ነበር:: ቀጥ ብዬ ተመለከትኩ የተሰበሰበውን መጋረጃ በእጇ እንደያዘች ፋና በሬ ላይ ቃፊር መስላ ቆማለች...መንፈስ !! ዝም ብዬ አየኋት::

"ተሻለህ ?" አለችኝ:: እውነቱን ለመናገር ሳቄ ነበር መጀመሪያ የመጣው::

"አ..ዎ ደህና ነኝ" አልኳት መጋረጃውን ለቅቃ ተመልሳ ሄደች:: ውስጤ ሊዳፈን ዳር ዳር ሲል የነበረውን ፍቅር ቆስቁሳው ሄደች:: የተዳፈነ ፍላጎቴ በአንዲት ,ቃል እንደገና ነበልባል ሆኖ ፋናን በመሻት ያንገበግበኝ ጀመረ:: ለሌላ ዘላለም እዚሁ ቤት እንደምኖር እያሰብኩ ነበር:: ምን ጉድ ናት ይህቺ ፋና !! ሲቆይ የገባኝ አንድ ነገር ቢኖር ፋና እንኳን ሌላ ሰው ጋር ራሷም ጋር ለማውራት የምታፍር አይነት ልጅ መሆኗ ነበር::

የተቋረጠ ሰላምታዬን ቀጠልኩ:: ፋናም ከወትሮው ትንሽ፣ በጣም ትንሽ ቀረብ ያለችኝ መሰለኝ:: ይህን ቀረቤታ በሌላ መንገድ ለመግለፅ ካስፈለገ በዓይን የማይታይ በጣም ደቂቅ የሆነ የመቀራረብ ለውጥ ልንለው እንችላለን:: ከተለመደው መቀራረብ በሙቶ ሚሊየን እጅ ያነሰ ረቂቅ የነፍስ መቀራረብ:: ለእኔ ግን ይታየኛል ፍቅር የሚሉት አጉሊ መነፅር ዓይኖቼ ላይ ተደንቅሮ ነበርና የማያሳየኝ ነገር አልነበረም ::

የማይታዩ መቀራረቦች ተደማምረው ወደሚታይ መቀራረብ ለመቀየር ዓመት ወስደዋል:: ይሄ ቀስ እያለ የተገነባ ፅኑ የመቀራረብ ግንብ የወሬ ዛዛታ፣ አስር ጊዜ የመሟሟገል ስሚንቶ አልነበረም ፀንቶ እንዲቆም ያደረገው - መሰረቱ ዝምታ ነበር:: በእኔና በፋና ውስጥ ዝምታ ነበር:: በዛች ውድና ዘላለማዊ በምትመስል የቡና ሰዓት በእጣን መጋረጃችን ውስጥ ሁለታችንም ዓይኖቻችን ሲገጣጠሙ ነፍሶቻችን የሚያወሩት ነገር ነበር:: ፍቅርተና እማማ አመለ በሚያወሩን ነገሮች የጋራ ሳቅ ስቀናል፣ ፋና ስትስቅ ሳቋን አጅቤ እስቅ ነበር ምንም ይሁን ጉዳዩ፤ እኔም ሳወራ ፋና ትስቅ ነበር - ድጋፍ ነው:: ሳቋ ውስጥ "ለዘላለሙ ሳቅ አይለይህ" የሚል ምርቃት ነበር::

ፋናን በየቀኑ አፈቅራት ነበር:: አዳዲስ አይነት ፍቅር፣ ሰርክ አዲስ ፍቅር:: እንተያያለን:: ዓይኖቻችን ውስጥ ከብረት የጠነከረ መሻት ነበር:: ቃል ሳንተነፍስ ነገሩን ጨርሰነው ነበር...
"ፋኒ የኔ መልአክ እንዴት ነሽ"

"አብርሽዬ የኔ ጌታ ዛሬ ናፍቀኸኝ ነበር የት አምሽተህ ነው"

"ምን አንድ ሞዛዛ አስተማሪ ሲሟዘዝብን አመሸ ፋኒዬ የኔ ውብ..." በቃ እንደዚህ የምናወራ ይመስለኛል:: ራሴ በፈጠርኩት የሀሳብ ንግግር በደስታ አብዳለሁ:: እኔና ፋኒ ተግባብተናል:: እማማ አመለ እና ፍቅርተ እዚህ ቤት ውስጥ የታፈነ ገሞራ ሊፈነዳ እየተብላላ መሆኑ በጭራሽ አልገባቸውም:: ፍቅር ወሬ አያስፈልገውም፣ አዳሜ ጉድ የሆነው የሲጋም የነፍስም ዓይኖቹን ዘግቶ ስለፍቅር እየደሰኮረ ነው:: እኔና ፋኒ ዓይኖቻችንን ከፍተናቸው ነበር:: እናም በዓይኖቼ የፋናን ልብ እየተመለከትኩት ነበር - ወደኛል ! የፋናም ዓይኖች ልቤ ላይ ከተደገሰላቸው የፍቅር ድግስ ድርሻቸውን አንስተው ሲመለሱ ይታወቀኛል:: የሰው ልጅ እድሜ በወራት ቢሰየም ያ ጊዜ ለእኔና ለፋና መስከረም ነበር:: የህይወታችን መስከ በአደይ አበባ የተሽቆጠቆጠበት የመኖር ጅማሬ::

ቀስ በቀስ ፋና ወደክፍሌ ጎራ ማለት ጀመረች፣ ፍራሽ ሜፍ ላይ ትቀመጥና እናወራለን:: ስለምን እንደምናወራ አላውቅም:: ብቻ ፋና ካለች አውራ አውራ ይለኛል:: ለፍላሬ እሆናለሁ:: ብዙ ጊዜ ፍቅርተም አብራን ስለምትሆን ነፃ ሆነን እናወራም ::

አንድ ቅዳሜ ቀን ከሰዓት በኋላ ፍቅርተ የት እንደሄደች እንጃ ቤት አልነበረችም፤ እማማ አመለም ለቅሶ ቤት ሄደው ነበር:: ፋና መጣችና መጋረጃዋን ገለጥ አድርጋ በር ላይ ቆመች፣ ፋና ግቢ ካላልኳት አትገባም::

"ፋኒ ግቢ!" አልኳት ገባችና ፍራሹ ሜፍ ላይ ተቀመጠች:: እኔም ፍራሽ ላይ ተቀምጫለሁ- ጎን ለጎን ነን:: ፋና እንደ እንግዳ መሬት መሬት እያየች ተቀምጣለች:: ውስጤ በሐሴት ይጨፍራል:: በዓለም ላይ ካሉ እፁብ ድንቅ ነገሮች ሁሉ ትልቁ ነገር ጎኔ ተቀምጧል-ፍቅር!!

ከብዙ ዝምታ በኋላ፣ "ታምሜ ያልጠየቅሽኝ ለምንድን ነው?" አልኳት ጥያቄዬ ድንገተኛ ነበር::ደግሞ የመቼውን ህመም አንስቼ እንደወቀስኳት ለራሴም ገርሞኛል::

"ቤተክርስቲያን ስሄድ እንዲሻልህ ስፀልይልህ ነበር:: በጣም ነበር የተጨነቅኩት ...ደግሞ እንዲሻልህ ተስዬልህ ነበር" አለችኝ:: ውስጤ አዘነ::

"እና ስእለትሽን አስገባሽ?" አልኳት እንደ ቀልድ ነበር የጠየቅኳት:: ፋና አቀርቅራ ዝም አለች:: ፋና የተሳለችው አንድ ፓኮ ሻማ ነበር::ብር ስላጣች ስእለቷን አላስገባችም:: ስትነግረኝ እንጀቴ ነው የተላወሰው:: እጇን በእጄ ያዝኩት፤ ደነገጠች:: ቀስ አድርጋ እጇን ወደ ኋላዋ ለመሳብ ሞከረች፤ እኔ ግን እጇን ይገፍ ወደ እኔ ሳብኳት ፤ ሰውነቷ ይንቀጠቀጥ ነበር:: ቀና ብላ አየችኝ ፤ ዓይኖቿ በእንባ ተሞልተው ነበር:: ከንፈሮቻችን ሲገናኙ የፋና ጉንጮች ላይ እንባዋ ተዘረገፈ:: ጥብቅ አድርጌ አቀፍኳት ፤ ደረቴ ላይ ተለጥፋ በእጆቿ የወገቤን ዙሪያ አቀፈችኝ::

*** *** ***

ከፋና ጋር ከተሳሳምንባት ቅዳሜ በኋላ ዋና ስራችን የእማማ አመለ እና የፍቅርተ እግር ሲወጣ መጠበቅ ሆነ...በቃ ወጣ ሲሉ ፋና ወደ ክፍሌ ሮጣ ትመጣና እቅፌ ላይ ናት፣ ከንፈሮቻችን እንዳይገናኙ ማድረግ ከሁለታችንም አቅም በላይ ነበር:: በፍቅር ሰከርን፤ አንዳንዴ እማማ አመለ ቤት ውስጥ ሆነውም ፋና ተነስታ ወደ ክፍሌ ትገባለች፣"አብርሽ ስራ ይዘሃል እንዴ?" ትላለች::እማማ አመለ ከትምህርት ጋር የተያያዘ ነገር አድርገው ስለሚያስቡት በጭራሽ አይጠራጠሩም::ፋኒ ወደ ክፍሌ ትገባና እንደ እብድ ትስመኛለች! ከሚፈታተነኝ ስሜት ጋር እየታገልኩ እማማ አመለ እንዳይሰሙ የተቻለኝን ሁሉ አደርጋለሁ፤ ፋኒ ግን መሳሳም ከጀመርን ነፍሷን አታውቅም፤ ማንም ቢመጣ ግድ አይሰጣትም::

ማታ ማታ ቡናችን ላይ ስንቀመጥ ፋኒ ዓይኖቿን ከእኔ ላይ መንቀል አትችልም፤ በቃ ዓይኗ ቡዝዝ ብሎ ታየኛለች:: አስተያየቷ ይጨንቀኛል:: ፍቅርተ ድንገት ብትጠራጠር ብዬ እፈራለሁ::

ደግነቱ ፍቅርተ ሳታቋርጥ ስለምታወራ ሁለታችንንም አትመለከተንም። ፋና ትምህርት ማጥናቷ ሁሉ እርግፍ አድርጋ ተወችው። በየምክንያቱ እኔ ክፍል መመላለስ ሆነ ስራዋ። መቸም እኔና ፋና ከዚህ በፊት እማማ አመለ አዕምሮ ውስጥ የፈጠርነው እምነት ረዳን እንጂ የፋና ባህሪ መቀየር፣ የሁለታችንን የፍቅር ግንኙነታችንን አፍ አውጥቶ የሚናገር ነበር። አንዳንድ ሰው አየ መሃል ላይ መቆም የማይችል፣ ወይ ጥቅልል አድርጎ ራሱን ይሰጣል፣ አልያም ገና ከሩቁ ከሰወ ይሸሻል - ፋና እንደዛ ነበረች። ሙሉ እሷነቷን ለእኔ ስለሰጠችኝ ለምትሰራው ነገር ሁሉ ሌ ሰው አልታይ አላት።

*** *** ***

የነፋና ኑሮ ሊገልፁት በማይችሉት ድህነት ውስጥ የተዘፈቀ ነበር። ባጭሩ ቤት ያላቸው የጎዳና ተዳዳሪዎች ይመስሉኛል። አንዳንዴ እማማ አመለ የከሰል መማገሪ ብር ያጡ ስለነበረ ከቤቷ ጋር ተያይዛ የተሰራች በላስቲክ የተጋረደች ኩሽና ውስጥ ምናምኑን ጓድፈው ይማግዱና ቡና ያፈላሉ። ቡናው ታዲያ ጣዕሙ ጭስ ጭስ ይላል። እኔ ያን ያህል ብር ባይተርፈኝም አንዳንዴ ከቤተሰብ ሲላክልኝ ለፋና አልያም ለፍቅርተ ትንሽ ብር ልሰጣቸው እሞክራለሁ። ሁለቱም ቢሞቱ ብር ከእኔ አይቀበሉም። ብዙ ጊዜ ሞክሬ ሲቸከኝ መጠየቁንም ትቼዋለሁ። አንድ ቀን ታዲያ ፋና ወደ ክፍሌ ገባችና እየፈራች "አብርሽ ሰላሳ ብር አለህ ?" አለችኝ ፊቷ ላይ የነበረው ሀፍረት ያሳዝን ነበር። ደስ ብሎኝ ለፋና ድፍን ሃምሳ ብር ሰጠኋት፣ ደስ ብሏት እየተጣደፈች ወጣች።

ፋና ወደ ማታ አንድ የተጠቀለለ ነገር ይዛ ወደ ክፍሌ ገባች። ፊቷ በደስታ ፈገግታ ተጥለቅልቋል፡ ፡ ጥቅልሉን ፈታታችና አንድ ጥቁር የሴት ጅንስ ሱሪ አወጣች፣ "ለፍቅርዬ ገዛሁላት" አለችኝ። ሱሪውን ሳይሆን ፋና ፊት ላይ የነበረውን ፈገግታና ደስታ አይቼ መጥገብ አልቻልኩም። ፋና እንደዚህ በደስታ ስትስከር አይቻት አላውቅም።

ትምህርት ቤታቸው ውስጥ በነበረ የስነተዋልዶ ስልጠና ላይ ተሳትፋ በተሰጣት አበል ከእኔ ሰላሳ ብር ጨምራ ለፍቅርተ ይህን ሱሪ ገዛች። ፋና እንዲህ አይነት ልጅ ነበረች። ቁንጅናዋ የልብሷን ተራነት ይሸፍነዋል እንጂ ለራሷ አንድም የረባ ልብስ የላትም። አዲሱን ሱሪ ይዛ ፍራሽ ጫፍ ላይ ተቀመጠችና በጀርባዋ ተደገፈችኝ። የሆነ ርካታ ይነበብባት ነበር።

"ፍቅርዬን እወዳታለሁ ከህፃንነታችን ጀምሮ ሁሉም ሰው እንደገፋት ነው የኖረችው። ሁልጊዜም ስለሷ እያሰብኩ እሰቃያለሁ።" አብርሽ ፍቅር እኮ እንደ መልኳ አይደለችም ደግ ነች፣ ጥሩ እህት፣ ጥሩ ጓደኛ ናት። ሁሉም ሰው ግን ይርቃታል" አለችና ማልቀስ ጀመረች። እንባዎቿን ጠረግኩላት። እንባዋ በንፁህ ጉንጮቿ ላይ ሲንኳለል መስተዋት ላይ የፈሰሰ ውሃ ይመስል ነበር፤ ጉንጯን ሳምኳት ፤ ወዲያው ግን በየት በኩል እንደተንሸራተትኩ እንጃ ከንፈራችን ተገናኘ። ቅልጥ ያለ መሳሳም ውስጥ ገብተን ይሄን የዘቀጠ ኑሮ የጠቆረ ድህነት ለደቂቃዎች ተሰናበትነው።

ሱሪው ፍቅርተን ቀየራት። ስትለብሰው ዳሌዋን ሰፋ አድርጎ ወገቧን ሸንቀጥ ስላደረገው የፍቅርተ

ቁንጅና መቃብሩን ፈንቅሎ ወጣ:: ስራውን ስትለብስ አንድ የጥንካሬ መንፈስ የለበሰች ይመስል አስገራሚ በራስ መተማመን ይታይባታል:: ጓደኞቿ ጋር መውጣት፣ አመሻሹ ላይ ከጎረቤት እኩዮቿ ጋር ተያይዛ መዞር ጀመረች:: በዕርግጥም ስራው የሰውነቷን ቅርፅ ጎላ አድርጎ አሳምሯት ነበር:: ይህንን አድናቆት ከአንዳንድ ወንዶች ጭምር እንደተቸራትም ፍቅርተ ራሷ በደስታ ለእኔና ለፋና እየነገረችን ሲታስቀን ነበር:: ልብስ መንፈስ ነው:: ስጋን ሽፍኖ የስጋን ውበት የሚያጎላ መንፈስ:: ይሄ መንፈስ ስራ ተመስሎ ፍቅርተ ላይ አርፎ ነበር ::

*** *** ***

የእነፋና ህይወት ከቀን ወደቀን ወደባሰ ድህነት እየተዘፈቀ ነበር የሚሄደው:: እማማ አመለ አልፎ አልፎ ልብስ ያጥቡላቸው የነበሩ የመንገድ ስራ ሙያተኞች ነበሩ:: ከዛች የሚያገኟት ገቢ እኔ በየወሩ ከምሰጣቸው የኪራይ ብር ጋር ተዳምራ ኑሯቸውን ስትደጉም ኖራለች:: ታዲያ የመንገድ ስራ ባለሙያዎቹ መንገዱን ሰርተው ስለጨረሱ የእማማ አመለም ገቢ ተቋረጠና ቤተሰቡ የባሰ ችግር ላይ ወደቀ:: አንዳንድ ቀን የወትሮውን ቡና ማፍሊያ ብር ስለሚያጡ ሁላችንም በጊዜ እንተኛለን:: ቤቱ እንደ መቃብር ቤት ፀጥ ይላል:: በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ በሰፈሩ ለሚያልፈው መንገድ ግንባታ ቤታቸው በቅርቡ እንደሚፈርስ ለእማማ አመለ ተነገራቸው:: እማማ አመለ ይህን መርዶ እንደሰሙ ሙሉ ቀን ታምመው ከአልጋቸው ሳይነሱ ዋሉ::

አንድ ቀን ታዲያ ፍቅርተ ትምህርቷን አቋርጣ ካፍቴሪያ በእቃ አጣቢነት ለመቀጠር መወሰኗን ለቤተሰቡ አሳወቀች፣ መርዶ ነበረ:: እማማ አመለ እያለቀሱ እግሯ ላይ ወድቀው ለመኗት:: ፋና ፊቷ ገርጥቶ እና አይኖቿ በእንባ ተሞልተው ዝም ብላ ፍቅርተን እና እናቷን ትመለከታለች:: በብዙ ልመና ፍቅርተ የዛን ቀን ትምህርት ቤት ሄደች:: ፋና ፊቷ በሐዘን ድባብ ተውጦ ከወትሮ ዝምታዋ ሺ ጊዜ የገዘፈ ዝማታ ውስጥ ሰጥማ ዋለች:: የዛን ጊዜ ፋና የአስራሁለተኛ ክፍል ፈተና ወስዳ ውጤት እየተጠባበቀች ነበር::

በቀጣዩ ቀን ወደ ማታ ላይ ፋና ወደ ክፍሌ መጣች:: አልሳመችኝም፣ ትክዝ ብላ ፍራሽ ጫፍ ላይ ተቀመጠችና "አብርሽ አረብ አገር ልላክሽ የሚለኝ የሆነ ጎረቤታችን አለ፣ ብዙ ልጆች ልኳል እዚሁ እኛ ሰፈር ነው ተፈሪ የሚባለው ታውቀው የለ ?" አለችኝ::

"እና..." አልኳት አሁኑኑ ብርር ብላ ትሄድብኝ ይመስል ስጋት ሁለመናዬን ወርሮት እጆቿን በእጆቼ እየያዝኩ:: ደንግጬ ነበር፣ መተንፈስ ሁሉ አቅቶኝ ነበር::

"አይ ቢያንስ ፍቅር ትምህርቷን እስክትጨርስ ለሁለት ዓመት ሰርቼ ብመለስ ብዬ አሰብኩ፣ በዛ ላይ ይሄ ቤት ከፈረሰ የት እንወድቃለን - ዘመድ የለን መጠጊያ" አለችኝ:: ድንጋጤዬ አስደንግጧት ሳይሆን አይቀርም ስትናገር ፈርታ ነበር::

"አብደሻል ፋኒ...ምን ሰይጣን ነው ይሄን ያሳሰበሽ...እንዴት እንደዚህ አይነት መጥፎ ነገር

ታስቢያለሽ" ጮህኩባት…፡፡

"ኧረ አብርሽ ቀስ አማማ እንዳትሰማ" አለችኝ በሹክሹክታ በአገጯ ወደዛኛው ክፍል እየጠቆመች፡፡

"ስሚኝ ፋኒ ! ትምህርቴን ልጨርስ፡ አንድ ዓመት የማትሞላ ጊዜ ናት የቀረችኝ፡፡ እንደጨረስኩ እንጋባለን፡ ስራ እይዛለሁ፡፡ ከዛ በኋላ አንቸገርም ፤ እባክሽ ለዚህች አጭር ጊዜ ብለሽ መጥፎ ነገር አታስቢ!" ፋናን ጨምድጄ ይዤ እንደ እብድ ለፈለፍኩ፡፡ የምናገረው ከልቤ ነበር፡፡ ፋናን ማግባት በምድር ላይ ካሉ ጉዳዮች ሁሉ ቅድሚያ የምሰጠው ጉዳይ ነበር፡፡ ፊቷ ላይ የነበረው ባዶነት ፤ ዓይኖቿ ውስጥ የነበረው ተስፋ መቁረጥ የነገረኝ ነገር ነበር፡፡ ፋና ስጋዋን አስቀምጣ ቀድማ ወደማታውቀው ዓለም ሄዳለች፡፡ በቃ የለችም ፡፡ ሳምኳት ምንም አልተሰማትም ! ፋና የኔ ውብ የእኔ መለአክ እንኳን ስሚያት ዓይኖቻችን ሲተያዩ ፊቷ በፍቅር ስሜት የሚቀላው ፋና አይኔ እያየ ከሰማለች፡፡ እንደ ግዑዝ ተራራ ከስሩ ውሃ እንደሚያመነጭ ግዑዝ ስጋዋ ብቻ እንባ እያፈለቀ አጠገቤ ተቀምጧል፡፡

"ምናባቴ ላድርግ አብርሽ ጨነቀኝኮ…ለስሙ የመጀመሪያ ልጅ ነኝ…ትልቅ እህት ነኝ፡፡ ቤተሰቦቼ በችግር ሲያልቁ እጄን አነባብሬ ማየት ብቻ ሆነ ስራዬ፡፡ እህቴ በብስጭት አንድ ነገር ብትሆንብኝ ዘላለም ሲፀፀተኝ ይኖራል፡፡ ማነው የዚህ ቤተሰብ ታዳጊ፡፡ ዘመድ የለንም፡ ማን መጥቶ ከዚህ መከራ ያውጣን ? …መሃል አዲስ አበባ ላይ ቤተሰቦቼ በረሃብ ሲሞቱ ዝም ልበል ?…መሃል አዲስ አበባ ቤተሰቦቼ በድርቅ ይለቁ ? …ጎረቤት የሚሰራ ወጥ እየሸተታቸው አንጀታቸው ታጥፎ ሲተኙ ዝም ልበል ? ንገረኛ አብርሽ ! እሺ ምን ልሁን፡ ሴተኛ አዳሪ ልሁን? እናቴ የቡና ሱስ እያሰቃያት አይኗ እንባ እያጎረፈ ጎረቤት የሚወቀጥ ቡና ድምፅ እያዳመጠች "ቡና በጠሩኝ" እያለች ስትመኝ እያየሁ ስንት ዓመት በዝምታ ልኑር?…እንዴት ልጆቿን ለማሳደግ እድሜ ልኳን የተራበች የተንከራተተች ባልቴት ልጆቿም ደርሰው በርሃብ ስትሰቃይ እያየች ዝም የምትል ልጅ ልጅ ትባላለች ? እሄዳለሁ ! የትም ቢሆን እሄዳለሁ" ብላኝ እንባዋን ጠራርጋ ከክፍሌ ወጣች፡፡ አፈር ለብሶ በዝምታ የኖረ ፈንጅ የድህነት ጨካኝ እግር ረግጦት ፈነዳ ፤ ውስጤ በፍንዳታው ሲናጥ ይሰማኛል፤ የአብሮነት ከተማ ሲፈራርስ፣ የፍቅር ቅርስ ሲወድም ይታየኛል፡፡

ማታ ላይ ፍቅርተ ፊቷ ሳቅ ለብሶ ሳቅ ጎርሶ መጋረጃዬን እስኪገነጠል በርግዳው ገባች፡፡ ተጠምጥማ ጉንጬን ሳመችኝ ፡፡ እውነቱን ለመናገር በዛ ከንፈር አፈሰችኝ ማለት ይሻላል ! ከዛም ድምጿን ቀንሳ፡ "ቀጠረኝ" አለችኝ፡፡ ለሶስት ዓመት ያፈቀረችው ልጅ ቅዳሜ ሊያገኛት ቀጥሯት ነበር፡፡ "ለምን?"…"እንዴት?" አላልኳትም የፋና ጉዳይ እያብሰለሰለኝ ነበር፡፡ ብቻ ለማስመሰልና አብሬያት ለመደሰት ሞከርኩ፡፡ ፍቅር ግን እንዴት ኃያል ነው በእግዚአብሔር ! ችግር እያግደው - በቃ በመከራ የተከበበን ሰው ከመሬት አስነስቶ ያስፈነድቀዋል ወይንስ ያፈቀረ ሰው ለሌላው የማይታይ ላፍቃሪው ብቻ የሚገለጥ ከችግር፣ ከድህነት፣ ከመከራ የሚታደግ የመላእክት፣ የእሳት ሰረገላ አገሩን ከብቦ ይታየዋል ?

ለፍቅርተ ቀጠሮ በነገረችኝ ሰዓት ቸልተኛ ልሁን እንጂ በእርሷ ደስታ የፋና የስደት ሐሳብ

ይጨነግፋል ብዬ ስላሰብኩ በሚያስፈልጋት ሁሉ ከጎኗ ሆኜ ድጋፍ ለመስጠት ወሰንኩ:: ቅዳሜ ጧት ሃምሳ ብር ሰጠኋት:: ላለመቀበል አንገራግራ ነበር፣ "ፀጉርሽን ተሰሪ! ደግሞ ቀጠሮ ቦታ ባዶ እጅ አይኬድም" ብዬ አሳመንኳት:: ብሩን ተቀበለችኝ::

ጥቁር ሱሪዋን ከአሮጌው ሻንጣ አወጣችና ማጠብ ጀመረች፣ "ይሄ ሱሪ እዳውን አየ እስቲ አሁን መች ለበሽውና የምታጥቢው?" አሉ እማማ አመለ:: ፍቅርተ እያንጎራጎረች አጠባዋን ቀጠለች:: በዚህ ሰዓት እግዜር ወርዶ ቢናገራትም መስማቷን እንጃ ! ሱሪውን አጥባ ስትጨርስ አስተካክላ ገመድ ላይ አሰጣችና ወደ ፀጉር ቤት በደስታ እየተንሳፈፈች ሄደች:: እኔም "ክላስ" ስለነበረኝ ወደ ግቢ ሄድኩ::

*** *** ***

ከሰዓት በኋላ ወደ ስምንት ሰዓት አካባቢ ከምማርበት ኮሌጅ ስመለስ እማማ አመለወርቅ በራቸው ስር ሁልጊዜ የሚቀመጡባት ጠፍጣፋ ድንጋይ ላይ ተቀምጠው አገኘኋቸው::አይናቸው ቡዝዝ ብሎ በሀሳብ በመመሰጣቸው እስካናግራቸው ድረስ አጠገባቸው መድረሴንም አላዩም ነበር:: ለወትሮው እዚህች ድንጋይ መቀመጫ ላይ የሚቀመጡት እጃቸው አጠር ሲል ለእለት ቡና ብር ቢጤ ሲቸግራቸው ነበር:: የድንጋይ ወንበሯ የመተከዣ መድረካቸው ናት::

"ማዘር ምነው ሰላም አይደሉም እንዴ ?" አልኳቸው::

ቀጥ ብለው እንባ በቋጠሩ ዓይኖቻቸው ተመለከቱኝና ሳግ በተናነቀው አሳዛኝ ድምፅ ! "የፍቅርዬን ሱሪ ወሰዱባት አብርሽ" አሉኝ ሌባ ቁሳቁስ ብቻ ሳይሆን ተስፋ ጭምር እንደሚሰርቅ የገባኝ ያኔ ነው:: ፍቅርተ ለዓመታት ስትመኘው ከኖረችው ፍቅር፣ በተዓምር ከተሳካ ቀጠሮ በአንድ ሱሪ ምክንያት መቅረት አልፈለገችም:: የሆዷን በሆዷ አድርጋ ሰፈር ውስጥ ወዳሉ እኩዮቿ ሁሉ እየሄደች ልብስ እንዲያውሷት ጠየቀች - አልተሳካላትም:: ሁሉም ልብስ አላቸው፣ ሁሉም ልብሳቸውን የማያውሱበት ምክንያትም አላቸው:: ሁሉም ግን አንድ ተራ ልብስ በዚያች ቀን ለፍቅርተ ከንጉስ ካባ የበለጠ ዋጋ እንደነበረው አያውቁም ነበር::

ፍቅርተ አንገቷን ደፍታ ወደ ቤት ገባችና ሁልጊዜ ፋና ትቀመጥበት የነበረው ኩርሲ ላይ ተቀመጠች :: የፋናን ወንበር ብቻ ሳይሆን የፋናን ዝምታ ወረሰች:: ከዛን ቀን ጀምሮ ፋናም ዝም፣ ፍቅርተም ዝም ! እማማ አመለ ብቻ እንዲሁ የልጆቻቸውን ዝምታ ለመስበር የባጥ የቆጡን ያወራሉ:: የማታ ማታ ቡናችን እንደወትሮው አይደምቅም ነበር:: የፍቅርተን ሱሪ የወሰደው ሌባ የፍቅርተን ምላስ የወሰደው እስኪመስለኝ ፍቅርተ ከዛ በኋላ እንደበፊቱ ስታወራ ሰምቻት አላውቅም::

"አብርሽ ሰላም ነው" ቢቃ የምታናግረኝ እችን ብቻ ነበር:: እንደ በፊቱም እቤቴ አትመጣም:: ከትምህርት ቤት ስትመለስ የእማማ አመለን ነጠላ በደንብ ልብሷ ላይ ጣል ታደርግና ቤተክርስቲያን ትሄዳለች:: አንዳንዴ በጣም አምሽታ ስለምትመለስ እና ጧት ስለምትወጣ ለሁለት ለሶስት

ብርሃን የሰለቸውና ከወትሮው ቀን እንነጋገርም:: በሰሱ መጋረጃ ዓይኖቹን ልኬ በደበዘዘው የባሰ አስፈሪ የሆነ ፊቷን አያለሁ::

ፋና ጋር የነበረን ግንኙነት ግን ቀስ በቀስ እንደነበረው ተመለሰ ፤እንደውም ከበፊቱ የበለጠ አብረን መዋል ጀመርን:: ፋናም የበፊቷ አፍቃሪ ፋና ሆነች:: ዓለምን ረስተን በዛች ደሳሳ ጎጆ ውስጥ የራሳችን ፀሐይ፣ የራሳችን ጨረቃ፣ የራሳችን ከዋክብት ያሉባት ዓለም ፈጠርን ፤ ፋናን ያፈቀርኳት ሳይሆን እኔን ራሴን የሆነች እስኪመስለኝ ሁሉ ነገሬ ሆነች::

የሶስተኛ ዓመት ትምህርት እንዳለቀ ለእረፍት ወደ ቤተሰቦቼ ለመሄድ ምን ያህል እንደተጨነቅኩ መግለፅ አልችልም:: ፋናን ትቼ መሄድ ራሴን ትቼ ከመሄድ በምንም አይተናነስም:: ግን የግድ መሄድ ነበረብኝና ወደ ቤተሰቦቼ ጋር ከፍለ ሐገር ለሁለት ወር እረፍት ሄድኩ:: ለተከታታይ ሁለት ሳምንታት ፋና በህዝብ ስልክ እየደወለችልኝ እናወራ ነበረ፣ ከዛ በኋላ ግን ድምፁዋ ጠፋ፤ ለአስራ አምስት ቀናት ጠበቅኩ ፤ ፋና አልደወለችም:: የማውቀው ስልክ አልነበረኝም፣ ፋናም ስልክ አልነበራትም - ናፍቆቷን መቋቋም ለእኔ ስቃይ ነበር ::

በመጨረሻ ወሰንኩ:: ቤተሰቦቼን የምማርበት ኮሌጅ እንደጠራኝ በመንገር ማቄን ጨርቄን ሳልል በአንድ ወሬ ወደ አዲስ አበባ ተመለስኩ:: አዲስ አበባ ስደርስ ልቤ ፈርቶ ነበር:: እቤት ስደርስ እማማ አመለ አንገቴ ላይ ተጠምጥመው ሳሙኝ:: እንባቸው አንገቴ ስር ሲረጥበኝ ነበር እያለቀሱ መሆኑን ያወቅኩት::

ወደ ቤት ስገባ ቤቱ ካለወትሮው ጭር ብሏል:: እማማ አመለ ጉድ ጉድ ብለው ቡና አፈሉ፣ "ድንገት መጣህብኝ" ብለው ቁራሽ እንጀራ በበርበሬ አቀረቡልኝ እና  የመጀመሪያውን ቡና ቀድተው ሲያቀብሉኝ እጃቸው ሲንቀጠቀጥና ሲኒው ከማስቀመጫው ጋር በእጃቸው እንቅጥቃጤ ምክንያት ሲንቀጫቀጭ ተመለከትኩ:: ልቤ የባሰ ፈራ::

"አቡዬ ይሄውልህ ፋኒዬ ድንገት ሳላስበው ብድግ ብላ አረብ አገር ሄደችብኝ" አሉና እንባቸውን ዘረገፉት ! የያዝኩት ቡና ሳላስበው ከእጄ ላይ ወድቆ ተከነበለ::

"እንዴት ማዘር?...ማን ወሰዳት?...እርስዎ እንዴት ዝም ይላሉ?..." የጥያቄ መዓት ዘረገፍኩባቸው፣ ራሴን መቆጣጠር አልቻልኩም ፤ እማማ አመለ ግን አንገታቸውን ደፍተው አንዲት የቄጤማ ዘለላ እያፍተለተሉ ስቅስቅ ብለው ከማልቀስ ውጭ ቃል አልተነፈሱም:: ሽበት የወረረው ፀጉራቸው፣ ቆዳቸው፣ በእርጅና ብዛት የተጨማደዱ እጆቻቸውና አስር ቦታ ላይ በክር የተሰፋ ኮንጎ ጫማ ያጠለቀ እግራቸውን ስመለከት ከፋና ናፍቆት ጋር ተደማምሮ እንባዬ ከውስጤ ገነፈለ ::እማማ አመለ ማልቀሴ አስደንግጧቸው ከፍራሻቸው ተነስተው መጥተው ጎኔ ተቀመጡና እንደ ልጅ አጥንታም ደረታቸው ላይ ራሴን አስጠግተው አቀፉኝ:: ሁለታችንም በዛች ልትፈርስ አንድ ሃሙስ በቀራት ደሳሳ ጎጆ ስቅስቅ ብለን ተላቀስን::

ወደ ማታ ላይ ፍቅርተ መጣች:: ገና ስታየኝ አቅፋኝ መነፋረቅ ጀመረች:: በቀጣዩ ቀን የማደርገው ነገር ግራ ገብቶኝ ፍራሽ ላይ ተቀምጬ ስቆዝም ፍቅርተ ወደ ከፍሌ ገብታ የተጣጠፈ ወረቀት ሰጠችኝ እና ወደ ከፍሏ ተመለሰች:: ፋና የፃፈችልኝ ደብዳቤ ነበር ፤ የፋኒ ትንንሽና ቁልጭ ያሉ ፅሁፎች:-...

"አብርሽዬ መቼም እንደምታዝንብኝ አውቃለሁ:: ጨካኝ ትለኛለህ አውቃለሁ:: ግን...በሌለህበት እዚህች ብዙ ነገር ያሳለፍንባት ጓዳ እየገባሁ ስንት ቀን አለቀስኩ መሰለህ...ችግራችን ገፋኝ... በየቀኑ የማየው ነገር አንገሸገሸኝ:: ከአንተ በላይ የቤታችንን ችግር የሚያውቅ ማን አለ አብርሽ? በእርግጥ የዛን ጊዜ ለመሄድ ማሰቤን ስነግርህ የሆንከውን ነገር አይቼ ሐሳቤን ቀይሬ ነበር፤ ግን የፍቅርዬ ሱሪ የጠፋ ቀን በቃ ወሰንኩ:: እንዳትቆጣኝ ሃሳቤንም እንዳታስቀይረኝ ፈርቼ ተደብቄ ደላላው ሰውዬ ጋር አስፈላጊውን ሁሉ ጨረስኩ፤ አንተ ለእረፍት እስከምትሄድ ነበር የምጠብቀው:: ፍቅርዬ በውስጧ የሞተውን ፍቅር፣ የከሰመውን ተስፋ ማዳን የምችልበት ሌላ ነገር የለኝም::

አፈቅርሃለሁ አብርሽ - አከብርሃለሁ እና እመለሳለሁ::እግዚአብሄር እንዲረዳኝ ፀልይልኝ:: ስለምታፈቅረኝ ከልብህ እግዚአብሄርን እንደምትለምንልኝ አውቃለሁ:: አብርሽ እዛ ትልቁ ዲክሽነሪ ውስጥ የነበረውን ጉርድ ፎቶግራፍህን ሳላስፈቅድህ ወስጄዋለሁ:: ሁልጊዜም ላይህ እፈልጋለሁ - ሁልጊዜም አብርሽዬ...ግን እንዳትረሳኝ ሁልጊዜም አፍቅረኝ::

አብርሽ ትወደኝ የለ ? እማማን ትወዳት የለ ? ፍቅርን ትወዳት የለ ? እኔ እና አንተ በፍቅር ልናሳልፋቸው ከምንችላቸው ውድ የፍቅር ጊዜያት ሁለት ዓመት ለምንወዳቸው ሰዎች ብንሰጥ ሁሉንም ነገር ታውቀዋለህና ይቅር ትለኛለህ ብዬ አስቤ ነው:: እንኳን እንዲህ ርቄህ መሄድ ከዚህች መጋረጃ አልፌ ከከፍልህ ስወጣ አልቅሽ አልቅሽ እኮ ነው የሚለኝ:: አብርሽ እፈራለሁ፤ ከፊቴ ምን እንደሚጠብቀኝ አላውቅም - ግን ምናባቴ ላድርግ...እመብረሃን ትርዳኝ !"

ደብዳቤውን አንብቤ ስጨርስ አቅመቢስነት ተሰማኝ:: በቃ ! ከአሁን በኋላ እድሜ ልኬን ለማንም ለምንም የማልጠቅም ከንቱ መሆኔ ገዘፈብኝ:: ፍራሽ ላይ በደረቴ ተኝቼ ወደ ዛኛው ከፍል በትካዜ መመልከት ጀመርኩ::

ከመጋረጃዬ ባሻገር ድህነት የነገሰበት ዓለም ይታየኛል - የተራቡ ባልቴቶች ቅንጦት ባሰከራት ከተማ ስር ተቀብረው ይታዩኛል:: ሊሰደዱ የሚያኮበኩቡ ወጣቶች ታዳጊ አጥተው ይታዩኛል... ትምህርታቸውን ትተው ለጉልበት ስራ የተሰለፉ ወጣቶች ይታዩኛል:: ለእለት ጉርስ ለዓመት ጉርስ የተቸገረ ቤተሰብ ይታየኛል:: ከመጋረጃው ወዲህ ከፍሌ ውስጥ ሬዲዮው ያወራል - ስለ ሙዚቃ ያወራል፣ ስለ ልብስ ያወራል፣ ስለ ፅዳት ያወራል፣ ስለ እድገት ያወራል፣ ስለ ፖለቲከኞች ምርጫ ያወራል፣ የአገር መሪዎችን ያሞካሻል:: ሬዲዮው አጠገብ በልቼ የተረፈኝ ዳቦ በወረቀት ተጠቅልሎ ተቀምጧል:: ከጎኑ እንቁላል የተጠበሰበት መጥበሻ ከነተረፈ የእንቁላል ጥብሱ ይታየኛል:: እኔ ያለሁበት ሆነው የእማማ አመለን ቤተሰብ ሲመለከቱት ይህ ቤት "ከሰሃራ በታች" ነው::

ችግሩ ፣ተስፋ ማጣቱ ፣ስደቱ የተጧጧፈበት፣ ሰው በአይነውሃው የሚጠላበት፣ በተፈጥሮ መልኩ ደረጃው ከፍና ዝቅ የሚልበት፤ ይሄ ቤት "ከሰሃራ በታች" ነው ! እኔ ቤታቸውን ተከራይቼ የምኖረው ስደተኛ ባለቤቶቹ ተወልደው ባደጉበት ጓዳ በችግር ሲሰቃዩ እየታዘብኩ ነውና ይሄ ቤት "ከሰሃራ በታች" ነው:: አዲሳባ እንዲህ ናት ! አገሬ ከነጭ ልብሷ፣ አገሬ ከጠጅና ጮማ ግርጌ እቻትና:: በስስ መጋረጃ ድንበር የተካለሉ ጎረቤቶች አንዱ ብሩን መጣያ አጥቶ በጥጋብ 'ሽቅብ ሲሽና' ከመጋረጃው ጀርባ በረሀብ ከንብል የሚሉ እልፎች የሚኖሩባት አገሬ እቻትና !

*** *** ***

ከተመረቅኩ በኋላ አዲስ አበባን ለቅቄ ወደ ቤተሰቦቼ ሄድኩ:: እዛው ስራ ስላገኘሁ አዲስ አበባን ለአራት ዓመታት ተመልሼ አላየኋትም:: ፋናም በውስጤ ደበዘዘች::ቀስ በቀስ ያች የፍቅር ጀምበር በመለያየት አድማስ ጠለቀች:: ሌላ ህይወት፣ ሌላ ታሪክ ውስጥ ገባሁ :: ከአራት ዓመት በኋላ የማስተርስ ትምህርቴን ለመቀጠል ወደ አዲስ አበባ መጣሁ ::

"ሂድ! ሂድ!" እያለኝ ከስድስት ወራት በላይ እነ እማማ አመለ ሰፈር ሳልደርስ ቆየሁ:: ምን እንዳስፈራኝ ባላውቅም ውስጤ በፍርሃት ይታመስ ነበር:: አንድ ቀን ግን ወሰንኩ:: ታክሲ ይዤ ወደ ወሎ ሰፈር ሄድኩ:: ከታክሲ ስወርድ የገጠመኝ ነገር አስደንጋጭ ነበር:: የእነፋና ቤት ይቅርና ሰፈሩ ራሱ ምልክቱ ጠፍቷል:: ሰፈሩ የለም መንገድ ሆኗል - ቀለበት መንገድ ሆኗል - በረሀ ሆኗል:: ወገቤን ይዤ ቆምኩ፤ ግራ ገባኝ፤ እንደ አዲስ ፋና ናፈቀችኝ:: እማማ አመለን ማየት ፈለግኩ ! ሁሉም የሉም:: ተስፋ ቆርጬ ተመለስኩ::

ከብዙ ጊዜ በኋላ የማስተርስ ትምህርቴን አጠናቅቄ በምርቃቴ ማግስት ለምርቃት የተነሳሁትን ፎቶዬን ለመውሰድ ካዛንችስ ወዳለ አንድ ፎቶ ቤት ሄድኩ:: ሮዳስ የምትባል ልጅ አብራኝ ነበረች:: ሮዳስ ፍቅረኛዬ ናት:: ፍቅር ከጀመርን ዓመት አልፎናል:: እርሷም እንደኔው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ማስተርሷን ስትሰራ ነው የተገናኘነው:: ፎቶ ቤቱ እንደደረስን ፎቶ ያነሳንን ልጅ አገኘነው:: የምርቃት ኮሚቴ ሆኜ ስሰራ ፎቶ የሚያነሳው ልጅ ጋር በደንብ ተግባብተናል::

ፎቷችንን እስኪሰጠን ለእኔና ለሮዳስ ሻይ አስመጥቶልን ስለምርቃት ፎቷችን የባጥ የቆጡን እያወራልን ስንጠብቅ፣ ድንገት ፎቶ ቤቱ መስተዋት ላይ የተለጠፈ አንድ ሰላሳ በአርባ ሴንቲሜትር ስፋት ያለው ፎቶ ተመለከትኩ:: ምን አስፈንጥሮ እንዳስነሳኝ አላውቅም:: ወደ መስተዋቱ ተንደርድሬ ሄድኩና ቆምኩ - ፋና ! ራሷ ናት...የራሷ የፋና ፎቶ ነው::

የለበሰችው አጭር ቀሚስ ፍም የመሰለ ቀይ ታፋዋን አጋልጧታል - ቢሆንም ፋና ናት ! ዓይኖቿን ጨፍና ወደ ሰማይ አንጋጥጣለች:: ቀይ የከንፈር ቀለም የተቀቡ ከንፈሮቿ በመጠኑ ከፈት ብለዋል:: ፀጉሯ ባጭር ተቆርጦ ወርቃማ ቀለም ተቀብቷል:: ቢሆንም ፋና ራሷ ናት! አፍንጫዋ ተበስቶ ቀለበት ተንጠልጥሎበታል:: ጡቶቿ ደረቷ ላይ በሰፊው እስከ ሆዷ ድረስ ቅድ ባለው ቀሚሷ ምክንያት ግራና ቀኝ በግማሽ ብቅ ብለው ይታያሉ:: ራቁቷን ናት ማለት

ይቀላል፡፡ ተረበሸኩ፡፡ ጩህ...ጩህ አለኝ፡፡

ጓደኛዬን ሮዳስን ረስቻት ጉርድ ፎቶ በመቀስ እየቆራረጠ ከመደርደሪያው ኋላ ወደ ቆመው ፎቶ አንሺ ተመለስኩና ወደ ፋና ፎቶ በእጄ እየጠቆምኩ፣

"ይህችን ልጅ ታውቃታለህ?" ብዬ ጠየቅኩት፡፡

ለአመል ያህል ወዳመለከትኩት ፎቶ ዓይኑን ላከና በፍጥነት መለሰልኝ፣ "ከዚህ ቀጥሎ፣ ቀጥሎ ያለው ሶስተኛው ቤት ውስጥ ትሰራለች፡፡ ከአረብ አገር ነው የመጣችው፣ አዕምሮዋ ትንሽ ትንሽ ችግር አለበት፡፡ ተጠፍራ ነው የመጣችው፡፡ ደግሞ አረቦች ደፍረዋት የወለደቻት አንዲት ልጅ አለቻት" አለኝ፡፡

"ምንድን ነው ቤቱ ?ማለቴ የምትሰራበት..."

"ቡና ቤት" ብሎኝ ወደ ስራው ተመለሰ !

"እ...ና ቡና ቤቱ ውስጥ ምንድን ነው የምትሰራው?" አልኩት ባለማመን፡፡

ቀና ብሎ በመገረም ተመለከተኝና፣ "ሴት ልጅ ቡና ቤት ውስጥ ምን ልትሰራ ትችላለች አብርሽ ?" ብሎኝ ጥያቄዬን በጥያቄ መለሰልኝ፡፡ ቀስ ብዬ ስዞር ሮዳስ ጎኔ ቆማ ልጁ የተናገረውን ሁሉ ስታዳምጥ አገኘኋት፡፡ ፎቷችንን ተቀብለን ስንወጣ ሮዳስ እንደ ቀልድ እንዲህ አለችኝ፣

"ደግሞ ብለህ ብለህ የሴተኛ አዳሪ አድራሻ መጠየቅ ጀመርክልኝ ?" አልመለስኩላትም፡፡ ሮዳስ ዛሬ ካለችበት የትምህርት እና የኑሮ ደረጃ ላይ ቆመው ቁልቁል ወደ ፋና ከተመለከቱ፣ ፋና...ከሰሃራ በታች ናት፡፡

# 4 ትንሽ ወደግራ ዘምበል...

አባቴ ሲራመድ ትንሽ እንከስ ይላል። ያን ያህል እንኳን አይደለም። ወታደር ስለነበር ታፋው አካባቢ ጥይት ጨረፍ አድርጋው ነው። ('ለጡረታ ሰበብ ትሆን ዘንድ ከእግዜር የተተኮሰች ጥይት' ይላታል አባቴ ራሱ) !! አንድ አራት እርምጃዎቹ 'ኖርማል' ይሆኑና አምስተኛዋ ላይ ትንሽ ወደግራ ዘምበል ይላል - እንደ እኛ ታሪክ !! የራሳችን ፊደል፣ የራሳችን ቋንቋ፣ አድዋ፣ መቅድላ፣ 'ድርቅ' እንከስ ወደ ግራ !! ይሄው ነው !

ታዲያ አባቴን ጥምድ አድርጎ የያዘው የግራ እግሩን በፈንጅ ያጣ ወታደር ጎረቤት አለን ፣ "ለዚች በየአምስት እርምጃው ለምትከሰት እንከሻው 'የአካል ጉዳተኛ' ተብሎ ጡረታ ይበላል። ይሄ ለጿግሜ ከመስከረም እኩል ደመወዝ ከመክፈል አይተናነስም - አይ እች አገር ! አይ ታሪክ !" እያለ ያሽሙረዋል - በከራንቹ መሬት እየቆረቆረ...!!

የአባቴን እግር የጨረፈችው ጥይት ለአባቴ ግንባር የተተኮሰች መሆኗን ዘንግቶ። የተጫረ እግር ከተቆረጠ እግር እያወዳደረ በጉድለት ቁና የታሪክ ገለባውን ሊሰፍር ይዳዳዋል ። ጡረታን የጉዳት ዳረጎት አድርጎ የሚያስብ ከንቱ !! ሰው አንገቱን ተቆርጦ ጡረታ እየተቀበለ መኖር ቢችል ኖሮ፣ "ለአገራቸው ክብር" አንገታቸውን የተቆረጡቱ "ግራ እግር ምን አላት" ብለው በተቆረጠው ግራ እግሩ በሳቁበት ነበር ፤ "አንዱ ባንዱ ሲስቅ ጀምበሯ ጥልቅ" (በጨለማ መሳቅ የለመደ ህዝብ ስለጀምበር መጥለቅ ምን ገዶት። ለምን እንጦሮጦስ አትወርድም። ኮከቦችን ወላ ጨረቃዋን አስከትላ።)

ቀን ቀን ትሁት፣ የተከበረ፣ የተጣላ የሚያስታርቅ የመንደሩ ዋልታ ነው አባቴ ። ማታ... አቤት ቀንና ማታ በአባቴ ባህሪ ሲለኩ ያላቸው ልዩነት። ጧት የነበረው አባቴ ሌላ ክፍለ ዘመን፣ ማታ የሚከሰተው ደግሞ ሌላ ላይ የተፈጠረ ፤ ሁለት አባት ያለኝ እስኪመስለኝ !! አባቴ ማታ ማታ ከራሱና ከእነዛ ሁለት ሥዕሎች ጋር ይጣላል ።

ጠጭ ነው፡፡ በየቀኑ ይጠጣል፡፡ ሲጠጣ ቤተሰብ አይረብሽም፡፡ እናቱን አይናገርም፡፡ ቤታችን ግድግዳ ላይ የተለጠፉት ሁለት ሥዕሎች ጋር ነው ዱላ ቀረሽ ግብ ግብ የሚፈጥረው - በቃል !!

"አባትህ ስራው ምንድን ነው ?" ብባል፣ "አባቴ ስራው ምን እንደሆነ አላውቅም" ነው መልሴ፡፡ "አባትህ ስራው ምንድን ነው ?" ብባል፣ "አባቴ ስራው ምን እንደሆነ አላውቅም" ነው መልሴ፡፡ "አባትህ ስራው ምንድን ነው ?" ብባል፣ "አባቴ ስራው ምን እንደሆነ አላውቅም" ነው መልሴ፡፡ ማረያምን አላውቅም !! ትምህርት ቤትም እንደዚሁ ብዬ መልሼ ሁሉም ሳቁብኝ፡፡ እኔ ግን ለምን እንደሳቁ አልገባኝም !! የተማሪዎቹ እሺ ይሁን - ምድረ ኩታራ፡፡ ቲቸር ምን አሳቀው ? (ከሳቁ በፊት እንትቱ ነበር የምለው፡፡) የቲቸር ሳቅ ስላበሳጨኝ ሆነ ብዬ እንዲህ ስል ሳቁን ተረጎምኩት፣ "አባትህ ቢያጣ ቢያጣ መምህር መሆን ያቅተዋል ?" ማለቱ ነው፡፡" ባይሰማኝም እንጀቱ ራሱ፡፡ ይሄን አስቀያሚ መላጣ፣ ኮቱ የተዛነፈ ሂሳብ አስተማሪ ተውትና ስላባቴ ልንገራችሁ...(ሲጀመር ሂሳብ አስተማሪ ስለአባቴ ሥራ ምን አገባው - ደሞ ይስቃል እንዴ!)

ስለአባቴ ሥራ እንዴት ልበላችሁ? አባቴ አሁን ሹፌር ነው ተብሎ አንድ ፌርማታ ሳያልፍ ሪፖርት ጸሐፊ ይሆናል፣ "እሳቸው የሚጽፉት ማመልከቻ መሬት ጠብ አይልም" ተብሎ ባለጉዳይ ቤታችን ሲመጣ፣ አባቴ መጋዝና ሚርቴሎውን ይዞ ገና ድሮ አናፂ ሆኗል፡፡ እንግዲህ በክረምት ጣራችሁ አፍስሶ ወይ የእንጨት አጥራችሁ ወድቆ ትላንት ግንቦት ላይ አናፂ የነበረ አባቴን ሰኔ አንድ "ጠግንልን" ብላችሁ ብትመጡ አባቴ ከተከመረ የከሰል ጆንያ ኋላ ቆሞ 'የከሰል ነጋዴ' ሆኖ ታገኙታላችሁ ("ዱቤ ከልክል ነው" ከሚል ፅሁፍ ጋር)...እና አባቴ ሥራው ምንድን ነው ልበል ? ብዙ ሥራ ያለውና ምንም ብር የሌለው አባት !

ብር ከአንዱ ይበደራል፣ የተበደረውን ከሌላ ሰው ተበድሮ ይከፍላል፡፡ ለሌላው ሰው ደግሞ ከሌላ ሌላ ሰው ተበድሮ ይከፍላል፡፡ ሕፃን እንደነበርኩ ታዲያ ይሄ የአባቴ 'የመበደርና ብድር የመክፈል ሳይክል' መጨረሻ ያለው ስለማይመስለኝ አባቴ እስከዘላለሙ በብድር የሚከሰስ፣ የሚታሰር አይመስለኝም ነበር፡፡ ብድር ይከፍላል፡፡ እጁ ላይ ምንም ብር አይኖረውም፡፡ ብር ለምን ይጠቅማል ቢሉኝ፣ ብድር ለመክፈል፡፡ 'ደመወዝ ለምን ይጠቅማል?' ቢባል ብድር ለመክፈል፣ ታዲያ ለምንድነው ሰዎች 'በባንክ ብድር ቤታቸው ተሸጠ' የሚባለው? - እንደኔ አባት ብልህ ስላልሆኑ ነዋ !!

ሥዕሎቹ፣

1. አባቴ በመጠኑ ሲሰክር (ሞቅ ብቻ ሲለው) ፊት ለፊቱ ቆሞ "ሳተናው ደህና አመሸህ!" የሚላቸው የአፄ ቴዎድሮስ ሥዕል የሽጉጣቸውን አፈሙዝ አፋቸው ውስጥ አስገብተው መቅደላ ጫፍ ላይ ሬሳና ቁስለኛ ከስራቸው ተለሸልሾ የሚታይበት ሥዕል፣ በቀኝ በኩል ከዕቃ መደርደሪያዋ በላይ ግድግዳው ላይ ተለጥፎ ይገኛል፡፡ (አባቴ ከዚህኛው ስዕል ጋር የመረረ ጥል የለውም፣ አልፎ አልፎ ካልሆነ...፡፡)

2. አባቴ ስካሩ ከመደበኛው ስካር ከፍ ሲልና፣ ቀን ከገጠመው የሕይወት ስንክሳር ጌሾ ጋር ሲቀየጥ ደግሞ ከማይጋጩት ባላጋራ ጋር ይጋጫል፣ "...የጌታ እየሱስ ክርስቶስ" ምሥል ጋር!!

ቀይ መጎናፀፊያ ለብሶ፣ ረዥሩም ምርኩዙን በብብቱ ስር ይዞ፣ በር እያንኳኳ...በግራ እየሱስ ቀይ መጎናፀፊያ ለብሶ፣ ረዥሩም ምርኩዙን በብብቱ ስር ይዞ፣ በር እያንኳኳ...በግራ
በኩል!! አባቴ ከዚህ ሥዕል ጋር ይጣላል (ድፍረቱ አይገርምም ?)

***    ***    ***

አባቴ ገና በር ሲያንኳኳ እናቴ ስካሩ አንደኛ ደረጃው ይሁን ወይም ሁለተኛው ደረጃ ታውቀዋለች፤ እንዴት ታውቃለች ?' እግዜር ይወቅ !! እነዚህ እናቶች በየድራፍት ቤቱ ስለማይደስኩሩ እንጂ በየሬዲዮና በየቴሌቪዥኑ ስለማይቀባጥሩ እንጂ ስንት ጉድ ተዓምር አለ በውስጣቸው:: ስንት ጉድ፣ መላ...:: እንኳን ባላቸው በር ሲያንኳኳ ቀርቶ ዙፋን ላይ ቂብ ሊል ያቆበቆበ ባለተራ
ዓይነ ውሀውን አንብበው ከፉ ይሁን ደግ ያውቃሉ - ዘመን ምስከር ነው !!

ሁለተኛው ዓይነት ስካር ከሆነ እናቴ ተንደርድራ ከርስቶስ ሥዕል ፊት ትሄዳለች - በፈጣን አነጋገር፣ "ጌታ ሆይ አባከህ የተናገረውን ቢናገር አትቁጠርበት ይቅር በለው" ብላ የንስሃ ቀብድ ታስይዛለች ! (ሙሉውን አባቴ ራሱ ስካሩ ሲበርድለት ያወራርዳል !!) ከዛ በሩን ትከፍትለታለች...!!

ፊቱ ወዝቶ አይኑ በአስፈሪ ሁኔታ ጉሽርጥ መስሎ ይገባል:: "ሰላም አመሻችሁ!" የለ ምን የለ! "የአባትህ ጉዳይ እዛ ቤት ተደብቋል፣ በግራ በኩል ከአልጋው በላይ ታገኘዋለህ" ብለው የላኩት ይመስል ዝም ብሎ ይገባና በቀጥታ ወደግራ ታጥፎ ከአልጋው በላይ የተሰቀለው የከርስቶስ ስዕል ፊት ይቆማል ::

ፂሙን እያሻሸ ለረዥም ደቂቃዎች በዝምታ ሥዕሉ ጋር አፍጥጦ ይቆይና ድንገት! ..."አንከፍትም!!" ብሎ ይጮሃል:: እናቴ ሽምቅቅ ትላለች::

"ለስንቱ እንከፈት፣ ሲያንኳኩ ስንከፍት ገብተው እኛን ሲያስወጡን:: በጣታቸው ሲያንኳኩ 'ቤት ለእንግዳ' ብለን ስንከፍት በከንዳቸው ሲደቁሱን ከመከፈት ጋር ተጣልተናል ፤ አንከፍትም...!!"

እናቴ ወደ ጣራው ዓይኗን ልካ በለሆሳስ ታነበንባለች:: ለከርስቶስ "ቅድም ያልኩህን እንዳትረሳው እደራ!" የምትል ይመስለኛል:: አባቴ ይንጎማለላል:: ረዥም ነው ቁመቱ:: ብን ተደርጎ የተበጠረ ጥቁር ከርዳዳ ፀጉሩ ላይ ወደፊት አካባቢ ትንሽ ሽበት ጣል ያደረገበት :: የጨርቅ ሱሪው የተኩስ መስመር ቀጥ ማለት፣ "ሱሪውን ከለበሰው ጀምሮ ተቀምጦ አያውቅም እንዴ" የሚያስብል፣ በሚገባ የተወለወለ እሮጌ የወታደር ቦት ጫማ :: ይንጎማለላል ...

"አንከፍትም ! አድሜ ልኬን በርህን ሳንኳኳ የከረቸምከብኝ፣ እንዴት ነው የኔን ልብ ዛሬ የምከፍትልህ:: የገቡትንም ማስወጫ አጥተናል እንኳን አዲስ ለሚያንኳኳ ልንከፍት - አንከፍትም!!" ጉዱ ፈላ" እላለሁ:: ይሄ ሥዕል ከድሮ ጀምሮ ግድግዳችን ላይ ስለተለጠፈ ነው መሰለኝ ከርስቶስ ከእኛ ቤት ሌላ መሄጃ ያለው አይመስለኝም ነበር:: እናቴና ከርስቶስ የአባቴን ባህሪ ችለው

የኖሩት ሌላ መሄጃ ስለሌላቸው ይመስለኛ ነበር፡፡እኔ፣ ክርስቶስና እናቴ የአባቴን ባህሪ ችለን የተቀመጥነው ሌላ መሄጃ ስለሌለን ይመስለኛ ነበር...

"እንከፍትልሀም...ይህቺ ሚስኪን (ወደናቴ እየጠቆመ) ለስንቱ ሃብታም፣ ለስንቱ ጀግና፣ ለስንቱ ባለ ሥልጣን የከረቸመችውን ልቧን ለኔ ከፈተች፡፡ ምን ተጠቀመች ? ምንም !! እድሜ ልኳን ጡረታ የወጣ ወታደር ባሏ ስከሮ ሲመጣ በር ከፋች ሆና ቀረች..." (ስለሌላ ባል እንጂ ስለራሱ የሚያወራ አይመስልም፡፡) "እሷን ተዋት...እቺ አገር ራሷ...እቺ እጇን ወደአንተ ትዘረጋለች የተባለችው... ሃሃሃ ...እች ኢትዮጵያ ...ጓደኞቼን ዋጥ ስልቅጥ ያደረገችው አገር ራሷ...ለንጉሥ ልቧን ስትከፍት፣ ለወታደር ልቧን ስትከፍት፣ ለወንበዴ ልቧን ስትከፍት፣ ለሶሻሊዝም፣ ለምናምኒዝም ልቧን ስትከፍት - ይሄው መከፈት መዘጋት የሰለቸው በሯ ተገንጥሎ ከፍቷን ቀረች፡፡እናስ ? ምናችን ጅል ነው የምንከፍትልህ ?...እንከፍትም !! እንከፍትም !! በከፈትን ቁጥር እየገባ የታጨቀብንን ጣጣ ባስወጣህልን ይልቅ ! ...ላንተም አይመችህ...ውስጣችን ነድዷል፣ ከስሏል - የተቃጠለ ቤት ውስጥ ለመኖር ይሄን ያህል ስታንኳኳ መኖር...ኤዲያ" እናቴ አንባዋ ጠብ ሲል ይታየኛል፡፡

ልቤ ይታፈናል፡፡ ልብ ድካም የሚባለው ይሄ ይሆን ? ቤታችን ይታፈናል፡፡ በጣም ብዙ መላዕክት ቤታችን ውስጥ ታጭቀው፣ "እረ ጌታ ሆይ ይሄ ሰውዬ አበዛው፣ ፍቀድልንና ወደዛ በሚጭቀን ሲኦል እንወርውረው..." እያሉ እየሱስን የሚያስፈቅዱ ይመስለኛል፡፡

"እስቲ ተዉት...እሱ ያለፈውን መከራ ማን አለፈ ? ...የዚህን ሚስኪን ልጄን ቀንበር ማን ተሸከመ? እስከመጨረሻው አለምነዋለሁ...!" የሚላቸው ይመስለኛል በሩን ማንኳኳቱን ሳያቋርጥ፣ ክርስቶስ የኔ ልብ አዋቂ ! አባቴ እያነሰ ክርስቶስ እየገዘፈ ይሄድብኛል - አሁን ደግሞ ለአባቴ እሰጋለሁ፡፡

ጎምለል ጎምለል..."እንከፍትም !! እናውቅም እንዴ...ወላ መስኮት ወላ በሩ በተዘጋ ቤት ስተት ብለህ ገብተህ 'ሰላም ለእናንተ' ስትል? አሁን ምን ያዘህ?...ግባ...ይሄው በግድግዳው ግባ፡፡ መቼም ዓይናችን እያየ አንከፍትልህም..." እያጉተመተመ ልብሱን ያወላልቃል፡፡ መጀመሪያ ኮቱን - ገበሩ ተቀዳዷል፡፡ እያጣጠፈ ያጉተመትማል - "ወይ መከፈት..." ሱሪውን በሥርዓት አልጋው ላይ ዘርግቶ በእጁ እየተኮሰ ያጣጥፋል፡፡ ቢሰክርም ባይሰክርም ልብሱን በመስመሩ ማጠፍና በሥርዓት ማስቀመጥ አይረሳም፡፡ ሊተኛ ሲል ያየኛል፡፡ ልክ የአልጋ ልብሱን ገለብ ሲያደርግ ኩርምት ብዬ እናቴ ስር...፡፡ "አይዞህ አንበሳዬ...ምነው ከኔ ከምትፈጠር በቀረብህ... የማይረባ አባት ለአንድ ልጁ እንኳን የማይሆን - ወይ አባት - አላየንም አባት - እንደለማዳ ውሻ ስምህን ተከትሎ ከሚጮህ ስሜ ሌላ ምን አወርስሃለሁ - ቤሳቤስቲን..." እየተናገረ አልጋ ልብሱ ውስጥ ገብቷል፡፡ በብርድ ልብሱ የታፈነ እንቅልፍ የተጫጫነው ድምፁ ያጉተመትማል፣ '...ከንቱ...ለራሴ ከንቱ ሆኜ የሰው ሰው ከንቱ አድርጌያት ቀረሁ...ግራ ገብቶኝ ግራ...' ረዥም ዝምታ፣ የተኛ እስኪመስለን ፡፡ ድንገት፣ "አለሜ...እራት በልታችኋል..." ይላታል እናቴን፡፡

"አዎ" ወይም "አልበላንም" አትልም፡፡ ሁልጊዜ መልሷ ይገርመኛል፣

"ቆንጆ ወጥ ሰርቻለሁ ፤ ትንሽ ልስጥህ እስቲ..." ትለዋለች፡፡ ገና ቅድም ተነስታ ጓዳው በር ላይ ደርሳለች፣

"እ...ይ..." ይላል ስልል ባለ ድምፅ፡፡ አንዳንዴ "አይ..." ብሏትም ታቀርብለታለች፣ ተነስቶ ይበላል፣ አንዳንዴ "አይ..." ካለ ትመለሳለች፡፡ በሁለቱ 'አይ'ዎች መሃል ያለውን ልዩነት ብዙ ጊዜ ለማጥናት ሞክርኩ፡፡ በድምፅ ርዝመት፣ በቅላፄ ተመሳሳይ ናቸው፡፡ እናቴ ግን በሁለቱ 'አይ'ዎች መሃል የአባቴን መሻት በቀላሉ ታውቃለች፣ አለመሻቱንም፡፡ (አለመሻቱ እንኳን አይ ካለ አይ ነው ፡፡ ግን እንዴት አይ ያለ ሰው አይ ያለበትን ጉዳይ እንደፈለገው ማወቅ ቻለች ??????)

አማርኛ አስተማሪያችን "ልጆች ቋንቋን ከቤተሰብ ከማኅበረሰብ ይማራሉ" አሉኝ እንጂ ቋንቋን የምንማረው ከሕይወት፣ ለዛውም መተሳሰብ፣ መከባበረ እና መፈቃቀር ካለበት የሕይወት ልምዳችን ብቻ ነው፡፡ አማርኛ አስተማሪያችን ራሳቸው፣ አባባ "አይ" ቢል እራት "አቅርቢልኝ" ማለት መሆኑን በጭራሽ አያውቁም፡፡ ከማህበረሰቡ ይሄን አልተማሩማ !! ስሜትና ስዋሰው ለየቅል ናቸው !!

ጧት ከእንቅልፌ ስነቃ ታዲያ ብቻዬን ነኝ፡፡ እናትና አባቴ ቤተ-ክርስቲያን ሄደዋል፡፡ የክርስቶስ ሥዕል ግን አሁንም አለ፡፡ ቆይ አባቴ ከሌለ ማን እንዲከፍትለት ነው የሚያንኳኳው ? በብርድ ልብሴ ተጠቅልዬ ሥዕሉን እያየሁ አስባለሁ፣ "አባታችሁን ታዘዙ፣ ቤተሰቦቻችሁ የማይወዱትን በመሥራት አታሳዝኗቸው" ይሉን የለ የሰንበት አስተማሪያችን ? ስለዚህ...

"አልከፍትም !!" እላለሁ ቀስ ብዬ...

# አገዛላታለሁ . . . !! 5

ቆንጆ ማለት ለዓይን የሚማርክ፣ ሊጆሮ የሚጥም፣ የሚያምር፣ የሚያስደስት፣ የሚያማልል፣ ሰው፣ እንስሳ፣ ሳር፣ ቅጠል፣ አየር፣ ውሃ፣ ቃል፣ ሁኔታ፣ ድርጊት ሌላም መዓት ትርጉም ይኖረዋል:: አሻሚ ነው ቃሉ:: 'ውብ' የሚለው ቃል ግን አያሻማም አያደናግርም፣ "ውብ" ማለት "እናቴ" ማለት ናት ! የእኔ እማማ ብቻ !!

እዎ እናቴ ውብ ናት !! በችግር የማይፈታ ውበት:: ማንም በአድናቆት ቃል በእንቶፈንቶ ድለላ ውሉን እጁ አስገብቶ የማይተረትረው ነጭ ቱባ ናት እማማ ፤ ፈገግ ስትል ከጥርሶቿ ድል ማድረግ በአካባቢው ይነዛል:: እንደ እናቴ ፈገግታ ልብ የሚሰነጥቅ ሳቅ አላየሁም፤ የእናቴ ፈገግታ ብርታቴ ነው:: ሰውነቴ በፈገግታዋ ይታደሳል:: የተፈጥሮ ፍልውሃ ነው ፈገግታዋ !!

ሕይወት ወገቧን አስራ ልታስለቅሳት ድንጋይ ስትፈነቅል እናቴ...እማምዬ...የኔ ፀሐይ...በአንዲት የአሽሙር ፈገግታ ትደቁሳታለች ፤ ሕይወት የጨለማ አረሟን በቤታችን ላይ ስትዘራ እናቴ በፈገግታዋ ትመነጋግለውና የደስታ እና የሐሴት አዝመራ ቤታችን ይዘናፈላል::እዛ ማሳ ውስጥ እኔ እቦርቃለሁ::አውቆም ይሁን ሳያውቅ አባቴ ቤታችንን የምድር ዋልታ ላይ በበረዶ ገነባው፤ እናቴ በፈገግታ ገመድ ጎትታ መሃል አዲስ አበባ፣ አራት ኪሎ፣ ፀሐይ የሞላበት አመጣችው ቤቱን ከነግቢው ከነዛፉ !! እንደዛ ነው የሚሰማኝ::

አባቴ በውትድርና ኤርትራ ሄደ:: "እነከሌ አገር ሊገነጥሉ፣ መሬት ሊሸርፉ ነውና ሄደህ ልክ አግባቸው!" በሚል ትዕዛዝ ከእኔ ከአንድ ልጁና ከሚወዳት ሚስቱ ተነጥሎ ሄደ :: "...እቤት ቁመና ! እቤት የትጥቅ ማማር !" እያለ ጎረቤቱ ሸኘው:: አምሮ ሊገድል፣ አምሮ ሊሞት አባቴ:: ሕፃን ነበርኩ፤ ብዥ ያለ ነው ትዝታዬ:: አባቴ ሄደ፤ (ዘመት ይሉታል):: ስልክ የለም፤ ደብዳቤ የለም፤ ሄደና ጠፋ::

እናቴ ታዲያ በፍፁም ንፅህና ስድስት ዓመት ጠበቀችው:: ያውም በደጃችን፣ በእናቴ ውበት

ሙቶ ጀኔራል እየሸለለ፣ ሺ ካድሬ እየቋመጠ፣ ሚሊዮን አብዮት ጠባቂ ምራቁን እየዋጠ !! "ንፅህናዋን በምን አወቅከ ?" ስድስት ዓመት ሙሉ ማታ ማታ አንዲት ቀን ሳታቋርጥ ፎቶው ፊት ተንበርክካ ምን እያለች ትፀልይ እንደነበር እናንተ ታውቃላችሁ ? የአባቴን ፎቶ አቧራ ዝር እንዳይልበት በቀን ስንት ጊዜ ትወለውለው እንደነበርስ...? ከቤታችን ዕቃዎች ውድ የተባለው መደርደሪያ ላይ ምን ይቀመጥ እንደነበርስ ? የአባቴ ፎቶ !! በዛ ናፍቆት በረበበበት፣ ምስኪን እናትና ልጅ ምዕመን በሆኑበት፣ የብቸኝነት ቤተ መቅደስ ውስጥ የአባቴ ፎቶ ፅላት ነበር::

አባቴ ፎቶ ጎን ተሳስቼ ደብተሬን ባስቀምጥ ሳታስደነግጠኝ ቀስ ብላ ታነሳዋለች :: ቤት ለማዘጋጀት እንዳይመስላችሁ፣ አባቴ ፎቶ አጠገብ ምንም እንዳይቀመጥ እንጂ !! እማማ የቃል ኪዳን ቀለበቷን ሸጣ ምን ገዛች...? ለኔ ቆንጆ ጫማና ልብስ ፣ ምድረ የትምህርት ቤት ማቲ የቀናበት የደብተር መያዣ ቦርሳ ፣ ለአባቴ ፎቶ ወርቃማ የብረት ከፈፍ ያለው ባለመስታዋት የፎቶ ማስቀመጫ፣ በተረፈችው የቃል ኪዳን ቀለበቷን የምትመስል 'አርቴፊሻል' ቀለበት :: በእንቁ ልብና በአርቴፊሻል ቀለበት ቃል ኪዳኗን አጠረች፣ከእኔ በስተቀር ይሄንን ማንም አያውቅም:: ለራሷስ ምን ገዛች?...ምንም !! እች ናት እናቴ!!

ስድስት ዓመት አባቴን ጠበቀችው::ይሄ ሊመጣ ይችላል ተብሎ እዛም እዚህም እየተባለ የሚጠበቀው ዓይነት ጥበቃ ሳይሆን 'ሙቼ ሄደና' ብሎ ከችች የሚሉት አይነት የመንፈስ አብሮነት፣ በሌሉበት ማክበር !! ...ይሄ የመጀመሪያው ዓመት ላይ "ሄደብኝ የኔ ጌታ የልቤ ቁራሽ የደሜ ጭላፊ..." እያሉ ጎረቤት እንዲያባብል ድራማ መስራት፣ ዓመት በጨመረ ቁጥር 'አሁን ተፅናናች ሰው መቅረብ ጀመረች' የሚባለው አይነት መጠበቅ ሳይሆን፣ ትላንትም ዛሬም ዓመታት ጉልበቱን በማይሰልቡት ጥልቅ መሻት ጠበቀችው:: ይህች ናት እናቴ!!

ስለ ኤርትራ በተወራ ቁጥር ኪሎ ስጋ ከአካሏ እየተገነጠለ ጠበቀች :: "ከኤርትራ የመጣ ሰው በኮተቤ አለፈ" ቢሏት ነጠላዋን አንጠልጥላ ኮተቤ ትገኛለች::" አንዲት ኤርትራዊት ተፈናቃይ አቃቂ ኪዩስክ ከፈተች" ቢባል ከአራት ኪሎ እየተመላለሰች የስሙኒ ሻይ ቅጠል ለመግዛት ደንበኛ የምትሆን ሴት ካለች እናቴ ብቻ ነበረች:: እች ናት እማማ!!

እርጋታዋ የእኔ እማማ በ"እልፍ ሲሉ እልፍ ይገኛል" ተረት እልፍኞቻቸው ውስጥ ተላላፊ እንደሚያበዙ ሴቶች አይደለችም ፣ ማንም የቃል ኪዳን መስመሯን አያልፍም፣ አገር ያውቃል፣ ቤታችን ቤተ መቅደስ ነው:: የፍቅር ፅላት በቅዱስ ቅዱሳን እማማ ልብ ውስጥ አለ:: እርጋታዋ ታማኝነቷን ይነግረኛል:: ዓይኗ ከአባቴ ፎቶ ላይ ከተነቀለ ቀጥሎ ማረፊያው እኔ ላይ ነው:: ጆሮዋ ወደ ውጭ አይቀሰርም:: የኔን አርቲ ቡርቲ ወሬ እንደወንጌል በጥሞና መስማት የነፍሷ እርካታ ነው:: አባባ መጽሐፍ ቅዱስ፣ እኔ ዮሐንስ ራዕይዋ...ታነበኛለች፣ ስባት ቀንድ፣ አስራ ስድስት ምላስ፣ ምንም ጆሮ የሌላቸው ልዩ ፍጥረቶች መሐል እናቴ ጆሮ ብቻ ሆና ትሰማኛለች...!!

ጥቁር ፀጉሯ ሲዘናፈል፣ እንደማር የለሰለሰ ቆዳዋ አላፊ አግዳሚ ሲጠራ፣ ረጋ ባለ እርምጃ እንደ ደመና ስትንሳፈፍ፣ "ፊዛዛ ውበቷን አቀለጠችው" ይሏታል:: "ጎታታ...እንደ ኤሊ ስትንቀረፈፍ

አድማዋን ፈጀች" ይሏታል፡፡ በሌጣ ልባቸው ሮጠው ምናምንቴ ስለቃረሙ የፈጠኑ የመሰላቸው የመንደራችን ከንቱ ሐሜተኞች፡፡ የፍቅር መስቀል ተሸከማ ዳገት የምትወጣ እናቴን ኤሊ ይሏታል፤ እፍ አውጥተው ኤሊ ይሏታል፡፡ የድንጋይ ልባሷ እንደነሱ ቀሚስ የትም ለማንም አለመገለቡ እየበገናቸው፤ ተኳኩለው የሚጠብቋቸው ወታደር ውሽሞቻቸው ያልተኳኳለች እናቴን እያዩ "ማናት ይህች ቆንጆ ?" ሲሏቸው እየበሸቁ...፡፡

እማምዬ ስድስት ዓመት ጠበቀችው አባቴን፡፡ "ይኼኔ ባሏ ከአስመራ ቆንጆዎች ጋር አሸሼ ገዳሜ እያለ ነው፤ እሷ እዚህ ጉልበቷን አቅፋ ትጠራሞታለች" እያሏት ጎረቤቶቻችን፤ አስመራ አድረው ቢት አዲስ አበባ የገቡ ይመስል፡፡ "ለታመነልህ ታመን" የቆሸሸ ዲስኩራቸው "በአልታመኑልንም" ሰበብ ባሎቻቸውን እንዲከዱ፤ ፍቅረኞቻቸውን እንዲቀጥፉ መንገድ እየጠረገላቸው፤ ለውስጣቸው ግልሙትና ጥቅስ እየሆነላቸው፤ "የአስመራን ግልሙትና በአዲስ አበባ ግልሙትና መበቀል ፅድቅ ነው" የተባለ ይመስል እማምዬን "ባልሽ ወንድ ነው አትመኚው" ይሏታል፡፡

አንድ ማለዳ በራችን ተንኳኳ፡፡ እማማ ከፈተች፡፡ ጎረቤቶቻችን አንድ የተጎሳቆለ ወታደር አስከትለው መጡና "ባልሽ ሞቷል" አሏት ፡፡ "በዚህ ወርዶ–በዚያ ሂዶ፤ መድፍ ተኩሶ፤ ታንክ ማርኮ፤ በጀግንነት ሞተ !" አሏት፡፡ ዝም ብላ ሰማቻቸው፡፡ "ሰው ቀጥ ብሎ የማያይ ጨዋ፤ ለትዳሩ ታማኝ፤ ወታደሩ ሁሉ እዛና እዚህ ሲል ባልሽ ግን የአንቺን ፎቶ ከደረት ኪሱ ሳይለይ በየበረሃው ለአገሩ ሲፋለም ኖሮ ሞተ" አሏት፡፡ ዝም ብላ ሰማቻቸው፡፡

አባቴ ሲሞት "ከጎኑ ነበርኩ" ያለው ጎስቋላ ወታደር ከአባቴ ሬሳ ኪስ ውስጥ አገኘሁት ያለውን ፎቶ ሰጣት፡፡ እናቴና አባቴ ጎን ለጎን ሆነው የተነሱት ጉርድ ፎቶ ግራፍ ነበር፡፡ ልክ መሀላቸው ላይ በጥይት የተቦደሰ ፎቶ እማማ እጅ ላይ እንዳለ በትከሻዋ ተንጠራርቼ ፎቶውን አየሁት፡፡ እን...ዴ ! በመድፍ ጥይት ነው እንዴ ፎቶውን የበሱት? እና እንዴት አንዲት ጥይት በቤተሰብ መካከል ይሄን የሚያህል በደም ነጠብጣብም የተከበበ ሽንቁር ትፈጥራለች? ገረመኝ፡፡

"ባለቤትሽ ደረቱ ኪስ ነበር ፎቶውን የያዘው፡፡ ከጠላት የተተኮሰ ጥይት ፎቶ ባስቀመጠበት ኪሱ በኩል ደረቱን መታችው" አለ ድምፁ የሰለለው ወታደር፡፡ እማማ ፎቶውን በትኩረት አየችው፤ ረዥዥዥም ሰዓት ዝም ብላ አየችው፤ አላለቀሰችም፡፡ ፊቷም ላይ ምንም ለውጥ አልታየም፡፡ ከፎቶው ይልቅ ሽንቁሩን የምታይ መሰለኝ፡፡ እንዴ በረዥሙ ተነፈሰችና ፊት ለፊት መደርደሪያው ላይ የተቀመጠውን የአባባን ፎቶ ተመለከተች ፡፡

አሁን ውሻ ሞት በከፈተው ቀዳዳ ጅብ ወንዶች ዘው ሊሉ አሰፈሰፉ፡፡"አይዞሽ ሰው መቼስ ዘላለም አይኖር ምናምን..." ብለው በማስተዛዘን ስም ወደ ቤተ መቅደሳችን ዘው ሊሉ፡፡ እናቴ "ማንም ለቀሶ እንዳይደርሰኝ" አለች፡፡ መንደሩ "ለየላት አበደች..." ብሎ አወራ፡፡

እማማ የእኔ መልአክ እኔንም ግራ አጋባችኝ ፡፡ አባቴ ሞቷል ወይስ አልሞተም ? ቢሞትም እማማ "አልሞተም" ካለች አልሞተም፡፡

ነበር:: ሬጋ ብላ ቁርስ ሰራችልኝ፤ የሚጣፍጥ ጨጨብሳ፤ ቀኑ የአባባ መርዶ የመጣበት ሰኞ ነበር:: ሬጋ ብላ ቁርስ ሰራችልኝ፤ የሚጣፍጥ ጨጨብሳ፤

ቀኑ የአባባ መርዶ የመጣበት ሰኞ ነበር:: ሬጋ ብላ ቁርስ ሰራችልኝ፤ የሚጣፍጥ ጨጨብሳ፤ ስኳሩ በዛ ካለ ሻይ ጋር :: እሷ አልበላችም::

ቀኑ የአባባ መርዶ የመጣበት ሰኞ ነበር::

ስኳሩ በዛ ካለ ሻይ ጋር :: እሷ አልበላችም:: ዓይን ዓይኔን እያየችኝ ጥርግ በእጇ የያዘቻትን የሻይ ማንኪያ እየነቀነቀች በጥልቀት ታየኛለች:: ዓይን ዓይኔን እያየችኝ ጥርግ አድርጌ በላሁ::

ትንጨዉን ስማኝ ወደ ትምህርት ቤት ሸኘችኝ:: ትንጨዉን ነው ያልኩት ? በልምድ ብዙ ወላጆች "የልጆቻቸውን ትንጭ ይስማሉ" እንላለን እንጂ እንደ እኔ እናት ከሆነ ግን ወላጆች የልጆቻቸውን ነፍስ ነው የሚስሙት :: አዎ እማምዬ ነፍሴን ስማ ነው የምትሸኘኝ!! ብዙ ከሄድኩ በኋላ ወደ ቤታችን ዞር ስል አረንጓዴ ቢጃማዋን ለብሳ የበሩን ጣውላ ተደግፋ ቆማ እያየችኝ ነበር፤ የደከማት ትመስላለች:: እማማን እንዲህ ከሩቁ ሳያት "ተመለስ ተመለስ... እቅፍ አድርጋት ከጎኗ አትለይ..." ይለኛል:: ሁለት ሰው እሆናለሁ፤ እግሬ ወደፊት እየሄደ ልቤ ወደ እማማ ወደኋላ ይሮጣል ::

ዓይኖቿ ብርታቶቼ ናቸው:: ከኋላዬ ስትቆም እልፍ አእላፍ መላዕክት ከነሰይፋቸው፤ ከነአሳት ሰረገላቸው እኔን ሊጠብቁ የቆሙ ይመስለኛል:: በምድር ላይ ያለ የጦር ሰራዊት ከነመሳሪያው ያጀበኝ... እናትዬ ከኋላዬ ስትቆም ሰማይ ይቀርበኛል፤ ደመና ባጭር የተቆረጠ ፀጉሬን ሲዳስሰኝ ይሰማኛል፤ የእግዜር እግር ስር የቆምኩ ይመስለኛል:: የምረግጠው ምድር በእግሮቼ ብርታት የሚናጥ፣ ድንጋዮቹ የሚፈነቃቀሉ ይመስለኛል:: የእማማን የዕይታ ጥሩር ከለበስኩ ማንንም አልፈራም ::ተራሮች ምንድናቸው? በእግሬ እንደማንከባልለው የጨርቅ ኳስ ናቸዋ !! ጨጨብሳ ባልበላም በጠረኗ ሺ ዓመት እኖራለሁ፤ በፈገግታዋ ዘላለም!!

እማምዬ የፍቅር ጥግ፣ የእናትነት አልፋና ኦሜጋዬ:: እናንተ "ሴት እናት ናት! ሴት እህት ናት!" የምትሉ 'በደፈናው ኃይማኖተኛ ሁሉ መነኩሴ ነው' እያላችሁ ነውና ይቅር ይበላችሁ፤ ሴትነት እናትነት አይደለም:: "ሴት ከውስጧ የወጣ ገዳም ውስጥ ስትመንን እናት ትሆናለች" ሴት..."ልጅ" የሚባል መስቀል ተሸክማ የሕይወትን ቀራንዮ ስትወጣ 'እናት' ትባላለች ፤ ሴት ልጅ የራሷን ዘመን ይቅርብኝ ብላ የልጇቿ የዘመን መስቀል ላይ በፍቅር ስትቸነከር ወደ እናትነት ከፍታ ታርጋለች::

እማማን ዞሬ አየኋት:: የምትወደው ባሏን መርዶ ቅድም የሰማች ሴት በር ላይ ቆማለች፤ አይገርምም ? እናት የላትም፤...አባት የላትም፤...ዘመድ የላትም፤ እኔ ብቻ ነኝ ያለኋት:: የማላውቀው ስሜት ወረረኝ:: በአንድ ጊዜ ጀግናም ፈሪም ሆንኩ - አኩል! "ማንም የላት" እና "እኔ አለሁላት" የሚሉ ኃሳቦች ተጋጨብኝ::

ትምህርት ቤቴ እስከምደርስ እንባዬ ጉንጮቼ ላይ እየፈሰሰ እንዲህ እያልኩ ለብቻዬ አነበንብ ነበር...

"ሳድግ ለእማማ አዲስ አበባ ሱቆች ውስጥ ያሉትን ቀሚሶች ሁሉ እገዛላታለሁ:: ፒያሳ ወርቅ

ቤቶች ውስጥ የተደረደሩትን ያልተደረደሩትንም የወርቅ ቀለበቶች፣ ሃብሎች፣ ጉትቻዎች ...ሁሉንም ለእማምዬ አገዛላታለሁ:: ለእናትዬ ትልቅ ቤት አገዛላታለሁ:: ትልቅ ግቢ አገዛላታለሁ...::

ባለ ሚሊዮን ሮቅ፣ ጫፉ ጨረቃን የሚነካ ሕንፃ አገዛላታለሁ:: በመጨረሻው መስኮት ብቅ ብላ የአባቴን ፎቶ ከነ ወርቃማ 'ፍሬሙ' ጨረቃ ላይ ታስቀምጠዋለች:: ማንም እንዳይደርስበት !! ሳድግ ለእማምዬ ስፈራችንን አራት ኪሎን እንዳለ አገዛላታለሁ:: ከነሐውልቱ፣ ከነዩኒቨርስቲው፣ ከነቤተመንግስቱ...!!

ሳድግ ለእማማ፣ ለእኔ ደግ፣ ለእኔ ሩህሩህ አዲስ አበባን አገዛላታለሁ:: ሳድግ...ለኔ ትሁት፣ ለኔ ቃልኪዳን አከባሪ ኢትዮጵያን አገዛላታለሁ !! ከነሕዝቡ፣ ከነኃይማኖቱ፣ ከነቤተ ክርስቲያኑ፣ ከነ መስጊዱ አገዛላታለሁ...::

ሳድግ ኢትዮጵያን...ከነተራራው፣ ከነራስ ዳሽኑ፣ ከነሸለቆው፣ ከነሜካው፣ ከነዋልያና ጭላዳው፣ ከነአዋሹ፣ ከነጫሜም አና አብያታው፣ ከነሶፍውመሩ፣ ከነላሊበላው፣ ከነፋሲለደሱ፣ ከነጣናው፣ ከነአባዩ፣ ከነአክሱሙ... አ ገ ዛ ላ ታ ለ ሁ!!

አዎ አገዛላታለሁ !! "አልፈልግም የኔ አንቦቀቅላ ይሄ ሁሉ ምን ያደርግልኛል ?" ብትልም አልሰማትም፣ አገዛላታለሁ...!!!

ሳድግ...ትልቁ የልቧ ስባሪ፣ የነፍሷ ቀንዲል፣ የፍቅሯ በር፣ የእኔም አለኝታ እንደቀልድ የወደቀባትን ምድር...

ኤ

ር

ት

ራ

ን

አገዛላታለሁ ! ለ እ ማ ም ዬ !!

# 6 የፍርምባ ጦርነት

በንቃት ድንበር እየጠበቅኩ ነው ፤ ጠላት ፊት ለፊቴ አፍጥጧል። በማንኛውም ሰዓት ወደ እኔ ሊንደረደር ይችላል። በመጠኑ ያደፈች ጅንስ ቁምጣዬን ከጉርድ ቀይ ካኒቴራ ጋር ለብሼ ነጠላ ጫማዬ ከእግሬ ላይ ትበር ይመስል በእግሮቼ ጣቶች በመንከስ ከቤታችን በር ላይ ነው ያለሁት፤ በእጄ ከአቅሜ በላይ የሆነ ብትር ይዣለሁ...የአያቴ የተሰበረ መቋሚያ ነው...መቋሚያውም የተሰበረው እዚሁ በዓይነ ቁራኛ የምጠብቀው ጠላት ጀርባ ላይ ነበር ። አባቶቻችን ያወረሱንን ጠላት  አያቶቻችን ባወረሱን ሰባራ መቋሚያ እየተከላከልሁ ነው።

ነገ በዓል ነው። ቤታችን ትንሽ ጠቦት ታርዶ ቤቱ ስጋ ስጋ ይሸታል። እናቴ ቤቱን እና ስጋውን እንድጠብቅ ጥብቅ ትዕዛዝ ሰጥታኝ ገበያ ሄዳለች። በዋናነት የተሰጠኝ ተልዕኮ፣

1. ዶሮዎች የተሰጣውን የሽሮ ክክ እንዳይበትኑ

2. ሌባ ወደቤታችን እንዳይገባ

3ኛው እና ዋናው..."ገንባው እዚሀች ግድም ድርሽ እንዳይል..." ነው። (እዚሀች ግድም ድርሽ እንዳይል ? ማን ? ገንባው !!)

ዶሮዎች ስጡ አካባቢ መለቃቀም ይችላሉ። ስጡን መብላትም ሆነ መበተን ግን የለባቸውም፤... ሌባ በአጥራችን ጥግ መሄድ ይችላል፣ "ደህና አደራችሁ" ብሎም ማለፍ አይከለከልም። ሰላምታ የእግዜር ነው ትላለች እናቴ...በዕርግጥ ሲደጋግሙባት 'ሦስት ጊዜ እንዴት አደራችሁ አንዱ ለነገር ነው' ትልና የእግዜር ሰላምታ ሲደጋገም ባለቤትነቱ የሰይጣን ሊሆን እንደሚችል  በተዘዋዋሪ ትናገራለች። እና ሌባው እስካልደጋገመ ድረስ ሰላም ብሎ ማለፍ ይችላል። ...ገንባው ግን... እዚሀች ግድም ድርሽ ማለት የለበትም ። ወላ ሰላም ማለት ሁሉ አይችልም። ሰላምታውን ደገመም አልደገመም ፤ ቢቃ የበላይ ትዕዛዝ ነው !!

ገንባው በመንደራችን የሚኖር ባለቤት የሌለው ትልቅ ድመት ነው ። የበግ ግልገል የሚያክል ገንባው በመንደራችን የሚኖር ባለቤት የሌለው ትልቅ ድመት ነው ። የበግ ግልገል የሚያክል ዥጉርጉር ድመት ! እኔ ከተቀመጥኩበት አንድ አስራ አምስት ሜትር ራቅ ብሎ ከኋላው ሽብረክ በማለት ሁለት የፊት እግሮቹን ቀጥ አድርጎና ደረቱን ነፍቶ ጉርድ ፎቶ ሊነሳ ፎቶ አንሽ ፊት የተቀመጠ ጎረምሳ መስሎ...ቁሟል ።

ተራ ድመት እንዳይመስላችሁ...በሰፈራችን ውስጥ ያልገለበጠው ድስት፣ ያልከፈተው መሶብ፣ የመንጠቅ ሙከራ ያላደረገበት የስጋ ዘር የለም። መንደራችን ውስጥ ዶሮም ይሁን በግ ሲታረድ ገንባውን ጠባቂ ቃፊር ማቆም ቸል የማይባል ጉዳይ ነው። "ገንባው ቢመቸው ቆሞ ከሚሄድ በግ ሳንባ ይመነትፋል" ይሉታል...ምኝ ሰፈርተኞች...!! ታሪክ የሚተነፍሱበትን፣ የተዓማኝነት ሳንባቸውን በቁማቸው እንደመነተፋቸው ማን በነገራቸው።

ገንባው ግዙፍ ቢሆንም የተጎሳቆለና በእድሜ የገፋ ድመት ነው። ትንሽ ያነክሳል። በዛ ላይ ዓንድ አይን የለውም። ጅራቱም ቆራጣ ነው። ሲጮኽ ድምፁ ያስፈራራል። እማማ ብርዘገን ለፋሲካ የገነጣጠሏትን ዶሮ ላጥ አድርጎባቸው ሲሮጥ ጉሮሮውን በቢለዋ ወግተውት ነው ድምፁ ተበላሽቶ የቀረው። የዛሬን አያድርገውና 'ሚያውውውው' ሲል የአይጥ ሰራዊትን የሚያርድ፣ ሴት ድመቶችን የሚያማልል ድምፀ መረዋ ድመት ነበር ።

ድሮ የጋሽ ታምሩ ድመት ነበረ። አንድ ቀን ታዲያ ፍርምባ የሚባል ነገር ሰረቀ ብለው አባ ታምሩ በአንካሴ ወጉት። ከዛ በኋላ እሳቸው ቤት መኖር አቆመ። ጨካኝ ናቸው። ፍርምባ ለምታክል ስጋ ብለው...ተወልዶ ካደገበት ቤት አባረሩት ፤ ያውም በአንካሴ ወግተው። እሳቸው ግን፣ "ድመቱን ለፍርምባ ብዬ አልወጋሁትም" ብለው ዋሹ። ትልቅ ሰው ይዋሻል ? ደግሞ እኮ ያኔ የሆነውን ሁሉ በዓይኔ በብረቱ አይቻለሁ...ማሪያምን አይቻለሁ !

ድመቱ ፍርምባውን በአፉ አንጠልጥሎ መሬት ለመሬት እየጎተተ እኛ ቤት ፊት ለፊት ወዳለው የውሃ መውረጃ ቱቦ ሲሮጥ አባ ታምሩ ልክ እንደኦሎምፒክ ተወዳዳሪ ግራ እጃቸውን ወደፊት ቀስረውና ጦር የጨበጠ ቀኝ እጃቸውን እስኪቻሉት ድረስ ወደኋላ ለጥጠው በሰፋፊ ርምጃዎች ተንደረደሩ ...1...2...3...ጦሩን ዥ....ው ....አደረጉት። ድመቱ ሲሮጥ ጦሩ ሲከተለው፣ ጦሩ ህይወት ያለው ይመስል ነበር። ልክ ቱቦው ጫፍ ላይ ሲደርስ የድመቱ የኋላ እግር ታፋ ላይ ጦሩ ተቀበቀበ...አቤ...ት ገንባው እንዴት አሰቃቂ ጩኸት እንደጮኸ። ...እንዳንቡላንስ ነው የጮኸው...ሚያያያያያያያያያያያያያ...! ሲጮህ በአፉ የያዘው ፍርምባ ወደቀ። አንድ ነጭ ያልቆሰለም ያልተወጋም ድመት ቀልቦት ወደቱቦው ውስጥ ጥልቅ አለ...!!

ጎረቤቱ ሁሉ፣ "አቤት አጨካከን እናትዬ የእግዜር ፍጡር ነው...ምን በደለ ?" እያለ ሲያጉረመርም አባ ታምሩ ታሪክ ፈጠሩ። "የልጅ ልጄን ዓይኗን ሊያወጣት ነበር እኮ፣ ግዴላችሁም ይሄ ድመት አውሬ ሆኗል..." በማለት የፍርምባውን ፀብ 'ትውልድ ለማዳን' የተደረገ ጦርነት አስመሰሉት።

የሚገርመኝ ታዲያ የመንደሩ ሰው ነው። በወሬ ወሬ " ይሄ ድመት ምን ሆኖ ነው የሚያነክሰው?"

ሲባል ፤ ..."ይሄ 'አውሬ' ነው...የጋሽ ታምሩን የልጅ ልጅ ዓይኗን ሊያወጣት ሲል እያየሁ ያፈነዳው በአንካሴ ወጉት" ይላል ፡፡ ጭራሽ አይጦቻቸውን እያሳደደ እንዳልፈጀላቸው 'አውሬ' የሚል ስም ሰጡት ለዚህ ሚስኪን ገንባው !!

ትልልቆቹ ሰዎች ሁሉ፣ ፀጉራቸው የሸበተው አስተማሪው ሰውዬ (ትልቁ ግቢ ቤት ውስጥ የሚኖሩት ሳይቀሩ ይሄን የፈጠራ ታሪክ ያወራሉ፡፡ታዲያ ስለአገር ታሪክ አናውራ ሲሉ አላምናቸውም ትላንት አፍንጫቸው ስር ያውም በጠራራ ፀሐይ የተፈፀመ የድመት ታሪክ ወጊው በፈለገው መንገድ የተረኩ ሁሉ ስለአገሬ ታሪክ አናውራህ ሲሉኝ እንዴት ልመናቸው ?በመንደራችን የድመት ታሪክ ያልታመኑ ሁሉ ስለአገራቸው አንበሶች ጀብዱ ሲደሰኩሩ እንዴት ልቤ እሺ ብሎ ይቀበል ?ታሪክ ማውራት ታሪክ ከመስራት እኩል ጀግንነት እንደሚጠይቅ የገባኝ ያኔ ነው ...፡፡

ከዛን ቀን ጀምሮ ጦርነቶች ሁሉ የአደባባይ ምክንያታቸው ምንም ይሁን ምን ከኋላቸው ፍርሃት የሚባል ስጋ ያለ ይመስለኛል፡፡ ገንባው አውሬ አይደለም፡፡ ገንባው የከለከሉትን የዕለት እንጀራ ነጥቆ "ተመስገን" የሚል ሚስኪን ድመት ነው፡፡ የዕለት እንጀራውን ሲነጥቁቸው የዘላለም ስሙን ነጠቁት፡፡ "ያኔ ባንካሴ ባንወጋው ኖሮ ትውልዱ ሁሉ እውር በሆነ_" እያሉ ከድመት ጥፍር በባሰ የውሸት ጥፍራም ታሪክ ጭፍን ትውልድ ይፈጥራሉ፡፡

በኃሳብ ካቀረቀርኩበት ቀና ስል ገንባው የለም፡፡ "በስማም የት ሄደ ?" ሰባራ መቋሚያዬን ወድሬ ወደ ጓዳ ሮጥኩ፡፡ መስኮቱ ገርበብ ብሏል፡፡ የጠቦቱ ታፋም ተሰቅሎ በነበረበት ቦታ የለም፡፡ ...ወይኔ ጉዴ ዛሬ እናቴ ገደለችኝ በቃ፡፡

ሮጬ ወደ ውጭ ስወጣ ገንባው ታፋውን እየጎተተ ወደ ቱቦው ጥልቅ ሲል አየሁት፡፡

"ወይኔ አንካሴ ኖሮኝ በነበር...ይሄን አውሬ አልለቀውም ነበር" አልኩ ለራሴ...፡፡

# ተ ሸ ከ መ ና ታ ል !! 7

እናቴ ሁልጊዜ እንድናጠና ስትመክረን እንዲህ ትላለች:-

"እናንተ ልጆች አጥኑ፣ ተማሩ እባካችሁ ! ...እኔ ባለመማሬ ነው ጉዴን ተሸከሜ የዋልኩት፤" ማንበብም መፃፍም ስለማትችል ንግግሯ በቁጭት ነበር:: አንድ ቀን ታዲያ ይሄ ተሸክማ የዋለችው ጉድ ምን እንደሆነ ለማወቅ ጓጉቼ ጠየቅኳት፣

"ማሚ የምን ጉድ ነው ተሸከመሽ የዋልሽው ?"

አወራችኝ...

**** **** ****

በደርግ ጊዜ መስከረም ሁለት ቀን ሕዝቡ በግድም ሆነ በውድ የድጋፍ ሰልፍ ይወጣ ነበር:: መስከረም ሁለት ደርግ ንጉሱን ገልብጦ ሥልጣን የያዘበት ቀን ነው:: በአጭር አገላለፅ መስከረም ሁለት የደርግ ግንቦት ሃያ ነበር:: ታዲያ እናቴ በወቅቱ የነበረውን የግዳጅ ውትድርና በመፍራት የመጀመሪያ ልጇን ወታደር ቤት እንዳይወስዱባት ከከተማው ወጣ ያለ አከስታችን ቤት ደብቃ፣ ሁለተኛ ልጇንም ገጠር እናቷ ጋር ልካ፣ ሦስተኛውን ልጇን አልጋ ስር አስቀምጣ፣ አባቴንም "ታምሜያለሁ በል!" ብላው፣ እሷ ግን ነጭ ልብስ ለብሳ ሰልፍ ወጣች:: ግዴታ ነዋ!

ቀበሌ ስትደርስ ሴት ወንዱ ያለውን ለብሶ ተሸቀርቅሮ፣ ቀበሌውም በተለያዩ መፈክሮችና በባለ ቀለም መብራቶች አጊጦ ጠበቃት:: የቀበሌው የኢ.ሴ.ማ ኃላፊ የነበረች ሴት በባለእጀታ የጣውላ ሰሌዳ ላይ ተፅፈው የተዘጋጁ በመቶ የሚቆጠሩ መፈክሮችን ለእናቴ እያሳየቻት፣"ምረጭና አንዱን ያዥ" አለቻት::

እናቴ ቀለል ያለችና በደማቅ ቀይ ቀለም የተሸሞነሞነች መፈከር መርጣ አነሳችና ወደ ሰልፉ ተቀላቀለች:: ከለበሰችው የሚያምር የአበሻ ቀሚስ እና ከራሷም ቁንጅና ጋር ተዳምሮ የአሎምፒክ መከፈቻ ላይ 'ኢትዮጲያ' የሚል ምልክት ይዛ ሰልፉን የምትመራ ቆንጆ የአበሻ ሴት ትመስል ነበር::

በዕለቱ መስቀል አደባባይ እናቴን በርካታ ሰዎች በግርምትና በአድናቆት ሲመለከቷት ዋሉ::

ታዲያ በዚያ ሰሞን ማታ በቴሌቪዥን ደጋግመው እናቴን ከነመፈክሯ ያሳይዋት ጀመረ፡፡ ምን ይሄ ብቻ፤ ዓመቱን ሙሉ ፎከረውም እናቴን ማሳየት፤ ኢህአፓ ብለውም እናቴን፤ መኢሶን ብለውም እናቴን፤ ቀይ ሽብር ብለውም እናቴን፤ ጓድ ሊቀመንበር ተናግረው ሲያበቁም እናቴን ማሳየት፡፡

ጭራሽ ብሔራዊ ውትድርና ተብሎ ምድረ ወጣት ሲጓፈፍ ፣ የብሔራዊ ውትድርና አገር አቀፍ ዓርማ የእናቴ ፎቶ ሆኖ በየቦታው ተለጠፈ፡፡ በነጭ ልብስ ተውባ መፈከር ይዛ የቆመች እናቴ የብሔራዊ ውትድርና አገር አቀፍ አርማ ሆነች፡፡ አንድ ጋዜጣ ላይ የእናቴ ፎቶ ስር እንዲህ የሚል ጽሑፍ ሰፍሮ ነበር፤

"አብዮታዊት ሶሻሊስት ኢትዮጵያ ነጭ ቀሚስ ለብሳ"

እናቴ ታዲያ መጀመሪያ አካባቢ በቴሌቪዥን በታየች ቁጥር በቁንጅናዋ የተመረጠች መስሏት አባቴ ላይ በኩራት ትነሰነሰበት ነበር፤

"ጓዳ ለጓዳ ስውል ቀላል ሰው አድርገኸኝ፤ እግሬ ወጣ ካለ አገር ነው የሚሰግድልኝ!" ትለዋለች ኩራ ብላ፡፡ አባቴ አፉን ሸርመም አድርጎ፤ "እዩኝ እዩኝ ማለት ደብቁኝ ደብቁኝ ያመጣል !" ይላታል፡፡

"የቅናት ወሬ ነው ይሄ" ትልና ሆነ ብላ ለማበሳጨት በቴሌቪዥን ደጋግሞ የሚታየውን ምስሏን አተኩራ እየተመለከተች፤

"እንዴት ፍሬ ልጅ እኮ ነኝ" ትላለች፡፡ አባባ ታዲያ "ሃሃሃሃሃሃሃሃ..." ብሎ በረዥሙ ይስቅና "ሰልፍ ላይማ መንግስትም አንድ ፍሬ ነኝ ነው የሚለው" ይላል፡፡

"ኤዲያ እንግዲህ በለቲካህን ልትጀምር ነው..." ብላ ወደ ጓዳዋ ትገባለች፡፡

ይሁንና እናቴ እየቆየች በቴሌቪዥን መታየቱ እና ስለ እርሷ መወራቱም ሲደጋገምባት ፈራች፡፡

በተለይም ጓድ መንግስቱ ኃይለማሪያም መስቀል አደባባይ በትልቁ የተሰቀለውን የእናቴን ፎቶ ለተሰበሰበው ሕዝብ እያሳዩ በደም ፍላት፤

"እንደነዚህ ዓይነት ጀግና እናቶች ያሉባት አገር በማንም ወመኔ ከሃዲ ስትወረር እንዴት ወንዶቿ አልጋ ስር ይደበቃሉ? እነዚህን በቅቧቃ ወንዳገረዶች ቂጣቸውን በሳንጃ..." እያሉ ንግግር ካደረጉ በኋላ እናቴ ስጋቷ ከፍ አለ፡፡

ስጋቷን ለማስታገስ፤ "እረ ይሄ መፈክር ምንድን ነው የሚለው?" ብላ የተማረ ሰው ጠየቀች፡፡ መስከረም ሁለት ሰልፍ ላይ ይዛ ስለወጣችው መፈክር ተሸክማው ስለነበረው ጽሑፍ ሚያዚያ ላይ "ምንድን ነው?" ብላ ጠየቀች፡፡

ሲነበብላት አመዷ ቡን አለ ፤ ብርክ ያዛት፡፡

መፈክሩ እንዲህ ነበር የሚለው...

"የአብዮት ጠላቶችን ለማደባየት እኛ እናቶች ልጆቻችንን፤ ካስፈለገም ባሎቻችንን በደስታ እናዘምታለን!!"

# ደወል !! 8

የአካባቢ ሳይንስ መምህርታችን እትዬ ሐረጓ ከስራ ተባረረች:: ምናለበት ሂሳብ አስተማሪያችን ጋሽ ቢጋለ ቢባረር፤ ምናለበት እንግሊዝኛ አስተማሪያችን እትዬ ፀሐይ ብትባረር:: ርዕሰ መምህራችን አቶ ተከሉ ራሳቸው ቢባረሩ ምን ነበረበት:: ኤዲያ እንደው እዚች አገር ደግ አይበረከትም::

ይሄ ዜና ለእኛ ለሦስተኛ 'ሲ' ክፍል ተማሪዎች ትልቅ መርዶ ነበር:: ልክ ሁላችንም በጅምላ ከትምህርት ቤት እንደተባረርን ዓይነት ስሜት ነው የተሰማን:: እትዬ ሐረጓ የተባረረችው "ሰው በማኅበር የተደራጀ እንስሳ ነው" ብላ በማስተማሯ ቢሆንም ርዕሰ መምህራችን አቶ ተከሉ ግን "መምህርት ሐረጓ የተባረረችው 'ሰው በማኅበር ከተደራጀ እንስሳ ነው' ብላ ፀረ ልማት ትምህርት በሕፃናት አእምሮ ውስጥ በመዝራቷ ነው" ብለው መምህራን ስብሰባ ላይ ተናገሩ አሉ:: ይሄን ወሬ የነገረችን የሂሳብ አስተማሪያችን ልጅ ገነት ናት፤ አባቷ ሲያወራ ሰምታ !

እስቲ ለአንዲት 'የ' ብለው እትዬን ያባርሯታል...? አንዲት 'ከ' ምርጥ መምህራችንን ታስባርራለች ? እግዚእእእእእእእ...ርዕሰ መምህራችን ራሳቸው ሰልፍ ሜዳ ላይ 'ነፍ' ጊዜ አይደል እንዴ የሚሳሳቱት ? ባለፈው እንዲያውም ማስታወቂያ ሲለጥፉ "ማንም ተማሪ 'ከአጥር' ከዘለለ እና ግቢ ውስጥም ይሁን ከግቢ ውጭ ከተያዘ የእኛ ተማሪ አይሆንም" ለማለት "ማንም ተማሪ 'ከጥር' ከዘለለና ግቢ ውስጥም ሆነ ከግቢ ውጭ ከተያዘ የእኛ ተማሪ አይሆንም" ብለው ማስታወቂያውን አሳስተው በመፃፋቸው ወላጅ ሁሉ ልጆቻችንን ጥር ወር ሲገባ ሊጨርሱብን ነው ብሎ ተንጋግቶ አልመጣም ? ...እና እትዬ ሐረጓ ላይ ሲሆን 'የ'ን ያካብዳሉ ? ወይኔ! አለቀስኩ፤ ስቅስቅ ብዬ አለቀስኩ ::

ለእናቴ ይሄንኑ አሳዛኝ ጉዳይ ስነግራት "ጉድ !...ዛሬም ተባረረች?" አለች እዝን ብላ:: በኋላ አባቴ ጋር ሲያወሩ የሰማሁት ነገር የባሰ አሳዘነኝ:: እትዬ ሐረጓ ለካ መባረር ብርቋ አልነበረም፤ መምህርቷ ነገር የሚመርባት፣ ችግር ዘሎ የሚለጠፍባት፣ ነገር ከየትም ተስቦ የሚሰበሰብባት ሚስኪን የመከራ ማግኔት ነበረች::

በጃንሆይ ጊዜ አማርኛ አስተማሪ ነበረች አሉ:: አንድ ቀን ታድያ ተማሪዎቿን ተረትና ምሳሌ

ስታስተምር "አንበሳ ሲያረጅ የዝንብ መጫወቻ ይሆናል" ብላ ጥቁር ሰሌዳው ላይ በትልቁ በመፃፏ ተከሰሰች:: በወቅቱ የንጉሡ ዙፋን በተማሪዎች መነቃነቅ ጀምሮ ነበር:: ደርጎችም ወታደራዊ ነጠላቸውን አሸርጠው የአብዮታዊ ዘፈን ዳርዳርታ እስከስታቸውን አራተኛ ላይ እያስነኩት ነበር፣ አብዮታዊ ዋንጫ ልቅለቃ፣ ወታደራዊ ሰራ ሰራ...ህዝቡ እያጨበጨበላቸው...::

እቺ ሚስኪን መምህርት ታዲያ እየተዋከበች ራሳቸው ንጉሡ ዙፋን ፊት ቀርባ ጃንሆይ ገሰጧት "ስሚ! ከላይ ናት ዙፋናችን፣ ከግዜር የተሰጠች...፣ ከእዮብ ትዕግስት የተቆነጠረች...፣ ከዳዊት እምነት የተጨለፈች...፣ ከሰለሞን ጥበብ የተዘገነች...፤ እንኳን ዝንብ ተማሪና ዝንብ ደርግ ቀርቶ ማንም አይጫወትብን::" አሏትና በዚህችው ምክንያት ከርቸሌ ተወረወረች! እንደሚወራው የንጉሡ እስር ቤት ያን ያህል ባያስከፋም የእስር ጥሩ የለውምና መምህርት ሐረጓ ከፋኝ አዝና ነበረ::

"ሳይደግስ አይጣላም" እንዲሉ መምህርቷ በእስር ላይ እያለች ደርግ ንጉሡን ገልብጦ ሥልጣን በመያዙ ተፈታችና "ሳይንስ አስተማሪ" ሆና ተመደበች:: "ኧረ እኔ አማርኛ አስተማሪ ነኝ" ብትል ማን ይስማት ! "አብዮት ተረትና ምሳሌ ሰልችቷታል፣ ስርዓተ ነጥብ ምናምን አትሻም፣ ሳይንሳዊ ወታደር፣ ሳይንሳዊ መደብ....ቀጥይ"

"እሺ!" ብላ ማስተማር ጀመረች...ሳይንስ ! በአማርኛ የትምህርት ክፍለ ጊዜ ለምዶባት "እጅን ከምግብ በኋላ መታጠብ ከዓረፍተ ነገር በኋላ አራት ነጥብ እንደማስቀመጥ ነው" እያለች ሳይንስ ትምህርት ማስተማሯን ቀጠለች::

የሳይንስ ትምህርት እያስተማረች ተማሪዎችም ወደዋት ስትኖር በአንድ የተረገመ ቀን "ዝንቦች ከቆሻሻ ይፈለፈላሉ" ብላ በማስተማሯ ተይዛ ታሰረች:: የፖሊስ ጣቢያው ኃላፊ እሳት ለብሶ እሳት ቅድሚያ ሰጥተን ታገስን:: ጭራሽ ዛሬ ከቆሻሻ ተፈለፈላችሁ ትይናለሽ !? እኛ የተፈለፈልነው ጎርሶ በፊቷ እየተንጎራደደ "ትላንት በአረጀ አንበሳ የሚጫወቱ ዝንቦች አልሽን፣ ለአንበሳው ማርጀት ከአብዮት ነው..." ብሎ ራሱን በዝንብ ወክሎ በመበሳጨት አብዮታዊ እርምጃ እንዲወሰድባት አዘዘ :: ያው በወቅቱ ሰላምታም ቅኔ ነው ተብሎ ሰምና ወርቁ ይፈለግ ነበርና መናገር ስጋት ነበር::

መምህርት ሐረጓ ነገ ዛሬ ገደሉኝ እያለች ልጧ ተርሶ፣ መቃብሯ ተምሶ ስትጠብቅ ሞት የፈረደባት ካድሬ ልጁ ርሷ የምታስተምረው ኖሮ አባቱን አልቅሶ በመለመኑ ተፈታች::

*"ትንሽ ሕፃን ይዛ ቁማ ከወደቡ*
*ላምላክ ብትነግረው ፀጥ አለ ወጀቡ"* እንዳለው ድምፃዊው ...

ካድሬው ቢሮው ጠራትና ቁርጥ ያለ ማስጠንቀቂያ ሰጣት:: "ስሚ አንቺ ሴትዮ፤ አሁን በልጄ ልመና ምሬሻለሁ:: ከአሁን በኋላ፣

" ፩. አንበሳ የሚባል ስም፤

ኗኝ. ዝንብ የምትባል ቃል...ከአፍሽ ቢወጣ ውርድ ከራሴ፤ ሂጂ ውጭ...ምን ትመስላለች እች! ለኮስማናውም ለምኑም በብድር የተገዛ ጥይት እንጨርስ እንዴ...!" ብሎ ለቀቃት:: መከላፈት ከሞት ጋር ሲወዳደር እዚህ ግባ አይባልምና በመከላፈቷ ሳይከፋት በምህረቱ ደስ ብሏት ወደ ኋላዋ እየተገላመጠች ወደቤቷ በረረች::

*** *** ***

አንድ ሌላ ቀን መምህርቷ ተማሪዎችን 'አንበሳ ግቢ' ወስዳ እንድታስጎበኝ በርዕሰ መምህሩ ታዘዘችና ለተማሪዎች ምን ብላ እንደምትነግራቸው ስታስብ ቆይታ እንዲህ አለች፤

"ልጆችዬ ! ቅዳሜ ጠዋት የ"እንስሳት ንጉሥ" የታሰረበት ሄደን ስለምንጎበኝ ከወላጆቻችሁ ስሙኒ ስሙኒ ተቀብላችሁ እንድትመጡ !" በቀጣዩ ቀን ግን ሌላ ጣጣ መጣባት:: አስጠንቅቆ የፈታት ካድሬ ከአራት አጃቢዎቹ ጋር ከተፍ አለ:: ደም ስሩ ተገታትሮ...

"አንች ሴትዮ ችግርሽ ምንድን ነው ? የአስለፍልፍ ይዞሻል ወይስ ሁለት ነፍስ ነው ያለሽ?"

"ምን አጠፋሁ ደግሞ ጌታዬ !" አለች እየተንቀጠቀጠች::

"የእንስሳት ንጉሥ የታሰረበት ሄደን እንጎበኛለን" ብለሽ ተማሪ አስልፈሽ ቤተ-መንግሥት ልትሄጅ ነው:: እንኳን አንቺ ስንቱ የሰብዓዊ መብት ተከራካሪ ነኝ ባይ እየጠየቀ አልቻለም:: ደግሞስ የአብዮታዊት ኢትዮጵያን ሕዝብ ነው እንስሳ የምትይው?"

በወቅቱ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ቤተመንግስት በቁም እስር ላይ ናቸው እየተባለ በርካታ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ ድርጅቶች እንጎብኛቸው የሚል ጥያቄ እያቀረቡ ነበር:: ያችን ቀን በትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር አማላጅነት ምህረት ተደረገላት:: አብዮታዊ ሽምግልና ነፍሷን አተረፈው::

ይሄው አሁንም እንደገና ከምትወደውና ከምታከብረው የመምህርነት ስራዋ እመድ አፋሽ አድኗ አፋፍሶ አስባረራት፤ ያውም በአንዲት 'የ' እና በአንዲት 'ከ'...፤ በአንበሳም፤...በዝንብም፤ ...በ'የ'ም..በ'ከ'ም... ፍዳዋን የበላች ሚስኪን መምህርት በተማሪዎቿ ዐይን ግን ፍፁም ሌላ ሰው ነበረች ::

*** *** ***

የአትዬ ሐረጓ ከፍለ ጊዜ ሲደርስ ሰኞ በሦስተኛው 'ፔሬድ' ሁላችንም ደስ ብሎን በር በሩን እናያለን፤ ብቅ ስትል ግር ብለን ከወንበራችን እንነሳለን፤ ወንበሮች ይንኳኳሉ፤ ይንሳጠጣሉ፤ ወረቀቶች ይንኮሻኮሻሉ...ከዐይኖቿ ስር በስሱ ማዲያት ጣል ያደረገባት፤ ሁልጊዜም ፀጉሯን በሻሽ የምትሸፍን፤ ከሻሹ ያፈነገጡ ነጭና ጥቁር ጢቃጠቆ የፀጉር ዘለላዎች ግንባሯ ላይ የሚታዩ፤ የተጎሳቆለች መልእከ ረጋ ባለ እርምጃ ትገባለች...::

"የአባትሽ ሥራ"

"ግንፕላ ሠሪ"

ያሬድ ...ሹፌር

ሳራ ...ዛፍ ቆራጭ

ታምሩ ...አባቴ ሞቷል እናቴ ልብስ ታጥባለች፤

ሸብሩ ...አባቴን አላውቀውም...

ከሁላችንም ፊቱ ወዛ ያለውን ኡስማንን ጠየቀችው፤

"ኡስማን አባትህ ስራቸው ምንድን ነው?"

"ቅቤ ነጋዴ" አለ ኡስማን ቀስ ብሎ፤ አይናፋር ነው፡፡

እትዬ ተስፋ በመቁረጥ በረዥሙ ተነፈሰች፡፡ እንደድሮው የሕዝብ ትምህርት ቤት የሚማር የባለስልጣን ልጅ የለም...በዝምታ ዕቃዋን ሰብስባ ድከም ባለ እርምጃ ከክፍላችን ወጣች፡፡

"ደህና ሁኑ ልጆች!" አላለችም፡፡

"የቤት ሥራችሁን ሳትሰሩ እንዳትመጡ!" አላለችም፡፡

...ሄደች ደጓ መምህርታችን፡፡

ከሁለት ወር በኋላ ርዕሰ መምህራችን አቶ ተከሉ ሰልፍ ሜዳ ላይ ቆመው እንዲህ አሉ...፣

"በታላቅ ትጋት እና የሙያ ፍቅር ላለፉት 28 ዓመታት ደከመኝ ሰለቸኝ ልረፍ ሳትል በመምህርነት ስታገለግል የቆየችው መምህርት ሐረጓ ባደረባት ህመም ምክንያት በሕከምና ስትረዳ ቆይታ ትላንት ማታ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይታለች፤...የአንድ ደቂቃ የህሊና ጸሎት !" አሉና አቀረቀሩ፡፡

ሁሉም ሲያጎነብስ ቀጥ ብዬ ርዕሰ መምህሩን አየኋቸው፡፡ እጃቸውን ወደ ኋላ አጣምረው ፊት የተሰለፈውን ተማሪ አፍንጫ ሊነካ የደረሰ ቦርጫቸውን ቀስረው ሳያቸው እትዬ ሐረጓን በጭካኔ የዋጧት መስሎ ተሰማኝ፡፡ ከነማጥፊያዋ፣ ከነጠመኔዋ፣ ከነግንፕላዋ፡፡

ገድሎ እንገት ማቀርቀር፣ የህሊና ፀሎት የሚባል የማስመሰል ካባ ለብሶ እነሆ ሰልፍ ሜዳችን ላይ...

የሆነ ነገር ቀጭ ሲል ሰምቼ ቀስ ብዬ እንደገና ወደፊት ተመለከትኩ፡፡ ተደገመ፡፡ እትዬ ሐረጓን ተከታ የገባችልን ውባለም የምትባል ወጣት መምህርት ማስቲካ ነበር፡፡ የቀጣዩ ዘመን ሌላ ግዴለሽ ደወል፡፡

# የአባዬ ስልክ እና ባዮሎጂ

# 9

እንዲህ እንደዛሬው በየሰዉ ኪስ ሳይልከሰከስ በፊት ስልክ ተዓምራዊ የሀብት መለኪያ ነበር፡፡ አቤ...ት ስልክ እንዴት እንደሚከበር ! እንደሚፈራ...! ያኔ ኔትወርክ እንጂ ስልክ አልነበረም፡፡ ዛሬ ግን ስልክ እንጂ ኔትወርክ የለም ፡፡

እንግዲህ በሰፈራችን አንድ የቤት ስልክ ብቻ ነበረ ያለው፤ ስሙ ደግሞ "የአባዬ ስልክ"፤ ብዙው የሰፈር ሰው የእኔን እናት ጨምሮ በዚህ ስልክ ነበር የሚጠቀመው፤ ደግሞ ድምፁ የትናየት እንደሚሰማ...ኪሊሊሊሊሊሊሊሊ ሲል የመንደሩ ሰው ሁሉ ሥራ ያቆማል፡፡ ወጣቶች ፍቅረኞቻቸው የደወሉ መስሏቸው የያዙትን ሥራ እርግፍ አድርገው ጆሮና ልባቸውን ያቆማሉ፣ እናቶች ሊጥም እያቦኩ ከሆነ ነጭ የቦከስ ጓንት ያጠለቁ መስለው ብቅ ይላሉ፡፡ የአባዬ የስልክ ድምጽ መቼም አይረሳኝም፡፡ አሁን የመጡ ስልኮች ቢዘፍኑ ቢንቀጠቀጡ የአባዬን ስልክ ድምፅ ከአዕምሮዬ ሊፍቁት አልቻሉም፡፡

ስልኩ ሲጮኽ ልጆቻቸው አረብ አገር ያሉ እናቶች ልባቸው ይሰቀላል...፤ እናቴ ራሷ " አቡቹ ! እስቲ እሱን ቆርቆሮ ቀንሰው" ትላለች፤ ቴፑን ማለቷ ነው፡፡ እንግዲህ ይሄ ሁሉ ሰው እንዳቆበቆበ የአባዬ ልጅ ቡጡጡ በራቸው ላይ ትቆምና "እማማ ፋጤ ስ...ልክ ! ከውጭ ነው ቶሎ በሉ!" ብላ ትጮሀለች፡፡ እማማ ፋጤ ወደ አባዬ ቤት ሲሮጡ ሌላው ጎረቤት ወደየስራው ይመለሳል፤ ስልኩ በተደጋጋሚ የሚጮኸው ለበዓል አካባቢ ነው፤ በተለይ ለአዲስ ዓመት!

ቀላል ስልክ እንዳይመስላችሁ፤ በዚህ ስልክ ሰንቁ ከውዱ ጋር አውግቷል፣ ሰንቁ የውዱን መርዶ ተረድቶ በድንጋጤ ስልኩ የተቀመጠበት ጠረንጴዛ ስር ተጠቅልሏል፣ ሰንቁ ከጠፋ ዘመዱ ተገናኝቷል፤ ሰንቁስ ብር እንደተላከለት ሰምቶ ፈንጥዟል ! ...ኧረ ሰንቁ ! ወደ አባዬ ቤት ሲንደረደር እንቅፋት አንግሎት ባፍጢሙም የተተከለ፣ ጥፍሩ የተነቀለ...አለ፡፡

ለምሳሌ የአረጋሽ ጥፍር ተጣምሞ የቀረው ወደ አባዬ ቤት ስትሮጥ እንቅፋት አንግሏት ነው፡፡ አረጋሽ

ህመሙን ቻል አድርጋው ስልኳን እናገረችና ልክ ስልኩን ስትዘጋው፣ "ኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡ..." ብላ ጮኸች፡፡ መርዶ የሰማች ነበር የምትመስለው፤ በኋላ ሲጣራ ከስልኩ በፊት ለመታ እንቅፋት ነው ያለቀሰችው፡፡ ጥፍሯ ግን ተጣምሞ ቀረ፡፡

ይሄ ስልክ ስልክ ብቻ አይደለም፤ ጩኸቱ የምስራች ነው!...ጩኸቱ መርዶ ነው፡፡ ከመንደራችን በላይ ያለው የጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ደውል ድምፅ የአባዩን ስልክ ጩኸት ያህል ግርማ ሞገስ የለውም - ለመንደርተኛው፡፡ የኛን መንደር ሰዎች ወፍራም እንጀራ፣ ደንዳና ናፍቆትና ፍቅር በቀጭን የስልክ ሽቦ ውስጥ ተጉዞ የሚያርፍበት ኬላ የት ነው ቢሉን "የአባዬ ቤት" እንል ነበር ::

ይህን ስልክ በጉጉት ከሚጠብቁ ቤተሰቦች መሃል የእኛ ቤተሰብ አንዱ ነበር፡፡ አባቴ ለሥራ ከእኛ ርቆ ይኖር ስለነበር እኛ ልጆቹን የሚመከረው ለሚስቱም የሆድ የሆዱን የሚናገረው በአባዬ ስልክ ነበር፡፡ እንደውም ግንባር ቀደሙ የአባዬ ስልክ ተጠቃሚ ቤተሰብ የእኛ ቤተሰብ ነበር ማለት ይቻላል። ታዲያ አባቴ ለበዓል ሲመጣ ለአባዬ የሆነ ነገር ይዞ ስለሚመጣ ስልክ ስንጠራ ቤተሰባዊ ቃና ባለው መንገድ ነው፡፡ "ስልክ !" ብቻ አንባልም፤ "እንዳይቆጥርበት ፍጠኑ ጋሼ ነው !" የሚል ማስጠንቀቂያም ይጨመርበታል፡፡

ለምሳሌ አባቴ ሲደውል እናቴ ከፊት፣ እህቴ ከኋላ፣ ወንድሜ ቀጥሎ፣ እኔ፣ ትንሸዋ እህቴ ተግተልትለን እንሄዳለን፡፡ መጀመሪያ እናቴ ናት የምታናግረው፤ ድምጿን ቀንሳ ፊቷ በሃፍረት፣ በናፍቆትና በፍቅር ተጥለቅልቆ ብዙ "አዎ" እና "አይይ!" የበዛበት ንግግር ታደርጋለች፡፡

አዎ!

አዎ!

አዎ!

አይይይይይ!

የአባዬ ስልክ ደግሞ ለከፋቱ ይጮሃል፤ በአሁኖቹ የእጅ ስልኮች ቋንቋ 'ላውድ ስፒከር' ላይ ያደረጉት ይመስላል፡፡

"እንደምነሽ ! ...ምነው ድምፅሽ ጎረነነ ? አመመሽ እንዴ የኔ እናት ?" ይላል አባባ፤

"አይይይይ! ደህና ነኝ! " ትላለች እናቴ፤ አንዳንድ የፍቅር ነገርም ስለሚናገር ቶሎ መስናበት ትፈልጋለች፡፡

ቀጣይ ተረኛ ትልቅ እህቴ ናት፡፡

"ምን ላላክልሽ"

"ሰኒከር ሚማ"

"እሽ!"

"ነጭ ..."

"እሺ የኔ ማር!" ድምፁ ውስጥ መናፈቅ አለ፤

"እንደባለፈው ሰፈ እንዳታመጣ ባባ"

"እሺ የኔ ቆንጆ!"

ወንድሜ ይቀጥላል...

"ታኬታ ሚማ ባለ ብሎኑን"

"ባለ ቡሎን ሚማ አለ እንዴ ?" ይላል አባቴ በግርምት፤

"እንከት!"

"እሽ እፈልጋለሁ ፤ አንተ ብቻ እናትህን እንዳታስቸግር፤ በደንብ ተማር!"

እኔ አባትህን እናግር ስባል አላናግርም፤ አብሬ ሮጬ አባዬ ቤት ድረስ ሄጄ ግን ብሞት አላናግርም፤ እናቴ ትበሳጫለች፡፡

"እሺ ምን ላምጣልህ ይልሃል" ትላለች በብስጭት፤

"ም ን ም!" እንባዬ ይመጣብኛል፤ አባቴን እወደዋለሁ፤ ግን በስልክ አላናግረውም፡፡ ለምን ቢባል መልስ የለኝም፡፡ የተባለው ነገር ሁሉ ሲመጣ ግን እህቴ ያንን ሁሉ ማብራሪያ ሰጥታ ሚማዋ ይሰፋል ወይ ይጠባታል፡፡ ወንድሜ ባለብሎን ታኬታ አይመጣለትም፤ "ኧረ እንዲያ የሚባል ሚማ የለም!" ይለዋል አባባ፡፡ እኔ ግን ምንም ሳልናገር ምርጥ ነገር ይመጣልኛል፤ አባቴ እኔን ራሴን እስኪመስለኝ ምርጫው ልክ ነው፡፡

*** *** ***

እኛ ሰፈር አንዲት ሴት ጎረመሰች የምትባለው በአባዬ ስልክ ቤተሰብ ወይም ዘመድ ያልሆነ ወንድ ከደወለላት ነው፡፡ ሁሉም ሴቶች ለፍቅረኞቻቸው የአባዬን ስልክ ነው የሚሰጡት፡፡ ወንዶችም አልፎ አልፎ ይሰጣሉ ፡፡ ታዲያ አባዬ ቤት የተወራው ነገር ስልኩ እንደ ሚጋፎን እየጮኸ ምስጢሩን ስለሚዘራው ጎረቤት ጋር ወዲያው ይደርሳል፡፡

"ሮማን የያዘችው ልጅ ሹፌር ነው መሰል ሁልጊዜ ከተለያየ አገር ነው የሚደውለው፣

"አትይኝም!"

"ሙች!...እንዴ ከጅቡቲ፣ እንዴ ከሞያሌ፣ ቢጡ ሲያወራ ሰምታ ነው የነገረችኝ":: ቢጡ የአባዬ

ልጅ ናት፤ ማን ከማን ጋር ምን አወራ የሚለውን ለመንደሩ የምታዳርሰው እሷ ናት::

እንዲህ እየተባለ ቢቃ የተወራው የተደረገው ሁሉ ሰፈሩ ውስጥ ይናኛል:: አንዲት ሴት ወይም ወንድ በአባዬ ስልክ ካልተደወለለት ጉርምስናው እውቅና አያገኝም::

እንዲት ሴት ስልክ ማናገር እና አለማናገሯ የፀባይ መለኪያ ሆኖ በመንደርተኛው ያስወቅሳታል:: አልያም ያስመሰግናታል:: "ውይ እሷ አንገቷን የደፋች፣ አባዬ ቤት አንድ ቀን ረግጣ አታውቅም " ይባላል:: ወይም "እች ልጅ የአባዬን ቤት አዘወተረች፤ መዘዟን እንዳትመዝ" ይባላል:: ታዲያ የአባዬን ቤት ከማይረግጡ 'ጨዋ' ጎረምሶች መሃል አንዱ እኔ ነበርኩ:: ስምንተኛ ክፍል ስደርስ ግን ጨዋነቴ ተገሰሰ::

***    ***    ***

የስምንተኛ ክፍል የባዮሎጂ አስተማሪያችን እትዬ መከሊት በጣም አይናፋር ሴት ነበረች:: 'ምእራፍ ዘጠኝ' የስነተዋልዶ አካላት የሚል ርእስ ላይ ስንደርስ ፊቷ ቀልቶ እያፈረች ስታስተምረን ትዝ ይለኛል::

"የስነ ተዋልዶ አካላት እንግዲህ...ያው...ወንድ እና ሴት ...ያው..." ጭንቅ ይላታል እትዬ መከሊት፤ እኛ ደግሞ ጆሮ ብቻ እንሆናለን:: ስልሳ የምንሆን የአንድ ክፍል አጉል እድሜ ላይ ለምንገኝ ተማሪዎች ይሄ ጉዳይ የነፍስ ጉዳይ ነበር - የምንጓጓለት፣ ለመስማት የምንሰስትለት፤ የስነተዋልዶ አካል ነገር ልባችንን ሰቅሎት፣ ትንፋሻችንን ውጠን እንቁለጨለጫለን:: በክፍለ ጊዜው መርፌ ቢወድቅ ይሰማል ፀጥታው::

"ውይ...ምነው ሁልጊዜ እንዲህ በትኩረት በተከታተላችሁ...! እያችሁ መማር ለራስ ነው፤ ትምህርት አገርን ይቀይራል:: ያደጉት አገሮች ዝም ብለው አላደጉም:: ...ትምህርት..." ኤጭጭ እኛ ስለ ስነተዋልዶ አካላት ለመስማት ጓጉተን እትዬ ምክር...መከራ፣ መከራ ምክሯ ሲያልቅባት...

"ወንድ ልጅ ሲጎረምስ ፂም ማውጣት የተለያየ የሰውነት ክፍሉ ላይ ፀጉር ማብቀል...እና ድምፅ መጎርነን ይጀምራል...ገባችሁ ?"

ስምረት እጇን ታወጣለች፣ "ፀጉር የሚወጣባቸው የተለያዩ አካላት የትኞቹ ናቸው ቲቸር?"

"ውይ አንች ደግሞ ፈተና ላይ የማይመጣ ነገር ምን አጠያየቀሽ ?" ትልና ታፍራለች እትዬ፤ ሁላችንም እንስቃለን::

መስፍን እጁን ያወጣል በተራው፤ የመስፍን እጅ ማውጣት ይገርመናል፤ በገመድ አስረውም ቢጎትቱት እጁ የማይዘረጋ ልጅ ዛሬ እጁን ሲያወጣ ይገርመናል:: ሽባ የተተረተረ ያህል በግርምት እንመለከተዋለን::

"ሴት ስትጎረምስስ ምን ምልክት ይታይባታል ?" ብሎ ይጠይቃል፤ ከፍሉ በሳቅና በጩኸት ይደበላለቃል:: እትዬ ታፍራለች::

"ዝም በሉ ልክ ነው ጥያቄው፤ የምን መገልፈጥ ነው:: እስቲ ከእናንተ ይህን ጥያቄ የሚመልስ" ትልና እኛኑ ታጋፍጠናለች:: ቶማስ እጁን ያወጣል "ሴት ስትጎረምስ ያው...አለ አይደል..." ብሎ ደረቱ ላይ እጆቹን ያሳርፍና እንደ ጡት ያጎብጣቸዋል:: የክፍሉ ተማሪ በሳቅ ያውካካል::

እትዬ በሃፍረት መግቢያው ይጠፋባታል፤ ድንገት አንድኛችንን ትጣራለች::

"አብርሃም !"

"አቤት!" እላለሁ በድንጋጤ፤

"የሴት ልጅ ጉርምስና ምልክቶች ምን ምን ናቸው?"

በፍርሃት ላብ ላብ እያለኝ እየፈራሁ ሞከርኩ "ስ.....ስልክ!"

"ምን ?"

"ስልክ...ማለት የአባዬ ስልክ" ከፍሉ በሳቅ ተንጫጫ፤

"ጥያቄው አልገባህም..." ብላ እንድቀመጥ ምልክት አሳየችኝ:: "መልሱ ስላልገባት ጥያቄው አልገባህም ትላለች እንዴ!"ብዬ አኮረፍኩ::

አጎጠጎጤ፣ የድምፅ መሰረቅረቅ፣ የዳሌ መስፋት እና የወር አበባ ማየት የሴት ልጅ ጉርምስና ምልክቶች መሆናቸውን ባዮሎጂው ነገረን::

*** *** ***

ትዕግስት የምትባል የከላስ ልጅ የወደድኩት በዛው ሰሞን ነበር:: ትዕግስት ቆንጆ፣ በነፃነት ያደገች የሃብታም ልጅ ናት:: ቤታቸው ስልክ አላቸው :: ብቸኛ ችግሯ አውርታ የማትጠግብ፣ ሳታቋርጥ ሙሉ ቀን የምታወራ ወሬኛ መሆኗ ነበር:: ስታወራ በጣም ትጮሃለች:: በቃ ቀስ ብሎ ማውራት አትችልም ::

ሁሉን ነገር ለመሞከር የቸኮለች ከመሆኗ ብዛት ጓደኛ እንሁን ብዬ በጠየቅኳት በቀጣዩ ቀን

ከዘፈኖቹን ኋላ ተቀምጠን ትንሿዋን ለማ አስገዘረችኝ፡፡ ከምር ነዘረኝ፡፡ በቀጣዩ ሳምንት ፕሪፈ
ከዘፈኖቹን ኋላ ተቀምጠን ትንሿዋን ለማ በጣም ስለወደደችኝ ከትምህርት ቤት ውጭ ለቀሪት ሰዓት
ለማ ንዝረቱን ነዉ አደረገችው፡፡
እናም የአባዬን ስልክ ቁጥር ሰጠኋት፡፡

*** *** ***

አንድ ቀን ከወደ አባዬ ቤት ስሜ ተጠራ !

"አብርሽ ሲ...ል...ክ!"

"አቤት ! መጣሁ !" አልኩ እናቴን

"ጋሼ አይደለም አብርሽን የሚፈልግ ሌላ ሰው ነው" አለች ሚጣ፡፡ "ሌላ ሰው" የታወቀ ነዉ ትርጉሙ፡፡

አባዬ ቤት ስደርስ የገጠመኝ ነገር አስደንጋጭ ነበር፡፡ ቀኑ የኪዳነምህረት ቀን ነበር፤ አባዬ ቤት ዝክር ተደርጎ በበል ጸዲቅ ስለነበር ከሩቅም ከቅርብም የተሰበሰበው ጎረቤትና ዘመድ እዝማይ ማዕድ ብሎ ያውካካል፡፡ መራመጃ እንኳን አልነበረም፡፡ ግጥም ብሎ በሰው ተሞልቷል ቤቱ ደግሞ ለክፉት ስልኩ ስር ያለች ኩርሲ ላይ እማማ በላይነሽ የሚባሉት የሰፈራችን ነገረኛ ባልቴት ተቀምጠዋል፡፡ ግና ከመግባቴ ለከፉኝ፡፡

"አቡዬ አንተም መጣህ!...ና እለፍ በዚህ!" አሉኝ፤

የደወለችው ትዕግስት ነበረች፡፡ በሆነ ነገር ተደባብረን ስለነበር አትደውልም ብዬ ነበር፡፡ ትዕግስት በባህሪዋ ጫጫ ናት፡፡ እንከዋን የሚፈጥህ ስልክ ጋር ተዳምራ! የስልክ ንግግር ሳይሆን ለዛ ሁሉ ሰው እዋጅ የምታውጅ ነበር የምትመስለው፡፡

"አብርሽዬ!"

"አቤት!" አልኩ ኮስተር ብዬ፡፡ ፀበል ቀማሹ ሁሉ ወሬ ቅመስ ተብሎ የተጠራ ይመስል ጭጭ ብሎ ጆሮውን ቀሰረ፡፡

"አብርሽ ምነው ጨዋ ሆንክ?" አለችኝ ትዕግስት፡፡ ልክ እንደ ሬዲዮ ድራማ ፀበልተኛው ይሰማል፡፡

"እ!"

"አብርሽ ችግር አለ...? ትላንት ከንፈርህን ስለሳምኩህ ደበርኩህ?"

እግዚአአአአአአአአ! ስልኩ አጠገብ የኪዳነ ምህረት ስዕል ተቀምጧል፤

"ኪዳነምህረት የዚችን ልጅ አፍ ወይም የፀበልተኛውን ጆሮ ከዘጋሽልኝ የዛሬ ወር አንድ ፓኮ ሻማ"ብዬ ተሳልኩ:: ስልኩን በጆሮዬ ለማፈን ወደ ጆሮዬ ጥብቅ አድርጌ አስጠጋሁት::

ትዕግስት ትቀባጥራለች::

"...አብርሽ እኔኮ ሴክስ እናድርግ ስትለኝ እንቢ ያልኩህ ፈርቼ ነው፤ በናትህ አብርሽ...እሽ በቃ አርብ አከስቴ ቤት አድሬያለሁ ልበልና አንተም አመቻችተህ..."

እማማ በላይነሽ ወሬ እያዳመጡ ፉት ያሉት ጠላ ሰርናቸው ውስጥ ገብቶ ትን አላቸው:: ከኩርሲያቸው ላይ እስኪፈነገሉ ተንፈራፈሩ:: "...ውሃ ውሃ ስጧቸው ! ጀርባቸውን ምቷቸው!" ይል ጀመረ ፀበልተኛው:: እኔም የአባዬን ስልክ ዘግቼ ቀስ ብዬ ወጥቼ ተፈተለኩ፤ ወደ ቤቴ::

ወዲያው ሰፈሩ ውስጥ ዝናዬ በመወራቱ እናቴ አበደች...

"እንዴት ታዋርደኛለህ! እንዲህ ላገር መሳቂያ ታደርገኛለህ፣ አብረሃም?! ... አባቱ ባይኖር ሴት ቢያሳድገው ልታስብለኝ ....!" እያለች እንባ እየተናነቃት ስትገስፀኝ በመሐሉ ቢጣ ተጣራች::

"ሶስና...ሶሲ ...ስ...ል...ክ ጋሼ አይደለም ! ሌላ ሰው ነው !":: እናቴ በድንጋጤ ውሃ ሆነች፤ ሶስና ትንሿ እህቴ ናት:: የሰባተኛ ክፍል ተማሪ ፤ ሶሲ ጎረመሰች ፤ በእህቴ መጎርመስ እኔ እና እናቴ መደፈር ተሰማን:: እናግራ ስትመለስ ልንወርድባት ተዘጋጀን!

# 10 ሁለት ብር ስንት ዶላር ነው ? (እንዴን ወንዝ ሁለት ጊዜ ስንሻገራት)

ከአስራ አንድ ዓመታት በፊት ደሀ ነበርን:: ያጣን የነጣን፣ ሙልጭ ያልን ነጭ ደሆች:: ከድህነታችን ከብደት የተነሳ ስንት ሰዓት ላይ እንደምንበላ ሳይሆን ስንት ሰዓት ላይ ርሀባችን ጋብ እንደሚል ነበር ዘወትር የምናስበው:: እኔና እህቴ ትምህርት ቤት፣ "አበበ በሶ ባላ" የሚል ምሳሌ 'ቲቸር' ሲናገሩ በመጎምጀት ምራቃችንን እንውጥ ነበር::

ቤታችን ውስጥ አንድ የረገበ የሸቦ አልጋ፣ ሁለት የሳር ፍራሾችና አራት የተወላገዱ ኩርሲ ወንበሮች ብቻ እንደነበሩን ዛሬም ድረስ እናቴ ሳጥን ውስጥ ያሉት ታሪካዊ ፎቶዎች ያሳብቃሉ :: ግድግዳ ላይ ገና እንደተረገዘኩ የሞተ አባቴ ፎቶግራፍ የዘመን ጥቀርሻ እንዳወየበው በላስቲክ ተለብዶ ተሰቅሏል::

እንግዲህ ቤታችን ሁለት ክፍል ነበረች:: አሁን የነገርኳችሁ የሳሎናችንን (ወጉ እንዳይቀር) ይዞታ ነው:: ወደጓዳ ስትገቡ ውስጣቸው የእንጀራ ላስቲክ ብቻ ያለባቸው ሁለት ትልልቅና አሮጌ የእንጀራ መሶቦች ታገኛላችሁ:: ጠርዛቸውን በደህና ቀን አይጥ የቸረቸፈው !!

ሁለቱም ሁልጊዜ ባዶ ነበሩ (አይጦች ከልጆቻቸው ጋር በእነዚህ መሶቦች አጠገብ ሲያልፉ ለልጆቻቸው እንዲህ እያሉ ታሪክ የሚያወሩላቸው ይመስለኛል:: "በድሮ ጊዜ በአያቶቻችን ዘመን፣ እነዚህ መሶቦች ውስጥ ተበልቶ የማያልቅ እንጀራ ነበር:: የዛሬን አያድርገውና ለሰንቱ የአይጥ ሰርግ ድግስ የበቃ - ወይ ጊዜ መሶብም እንደ ዓለማያ ሀይቅ ይደርቃል !"

እናቴ ታዲያ አማኝ ናት:: በየሦስት ቀኑ መሶቡ ውስጥ የሚቀመጡትን የእንጀራ ላስቲኮች እያጠበች አድርቃ ወደ መሶቡ ትመልሳቸዋለች:: "በረከት ሲመጣ አዋጅ አያስነግርም፣ ድንገት ከተፍ ቢል ተዘጋጅተን መጠበቁ ደግ ነው" ትላለች:: ይሄን መራር ሰብከቷን አልወደውም - ግን ትንቢቷ ሰመረ::

እናቴ ነብይ ነበረች:: ደሀ ነብይ በቤቱ አይከበርም፣ እናትም ብትሆን !! አከበርናትም አላከበርናትም ትንቢቷ ሰመረና በረከት እንደሙብረቅ ወረደብን:: (ምናባቴ ልበል ታዲያ) በስድስት ወር ውስጥ

መክከለኛ ገቢ ካላቸው ጎረቤቶች ተርታ ተሰለፍን፡፡ ጎረቤቱ ጉድ ብሎ ሳያባራ፣ በዓመቱ ምን የመሰለ ቤት ሰራን - ባለ አምስት ክፍል ዙሪያውን በግንብ የታጠረ፡፡ አጥሩ፣ ሰው እንዳይመጣብን ሳይሆን፣ በለመደ አግራችን ልንቀላውጥ እንዳንሄድ ራሳችንን ከነበረ ልምዳችን መከለያ ይመስላል፡፡

በተለይ ገና ሀብታም እንደሆንን አካባቢ አኗኗሩን እንላመደው ብለን ተቸግረን ነበር፡፡ እንግዲህ የዚህ ድንገተኛ ለውጥ ምክንያቱ እህቴ ፈረንጅ ማግባቷ ነበር (ደግ ፈረንጅ)፡፡ እንዴት እንዳገባችው (ይቅርታ እንዳገባት) ላውራችሁ፡፡ ከትምህርት ቤት እየመጣች፣ ልክ ኡሰማን ሱቅ አካባቢ ስትደርስ፣ ፈረንጁ መኪናውን ፊጭጭጭጭ አድርጎ አቆመና "አ…ማይ…ጋድ" በማለት የእህቴን ውበት አደነቀ፡፡

በበኩሌ የእህቴ ውበት የፈረንጅ መኪና ማስቆም ቀርቶ የራሷን ሳንቲም 'ሆጭ' አድርጋ ከፍላ የምትሳፈርበት ታክሲ እንኳን እጇን ብትዘረጋ የሚቆምላት አይመስለኝም ነበር፡፡ ግን ምን ይደረግ፣ ፈረንጆች ነገራቸው ሁሉ ግራ ነው፡፡ መኪናውን እዛው ጥሎት እህቴን ተከትሎ ቤታችን ድረስ መጣ፡፡

እናቴ ለዕርዳታ የመጣ መስሏት፣ ከዓይኖቿ 'ትራጄዲ' ብርሀን ለቀቀች፡፡ የመንደራችን እንግሊዝኛ አዋቂ (የእህቴም ወዳጅ ብጤ) ሲራጅ ተጠርቶ መጣና ፈረንጁ ምን እንደሚል ተረጎመልን፡፡ "እሷን ማግባት እፈልጋለሁ" ነው የሚለው አለ ቅር ብሎት - ወደ እህቴ እየጠቆመ፡፡

እናቴ ባለማመን፣ "ማንን እጅጋየሁን" አለች፡፡ (እህቴ እጅጋየሁ ነው ስሟ)

"አዎ…ሌላ ማን አለ ታዲያ እማማ አረጋሽ" ሲራጅ ተነጫነጨ (እህቴ ጋር ማታ ማታ እዛ እንጆሪዋ ዛፍ ስር ይቆሙ ነበር) እናቴ፣ አንዴ ፈረንጁን፣ አንዴ እህቴን ስታይ ቆየችና፣

"ሲራጅ…ግን…እንግሊዘኛ በደንብ ታውቃለህ ?" ስትል ባለማመን ጠየቀች፡፡ ፈረንጁ ግን ወደ እህቴ እየጠቆመ በተኮላተፈ አማረኛ "ኮንጆ…ኮንጆ.." በማለቱ "ይሄ ሰው አምርሯል" አለች እናቴ፡፡ ያው ጉዳዩ የፈጀውን ጊዜ ፈጅቶ በአንድ ወር ውስጥ ተጋቡ፡፡

ይሄ ፈረንጅ (ይቅርታ የእህቴ ባለቤት) ታዋቂ የታሪክ ተመራማሪም ነበር፡፡ይሄን የሰማሁ ቀን፣ "እህቴ ከመከሳቷ የተነሳ ሉሲን መስላው ይሆን" ብዬ አሰብኩ፣ ወይስ እህቴ ይሄን ሚስኪን ፒተር ማንትስ ምናምን አስነካችው…፡፡ከተማውን የሞሉት ቆነጃጅት ሁሉ ፒተርን ሲያዩ ተብድረው የሚሰቁ፣ መቃመጫቸውን እንደባንዲራ የሚያውለበልቡ፣ እንደ አቦሸማኔ ሽንጣቸውን እየመዘዙ እማላይ ሊሆኑ የሚደክሙ ስለምን ለዓይኑ አልሞሉም ? ግዴላችሁም ይሄ ፒተር ጤነኛ አይደለም፣ ጉዳይ ዘመን የሌለው አፅም ሲያገላብጥ፣ ተዘግቶ የኖረ ዋሻ ሲበረብር አንዳች ነገር ተጣልቶታል፡፡

እንዲት የከርዳዳ ፀጉሯ ቁማታ አዳማ ድረስ የሚሰማ፣ በመረገጥ ብዛት ሶሉ ተረከዙ ላይ የተሸነቆረ ነጠላ ጫማ የምትጎትት ሴት በልዕልት ሂሳብ የሚያሳይ፣ ሰይጣነ መነፀር ዓይኑ ላይ የለጠፈበት ነገር አለ፤ እንጂ እህቴ ላይ እንዲህ ሙጭጭ ባላለ፡፡ ሚስኪን ፒተር ቤት መጥቶ

ስለ ዘመናዊ ... በላይ ቆጭ ብሎ እህቴን ዓይን ዓይኗን ሲያይ በእውነት እንደቢጋ ዘመኗ እዛች ጠማማ ዱካ ላይ ቆጭ ብሎ እህቴን ዓይን ዓይኗን ሲያይ፣ በእውነት እንደቢጋ ዘመኗ አንጀቱ ይንሰፈሰፋል::

እንግዲህ ይሄ ፈረንጅ እህቴን ጠቅልሎ ከመውሰዱ በፊት፣ ትምህርቷን እንድትጨርስ ተብሎ ለሁለት ዓመት እዚሁ ተቀመጡ:: ፒተር ታዲያ በየስድስት ወሩ እየመጣ ቤታችንን ግምጃ ከማድረጉም በላይ፣ ይሄን ዶላር ልኬ ልሙት አለ ! ይልካል፣ ይመነዝራል:: ይልካል፣ ይመነዝራል ወላ በጥቁር፣ ወላ በነጭ ገበያ እየተመነዘረ ዓለማችንን አየን:: ሰልካችን ከፈረንጅ ጎረቤቱ "እህ አብርሃም ወደ ባንክ ሊሮጥ ነው" ይላል:: ቤታችን እግር የጣለው ሰው ሁሉ በሞቴ እኔ ስሆን ተብሎ ተጋብዞ ነው የሚሄደው:: የእንግዳ ማረፊያ፣ የአብርሃም ድንኳን !! በየቀኑ በ አያሉ የሚመፀወቱ የኔ ብጤዎችም ብዙ ነበሩ:: አንዳንዶቹማ ደንበኛ ከመሆናቸው ብዛት "ስለመብርሃን" አይሉም:: የግቢያችንን በር ያንኳኳሉ፣ በቃ በልተው ጠጥተው ይሄዳሉ::

እንደውም አንዱ የኔ ብጤ መመፅወቱን መብት አድርጎት፣ "ምነው ዛሬ ጨጨን አሳነሳችሁት ብሎ እስከመቆጣት ደረሰ:: ይሄው ሰውዬ ሌላ ቀን የጎድን አጥንት ስለተሰጠው አኩርፎ ሳይመርቅ ሄደ:: እናቴ እንደገና ጠርታ፣ ወዙ የሚፍለቀለቅ ቅልጥም ሰጠችው:: ደስ ብሎት፣ "በዚ የሚያይሽ ቅልጥሙ ይሰበር" ብሎ መረቃት::

ይሄ ሁሉ ርዝቅ ሲመጣ፣ ግቢያችንን በሞላው የበረከት ውሀ ድሎት ሲዋኝ፣ "ደሀ ብር አየማ ሲቆጥር ይጥላል" እንደሚባለው የእህቴ ፀባይ ይቀያየር ጀመረ:: ልብሷን ለባብሳ፣ በርሳዋ አንጠልጥላ ጧት የውጣች ማታ ትመለሳለች:: ድሮ ከሰው የማይቆጥሯት ጎረምሶች ሁሉ እንደጥላ ከስሯ አንጠፉ አሉ:: እሷን ብለው ሳይሆን የፈረንጅ ሚስት ጋር ዋልን ለማለት::

እጅግዬ፣ እጅግሻ፣ ጂጂ፣ ጃ፣ ጆ፣ ጅን፣ ጅንእድ (ካፒታሏን ይሆን?) በቃ ስሟ ፍዳውን አየ:: በዚህ ዘመቻ ፈታውራሪው 'ሲራጅ' ነበር (ተከተለኝ ወደ እጅጋየሁ ልዘምት ነው...):: የእህቴ ድፍረት ገደቡን ጣሰና ጭራሽ አርግዛ ቁጭ:: ደግነቱ በዚያ ዓመት የእናቴ አምላክ የፒተርን እግር ያዘው::

እናቴ መጀመሪያ አርግዝናው ከፒተር መስሏት ነገር ልታበላሽ ነበር:: "ለፒተር ንገሩልኝ ደስ ይበለው፣ 'ዓይንህን ባይንህ ልታይ ነው' በሉልኝ" ምናምን...! ልጅቱ ስትወለድ ከፆታዋ በስተቀር ቁርጥ 'ሲራጅን' !! (የመንደራችን ነገረኛ ሴቶች ግር ብለው 'ላንግዌጅ' ትምህርት ቤት ተመዝገው ይሄን ጉድ ለፒተር ለመንገር !!) ጉዳዩ ተሸፋፍኖ፣ ተደባብሶ 'ሾላ በድፍን' - የስድስት ወር ልጇን ለእኛ ጥላ እህቴ አሜሪካ ገባች::

ሕፃኗን እልም ያለ ገጠር የምትኖር አክስታችን ጋር ላክናት:: ሲራጅ "የገጠራቱ ኢትዮጵያ ሕፃናት የትምህርትና የጤና ዕድል የማግኘት ዕድላቸው እናሳ ነው" አለ...ሃሃሃሃ (ሰውየው እሱ ከሚስቱ ውጭ ፋጤ ከምትባል ሴት በድብቅ ወልዶ ልጁ ሞተ ብለው አረዱት:: ሚስቱ ፊት አያለቅስ ነገር ቸገረው:: ዝም አይል ነገር ልጁ ሆኖበት እና ምን አለ፣ "እጅብ እላህ የፋጤን ልጅ ትገልባት") ሲራጅም ልጀን ገጠር አትላኩብኝ አይል ነገር ቸግሮት፣ ዝም አይል ነገር የአባት

እንጀት ሆነና፣ "እጀብ እላህ የገጠሪቱን ኢትዮጵያ ሕፃናት..." ብሎ አረፈው::

"ሄሎ አብርሽዬ ደርሻለሁ:: ለሲራጅ ደርሻለሁ በልልኝ::" አይዋት እንግዲህ እህቴ ከነስንከሳሯ አሜሪካ ላይ:: እንደነገ ልትበር እንደ ዛሬ ማታ፣ በጓሮ በኩል እንጆሪው ዛፍ ስር ሲራጅ ጋር ቆጭ ብለው አያወሩ:: ሲራጅ አንባውን ሲጠርግ አየሁት:: አሳዘነኝ:: ለስንቱ ልዘን ?!

ሲራጅ ጋራጅ እየሰራ እናቱን ይረዳል፣ እህቱን ያስተምራል:: በፊት ደስ የሚል ቀይ ልጅ ነበር - መልከ መልካም:: ጥቁርቁር ብሷል አሁን:: በየበረሃው ተበላሽቶ የቆመ መኪና ተከትሎ ሲባዝን !!

እዚህ እንጆሪ ዛፍ ስር ሕፃን ሆነን ፣ እኔ፣ እህቴና ሲራጅ እቃቃ እንጫወት ነበር - ሲራጅ እና እህቴ ባል እና ሚስት ሆነው:: ደግሞ ሲራጅ ከመብሰሉ ብዛት ወደ ጥቁርነት የሚያደላ ያሞከሞከ የእንጆሪ ፍሬ ለእህቴ ይሰጣት ነበር::  ከፍ ስንል እህቴና ሲራጅ አይነ ውሀቸው አላምርህ ሲለኝ ብቻቸውን ተውኳቸው:: ይሄው አሁንም እዛው ቦታ ላይ እህቴ በጋራጅ ስራ የፈረጠመው የሲራጅ ትከሻ ላይ ራሷን ጣል አድርጋዋለች - የሆነ ህልም ነገር ነበር የሚመስለው::

በፊት በፊት፣ እናቴ ሳንቲም ይቸግራትና የዘወትሩን ቡና እንኳን ሳታፈላ በር ላይ ቆጭ ብላ ትተከዛለች:: እህቴ ወጣ ትልና ቡና ዳቦ ምናምን ይዛ ትመጣለች:: ቤታችን ትንሽ ፋሲካ ይሆናል፤ ደስ ብሎን እናድራለን:: ይሄ ነገር አንዴ፣ ሁለቴ ሳይሆን ለዓመታት የተደጋገመ ነገር ነበር::

ሲራጅ ብር እየሰጣት እንደሆነ እኔ አውቃለሁ:: እናቴም ታውቃለች:: ግን "ከየት አመጣሽው?" ብላ እህቴን አትጠይቃትም:: ድህነት ልጇን የመገሰፅ ድፍረቷን ሰልቦት !! ሲራጅ ለእኛ ቤተሰብ፣ በትላንትና እና በዛሬ መካከል የነበረ ድልድያችን ነበር:: እዩት እንግዲህ የእንጨት ድልድዩን አፍርሰን የብረት ድልድይ ስንዘረጋ:: ተመልከቱ እንዱን ወንዝ፣ ሁለት ጊዜ ስንሻገር:: ሳንደፈር የኖርን ማለት ምንድን ነው:: ምድራችንን ፎክረን ለተቀበልናቸው ባዕዳን ሚስቶቻችንን አልቅሰን እናስረከባቸዋለን:: ኡፍፍፍ...ይሄ የነማን ጦርነት ነው - የሲራጅና የፒተር፣ የእበሻና የፈረንጅ፣ የጥቅምና የፍቅር፣ የብረት መዝጊያና የጭራሮ  መዝጊያ፣ የህሊናና የሆድ፣ የነፍስና የስጋ ወይስ የሰውና የፈጣሪ?

*** *** ***

ከአራት ዓመት በኋላ እህቴ መጣች አምሮባት (ፈረንጅ መስላ፣ 'ሰው ማንን ይመስላል ቢሉ ኑሮውን'):: አገር ምድሩን ጉድ ያሰባለ መኪና:: አንድ ቸኮሌት የመሰለ የሁለት ዓመት ሕፃን ልጅ - ይዛ መጣች::

ባለ ምናምን ኮከብ ሆቴል ፒተር፣ እኔ፣ እሷ እና የሁለት ዓመት ክልስ ልጇ ምሳ እየበላን፣ ፒተር የራሱን ጨርሶ እጁን ሊታጠብ ሲሄድ:: ልጁ ድክ ድክ እያለ አባቱን ተከትሎ ከዓይናችን እንደተሰወሩ፣ እህቴ ወደኔ ሰገግ ብላ፣ "አብርሽ ሲራጅ አሁንም ሰፈር ነው የሚኖረው?" አለችኝ

እፍረት በተቀላቀለበት ጉጉት:: ያስታውቃል በሆዷ አፍናው የኖረችውን እሳት በሰው አገር ስታምሰለስለው የኖረችውን ህመም ዛሬ ከእኔ ከወንድሟ ጋር ልትካፈለው እንደተነፈሰችው ሰው መስያት !!

እውነቱን ለመናገር ሲራጅን ረስቸው ነበር፣ "እኔንጃ ካየሁት ቆየሁ:: የሆነ ሰዓት ላይ ግን ጅዝብ ነበር" እልኳት በግዴለሽነት:: ዩኒቨርስቲ ገብቼ ስለነበር በእርግጥም ካየሁት ሁለት ዓመት አልፎኝ ነበር:: ለመጨረሻ ጊዜ ያየሁት ሰፈር ድንገት ከሥራ ሲገባ ነበር:: ጅዝብ ብሎ ኮሌታቀ የነተበ ሸሚዝ ጉልበቱ እና መቀመጫው ላይ የሳሳ ጅንስ ሱሪ በጥቁር ተረከዟ በተጣመመ ጫማ፣ በእጁ ባንጠለጠላት ፌስታል ሦስት ዳቦዎች ይዞ፣ "እሽ አብርሽ ሥራ ጥሩ ነው" አለኝ ተማሪ መሆኔን ረስቶታል:: ደግሞ አይኔን ማየት አልፈለገም:: እህቴ ያዘጋጀችውን ጉርሻ ወደ ሰሀኑ መልሳ ፍዝዝ ብላ ቀረች::

ፒተር ያመጣልኝን ስልክ እየጎረጎርኩ እህቴን ከትካዜዋ ጋር ረሳኋት:: ፓ እንዴት ቀውጢ ስልክ ነው...!!

"እኔ የምልሽ ይሄ ስልክ ዋጋው ውድ ነው አይደል ?" እልኳት በማዳነቅ:: እህቴ በትዝብት እያየችኝ፣ "ሰባት መቶ ዶላር..." አለችኝ ድምፅዋ ሻክሮ ነበር::

"ወደኛ ብር ሲመነዘር..." ብዬ ሳሰላ...::

"ወደ እኛ ብር ሲመነዘር ሲራጅ ለእማማ ቡና ብሎ ከሚሰጠኝ ሁለት ብር አይበልጥም:: ሲራጅ ለአብርሽ ብሎ ይሰጠኝ ከነበረው እስከርቢቶ አይበልጥም" ብላኝ ወደ መታጠቢያ ቤቱ ሄደች፣ ፒተርና ልጁ ታጥበው ሲወጡ እሷ ልትታጠብ ስትሄድ መንገድ ላይ ተላለፉ:: ፒተር ፈገግ አለላት፣ እህቴ እንደማታውቃቸው ዝም ብላ አልፋቸው ሄደች::

ሲራጅ እስከርቢቶ ይልክልኝ እንደነበር ትዝ አለኝ:: ያኔ በልብስ፣ በጫማ፣ በደብተር መያዣ ቦርሳ ይበልጡኝ የነበሩ ሕፃናትን የማስቀናበት ብቸኛ ንብረቴ ሲራጅ ያመጣልኝ የነበረው ቀይ እስከርቢቶ ብቻ ነበር:: ሙሉ ቀይ ቢክ እስከርቢቶ::

ስልኩን ጠረጴዛው ላይ አስቀምጬ ወደ መታጠቢያ ቤቱ በትካዜ አመራሁ:: እህቴ እያለቀሰች ነበር:: ከአሜሪካ በመጣልኝ ስኒከር ጫማ ሲራጅ የሚባል አራት ዓመት ተቀብሮ የኖረ ፈንጅ ረገጥኩ:: ሲመቸን የምንረግጠውን እናውቅ ! ረገጥኩት - ቡምምምምምምምምምምምምም... ቁስለኛ እህቴ፣ ሙት እህቴ!

አፍረት በተቀላቀለበት ጉጉት:: ያስታውቃል በሆዱ አፍናው የኖረችውን እሳት በሰው አገር ስታምሰለስለው የኖረችውን ህመም ዛሬ ከእኔ ከወንድሟ ጋር ልትካፈለው እንደተነፈሰችው ሰው መሲያት !!

እውነቱን ለመናገር ሲራጅን ረስቸው ነበር፤ "እኔንጃ ካየሁት ቆየሁ:: የሆነ ሰዓት ላይ ግን ጅዝብ ነበር" አልኳት በግዴለሽነት:: ዩኒቨርስቲ ገብቼ ስለነበር በእርግጥም ካየሁት ሁለት ዓመት አልፎኝ ነበር:: ለመጨረሻ ጊዜ ያየሁት ሰፈር ድንገት ከሥራ ሲገባ ነበር:: ጅዝብ ብሎ ኮሌታዋ የነተበ ሸሚዝ ጉልበቱ እና መቀመጫው ላይ የሳሳ ጅንስ ሱሪ በጥቁር ተረከዟ በተጣመመ ጫማ፣ በእጁ ባንጠለጠላት ፌስታል ሦስት ዳቦዎች ይዞ፣ "እሽ አብርሽ ሥራ ጥሩ ነው" አለኝ ተማሪ መሆኔን ረስቶታል:: ደግሞ አይኔን ማየት አልፈለገም:: እህቴ ያዘጋጀችውን ጉርሻ ወደ ሰሀኑ መልሳ ፍዝዝ ብላ ቀረች::

ፒተር ያመጣልኝን ስልክ እየጎረጎርኩ እህቴን ከትካዜዋ ጋር ረሳኋት:: ፓ እንዴት ቀውጢ ስልክ ነው...!!

"እኔ የምልሽ ይሄ ስልክ ዋጋው ውድ ነው አይደል ?" አልኳት በማዳነቅ:: እህቴ በትዝብት እያየችኝ፣ "ሰባት መቶ ዶላር..." አለችኝ ድምፅዋ ሻክሮ ነበር::

"ወደኛ ብር ሲመነዘር..." ብዬ ሳሰላ...::

"ወደ እኛ ብር ሲመነዘር ሲራጅ ለእማማ ቡና ብሎ ከሚሰጠኝ ሁለት ብር አይበልጥም:: ሲራጅ ለአብርሽ ብሎ ይሰጠኝ ከነበረው እስከርቢቶ አይበልጥም" ብላኝ ወደ መታጠቢያ ቤቱ ሄደች፡ ፒተርና ልጇ ታጥበው ሲወጡ እሷ ልትታጠብ ስትሄድ መንገድ ላይ ተላለፉ:: ፒተር ፈገግ አለላት፣ እህቴ እንደማታውቃቸው ዝም ብላ አልፋቸው ሄደች::

ሲራጅ እስከርቢቶ ይልክልኝ እንደነበር ትዝ አለኝ:: ያኔ በልብስ፣ በጫማ፣ በደብተር መያዣ ቦርሳ ይበልጡኝ የነበሩ ሕፃናትን የማስቀናበት ብቸኛ ንብረቴ ሲራጅ ያመጣልኝ የነበረው ቀይ እስከርቢቶ ብቻ ነበር:: ሙሉ ቀይ ቢክ እስከርቢቶ::

ስልኩን ጠረጴዛው ላይ አስቀምጬ ወደ መታጠቢያ ቤቱ በትካዜ አመራሁ:: እህቴ እያለቀሰች ነበር:: ከአሜሪካ በመጣልኝ ስኒከር ጫማ ሲራጅ የሚባል አራት ዓመት ተቀብሮ የኖረ ፈንጅ ረገጥኩ:: ሲመችን የምንረግጠውን እናውቅ ! ረገጥኩት - ቡምምምምምምምምምምም ቁስለኛ እህቴ፣ ሙት እህቴ!

# እግዚአአአአአአአአአ 11

እማማ የውብዳር ጓደኛዬን ያሬድን ልጅ ልከው አስጠሩት እና እንዲህ አሉት፡-

"ያሬድ ምንስ ባልወልድህ እናትህ አልነበርኩም ? እሳድጌ አሳድጌ እንዲህ ከሰው በታች ታደርገኛለህ...?"

"ምን አደረኩ እማማ የውብዳር...?"

"እሄሄ...! የምትከፍለው የላትም፣ ያጣች የነጣች ደሃ ናት ብለህ ነው...!?"

"ኧረ እኔ ለማንም እንደዚህ አላልኩም !" አለ ግራ ገብቶት እኔን እየተመለከተ፡፡ አላለም እንድልለት ፈልጓል፡፡

"ነው እንጂ !! ምን የመሳሰለ የመልአከ፣ የፃድቃን ሰማእታት ሥእል በየሰዉ ቤት ስትስል፣ የኔን የየውብዳርን ቤት ሰይጣን ይፈንጭበት፣ ዲያቢሎስ ከነሠራዊቱ ይፈንጭበት፣ ሌጌዎን እስከስታ ሲያወርድበት ውሎ ይደር ብለህ ነው የእኔን ቤት ለይተህ የተውከው?!" አሉት በትዝብት እያዩት፡፡ እንደሚጠቀሟቸው ቃላት ከብደት ግን ድምፃቸው አያስፈራም ነበር፡፡ እንደውም የሆነ የሚያስቅ ዜማ ነበረው፡፡

"እእእ...ለዚህ ነው እንዴ ...ኧረ ጣጣ የለውም ከፈለጉ ከማንም አስበልጬ የፈለጉትን እሥልሎታለሁ!" አለ ፀጉሩን እያፍተለተለ በፈገግታ፡፡

"ተባረክ የኔ ልጅ...! ብሩክ ሁን !!"

"አሜን" አለ ያሬድ፡፡

"እኔ ደሞ እንዲህ ትልቅ ባለሙያ መሆንህን የት አባቴ አውቄ ! መንደር ለመንድር እዚህ ቦዘኔ ጋር ተያይዘህ ስትዞር (እኔን በአገጫቸው እየጠቆሙ) 'አይ መባከን !' አላለሁ፡፡ ለካ አንተ

እንዲህ አጀ ወርቅ ነህ፡፡ ገና ትላንት አይደለም እንዴ የሰማሁት...፤ እች ማናት ኮማሪዋ...እዚህ ታክሲ መቆሚያው ጋ ድራፍት ቤት ያላት...ኤዲያ ስሟ አይያዝልኝም..." እያሉ እንዴ መሬት እንዴ ሰማይ ሲመለከቱ፤

"ናርዶስ !" አልኩ ሳይጠይቁኝ፡፡

ፈገግ ብለው "እ...ዎ ናርዶስ" አሉና ወሬያቸውን ሊቀጥሉ ካሉ በኋላ የሆነ ነገር ትዝ እንዳለው ሰው ኮስተር ብለው ወደኔ በመዞር "ደህና ሰው ቢጠይቅህ አታውቅም እንጅ ኮማሪና ሜት ነጋዴማ አይጠፉህም" አሉኝ፡፡

ያሬድ አቀርቅሮ በሳቅ ፍርስርስርስ !! ኮማሪና ሜት ነጋዴ ደህና ሰው አይደለም ያለው ማነው?

"... እናልህ እሷ ቤት የሳልከውን የጊዮርጊስ ሥዕል በቀደም መሃበርተኛው ሁሉ እያየ ጉድ ሲል...'ማነው የሳለው ?' ብላቸው የጉልላት ልጅ አሉኝ...እሃ ጉልላት እች የኔ ጉልላት? ...እሱማ ምን የጉልላት ልጅ ነው? የኔው የራሴው ልጅ አይደለም እንዴ ? ብዬ መጣሁልህ፡፡ ሙችስ ባልወልድህም ልጄ ነህ፤ ንፍጥህን ጠርጌ ያሳደኩህ" አሉ፡፡

"ልክ ነው" አለ ያሬድ እየተቅለሰለሰ፡፡

"እሁ እሁ እሁ እሁ እ ሁ..." ብለው ሳል የሚመስል ሳቅ ሳቁና ቀጠሉ፤

"...መቸስ ያ...ጊወርጊስ ማንም ቤት የለ !! የፈረሱ ግርማ ሞገስ...የዘንዶው ርዝማኔ_ነብስ ያለው እኮ ነው የሚመስለው ! ተባረክ ! ...መሃበርተኛው ሁሉ ነው የመረቀህ፡፡ ሙችስ የእኛ መሃበርተኞች ምርቃት ብቻ የት እና የ....ት እንደሚያደርስህ...!! ቀላል ማኅበር እንዳይመስልህ! የዚች የ....አስተማሪዋ ልጅ ማነው ስሙ?" ስሙ ጠፋቸው፤

"አድማሱ" አልኩና አስታወስኳቸው፡፡

"አንተ ሌላም ሥራ የለህ የመንደርተኛ ስም አጥና" ብለው ከወረፉኝ በኋላ ወሬያቸውን ቀጠሉ፤ "እናልህ እሱ የዛሬ ሦስት ዓመት እኛ ማኅበር ላይ ምን የመሰለ የፅዋ ልብስ አምጥቶ ሰጠ - ስአለት ነበረበት፡፡ ታዲያ መኅበርተኛው አንድ ባንድ መረቀው፡፡ አሁን አማሪካ ነው ያለው፡፡ አንቱ የተባለ ሃብታም ሁኗል አሉ፡፡ በሦስት ዓመት! ሰው በሰላሳ ዓመት የማይደርስበትን ቂብ ብሏል፡፡" አሉና ስለ ማኅበራቸው ምርቃት ከፍ ያለ ዋጋ በዝርዝር ማስረጃ እያጣቀሱ አወጉ፡፡

"አሁን እንኳን የጠራሁህ እ..." ስሙ ጠፋባቸው፡፡

"ያሬድ" ብዬ አስታወስኳቸው፡፡

በብስጭት እየተመለከቱኝ "ወቸ ጉድ ! ባለቤቱ እያለ አንተ ቱሩጁማን ነህ ?..." ያሬድ አሁንም

በሳቅ ፍርስስስ - እንዳቀረቀረ !

ከዚህ ጊዜ በኋላ ለረዥም ጊዜ 'ቱረጁማን' እያለ ይጠራኝ ነበር::

"...አሁን የሚመጣው ታህሳስ በ27 የኔም የመድኃኒያለም ዝክር አለች:: እንደው የመድኃኒዓለምን ሥዕል...ይሄ...ቤት የሚያንኳኳበትን እንድትሥልልኝ ነበር..." አሉት::

"ፒስ !" አለ ያሬድ::

"ምናልከኝ ?"

"ጣጣ የለውም !" አላቸው ፈጠን ብሎ::

ያሬድ ሥዕል ሳልልን ሲሉት ሲነጫነጭ ነበር የማውቀው:: አሁን ፈጠን ብሎ መስማማቱ ገርሞኝ ቀጥ ብዬ ተመለከትኩት:: ፊቱ በፈገግታ ተጥለቅልቆ ነበር:: "እችን ሴትዮ ቀልቡ ወዷቸዋል ማለት ነው" ስል አሰብኩ:: በሥዕሉ ተስማሙና ለያሬድ ቀብድ መቶ ብር ሰጡት::

***     ***     ***

ያሬድ ጓደኛዬ በጣም ጎበዝ ሠዓሊ ነው:: "ሞናሊዛን በግራ እጄ እስላታለሁ" ይላል ችሎታው ላይ ጉራ መርቆበት ሲያወራ:: ሥዕል አልተማረ፤ ሠዓሊ ዘመድ የለው፤ ሥዕል ሲሳል አይቶ አያውቅ - ከመሬት ተነስቶ ሠዓሊ ሆነ:: ከመሬት የተነሳነው እንኳን አብረን ነበር:: እርሳስ ይዘን የሴት ምስል መሣል ጀመርን:: እኔ የምስላቸው ሴቶች እግራቸው አያርፍም፤ አንዴ ወደግራ ይንሻፈፋሉ፤ አንዴ ወደቀኝ ይወላገዳሉ...ሌላ ጊዜ ቀኝ እግራቸው አረፍ ይሆንና ግራው ይዘነፋል - በተለይ የሱሪ ለባሽ ሴቶችን ሥሥል አልሆንልህ አለኝ::

ያሬድ ታዲያ "አንተ እርፈህ ቀሚስ ለባሽ አትስልም እንዴ...ቀሚስ እንኳን ያንተን ቀሽም የሥዕል ችሎታ የስንቶቹን ደጋን እግር ሸፍኗል" ሲለኝ ከዚህ ሁሉ ከወገብ በላይ ብስላቸውስ ብዬ ስሞክር አሁንም እኔ የምሥላቸው ሴቶች አይናቸው አያርፍም፤ ይንሸዋረራሉ፤ ይጠናገራሉ:: ፊት ለፊታቸው የልብ ቅርፅ እሥልና ወደልቡ እንዲያዩ ላደርጋቸው ስሞክር አይናቸው የእኔን ልብ ትቶ ያሬድ ከጎን ወደሳለው መኪና ይመለከታል:: ሰለቸኝና እርግፍ አድርጌ ተውኩት:: ያሬድ "መክሊትህ አይደለም በቃ!" ሲለኝ ጭራሽ ተስፋ መቁረጤ ጉልበት አገኘ::

ያሬድ ግን ከሴቶቹ ሥዕል ወደ ሞናሊዛ አደገ:: ይባስ ብሎ ቅድስት እርሴማን ሁሉ ቁልጭ አድርጎ ሳላት::እንደውም በእጇ የያዘችውን ፅዋ ረስቶት እኔ አስታውሼው ነው የሣለው:: ከዛ ድንግል ማሪያምን ልጇን እንዳቀፈች ሣላትና መንደርተኛው ሁሉ "...ይሄ ልጅ የት ይደርሳል" እያለ ሲጠብቀው ሰላማዊት ለምትባል ስምንተኛ ክፍል እራት አመት ለደገመች ልጅ "ወደ ዘጠነኛ ክፍል ተዘዋውራለች" የሚል 'ፎርጅድ' ካርድ ሲሰራ ተይዞ ሁለት ዓመት ታሰረ::

በዕርግጥ ያሬድ በጣም ጎበዝ ከመሆኑ የተነሳ ሰላማዊት ራሷ የእውነት ወደ ዘጠነኛ ክፍል ያለፈች መስሏት እኔና ያሬድን ምሳ ጋብዛናለች:: "ወጣ ወጣና እንደሸንበቆ ተንከባለለ እንደ ሙቀጫ" እንዲሉ ያሬድ ማረሚያ ቤት ሰነበተ::

ከእስር ቤት ሲወጣ ፍልስፍና ጀምሮ ነበር:: በተለይ ከእግዚያብሔር ጋር 'መሳፈጥ' አበዛ:: ኧረ እንደውም ከሥዕሉ ወደ ፍልስፍናው አዘነበለ:: አገር የሚያክል ሸራ ይወጥርና ምን ተዓምር ሊሥል ነው ብዬ ስጠብቅ መሐል ላይ አንዲት በዓይን እንኳን ለማየት የምታስቸግር ጥቁር ነጥብ ብቻ ጠብ አድርጎ "ጨረስኩ" ይላል::ብስጭት ብዬ "ምንድን ነው ይሄ ?" እለዋለሁ:: ራቅ ብሎ ሸራውን በትኩረት ሲመለከት ይቆይና "...በዚህ ግዙፍ ዓለም ላይ የሰራኸውን ብትሰራ ነጥብ ነህ...፤ ሌሎች ነጥቦች ጋር ካልተደመርክና ካልተሰለፍክ መስመር የለም ሥዕል የለም...፤ ሁለት ዓመት ስታሰር እኔ ማለት እች ነጥብ ነበርኩ" ይላል:: ብሩሹን አነሳና ከነጥቧ ጎን አንዲት ሌላ ነጥብ አስቀምጥና "እኔ ነኝ" እለዋለሁ፤ እንሳሳቃለን:: ወጣ ብዬ ስመለስ ግን እኔ ሸራው ላይ የለሁም:: መስመር መሆን ካልፈለገ የራሱ ጉዳይ ብዬ እተወዋለሁ !

እየቆየ ያሬድ የሚሥላቸው ነገሮች ሁሉ ግራ አጋቢ ሆኑ:: አንደኛው ዓይኗ ሰፌድ፣ ሌላኛው አይኗ አስር ሳንቲም የሚያክል፣ ቁመቷ ከመርዘሙ ብዛት ዛፍ የመሰለች ሴት ይሥልና "ሰው እድሜው በጨመረ ቁጥር ዕይታውም ይሄው ነው፤ አንድ ዓይንህ ከዘመንህ ጋር ያድጋል፣ አንድ ዓይንህ ግን የማያድግ፣ የማይቀየር፣ ትላንትህን ብቻ እየተመለከተ እስከ ዕለተ ሞትህ ይኖራል" ይለኛል፤ ምኑም አይገባኝ::

ይቀጥላል የያሬድ ሥዕል:: አንድ ቀን ማሲንቆ ሣለ:: ቋሚው ላይ የቆመችው አንዲት መለሎ ሴት ስትሆን እንደጭራ ቋሚው ጋር ተቋጥራለች:: ከጎኗ ወገቡ የጎበጠ ወንድ ልክ እንደ ማሲንቆ መምቻ ደጋን ተስሏል::

"ይሄ ደግሞ ምንድን ነው?" አልኩት በማናናቅ::

"ይሄስ ምንድን ነው ?" ብሎ መልሶ ጠየቀኝ የእኔን ጭንቅላት በሁለት እጁ ይዞ እየወዘወዘ::

"እናትን ልቀቀኝ ወደዛ" አልኩና ገፋሁት::

እሱ ግን የበለጠ አጥብቆ ይዞኝ "ሁልጊዜ ማብራሪያ አትጠይቅ፣ ሥዕል የሠአሊው ብቻ አይደለም፣ እንደውም የተመልካቹ ነው:: እንደመሰለህ ተርጉመው፣ እንደገባህ ተንትነው" ብሎ ወደ ኋላዬ ገፋኝ፤ ተንገዳግጄ ቆምኩ::

ያሬድ አልጨከነም፤ ስለሥዕሉ እንዲህ አለኝ:-

"ስለፍቅር አንዱ ይቃና ዘንድ አንዱ እንዲጎብጥ ግድ ይላል:: ፍቅር ዝቅ ማለትን ይጠይቃል:: በአንዱ ዝቅታና በሌላው ከፍታ የፍቅር ዜማ ይደምቃል" አለኝ:: ማሲንቆና የማሲንቆ መምቻ፣

ለውና ሰው ሁኖ እንዴት እንደታየው እማዜር ይጠቅሳት:: እንዲሁ ልከራከረው ብዬ "ሻምሊንና የሻምሊን መጫወቻ ዘንጉ ሁለቱም ቀጥ ያሉ ናቸው ግን አሪፍ ዜማ ይፈጥራሉ የግድ መጉበጥ ለምን አስፈለገ ?" ብዬ በንግግሬ በነልነት ትክሻዬን ነቅነቅ አደረኩ::

"ተሳስተሃል ! የሻምሊን ሳጥኑ ትከሻ ላይ ዘና ብሎ እርፎ መጫወቻው ሲንከራተት ነው ዜማ የሚፈጠረው፤ ሁለቱም ሰው ትከሻ ላይ ቀጭ ቢሉ ምንም አይፈጠር ነበር፤ ምንም !" አለና ተነስቶ ወጣ::

***     ***     ***

ጓደኛዬ ያሬድ ታህሳስ 23 የእማማ የውብዳርን የክርስቶስ ሥዕል ስሎ እንደጨረሰ አብረን ወደ ቤታቸው ሄድንና አስረከብናቸው !! ደስ ብሏቸው ፊታቸው በፈገግታ ደምቆ ሁለታችንንም ከመረቁን በኋላ ሥዕሉን የተሸፈነበትን ወረቀት ቀስ አድረገው ገለጡት:: ገልጠው ሲያዩት ቤትዮዋ ግራ ገባቸው !! ራቅ ቀረብ፡ ቀረብ ራቅ እያደረጉ አዩትና ፈገግታቸው ከፊታቸው ላይ ከሰም እንዴ ያሬድን፡ እንዴ እኔን፡ እንዴ ሥዕሉን እያፈራረቁ ቃኙን:: ልቤ በፍርሃት ተውጦ ሲዘል ይሰማኛል::

"ያሬድ!" አሉት

"አቤት ማዘር!" አላቸው በፍፁም መረጋጋት ፀጉሩን እያፍተለተለ::

"ክርስቶስ በር እያንኳኳ አልነበርም የተባባልነው ?"

"ነበር" መለሰ ያሬድ አሁንም ረጋ ብሎ::

ቀረብ...በጣም ቀረብ አድርገው ሥዕሉን በትኩረት ተመለከቱትና...

"እንዲህ ያለ መድሃኒዓለም አይቼም ሰምቼም አላውቅም" አሉ ግራ ተጋብተው::

ያሬድ መለሰላቸው፣ "እሱማ መድሃኒዓለምን ማን አየው ብለው...ያው ቢቃሉ መሰረት እንስለዋለን እንጂ" አለና ያሬድ እስር ቤት የጀመረችውን ፍልስፍና መስኮት ከፈተላት:: በዕርግጥ ያሬድ ሥዕል ሲስል አስተያየት መቀበል አይወድም:: "ማመልከቻ የምፅፍ መሰለህ እንዴ እየነገርከኝ የምስለው?" ይላል:: ቢሆንም ይሄን የእማማ የውብዳርን ክርስቶስ ሲስል "ኧረ ይሄ ነገር እችን ቤትዮ ያሳብዳቸዋል" ብዬው ነበር:: ያሬድ ግን ከሥዕሉ ላይ አይኑን ሳይነቅል..."ንቢቷቸው ካበዱ አንድ ነገር ነው" ብሎ አስተያየቴን አጣጣለው:: ከዛም "የሥዕልም ይሁን የሌላ ኪነጥበባዊ ፈጠራ አላማው ሰዎችን በሰሩት መንገድ ላይ ሲረግጡ እንዲኖሩ ጫማ ማቀበል አይደለም፤ አዳዲስ ጫካዎችን መንጥሮ አዲስ መንገድ መፍጠር ነው፡ ነገሮችን ከተለየ አቅጣጫ ማሳየት ነው:: አዲስ የሕይወት ቅመም፡ አዲስ ጠብ የሚል ፋይዳ ያለው እውነት..."

“ኧረ ባከህ አንተ ልጅ! ለአንዲት ባልቴት የአንተ ፍልስፍና አይገባም፤ ያውም በእምነት ነገሮች ዙሪያ ኢትዮጵያ ውስጥ ብትፈላሰፍ 'እብድ !' የሚል ካባ ነው የሚያስደርብልህ፤ ለዛውም ከዱላ ከተረፍክ ነው” አልኩት::

“ፍልስፍና ዋጋ ያስከፍላል:: ዓለማችንን የቀየሩ ፈላስፎች ዋንጫ አይደለም የተሸለሙት፤ መርዝ የተሞላ ፅዋ እንጂ:: እንዲያውም አልሸሹም፤ በድፍረት ጨለጡት እንጂ:: ስለ እውነት ማፈግፈግ ወደ ምንም መድረስ ነው፤ ደፋር መሆን አለብህ::” እያለ የማያባራ ዲስኩሩን ሲግት 'የራስህ ጉዳይ!' ብዬው ዝም አልኩ:: ይሄው አሁን እማማ የውብዳር ጋር ተፋጠጠ፤ ፈላስፋው ከነተፈላሰፈበት ስዕሉ::

ሥዕሉ አንዲት ከፍል ቤት ውስጥ ያልተነጠፈ አልጋ፣ ግማሽ ብርድ ልብሱ መሬት ላይ ተንዘርዝሮ እዛው መሬቱ ላይ ግማሽ ገፆቹ የተገነጠሉ መጽሐፍ ቅዱስ ወድቋል:: የቆሸሹ ካልሲዎች በየቦታው ተበታትነዋል:: በጣም ብዙ የቢራ ጠርሙሶች በስዕሉ ግራ በኩል ይታያሉ:: የቢራ ጠርሙሱ አጠገብ አንድ እግር የሴት ጫማና የጡት ማስያዣ ወድቋል:: የምታበራ የቃል ኪዳን ቀለበት ደግሞ በጎኑ ከወደቀ የወንድ ጫማ ስር ትታያለች:: የተራቆተች ሴት ሥዕል ከተዘበራረቀው አልጋ በላይ ተለጥፏል:: አልጋው ላይ ከአንሶላ አፈትልኮ የወጣ የሴትና የወንድ እግር ይታያል:: ኮሚዲኖ ላይ በርከት ያለ የአሜሪካ ዶላር ዝርክርክ ብሏል:: ከዚህ ሁሉ መዝረክረክ ፊት ለፊት መሐል ወለሉ ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ በሁለት እጁ እራሱን ይዞ ቆሟል:: ...ይሄ ነው ሥዕሉ!

“ጌታ ራሱን ይዞ ታይቶም ተሰምቶም አያውቅ !” አሉ እማማ የውብዳር ባለማመን:: ቀጠል አደረጉና “ለመሆኑ በሩ የት አለ ? የሚንኳኳው በር የት አለ ?” ሲሉ ጠየቁ በቁጣ::

ያሬድ ጓደኛዬን እስር ቤት የለከፈችው ፍልስፍና ታስለፈልፈው ጀመረች:

“እ...ክርስቶስ በየቤታችን ከገባ ቆየ:: አሁን ይሄን ሁሉ ዘመን ቤታችንን ዘግተን ስናደርግ የቆየነውን ጉድ፣ እንዲሁም የኖርንበትን መዝረክረክ፣ መጨማለቅ፣ ማስመሰል እና መታበይ አይቶ ራሱን ይዞ እግዚዚዚዚዚዚዚዚዮ እያለ ነው....” አላቸው ወደ ሥዕሉ ከተለያየ አቅጣጫ አይኑን እጨንቁሮ እየተመለከተ፣ እንደማማ የውብዳር ክርስቶስ ራሱን በሁለት እጁ ይዞ::

“ምን እያለ ?” አሉ እማማ የውብዳር ግራ ተጋብተው::

“እግዚአአአአአአአአአአአአአአአአአአአአአአአአአ...” ያሬድ አይኖቹን ጨፍኖና ራሱን ይዞ በየቅጣጫው እየዞረ ረዥም እግዚዮታውን ሲያሰማ እኔም ተገርሜ ያሬድን ስመለከት ነበር ከምኔው እንዳነሱት ያላየሁት የእማማ የውብዳር የመጥረጊያ እጀታ ያሬድ ጀርባ ላይ ያረፈው::

ጓደኛዬ ያሬድ በቅፅበት “በአዕምሮ መሮጥ” ከሚለው ፍልስፍና ተመልሶ በእግር ወደ መሮጥ ተሸጋገረ:: ተከታትለን ከእማማ የውብዳር ቤት ወጣንና (እንደውም ያሬድ በሩ ጠፍቶበት

ግድግዳው ጋር ከተጋጨ በኋላ ነበር በሩን እግኝቶት የወጣው፣ ወደ ታች ወደ ወፍጮ ቤቱ ተፈተለከን::

ፈላስፋ ያቀረቡለትን መርገዝ በድፍረት ሲጨልጥ እንጂ እንዲህ እንደ አቦሸማኔ ሲሮጥ ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅም:: ያዘው ! ...እረስቶትል ሮጠ፣ ሶቅራጥስ የነሳራን የልብስ ማጠቢያ ገንዳ ዘለለ፣ ኮንፊሽየስ የእማማ ዙሪያሽን ስጥ ረጋግጦ አለፈ፣ ዲዮጋን በአባ እጅጉ ቤት ወደ ወንዙ ታጠፈ፣ እሾ እንዱን መንገደኛ ቁስ ገፍትሯቸው ፈረጠጠ ...እኔም ተከተልኩ...

“ብጭር ቅር !” እማማ የውብዳር ተራገሙ...

“በመሣበር የመረቁትን በየግላቸው እየረገሙ መሣበራቸው እንዴት ፀንታ ትቆማለች ?” እለ ያሬድ::

“በከሀ እርፈህ ሩጥ:: የፀበሉ ቀን በመሣበር ይረግሙሃል” አልኩት፣ አበሳጭቶኝ ነበር:: እየሸሸ ኢቃቂር ያውጣል እንዴ?!

# 12 ንፋስ ወዴት ነህ ቢሉት ማርና ወተት ወዳለበት

እማማ አረጋሽ ቤት ሩጫ ልናይ ተሰብስበናል:: ልጃቸው ከውጭ አገር ትልቅ ቴሌቪዥን ስላመጣችላቸው በሳቸው ቴሌቪዥን ማየት የሩጫ ጥም ይቆርጣል:: መቸስ ቴሌቪዥን ግድግዳ በሉት:: የእማማ አረጋሽ ቤት ከሦስት ግድግዳና ከአንድ ቴሌቪዥን ነው የተዋቀረው ቢባል ማጋነን አይሆንም:: ባለቤታቸው አቶ ፈንታው ነፍሳቸውን ይማራቸው ዜና ለማየ በየቀበሌው እንደዞሩ ይሄን ዓለም ሳያዩ ሞቱ፤ ሳያልፍላቸው ሞቱ:: "ቁጭ ብለው ቴሌቪዥ በማያ ጊዜያቸው ሞቱ" ይላል ጎረቤቱ::

ጀመረ ሩጫው - ገንዘቤ ዲባባ፣ አበባ አረጋዊ ቴሌቪዥኑን እየሞሉ ደግሞ ራቅ እያሉ...

እኛም "ገንዘቢ...ገንዘብዬ...ገንዘባችን...ሩጭ አሳያቸው...እይዞሽ" እያልን፣ ያው አበባ አረጋዊ ፊት ብላ ወርቁን ወሰደችው:: ያውም የስዊዲን ማልያ ለብሳ በስዊዲን ባንዲራ ተውባ ! ብዙዎቻች ቀዝቀዝ ሰንል እማማ ወለላ "እልልልልልልልልልልልልል እሰይ እሰይ" አሉ (ጎረቤት ናቸው

"እንዴ ለስዊዲን እኮ ነው የሮጠችው" ብንላቸው፣

"ይሁና ልጃችን ናት" አሉ::

እማማ አረጋሽ ታዲያ፣ "አይ ወለላዬ አሁንስ እማማ ፅጌን መሰልሽኝ" አሉ::

ስለ እማማ ፅጌ ለመስማት ጆሯችን ቆመ::

"ማናቸው እማማ ፅጌ ?"

እማማ አረጋሽ ስላነሷቸው ሴት ታሪክ አወጉን...

*** *** ***

በድሮ ጊዜ እኛ ሰፈር እች አሁን ጋሽ እቁባይ ገፋ አድርገው ያጠሯት ቦታ ላይ አንዲት የእማማ ፅጌ ድንጋይ የምትባል ጥቁር ድንጋይ ነበረች - አጠገቧ ደግሞ የላስቲክ ቤት:: አሁንም አጥሩ ውስጥ ድንጋዩ አለ:: ታሪኩን ቢያጥሩት ያው አጥሩ ውስጥም ሁኖ ቢሆን ይጮሃል::

እማማ ፅጌ አንዲት ልጅ ነበረቻቸው:: መቼስ ቁንጅናዋ አይወራም:: መልአክ፣ መልአክ በሏት:: አንዲት ልጃቸው ናት፣ አባቷ አይታወቅም:: እችው ባልቴት እናቷ እዚህች ድንጋይ ላይ ተቀምጠው ድንችም ቲማቲምም እየቸረቸሩ አሳደጓት:: በኋላ ሀመሙም እርጅናውም ሲጫጫናቸው ግማሽ ቸርቻሪ፣ ግማሽ ልመና በሆነ ሕይወት ይውተረተሩ ጀመር ::

መቼስ ልጅቱ መንገድ ዳር እየኖረች ልዕልት መሰለች:: የመንደሩ ሴቶች ጠርሙስ ሙሉ ቅባት ጨርሰው፣ ያማረ ለብሰው፣ ትኩስ በልተው ጠብ ያላለላቸው መልክ እዚህች መንገድ ዳር ላስቲክ ከልላ በምፅዋት የምትኖር ልጅ ላይ ፈሰሰ:: ፀጉሯ ተዘናፈለ፣ ዳሌዋ ሞላ ወንዱ ሁሉ ዓይኑ ይቀላውጣት ጀመረ::

አንድ ምሽት እማማ ፅጌ ኡኡ አሉ:: መንደርተኛው ወደ ላስቲኳ ቤታቸው ተሰበሰበ:: ልጅቱ የለችም ጠፋች:: መንደርተኛው እማማ ፅጌ ጋር በመሆን ሳምንት ሙሉ ፈለገ:: የለችም:: ቆንጆዋ፣ ባልቴት እናቷን ትታ ምጥ ትግባ ሰምጥ እልም ድርግም አለች:: ጎረቤቱ ተሰፋ ቆርጦ ወደ የራሱ ጉዳይ ቢመለስም ሚስኪኗ ባልቴት ግን ከዛች ቀን ጀምሮ ለአስራ አንድ ዓመታት ታየች በተባለበት ተንከራተቱ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ የቀራቸው ከተማ የተረፉቸው መንደር የለም::

በየደረሱበት የዕለት ጉርሳቸውን እየለመኑ ፅንፍ የለሽ በሆነ የእናት ፍቅር ልጃቸውን ፈለጉ::

በአስራ አንደኛው ዓመት ልጃቸው ውጭ አገር ኖራ እንደተመለሰችና አንድ ባለፀጋ ልታገባ ሰርጉ እየተደገሰ መሆኑን ከሁነኛ ሰው ሰሙ:: "አይ ልጄ ፈልጋ አጥታኝ ነው" አሉና ወደ አዲሳባ አቀኑ:: አዲሳባ እንደገቡ አንድ ጥግ ላይ ከያዟት ፌስታል ለከት ቀን ብለው ያስቀመጧትንና ላለፉት አስራ አንድ ዓመታት ለብሰዋት የማያውቋትን ቀሚስ አውጥተው ለበሱ:: ራሳቸውን አየት አደረጉና፣ "እመቤት መሰልኩ አይደለም እንዴ፣ ልጄንማ አላዋርዳትም" አሉና ፈገግ አሉ::

ልጃቸው 'አለች' ወደተባለበት ቤት ሳያርፉ ጉዞ ጀመሩ:: ቤተ መንግሥት የመሰለው ቤት በሁለት ዘበኞች ይጠበቃል:: "የልጄ ቤት" አሉ በኩራት ፊት ለፊት ቆመው፤ ከዛም ጠጋ ሲሉ "እግዜር ይስጥሽ" አለ አንዱ ዘበኛ፣ እማ ፅጌ ይሄን ቃል ሺ ጊዜ ሰምተውታል የዛሬው ግን ለየት አለባቸው::

ሳቅ ሳቅ አላቸው:: ይሄ ጥበቃ ከደቂቃዎች በኋላ ጎንበስ ቀና ሲልላቸው ታያቸው፣

"ልጄዋ እኔ እንኳን የመጣሁት ቢጣዬን ብዬ ነው"

"ቢጣ ማናት?"

"ልጄ ናታ እዚህ ቤት እንደምትኖር ነግረውኛል"

"እንደዛ የምትባል ሴት የለችም እዚህ እማማ"

ጢጋ አሉትና፣ "ሙሽራይቱ ማነው ስሟ"

"እሜቴ ስማቸው ብሩክታዊት ነው"

ግራ ተጋብተው ከግቢው በር እንደቆሙ ቢጣ ከሸበላ ባለቤቷ ጋር ውሃ በመሰለ መኪና ብቅ አለች:: ራሷ ናት፣ እናትና ልጅ ፊት ለፊት ተፋጠጡ:: እናት ችለው መቆም አልቻሉም ጉልበታቸው ተብረከረከ፣ "ቢጣዬ ያይኔ አበባ..." ብለው ወደ መኪናው በእንብርክክ ቀረቡ ልጅ ኮስተር አለች፣ የመኪናውን መስተዋት ዝቅ አደረገች፣ ጥቁር መነፅሯን ወደ ፀጉሯ ከፍ ራሷን መታ አድርጋ ውብ ፀጉሯን ወደ ጎን አለችና፣

"ምንድነው?" አለች ፊቷን አጨፍግጋ::

"ቢጣዬ...እናትሽ ስንከራተት ኖሬ ይሄው መጣሁልሽ:: ሄድኩ አይባልም? ሜዳ ላይ ጣል አድርገሽ ማን አላት ብለሽ..."

"ማነህ ወደዛ ውሰዳት! የማንም ወፈፌ እየመጣ...እንሂድ 'ሃኒ'" አለች ቢጣ መኪናውን ወደ ሚያሽከረክረው ሰው ዞር ብላ...::

"ሃሃሃሃሃ ሃኒዬ አትበሳጭ አዲሳባ በነዚህ ዓይነት ፈጣጣዎች ነው የተሞላው" ነዳጁን ሰጥቶ ፈትለከ:: እማማ ፅጌ ተንበርክከው ቀሩ:: ራሳቸውን አይተው "ልጄ አስከትረሳኝ ተጎሳቁያለሁ ማለት ነው?" አሉ - በልጃቸው አልፈረዱም::

እስከሰርጉ ቀን ከግቢው ፊት ለፊት ካለች በረንዳ ላይ ዝናብና ፀሐይ እየተፈራረቀባቸው ልጃቸው መኪና እንደልብስ እየቀያየረች ስትገባና ስትወጣ እየተመለከቱ በልጃቸው ምቾትና ታላቅ ደረጃ መድረስ የራሳቸውን መከራ ረስተው ቆዩ:: አንድ ቀን እናቴ ብላ እጇን እንደምትዘረጋላቸው ተስፋ በማድረግ:: (ልጅ ያላየቻቸው እየመሰለች ሲታልፍ ቆየች ከአንድ ወር በላይ !!)

የሰርጉ ቀን፣ እናት ያችን ቀሚስ ከፌስታላቸው አወጡና ለበሱ፣ የኖሩባትን በረንዳ ጠራርገው ፌስታላቸው ውስጥ ያስቀመጧትን ትንሽ ብልቃጥ አወጡና በረንዳው ላይ ባለ መስታወት ዓይናቸውን ተኳሉ::

ከሰዓት ሙሽራዋ በነጭ ቀሚስ ተውባ በከፍት መኪና ስትደርስ ጎረቤቱ፣ ሰርገኛው ሲተረማመስ መሃል መንገድ ላይ ከሰርጉ መኪና ፊት ለፊት እማማ ፅጌ እስከሲታቸውን አወረዱት:: ሰው ሁሉ እብድ መስለውት ለእፍታ ትኩረቱን ወደ ባልቴቷ አዞረ:: ከሚሜዎቿ ከሙዚቃው በላይ

የዘፈ ድምፅ ከባልቴቷ ወጣ።

“መጣችም ሄደችም ደግሞ ከደግሜ ሲጋዋ ከሲጋዊ የተጨለፈ ልጁ ቢጣዩ እቻት ፡ እንኳን ደስ ያለሽ በሉኝ፣ ሙሽሬው ልጁን አደራ” አሉና ፊታቸውን አዙረው ወደ በረንዳቸው ሄዱ ፡ ከኋላቸው የእድምተኛው ሳቅና ፌዝ እየተከተላቸው።

ሌሊቱን ሲጨፈር፤ ሲደለቅ ታድሮ ጧት ያደረው ሰርገኛ ሲወጣ የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት የአስከሬን ማንሻ መኪና ከሰርጉ ቤት ፊት ለፊት ካለ ሱቅ በረንዳ ላይ የአንዲት ባልቴት ሬሳ ሲያነሳ ታየ። ሬሳው ከተነሳበት በረንዳ ንፋስ እየገፋ ወደ ሰርግ ቤቱ በር የወሰደው አንድ ጥቁርና ነጭ ፎቶ ዘበኛው እግር ስር ደረሰ። እናትና ልጅ የተነሱት ፎቶ ነበር።

“ወይ የሰው መመሳሰል...ልጅቱ እትዬን አትመስልም...?” አለ ዘበኛው ለጓደኛው፤

“ኡዲያ እሱን ወዲያ ጥለህ ይሄን ያዝ!” ብሎ ከሰርጉ የተረፈ ቢራ ሰጠው። ዘበኛው ፎቶውን ጥሎ ወደ ቢራው ዞረ። ንፋስ ጥቁርና ነጩን ፎቶ ወዳልታወቀ ቦታ እየገፋ ወሰደው።

“እኛ ያሳደግናት በማር በወተት...” የሰርግ ዘፈን ከግቢው ይሰማል።

# 13 'ቆጠራ ላይ ስለሆንን መግባት ክልክል ነው' ኮሚቴው !!

"ይሄ የተከበረና የታፈረ ቤተሰብ ተዋርዷል ! ተቃልሏል ! አገር ከመቃጠሉ በፊት እሁኑኑ ይሄን ጉድ አጣርታችሁ ንገሩኝ" አለ አባቴ እኔንና እህቶቼን ሰብስቦ:: ፊቱ ላይ የሚንቀለቀለው ብስጭት አቤት ሲያስፈራ:: አባባ እንዲህ ሲሆን አይቼው አላውቅም:: ጉዳዩን ከሰማን በኋላ ወዲያው ኮሚቴ ተቋቋመ...::

የኮሚቴው አባላት፣

አብርሃም (ቅፅል ስም የለውም)... ትልቅ ወንድም፣ የቤተሰቡ ብቸኛ ወንድ ልጅና የኮሚቴው ሰብሳቢ::

ኖአሚን (ቹቹ)...የቤተሰቡ የመጀመሪያ ልጅ ለእረፍት ከአሜሪካ የመጣች፣ የኮሚቴው ጸሐፊ::

ሮዛ (ቢጢቃ)...የአብርሃም ታናሽ እህት የሁለተኛ ዓመት የዩኒቨርሰቲ ተማሪ፣ ገንዘብ ያዥ::

መቅደስ(ባርቾ)...የአከስት ልጅ፣ በአባቴ ጥሪ ለዚሁ ጉዳይ ከናዝሬት የመጣች..."ሙድ" ያዥ እና አባል::

ኮሚቴው በቀጥታ ተጠሪነቱ ለአባቴ ሲሆን፣ የስራ ዘመኑም ይህ ጉዳይ እስኪጣራ ብቻ ይሆናል።

አገር ሊያቃጥል የተፎከረበት ጉዳይ...፣

አባቴ እሁድን የሚያሳልፈው በማንበብና በመፃፍ ነው:: ሁልጊዜ የሚያነበው፣ 'የደጃዝማች ወንዱ በቀለ የጦር ውሎ' የሚል መጽሐፍ ሲሆን የሚፅፈው ደግሞ ማመልከቻ !! ለቀበሌ... ለክፍለ ከተማ...ለዕድር...ለጡረታ ሚንስቴር...

አንድ ቀን ታዲያ ማመልከቻ ጽፈና ልክ ፊርማው ላይ ሲደርስ እስክሪብቶው አቋረጠ፡፡
"አብረሃም እስቲ እስክሪብቶ አምጣ?" አለኝ እየተጣደፈ፡፡
"እረ አልያዝኩም አባባ"
"ኡዲያ...የተማረ ሰው እንዴት እስክሪብቶ ከኪሱ ይጠፋል? ጠመንጃ የሌለው ወታደር ማለት ነው..." ብሎ ከተማረረ በኋላ ህፃኗን እህቴን፤
(ራሴን አምኘ ስለነበር የአባባ ንዝንዝ አልተመቸኝም፡፡)
"ቢጡ እስክሪብቶ አምጭልኝ!" አላት፡፡
"እሺ..."ብላ እሽንኩሊቷን ለእኔ አሳቅፋኝ ሮጠች(ፊጣን የኬጂ ተማሪ ነች)፡፡
"እሰይ የኔ እንበሳ! ካንተ ትሻላለች" አለ ወደኔ እያየ፡፡
ቆይታ ቆይታ ተመለሰችና፣ "አባባ ቀይ እስክሪብቶ ነው"
"የሆነው ይሁን..." አላት ስስቅ ወደኔ በብስጭት እያየ፡፡
ቆይታ ቆይታ መጣች፣ "ይሄው..." ያመጣችው እርሳስ ነበር፡፡
"አይ...ይሄ ምን ያደርግልኛል? እስክሪብቶ ነው ያልኩሽ" አለ አሁን እሱም ሳቁ መጥቶ ነበር፡፡

"ከተሳሳተብህ ታጠፋዋለህ ብዬ ነዋ ! ላጲስ አለው እየኸው፡፡"

"ሂጅ ሀና መኝታ ቤት ፈልጊና አምጪ...እይ ቢጣዬ ፊርማ በላጲስ ቢጠፋ...የብድር ሰነድ ላይ የፈረምነውን ስንት ጉድ ፊርማ ባጠፋነውና አገር እዳይ ባለች፡፡"

ቢጡ ወደ ሀና መኝታ ቤት ሮጠች (ሀና የ12ኛ ክፍል ተማሪ እህቴ ነች፡፡ ጨዋ፣ ጎበዝ ተማሪ...) አቤት አባባ ሲወዳት፣"ሀና ትሙት" ካለ አበቃ !!
ቢጡ የሀናን ቦርሳ ተሸክማ መጣች፡፡

"አልከፈትም አለኝ አባባ፡፡"

አባባ ቀስ ብሎ ቦርሳውን ከፈተና እስክሪብቶውን ፍለጋ ጀመረ፡፡ ድንገት ትንሽ ፓኬት ነገር እጁ ላይ ዱብ አለች፡፡ ወደ ዓይኑ ጠጋ አድርጎ እያት፡፡ ራቅ...ቀረብ...እንደገና ራቅ...
"እሃ...አብርሃም !" አጠራሩ ከመጥበቁ የተነሳ ስሜ የሚሰበር እስኪመስለኝ፡፡
"አቤት አባባ..."
"ሂድ መነፅሬን አምጣልኝ...ቶሎ በል"
"እ" አልኩ ግራ ገብቶኝ፡፡
"መነፅሬን አምጣ እኮ ነው የምለው..." ጩኸቱ አስበረገገኝ፡፡

"አባባ...መነፅርህን እኮ አድርገኸዋል" አልኩ፡፡ እጁን ወደ ዓይኑ ልኮ መነፅሩ ዓይኑ ላይ መኖሩን

አረጋገጠና፣

"አንቺ ወደ ውስጥ ግቢ..." አላት ቢጡን በቁጣ

"እሺ" ብላ ሮጠች::

"ይሄ ምንድን ነው...?"

እኔም ደነገጥኩ፣ የድንገተኛ አርግዝና መከላከያ ፖስት ፒል፣ አባባ አውቆታል::

"እ...እንጃ ምንድን ነው ?"

"ምን ትጠይቀኛለህ አንብበዋ"

አየት አድርጌ፣ "መድኃኒት ነው...ያው ራሷን አሟት ምናምን ሊሆን ይችላል::"

"ዝም በል:: እንካኺ...እንካ ራሴን አመመኝ ስትል አልነበረም፣ እንካ ዋጠው የራስ ምታት ከሆነ:: ሂድ እህቶችህን ጥራ" አለ በጩኸት:: ሁሉም ተሰባሰቡ:: ሀና የለችም ነበር፣ 'ላይብረሪ' ብላ ሄዳለች::

አባባ አጭርና ታሪካዊ ንግግር አደረገ (የሁላችንም ልብ በሐዘን ተነክቶ ነበር::) ይሄን ሁሉ ቤት ሲያሳድግ የዚህ ዓይነት ውርደት ደርሶበት እንደማያውቅ:: በተለይ ይሄን ጉዳይ ልዩ የሚያደርገው፣ መድኃኒቱ ትልቅ ተስፋ በሚጥልባትና በሚኮራባት ልጁ ሀና ቦርሳ ውስጥ በመገኘቱ መሆኑን በተጎዳ ድምፅ ከገለፀ በኋላ፣ 'በጥብቅ' የሀና መኝታ ቤት እንዲበረበር ትዕዛዝ ሰጠን::

"አብርሃም እህቶችህ ባሉበት ይሄን ጉዳይ አንተ ራስህ እየመራህ መርምር፣ ባይልልህ ነው እንጂ ቤተሰብ መሪ መሆኛህ ነበር...ወይ ውርደት !!" ብሎ ጠረጴዛውን ደቃው፣ እንደ ፍርድ ቤት መዶሻ የዕለቱ ስብሰባ መዝጊያ ተደርጎ ተወሰደ::

የምርመራ ቡድኑ ከላይ በጠቀስኩት ኮሚቴ በመዋቀር (አባቴ ደውሎ የጠራት የአክስታችን ልጅ በማካተት) ወደ ሀና መኝታ ቤት ዘመተ:: እናቴ የኮሚቴው አባል ልትሆን ብትጠይቅም 'የእናት አንጀት...' በማዘንም ይሁን በሌላ ምክንያት ሊያዳላና የኮሚቴውን ስራ ተዓማኒነት ሊያሳጣው ይችላል በማለት ሳትካተት ቀረች::

ኮሚቴው ገና ከጅምሩ ፀብ ጀምሮ ነበር:: ምክንያቱ ደግሞ እኔ እንደቀልድ የወረወርኳት ጥያቄ ነበረች፣ "ምናልባት ሀኒ ቦርሳ ውስጥ ከእናንተ አንድኛችሁ አስቀምጣችሁባት ይሆን?" ሁሉም ተንጫጩ:: እንደምንም አረጋግቻቸው (የሕዝብና የመንግስት ኃላፊነት ስላለብኝ) ስራችንን ቀጠልን::

የሀኒ መኝታ ቤት ሲፈተሽ መሳቢያዋ ውስጥ ለቁጥር የሚያዳግቱ የወንድ ፎቶዎች ማግኘታችን አስደነገጠን:: ጨዋዋ ሀኒ እየዞረች ፎቶ ማንሳት ጀምራ ይሆን ? ሲቀጥል የባሰው መጣ:: ወ በጡት ማስያዣ፣ ወላ ከወንዶች ጋር:: ብቻዋን...ሀይቅ ዳርቻ ላይ:: ...ቆይ አዲስ አበባ ሀይቅ አለ እንዴ...ታዲያ የት ሄዳ ተነስታ ነው ? በጀልባ (ታይታኒከኛ ፎቶ):: ከቤት ወጥታ የማታውቅ

ልጅ በምን ከንፍ በራ ሀይቅ ዳር ተገኘች ? ኧረ ጉድ...ጭፈራ ቤት...ማታ በሚኒስከርት...ሀና በሚኒስከርት (ሀናን በሚኒስከርት አየናት ከሚሉኝ፣ አንተን በሚኒስከርት አየንህ ቢሉኝ አምን ነበር) ጎረቤ ይሆን 'መነፅሬን አምጣ' አለ አባባ:: እውነቱን ነው፤ 'ኧረ መነፅሬን አምጡ' አለ የሰኘው! ሲጠቆ ልደብት ሆኖ አረፈው:: እኛ ሳሎን ተቀምጠን፣ ዘራፍ የነሉሲ፣ የእነ ማንትስ ልጆች...የመደሰው ደም...አባይን ገደብነው ስንል...መኝታ ቤታችን፣ የታሪክ የወግና ባህል ግድባችን ፈርሶ እገር ተጥለቅልቋል:: ንበዝ መነፅራችንን ስጡን:: 11:30 ቤቷ የምትከተት ልጅ ጭፈራ ቤት !!

ቡና ላጥቆጥ ተከፈተ ('ብልግና ተከፈተ' ቢባል ይሻላል::) የወሲብ ፊልም ከአፍ እስከገደፉ፣ ቢቃ አባባን ካሁኑ መሰናበት አለብን - ደም ግፊቱ... ታላቅ ታሪካዊ አደራ የተጣለብኝ ሰው ባልሆን ኖሮ ባለቀስኩ ነበር፣ ግን ስራዬን ቀጠልኩ፤ የወንዶቹ ፎቶ እጅግ ከመብዛቱ የተነሳ ለሪፓርት እንዲመች ይቆጠር ብለን መቁጠር ጀመርን:: መኝታ ቤቱ በር ላይ፣ "ቆጠራ ላይ ስለሆንን መግባት ክልክል ነው ኮሚቴው !!" የሚል ጽሑፍ ለጠፍን:: ከፎቶዎቹ ኋላ ስማቸው ተጽፏል:: 43 ዘሩ...44 ሚኪ...44 ፒተር(ፈረንጅ ነው)(የአክስቴ ልጅ ምራቋን ስትውጥ ጉሮሮዋ ሲንራገጭ ሰማሁት:: ፈረንጁን የዋጠችው ነው የምትመስለው::) 45 ሽምሰዲን (የሰፈራችን ባለሱቅ) 'ደንበኛዬ ነው' ትላለች ሀኒ:: እይ ሀኒ እዚህ ሚስኪን ቤተሰብ ላይ ቅኔ ስትዘርፍበት ነው የኖረችው:: ግዴለም !...46 ሀውቹባን (ቻይናዊ):: እቺ ልጅ ዓለም አቀፍ ስብሰባ ጠርታ ነበር እንዴ?

"ዊ መስት ኮል 911 ኢሚዲየትሊ" አለች ለዕረፍት ከአሜሪካ የመጣችው ትልቋ እህታችን ፊቷ በድንጋጤ አመድ መስሎ፣ እንባዋ በዓይኗ ሞልቶ:: ...ኮሚቴው በሳቅ ፍርስስስስስ:: ከሳቂታ ኮሚቴ ጋር አብሬ በመስራቴ ኩራት ተሰማኝ::

ቢጡ ስንስቅ ሰምታን በሩን እንኳኳችና፣ "አብልሽ ኮሚቴው ውስጥ አስገባኝ" አለችኝ:: ሳቅ ሁሉ ደስታ የሚመስላቸው ሚስኪኖች ስንቱ ኮሚቴ ውስጥ ገብተው እንደቀለጡ ባወቀች...

"ቢጣ ተመለሽ ! ማንበብ ትችይ የለ...የተለጠፈውን አታነቢም ?" አልኳት::

እየሞኸች ማንበብ ጀመረች፣ "ቆ...ጠ...ራ...ላ...ይ...ስ...ለ...ሆ...ን...ን......አብልሽ እኔም እኮ ቁጥር እስከ መቶ እችላለሁ:: ልቁጠርልህ ? ስማኝ...ዋን...ቱ...ስሪ...ፎር...ፋይፍ....." የፈረንጁን ፎቶ እያየሁ የቢጣን እንግሊዝኛ ሳዳምጥ፣ "ተከብበናል..." አልኩ ለራሴ::

"ምናልክ አብልሽ...ከልገባህም በአምሀሪክ ልቁጠርልህ ? አንድ...ሁለት...ሾሽት..."

ለምሳ ስንወጣ ቢጣ በሩ ስር እንቅልፍ ወስዷት በእንቅልፍ ልቧ ትቆጥራለች፣ "አርባ ሾሽት ባ አላት...ባ እምስት..." እንደገና ኮሚቴው ባሳቅ ፍርስስስስስስ:: የራብው ኮሚቴ ሲስቅ ይደብራል...!!

# 14 የመግቢያ ፈተና

አስራ ሁለተኛ ክፍል ተፈትኜ ዩኒቨርስቲ የሚያስገባ ውጤት በማምጣቴ መንደሩ በደስታ አበደ የበለጠ ወሬውን ያሞቀው ደግሞ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መመደቤ ነበር::

'አሳቷ ኸዋና ከተማው ከባህሩ ዘላ ጥርቅም አለች' ተባለልኝ:: ወሬው ሁሉ ስለኔ ሆነ...::

"...የአቶ ዘለቀ ልጅ ይንበርስቲ በጠሰ..."

"የትኛው..."

"ይሄ ባለፈው በሬ ወግቶት የነበረው"

"...ኧረረረረረረረረ ...ሰው ሁሉ ሞኛሞኝ መስሎ፣ ለካስ እንዲህ ጥይት ነው ጃል"

"ቀለም ዘልቆት ነው ፈዘዝ ያለው እይ...ጎበዝ ነው ከድሮውም...ኧረ::" ወሬው ከመንደር መንደር ተሰራጨ፣ በዛን ሰሞን የመንደሩ ሕፃናት አጥንተን እንሙት አሉ:: ለወትሮው በቅስቀሳ ትምህርት ቤት የሚሄደው ውሪ ሁሉ፣ ሰዓቱ ሳይደርስ ደብተሩን እንጠልጥሎ ቱርርር እያለ ይበር ጀመር::

ሁሉ ነገር ተሰናድቶ ድል ያለ የመሸኛ ግብዣ ተደረገና ቤተሰብ፣ ወዳጅ ዘመድ ሁሉ ተሰባስቦ ጨዋታው እንደደራ፣ ከከተማ የመጣው አጎቴ ስለሁኔታው ያወጋኝ ጀመር፡

"መላኩ"

"አቤት አጎቴ"

ክሆነስ ሆነና የትኛው ሰርቶ ነው የደለደለህ...ስድስት ኪሎ የሚባለው ነው...የሃይት ሆቴርታል አጠገብ..."

"አይ አይደለም አትቴ"

"አምስት ኪሎ የሚባለው ነው ቢቃ...እዛ የአክስቴ ቤት ነን፡፡ ከደንበርሶቹዎ ጋር ኩታ ገጠም ናቸው...እንዲህ አጥር ነው የሚለያቸው" አለች ከመንደራችን በገኛዋ አዲሳባን ሁለተ ጊዜ ሂዳቢታለች የምትባለው አረጋሽ፣ በዕርግጥም ወደ አምስት ወር አዲስ አበባ ቆይታ ተመልሳለች... አትቴ ቀበለ፤ "አምስት ኪሎ የት ነው?...ወደ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ይቀርባል መሰለኝ የሚባለው እውነት ነው?"

"ኧረ አትቴ አይደለም"

"ተዉት በቃ አራት ኪሎ ነው" አለች አረጋሽ፣ ቀጠል አድርጋም፤"እዛው ዝቅ ብሎ እኮ ነው! ከዚህ እንደ እቶ አስራት ቤት ቢሆን ነው፤ አትቴ ትግስ ቤቱ እዛው ስር ነው" መሰለኝ፤ ለመሆኑ አራት ኪሎ በመሆኑ ከፍቶኸል?" አለ አትቴ ፊቴን እያየ፡፡

እናቴ ፊቴ ላይ ያለውን ቅሬታ አንብባ እንዲህ አለች፤

"አይዞህ የኔ አንበሳ፤ እግርህ አዲሳባን ይርገጥ እንጂ ግዴለም...ከአራት ጀምረህ አምስትም፣ ስድስትም ሰባትም ኪሎ ትገባለህ፡፡ ሰንቅ ነው? እኔ እናትህ እያለሁ አትቸገርም" አለች፡፡ "እናትህ እውነቷን ነው፤ የትም ብትሆን እንዳትሰጋ!" አለ አባቴ ቀከራ በሚመስል ድምፅ፡፡

አትቴ ቀላል ሰው አይደለም፣ ጊዜው ራቅ ይበል እንጂ አዲሳባ አንድ ወር ከአስራ አምስት ቀን ሰንብቶ መጥቷል፡፡ ...እናም ባለችው እውቀት ስለ አራት ኪሎ እንዲህ አለ፤ "ኧረረረ ዋናው ጥንቅላቱ ላይ ነህና፤ ቤተ መንግስቱ ውስጥ በለው ቢቃ" አለ ጋቢውን ወደ ትከሻው ከፍ እያደረገ፡፡

ጥያቄያቸው ምርር ስላደረገኝ እንዲህ አልኩ፤ "እኔ የተደለደልኩት ኮሜርስ የሚባል ቦታ ነው፡፡"

"እእእእ" አጉረመረሙ፡፡

"እሱ ደሞ ወዴት ነው? አዲስ አባ ነው...ሲባልም አልሰማሁ" አለ አትቴ፡፡

"እኔም የት እንደሆነ አላውቅም አትቴ፤ ብቻ እዛው አዲሳባ እንዱ ግድም ነው" አልኩ፡፡ "እኔም የት እንደሆን አላውቅም አትቴ፤ ብቻ እዛው አዲሳባ እንዱ ግድም ነው" አልኩ፡፡

በዕርግጥም አራት ኪሎ፣ አምስት ኪሎ፣ ስድስት ኪሎ ካልተባለ ዩኒቨርስቲ ስለማይመስለኝ ኮሜርስ ባሉት ነገር ከፍቶኝ ነበር፡፡

"ከሆነስ ሆነና የትኛው ስርፋ ነው የደለደሉህ...ስድስት ኪሎ የሚባለው ነው_የካቲት ሆስፒታል አጠገብ..."

"አይ አይደለም አጎቴ"

"አምስት ኪሎ የሚባለው ነው በቃ...እዛ የአከስቴ ቤት ጎን:: ከይንበርስቲው ጋር ኩታ ገጠም ናቸው...እንዲህ አጥር ነው የሚለያቸው" አለች ከመንደራችን ብቸኛዋ 'አዲሳባን ሁለት ጊዜ ሂዳበታለች' የምትባለው አረጋሽ፣ በዕርግጥም ወደ አምስት ወር አዲስ አበባ ቆይታ ተመልሳለች_ አጎቴ ቀጠለ፣ "አምስት ኪሎ የት ነው?...ወደ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ይቀርባል_መሳኩ_የሚባለው እውነት ነው?"

"ኧረ አጎቴ አይደለም"

"ተዉት በቃ አራት ኪሎ ነው" አለች አረጋሽ፣ ቀጠል አድርጋም፣"እዛው ዝቅ ብሎ እኮ ነው! ከዚህ እንደ አቶ አስራት ቤት ቢሆን ነው፤ አጎቴ ጉግሳ ቤቱ እዛው ስር ነው" "መላኩ፣ ለመሆኑ አራት ኪሎ በመሆኑ ከፍቶኸል?" አለ አጎቴ ፊቴን እያየ::

እናቴ ፊቴ ላይ ያለውን ቅሬታ አንብባ እንዲህ አለች፣

"አይዞህ የኔ አንበሳ፣ እግርህ አዲሳባን ይርገጥ እንጂ ግዴለም...ከአራት ጀምረህ አምስትም፣ ስድስትም ሰባትም ኪሎ ትገባለህ:: ስንቅ ነው? እኔ እናትህ እያለሁ አትቸገርም" አለች:: "እናትህ እውነቷን ነው፣ የትም ብትሆን እንዳትሰጋ!" አለ አባቴ ፉከራ በሚመስል ድምፅ::

አጎቴ ቀላል ሰው አይደለም፣ ጊዜው ራቅ ይበል እንጂ አዲሳባ አንድ ወር ከአስራ አምስት ቀን ሰንብቶ መጥቷል:: ...እናም ባለችው እውቀት ስለ አራት ኪሎ እንዲህ አለ፣ "ኧረረረ ዋናው ጭንቅላቱ ላይ ነህና፣ ቤተ መንግስቱ ውስጥ በለው ቢቃ" አለ ጋቢውን ወደ ትካሻው ከፍ እያደረገ::

ግምታቸው ምርር ሰላደረገኝ እንዲህ አልኩ፣ "እኔ የተደለደልኩት ኮሜርስ የሚባል ቦታ ነው::"

"እእእእ" አጉረመረሙ::

"እሱ ደሞ ወዴት ነው? አዲስ አባ ነው...ሲባልም አልሰማሁ" አለ አጎቴ::

"እኔም የት እንደሆነ አላውቅም አጎቴ፣ ብቻ እዛው አዲሳባ አንዱ ግድም ነው" አልኩ:: በዕርግጥም አራት ኪሎ፣ አምስት ኪሎ፣ ስድስት ኪሎ ካልተባለ ዩኒቨርስቲ ስለማይመስለኝ 'ኮሜርስ' ባሉት ነገር ከፍቶኝ ነበር::

"ምንድነውሳ የሚያስተምሩት?" አለ አባቴ።

"'የንግድ ስራ' ይላል ወረቀቱ ላይ" አልኩ።

"መድሃኒዓለም! ንግድ ምን ትምህርት ይላል? ይሄው እኛ ዝም ብለን እያቀላጠፍነው እይደለም?!" አለ አባቴ፤ ታዋቂ የእህል ነጋዴ ነው።

"እንዴዴዴዴዴ ባንክ የምትሰራው የአከስቴ ልጅ የተማረችበት ነው፤ ኧረ ጥሩ ተማሪ ቤት ነው ሲሉ ሰምቻለሁ። ሞት ይርሳኝ! ያ በሪሁን፣ የእናቴ የእህት ልጅ፣ ቤቱ እዛው ነው" አለች አረጋሽ።

ጋሽ ዘለቀ የመንደራችን አስቂኝ ሽማግሌ፤ "አረጋሽ እንደው ያንች ዘመዶች ሁሉ ዩኒቨርስቲ አጥር ስር ብቻ ነው እንዴ ቤት የሚሰሩት?!" አሉና ሰዉን አሳቁት።

ሁሉም እንደየአቅሙ የሰማውንም ያየውንም ስለአዲስ አበባ ይመክረኝ ጀመረ።

የመጀመሪያው አጎቴ ነው፤ "መላኩ...አዲሳባ እንዲህ ቀላል አገር እንዳይመስልህ ባህር ነው... በህር...በዛ ላይ ሌባው አይጣል፤ ሴት ወንዱ ሞላጫ ነው። ሱፉን ግጥም አድርጎ መኳንንት የመሰለው ሰው፣ ጤጋ ብሎ ከኪስህ ገንዘብህን ይከተልብኸል። ሴቷ ስትውረገረግ ልብህን ትሰልበዋለች። አንዳች አፍዝ አደንግዝ አላቸው። ጠንቀቅ ብለህ እንደወታደር ነው መኖር፤ የአዲሳባ ሕዝብ ፈዛዛ አይወድም"

አጎቴ አዲስ አበባ የሄደው ለሕክምና ነበር። ታዲያ ከቆየባቸው አርባ አምስት ቀናት ሰላሳ ዘጠኙን ጥቁር አንበሳ ተኝቶ ነው ያሳለፈው፤ ሁለት ቀን የካቲት ሆስፒታል...አንድ ቀን ጦር ኃይሎች...ከህመሙ ጋር እየታገለ ስለአዲሳባ ይሄን ሁሉ ማወቁ ግሩም ነው።

ዙሪያሽ ነበረች ቀጣይ መካሪ፣ "ወይ አዲስ አበባ...ሂሂሂ...የጉድ አገር እኮ ናት፣ መንገድ ስትሻገር ነጭ ነጯን እየረገጥክ ነው፣ ሳት ካለህ መኪናው አያፈናፍንም..."

"ይሄ አዲስአባ ሰፊ አገር ነው አልተባለም እንዴ? የምን የማሪያም መንገድ ነው! ነጩን ጥቁሩን እንዳሻው ይራመድ እንጂ" አለች እናቴ።

"ሂሂሂሂ ሕግ ነው፤ እንደኛ አገር ያገኙበት መርገጥ የለም እናቴ፣" ብላ አረጋሽ ቀጠለች፣ "እና...መላኩ ዋናው ነገር...ዋናው የአዲስአባ ሴቶች አሳሳቾች ናቸው፤ ያንተ ዓይነቱን ሸበላማ ካዩ ተከትለውህ ነው የሚመጡት። ኮስተር በል፣ ፊት አትስጣቸው! ኧረ በድንግሏ...ሃፍረት የሚባል አያቃቸውም..."

"ምንድነውሳ የሚያስተምሩትን?" አለ አባቴ፡፡

"'የንግድ ስራ' ይላል ወረቀቱ ላይ" አልኩ፡፡

"መድሃኒዓለም! ንግድ ምን ትምህርት ይላል? ይሄው እኛ ዝም ብለን እያቀላጠፍነው አይደለም?!" አለ አባቴ፣ ታዋቂ የእህል ነጋዴ ነው፡፡

"እንዴዴዴዴዴ ባንክ የምትሰራው የአከስቴ ልጅ የተማረችበት ነው፤ እረ ጥሩ ተማሪ ቤት ነው ሲሉ ሰምቻለሁ፡፡ ሞት ይርሳኝ! ያ በሪሁን፣ የእናቴ የእህት ልጅ፣ ቤቱ እዛው ነው" አለች አረጋሽ፡፡

ጋሽ ዘለቀ የመንደራችን አስቂኝ ሽማግሌ፣ "አረጋሽ እንደው ያንች ዘመዶች ሁሉ ዩኒበርስቲ አጥር ስር ብቻ ነው እንዴ ቤት የሚሰሩት?!" አሉና ሰዉን አሳቁት፡፡

ሁሉም እንደየአቅሙ የሰማውንም ያየውንም ስለአዲስ አበባ ይመክረኝ ጀመረ፡፡

የመጀመሪያው አጎቴ ነው፣ "መላኩ...አዲሳባ እንዲህ ቀላል አገር እንዳይመስልህ ባህር ነው... በህር...በዛ ላይ ሌባው አይጣል፣ ሴት ወንዱ ሞላጫ ነው፡፡ ሱፉን ግጥም አድርጎ መኳንንት የመሰለው ሰው፣ ጢጋ ብሎ ከኪስህ ገንዘብህን ይከተልብኻል፡፡ ሴቷ ስትውረገረግ ልብህን ትሰልበዋለች፡፡ አንዳች አፍዝ አደንግዝ አላቸው፡፡ ጠንቀቅ ብለህ እንደወታደር ነው መኖር፤ የአዲሳባ ሕዝብ ፊዛዛ አይወድም"

አጎቴ አዲስ አበባ የሄደው ለሕክምና ነበር፡፡ ታዲያ ከቆየባቸው አርባ አምስት ቀናት ሰላሳ ዘጠኙን ጥቁር አንበሳ ተኝቶ ነው ያሳለፈው፤ ሁለት ቀን የካቲት ሆስፒታል...አንድ ቀን ጦር ኃይሎች...ከህመሙ ጋር እየታገለ ስለአዲሳባ ይሄን ሁሉ ማወቁ ግሩም ነው፡፡

ዙሪያሽ ነበረች ቀጣይ መካሪ፣ "ወይ አዲስ አበባ...ሂሂሂሂ...የጉድ አገር እኮ ናት፣ መንገድ ስትሻገር ነጭ ነጯን እየረገጥክ ነው፣ ሳት ካለህ መኪናው አያፈናፍንም..."

"ይሄ አዲስአባ ሰፊ አገር ነው አልተባለም እንዴ? የምን የማሪያም መንገድ ነው! ነጩን ጥቁሩን እንዳሻው ይራመድ እንጂ" አለች እናቴ፡፡

"ሂሂሂሂሂ ሕግ ነው፤ እንደኛ አገር ያገኙበት መርገጥ የለም እናቴ፣" ብላ አረጋሽ ቀጠለች፣ "እና...መላኩ ዋናው ነገር...ዋናው የአዲስአባ ሴቶች አሳሳቾች ናቸው፤ ያንተ ዓይነቱን ሽበላማ ካዩ ተከትለውህ ነው የሚመጡት፡፡ ኮስተር በል፣ ፊት አትስጣቸው! እረ በድንግሏ...ሃፍረት የሚባል አያቃቸውም..."

"አንድ ቀን የአከስቴ ልጆች ካማሪካ መጡና እራት እንብላ ብለው ሰብስበው ወሰዱን:: ጉድ እየሁ...ጉድ...ሴት እና ወንድ፣ ሴትና ወንድ ሁነው ነው የሚቀመጡት:: አንድ ብ;ቻህን ቁረር ብሎ መቀመጥ ነውር ነው የተባለ ይመስል...:: ሃዲያ አንድ ጊዜ ይጎርሱና መሳሳም፣ ደሞ ይጎርሱና መሳሳም...አማምላከን እህሉን በውሃ ሳይሆን በመሳሳም የሚያወራርዱት ነው እኮ የሚመስሉት...ሁሁሁሁ" ብላ በእፍረት ሳቀች::
"ወላዲት አምላከ!ኸምግብ ቤቱ ነው የሚሳሳሙት?
ፈረሰኛው ጊወርጊስ!"

ሁሉም በወሬው ተገርመው ተንጫጩ::

ቀጠለች አረጋሽ፣ "ደሞ ሴቶቹ እንዲቹ እርቃናቸውን ቁራጭ ልብስ ጣል አርገው እንዲቹ እንደፈጠራቸው ነው የሚመናቀሩት...የቆዳቸው ልስላሴ...መስተዋት ነው የሚመሳስሉት... 'አይበርዳቸውም ወይ?' እላለሁ እኔማ" አለች:: ...ገረመኝ!!

"እና መላኩ፣ በሌላ ሌላው እንኳን አንተ አትመከርም፣ በሴቶቹ እንዳትፈተን አደራ!" ብላ ምከሯን ጨረሰች::.

እንደጧት አዲሳባ ልሳፈር ሌሊቱን ሲያቃዠኝ አደረ:: እራት እየበላሁ ይመስለኛል፣ የቆዳዋ ጥራት መስተዋት የመሰለ ሴት እርቃኗን ጎኔ ተቀምጣ እንጄ በጎረስኩ ቁጥር የምትስመኝ ይመስለኛል፣ ልክ እንደማወራረጃ:: ከዚሁ ፈተናው ጀመረኝ::

# 15 እብድ እና ዘመናይ

ጓደኞችን አመሃ አበደ !!

ድንገት ነው እንደ ትንታ፣ እንደ ሳል፣ እንደ ንጥሻ አብደቱ ያመለጠው:: እቺ አይምሯችን ግን ከንቱ ናት ለካ! ደርሰን እናሞካሻታለን እንጂ አንዳንዴ እንዲህ ሜዳ ላይ ጣጥላን ትወፍፋለች ለካ:: ሰው ከንቱ !! አይምሯችንን ልንጠብቃት ይገባል፣ አለች ስንላት ገደል ገብታ ገደል ታስገባናለች፤ ወይኔ አምሽ! ምነው ሴት ሆኖ ተፈጥሮ በነበር !?...ይሻለው ነበር ! ባንዴ ከማበድ በየቀኑ ትንሽ ትንሽ ማበድ !

የስነ አእምሮ ጠበብት "ሴቶች የማበድ እድላቸው ከወንዶች ጋር ሲነፃፀር በጣም አነስተኛ ነው፤ ምክንያቱም ሴቶች ብስጭታቸውን፣ መከፋታቸውን በእንባ ይሸኙታል፤ በጩኸት ይሸውዱታል፤ ወንዶች ግን አፍነው ስለሚይዙት ውስጣቸው ይጠራቀምና ድንገት ገንፍሎ ጉድ ያደርጋቸዋል" ይላሉ:: በነጋዴ ቋንቋ ስንገልፀው ሴቶች የሚያብዱት በችርቻሮ ሲሆን ወንዶች ግን በጅምላ ነው እንደማለት::

ጓደኞችን አመሃ ኮሌጃችን ውስጥ ወላ ባለባበስ፣ ወላ በትምህርት የሚደነቅ ሲበዛ ዝምተኛ ልጅ ነበር:: 'ሃይ፣ ባይ' ነው ቅፅል ስሙ:: በቃ ስንገናኝ 'ሃይ' ይላል:: አንዲት ቃል ሳይተነፍስ ስንለያይ፣ 'ባይ' !! አምሻ ልዩ ልጅ ነበር:: ምድረ ኩታራ ከየዶርማችን ሱክ ሱክ እያልን ወደ 'ክላስ' ስንጣደፍ አምሃ ፀዳ ባለ ፓጃሮ መኪናው ከተፍ ይላል:: እንግዲህ እኛ ባየነው ነገር ሰላምን የምንለካ የዋህ ከተሜዎች የአመሃ ተድላ እና ሀብት ተደማምሮ እንኳን እብደት ድብርት በአመሃ አጠገብ ያልፋል ብለን በምን አባታችን ጠርጥረን:: "ፀጉራም ውሻ አለ ሲባል ይሞታል" እንዲሉ አበው በሀብት ፀጉር የደለበ የመሰለን አመሃ 'አለ' ስንለው 'ለቀቀ' !!

አመሃ እና እኔ ጓደኞች ነን:: እንደውም አመሃ ሁለት ጓደኛ ብቻ ነው ያለው፤ እኔና ናትናኤል የሚባል የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አብረው ሳንፎርድ የተማሩ ልጅ:: በቃ ሌላ ጓደኛ

የለውም::ያው ፍቅረኛው እንዳለች ሆና !! ቤቱ ሁሉ ወስዶ ከሞሊቃቃ እናቱ ጋር አስተዋውቆኛል::

እንደ አመሃ እናት በጣም አጭር ጅንስ ቁምጣ የለበሰች ወጣት እናት ከዛ በፊትም ከዛ በኋላም አይቼ አላውቅም:: የእግሮቿ አረዛዘም፣ ሰበር ሰካ አረማመዷ ወጣት ይፈትናል:: ከላይ ጣል ያደረገችው ስስ ቡዲ ነገር የጡት መያዣዋን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል:: አመሃ ሁለታችንን ትቶን ወደ ውስጥ ሲገባ፣ "የዛሬ ልጆች ቆንጆዎች ናችሁ" አለችኝ:: አነጋገሯ እንደ ማስቲካ ይለጠጣል፣ ከአስተያየቷ ጋር ተዳምሮ አድናቆቷ እናታዊ አድናቆት አልመስልህ አለኝ:: የለም የለም እቺ ሴት የእናት ቀለም የላትም::

ፊት ለፊቴ ተቀምጣ አንድ እግሯን ሶፋው ላይ አውጥታ በረዣዥም የእጇ ጣቶች ጉልበቷን በስሱ እንደማከክ አደረገችው:: ቁምጣዋ ተሰብስቦ የተላጠ ብርቱካን የመሰለ የደላው ሰውነቷን አጋለጠው:: ጥርት ያለ የታፋዋ ቆዳ ላይና የሚያማምሩ የእግሯ ጣቶች ላይ ዓይኔን አለማሳረፍ አልቻልኩም:: በዛ ላይ ውስጥን ሰርስሮ የሚያይ የሚመስል አስተያየቷ "ምነው ባልመጣሁ!" አስባለኝ::

በምድር ላይ ያሉ እናቶች ሁሉ ሸንሸን ቀሚስ 'ዩኒፎርማቸው' ይመስለኝ ነበር:: ያደግኩበት መንደር ሁሉም የሚለብሱት እንደዛ ስለነበረ ሲቀመጡ እንኳን ዘርፋፋ ቀሚሳቸውን እንዴት ሰብሰብ አድርገው እንደሚቀመጡ ሳስብ የዚች "እናት" ነገር ግራ ገባኝ:: መቼም "እናት ምን መምሰል አለባት?" የሚል ጥያቄ ቢነሳ ያው "እናት መምሰል አለባት" ነው መልሱ:: እቺ ሴት ግን ምኗም እናት አይመስልም:: የእናት ለዛ የላትም፤ የእናት የዋህነት፣ ደግነት ፊቷ ላይ ከነአካቴው የለም:: ዘላ ያልጠገበች የአስረኛ ክፍል ተማሪ ነው የምትመስለው::

የአመሃ አባት ውጭ አገር በሚገኝ ዩኒቨርስቲ መምህር ናቸው:: እናቱ አብራቸው ሄዳ እዛ እንዲኖሩ ብትለመን፣ ብትመከር "በአንገቴ ገመድ ቢገባ አልሄድም!" በማለቷ ሁለቱ ብቻቸውን እዚህ በቅንጦት የተምነሸነሸ ቪላ ውስጥ ይኖራሉ:: አባቱ በስድስት ወር አንዴ ብቅ እያሉ ይጎበኟቸዋል - ራሱ አመሃ ነው የነገረኝ:: ሁልጊዜም አባቱ ሲመጡ ታዲያ እናትና አባት ዱላ ቀረሽ ንትርክ ውስጥ ናቸው:: አባት የሚስታቸውን ባህሪ ያውቁታል:: ሚስትም የባሏን ባልነት ባትረሳም የትዳሩ ነገር እጅ እጅ ብሏታል::

የሆነው ሆኖ አምሃ አበደ:: ከማበዱ በፊት የሚጠረጥር ዘመድ፣ በጊዜ አፋፍሶ ፀበል የሚወስድ ወዳጅ ዘመድ አጥቶ እንጂ አምሃ ግልፅ የሆኑ ምልክቶች ሲያሳይ ነበር - በተለይ ለእኔ::

ምልክት አንድ:- ህዳር ላይ የሚያብድ፣ መስከረም ላይ ሱሪውን ከፍ ከፍ ያደርጋል ይላሉ እማማ ሩቂያ፣

አንድ ቀን አመሃ (ለይቶለት ከማበዱ አንድ ወር በፊት) ሱሪውን አስር ጊዜ ከፍ ከፍ ያደርጋል:: "ሰፍቶህል እንዴ ይሄ ሱሪ ?" አልኩት:: "አይ ቀበቶዬን ረስቼ ሳላረገው ነው የመጣሁት" አለኝ፣ እንዲህ የምንባባለው ወደ ላይብረሪ እየሄድን ነበር:: ላይብረሪ ውስጥ ጎን ለጎን ለመቀመጥ ቦታ

ስላልነበር በያገኘነው ወንበር ተራርቀን ተቀመጥን:: ድንገት አመሃ ቁጭ ሲል ሸሚዙ ከኋላው ሰብሰብ አለና ቀበቶ ማድረጉን አየሁ:: ያውም ጥቁር የቆዳ ቀበቶ:: "ቀበቶ አላደረግኩም" ማለቱ ገርሞኝ ስንወጣ እጠይቀዋለሁ ብዬ በዛው ረሳሁት::

ምልክት ሁለት:- "አላህ ሲቆጣ ብትር አይቆርጥም፤ ያደርጋል እንጂ ነገር እንዳይጥም" ይላሉ እማማ ፋቅያ፣ የሰፈራችን አድባር፤

እኔና አመሃ አንድ ታዋቂ ሬስቶራንት ውስጥ ገባንና ምግብ አዘዝን - 'ፒዛ':: አመሃ ቀመስ አደረገና አስተናጋጇን ጠርቶ፣ "ምንድን ነው ይሄ ሁሉ ጨው ! ቤቱ ውስጥ ያለውን ጨው ሁሉ ነው የምጆራችሁት ?" ብሎ ጮኸባት:: እንደ እውነቱ ከሆነ አመሃ ሲጮህም ሆነ በቁጣ ሲናገር ሰምቼ ስለማላውቅ ከምላሴ ይልቅ አመሃን አምኜው ነበር:: አስተናጋጇ ግን በትህትና፣ "ይቅርታ እኛ ፒዛ ስናዘጋጅ ጨው አንጠቀምም፣ ደንበኛው ራሱ በሚፈልገው መጠን እንዲጠቀም ለብቻ ነው የምናቀርበው" አለች ፊታችን የተቀመጠውን የጨው እቃ እያሳየችን::

"ሂጂ ወደዛ !! ይሄን ልመን እንችን ?" አላት ምላሱን በአስፈሪ ሁኔታ ጎልጉሎ በግራ እጁ ሜፉን በመያዝ በቡካው ሜፍ ለአስተናጋጇ እያሳያት:: ፒዛውን ትተነው ሌላ ቤት ገባን:: አመሃ ሰሰላሳ አዘዘ:: አንድ ጊዜ ተጎንጭቶ ፊቱን አጨፈገገና፣ "ቱ !" ብሎ ወለሉ ላይ ተፋው:: ፊት ለፊት ተቀምጠው የነበሩ ወንድና ሴት ፍቅረኛሞች ፊታቸውን አጨፈገጉና ተመለከቱት:: "እንዴት ሚሪንዳ ውስጥ ለሚ ትጨምሩላችሁ ?" ብሎ አዛም ግብ ግብ ፈጠረ:: በቃ ይሄ ልጅ ነገር ሁሉ አልጥመው አለው:: (ሊያብድ አስር ቀናት ብቻ ነበሩ የቀሩት)

ሦስተኛ ምልክት:-...እብድ

ሌላ ቀን መኪናውን እያሽከረከረ ወደ ማቆሚያው አመራና የዶክተር ታደሰን አሮጌ ዲኤክስ መኪና አርፋ በቆመችበት ከኋላዋ ገጫት:: ድሮም ሆድ የባሳት ነበረች:: ከዛም ሰው ተሰብስቦ ወሬ ሲያይ አመሃ ረጋ ብሎ ወረደና ልክ እንደ ትራፊክ ፖሊስ ኮስተር ብሎ ግጭቱን ከተለያየ አቅጣጫ ኢይቶን እያጨነቆረና አንገቱን እየሰበቀ ከተመለከተ በኋላ (ፎቶ የሚያነሳ ነበር የሚመስለው) ወደ ዶክተር ታደሰ ቢሮ ሄደ:: ሳያንኳኳ በሩን በርግዶ ገባና ዶክተሩ ላይ አፍጥጦ፣ "አንተን ብሎ ዶክተር... መኪና እንኳን በስርዓት ማቆም የማትችል..." ብሎ ሙልጭ አድርጎ ሰድቧቸው ወጣ፤

"ይሄ ልጅ እብድ ነው እንዴ !" አሉ ዶክተሩ::

አራተኛው ምልክት:- ዘመናይ

ሄለን የምትባል 'ዘመናዊ' የዲፓርትመንታችን ልጅ አለች:: ምንም ነገር ስትናገር ለነገ የማትል፤ "ውይ እሷ ጣጣ የላትም፣ 'ፍሪ' እኮ ነች" እያለ ለእብደት የቀረበ ዘመናዊነቷን ተማሪው ያባባሰባት:: አመሃ ጋር አንድ ሰፈር ናቸው:: እንደውም ቤተሰብ ናቸው ማለት ይቀላል::

አንድ ቀን እመሃ፣ እኔ፣ እሷ ሆነን ዩኒቨርስቲው መናፈሻ ውስጥ እንደተቀመጥን አንዱ አስተማሪ በፊታችን ሲያልፍ፣ "ይሄ ሰድ የሆነ ሰውዬ ባለፈው ቢሮው አስገብቶ ቀሚሴን ሊገልበው..." አለች::

"ምን !? ያንቺን ቀሚስ ሊገልብ ይሄ ቆሻሻ" ብሎ አመሃ ወደ ሰውዬው ሊንደረደር ሲነሳ እንቅ አድርጌ ያዝኩት:: መጠርጠር ጀምሬ ነበር - አምሽ ለቀቅ እያደረገ እንደነበር::

"ምን ነካህ አመሃ ስትቀልድ እኮ ነው እሷ !" አልኩት::

"እየቀለድሽ ነው ?" አላት አመሃ ወደ ሄለን ዞሮ:: 'አዎ' እንድትል ጠቀስኳት፣

"አዎ!" ከማለቷ፣ አመሃ በጥፊ አጮላት:: አስደንጋጭ ነገር ነበር:: ስድድብ ጀመሩ፤

"ቺዝባ !" አለችው:: ሰው ስትሳደብ አይቻት አላውቅም:: መናፈሻው ውስጥ ያለ ተማሪ ሁሉ ወደ እኛ ዞረ::

"ሸርሙጣ !" አላት:: ከአመሃ ይሄ ቃል ይወጣል ብሎ ማንም አይገምትም::

"ቆሻሻ !" አለችው::

"ማጋጣም!" አላት::

"ስማ አባትህ ቾክ እያቦነነ ባመጣው ገንዘብ ስትሞላቀቅ ጠገብክ !"

"እና እንዳንቺ እናት በመሸርሞጥ ሃብታም መሆን ይሻላል ?" ተማሪ በተሰበሰበበት እብድና ዘመናይ ልክ ልካቸውን ተነጋገሩ:: አመሃ ሊለይለት ሶስት ቀን ቀርቶት ነበር::

ስድስተኛው ምልክት፡- ልበቢስ

የመጀመሪያውን ሴሚስተር ጨርሰን ሁለተኛውን መጀመራችን ነበር::አዲስ ኮርስ የሚሰጡን መምህር ወደ 'ክላስ' ገቡ:: ፀጉራቸው ወደ ኋላ የተደለሰ ህንዳዊ ናቸው:: ስታትስቲክስ የሚባል ኮርስ ነው የሚያስተምሩት:: ይሄ መምህር ከአንድ የመንግስት የኒቨርስቲ በተማሪዎቹ የ'እንፈልጋቸውም' ተቃውሞ የተባረሩ ህንዳዊ ቢሆኑም አሁን የምንማርበት ኮሌጅ ግን፣ "ከውጭ በመጡ ታዋቂ መምህራን..." እያለ የቴሌቪዥን ማስታወቂያ የሚሰራባቸው የስንፍና ጥግ ናቸው:: ያው እንግዳ ተቀባይ ነንና አክብረን ተቀበልናቸው::

በተኮላተፈ እንግሊዝኛቸው ማስተማር ጀመሩ፤

"ስታትስቲክስ ከሌሎች የጥናት መስኮች የሚለየው አንዲት አገር 'የልብ ምቷን' የምታዳምጥበት መሳሪያ በመሆኑ ነው" አሉ በኩራት::

አመሃ ድንገት ብድግ ብሎ "ዝም በል !" አላቸው::

'ቲቸርን' ከራማቸውን ነው የገፈፈው:: እኛንም እንጂ !

አመሃ በብስጭት ዲስኩሩን ቀጠለ:: "ሁሉም አስተማሪ እየመጣ 'የልብ ምት፣ የልብ ምት' ይልብናል:: 'ኢኮኖሚክስ' የአንዲት አገር የልብ ምት የሚለካበት የጥናት መስክ ነው፤ 'ሕግ' የአንዲት አገር የልብ ምት የሚለካበት...'ፖለቲካል ሳይንስ' ሁለንተናዊ የአገር የልብ ትርታን የሚያዳምጥ የጥናት ዘርፍ ነው... ቆይ የዚች አገር ልብ በስንቱ ነው የሚለካው? ሲጀመር አገራችን ልብ ቢኖራት እንዳንተ አይነቱ ፊት ታስቀምጠን ነበር?

አገራችን 'ልብ አላት ወይስ የላትም?' የሚለውን ሃቅ የሚያጠና የትምህርት ዘርፍ ያስፈልገናል፤ የልብ ትርታ ከመለካታችን በፊት ልብ መለኪያውን ይዞ ከየዩንቨርስቲው በየዓመቱ ወደ ሕዝብ የሚጎርፈው ሁሉ 'እዚህ ልብ የለም፣ የምትሄድበት ሄደህ ፈልግ፣ ካልሆነም ልብ ፍጠር' እየተባለ ስለ የትኛው ልብ፣ ስለየትኛው ትርታ ነው የምትቀባጥረው ? ሳልፈልግ ብዙ አታስወራኝ... ሃሃሃሃሃሃ"

አመሃ ለየለት !! አፋፍሰን አማኑኤል ወሰድነው:: እዛው ቀረ !! እናቱ ተጠርታ መጣች:: ሰውነቷ ላይ ጥብቅ ያለች አጭር ሚኒስከርት ለብሳ ከመኪናዋ ወረደችና ሰበር ሰካ እያለች ወደ እኔ መጣች::

"ምን ሆኖ ነው ?" አለችኝ፣

ነገርኳት::

"ድሮም የአባቱ ልጅ ነው፣ ሴታ ሴት፣ ለየለት" አለች በብስጭት:: ምን እንዳበሳጫት አላወቅኩም፤ ከብዙ ጊዜ በኋላ ሄለን አመሃ በእናቱ ምክንያት አዕምሮው እንደተናጋ አወጋችኝ::

"አንድ ቀን አመሃ ሶደሬ ሊሄድ ከሴት ጓደኛው ጋር ቀጠሮ ያዙ:: ታውቃት የለ ያች ሚዳቆ የመሰለች ጓደኛው:: እናልህ ለእናቱም ይሄንኑ ነግሯት መንገድ እንደ ጀመሩ የጓደኛው እናት የደም ግፊታቸው ከፍ ብሎ ጉዟቸው ተሰናከለ:: ሆስፒታል ቆይቶ ወደ ቤቱ ሲመለስ እናቱ ናትናኤል ከሚባለው ከራሱ ከአመሃ ጓደኛ ጋር ያውም አባቱ አልጋ ላይ...ሂሂሂሂሂ"

ሄለን 'ፍሪ' ስለሆነች በሚያሳብድ ቃል ነው የነገረችኝ፤ መሳቋ አበሳጨኝ::

"አብርሽ" አለችኝ እየሳቀች::

"ምን ሆንሽ !" አወራሯ አበሳጭቶኝ ነበር::

"ተረኛው አንተ ነህ...ሂሂሂሂ"

ተራዬ ለአብደቱ ይሁን ለ.... አልገባኝም፤ ግን አልጠየቅኳትም:: ምክንያቱም ሄለንም በጅምላ አብዳ ሳይንሱን ጉድ ልታደርገው እየተዘጋጀች ስለመሰለኝ ነበር::

# ከፍሪጅ የተጫረ እሳት 16

አዲሳባ ውስጥ ከሚኖሩ ሃምሳ ዱርዬ ሴቶች መካከል የሰላሳ ዘጠኙ ስም ሜሮን ይመስለኝ ነበር፤ አምስቱ ሄለን፣ አምስቱ ሃያት፣ አንዷ ግን አንድ ነጥብ አምስት ሚሊየን ስም እየቀያየረች የምታጭበረብርና ስሟ የማይታወቅ፤ ቦሌ ቢባል ካዛንችስ፣ ፒያሳ ቢባል አራት ኪሎ፣ ነርስ ብትሆን ሱቅ ጠባቂ፣ የዩኒቨርስቲ ተማሪ ብትሆን ሴተኛ አዳሪ…ብቻ ስሟን የምትቀያይር ሴት ነበረች የምትመስለኝ::

አዎ ስሟን እየቀያየረች በአንድ ነጥብ አምስት ሚሊየን ስም የምትዶርር (ዱርዬ የምትሆን)… ትዕግስት፣ ሳባ፣ ገነት፣ ማርታ፣ መቅደስ፣ ትርሃስ፣ ሐረገወይን፣ ወላንሳ፣ ዙሪያሽ፣ ፍሬ፣ ቃልኪዳን፣ ቲቲ፣ መዓዛ፣ ራሄል፣ ሚሚ፣ ሙና፣ እስናቁ፣ ዘሪቱ፣ መንበረ፣ አለምነሽ፣ ያኔት፣ ሊና፣ ሳራ፣ ሃና…አንድ ነጥብ አምስተኛው ላይ ሜሮን ትሆናለች:: እች እስስት !!

እስስት ብያለሁ አዎ !! ስም እኮ ቀለም ነው፤ ሰው ስሙን ሲቀያይር ቀለሙን ለመቀየር መሞከሩ ነው:: እና ጥሩወርቅ ጎጃምኛ ቀለሟን ቀይራ 'ሊያ' ነኝ ስትል ምን እየሆነች ነው? አካባቢዋን እየመሰለች፤ አዲሳበባን እየመሰለች:: እስስትስ ከዚህ የተለየ ምን አደረገች ? ያው አካባቢዋን ለመምሰል ቀለሟን ነው የቀየረችው:: አነጋገርን ለመቀየር የሚደረግ ድካም ምንን ለመቀየር ነው ? ቀለምን !! እናም ሰውና እስስት ከሚመሳሰሉበት ባህሪ ዋናው የተጠጉትን መምሰላቸው ይመስለኛል::

ስምንተኛ ክፍል እንደነበርኩ ፍቅር ያዘኝ:: ሜሮን ከምትባል፣ ሁልጊዜ በብዙ ሴት ጓደኞቿ ከምትከበብ ልጅ:: ደግሞ ስትስቅ ታምራለች:: ስትኮሳተር ግን ታምራለች፤ አነጋገሬ ተምታታ

አይደል ? እንዲህ ነበር የተምታታብኝ !! ቀይ ናት፣ ከቢጫነት ጋር የሚዋሰን ቅላት:: አፏ ሳቁ ያለ...ከንፈሯ ቀይና ወደታች ወረድ ብሎ የሆነ "ከምታፈጥ መጥተህ አትስመኝም!" ብሎ የሚጣራ ነገረኛ ከንፈር፤ ሕፃን ሆነን አባ ገመቹ አጥር ላይ ተንጠልጥሎ የሚያስጎመዠንን ፕሪም የመሰለ::

የላይ እና የታች ከንፈሮቿ በአንድ ላይ ሲታዩ የሆነ ልብ የሚሰውሩ የልብ ቅርፅ:: ሜሮንን በአይኔ ሳይሆን በልቤ ነበር የማያት:: ሳያት 'የልቤ ሽፋሽፍት ይርገበገባል' ! በስንት መከራ ያውም ወደ ዘጠነኛ ክፍል ስናልፍ "ሳይሽ የልቤ ሽፋሽፍት ይርገበገባል..." ብዬ ደብዳቤ ፃፍኩላት:: 'ሄለን እና 'ሃያት' የሚባሉት ጋጠወጥ ጓደኞቿ ጋር በመሆን በዚች ዓረፍተ ነገር ምክንያት ዓመቱን ሙሉ መሳቂያ መሳለቂያ አደረጉኝ:: መሪያቸው እንዲት ስሚን የማላውቃት አይጠ መጎጥ የመሰለች ልጅ ነበረች::ልክ እኔ ሳልፍ ደረታቸውን በእጆቻቸው እያራገቡ በሳቅ ያውካካሉ:: አይጠ መጎጧ በአካፋ ዓይኗ አሸዋ ወንድ ስትግፍ የምትውል ከንቱ !! ስሟን አላውቀውም፤ ስሟን አስር ጊዜ ትቀያይራለች፤...ስሟ ብዙ ነው:: ሁሉንም ስሞቿን የኢትዮጵያ ቁሶች ሁሉ እየተጋገዙ ይጥሩት !!

የእርሷ ሳቅ ሳቄን ገድሎታል:: የእርሷ የፌዝ ዕይታ ሩቅ እንዳላይ አንገቴን አስደፍቶኛል:: 'የልብ ሽፋሽፍት' የሚል ግጥም ፅፋ ለፀረ ምንትስ ክበብ ዓመታዊ ዝግጅት ሰልፍ ሜዳ ላይ አንብባ 843 ተማሪ ወደ እኔ ዞሮ ገልፍጧል:: 843 ተማሪ × 32 ጥርስ = 26 976 ጥርሳቸው ይርገፍና !! ቀይ የአስተማሪዎቹን ረስቼው ነበር:: + 23 × 32 = 736 – 32 (ቲቸር ሙሉ አንድም ጊዜ አልሳቁም)::

የፍቅር "አፒታይቴን" ምድረ ጥርሳም በሳቃቸው ቆልፈውት አስራ ሁለተኛ ክፍል ጨርሼ ዩኒቨርስቲ እስከምገባ ድረስ ሴት የምትባል ፍጥረት አጠገብ ድርሽ ብዬ አላውቅም:: እና ምን ተባልኩ ? ጨዋ !! እንኳንም ያልቀረብኩ !! ምናቸው ይቀራል?! ያች አይጠ መጎጥ፣ አስቀያሚ፣ ጥርሳም፣ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊየን ስማም !! ዛሬ የራሷ አንድ ስም እንኳን ጠፍቶ ማንም 'እንቺ' የሚላት የካፍቴሪያ አስተናጋጅ ሆናለች:: ሻይ አዞ ስሙኒ ጉርሻ ለተወላት ሰብለ፣ ቡና ጠጥቶ ለገለፈጠላት ናኒ እየሆነች እስስቷ የስሟን ቀለም እየቀያየረች አለች:: ብር ዛፍ ቁርስ ቤት ሳልፍ ሳገድም ከነቀይ ሸርጧ አያታለሁ::

ዩኒቨርስቲ የተመደብኩት እዚሁ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ነበር:: ደስ አላለኝም:: ምክንያቱም ከአዲስ አበባ ውጭ ከወላጅ ራቅ ብዬ የመኖር የቆየ ፍላጎቴ ተሰናከሏልና:: እስከፊው ነገር ደግሞ ዩኒቨርስቲው "የአዲስ አበባ ልጆች እየተመላለሳችሁ ተማሩ በቂ መኝታ የለኝም" አለ፤ ይሄ ደግሞ ዩኒቨርስቲና 'ሃይ ስኩል' የሚለያዩበትን አንድ ድንበር አፈራረሰው:: ዩኒቨርስቲ ውስጥ የገባሁ አልመስልህ አለኝ:: ወደ አስራ ሶስተኛ ክፍል ያለፍኩና እዛው የነበርኩበት ትምህርት ቤት የቀጠልኩ አይነት ስሜት ነበር የተሰማኝ:: ያ ሁሉ የተወራለት፣ በፊልም እና በሰመመን መጽሐፍ ብዙ የተባለለት የዩኒቨርስቲ ሕይወት፣ ላየው የጓጓሁለት "የግቢ ላይፍ" ውሃ በላው !! ወይ ነዶ!

አንድ አራት ወር እየተመላለስኩ እንደተማርኩ እዛው ዩኒቨርስቲው አካባቢ ቤት ተከራይቼ ለመማር ወሰንኩ:: ምንም እስቤ ሳይሆን የአዲስ አበባ ታክሲ ጊዜዬን እየበላብኝ ስለተቸገርኩ ነበር:: ማንም አልተከራከረኝም፤ ዩኒቨርስቲው ከሚወረውርልኝ ሳንቲም ላይ ቤተሰብ በየወሩ ድጎማ እየመረቀበት ቤት ተከራየሁ::...ድክም ያለች ቤት አንድ ሰፈር ውስጥ....:: እንግዲህ የእኔ ቤትና ከጎኔ ያሉት ጭርንቁስ ቤቶች በመደዳ የተሰለፉ ነበሩ:: ፊት ለፊት ደግሞ ፊታቸውን ወደ እኔ ቤት ያዞሩ በስሪትም፣ በመጠንም ከእኔ ቤት ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ሌላ መደዳ ቤቶች አሉ:: መስኮቴን ስከፍት ፊት ለፊት ያለው ቤት መስኮት ጋር እፋጠጣለሁ:: በሬን ስከፍት ፊት ለፊት ካለ በር ጋር !! በሁለቱ መደዳ ቤቶች መካከል ቀጭን የእግር መንገድ አለች:: የእኔ ቤትና ፊትለፊቴ ያለው ቤት ጣራቸው ሊገጣጠም ምንም ያህል ስለማይቀረው በመካከላችን በቀጭኗ የእግር መንገድ የሚያልፍ ሰው ረዥም ኮሪደር ውስጥ የሚያልፍ ሊመስለው ይችላል:: ከበሬ ላይ አንድ ጠቀም ያለ ርምጃ ወደፊት ብራመድ ፊት ለፊት ያለው ቤት በር ላይ አርፋለሁ:: ይሄ ነው የተከራየሁት ቤት...::

ሜሮንን ተሻግሮ ሜሮን አለች ወይ...

በአንድ ርምጃ ርቀት ጣራዬ፣ ከጣራው የሚነካካው ቤት ውስጥ ፊት ለፊቴ 'ሜሮን' የምትባል ልጅ መኖሯን ያወቅኩት ቤቱን በተከራየሁ በሁለተኛው ቀን ነበር:: በጊዜና ቦታ ርቀት ትቼው የመጣሁት "ሜሮን" የሚባል እንደ ጥላ የሚከተል ስም እዚህም መጣ:: ሜሮን...ሜሪ...ሜሪቾ... ሜሪዬ...ይላታል የመንደሩ ሰው:: ጥቁር ትሁን ቀይ አይቻት አላውቅም ነበር:: ለሰባት ወራት ያህል ጧት እየወጣሁ፣ ማታ እየገባሁ በሰላም ኖርኩ::

በአንድ ጠራራ የግንቦት ቀን ከ'ከላስ' ወደ ቤቴ እየገባሁ ነበር:: የፀሐዩ ቃጠሎ ከንፈሬን ሁሉ አድርቆታል፤ ሰውነቴ ሁሉ የተነነ ነው የመሰለኝ:: ድርቅ የመታኝ !! ቀዝቃዛ ውሃ ለመግዛት ጫፍ ላይ ወዳለች ኪዮስክ ሄድኩና "ቀዝቃዛ ውሃ ስጭኝ እስቲ" ብዬ አስር ብር ባለሰሃኑ ሚዛን ላይ ጣል አደረግኩላት:: አስር ብሩ ሚዛኑ ላይ ሲያርፍ ሚዛኑን ዝቅ አላደረገው ከፍ...
"ቀዝቃዛ የለም !" አለች አስር ብሩን በእጇ ይዛ፣
"እሽ ቀዝቃዛ ኮካ"
"ቀዝቃዛ ኮካም የለም ከውጭ ልስጥህ ?" አለች፣
"ቀዝቃዛ ነገር ምንድን ነው ያለሽ ?"

"ፍሪጅ የለኝም ከውጭ ነው ሁሉም !"

"ተይው በቃ !" ብዬ ብሬን ልቀበል እጄን ዘረጋሁ:: ቅር እያላት ብሬን መለሰችልኝ:: ፊቴን ኮሰኮስኩ: : በጣም ነበር የተበሳጨሁት:: ኤጭ!!

ቤቴ ገብቼ ቁታ ቀየርኩና ፍራሹ ላይ በጀርባዬ ተንጋልዬ በእፎይታ ተነፈስኩ:: ወዲያው በር

ሲንኳኳ በግርምት ወደበሩ ተመለከትኩ:: ጆሮዬን አቁሜ ብጠብቅም ምንም ድምፅ አልነበረም፣ መልሼ ጋደም ልል ስል በድጋሜ ተንኳኳ፤ በቀስታ ! ላለፉት ሰባት ወራት አንድም ጊዜ በሬ ተንኳኩቶ ስለማያውቅ ተገረምኩ:: "ማነው?" አላልኩም:: በቀጥታ ሄጄ ከፈትኩት:: አንዲት ቆንጆ ጠይም ልጅ በሬ ላይ በትልቅ የጠርሙስ ጆግ ውሃ ይዛ ቆማለች:: ጆጉ ላይ የገገረው በረዶ ስለሚታይ ቅዝቃዜው ያስጎመዣል:: ምራቄን ዋጥኩ እና ልጅቱን አየኋት:: እሷም ታስጎመዣለች፣ እሷን እንደመድኃኒት ውጦ በያዘችው ውሃ ማወራረድ ነበር!!

እየፈራች "ሉቅ ውሃ ጠይቀህ ስላጣህ ከቤት አምጥቼልህ ነው"አለችኝና ውሃውን ዘረጋችልኝ:: ሳላንገራግር ተቀበልኳት:: 'ቴንኪው' የለ ! ምን የለ !

ቆንጆ ነች ! በጣም ቆንጆ ነች ! በተለይ ዓይኗ፣ በተለይ ጥቁር የሚያብረቀርቅ ፀጉሯ ከቁጥርጥሩ ገና የተፈታ እንደሆነ ያስታውቃል:: በተለይ ደግሞ ጡቷ ! የለበሰችውን ስስ በዲ በሸካከቶ ሊተኮስ የተሰናዳ የሆነ ተተኳሽ ነገር !! በተለይ ደግሞ ሁሉም ነገሯ::

የተጋለጠ ደረቷ ማር የተንጣለለበት ሜዳ ይመስላል:: ቆንጆ ነበረች፣ ግን ልጅ ነበረች፤ ቢበዛ አስራ ስድስት ቢሆናት ነው:: ዘር ስትል መቀመጫዋንም እይቻለሁ...(ለምን ይደበቃል?):: ለአስራ ስድስት ዓመት ልጅ ይበዛል፤ ግን ቆንጆ...ቆንጆ እና ልጅ፣ ቆንጆ ልጅ !! እንትፍ ትፍ ትፍ አደጊ !! መቼም አዲሳባ ቆንጆ እያጣመመ ነው የሚያሳድገው !! ለማንኛውም አደጊ !!

ከእኔ በር ወደ ራሷ ቤት ስትሄድ እኔም ውብ ሰውነቷን ቆሜ ስገመግም አንድ መንገደኛ..."ታዲያስ ሜሪ !" አላት፤ እርፍ !! ሜሮን ናት ለካ !! በፍቅር ውሃ ጥም ለዓመታት ያደረቀችኝን ሜሮን የምትባል ደረቅ ወንዝ ተሻግሬ በቀዝቃዛ ውሃ ጥሜን የምታስታግስ ሜሮን የምትባል ጅረት ላይ ደረስኩ::

*ሜሮንን ተሻግሮ ሜሮን አለች ወይ...*

*ምትና ውሃ ጥም አንድ አይደለም ወይ::*

'እየጠጣህ አብርሽ !' ብዬ ራሴን ጋበዝኩት:: ቀዝቃዛውን ላንደቀድቀው ነበር፤ ግን ገና እንዴ ስጎነጭለት ጥርሶቼ ሁሉ ጠፉኝ፤ በታቸው ላይ ደነዘዙ፤ ምን እዳ ነው ! ልብም ጥርስም ደንዘዘ የት ይደረሳል !? ጥርስ የሌለው ልበ ቢስ አንበሳ የሆንኩ መሰለኝ፣ ቢሆንም አንድ የተለከሰ ነገር ነበር::

ፍሪጅ እና በኖ ውሃ በምን ይለያያል !?

ሜሮን ትላንት ያመጣችልኝን ጆግ ልትወስድ ስትመጣ ፈገግ ብዬ ተቀበልኳት:: ባዶዋን አልነበረችም:: ሌላ ጆግ ሙሉ ቀዝቃዛ ውሃ ሰጥታኝ ባዶ ጆግ ወሰደች:: ...ጆግ ውሃ ...ጆግ ...ውሃ ...፤ ከብዙ የጆግና ውሃ ምልልስ በኋላ ተቀራረብን::

"የት ነው የምትማሪው ?"

"ሚኒሊክ..." ጆግ ውሃ ...ጆግ ውሃ...

"አሳይመንት ተሰጥቶኝ ነበር ጊዜ ካለህ ትሰራልኛለህ ?"

"አምጭው ኸረ !" ብጥርጥር አድርጌ ሰራሁላት፣ አስረዳኋት፤...እንዴዴዴዴ! እንዲህ አይነት አደገኛ አስተማሪ ነበርኩ እንዴ ለካ !

ጆግ...ውሃ ...ጆግ...ዉሃ... እና አንድ ቀን ለስላሳ ቅዝቅዝ ያለ ሚሪንዳ !!

"የምን ለስላሳ ነው ሜሮን ?"

"ታዘብኩህ ዛሬ ልደቴ ነበር፣ 16 አመቴ፤ 'ሃፒ በርዝደይ!' ሳትለኝ" ፈገግ ብላ::

"በቃ ቅዳሜ ራሴ አከብርልሻለሁ"

"ፕሮሚስ ?!" ብላ የሚያምር መዳፏን በጉጉት ዘረጋችልኝ፤ ፊቷ በፈገግታ ተጥለቅልቆ ነበር::

"ፕሮሚስ !" ብዬ መዳፌን መዳፏ ላይ አስቀመጥኩ:: ለመጀመሪያ ጊዜ መነካካታችን ነበር !! እጇን አልሰበሰበችም፤ እኔም እጇን አላነሳሁም:: እግዜር "መሃላውን እስካፀድቀው እጃችሁን እንዳለ ሳይለያይ አቆዩት!" ያለን ነበር የምንመስለው:: ዓይኗ ውስጥ ፀሐይ አየሁ፤ ሁለት ፀሐይ! አማረችኝ:: የሆነ የሚያምር መናፈሻ መሰለችኝ:: ውስጧ አረፍት የተዘራ:: ሲደከም ለኖረ አንድ እኔ ሰፊ አልጋና አረፍት ያለባት አገር::

ጆግ ውሃ ...ጆግ ውሃ ...ቅዳሜ ሆነ !!

ከማክሰኞ እስከ አርብ ያላሰብኩትን ቅዳሜ ጧት ተጨነቅኩ:: የአስራ ስድስት ዓመት ልጅ ይገፔ የት አባቴ ነው የምጋብዛት ? ...ቤተሰቦቿስ ምን ይላሉ? (ለነገሩ ሴት አያቷ እና እሷ ብቻ ናቸው የሚኖሩት) ... ቢሆንም ጎረቤቱስ ምን ይላል?...ወይ ጉድ !

ሜሮን በጧት መጣች፤ ተኝታም ያደረች አልመሰለኝም::

"አንተ እስካሁን ተኝተሃል !?" አለችኝና የተኛሁበት ፍራሹ ጫፍ ላይ ተቀመጠች:: ቤቴ መግባት ፍራሽም ላይ መቀመጥ ጀምራለች:: ጧት ስትመጣ ደስ አይለኝም፤ ስስ ፒጃማ ቁምጣና ባለማንገቻ ጉርድ ቦዲ ስለምትለብስ እፈተናለሁ:: በዛ ላይ በጣም ተጠጋግተን ስለምንቀመጥ ጠረኗ አፍንጫዬን ይዞ ወደ ጡቶቿ መሃል ይጎትተኛል:: ፈተና ነው በቃ !...እርሷ ደግሞ በፍፁም 'ንጹህ' ልብ እንደፈለገች ትሆናለች::

በቃሌ መሰረት ልደቷን ልናከብር ተቀጣጠርን:: ከሰፈር አብረን መውጣቱ ለጎረቤት ሃሜት ስለሚዳርግ የሆነ እሷ የመረጠችው ሬስቶራንት ስምንት ሰዓት ላይ እንገናኝ ተባባልን...::

ነበር የደረስኩት:: ቀይ የለበሱት እኔ በበኩሌ የዚህ ዓይነት ቤት አይቼ አላውቅም፤ ቀድሚያት ነበር የደረስኩት:: ቀይ የለበሱት ጠረጴዛዎች የአገር ሹካና ማንኪያ፣ ቢላዋና የጨው የምናምን እቃ ዙሪያቸውን ተደርድሮባቸው፣ ፈዘዝ ያለ ብርሃን ያለበት አዳራሽ ውስጥ በሰፊው ተንጣለዋል::

ምቾት አይመቸኝም፤ ቅንጦት አያቀናጣኝም፤

ጨንቀኝ !

ሜሮን ስትደርስ ልቤ በድንጋጤ ልትቆም ምንም አልቀራትም:: የሚያምር አጭር ጉልበቷ ላይ የቆመ ቡና ዓይነት ቀሚስ ለብሳለች:: ውብ እግሮቿን ለማሳየት ሆን ተብሎ የተሰራ የሚመስል ረዥም ተረከዝ ያለው ጫማ፣ ጥልፍልፉ ፍርጥም ያለ ባቷ ላይ እንደሃረግ እየተጠመጠመ ወጥቶ ጉልበቷ ላይ የደረሰ...፣ ጡቶቿ ደረቱ ላይ ክፍት በሆነው ቀሚሷ ታቅፈውና ተሳስመው የሲኦል ሸለቆ እንደሰሩ...፣ ፀጉሯ ወደ አንድ በኩል ተሰብስቦ በማስያዣ ተይዟል፤ ዓይኗ በኩል ተከቧል፣ ...እህህህህህ ስታምር! የአዲስ አበባ እናቶች እድሜ አቆጣጠር አይችሉም ይሆናል እንጂ ይህቺ ልጅ አስራ ስድስት ዓመቷ ብቻ አይመስለኝም:: በዚህ እድሜ ቀጠሮን የመከሸን ሳይንስ እንዴት ነው መካን የሚቻለው? እኔ እኮ በዚህ እድሜም አልቻልበትም::

ቆሜ ተቀበልኳት፤ ጉንጫችንን አነካካነው፤ መሳሳም መሆኑ ነው:: ...አቤት ሽቶዋ! ...ፊቴ ዝም ብላ ቆመች ! ...ቆምኩ ...እሃ ለካ ወንበር ይሳባል ! ሳብኩላት፤

"ቴንኪው !" ብላ ተቀመጠች፤

"በጣም ቆንጆ ሆነሻል"

"አመሰግናለሁ" የተጠና ምልልስ መሰለብኝ እንጂ ከልቤ ነበር የተናገርኩት:: በዚህ ቀን ከሜሮን ጋር ከዘፍጥረት እስከ ራእይ አወራን:: ሜሮን ካለ እድሜዋ የበሰለች ጉድ ነበረች፤ ...እናም እንዲህ አልኩ፣

" 'አዲስ አበባ ውስጥ ከሚኖሩ ሃምሳ ዱርዬ ሴቶች ውስጥ ስላሳ ዘጠኙ ስማቸው ሜሮን ይመስለኛል' ግን ማናባቱ ነው ይሄን ቀጠራ ያካሄደው ደደብ...!"ሜሮን ጋር ተዋድደን ነበር በቃ ! እኔ ጋር በመሆኗ ነፍሷን እስከትስት ተደስታ ነበር::...እኔማ ነፍሴን ከሳትኩ ሰንብቻለሁ:: ልዩ ሰው አድርጋ እንደምታስበኝ ነገረችኝ፤ ሰፈር ውስጥ ዝምታዬ መስጧታል::

ደግሞ ወሬው ሁሉ ከየት መጣልኝ ? የሰው ሰው በሳቅ ልገድል !! እግዜር ሲያስወድድህ ብዙ ሳቅ የወደደህ ሰው ልብ ውስጥ ያስቀምጣል፤ ከዛም የውድህ ሳቅ መውጫ በር፣ መተንፈሻ መስኮት ያደርግሃል:: አንተ በፈለግከው መንገድ አፍህን ከፈት፣ ቃላትን አውጣ፤ ሜሪዬ የኔ ውብ አቤት ሳቋ ሲያምር ! እዛ ዩኒቨርስቲ "ሄይይ ምን አዲስ ነገር አለ ?" እያሉ ሳቅ ፍለጋ እንደሚባዝኑ ሕይወታቸውን በጊዜ ያሚጠጡ ደነዝ ሴቶች አይደለችም:: ቻፕስቲካም ከንፈራቸውን እስከጆሮ ግንዳቸው ለቀው በ 'ዊትኒ ሆስተንኛ' ለመሳቅ ቆርቆሮ ድምፃቸውን እንደሚያንኳኩ ኳኳታሞች

አይደለችም፤ ሜሪ ራሷ ሳቅ ነበረች፤ ፍንትው ስትል ከእግር ጥፍሯ እስከ ራስ ፀጉሯ በሳቅ የምትጥለቀለቅ ! እንደእኔ አይነቱ ሰው 'ተሳቀልኝ' ቢል ያምርበታል፤ ተስቆለታላ...!!

ልብ ነበራት፤ የፍቅር የሰላም ያልተነካካ:: 'ውይ ወንዶች!' እያሉ ያለፈ እንኩሮ ሕይወታቸውን አዲስ የፍቅረኛ ምጣድ ላይ በትዝታ ስም እንደሚጠፈጥፉ ሴቶች አልነበረችም:: ብታውቀውም ባታውቀውም ነገ ይናፍቃታል:: ማንንም አልጎዳች፣ ማንም አልጎዳትም:: ተረት አይደለችም:: "እነእከሌ ተፋቀሩ" ስትባል አትቀናም:: "ተለያዩ" ሲባል አትፈርድም፤ ከተማውን የሞላው ፈራጅኮ ግማሽ ፍርዱ በቀል ነው:: የደረሰበትን ሊበቀል፣ ያደረሰውን ሊያስተባብል...! ሜሪ ግን ብቻዋን ናት:: ብቻዋን ወደ ሕይወቴ መጣች፤ አልከበደችኝም::

ከዛን ቀን ጀምሮ ሁልጊዜ ማታ ማታ በር ላይ እንቆምና ስናወራ እናመሻለን:: ውሃ ልትደፋ ወጥታ ሊሆን ይችላል:: "ቻው በቃ መሸ !" ትለኝና ቆም ትላለች:: ከቻው በኋላ አንድ የሆነ ነገር የማድረግ ፍላጎት ሁለታችንም ልብ ውስጥ አለ:: ግን ማን ይድፈር ? ከቻው በኋላ አንድ ሰዓት እናወራለን:: "ምን አወራችሁ ?" ቢባል እንጃ !! ብዙ ጊዜ ቤቴ እንዳትገባ ሆን ብዬ እከላከላለሁ፤ ፈተናው ይከብደኛል፤ ስለዚህ በር ላይ ቆመን እናወራለን:: ወሬኛ ነኝ:: የማላወራላት ነገር የለም !! ባወራሁበት የምከፈለው ደመወዝ ሳቋ ነው:: የጠገበ ደመወዝ:: እግዜርዬ የፍቅር ዩኒቨርስቲ አስመርቆ የሰጠኝ ምርጥ ስራ - "ሃሌ ሉያ !" አስመርቆ 'ስራ ፍጠር' ቢለኝ ምን ይውጠኝ ነበር ? ሳቋ ደመወዜ ነው::...እስቃታለሁ፤ የማወራላት ምንም የማይጠቅም ነገር ቢሆንም የሳቅ ደመወዜን አስቀርታብኝ አታውቅም::

ታዲያ አንዳንዴ ማታ ቆመን ስናወራ ከሩቅ የጅብ ድምፅ ይሰማል:: እውውውው...! ወደ እኔ ጠጋ ትላለች፤ ሜሪዬ የመጨረሻ ፈሪ ናት:: ጠረኗ ይጠርነኛል:: ከምሽቱ አየር ጋር ወደ ሳንባዬ ተስገብግቤ እስበዋለሁ፤ ጠረኗን !! እሷን ራሷን እንደአየር ስቤ ውስጤ ያስገባኋት እስኪመስለኝ፤ ጅቡን እድሜውን ያርዝምልኝና በጣም ትጠጋኛለች::

ስለጅብ አወራላታለሁ:: "የጅብ ጥፍር አንገትሽ ላይ ካሰርሽ በቃ የሄድሽበት ሁሉ ሲበሉ ነው የሚያደርስሽ"

"ውሸትህን ነው ! ሂሂሂሂሂሂ..."

"ለምን እዋሸሻለሁ በሳይንስ የተረጋገጠ ነው"

"አላምንህም ! ሃሃሃሃሃ..."

"እይውልሽ የአሜሪካ ሳይንቲስቶች ናቸው እኮ ያጠኑት"

"ው....ይ ውሸት አላምንልህም ! እንዴት አድርገው ያጠኑታል ? ... ታየኝ እኮ ስንት ስራ ትተው አንገታቸው ላይ የጅብ ጥፍር አስረው ሲዞሩ ! ሂሂሂሂሂሂሂ..." ፍልቅልቅ ትላለች::

"ቀላል ነው፤ አንድ ጊዜ ይህን ጥናት እናጥና ብለው አለቃቸውን ሊያስፈቅዱት የጅብ ጥፍር አንገታቸው

ላይ ልክ እንደዚህ እንደማተብ (እንገቷ ላይ ያሰረችውን ማተብ እየነካካሁ) አስረው ሳይንቲስቶቹ ወደ ኃላፊያቸው ክፍል ሲገቡ ኃላፊው ምን እያደረገ አገኙት መሰለሽ...? በርገሩን እየገመጠ::"

"ሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃ....ውሸት ! ውሸት !"

"...ከዛ ጥናቱ ተፈቀደላቸውና ወደ አፍሪካ መጡ፤ የሆነ ሰው የማይኖርበት ጫካ አካባቢ አውሮፕላናቸው ተከሰከሰ"

"አ ማይ ጋድ ! እውነትህን ነው ?" አለች ደንገጥ ብላ::

"ያ ! ግን ማንም አልሞተም:: በተዓምር ተረፉ:: ሁሉም እንገታቸው ላይ የጅብ ጥፍር አስረዋል፤ ከዛ የሆነ ነገር ሸትቷቸው ዞር ሲሉ ጫካው ውስጥ የሚኖሩ አዳኞች ምን የመሰለች ጥንቸል ለምሳቸው እየጠበሱ..."

"ወ...ይኔ ውሸትህ ሂሂሂሂ...አልሰማህም !"

"እስኪ ጥናቱን የበለጠ ለማረጋገጥ ወደ ሌላ ዓለም እንውሰደው አሉና ናሳ ጋር ተነጋግረው ወደ ጨረቃ የሚጓዙ ጠፈርተኞች አንገት ላይ የጅቡን ጥፍር አሰሩላቸው::"

"አሁንስ አበዛኸው ሕፃን ልጅ መሰልኩህ እንዴ ?" ብላ የውሸት ተቆጣች:: ሜሪ ከዚህ ቁጣዋ ቀጥሎ የሚፈነዳውን ሳቅ ስለማውቅ ውሸቴን ቀጠልኩበት::

"ልክ ጠፈርተኞቹ ጨረቃ ላይ ሲያርፉ ከእነሱ ቀድመው ጨረቃ ላይ ያረፉ የሩሲያ ጠፈርተኞች ራት ሊበሉ ሲዘገጃጁ ደረሱ አልሻለሁ"

"ሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃ ሁለተኛ አላዋራህም እሺ ! ስታስጠላ ! እኔ ቁም ነገር የምታወራ መስሎኝ ! ሂሂሂሂ..." ሳቋ መቆሚያ የለውም:: እኔም በሳቋ ልቤ ሃሴት ያደርጋል::

እስካሁን ስሚያት አላውቅም:: 'ሳማት ሳማት...ከንፈሯን ጉረሰው ጉረሰው' ይለኛል፤ ጨለማ የሆነ ሰይጣን ነገር ሳይኖረው አይቀርም ! ቀን እዚሁ ቦታ ላይ ቆመን በጭራሽ የማይሰማኝ ስሜት ማታ የሚገፋፋ አንዳች ነገር አለው:: ወደ ደረቴ ስትጠጋኝ የጡቶቿ ጫፎች ደረቴን ሸንቁረው በጀርባዬ በኩል ብቅ ያሉ ይመስለኛል:: ...ፈተና ነው !

ጅብ ሲጮህ ስለጅብ አወራታለሁ:: ድመት ከጮኸ ስለድመት፤ አበባ ካለች ስለአበባ...:: ስናወራ ስናወራ ሰካራሙ ጎረቤታችን ጉግሳ እየተወላገደ፣ እየዘፈነ ይመጣል::

"አንተ ጉግሳ መጣ አራት ሰዓት..." ትላለች ሜሪ:: ጉግሳ አራት ሰዓት ላይ እንደሚመጣ የታወቀ ነው፤ የመንደሩ ሰዓት ነው ጉግሳ:: ወሬ ሲወራ ሁሉ '...ልክ ጉግሳ ሲመጣ...' ይባላል:: ልክ አራት ሰዓት እንደማለት:: እየዘፈነ፣ እየገጠመ (ኢያዝናና እና ኢያስተማረ ይሉታል ሲፎግሩ) ከተፍ ይላል፤ ጉግሳ::

*ለአግሩ ሜማ የለው ለራሱ ባርኔጣ፤*
*የቅጣቸው ለባት አሁን ገና መጣ::*

ይላል ጉግሳ (ቅጣቸው ልጁ ነው):: ወተር ወተር እያለ በጨለማው ውስጥ ሲራመድ የእማማ ትሩፋት ቡችላ ትጮህበታለች:: ው ው ው ው ው ው ው ው...!!!

ጉግሳ ቆም ብሎ ቡችላዋ ወዳለችበት ግቢ በንቀት እየተመለከተ፤

"ቡችላ...! ወንድ ከሆንሽ...የእመቤትሽ ውሽሞች አጥር ሲዘሉ አትጮሂም ? በአገልግል ዶሮው ተቋጥሮ በጓሮ በር ለውሽሞች ሲላክ አትጮሂም ? ...ውሻ ...የውሻ ልጅ !! ...ይቅርታ ! ደግ እናትሽን አሰደብሽኝ...! ነፍሷን ይማርና እናትሽ ጥሩሩሩሩሩሩ ውሻ ነበረች:: ቤቴ ድረስ ሸኝታኝ ነበር ቤቷ የምትገባው:: ...የልጅ ዘመድ የለውም አንች..." አይጨርሰውም::

ጉግሳ እኔና ሜሪን ያየናል:: ከእርሱ በፊት ቀድሞ አጠገባችን የሚደርሰው የአረቄና ጠጅ ሽታው ነው:: ቆም ብሎ ንፋስ እንደገፋው ዛፍ እየተወዛወዘ ኮፍያውን ያወልቅና በአከብሮት ጎንበስ ብሎ (በግንባሩ እንዳይደፋ እሰጋለሁ) "ወጣቶች ልጆቻችን...የነገ አገር ተረካቢ እንደምን አመሻችሁ...! ሃሃሃሃሃ...!! እኛንም እንዲህ ነበር ድሮሮሮሮሮ የሚሉን፤ ኪኪኪኪ...:: የአገር Cከከቡ ሲዘገይ እየጠጣን እንጠብቀው ብለን ሰካራም ሆንን ! ሃሃሃ..." ይላል በሰካር ድምፅ::

"ደህና አመሹ ጋሽ ጉግሳ!" እንለዋለን::

ትክ ብሎ ያየንና፣ "መፋቀር ጥሩ ነው፤ እጅግ በጣም በጣም...ጥሩ ነው !! ይሄ ቡዳ ሰፈር! ቡዳ እንዳይበላችሁ ቤት ግቡ!" ይለናል:: ሜሪ ሳቋን አፍና ዝም ትላለች::

"መጽሐፉ...ጋብቻ ቅዱስ ነው ይላል፤ ደግሞ ፍቅር ከሌለ ቆርቆሮ...ቁራሌ ቆረቆንዳ ነህ ይላል፤ እኔ አሁን አምሳልን አፈቅራታለሁ:: አስራ ሶስት ዓመት ስንኖር ተጣልተን አናውቅም:: ለምን ?...ፍቅር ይሻላላ !! መጽሐፉ ተፋቀሩ ይላል !...ጎበዞች ! አይዟችሁ ደህና እደሩ !" ይልና እየተወላገደ ያልፋል:: ሜሪ ደረቴ ላይ ድፍት ብላ በሳቅ ፍርስስስስ ትላለች::

ጉግሳ ትንሽ አለፍ እንዳለ፣ "እያንዳንድሽ ወየውልሽ ! ...በየጥጋጥጉ እየቆምሽ የምትባልጊ ሁሉ! ...ወየውልሽ !" ይላል እጁን ወደ ሰማይ ዘርግቶ፤ አመልካች ጣቱን እየነቀነቀ:: "መጽሐፉ... በጨለማ የሰራሽውን ሁሉ በፀሐይ አገልፀዋለሁ፤ ስራሽን እንደ በርበሬ ዛላ፣ እንደታጠበ ልብስ፣ ለወፍጮ እንደተዘጋጀ የሽሮ ክክ ፀሐይ ላይ አሰጣዋለሁ ይላል መጽሐፉ!...ወዮልሽ...! አርፈሽ አትማሪና ኮከብ ስትቆጥሪ እምሽ...!" ካለ በኋላ በዜማ ይቀጥላል፤

*እንኳን ቤትና የለኝም አጥር፣*
*ሊደጅ ሊድራለሁ ኮከብ ስቆጥር...*

"...ኮከብ ቆጣሪ አስማተኛ ሁሉ...!!" ሌላ ርዕስ ውስጥ ይገባል፤ ጉግሳ እንዲህ ነው::

ሜሪ ጋር አንዳንዴ 'ወክ' እናደርጋለን:: ንፁህና ፀጥ ያለ ኤምባሲ አለ:: በሱ በኩል ማታ ከንዴን ደገፍ ብላኝ በጣም ተነካክተን ብርዱ ለስላሳ ቆዳችን ላይ የፈጠራቸው መንደብደቦች - የእኔ እንድብድቦችና የሜሪ እንድብድቦች እየተነካኩ፣ ሽቶዋ እየተቀላቀለብኝ ደስ ብሎን እንዝናናለን:: ስንሄድም ሆነ ስንመለስ አገር ቢያየን ግድ አልነበረንም:: አሁን እውርተናል:: 'ውስጤ ውስጥ ነሽ' ብያታለሁ፤ 'ወድጄሻለሁ!' ብያታለሁ፤ ምንም አላለችኝም፤ ግን አንባዋ መጥቶ ነበር::

አንድ ቀን ከ'ወክ' ስንመለስ እኔ ቤት ገባን:: ፍራሽ ላይ እግሯን አነባብራ ዘርግታ ተቀመጠች:: ቀሚሷ ስላጠራት ትንሽ ተጨናንቃ ነበር:: አጠገቧ ተቀመጥኩ:: ሁለታችንም የሆነ ነገር በጣም በጣም ፈልገናል፤ ግን...፤ አየኋት ቀሚሷ ላይ ባለች ቁልፍ ትጫወታለች:: ፈራሁ ! ... አዕምሮዬ በሀሳብ ተራወጠ፤

1. የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንዲት ሴት አስራ ስምንት ዓመት ሳይሞላት ወዳና ፈቅዳም ሆነ ሳትወድና ሳትፈቅድ ወሲብ ብትፈፅም፣ ወሲብ የፈፀመባትን ሰው ዘብጥያ ...ከርቸሌ... ወላ ጀሜ አስገባው ይላል!!

2. ሕገ እግዜር ወዳ ፈቅዳ ሴት ወንድ ምናምን አይልም፤ "አታመንዝር!" በቃ !! ከፈለግክ የከጀልካትን ሴት አግብተህ እንዳሻህ ሁን:: አለበለዚያ አምሮትህን 'ሲያምርህ ይቅር!' ብለህ ገስፀው:: ከዚህ በተረፈ ሲኦል ወላ ጀሀነም ትወረወራታለህ ! ይላል::

3. የእኔ ይዞ ሟች ልብ የሜሪን የሚያምር ባት፣ የፈረጠመ ዳሌና ጫፋቸው የሚጣራ ጠይም ጡቶች እያየ ከምድራዊውም ከሰማያዊውም ሕግ ሊያጋጨኝ በደም ፍላት ደም ይረጫል:: ልቤ ሲደልቅ ግግም ግግም...ግግም ሲል አንድ ታዋቂ ትግረኛ ዘፋኝ ከነከበሮ ደላቂው በልቤ አዳራሽ የሙዚቃ ስራውን የሚያቀርብ ይመስለኛል::

የልቤ ምክር፣ "እብርሽ ሜሪ ትወድሃለች:: ያደረጋችሁትን ለማንም አትናገርም:: ደግሞ እያት ከንፈሯ እንዴት እንደሚንቀጠቀጥ...ስትንከረፈፍ አንዱ እንዳይልፍህ !...እጆችህን ጡቶቿ ላይ አሳርፋቸው - አይዞህ ጠጋ በላት...:: ኤጭጭጭጭ የምን መጨናነቅ ነው...የወንጀል ሕጉ አንጀባ ነው ባክህ !...እግዜር ደግሞ እንኳን አንተን ስንቱን ይቅር ብሎ የለ !? ...ኧረ ሳይመሽ ፍጠን ! ነገ በዚህ ስሜት አታገኛትም:: እንደውም ያልፈለካት መስሏት በዛው ነው የምትቀረው...ቱ..." ብሎ ደም ይተፋል ልቤ፤

እነሆ በህገ እግዜር፣ በወንጀለኛ መቅጫ ህግና በግልፍተኛ ልብ መሃል ሚስኪኑ አብረሃም...

ሜሪ አንድ እግሯን ሰብሰብ ስታደርገው ከጠይምነቷ የቀላ ለስላሳ ታፋዋ ተጋለጠ:: ቀሚሷን ሳብ አደረገችው፤ ግን አልሸፈናትም:: ቀጥ ብላ አየችኝ:: አይኗ ቡዝዝ ብሎ ነበር:: ትከሻዬ ላይ ራሷን ደገፍ አደረገችው:: ...ኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡ ጠረኗ አመንዝር ይለኛል::

ውቢቷ አመንዝር ይለኛል...። ልቤ አመንዝር ይለኛል...። ቤቱ አመንዝር ይለኛል...። ሁኔታው አመንዝር ይለኛል...።ፍራሹ "ኑ እንጂ እየጠበቅኳችሁ አይደለም እንዴ! የምን መጎለት ነው!' ይለኛል። እርግጠኛ ነኝ ሰይጣንም እንደአምፌ ቲያትር ከነጅሪው ተሰብስቦ እያየን ነው።

ሜሪ በቀኝ እጄ ጣቶች እየተጫወተች ነበር። አቤት እጇ አለሳለሱ !! ደግሞ ይሞቃል ! ...ቆይ ምናባቴ ነው የማደርገው ? ... ሕግ ይሄን ያያል ? አያይም ! ?

ሕግ የሜሪ ጡቶች ማማራቸውን እንደቅጣት ማቅለያ ያያል...?

እናቴ አበባ ይዛ ምርቃቴ ላይ ለመገኘት ካሁኑ ስታወራ ምን ያህል በደስታ እንደምትምነሸነሽ እያወቅኩ...ምርቃት በቴሌቪዥን ባየች ቁጥር "አሁን የኔ ልጅ..." እያለች በደስታ እና በተስፋ ፊቷ ላይ የምትለኩሰውን ብርሃን እፍ ብዬ ላጥፋው ? "ልጅሽስ ?" ስትባል (ኧረ ሳትባልም።) በኩራት "ዩኒበርስቲ ገባኮ" እያለች በሳቅ የምትምነሸነሽ እናቴን በሐዘን አንገቷን ደፍታ እስር ቤት ስሃን ይዛ እድሜ ልኳን እንድትመላለስ ልፍረድ ? ... ከሁሉም በላይ እግዚያብሄር ይቅር ባይ ነው፤ ልክ ነው ! የንስሃ ቀብድ ግን አይቀበልም። "ላጥፋ እንዴ፣ ይቅር ትለኝ እንደሆን ?" እንደማለት !!

የሜሪን እጅ ከእጄ ላይ አነሳሁ። ከፍራሹ ላይ ተነስቼ ቆምኩ፤ ከዛም "መሽ አይደል ?!" አልኳት፤ "ውጪ" ነበር የሚመስለው አነጋገሬ - ገብቷታል። ተነስታ ልብሷን አስተካከለችና "አንተ ፍሪጅ አያስፈልግህም፤ ራስህ ማቀዝቀዣ ነገር ነህ" አለችኝ። "ደህና እደር!" ሳትለኝ ወጣች፤ አልተመለሰችም!! የፍሪጅ ውሃውም በዛው ቆመ !!

እግዚያብሔር ታዲያ እንዲህ ሲል በታላቅ ድምፅ ያወጀ መሰለኝ፤

"ልጄ አብረሃም ሆይ ! ህግጋቴን ላከበሩ፣ በፈተና ሰዓትም የቃሌን ጭላንጭል ሊመለከቱ ለተፍገመገሙ ሁሉ፣ አንድ ጀግ ቀዝቃዛ ውሃ ቢከለከሉ እንኳን ስለነሱ ዓለምን በቀዝቃዛ ውሃ እረሰርሳታለሁ !!!"

ከረምት ገባ !!

ዝናብ፣ ውሽንፍሩ፣ ደመናው ... አዲስ አበባ ቀዝቀዝ አለች !! ከረምቱ የእኔ ከረምት መሰለኝ።

አዲሳባ ውስጥ ፍሪጅ ካላቸው ሃምሳ ሴቶች መካከል ሃምሳውም ስማቸው ሜሮን ይመስለኛል፤ የፍሪጆቹ ዓይነትና ስም ቢለያይም ባህሪያቸው አንድ ነው፤ "አመድ በዱቄት መለወጥ" በሰጣት የፍሪጆቹ ዓይነትና ስም ቢለያይም ባህሪያቸው አንድ ነው፤ "አመድ በዱቄት መለወጥ" በሰጣት ጠብታ ውሃ ጎርፍ ማግኘትን በውለታ መልክ መቀበል ያምረዋል - ፍሪጁ !! ፍሪጁን ከነስጦታው የሚሹ ይሄ ታላቅ ከረምት የእነርሱ አይደለም !!

ፍራሼን ተመለከትኩት፤ ሰፊና ንፁህ ነው። ብቸኝነት ሰላም፣ ፍራሹም ሰፊ ነው።

# 17 የታረሙ ነፍሶች

እጅጋየሁ ማታ ሦስት ሰዓት ላይ በቤታችን ስልክ ደወለች... 'ማዘር' ጋር አስራ አምስት ደቂቃ የሚሆን ሲያወሩ ቆዩና ጥግብ ሲሉ ማዘር እንዲህ አለች፣ "አብርሽ ስልኩ ያንተ ነው ና እናግራት...ቶሎ በል እንዳይቆጥርባት እጅግዬ ናት::"

እጅጋየሁ ሰባትና ስምንተኛ ክፍል አብረን የተማርን ጓደኛዬ ናት:: ይሄው እስካሁንም እንኳን ከኔ ጋር፣ ከቤተሰብ ጋርም ጥብቅ ወዳጅ ሆና ቀጥላለች:: በተለይ ማዘር ጋር በከፉ በደጉ ይጠያየቃሉ፤ እንደውም እውነቱን ለመናገር እጅጋየሁ ከእኔ ይልቅ የእናቴ ጓደኛ ነው የምትመስለኝ:: ከልቧ ጥሩ ልጅ ናት:: የታመመ አሳዳ የምትጠይቅ፣ ሃዘን ካለ ከሃዘንተኛው ሳትለይ የምታፅናና (ጊዜው እንዴት ይበቃታል?) ሰርግም ካለ የጥሪ ካርድ ከማዘጋጀቱ ጀምሮ እስከቤተሰብ ቅልቅል ጎንበስ ቀና ብላ የምታዳድር ሌሎችን የማገልገል ፀጋ ያትረፈረፈላት ልጅ ናት:: እች ናት እጅጋየሁ !!

እኔ ታዲያ ወሬዋ ይሰለቸኛል:: ይንዛዛል:: ማቋረጫ የለውም (ስለእጅጋየሁ ወሬ ለእናቴ ስነግራት ግን 'ይንዛዛል' አልልም፣ የምለው "ትንሽ ወሬዋ ዘለግ ይላል" ነው:: እናቴ ታዲያ እንዲህ አሳምሬም ነግሬያት ትበሳጭብኛለች፣ "ሂድ አባክህ ወሬኛ ! ዝም ብለህ ወረቴ አለቀ አትልም... ዘለግ....አጠር !! ሆዷ ከፋት የለውም፤ ውስጧ ያለውን ሁሉ ስለምታወራ ነው፣ 'እንደሌሎቹ' ነገር በሆዷ የምታብላላ 'ማሸንክ' አይደለችም::"

እንግዲህ "ሌሎቹ" እና "ማሸንክ" የሚሉት ቃላት ዝምተኛዋንና የአሁኗን ፍቅረኛዬን 'ቤዛ'ን ኢላማ ያደረጉ የእናቴ ጥይቶች ናቸው፤ እናቴ ቤዛን አትወዳትም:: ከእጅጋየሁ ጋር እንድንጋባ ነበር ፍላጎቷ:: ምን ያደርጋል፣ እጅጋየሁም አይታኝ አይታኝ አገባች:: (ኧረ እንዲያውም የዛሬ ስድስት ወር አካባቢ 'ወለድኩ' ብላ ማዘር ሄዳ አይታታለች::) እኔም ከቤዛ ጋር ፍቅር ጀመርኩ::

ከስምንተኛ ክፍል ወደ ዘጠኝ አልፌ ወደ ሌላ ትምህርት ቤት ስዘዋወር እጅጋየሁ ደገመችና

እዛው ስምንተኛ ክፍል የተማርንበት ትምህርት ቤት ቀረች:: ታዲያ ልክ መስከረም ገብቶ ትምህርት ስንጀምር ደብዳቤ ፃፈችልኝ:: ደብዳቤዋ ላይ መቼም የማልረሳው ግጥም ነበር::

የባህርዳር ቅጠል ዳርዳሩ ለስላሳ፣

ተለያየን ብለህ እንዳንረሳሳ::

እኔም ያለሁ አዲስ አበባ እሷም ያለች አዲስ አበባ፣ "ባህርዳር ድረስ ሄዶ ቅጠል የሚያስበጥስ፣ ሙሾ የሚያስወርድ ምን ጉድ ተፈጠረ?" አልኩና ተገረምኩ:: እጅጋየሁ ነገረ ስራዋ ሁሉ የትልቅ ሰው ነበር ፤ ያኔ ትልቅ ሰው ማለት ዛሬ ላይ አካባጅ የሚለውን ቃል ይተካል::

ይሄው ዛሬ ደግሞ ደወለች:: መቼም የደወለችበት ምክንያት ወይ የታመመ አልያም የሞተ ሰው ቢኖር ነው:: ሁለቱም ግምቶቼ ልክ ካልሆኑ ግን የሚያገባ ጓደኛችን አለ ማለት ነው::

"ሄሎ"

"አንተ...ወይ የሰው ነገር:: በቃ እንዲህ በዋል ፈሰስ ሆነህ ቀረህ ? ምን ይሻልሃል ? ወለድኩ ብዬ አፍ አውጥቼ ተናግሬ 'ማሪያም ትማርሽ!' ማንን ገደለ ?"

"አይ...ኧ..." አፍሬ ነበር::

"ተወው ተወው... ደህና ነህ ግን ? ስራ ጥሩ ነው ? ቤዚዬስ እንዴት ናት ? ባለፈው መንገድ ላይ አግኝቻት ጉንፋን ያዘኝ ብላ፣ ተሽላት ? ውይ የሷ ነገር በሽታ አትችልም እኮ ሂሂሂ" የትኛውን ልመልስ ? ትቀጥላለች:: "አብርሽ ልጄ አለቀሰችብኝ፣ ቶሎ ጉዳዬን ልንገርህ...ቲቸር በለጠ እኮ ሞቱ..."

"ምን...?"

"ይሄውልህ ዛሬ አረፉ:: ነገ ሥላሴ ነው ቀብራቸው፣ ልንገርህ ብዬ ነው፣ ከተመቸህ ብቅ በል - አብርሽ ...አባክህ ከሰው አትለይ..."

"ትቀልጃለሽ በዚህማ አይቀለድም:: ...ለቲቸር በለጠ ቀብር ...ብሞት አልቀርም ለምን ሺ ስራ ጥንቅር አይልም" አልኩ::

"ግን ምን አገኛቸው በናትሽ...?"

"ሚስታቸው...እንገብግባ ገደለቻቸው::"

"አትቀልጅ ባክሽ"

"እመቤቴን ! በስተርጅና እንዲት እሳት አግብተው፣ ቀን ምድረ ውሪ ጋር ሲዳረቁ ውለው ሲገቡ እሷ ደግሞ ማታ ከቤት በምላሷ ትጠብሳቸዋለች:: ቢቃ ሳይደላቸው ድፍት አሉትና አረፉ፣ ከንፈሯን መጠጠች::

"የሚስት ምላስ ቢደፋ ኖሮ ቢኒ ገና ድሮ..." ቢኒ ባሷ ነው::

"አትምጣሞጥ አንተ! እኔይቱ ልጅት!" ሳቋ ይቀድማታል:: ነገ መምህር በለጠ ቀብር ላይ ልንገናኝ ተቀጣጥረን ተለያየን::

*** *** ***

ምንጊዜም የአማርኛ ክፍለጊዜ ሊጠናቀቅ ሲል እሮጌ የሸራ ቦርሳቸውን ከፍተው በስርዓት ከተሰደሩ ወረቀቶች መሐል አንድ በካኪ ወረቀት የተሸፈነ ትልቅ መፅሐፍ የሚያወጡ፣ ከወገባቸው በመጠኑ ጎበጥ ያሉና ትንሽ ዘርፈፍ ያለ ቅጠልማ ሹራብ የሚለብሱ እድሜያቸው ወደ ሃምሳ ዓመት የሚሆን ሰው - መምህር በለጠ !!

ተማሪዎቻቸው መልስ ስንመልስ ትናንሽ ዓይኖቻቸውን ጠበብ አድርገው በጥሞና ሲመለከቱን በዓይናቸው የሚያዳምጡን ይመስለን ነበር:: መምህር በለጠ !! በመምህር በለጠ ክፍለ ጊዜ ደስታችን ፊታችን ላይ ይንበለበላል:: የማይወዳቸው ተማሪ አልነበረም:: መስፍን እንኳን አምስት 'ፔሬድ ዘግቶ' በእሳቸው ክፍለ ጊዜ ቢሞት አይቀርም::

እንደውም አንድ ቀን በቲቸር በለጠ ክፍለ ጊዜ ለመታደም በአጥር ዘሎ ሲገባ ተይዞ ወላጅ ጠሪ፣ የመስፍን አባት፣ "ይሄ የልጄን የትምህርት ፍቅር ነው የሚያሳየው፣ ዘሎ ሲወጣ አልተያዘም ዘሎ ሲገባ እንጂ" አሉ:: መስፍን ከግቢ ውጭ የበላው ፓስቲ የዘይት መሃተሙን ከንፈሩ ላይ እንዳተመበት በቲቸር በለጠ ክፍለ ጊዜ ከተፍ ይላል - ያውም ፊት ወንበር ላይ !! በሒሳብ ክፍለ ጊዜ መስፍን 'ፊት ወንበር ሂድ!' ከሚባል ሞያሌ ድረስ በባዶ እግሩ ቢሄድ ይሻለዋል::

...በካኪ ወረቀት የተሸፈነው መጻሐፍ ይከፈታል፣ "ፍቅር እስከ መቃብር" ነው !!

በመምህር በለጠ ሊተረክ ተከፈተ:: ምድረ ማቲ አይናችን፣ አፋችን አብሮ ተከፈተ:: ፍቅር እስከ መቃብር ተነስቶ መምህር በለጠን አለማንሳት፣ ከመጻሐፉ ላይ በዛብህን ከመርሳት አይተናነስም፣ እንደውም ፍቅር እስከ መቃብር ገለጥ ገለጥ ቢደረግ፣ በዛብህ...ሰብለ ወንጌል...ጉዱ ካሳ...መምህር በለጠና...ፊታውራሪ መሸሻ እኩል የመጻሐፉ ገፀ-ባህሪያት ሆነው የሚገኙ ይመስለኛል::

በሚያምር ድምፃቸው ትረካውን ይጀምራሉ:: ከዝምታችን ብዛት የልብሳችን ቁማታ ይሰማል፣ ጭጭ...መምህር በለጠ በትረካቸው መሐል የግል አስተያየታቸውን ይጨምራሉ:: አንዳንዴ አስተያየቱን ጣል የሚያደርጉት በሚተርኩበት ድምፅና ፍጥነት ስለሆነ አስተያየቱን ከታሪኩ መለየት ያዳግተናል ፤ ቢሆንም አስተያየቱን የታሪኩን ያህል እንወድደዋለን::

እንደ ፊታውራሪ እየጎደሩ፣ እንደ በዛብህ እየተቅለሰለሱ፣ እንደ ሰብለ ረጋ ብለው፣ እንደ ጉዱ ካሳ እያፌዙ እና እያሸሞሩ፣ እንደ ሃብትሽ ይመር እየተቆናጠሩ፣ እንደ ቂስ ሞገሴ እየተሽቆጠቆጡ በግርምት አስጥመውን...እያለ ኪሊሊሊሊሊሊሊሊ ይላል ከፍለ ጊዜው ማብቃቱን የሚያረዳው ደወል፡፡ ኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡ...ኤጭጭ...! በየአፋችን እንንጫጫለን፡፡

'ቲቸር' መጸሐፉን ደጋግመው ደጋግመው ስላነበቡት የሚበልጠውን በቃላቸው ነበር የሚወጡት፤ እያነበቡ ድንገት በመሐል አንዱን ወይም አንዷን ተማሪ ይጠራሉ፣

"ሃና!"

"አቤት ቲቸር!" ድንገት በመጠራቷ ደንግጣ ታፈጣለች፡፡ የከፍላችን ጎበዝ ተማሪ ናት ሃና...

"የሰው ልጅ መሰረታዊ ፍላጎት ምንድን ነው ?" ይጠይቋታል፡፡

"ምግብ...ልብስ...መጠለያ..." መለሰችው እንላለን እኛ በሹክሹክታ፡፡ ገና ትላንት ነው አካባቢ ሳይንስ መምህርታችን ያስተማረችን፡፡

"አይደለም ! በጭራሽ አይደለም ! ሳይንሱ እውነታውን ጋርዶብናል፡፡ እንጀራን ማን ህሊና ውስጥ ቦታ ሰጠው ? 'የምድር ፍሬ፣ የወንዝ ውሃ ይሙላህ' የተባለን ሆድ ማነው የሰው መሰረት ያደረገው? የለም! በየጫካው በየዱሩ ርቃናቸውን የሚኖሩ ወገኖቻችን ርቃናቸው ጌጣቸው ነው፤ ቤትስ ቢሆን - የሰው ልጅ ተንኮሉን ሊከልል፣ ማካፈሉን ሊጋርድ ግድግዳ አቆመና 'ስስታም' እንዳይባል 'ቤት መሰረታዊ ፍላጎት ነው' አለ - ለግርዶሹ ስም አወጣ፡፡ ልጆች ልብ በሉ...የሰው መሰረታዊ ፍላጎት አንድ ነው፣ እሱም ፍቅር ነው፡፡ ካለፍቅር ሰው የቁም ሙት ነው፡፡ ሰው ሰውን ሲያፈቅር፣ ሰው አምላኩን ሲያፈቅር፣ ሰው አገሩን ሲያፈቅር፣ ሰው እውነትን ሲያፈቅር፣ ሰው ነፃነትን ሲያፈቅር ነው ህያው የሚሆነው፡፡ ሰው ነገውን ሲወድ፣ ነገውን ሲያፈቅር ነው ነገ ለሚፈጠር ትውልድ ፍቅር የሚያወርሰው ... እስትንፋሱ የሚቀጥለው፡፡ በሉ መልሱልኝ፣

"በዛብህ እንጀራ አጣ?" ይጠይቁናል፡፡

"አላጣም!" በአንድ ላይ እንመልሳለን፡፡

"ልብስ አጣ?"

"አላጣም"

"ቤትስ?"

"አላጣም"

"አያችሁ! ፍቅርን ብሎ፣ ፍቅርን ተርቦ፣ ፍቅርን ተራቁቶ ሲንከራተት አባይ በረሃ የሽፍታ ሲሳይ ሆኖ ቀረ!" እዝን ብለው በመስኮት ወደ ውጭ እየተመለከቱ ከቆዩ በኋላ፣ "ፍቅር ነው የሰው መሐሉ" ይሉና ሁላችንንም ያዩናል...

መምህር በለጠ ይሄው ሞቱ ! እጅጋየሁ እንዳለችው በሚስታቸው ብስጭት ሞተው ከሆነ የሰበኩትን ፍቅር አጥተው ሞቱ !!

ሃና የክፍላችን ጎበዝ ተማሪ ታዲያ ያሏትን 'ለቀም' አደረገችና የአካባቢ ሳይንስ ፈተና ላይ የሰው መሰረታዊ ፍላጎት 'ፍቅር' ነው ብላ በመመለሷ 'ኤክስ' ገባባት::

ቲቸር በለጠ ይሄን ሰምተው ሳቅ አሉ፤ ከዛም ረጋ ብለው መከሩን፣

"ልጆች! በሉ የተባልነውን ስንላችሁ ብቻ ነው ትምህርት ተማራችሁ የሚባለው:: የነፍስ ሃቅ ትምህርት መስሏችሁ ተቀብላችሁ አትሩጡ!! ነፍስ ያመነው እና ወረቀት የሚያምነው የተለያየ ነው:: ይሄን አትርሱ:: የነፍስን እምነት የሚሸከም ትከሻ ያለው ወረቀት እምብዛም ነው:: ስንቱ ነብሱ ሹክ ያለውን ለወረቀት ሹክ ብሎ እንጦሮጦስ ወርዷል !!" ብለው በዝምታ ከዳር እስከ ዳር የተኮለኮልነውን ተማሪዎች ይቃኙንና ድንገት፣

"ሃና !" ብለው ይጣራሉ፣

"አቤት ቲቸር!"

"...አስተማሪሽ ነፍስሽን ማረም አትችልም፣ ለዛ ነው 'ኤክስ' የገባብሽ" ካሉ በኋላ የሃናን አማርኛ ደብተር ወስደው በቀይ እስክርቢቶ ፈረሙበት:: "አማርኛ ፈተና ላይ ሁለት ነጥብ ጉርሻ ሰጥቼሻለሁ::" የሃና ነፍስ ታረመ !! (ሃኒን ከብዙ ዓመት በኋላ አንድ ዓለም አቀፍ ስብሰባ ላይ በጦርነት ስለሚጎዱ ህፃናትና እናቶች የምርምር ወረቀት አቅርባ በቴሌቪዥን አየኋት:: ያቀረበችውን ወረቀት አፈላልጌ አነበብኩት:: እውነትም ሃኒ ነፍሷ ታርሟል::)

መምህር በለጠ...ትረካቸውን ቀጥለው እንደፈዘዝን...ድንገት፣

"አንተ እሳት ትውልድ ዝሙትና ፍቅር የየቅል ነው:: ስብለ ዝሙት ብትሻ እንደ ውሻ እግሯን የሚከተል መኳንንት ነበረላት:: ልብ በሉ ... ትዳር አያስጨፍርም:: 'ብቻዬን ከመውደቅ ሁለት ሆኜ ልውደቅ' የሚሉም ጅሎች ናቸው ፤ አብሮ መሆን እና አንድ መሆን የየቅል ነው:: ትዳር አንድ መሆን ነው !! በጥቅም በሰከረ ትዳርና በፍቅር በሰከረች ስብለ መሐል አንድ የሰከረ እርምጃ ሲቀር ፍቅር በመሐል ገባ::

...በላይ ዘለቀ ከነተከታዮቹ ቤልጅግ ይዞ የናኘበትን ጫካ ስብለ ፍቅር ታጥቃ ብቻዋን ዘመተችበት:: በላይም ለአገሩ ፍቅር፣ ስብለም ለበዛብህ ፍቅር ... አያችሁ ... የአባይን በረሃ

የሚያሸግር ድልድይ ምንድን ነው ... ፍቅር !! ያልተበረዘ ያልተከለሰ ሃቅን ወደ ትውልድ ማስተላለፊያው መንገድ ምንድን ነው ? ፍቅር!! ሰብለ አንበሳና ነብሩን ፊት ለፊት ተጋፈጠች ...!"

"መስፍን!"

"አቤት ቲቸር!"

"...አንተ ዱርዬ ፓስቲ ቤት ለፓስቲ ቤት ልጃገረድ ይዞ መዞር ፍቅር አይደለም..." የክፍሉ ልጅ በሳቅ ያውካካል:: መስፍን ሁልጊዜም ከሴቶች ጋር ሻይ ቤት መታየቱ የታወቀ ነው::

"አበባ!"

"አቤት!"

(ወደ አበባ በመጽሐፉ እየጠቆሙ) "ከማንም ጎረምሳ ጋር ሲገቡና ሲወጡ መላፋትና መጓተት ፍቅር አይደለም:: ፍቅር ራስን ያስከፍላል:: ፍቅር ብታገኘውም ያስከፍልሃል፣ ብታጣውም ያስከፍላል ... ክፍያው የየቅል ቢሆንም !!"

መምህር በለጠ በአማርኛ ክፍለ ጊዜ የፍቅር ሰዋሰው የሚያስተምሩ፣ የነፍሳችን ስንኝ ከፍቅር ስንኝ ጋር ቤት እንዲመታ የገሰፁን መምህር ይሄው እንደተባለው ከሆነ 'ፍቅር ተርበው' ሞቱ !!

"...እሳት ትውልድ ንቃ፣ ዘመኑ የእነ ቄስ ሞገሴ ዘመን ነው:: ተመሳሰሎ፣ ተለጥፎ የመኖር ዘመን:: ሆድን እናት ላይ አስቀምጦ እዩኝ ማለት:: ፊት ለፊት 'ለምን?' ከማለት ፊት እያዩ፣ ፊትን የመምሰል አስለትነት አዋቂ የሚያስብልበት ዘመን ነው:: አብብነት ዝና የሆነበት:: እነጉዱ ካሳን የማውገዝ ዘመን..." ይላሉ ሲናገሩ አንዳንዴ ከተረከዛቸው ብድግ ብለው በጥፍራቸው እየቆሙ መፅሐፉን በአመልካች ጣታቸው አልባትነት ከፍለው ይዘው ከፍ ዝቅ እያደረጉ ስለሆነ፣ የሙዚቃ ኦኬስትራ መሪ ይመስሉ ነበር::

ሞቱ መምህሩ !!

አንድ ቀን 'አበበ በሶ በላ' ብለው ፃፉና፣ "አበበ አንተ ነህ፣ አበበ እኔ ነኝ፣ አበበ በዛብህ ... አበበ ሰብለ ናት:: ... አበበ ጉዱ ካሳ፣ አበበ ቄስ ሞገሴ፣ አበበ ፊታውራሪ መሸሻ ... አበበ ወዛደሩ፣ አበበ ምሁሩ":: አነጋገራቸው ስብከት ይመስል ነበር::

" ... አበበ ሰብለ ስትሆን፣ በሰው ... የታሰርክበትን የባህል ሰንሰለት በፍቅር ቢላዋ መበጣጠስ ነው:: ... የጥቅም ጣኦትህን አሽቀንጥረህ የፍቅር ፅላትህን ማንገስ ነው:: አበበ በዛብህ ሲሆን፣ በሰው መርገምትና ማስፈራሪያን የናቀ ፍቅር ነው:: ሌሎች ሰራላቸው ደስታ የሚኙብህን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሰእለት ማሽቀንጠር ነው::ላልተሳልከው ስእለት ህይወትህን

አለመስጠት !! አበበ ፊታውራሪ መሸሻ ሲሆን በሰው ቅራሪ ርዝራዥ የዘር ማንዘር ኩብር ነው ... በዘር መኮፈስ ... ትዕቢት፡፡ አበበ ጉዱ ካሳ ሲሆን፣ በሰው በጨለመ ዘመን በአብደት ደመና የተሸፈነ መብረቃዊ መገለጥ ነው..." አሉና ኮስተር ብለው ቃኙን፡፡

ይሄው 'ቲቸር በሰጠ' ሞቅ !!

*** *** ***

የቲቸር በለጠን አስከሬን ከተሸከሙት ሰዎች መካከል አንዱ እኔ ነበርኩ፡፡ ከፊቴ መስፍን አለ፤ አስከሬኑ ከበደኝ፡፡ የተሸከምኩት የመምህሬን ኮሰማና አካል መሆኑን እስከጠራጠር አስከሬኑ ከበደኝ... !!

በአብረቅራቂ ልብስ ተሸፍኖ በእሳት ትውልድ ታጅቦ ወደ መቃብር የሚጣደፈው አስከሬን ጋር ...ሰብለ ...በዛብህ ...ጉዱ ካሳ ...ፊታውራሪ መሸሻ ...የኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍ ...ታላላቆቹ የጥበብ ሰዎች ...ፍቅር ራሱ አብረው ወደ መቃብር እየተወሰዱ መሰለኝ፡፡ ካለነገሩ አልከበደኝም ይህ አስከሬን !! አህሳ ...ማን ተረፈ፣ ...እነ ቄስ ሞገሴ አልቃሽ ሆነው፣ ቀብር ቆፋሪ ሆነው፣ አጃቢ ሆነው ምድርን ሞልተው...

አበበ መምህር በለጠ ሲሆን፣ በሰው ነፍሱ የታረመ ትውልድ ነበር!!

ይሄን ያለ ግን አልነበረም፡፡ ሁሉም ሰው የሚያወራው ስለሚሰታቸው ኢቃጣይነት ብቻ ነበር፤ ከሟቹ ይልቅ የሞቱ ምክንያት መማነኑ የሞተን ሰው ሥራ ህያው ከማድረግ ይልቅ የቋሚን መቆም በምክንያት መዝለፍ ስለሚቀል ይሄንኑ ተራ መንገድ የመከተል አምልኮ መሰለኝ፡፡

# በብረትና ቻፕስቲክ በተከበበ ከተማ እነሆ የመልአክ ድምጽ ተሰማ

# 18

እንዲት ፍቅረኛ ነበረችኝ:: ይሄን አደረገኝ ሳትል ርግፍ አድርጋ ተወችኝ:: የተወችኝ ሰሞን አዕምሮዬ ነገር እየቀላቀለ አስቸግሮኝ ነበር:: የምይዝ የምጨብጠውን አጥቼ ነበር:: ብዙ ነገር ነበር:: በተለይ ደግሞ ከተለያየን ከአምስት ወር በኋላ እንደወለደች ስሰማ "እንዲት ሴት የምታረግዘው ስንት ወር ነው?" ብዬ አሰብኩ:: መቼም ከእኔ አለማርገዟ ጥያቄ አልነበረውም፤ ምክንያቱም "ከጋብቻ በፊት ዝንቤን እሽ እንዳትል!" ብላኝ ስለነበር ቃሏን አክብሬ ከመሳም ዘልዬ አላውቅም::

ለዛውም ከንፈሯን እያሳደድኩ ነበር የምስማት:: በደቡብ በኩል ከንፈሬን ሳሞጥሙጥ ወደሰሜን እየዞረች፤ ከሰሜን ስንደረደር ወደ ምስራቅ እየሸሸች ፍዳዬን አብልታኝ ነበር የኖርነው:: ስንትና ስንቱ ከንፈሯን የሳተ ከንፈሬ ባዶ አየር ስሟል:: አየር ስታስመኝ ከርማ በመጨረሻ አየር ላይ ትታኝ ሄደች:: ደግሞ እኮ የአካሄዷ ከፋት "ቻው" ማለት ማንን ገደለ ? "አልፈልግህም!" ማለት ምን ችግር አለው ? አንድ ቅዳሜ ደውዬ "ዛሬ እንገናኝም እንዴ ፍቅር?" ስላት "ለምንድን ነው የምንገናኘው ?" ብላ ግራ የገባው ጥያቄ ጠየቀችኝ:: ቢቃ በዛው ቀረች::

እና ይሄው በተለያየን በአምስት ወሯ ወልዳ አረፈችው:: ነርስ ነበረች፤ በኋላ ስሰማ አንድ ዶክተር ነው አሉ ያገባት:: እኔ ባድግ "ዶኩተር እሆናለሁ" እንዳልኩት ፍቅረኛዬ "ሳድግ ዶክተር አገባለሁ" ብላ ሳትመኝ አልቀረችም:: ከዛ በኋላ የሴት ዘር ጠላሁ:: በተለይ ነርስ የሚባሉ ሴቶች፤ ዶክተሮች ራሳቸው በሽታ ፈዋሽ ሳይሆኑ በሽታ መስለው ታዩኝ:: ለዛ ነው ሆስፒታሎች ሲኦል የሚመስሉኝ:: ለእኔ በሽታ ማለት ወደሞት ሳይሆን ከሞት የባሰ ወደምጠላቸው ነርስና ዶክተሮች የሚወስደኝ የሲኦል መንገድ ነው::

*** *** ***

ስምኑን ታዲያ ወደ አንድ የግል ሆስፒታል ጎራ ብዬ ነበር:: በሕይወታችን ውስጥ የጠላታችንን ደጅ የሚያስጎበኙን የባሱ ጠላቶች ይገጥሙን የለ ! በቃ አመመኝና ወደምጠላው ሆስፒታል ሄድኩ:: ሆስፒታሉ ውስጥ ለቁጥር የሚያዳግቱ 'ሴት' ነርሶችን ስመለከት "ይህ ነገር የግል ክሊኒክ ነው ? ወይስ የግል ሆስፒታል ?" ብዬ አሰብኩ::

ገና በሩ ላይ ስደርስ አንዷት በተናገረች ቁጥር ከንፈሯ ጆሮዋ ጥግ እና ጥግ እየደረሰ የሚመለስ እዚያው ሃዲድ ከንፈሯ ላይ የደፈደፈችው ቻፕስቲክ አፏን ፀሐይ ላይ የተቀመጠ የቅቢ ቅል ያስመሰለው ነርስ ወደኔ መጣችና በቁሙ የሞተ ፈገግታ እያሳየችኝ፣ "ምን ልርዳክ ?" አለችኝ፣ ስትናገር ቃላቶቹ ያዳልጣቸዋል - ቻፕስቲኩ ይሆን ?! ጥርሷ በብረት ታስሯል:: እስኪ አሁን እስኪፈታላት ብትታገስ ምን ትሆናለች ? 'ካልሳቅሽ ወየልሽ!' ያላት አለ ? መቼም የዚህች ነርስ ጓደኛ ብሆን (አይበልብኝና) ከንፈሯን እንድታሳስረው ነበር የምመክራት::

"እኔ እንኳን የመጣሁት እናንተን ለመርዳት ነው" አልኩ ስለ ከፍያቸው ውድነት ማሽሞሬ ነበር፤ እርሷ ግን ፊቷ በፈገግታ ተጥለቀለቀ፤ አቁነጠነጣት:: 'የተናገርኩት ይሄን ያህል ያስደስታል ወይንስ የእውነት የእርዳታ ድርጅት ልከኝ የመጣሁ መስሏት ነው?' እያልኩ ስገረም "እ..ው...ኬ..! አዲስ የተመደቡት ዶክተር እርስዎ መሆን አለብዎት?" ብላኝ እርፍ:: አቤት 'ኦ..ኬ..!' ላይ ከንፈሯን እንዴት እንደምታደርገው ! አንዳንድ የከተማችን ዘመነኛ ሴቶች በእንግሊዝኛ የከንፈር ቀመር አማርኛ ካላወሩን እያሉ ከንፈራቸውን ለጥጠውት ሊሞቁ ነው::

ልጅቱ በደስታ ተጥለቀለቀች:: "ክርስቶስ ሊፈውስህ መጣ" የተባለ የአድሜ ልክ በሽተኛ እንኳን እንደሷ አይፍነከነክም:: የቃልኪዳን ቀለበቷን አውልቃ ሳትደብቀው በፊት (ማን ይሆን ያገባት?) ፈጠን ብዬ "እኔ እንኳን ልታከም የመጣሁ በሽተኛ ነኝ" አልኳት:: ወዲያው ፊቷ ላይ የተጥለቀለቀው የሳቅ ማዕበል ድራሹ ጠፍቶ፣ "ተከተለኝ" አለችና ወደ ካርድ ክፍል መራችኝ፤ እየተቆናጠረች፣ የሆነ ሰበር ሰካ የማለት ሙከራ ዓይነት:: እች አረማመድ ለአዲሱ ዶክተር ተቀምራ የተቀመጠች ሳትሆን አትቀርም::

ካርድ ክፍሉ ውስጥ አንድ እግሯን አጥፋ ተሽከርካሪ ወንበር ላይ የተጎለቱች ሌላ "ቻፕስቲካም ሴት፣

"ስምህ" አለችኝ፣

"ስሜ ምን ሆነ ?" ስል ጠየቅኳት:: ልክ አማርኛ ዘጠነኛ ቋንቋዬ ሳይመስላት አልቀረም::

"አይ ስምህ ማነው ማለቴ ነው"

"እ...አብረሃም !"

"እድሜህ ስንት ነው ?" (ማስቲካዋን ቀጭ)...

"250 ብር ክፈል!"አለችኝ፤ከፈልኩ::

ካርዱን አቀበለችኝ:: እየሁት ስሜን አሳስታ ነው የፃፈችው::

"ስሜን አሳስተሽዋል" አልኳት፣ በመስተዋቱ ሽንቁር ጎንበስ ብዬ::

"ቶ_ሪ! እስኪ...አብርሃም...አይደል ስምህ?" አለች ስህተቷ አልገባትም::

"አዎ አንቺ ግን 'አርሃም' ብለሽ ነው የፃፍሽው 'ቢ'ን ረስተሻታል::"

ኮስተር ብላ አዲስ ካርድ አወጣችና እያቀበለችኝ፣ "ስምህን ሞልተህ ትሰጠኝ?" አለችኝ፣ የቅሬታ ፈገግታ እያሳየችኝ:: የዚህችም ጥርስ በብረት ታስሯል:: ደምዛቸውን ቻፕስቲክና የጥርስ ማሰሪያ ብረት የሚከፍሏቸው ነው የሚመስሉት፤ ወይስ "ሆዴን ከመቻል ተርፎ ጥርሴን የሚያሳስር ባል ወላ ጓደኛ አለኝ" መልዕክት ነው ?!! መቼስ የአዲስ አበባ ወንድ ብሩ ተረግሟል::

ስሜን ሞልቼ ሳበቃ "እድሜዬንም ልሙላልሽ?" አልኳት፤ ሆን ብዬ ለማበሳጨት ነበር:: የመንጠቅ ያህል ካርዱን ከእጄ ላይ ወሰደችና የምትሞላውን ነገር ሞልታ፣ "ዶ/ር ሰናይት ጋር ነህ:: ከፊትህ አምስት ሰው ይቀድምሃል" አለችኝ:: በጣም ተበሳጭታለች::

"ይቅርታ ወንድ ዶክተር የላችሁም ?" አልኳት:: በረዥሙ ተንፍሳ ካርዴን ተቀበለችኝና "ዶክተር እምሃ" ብላ ፃፈችበት::

"አመሰግናለሁ!" አልኳት በሚያበሳጭ ድምፅ፤ ከዛም ካርዱን እየሁትና ተመልሼ..."ይቅርታ የዶክተሩን ስም ማን ነበረ ያልሽኝ?" አልኳት::

በግርምት አየችኝና "ዶ/ር እምሃ 3 ቁጥር ላይ" አለች ቃሉን ረገጥ አድርጋ::

"'እማ' ነው የሚለው፤ 'ኤች' የለችም" አልኳት ካርዱን እያሳየኋት:: (የእውነትም የለችም ነበር):: ስልችት ብያት እንጎሽግሻት በመጨረሻ ትዕግስቷ አስተካከለቻት::

ወረፋ ስጠብቅ ከፊቴ የሚቀድሙኝ አራት የሚሆኑ ሴት ታካሚዎች እየገቡ በጣም ከቆዩ በኋላ በጣም እየሳቁ ይወጣሉ:: አረማመዳቸው ራሱ ይቀየራል:: እየተንኳተቱ ገብተው እንደ ሞዴል እየተውረገረጉ ይወጣሉ:: "ውስጥ የተቀመጠው ዶክተር ነው ወይስ 'ኮሜዲያን'?" እያልኩ ሳስብ ተራዬ ደረሰና ለመሳቅ ተዘጋጅቼ ገባሁ:: ወይ መሳቅ !

ጎልማሳ፣ መላጣ ዶክተር ኮስተር ብሎ በአስከርቢቶው ወንበር ጠቆመኝ:: ስታይሉ ነው መጨረሻ ላይ ያስቀኛል...

"እሽ አብርሃም! እንዴት ነው የሚያደርግህ?" አለኝ ከበፊቱ በባሰ ኮስተር ብሎ፤ የመጨረሻዋን ሴት እኔ ያባረርኳት ሳይመስለው አይቀርም...መላጣ! ምናባቱ ያኮሳትረዋል?!

ብሩ ተንኳኳ::

"ይግቡ!" አለ:: የመጨረሻዋ ታካሚ ነበረች ተመልሳ የገባችው:: ስልኳን ረሲታ ልትወስድ ነበር:: (በሽታዋ አልዛይመር ነበር እንዴ?) ዶክተሩ ፈገግታው ፈነዳ:: "አኬ !" ብሎ ተነስቶ በሁለ እጁ አቀበላት:: ዳሌዋ ሰፋ ያለ መልከመልካም የሃብታም ሚስት ነገር ናት:: ልክ ስልኳ ሲሰጣት የሆነ ዓይነት ለየት ያለ መተያየት ያየሁባቸው መሰለኝ::

"ቴንኪው ዶክተርዬ !" ብላው በተረከዘ ረጅም ጫማዋ ወለሉን እየደቃችው እና እየተውረገረገ ወጣች:: የሽቶዋ ጠረን ግን ክፍሉን ሞላው:: ዶክተሩ ከተዘጋው በር ላይ ዓይኑን መሰብ ፈገግታውን አከሰመው:: ልክ 'እፍ' እንዳሏት ሻማ ወደ እኔ ሲዞር ፈገግታው ድርግም ብሎ ጠፋች::

"ይቅርታ...(ካርዴን እየት አድርጎ) አብርሃም...! እንዴት ነው የሚያደርግህ ?"

ነገርኩት::

"ያስቀምጥሃል?"

"አያስቀምጠኝም"

"ያስመልስሃል?"

"አያስመልሰኝም"

('ስልኬን ብረሳም አያስመልሰኝም' ብለው አሪፍ ነበር:: 'በሽተኛ ቅኔ አያምርበትም' ብ ተውኩት::)

"ምግብ ይዘጋሃል?"

"አይዘጋኝም!"

"የመቆረጣጠም ስሜት አለው?"

"የለውም !!"

ታይፎይድ ለማለት ቋምጦ ነበር::

ስላበሳጨኝ ባጭሩ ነበር የምመልስለት:: 250 ብሬን ከፍዬ ይገላምጠኛል እንዴ ደሞ ?ይህ የሕፃናት ምኞት የሆነ ስራውን ሊኮራበት ይፈልጋል:: ደግሞ ምን ያጣድፈዋል? ከእኔ በፊ የገቡት ሴቶች በሌላ በር የወጡ እስኪመስለኝ ነበር የቆዩት::

"እጅጌህን ሰብስብ" አለኝ ማዳመጫውን ጆሮው ላይ እየሰካ:: ኧረ ይሄን ሰው አንድ በሉት ጉርድ ሸሚዝ ለብሼ እጅጌህን ሰብስብ ይላል:: ለምን ከቀልቡ አይሆንም ?!

ቀዮሎ ደረቴ ላይ ማዳመጫዋን ለጠፋትና (አቤት መቀዝቀዟ!) "ተንፍስ!" (ትንሽ ወደ

አለ እንዳልተነፍስበት) እንጀቴን አሳረረው:: አጥንታም ደረቴ ላይ ቀዝቃዛ ማዳመጫውን ለጥፎ "ተንፍስ!" ይለኛል:: ከእኔ በፊት ያከማትን ሴት ደረት እያሰበ መሆን አለበት:: (ታዲያ ምን አቆየው ? ወይስ የተጎዳ ልቤ ዶክተር መሆኑን አውቆ ሲጮህበት ሰምቶ ይሆን?) ወረቀት ላይ ምልክት አደረገና ወደ ላብራቶሪ ላከኝ:: ላብራቶሪ ማለት በተለይ የግል ሆስፒታሎች ቫይረስ፣ ባክቴሪያ፣ ጀርም እና የታካሚውን ብር ፈልገው የሚያገኙበት ቦታ ነው!!

ወደ ላብራቶሪው ስገባ 'መልዓክ' ጠበቀኝ:: ቢቃ መልዓክ ነጭ ጋውን ለብሶ !! ውብ የሆነች ልጅ ከመቀመጫዋ ተነስታ ተቀበለችኝ:: ያውም በፈገግታ!! አቤት ፈገግታዋ ሲያምር! ልክ የህንድ ፊልም ላይ አክተሩ ያፈቀራትን ሴት ሲያይ እንደሚፈዘው ፈዘዝኩ...:: አቤት ፈገግታ! ምን የተባረከ በሽታ ነው ዛሬ እዚህ የጣለኝ ? ጥርሷ በብረት አልታሰረም:: (ከአስራቱ ነፃ ወጥቶ ይሆን?) ቁመቷ ደግሞ ሲገርም...! እኔ እንኳን ረጅም የምባለው ትከሻዋ ላይ ቀረሁ!! በዛ ላይ የድምፅዋ መለስለስ ! ወላ መስረቅረቅ...! ቆዳዋ ጥርት ከማለቱ ብዛት አንገቷ ስር ያለው ደም ስር ጥቁር አረንጓዴ ሆኖ ይታያል:: ወረቀቱን አየችና "ምን ገጠመህ አብርሽ?" አለችኝ:: አፌ ቁርጥ ይበል ! መኪና ሙሉ ብርቱካን፣ ተሳቢ መኪና ሙሉ ሙዝ፣ ቡቴ መኪና ሙሉ የማንጎ ጭማቂ ይዞ ሌላ ሰው ከሚጠይቀኝ እሷ በሳምንት አንዴ "ምነው አብርሽ?" ብትለኝ እመኑኝ እፈወሳለሁ!!

"ትንሽ አመመኝ" አልኳት:: ካለውትሮው የራሴ ድምፅ ጨዋ ሆኖ ተሰማኝ:: እንድታዝንልኝ ሳልፈልግ አልቀረሁም::

"ቆየብህ ?" ጥያቄዋን ቀጠለች:: መርፌና ስሪንጅ እያዘጋጀች:: ጋዜጠኞች ጥያቄና አጠያየቅን ከዚህች ልጅ ቢማሩ ምናለበት?

"እይይ ትላንት ነው የጀመረኝ" አልኳት:: ወደዛ ወደዚህ ስትል ዓይኔ አብሯት ይንከራተታል:: አቤት ዓይኔ ሲያሳዝን...! ደግሞ መቀመጫዋ ሲያምር! ጨከና እዚህ መቀመጫ ላይ መቀመጧ ገረመኝ::

"እ! ጥንቁቅ ልጅ መሆን አለብህ ፤ በጊዜ ነው የመጣኸው::እስቲ እጅህን እዚህ ጋር አድርገው! ጨብጠው ! ከንዴ ላይ ያረፉት ውብ ጣቶቿን ተመስጬ እያለሁ::ጣቶቿ የእኔ ደም ስሮች መሰሉኝ፣ ጥፍር ቀለም አልተቀባችም:: ቀይ እና ረዣዥም ጣቶቿ ተወዳዳሪ የላቸውም::

የላስቲክ ጓንት ስታጠልቅ ከፍት አለኝ:: በጣቶቿ ውበት ብቻ ለፈውስ ተቃርቤ ነበር:: ያልቅ የላስቲክ ጓንት ስታጠልቅ ከፍት አለኝ:: በጣቶቿ ውበት ብቻ ለፈውስ ተቃርቤ ነበር:: ደሜ ወደ ስሪንጁ ሲገባ የገረመኝ እለንጋ ጣቶቿ ላስቲክ ለብሰውም ውበታቸው አለመደብዘዙ:: ደሜ ወደ ስሪንጁ ሲገባ እየሁት:: ልንገራችሁ አይደል...! "አብርሽ እግረመንገዴን ለቀይ መስቀል ደም ልውሰድ እንዴ?" ብትለኝ እንስራ ሙሉ ደም በደስታ እለግስ ነበር:: አይ ቀይ መስቀል...! ምን አለ ይህችን መልዓክ ቀመስ ልጅ በቴሌቪዥን ብቅ አድርጎ "ደም ስጡ !" ቢልና ህልሙን ቢያሳካ፣ እንዴ ፈገግ ብትል ለኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ከፈሰሰው ደም በላይ፣ እይተነውም ሳናየውም ከፈሰሰው

ደም በላይ እንለግስ ነበር።

"አሳመምኩህ እንዴ?" አለችኝ ድንገት ፈገግ ብላ። ለኔ ግን ፈገግግግግግግግግግ ሆነ! የላብራቶሪው ቅራቅንበዎች ሁሉ የሳቁ መሰለኝ። አጉሊ መነፅሩ አግሩን አንስቶ የሳቀ መሰለኝ።እጋነንኩት፣ ደግ አደረግኩ !!

"ኧረ አላመመኝም !" አልኩ ፈገግታዋን በፈገግታ እየመለስኩ። እሷን የሆንኩ መሰለኝ። በታ ባቋ ግድግዳውም ላይ፣ መደርደሪያውም ላይ፣ እኔም ላይ ነጥሮ ይመለሳል። "ዓለም የገደል ማሚቱ ይሁንልሽ!" ብሎ የመረቃት ሰው አለ።

ይህችን የመሰለች ቆንጆ እዚህች ቀዝቃዛ ክፍል ውስጥ መገኘቷ ገረመኝ። ቁራጭ ቆንጆና ይዘው ከተማውን የሞሉት ምድረወልጋዳ፣ ወልካፋ፣ ጉረኛ፣ ቻፕስቲካም፣ 'ሂዩማንሄራም'፣ ከሃሳ ሁሉ ታይፈስ እየያዛቸው እዚህ በመጡና በቅናት ደም ግፊት ጨምረው በሄዱ!!

ትንሽ የፕላስቲክ ብልቃጥ እየሰጠችኝ "መፀዳጃ ቤት ትሄድና በዚህች ትንሽ...ታመጣለህ" አለችኝ ፤ ደበረኝ፣ ለምን እንደሆነ እኔንጃ! በዕርግጥ እቺን ለመሰለች ልጅ፣ ቆንጆ አንቡጥ አበበ ይዞ መሄድ እንጂ ከመፀዳጃ ቤት በብልቃጥ "..." ይዞ መሄድ ደስታ ሊፈጥር አይችልም። ምን ይደረግ ሰኔና ሰኞ ገጠሙብኝ። ቢሆንም "በዚህች ትንሽ...ታመጣለህ" ስትለኝ "..." ራሱ እሷ ስትጠራው ሲያምር! 'ይሄ ነገር ከዚህ በፊት ስሙ እንዲህ ያምር ነበር እንዴ!' አልኩ ለራሴ ።

ወጥቼ ወደ መፀዳጃ ቤቱ ስሄድ አንዲት ጠረንገሎ ነርስ ቆማ በስልክ እያወራች ትገለፍጣለች ማስቲካ እያላመጠች ፀጉሯን ስልክ ባልያዘው እጇ እያፍተለተለች በስልክ የሞቀ ወሬ ይዛለች፤ "ይቅርታ ሽንት ቤቱ በየቱ ጋር ነው?" አልኳት ሆን ብዬ 'መፀዳጃ ቤት' የሚለውን ቃል አልተጠቀምኩም።።ስልክ እንደያዘች ያላየሁ በመምሰል ነበር ጮክ ብዬ የጠየቅኳት፣ በምልክት ጠቆመችኝ...የስልኩ ወግ ያጓጓት ትመስላለች። አሁን ከዘጋው የደወለላት ሰው መቼም የማይደውልላት ይመስል።

"ይቅርታ ወደ ግራ ነው?" ያልገባኝ መስዬ ጠየቅኳት።

ስልኩን በእጇ መዳፍ አፈነችና "ወደ ቀኝ በዛጋ ስትታጠፍ" አለችኝ በትህትና ድምጽዋን ዝቅ አድርጋ ዓይኗን እያስለመለመች። ትህትና አያምርባትም። የተጠና ትህትና መሆኑ ያስታውቅባታል አንዳንድ ሴቶች ትህትና አያምርባቸውም። እንደሰፊ ሸራብ ፊታቸው ላይ ሲንዘላዘል ከልባቸው እንዳልሆነ ያስታውቅባቸዋል። ትህትና በቀመር አያምርም። ትህትና ከእውነተኛ ማንነት ሌሎችን ሳይሆን ራስን ከማክበር ፈንቅሎ የሚወጣ ባህሪ ነው። ብዙ ቦታ ያጋጥሙኛል ያልፈጠረባቸውን ባህሪ ዓይናቸውን እያስለመለሙና ድምፃቸውን ለመስማት እስከሚያስቸግር ዝቅ አድርገው "ጨዋ" ለመባል የሚሞክሩ ለዛ ቢሶች። እንዷ የእኔ ፍቅረኛ የነበረችው ነርስ ነበረች፣

ፊቴ ቁጣ መንገድ የጠቆመችኝን ነርስ "ታዲያ በምልክት ያሳየሽኝ እኮ ወደ ግራ ነው...ግራና ቀኝሽን ሳትለይ ነው የሽንት ቤት አቅጣጫ ጠቋሚ አድርገው የቀጠሩሽ?!" ብያት መንገዴን ቀጠልኩ:: ስልኩን በመዳፏ እንዳፈነች በግርምትና በብስጭት አፈጠጠችብኝ:: "ሳልሰማ የአዕምሮ ህክምና ጀመርን እንዴ?" ሳትል አትቀርም::

መፀዳጃ ቤቱ እየተፀዳ ስለነበር የፅዳት ሰራተኛዋ "ይቅርታ እዛ ተጠቀም ለጊዜው" አለችኝ በትህትና:: የሴቶችን መፀዳጃ ቤት እያሳየችኝ:: "አይይይ! ከተፀዳ ሲአል ያልተፀዳ መፀዳጃ ቤት ይሻላል" አልኳት:: አልገባትም:: ምን ይገባታል? ከመናር ብዛት ሴትነት ገነት መስሏት!!

የላብራቶሪ ውጤቴ ጋር የወሰድኩት ነገር አስደሳች ነበር:: የላብራቶሪ ቴክኒሻኗን ስልክ !! ሃሃሃ "በደማችን ያመጣነውን ስልክ ማንም አይቀማንም" ማለት ዳድቶኝ ነበር:: ደግሞ ስሟ ሲገርም "መና" - ጠበቅ አድርጋችሁ አንብቡት !! ይሄን ስም ሌሎች ሴቶች ላይ ከሰማችሁት ስትፈልጉ ላላ አድርጋችሁ ማንበብ ትችላላችሁ::

*ለመና ግጥም ፃፍኩላት፤*

*አይንሽን ለማየት ሁልጊዜ እንድመጣ፤*

*ከሰኞ አስከ ሰኞ ምናል ጤና ባጣ!!*

"...አብርሽ ተሻለህ...?" በቀጣዩ ቀን ደውላ መና ደህንነቴን ጠየቀችኝ:: 'የሰው መውደድ ይስጥህ!' ከተባላችሁ መልዓክንም እንደሚያጠቃልል እንዳትረሱ!!

"አብርሽ እንዳልጠይቅህ ቤትህን ደበቅከ..." ከ 3 ቀን በኋላ ደውላ...

ጉድ በል ጎጃም...አለ !

"...እኔ የምልሽ መናዬ ደም ስትወስጂ በስህተት ልቤን ወስደሽው ይሆን እንዴ....?" ያልኳት ፊቷ ላይ የይለፍ ምልክት ካየሁባትና ተቀጣጥረን አራት ኪሎ አካባቢ ቡና ከጠጣን በኋላ ነበር::

ሳቀችልኝ...! በሳቅ ፍርስስስስ አለችልኝ:: 'ያወራኸው ይጣፍጥልህ!' ተብላችሁ ከተመረቃችሁ መልዓክትም ይስቁላችኋል:: ሌላ ቀን የፅሁፍ መልዕክት ላከችልኝ - hi Arish...:: 'ቴ' ተረስታለች፤ "ቢ" ፊደልን ድሮም አልወዳት - እንኳን ረሳቻት!!

# 19 ዝግመት ለውጥ

ረኸም ነገር አልወድም፡፡ ረኸም ቁመት እንደ ሰብለ፣ ረኸም መንገድ በእኔና በእነሰብለ ቤት መካከል እንዳለው፣ ረኸም ወሬ ሰብለ እኔን አስቀምጣ በስልክ እንደምታወራው፣ ረኸም ዕድሜ እንደሰብለ አያት እና ረኸም ቀን እንደዛሬው... ዛሬ እሁድ ነው !

እሁድ ከመርዘሙ የተነሳ የሚመሸው ከነገ ወዲያ ይመስለኛል፡፡ እሁድ ለእኔ መጀመሪያና መጨረሻ ያለው ዘላለም ነው፡፡ "ለምን?" እንዳትሉኝ፣ ታሪኩ ረኸም ነው፡፡ ረኸም ታሪክ አልወድም፣ እንደ እኔና እንደሰብለ የፍቅር ታሪክ፡፡

ሰብለ ፍቅረኛዬ ነበረች፡፡ ሰብለ የሚለው ስም በዝግመት ለውጥ የተገኘ ይመስለኛል፡፡ ሰላቢ... ሰለበ...ሰብለ... እያለ የተሻሻለ ዓይነት፡፡ እሁድም ከ24 ሰዓት ተነስቶ ዘላለም የሆነ...

ዛሬ እሁድ ነው፣ 'ይሄ ጋግርታም ሕፃን እሁድ፣ አርጅቶ መካነ ሰኞ ውስጥ እስኪከተት ምናባቴ እየሰራሁ...የት አባቴ ሄጄ ላሳልፈው ይሆን?' እያልኩ እሰባለሁ፡፡ አንድ ሀሳብ መጣልኝ፡፡ ቤቴ በር ላይ ተቀምጬ ፀሐይ እየሞቅኩ የሆነ ነገር ማንበብ...በቃ !

ኩርሲ ነገር አወጣሁና ተመልሼ ከጠረጴዛዬ ላይ የሚነበብ ነገር ስፈልግ አንድ ጋዜጣ አገኘሁ፣ መልሼ አስቀመጥኩት -ረኸም ጋዜጣ ነው ! የሰብለ አባት ይሄን ጋዜጣ ይወዱት ነበር... ነብሳቸውን ይማረውና... እሳቸው የሞቱ ቀን የቀብር ሥነ ሥርዓቱ አረዛዘም መቼም አይረሳኝ...፡፡ ከሰው የተለየ ኃጢያት የተበተባቸው ይመስል ፍትሀቱ ረኸም ነበር፡፡ ለነገሩ አራጣ አበዳሪ ነበሩ፡፡

ሀሳቤን ቀየርኩና ጋዜጣውን ይዤ ወጣሁ፣ ፀሐዩ ሲጠነክር አናቴ ላይ ባል አደርገዋለሁ፡፡

በር ላይ ቁጭ ብዬ አላፊ አግዳሚውን መመልከት ጀመርኩ፡፡ እማማ ትሁኔ የሸሮ እህል

ያሰጣጣሉ፤ የሚገርሙ ሴትዮ - ሁልጊዜ የሚያሰጡት ነገር አያጡም። የሚሰጣ ነገር ቢጠፋ፤ የማሰጫውን ሰማያዊ ፕላስቲክ ብቻውን ያሰጡታል። ታዲያ ያሰጡትን ቢያሰጡ፣ ስጡ ላይ አንድ ሁለት ከሰል ጣል ማድረጋቸው አይቀርም። አንድ ቀን ጠየቅኋቸው።

"እማማ ትሁኔ!"

"ወዬ አብርሽ"

"ይሄ ከሰሉ ምንድን ነው ?"

"የቱ ?"

"ይሄ ስጡ ላይ ያለው"

"እረ...ይሄን እስከዛሬ አታውቅም? ሆሆ..." ካሉ በኋላ ባለማወቄ ተገርመው አጭር ማብራሪያ ሰጡኝ።

"ይሄ እንግዲህ...ስጥ ስታሰጣ አንድ ሁለት ከሰል ጣል ካደረግክበት ሰላቢ አጠገቡ አይደርስም፤ መዳኒት ነው" አሉ ወደ አልማዝ ቤት እያዩ - ፅበኛ ናቸው።

"ሰላቢ ምንድን ነው ?"

"የሚሰልብ ነዋ...አንተ ይንበርበቴ በጥሰህ ሰላቢ ይጠፋሃል....ሰላቢ ባይኑ የሚሰልብ ነው - ያየውን ነገር ሁሉ ላጥ የሚያደርግ። እህል አይል፤ ዘይት አይል፣ ሊጥ አይል...የተጋገረ እንጀራ - በቃ አየት ሲያደርጋት ሽው ነው...ወደቤቱ ያጋባታል ..." አሉ አልማዝ እንድትሰማ ጮክ ብለው።

ከሰል ከሰላቢ ቢያድን እኔ ኩንታል ከሰል ተሸክሜ ሰብለን ስከተላት በዋልኩ ነበር። አንድ ሰላቢ ባለጋራጅ ነው የሰለበኝ። ለነገሩ ሰብለ እንኳን ከሰል ጣል ማድረግ፣ ከሰል ጉድጓድ ውስጥ ቢያስሯትም መሰለቧ አይቀርም። ሲፈጥራት ሰላቢ ነገር ነበረች። ከፍቅር የበለጠ ምን ከሰል አለ? ሲያቀጣጥሉት የሚንቀለቀል እሳት። የከህደት እመድ ሲያለብሱት፣ የተዳፈነ ረመጥ፤ ሲያጠፉት ጥቁር ታሪክ ! ከፍቅር የባሰ ምን ከሰል አለ?!

አንድ ባለጋራጅ ነው ከእጄ ነጥቆ ሰብለን የወሰዳት። ምን ይወሰዳታል፣ ሄደች እንጂ። አንዳንዴ ከሥራ ስወጣ፣ በምታምር ቀይ መኪና ሲሸኛት እንተጣጠማለን። ጋቢና ተቀምጣ በኩራት ታየኛለች፣ 'እየህ ያለሁበትን' ዓይነት መኩፈስ። ሰው ከሰው ልብ ላይ ወርዶ፣ ቆርቆሮ ውስጥ ስለተቀመጠ ይሄን ያህል መኩፈስ ነበረበት?

በ'ሬ ላይ ተቀምጬ አላፊ አግዳሚውን መመልከቴን ቀጠልኩ። ኢጫጮ...መምሬ ታምሩ ሳር ቅጠሉን ሰላም እያሉና እያሳለሙ መጡብኝ!! ምክራቸው ረዥም ስለሆነ ሳያቸው ገና ይደክመኛል። እንግዲህ "ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም"

ሊሉኝ ነው፤ ታዲያ ለእሳቸው ስል ከማን አባቴ ጋር ልሁን? የእናቴ ንስሀ አባት ነበሩ፣ እሳቸው ግን ራሳቸውን የእኔም ንስሀ አባት አድርገው ቁጭ አሉ፣ ንስሀ አያቴ::

እጠገቤ ሲደርሱ፣ "አብረሃም እንደምን አደርክ?"

"ደህና አደሩ አባ"

"አይ የአንተ ነገር:: ሰው ሲያነብ መነጥሩን ነው የሚወለውለው:: አንተ ሁልጊዜም ሳታነብ ጥርስህን ትፍቃለህ፣ በጥርስህ ታነብ ይመስል" አሉኝ፤ አሁን ይሄ ከንስሃ አባት የሚጠበቅ ንግግር ነው ? በዕርግጥ የወይራ መፋቂያ በእጄ ይዤ ነበር:: በአክብሮት ቆምኩና ሁለት እጆቼን አንስቼ እንደተሸከመች ሴት ከኋላዬ አነባብሬ ግንባሬን ወደ አባ አስገግኩ::

ወደ ሰማይ ዓይናቸውን ተክለው ጋቢና ካቦርታቸውን በቀኝ እጃቸው እየሰረሰሩ ከኮታቸው የውስጥ ኪስ መስቀላቸውን ሊያወጡ ሲታገሉ በትዕግስት ጠበቅኳቸው:: ሁልጊዜም እንዲህ ሲያደርጉ መስቀላቸውን ከውስጥ ኪሳቸው ሳይሆን ከልባቸው ውስጥ የሚያወጡ ነው የሚመስለኝ:: አሳሰሙኝ:: እዚህ ሁሉ ልብስ ውስጥ ተቀምጦ መስቀላቸው ግንባሬን ስትነካኝ ለምን እንደምትቀዘቅዘኝ ይገርመኛል !!

"አብረሃም!" አሉኝ ድምፃቸውን አለስልሰው:: (እንግዲህ ሊጀምሩ ነው)

"አቤት አባ"

"እንደው ቢመክሩህ አልሰማ አልክ...ኧረ ተው...ተው አብረሃም ተው:: እኔ ወድጄ አይደለም የምነዘንዝህ የናትህ አደራ ከብዶኝ ነው:: ምናለ እንዲን ጥሩ ክርስቲያን አግብተህ ብታርፍ:: ሰነፍ የት ታገኛታለህ፣ ቤተስኪያን መምጣቷንም ትተኸዋል....!! እስቲ ምን ጎደለህ? የጠገበ ደመወዝ ትበላለህ፣ ምን የመሰለ ሰፊ አልጋ አለህ..." አሉ በአገጫቸው ወደ ቤቴ ውስጥ እያመለከቱ:: እንዴ አባ...አልጋና ትዳር ምን ያገናኘዋል፣ ያላገባሁት አልጋ ይጠበኛል ብዬ መሰላቸው እንዴ... ወይስ በትዳር ወጥመድ ውስጥ እንድገባ አልጋዬ ላይ ቁራጭ ሲጋ እየጣሉልኝ ነው::

"ሁልጊዜ ልጅነት የለም...እየው..." አሉና ምስጢር እንደሚያወራ ሰው ጠጋ አሉኝና ጋቢያቸውን ወደ ላይ ወደ ትካሻቸው አስተካከሉ:: ከዛም ድምፃቸውን ቀነስ አድርገው፣ "...እንደውም አንዷት ትሁት እግዜር የባረካት ልጅ አቃለሁ፣ ከዚህ...ማነው...ይሄ ሴቶቹ ከሚሄዱበት አገር ማነው..."

"አረብ አገር" አልኩ ቶሎ እንዲላቀቁኝ:: አረብ አገር የሚሄዱት ሴቶች ብቻ ናቸው የተባለ ይመስል !

"እእእ ተባረክ አረብ አገር...እና እዛ ሄዳ ትንሽ አመም አድርጓት ነው የመጣችው ...ጨ...ዋ ድምፅ ሲወጣት የማትሰማ፣ ከቤቷ ቤተስኪያን ከቤተስኪያን እቤቷ ነው - እርግት ያለች የጨዋ ልጅ ላንተ የምትሆን ናት ግዴለህም እያት ! ሳምንት እኔው ራሴ አስተዋውቅሃለሁ:: እንተም ዞርዞር እንኳን የትዳር አጋር ልትፈልግ ራስህም ጠፍቶሃል...ምን ታረግ...ቤትህ ጠበል አይረጭበት፣

ዳዊት እንኳን አትደግም" ሊቃወም አፈን ከፍቼ ተውኩት::

"አይደለማ አይደለም..."ብለው እንደገና ሌላ ረዥም ምክር እንዳይጀምሩ ፈርቼ ዝም አልኩ:: ብቻቸውን በግዕዝ እያነበነቡ ወደታች ወረዱ::

እንዲሁ ስለመምሬ እና ለትዳር ስላሰቡልኝ ልጅ እያሰብኩ የያዝኩትን ጋዜጣ መቃኘት ጀመርኩ::

በደማቅ ጥቁር ቀለም፣ "በማኅበር ተደራጅተው ጫት የሚያመርቱ አርሶ አደሮች ኑሯችን ተለውጧል አሉ..." ይላል::

ወረድ ብሎ፣ "አንዳንድ የማኅበሩ አባላት ጫት በመሸጥ አይሱዙ መኪና ገዝተናል፣ ልጆቻችንንም ከተማ ልከን እያስተማርን ነው ሲሉ ገልፀዋል" ከጽሑፉ ስር አይሱዙ መኪና ተደግፈው ፎቶ የተነሱ አርሶ አደር ምስል ይታያል::

ወረድ ብሎ ሌላ አርዕስት፣

"አንድ አይሱዙ መኪና ሃያ ሜትር ጥልቀት ያለው ገደል ውስጥ ገብቶ ከላይ ጭኗቸው የነበሩ ሰባት ሰዎች ሞቱ:: ከሟቾቹ አራቱ ከገጠር ከተማ እየተመላለሱ የሚማሩ ተማሪዎች ሲሆኑ ፖሊስ የአደጋው መንስዔ 'ሹፌሩ ጫት እየቃመ ማሽከርከሩ ነው' ብሏል !"

ጋዜጣውን አጥፌ ሰፈራችንን ማየት ጀመርኩ:: ቅድስት ቀይ የአራት ልብስ ለብሳ እቃ ታጥባለች፣ እያንጎራጎረች፣ "በሰባራ ፎሌ ውሀ አይጠለቅም..." አይ ቅድስት ! እንደኛ ሰፈር ሴት የባከነበት መንደር ያለ አይመስለኝም:: ቆንጆ ናት 'ሞዴል' የመሆን ፅኑ ፍላጎት ነበራት:: እንደውም የሰፈር ልጆች ሲፎግሯት፣ "'ውበት ውጪያዊና ውስጣዊ ነው' ሲሉ ሰምታ ውስጣዊ ውበቷን ለማየት እልትራሳውንድ' ተነሳች" ይሏታል:: ስታንጎራጉር እየሰማኋት በድምጿ ማማር ተገረምኩ፣ "ወይ ይህቺ አገር ዘፋኞቿ በየማጀቱ እቃ እያጠቡ እቃ አጣቢዎቿ በየአደባባዩ እንዝፈን እያሉ ያደነቁሩናል" አልኩ ለራሴ:: የቄሳርን ለእግዜር፣ የእግዜርን ለእግዚሃር::

*** *** ***

የመንደራችን የአንድ እሁድ ውሎ ከሞላ ጎደል እንደሚከተለው ነው:: ከጧቱ 12:00 ሰዓት እልማዝ የምትባለው ጎረቤታችን በሯ ላይ ስለተጣለው ድግምት ታማርራለች፣ ትራገማለች፣ ጠበል ታርከፈክፋለች:: ድግምት በመጣል የሚጠረጠሩ ጎረቤቶቿን ታሸሙራለች፣ "እችን ኑሮ ብለዋት..." እያለች፣ ብዙ ጊዜ የሞተ እይጥ ነው በሯ ላይ ተጥሎ የሚገኘው::

ከ 12:30 እስከ ጧቱ 2:00 ሰዓት እማማ ዘብይደሩ ጭንቅሎ የተባለውን የልጅ ልጃቸውን ይረግማሉ፣ ይሳደባሉ፣ ይወግራሉ:: አንዳንዴ ወገራው ሲበዛ ገላጋዮች ይገባሉ:: "ባጭር ቅር..." ይሉትና ሲታመም ሆስፒታል ለሆስፒታል እዝለውት ይዞራሉ::

ከሁለት ሰዓት እስከ አራት ሰዓት የመንደሩ ልጆች እኔ ቤት ፊት ለፊት ያሉት (ሰርቪስ ቤት እንኳን የማታቀም) ቢጢቃ ሜዳ ላይ ኳስ ይራገጣሉ:: የሚያስነሱት አቧራ ልጆቹን ስለሚሸፍናቸው እንደ ህልም ነው ብዥ ብለው የሚታዩት::

ከሚጫወቱት ልጆች መሃል ጭንቅሎ (የእማማ ዘብይደሩ የልጅ ልጅ)፣ ሃይለሚካኤል 'አረብ' (የእማማ የውብዳር የልጅ ልጅ)፣ ሙስጠፋ (የእማማ ዘሃራ የልጅ ልጅ)፣ ሲቲና 'ወንዳወንድ ስለሆነች ከቤ' ይሏታል (የእማማ ትርሃስ የልጅ ልጅ ናት)፤ ከላይ ከተዘረዘረው የዘር ሃረግ እንደሚታየው መንደራችን አንድ 'እናት' የሚባል ትውልድ ገድፏል፣ 'አባት' የሚባል ሃረግ ዘሏል:: ሕፃናቱ ከአያቶቻቸው ጋር ነው ያደጉት:: ያውም አቅም ከሌላቸው ደሃና አቅመ ደካማ ባልቴት አያቶቻቸው ጋር! 'እናቶቻቸው የት ሄዱ? አባቶቻቸውን ምን በላቸው?' ቢባል መልሱ ከሁለት ጉዳዮች አያልፍም:: አንድም ወልደው ለእናቶቻቸው እየሰጡ አረብ አገር ሄደዋል፣ አልያም በኤች.አይ.ቪ አልቀዋል:: የመንደራችን እውነታ ነው ይሄ !! ደግሞ ሕፃናቱ የተመካከሩ ይመስል በየምክንያቱ ሲጣሉና ሲነታረኩ የሁሉም መሃላ አንድ ዓይነት፤ "እናቴ ትሙት !!" የሚል ነው::

ልክ ከአራት ሰዓት እስከ አምስት ሰዓት፣ ሁለቱ የመንደራችን እንጀራ ሻጮች ሙሉና ዝናሽ ዱላ ቀረሽ ስድድብ ይጀምራሉ:: በደንበኛ መቀማማት ነው የሚጣሉት፣

"ለማያውቅሽ ታጠኚ...ደግሞ ሙያ እንዳለው ሰው:: ማየት የተሳነው እንጀራ እየጠፈጠፍሽ... እኩል ታወሪያለሽ..."

"ኤጅ አባክሽ...እኔ ሙሉ በወፍጮ ቤት ጥራጊ አይደለም ደንበኞቼን የማስተናግደው፣ ጥርት ባለ ጤፍ ጥር...ት"

"ሂሂሂሂሂ 'መጣፈጡ ቀርቶ እጄን በለቀቀኝ አሉ አትዬ አሰለፍ፤ ጥራቱ ቀርቶብሽ ቡሃቃሽን በወር አንዴ እንኳን ባጠብሽው:: ሰዉን ሁሉ በሆድ ቁርጠት ፏፏረሽው" ትላለች ዝናሽ:: የሙሉ ስድድብ ደንበኛ ስለሆንኩ በዚህ አባባሏ ሆዴ ይፍሟል፣ ...ኡ..... ወር ሙሉ የማይታጠብ ቡሃቃ ...እቺ ስድድብ ደንበኛን ለማስከዳት ወሳኝ የቃላት ጦርነታቸው ናት::

ልክ አምስት ሰዓት ሲሆን እማማ መጣፈጥና ስንቅነሽ ቡና ይጠራራሉ:: ወደ ስድስት ሰዓት ጀሚላ የቅንድቧን ኩል ጆሮና ጆሯዋ ጥግ ድረስ ተኩላ በስልኳ እያወራች ወደላይ ትጣደፋለች፣ "ሃቢቢ መጣሁ...ወጥቻለሁ" እያለች:: አፍንጫ የሚሰነፍጥ ሽቶዋ መንደሩን ያውደዋል:: ጀሚላ ስታልፍ ጥርኝ ያለፈች ነው የሚመስለው:: የታከከችው ነገር ሁሉ ሽቶ ሽቶ፣ ሙቼም 'ሃቢቢ'ዋ የአፍንጫ መሸፈኛ ማስክ ያደረገ ሰው መሆን አለበት::

ይሄን ሁሉ ሳይ ይከፋኛል:: ብቸኝነት ይጫጫነኛል:: ከወንዙ ተገንጥሎ ኩሬ ውስጥ እንደተኳተረ ውሃ አዛው የምሻግት አልያም የተቀመጥኩበት በትነት የማልቅ ነገር መስሎ ነው የሚሰማኝ

ይሄ...የተረገመ እሁድ ወደዛ አልቆ ሥራዬ በገባሁ ! ለነገሩ ከእሁድ ይሻላል ብዬ እንጂ ሥራዬም ሠልችቶኛል:: የባንክ ሠራተኛ ነኝ:: ብዙ ሰዎች የባንክ ሠራተኛ መሆኔን እንደትልቅ እና አስደሳች ሥራ አድርገው ሲያወሩ ይገርመኛል:: ለእኔ የባንክ ሥራ በምድር ላይ ካሉ አስከፊ ሥራዎች ሁሉ አስከፊው ይመስለኛል:: እንደውም ለሰው ሳይሆን ለሮቦቶች የሚስማማ ሥራ ቢኖር የባንክ ሥራ ነው እያልኩ አስባለሁ::

አንድ አይነት ቅርፅ ያላቸው 'ብር' የሚባሉ መርገምቶችን መቁጠር:: አራት ዓመት ሙሉ ቆጠርኳቸው...ሌጭ..ድፍን አገር የሚራኮትለት ብር ለእኔ አንዳች ቆሻሻ ነገር መስሎ ነው የሚታየኝ:: ብር ይሸታል:: ካላመናችሁ ወደ አፍንጫችሁ አስጠጉና ሞክሩት:: እንደ ብር መጥፎ ሽታ ያለው ነገር ምን አለ ? ለነገሩ የዘንድሮ ብር ላሽትተውም ብትሉ አፍንጫችሁ ላይ ሳይደርስ ያልቃል - በላቢ ነገር ነው::

ምስላቸው ብር ኖት ላይ ያሉት ሰዎች ከመኖር ብዛት የቢሮ ባልደረባ መስለውኛል:: ደግሞ አልወዳቸውም:: ለምሳሌ አንድ ብር ኖት ላይ ምስሉ ያለውን ሰው መንገድ ላይ ባገኘው ገለማምጨው የማልፍ ይመስለኛል:: አስር ብር ላይ ያለችው ሴትማ በስማም ስታበሳጨኝ፤ የሆነች ነገረኛ ነገር:: በደንብ አይታችኋታል? ስፌት የምትሰፋ ትመስላለች እንጂ ጆሮዋን አቁማ ነገር የምትሰማ እኮ ነው የምትመስለው:: ደግሞ ፊቷ ላይ የአሽሙር ፈገግታ አለ:: ከሁሉም ከሁሉም የሚያበሳጨኝ ነገር ደግሞ ከንፈሯ !! የከንፈሯ ማማር የሰብለን ከንፈር እኮ ነው የሚመስለው !! ከነስፌቷ አጎኗ ላለው አንበሳ ነበር መስጠት !!

ባንክ ቤት ስትሰሩ ስጋችሁ በሉፍ ተጀቡኖ ወሩ መጨረሻ ላይ የሉፍ ቆሎ መግዣ እንኳን የማይተርፋችሁ መናጢ ደሃ መሆናችሁን ብዙ ሰው አይረዳም:: ቁጥርና ስጋት ባንድ ላይ የሚኖሩት ባንክ ቤት ውስጥ ነው:: ብር ስትቆጥሩ በስጋት ነው:: አንዱን የብር ኖት ሌላ የተደረበበት እየመሰላችሁ በፍትጊያ ፍዳውን ታበሉታላችሁ:: በዛ ላይ ሰው ለብር ያለውን ሟችነት፣ ስግብግብነት፣ ደግነትም ጭምር ትታዘባላችሁ::

ሃሃሃ የሆነ ነገር ትዝ አለኝ:: አንድ ቀን እንዲ እኔ ወዳለሁበት መስኮት ጢጋ አለችና ትልልቅና የተራቆቱ ጡቶቿን መስታወቱ ጋር ጨፍልቃቸው በሽንቁሩ ታናግረኝ ጀመረ:: ደረቷና ጡቷን የወረራት ብጉር መሰል ነጠብጣብ ያስቅቃል፡ ሙዑ ሺ ቁጫጮች የሚርመሰመሱበት ደረት ነው የሚመስለው:: እንደው አንዳንድ ሴቶች ምን ማሳየት እና ምን መደበቅ እንዳለባቸው አያውቁም::

እኔ ደግሞ ከኋላዋ ተራ የሚጠብቁ ደንበኞች ወደሷ ሲያፈጡ፣ "እቺ ሴት ታዋቂ ትሆን?" ብዬ አሰብኩ:: ለካስ ወደኔ ስታጎነብስ በጣም አጭር ጉርድ ቀሚሷ ከኋላዋ ታፋዋ ድረስ በመራቆቱ ነበር ያ ሁሉ ዕይታ፤

"ምን ልታዘዝ የኔ እመቤት" አልኳት:: በሚያበሳጭ መሞላቀቅ ቻፕስቲክ እውጥታ ደዘደዝ ከንፈሯን ቀባችና ቀጭ አድርጋ ዘግታ ወደ ቦርሳዋ መለሰች:: በትዕግስት ጠበቅኳት::

"ዶላር ተልኮልኝ ነበር"

"ከየት ነው?"

"ከዲሲ ...አሜሪካ"

"የላከው ሰም?"

"ዳኒዬ" አለች በፈገግታ::

"ዳንኤል ነው?"

"ዎ"

"ስንት ነው የላከልሽ?"

"ስሪ እር ፎር ሃንድረድ ዶላ...ር" ስታወራ አንገቷን ትሰብቀዋለች::

"ስሪ እር ፎር ሃንድረድ ዶላ...ር" ስታወራ ልክ ዶላሩ ሰላውም መላኪያው ከዛው ላይ የሚቆረጥ ነበር::ይሄኑ ዳንኤል የላከላት ግን አንድ መቶ ዶላር ስዛውም መላኪያው ከዛው ላይ የሚቆረጥ ነበር፡፡ ስልኳን አውጥታ ስንግራት...ደዘደዘ...ሞልቃቃዋ እና ቋጫጯሚ ሞልቃቃ - ፊቷ ተቀያየረ፡፡ ስልኳን አውጥታ ስትግራት...ደዘደዘ...ሞልቃቃዋ እና ቋጫጯሚ መቶ ዶላር ብቻ ነው የላከልኝ - ዳንኤል ደወለችና ጥርት ባለ አማርኛ፡ "አንቾ ያ ችጋራም መቶ ዶላር ብቻ ነው የላከልኝ - ዳንኤል ደወለችና ጥርት ባለ አማርኛ፡ "አንች ያ ችጋራም ..." የለበሰ ጎልማሳ ሰው መጣና፣ እርገጤ ነው" ብላ እርፍ፡፡ ወዲያው አንድ ቁሽሽ ያለ ቱታ የለበሰ ጎልማሳ ሰው መጣና፣

"ይቅርታ ይቺን ብር ትራንስፈር ታደርግልኝ" አለኝ እየተጣደፈ. በልጅቱ ትከሻ ላይ የባንክ ደብተሩን እያቀበለኝ፡፡ ልጅቱ የቱታው መቆሸሽ ደብሯት ፊቷን አጨፈገገች፡፡

"ወደየት ነው?" አልኩት፡፡

"ወደ ጅማ"

"መጠኑ..."

"አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊየን"፡፡ ሞልቃቃዋ ሰውየውን ቀጥ ብላ እየችውና ፈገግ ብላ በአክብሮት በታውን ለቀቀችለት፡፡ ወዲያው የሚያደርጋትን አሳጣት፤ "ወደዚህ ጠጋ ብለህ እናግረው፤ ስሪ ቦታ ያዝኩብህ" አለችው በፈገግታ፡፡ ዞሮ እንኳን አላያትም፡፡ (የውሸት አክብሮቷና ፈገግታዋ ከሰረ፡፡) ሰውዬው እናትዬ ስራ ልቡን ያወለቀው ላብ አደር ነገር ነው እሷን ለማየት ጊዜውም የለው...!! "ሚስኪን ዳኒዬ!" አልኩ በሆዴ፡፡

በቃ ይሄ ነው ስራዬ ብር መቁጠር መስጠት፡፡ ብር ማስገባት፣ ማስወጣት...ኤጭጭ !! ቢሆንም ከእሁድ ይሻላል፡፡

ኢማማ መጣፈጥ ስንቅንሽን ቡና ሲጣሩ ስማሁ ገና አምስት ሰዓት...ወይ እዳ!

ቅድስት አሁንም እያንጎራጎረች ነው፤ "የቤቴ ወለሉ ጣራ እና ግድግዳው..." የቤታቸውን ግድግዳና

ጣራ ከውጭ በኩል በረኸኛም መጥረጊያ እያፀዳች ነበር:: ቆንጆ ናት፣ ፀይም ቆዳዋ ጥርት ያለ! በተለይ እንዲህ ከኋላዋ ሆኖ ስትንጠራራ ሳያት የአቦሸማኔ ሸንጥ:: ቅድስት ቆንጆ ናት:: እንደው ተፈራርተን እንጂ እኔና ቅድስት ሳንከጃጀልም አልቀረን:: ባየኋት ቁጥር እቅፌህ ሳማት ሳማት ይለኛል:: ...እሷም በሰበብ አስባቡ እቤቴ ጎራ ማለት ታበዛለች ግን - እንፈራራለን::

ቅድስት፣ አርሴማ፣ ሃያት፣ ጀሚላ፣ ሜሮን፣ ሄሩት እና ሄለን አረብ አገር ለስራ ሄደው የተመለሱ የመንደራችን ሴቶች ናቸው:: ያልተመለሱትንማ አረብ አገር አዛው ይቁጠራቸው...::

መጀመሪያ አረብ አገር የሄደችው አርሴማ ነበረች፣ እንዳሁኑ ባልተለመደበት ጊዜ:: ታዲያ አርሴማ ብዙ አልቆየችም፣ ባልታወቀ ምክንያት በሦስት ወሯ ተመለሰች:: ዘጠኝ ወር ሲሞላት ግን ምክንያቱ ታወቀ፣ ወንድ ልጅ ተገላገለች ! የመንደሩ ሰው እርጉዝ መሆኗን ካወቀበት ቀን ጀምሮ፣ "የሚወለደው ልጅ አረብ ይመስላል...አይመስልም" እያለ ሲነታረክ፣ ሲወራረድና ብር ሲያሲዝ ከረመ:: አርሴማ የሚያምር ክልስ ልጅ ወለደች:: ገና ከእራስ ቤት ሳትወጣ ደግሞ መነሻው ያልታወቀ ወሬ ይናፈስ ጀመረ::

"አርሴማ የወለደችው ትሰራበት የነበረ ቤት ተቀጥሮ ከሚሰራ ፓኪስታናዊ ዘበኛ ነው" ይሄ ወሬ ለጉድ ተናፈሰ::

"ቱ! ለሞላ ወንድ!" ተባለ:: "እንገት ደፋ እገር አጥፊ" ተባለ::

ይሄ ወሬ እድሜው ከሳምንት አላለፈም:: የመልስ ምት በሚመስል ሌላ ወሬ ተተካ:: "አርሴማ ያረገዘችው ከኪዌቱ አሚር ሁለተኛ ልጅ አብደል ናስር ነስረዲን ነው...እነሱ ቤት ነበር የምትሰራው..." ይሄኛው ወሬ ከመጀመሪያው የበለጠ ገነነ:: እንደውም በቅርቡ መጥቶ ሰፈራችንን በሊዝ ሊገዛውና ለአርሴማ በኢትዮጵያ አንደኛ የሆነ ሕንፃ ሊገነባላት እንደሚችል ሁሉ ተወራ::

"ሲወዳት መቻስ ለብቻው ነው፣ እሷን ሲያይ ጥምጣሙ እስኪበር ነው ቢደሰታ የሚምነሸነሸው" እየተባለ ወሬው ደመቀ:: ጥምጣሙ እስኪበር የሚያፈቅር የአሚር ልጅ እዚህ ጭርንቁስ መንደራችን ውስጥ መጥቶ ለማየት እኔ ራሱ ጓጓሁ፣ የፍቅርን ኃያልነት ለመታዘብ አሰፈሰፍኩ::

ሕፃኑን ልጅ አያቱ "ኃይለሚካኤል" አሉት፤ ኃይለሚካኤል አብደል ናስር ነስረዲን በዚህ ሁኔታ የመንደራችን አባል ሆነ:: (አረቡ ይሉታል በቅፅል ስም፣ በኢትዮጵያና ኩዌት መካከል ወደፊት ለሚኖረው ወዳጅነት ይህ 'ታሪካዊ' እንቦቅቅላ ታላቅ ሚና ሳይኖረው አይቀርም... ሂሂሂ):: እድጎ አስር ዓመት እስኪሆነው ግን አባቱ ነኝ ያለ የአሚር ልጅ አልታየም:: አንድ ቀን ታዲያ አያቱ፣ "አሚሩ ቀርቶበት ዘበኛውም በመጣና የአባትን ጣዕም ባወቀው" አሉ በቁጭት::

ከአርሴማ በኋላ ሜሮንና ጀሚላ አረብ አገር በመሄድ ሁለት ዓመት ቆይተው ተመለሱ:: እነጀሚላ

ተከልክሎ ነበር:: በአንድ እግሩ ቤት አዲስ ምንጣፍ ስለተነጠፈ ጫማ ሳያወልቁ መግባት ተከልክሎ ነበር:: በአንድ እግሩ ምንጣፉን የረገጠ እንግዳ በጀሚላ ፎቴኸት ሁለተኛ እግሩን በአየር ላይ እንዳንጠለጠለ ደርቆ ይቆማል:: አማማ ሐዋ (የጀሚላ እናት) ታዲያ "ይሄን ምንጣፍ ወዲያ አንሽልኝ ሲታመም ጣያቂ፣ ሲቸግረኝ ደራሽ ጎረቤቶቼን አላቀቀብኝ" አሉ:: ሲቆይ ግን ምንጣፉም ቆሸሸ መዓቀቡም ተነሳ፣ መጀመሪያ ቤተሰቡ ከዛም ሁላችንም መንደርተኞች ከነጫማችን መግባት ጀመርን::

ሚሮን እንደመጣች አካባቢ ደግሞ የተረፈ ምግብ ቆሻሻ መጣያ ውስጥ እየደፋች አስቸግራ ነበር:: "ኧረ ለልጆቹ መከሰስ ይሆናል እህሉን አትድፊ ጡር ነው" ብትባል፣ "ላላ ላላ" እያለች መገልበጥ ሆነ:: ከወሮች በኋላ እንኳን ሊተርፍ ቀናውም እያነሰ ቤተሰቡ መነጫነጭ ስለጀመረ እህል መድፋቱ በዛው ቆመ::

አረብ አገር የሄዱት ሁሉ ኮንትራታቸውን ጨርሰው ባንዴ ወደ መንደራችን በመጡበት ወቅት የሚገርም የባህል፣ የኢኮኖሚ፣ የቋንቋ መቀየጥ ተከሰተ:: ፓስፖርት፣ ቪዛ፣ ኮንትራት፣ ባርሜል፣ ካርጎ፣ ጉምሩክ፣ ሃቢቢ...ሃቢብቴ የሚሉ ቃላት ተዘወተሩ:: በመንደራችን ሻይ አብዝቶ መጠጣትና ሩዝን ከእንጀራ እኩል ገበታ ላይ ማቅረብም ተለመደ:: በሳተላይት ዲሽ የአረብኛ ፊልሞችና ተከታታይ ድራማዎችን ማየትም አንዱ ለውጥ ነበር::

እርስ በእርስ መንደርተኞች ሲጣሉ አረብኛ ስድቦችን መቀላቀል ሁሉ ተጀመረ:: እንደውም አንድ አረብኛ ስድብ ለእኔም ደርሶኛል:: ቅድስት የአስቴርን ሲዲ ልትዋስ ቤቴ ስትመጣ በቃሌ የሸመደድኩትን ግጥም ብቻዬን ሳነበንብ ደረሰችና "መጅኑን!" አለችኝ:: በኋላ ሚሮን እንደተረጎመችልኝ ከሆነ "ወፈፌ" ማለት ነው አሉ::

በዚህ ወቅት ሂሩት አረብ አገር እሄዳለሁ ብላ ተነሳች:: "እንዴ ደግሞ አንቺ ምን አጣሽ ኑሮችሁ ጥሩ፣ ትምህርትሽን እየተማርሽ ነው" ብትባል

"እንዴት ነው ምን አጣሽ...ተውኝ...ተውኝ አባካችሁ ሆድ አታስብሱኝ:: ያጣሁትን እኔ ነኝ የማውቀው:: የመንደሩ ሴት ሁሉ በአረብኛ ሲሰዳደብ እኔ እስከመቼ በአማርኛ ስሳደብ እኖራለሁ - ማን ከማን ያንሳል?!" አለች እንባ እየተናነቃት:: ሄደችና ሁለት ዓመት ቆይታ ብዙ አረብኛ ስድቦችና አንድ በርሜል ልብስ ይዛ ተመለሰች::

አስገራሚ በሆነ ሁኔታ በርሜሉ ውስጥ ሙሉ የቤይሩት መቶ አለቃ ዩኒፎርም ተገኘ:: የሂሩት አባት ያንን ግጥም አድርገው ለብሰው አንዳንድ ቤይሩት ኖረው የመጡ ሴት እህቶቻችንን በሰላም አገር ሲያስደነግጡ ከረሙ:: ሂሩትም ሃሜት አልቀረላትም፣ "ፖሊስ ቤት ተቀጥራ ነበር የምትሰራው ልብሱን ሰርቃ አምጥታ ነው" አሏት::

ሂሩት ግን አንድ ቀን ቁጭ ብለን ስናወራ ስለ'ዩኒፎርሙ' ይሄን ታሪክ ነገረችኝ:: አንድ መቶ አለቃ ሂሩትን ድንገት አያትና በፍቅሯ ተነደፈ:: መጀመሪያ በሃር የተጠለፈ መሃረቡን ላከላት

(የፍቅር መግለጫ መሆኑ ነው) ዝም ስትለው "አሃ እንሶብሽ ነው!" በማለት የፖሊስ ኮቱን ከነሙሉ መዓረጉ ላከላት:: በመጨረሻ መልስ ሲያጣ ሱሪውን ላከላት:: በሱሪው ተጠቅልሎ ደግሞ ክላሽንኮቭ ጠመንጃው አብሮ ነበር:: እንግዲህ ወንድ ልጅ ሱሪና ጠመንጃውን ከሰጠ ምን ቀረው? ይሄ ሚስኪን አፍቃሪ ፖሊስ እስካሁን በፓኪ አውትና በግልገል ሱሪ በቤይሩት ጎዳናዎች ላይ ግዳጁን እየተወጣ ይገኛል:: (አያድርስ ነው...አይሳቅም ! እኔስ እሰሁ አይደል ለዘች ሰላቢ ስብለ ነፍሴን ሰጥቼ እርቃኔን የቀረሁ::)

ሄሩት የኒፎርሙንም ክላሽንኮቭ ጠመንጃውንም ይዛ ወደ ኢትዮጵያ ስትገባ ኤርፖርት ፍተሻ ላይ ተያዘች::

"መለዮው አያልፍም ይወረሳል፤ ዩኒፎርሙን ችግር የለም ማስገባት ትችያለሽ" አሏት ፈታሾቹ::

"እረ የሰው ስጦታ ነው በናታችሁ!" ብትላቸው፤

"ሕግ ነው" ብለው ግግም አሉባት:: ወደ ሀላፊው ቢሮ ገብታ ጉዳዩን ነገረችው:: ገና 'ክላሽ' ስትለው፤ "አያልፍም" አላት በቁጣ::

"ምናለበት ባታካብዱ...ባንድ ጠመንጃ መንግሥት አይገለበጥ!" አለችው ግልፍ ብሏት::

"ዋይ...ተይ ባክሽ እኛም ደርግን ስንገለብጠው ባንድ ክላሽንኮቭ ነው የጀመርነው..." ብሎ ሸኛት::

ሄሩትና ጀሚላ "ዩኒፎርም ሰርቃለች" በሚለው ሐሜት አሷራ ያስነሳ ፀብ ገጠሙ:: በአረብኛ እና በአማርኛ ነበረ ስድድቡ:: ቅድስት መሀል ገብታ እየገላገለች አግረ መንገዷን አረብኛ ስድቦችን ለእኛ ለመንደርተኞች ትተረጉምልን ነበር::

"ከልብ!" አለች ሄሩት ጀሚላን:: ቅድስት፤ "እረ እንዲህ አይባልም አግዜር አይወደውም ሄሩት" በማለት ነገሩ ለማብረድ እየሞከረች ወደ እኛ ዞር ብላ፤

"'ከልብ' ማለት ውሻ ማለት ነው::" ትለንና ወደ መገላገሏ ትመለሳለች::

እልልልልልልልልልልልልልልልልልልል አሁድ መሽ ! ድንገት ቅድስት ዝንጥ ብላ እቤቴ መጣች፤ ከሰዓት ሰርግ ነበራት:: ኡፍፍፍ የለበሰችው ረዥም ቀሚስ እንዴት እንዳማረባት:: ሰናወራ ቆየንና "ለምን ቡና አናፈላም" ብላ ሳታስፈቅደኝ ማቀራረብ ጀመረች:: ባንዴ ቤቱን ነፍስ ዘራችበት:: እጣኑ ተጫጭሶ ሙዚቃው ተከፍቶ ቅድስት ፊት ለፊቴ የሚያምር ጠይም አግሯ በቀሚሷ ቅድ እየታየ እንደተቀመጠች ደስታ መላ ሰውነቴን አጥለቀለቀኝ:: እውነቱን ልንገራችሁ አይደል፤ ማግባት ሁሉ አማረኝ::

በድፍረት "ዛሬ ለምን እዚህ አታድሪም?" አልኳት::

"ባለጌ!" ስትለኝ ላለመስማት ጆሮዬን ልይዝ ነበር።

"እና ካሁን በኋላ ልሄድልህ ነው?" ስትለኝ ማመን አልቻልኩም። ዞር ብዬ አሊጋዬን አየሁት። እስከዛሬ እዚህ ባህር ላይ ብቻዬን የምንሳፈፍ ሚስኪን ጀልባ መሆኔ ተሰማኝ። ዘልዬ አቀፍኳትና ግጥም አድርጌ ከንፈሯን ሳምኳት።

"ሂድ መጅኑን!" አለችኝ። እንደዚህ ቃል አሪፍ የፍቅር ቃል ሰምቼ አላውቅም። ራሴ ስተረጉመው፣ "በፍቅር የወፈፈ" ማለት ሳይሆን አይቀርም !! "ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም" እያጉመጠመጥኩ... አየሁት...

እደግመዋለሁ...እባ ልከ ናቸው።

የእሁድ ሌሊት እንዴት አጭር ነው - ለዚህ ጊዜማ ይጣደፋል !

# ፈንዲሻ ሲቆሉት ድምፅ ሲበሉት ድምፅ

# 20

የአንድ ደቂቃ የህሊና ጸሎት አድርገን እንደተቀመጥን፣ ፕሮግራሙ ቶሎ እንዲያበቃ ሌላ የህሊና ጸሎት ጀመርኩ፡፡ ዓለም ዓቀፍ የሴቶች ቀንን ለማክበር የክፍለ ከተማው የሴቶች ሊግ ባዘጋጀው ፕሮግራም ላይ ተገኝቻለሁ፡፡

ሊጉ በመሥሪያ ቤታችን በኩል ግዳጅ የተቀላቀለበት ጥሪ አቅርቦልን አለቃዬ "ሂድ !" ስላለኝ የቀበሌው አዳራሽ ውስጥ ተገኝቻለሁ፡፡ ያውም ቅዳሜን በሚያክል ቀን – ክሰዓት!! ሰኔና ሰኞ ገጥሞብኝ፡፡

"...አሁን ደግሞ የክፍለ ከተማችን የሕፃናትና ሴቶች ጉዳይ ምክትል ኃላፊ ወ/ሮ ደርባቤ በላቸው ጎጆአስራውን ሰብሮ ወሰዳት ልጅቱን' የሚል ምርጥ ግጥም ያቀርቡልናል..." አለ ጉጉት የመሰለው መድረክ አስተዋዋቂ፡፡ አፉ ላይ የደቀነውን ማይክሮፎን ድምፅ ማጉላቱን የተጠራጠረ ይመስል በጣም እየጮኸ ነው የሚናገረው፡፡

ቀጠለ "ወ/ሮ ደርባቤ ለክፍለ ከተማችን፣ ብሎም ለከተማችን፣ ብሎም ለኢትዮጵያ ሴቶች፣ ብሎም ለአፍሪካ ሴቶች ታላቅ ምሳሌ የሚሆኑ የዘርፈ ብዙ ሙያዎች፣ ተሰጥኦዎች፣ ትምህርቶች፣ ስልጣኖች ባለቤት ናቸው" አለና፣ "...እስቲ ወ/ሮ ደርባቤን ወደ መድረክ..."

...ጯ...ጯ.......ጯ

ጥልፍ ቀሚስ የለበሱትና አንዳንድ ልማታዊ ዝግጅቶች ላይ ልማታዊ ግጥም በማቅረብ የሚታወቁት ወ/ሮ ደርባቤ መድረክ ላይ ቆመው በፈገግታ ለሕዝቡ ጎንበስ ቀና እያሉ ምስጋና ይሁን ሰላምታ ያለየለት ግማሽ ስግደት አቀረቡ፡፡ ግጥሙን ሲያቀርቡ ነው ብለን ፀጥ ስንል አስተዋዋቂው ማዋደዱን ቀጠለ፣ "...ብታምኑም ባታምኑም ወ/ሮ ደርባቤ ይሄን ዝግጅት አስመልክቶ ግጥም እንድትፅፍልን የነገርናት (እንች አላት) ትላንት ዘጠኝ ሰዓት ነው፡፡ ይገርማችኋል ሌሊቱን ስትፅፍ

አድራ ቢት ስደውልላት በስልክ ማጥሙን አነበበችልኝ...'ወይ መባረክ' ነው ያልኩት...::"(በሕዝባ ስልክ ስምንት ገፅ ማጥም አያነበቡ አላየንም ባርኮት)::

"...የማጥሙን ጥልቀት እና ውበት ራሳችሁ ታዘቡት...እስቲ ለዚህች ብርቱ ሴት ሞቅ ያለ ጭብጨባ..." ብሎ ጭብጨባውን ራሱ ጀመረው:: ማይኩን በሌላኛው እጁ ሊጠፈጥፈው አዳራሹ ን...ን...ን... በሚል ለጆሮ የሚቀፍ አሰቀያሚ ድምፅ ተሞላ:: ከታዳሚው የተንበጫረቀ ደካማ ጭብጨባ ጋር ተዳምሮ ጓጓታው በቀላል የነፍስ ወከፍ መሳሪያዎች የታጀበ የከባድ መሳሪያ ድምፅ ነበር የሚመስለው::

ብዙው ታዳሚ በየእጁ ፈንዲሻ እና ለስላሳ ይዞ ስለነበረ ማጨብጨብ አልቻለም እንጂ ለጭብጨባማ የእኛን ክፍለ ከተማ የሴቶች ሊግ ጽሕፈት ቤት ሰራተኞች ማን ብሏቸው... ...በተለይ እጃቸው ባዶ ሲሆን የሚያጨበጭቡት ጭብጨባ ቢሾፍቱ ይሰማል:: እጃቸው ባዶ ሲሆን ለዜና ያጨበጭባሉ፣ ለሪፖርት ያጨበጭባሉ፣ የቀበሌው ሊቀመንበር ሲያስነጥሱ ሁሉ ያጨበጭባሉ፤ እጃቸው ሞላ ካለች ግን ጠቅላይ ሚንስትራችን ቢዘፍኑም አያጨበጭቡም:: አንዳንዴ ታዲያ ጭብጨባዎች ሲቀንሱ ኢኮኖሚያችን ያደገ ይመስለኛል::

ቀጠለ አስተዋዋቂው (ወ...ይ ዛሬ) "ወ/ሮ ደርባቤ...ገጣሚ ብቻ አይደሉም፤ የታሪክ ተመራማሪም ናቸው:: (ወ/ሮ ደርባቤ ቆመው በቁማቸው ገድላቸው ሲለፈፍ በፈገግታ ያዳምጣሉ)...ከፍተኛ እድናቆት ያተረፈውንና...'የክፍለ ከተማችን የእድገት ማራቶን ሩጫ ከዘመነ ደርግ ውድቀት በኋላ' የሚለውን መጽሐፍ ጨምሮ አራት የግጥም መጻሕፍትን አሳትመዋል፤ ይሄን ያህል ካልኩ እንዳላሰለቻችሁ ወደ ወ/ሮ ደርባቤ ልምራችሁ..." ብሎ ማይኩን በአክብሮት ለሴትዮዋ አቀበላት:: ('እፎይ! አንድ እዛ ለቀቀ' ይላሉ አማማ ሩቅያ ሲ.ተርቱ)

...ማይኩን ተቀብላ ን...ን... እደረገችና (የፈረደበት ማይክ ተጠፍጥፎም፣ ያወሩትን ሁሉ ተቀብሎ አትልቶም አላዘነኝ):: "እ...እኔ እንኳን የተባለውን ያህል ነኝ ብዬ አላምንም...፣ ምክንያቱም እንደ እኔ ዕድሉን ቢያገኙ...እንኳን ኢትዮጵያን ዓለምን 'ጉ...ድ' የሚያሰብሉ ሴቶች ከእናንተ መሀል አሉ ብዬ ስለማምን ነው..." አለች ወይዘሮ ደርባቤ::

ጭብጨባ...!! ቿቿቿቿቿቿቿቿ (ፈንዲሻው አለቀ እንዴ ጭብጨባው ደመቀ!)

ከጎኔ የተቀመጠች ሴት "እውነት ነው" ብላ ጮኸች:: (ዓለምን 'ጉድ' ከሚያስብሉት ሴቶች መሐል አንዷ ሳትሆን አትቀርም:: ዞር ብዬ ሳያት በግራ እጇ 'ሞባይል' ስልኳን፣ በቀኟ፣ መዳፏ ...ከፈንዲሻው ኮርሽም አደረገችለት::) በስሜት ወደ መድረኩ እያየች ቁጭ ብድግ ትላለች::

ሴትዮዋ ግጥሟን ከማቅረቧ በፊት ሰላሳ ደቂቃ አወራች::...እንዴት የወንዶችን ተፅዕኖ ተቋቁማ 'ታላቅ ገጣሚ' ለመሆን እንደበቃች፣ ሴቶች የርሷን ፈለግ ይዘው እንዲከተሏት፣ (ብትወዷስ እኔ

ምላሱ ጻርዳርታ)...ይሄን ሁሉ አወራችና "እንዳላሰለቻችሁ" (ጎና ድሮ የሰለቸነውን !?) በማለት ወደ ግጥሟ ተሸጋገረች !!

ወደ መድረክ ስትወጣ መነፅሯን በታዋ ላይ ረስታው ስለነበር፣ "እቀብሉኝ!" ስትላቸው የእጅ ቦርሳዋን አራት ሰዎች ግራና ቀኝ ይዘው (ማሸርገዳቸው ስላበሳጨኝ የጨመርኩት ነው) አቀበሏት...፡፡ቦርሳዋ ውስጥ አስር ደቂቃ ፈልጋ መነፅሯን ቤቷ መርሳቷን አረጋገጠች፡፡...እናም ወደ ብርሃኑ ቀርባ ግጥሟን ማንበብ ጀመረች፡፡

*እንስራውን ሰብሮ ወስዳት ልጅቷን (ርዕስ)*

*ሽረ እያ ደገፋው አንተ ትልቅ ሰው፣*

*አንዲት ፍሬዋን ልጅ ማስቸገርህን ተው፣*

*ውሃ ልትቀዳ ወንዝ ስትሄድ፣*

*ቀሚሽ አውረኝ አልካት በግድ...፣*

*ይሄ አልበቃ ብሎህ ሰው ጭር ሲልልህ፣*

*ሕፃኗን ደፈርካት አግዜር ይይልህ !!* ('ውይ ወንዶች፣ አሉ ክንኔ ያለችዋ ባለ ፈንዲሻ)

*ደሟን እያዘራች እቤቷ ስትደርስ፣*

*እንስራ ሰበርሽ ብለው ገረፏት እያድርስ...*

*ደም በሌላ ቀን እንደሚ አድብተህ...፣*

*አሁንም ደፈርካት አንተ ግን ምን ዓይነት ሰው ነህ...፡፡* ('በስማም ጭካኔ...ሌላዋ ሴት)

አዳራሹ ፀጥ ብሎ 'ግጥሙን' እያዳመጥን ድንገት ጎኔ ያለችው ሴት ጎርደምደምደም...ከሽሽሽ... ስታደርግ ደንግጬ ዞሬ ተመለከትኳት፡፡ ተመስገን ፈንዲሻ እየበላች ነው፡፡...እኔማ በግጥሙ ተመስጣ በስህተት ስልኳን ቀረጣጠመቻት ብዬ ነበር፡፡

ግጥሙ ለድፍን ሀያ ሰባት ደቂቃ ተነበበ፡፡ የግጥሙ የመጨረሻ ስንኞች...

*ፈረቀላ ተይዞ ስትንከራተት፣*

*ጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኛ አግኝታት፣*

*አዲሳባ በመኪና አመጣቻት...*

*መንግሥታችን በሠራው ዘመናዊ አሲፓልት...!*

እመሰግናለሁ !!

ቿቿቿቿቿቿቿቿቿቿቿቿ...(ታዳሚው ፈንዲሻውን ጨርሶ ነበር)

ለመውጣት ሳቆበቁብ አስተዋዋቂው እንዲህ አለ...

"'ለሴቶች ቀን ያልሆነ ግጥም ለመቼ ይሆናል' በማለት ወይዘሪት ዘቢደር የወጣቶች ሊግ አስተባባሪ ለማንበብ ሃያ እንብባው የተደነቀላትን 'ታታሪዋ ሥራ ፈጣሪ!' የሚለውን ግጥሟን ሳቅርብ ብላለችና እስቲ ወደ መድረክ..."

ቿቿቿቿቿቿ...

ተነስቼ ወጣሁ፡፡ ወደ ቤቴ ስሄድ ከኋላዬ የአስተዋዋቂው ድምፅ ይሰማኛል፡፡

"...ወጣት ዘቢደር 'የአንበሷ ጣጣ' የሚል በቅርቡ በታተመ የግጥም መድብሏ ከፍተኛ እውቅና ያተረፈች ብርቱ ሴት ስትሆን..." እያለ ቀጠለ፡፡

ይሄ ቀበሌ ነዋሪው ሳይሰማ ማተሚያ ቤት ከፈተ እንዴ?...እንዴት ነው ይሄ መድብል ማሳተም እንዲህ የቀለለው ጎበዝ ?!

# "ሽረኛ" "እና" "ደህና" በአንድ ላይ ሲሄዱ በሽረኛው በኩል ተናደ መንገዱ

# 21

ሽረኛ፣

የዶክተር ደበሙ እርገጤ መዝገበ ቃላት 'ሽረኛ' የሚለውን ቃል ሲያብራራው እንዲህ ይላል፤ ሽረኛ – ስም፣ እንዳገባቡ 'ተውላጠ ስም'፤ እንዳወጣጡ 'ግስ'፤ ሳይገባም ሳይወጣም ራሱን ችሎ ዓረፍተ ነገር !!

ትርጉሙ፡– (በተንኮል የሰው ማንነት፣ መልካም ስም፣ መልካም ሥራ፣ መልካም ግንኙነት የሚሸረሽር፣ የሚሰረስር፣ የሚቦረቡር፣ የሚደረምስ፣ የሚያጠለሽ...) ይለዋል፡፡ መዝገበ ቃላቱ ይሄን ሁሉ ነገር ከሚያንዛዛ በቀላሉ መግለፅ ይችል ነበር ልክ እንደዚህ፣

ሽረኛ፡– ሰው – አቶ እጅጉ !! በቃ!! አጭር ግልፅና ወቅታዊ ፍቺ !!

ምሳሌ፣ አቶ እጅጉ ሽረኛ ነው፡፡ ትክክል !! ይሄ ምሳሌ አይደለም፣ እጅጉ (እጅ እግሩን አስሮ ሲአል ይወርውረውና) 'ሽረኛ' ነው፡፡ ሽረኛ ብቻ አይደለም፣ ምቀኛም ነው፡፡ የሚቀናበት ነገር ቢያጣ እኩል በተሰጠን 24 ሰዓት ይቀናል፡፡ ("እንደው በየትኛው ጊዜ ብትማሩት ነው ይሄን ሁሉ ነገር ያወቃችሁት?" ይላል የማያውቀውን ነገር አውቀን ካገኘን፡፡ ለነገሩ እሱ ምንም አያውቅም፡፡) ምን ይሄ ብቻ! እግዜር በፈጠረው አየር ሳይቀር ይቀናል፤ የቢሯችን መስኮት ተከፍቶ እንደልብ አየር ሲገባ ብቅ ይልና፣ "ይሄን አየር በነፃ ትሉታላችሁ" ይላል፡፡ እንክፉል? ሽረኛም ምቀኛም ብቻ አይደለም መሰሪ ተንኮለኛም ነው፡፡'አሚልቶ አይሰጥም' ይባላል እንጂ ይሄው የተሟላ ክፉ ሰው፡፡

እንግዲህ ሽረኛ፣ ምቀኛ፣ መሰሪ ሆኖ ደግሞ አለቃዬም ነው፡፡ ጥሎብት አይወደኝም፡፡ እኔም ስለማልወደው 'ተመስገን ቢወደኝ ምን ይውጠኝ ነበር?' እላለሁ ሁልጊዜ፤ ለምወደው ሰው

ነው የምጨነቀው፡፡ አሁን በዚች ቅፅበት በሆነ አጋጣሚ ነገር ሎተሪ ምናምን አይነት እድል ገጥሞኝ በድንገት የብዙ ብር ባለቤት ብሆን (እረ የትንሽም ቢሆን) የመጀመሪያ ሥራዬ ሁለት እጆቼን ኪስና ኪሴ ከትቼ በቀዳዳ ኪሴ ውስጥ በሾለኩ ጣቶቼ ራቁት ታፋዬን በማኳጨው ሙዚቃ 'ሪትም' እየተመተምኩ ጀነን ብዬ ወደ አለቃዬ ቢሮ ሄድና አንኳኳለሁ፣ ኖ...ኖ... አላንኳኳም፤ በሩን በእግሬ ገፋ አድርጌው እገባለሁ፡፡ (ካፈቀሩ ከነፍስ፣ ከጠሉም ከነፍስ ነው የምን ማስመሰል) ፊት ለፊት፣ ጉማሬ ፊቱ አለቃዬ ሁልጊዜ በሚደፈርሱ አስቀያሚ ደመኛ አይኖቹ ያፈጥብኛል፡፡ ቀጥሎ ኪሶቼ ውስጥ የወሸቅኳቸውን እጆቼን በቁጣ ያሃል፣ (ደንግጨ ከኪሴ እንዳወጣቸው እንድርበተበት፡፡) ፀጥ ብዬ በትዕቢት ሳየው የኢትዮጵያን ሴጋራ ሁሉ ብቻውን ያጨሰ ከሚያስመስሉት አስቀያሚና ገጣባ ከንፈሮቹ ቃላት ይፈለፈላሉ፤ ሰው ሰው የማይሸቱ አብሪተኛ ቃላት፡፡

ምናልባትም፣ "ብላችሁ ብላችሁ ማንኳኳቱንም ተዋችሁት..." ይል ይሆናል፡፡ (እግዜርና ሰይጣን ለዚህች ቅፅበት አርቅ አውርደው ይሄን ድንጋይ ራስ አለቃዬን በመዶሻ ያንኳኩትና፡፡) ወይም፣ "ኪስህ የወሸቅከውን እጅህን አውጣ!" ሊልም ይችላል፣ አላወጣም ! (ኪሴ ቀዳዳ ቢሆንም ቀዳዳውን ተሻግሮ ያለውም ወንድነት የራሴ ርስት ነው - ዘራፍ ! በቀዳዳ እኛነታችን ውስጥ አያለፉ ወንድነታችንን ያኮላሹን ከፋዎች ሁሉ ከዛሬ ጀምሮ አድርጉ ያሉትን አናደርግም፡፡)

ኮራ ብዬ "እእእእ አቶ አጅጉ" እለዋለሁ፡፡ ("አቶ" በማሽፍ ሲጠራ እንዴት ያለ አሪፍ ስድብ ነው፡፡) ለምሳሌ፣ እኔ "አቶ" ከሚለው ቅፅል ይልቅ ከስሜ በፊት ለሃሪን የሚያህል ባዶ ምድረ በዳ ቢዘረጋ ይሻለኛል፡፡ በተለይ አለቃዬ "አቶ" ከሚለኝ !! ...እዎ ! እሱ "አቶ" ሲለኝ በውስጡ "መቼም ለአቶነት አትበቃም በቸርነቴ 'አቶ'ነት ልስጥህ እስቲ" የሚል ይመስልበታል፡፡ 'አቷም'!!

እና "አቶ አጅጉ ከዛሬ ጀምሮ ሥራ ለቅቄያለሁ" እለዋለሁ - በኩራት፡፡ 'እእእእ' የምትለዋን ዘገምተኛ ቃል ማስቀደም አልረሳም፡፡ አራት ዓመት ሙሉ የሱን አስቀያሚ 'እእእ' ቻዬ ኖሬ የለ - ስለዚህ የምለው እንደዚህ ነው፡፡ "እእእእ...አቶ አጅጉ ከዛሬ ጀምሮ...እእእእ ሥራ ለቅቄያለሁ !!"

ይደነግጣል፣ አያምንም፡፡ እኔ ሰፈጋ የዋልኩበትን ሥራ ሁሉ ለአለቆቼ እንዲህ ሠርቼው እንዲህ አድርጌው እያለ በሰልክ መወሽከቱ ሲቆም ስለሆነ ይደነግጣል - እሰይ ! ወሽካቶች መደንገጥ አለባቸው፡፡

ወዲያው የበሰበሰ የማኔጅመንት 'ሲስተሙን' እኔ ላይ ሊሞክራት ይፍገመገማል፣ "አትደንግጥ የበታች ሠራተኛህ ፊት አዋቂ፣ ልበ ሙሉ ምንትስ ሆነህ ቅረብ፣ ባትሆንም ሁን..." የምትለዋን ያስብና ጉሮሮውን ጠራርጎ፣ "እእእ...እዚህ መሥሪያቤቱ ራስህን ለማሳደግም ሆነ ቤተሰብህን ለመርዳት አይሻልህም?" ይላል፡፡ ሥራ ብለቅ ቤተሰቦቼ በረሃብ ዛሬውኑ የሚያልቁ በሚያስመስል ሁኔታ 'ቤተሰብ' የምትለዋ ቃል ላይ አፅንኦት ሰጥቶ፡፡

ከፋዎች መሳሪያ ልጅህ ላይ ባይደግኑም፣ እናትና አባትህን አፍነው ባይወስዱም፣ የነገን ጨለማነት እየነገሩ ያግቱሀል፡፡ ስንቱ መሰለህ ቁራጭ ዳቦ እንዳይነሱት ፈርቶ ለማንም አጋሰስ ጉልበቱን

የሚገፈግፈው፣ ስንቁስ ነው 'ከሥራ መባረር' የሚባል የታንክ አፈ ሙዝ ልቡ ላይ ተደግኖበት ዘመናዊ ባሪያ የሆነው !! ስንቷን ሚስኪን በፀሃፊነት ስም የጭን ገረዱ ያደረጋት ጋንጩር አለ . ቢሮ ይቁጠረው !!

ሀላፊ ሲባል አርቲስት ነው:: ወንበሩን መድረክ ያደረገ ተዋናይ:: ያውም ድብን ያለ ትራጀዲ የሚተውን:: እና እኔ ምን አለዋለሁ... ሃሳቤ ደስ ብሎኝ ሳምሰለስል፣ ዙፋን ዘው ብላ ወደ ቢሮዬ ገባች:: ጥሎባት ማንኳኳት አትወድም:: 'አንኳኪ!' ብሏት የሚያውቅም የለም::

"አብርሽዬ" ትለኛለች:: (ስሟን ከነአያቷ ቁስ ይጥራትና) ! ሁልጊዜ ስትጠራኝ እንዲሁ ነው:: ታዲያ አጠራርዋ ከማማሩ ብዛት እኔን ለጠራችኝ ሌሎቹ 'ወይዬ' ሲሏት ይዳዳቸዋል::

"እንዲህ በሀሳብ ጭልጥ ያልከው ወዴት ሄደህብኝ ነው?" ወዴትስ ብሄድ ምን አገባት:: ጭራሽ የምሄደውስ የምቀረውስ ለሷ ነው እንዴ? ('ሄደህብኝ !!' ጥርግ ብል እንትናዬ እያለች አንዱ ቢሮ ልትንኳተት::)

"እ...ምነው ጠፋሽ?" አልኩ እንደመጣልኝ:: የምለው እጥቼ እንጂ ዙፋን ደግሞ መቼ ጠፍታ ታውቅና:: በአንድ ጊዜ ሰባት ቢሮ ውስጥ የምትገኘውን ዙፋንን ጠፋሽ ማለት መሬትን "ምነው በዚህ ሳምንት መዞርሽን አቆምሽ?" ብሎ ከመጠየቅ አይተናነስም::

"ሆሆ ከየት ተገኘሽ፣ አሁን እንኳን ስመጣ አራተኛዬ ነው" አለችና ከጠረጴዛዬ ፊት ለፊት ወንበር ስባ ተቀመጠች:: ወንበሩ ተንጫጫ:: ጉርድ ቀሚሷ ቀይ ታፋዋን ወለል አድርጎ ያሳያል.... ኤጭጭጭጭጭጭጭጭ!!

"ቆንጆ ናት" ይባላል:: "ትሁት ናትም" ይሏታል:: "የሰለጠነች፣ ሰው አክባሪ" የሚሏትም ብዙ ናቸው፣ እንደው ባጠቃላይ እዚህ ቢሮ ዙፋንን ለማናገር፣ ለማቅረብ፣ ቢመቸው ወደ አልጋው ጎትቶ አብሯት ለመጋደም የማይመኝ ያለ አይመስለኝም::

ዙፋን እኛ ቢሮ ሥራ ስትጀምር ከሥራ ልምዷ ጋር ከእግዜር የተላከ "ከዛሬ ጀምሮ 'ያየ አመነዘረ' የሚለው ጥቅስ ተሰርዟል" የሚል ደብዳቤ ይዛ የመጣች ይመስል፣ እዛ ፋይናንስ ከሚሠራው ዲያቆን ወልዱ ጀምሮ ሰው ሰላም ሲል አገጩ መሬት እስኪነካ የሚያጎነብሰው ጴንጤው ምክትል ኃላፊያችን የዙፋንን እግርና መቀመጫ አይተን እንሙት አሉ:: ዙፋንም ታዲያ የዕለት እንጀራዋ የሰው አይን ይመስል ነገረ ሥራዋ ሁሉ የታይታ ነው:: አቤት መታየት ስትወድ:: ሰው ከኋላዋ እንደሚያይት ከጠረጠረች ለከፉ ቀን ያስቀመጠችውን መቆናጠር ሁሉ ትጠቀምበታለች::

ጥሎብኝ አልወዳትም፣ እሷም ታውቀዋለች፤ ምንም ትልበስ፣ እንዴትም ትራመድ እንደገለባ ትቀልብኛለች:: ብትሞት ቢሮዬን ሳትረገጥ አትውልም - 'ዛሬስ እንዴት ነኝ?' ልትል አይነት:: የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ፀሃፊ ናት:: ቅርብ ጊዜ ነው የተቀጠረችው - ሃሃሃ ወይ መቀጠር፣ ቅጥር ነፍስ ገዳይ::

የአለቃዬ አሊቃ ፀሃፊ ናት፡፡ የተመቻት የሃብታም ልጅ፣ ቤት ከመዋል ብላ ፀሃፊ የሆነች፡፡ እሷ 'ፀሃፊ' ሲሏት አትወድም፡ 'ሴክሬታሪ' ነኝ ነው የምትለው፡፡ ውድ ልብሶችን የምትለብስ፣ በተረከዘ ረጅም ጫማ ከቢሮ ቢሮ 'ሲታውደለድል' የምትውል ቆንጆ እንዴት ፀሃፊ ትባላለች? የሚያማልሉ ቀያይ እግሮች ያሏት፣ የከረመና የታጀለ የወረቀት ጠረን የሞላውን ቢሮ በሽቶዋ የምትፈውስ ዙፋን እንዴት 'ፀሃፊ' ትባላለች? ገና ሳያት እንደረኸምና እንደማያልቅ መንገድ ትደከመኛለች፤ እንደ ረኸም ሰዛ ቢሰ ወሬ ትሰለቸኛለች፡፡ ከልቤ ትሰለቸኛለች፡፡ ባትመጣብኝ ደስታዬ ነው፡፡ ይሄንን ነገር ማመን አልቻለችም፡፡ በሕይወት ዘመኗ እንደኔ ፊት ነስቷት የሚያውቅ ወንድ ያለም አይመስለኝም፡፡

...ትለዋለች በተዘዋዋሪ፡ "...አከሌ እኮ ጨዋ ነው፤ የኔ ጌታ እሱን ያገባች የታደለች፡፡ ቢሮው ስሄድ ከወንበሩ ብድግ ብሎ ሥራውን አርግፍ አድርጎ ትቶ እኮ ነው የሚያዋራኝ..." እንኳን ተነሳላት ! ለምን ከመነሳት አልፎ ዘሎ ኮርኒሱ ጋር አይጋጭም፡፡ እንኳን ለደቂቃ ሥራ ማቆም፤ ለምን የሥራ መልቀቂያ አያስገባላትም፡፡ እዝግ፣ ታዝገኛለች፡፡ ኮተታም ከብር አሳዳጅ፡፡

የጠላሁባት ምክንያት እንደ አንዳንድ ወንዶች ከራሳቸው ጋር ፈተና ሲገቡ መሻታቸውን ሲሸሹ ሴት እንደሚያንቋሽሹት አይነት አይደለም፡፡ ቁልጭ ያለ አገር ያወቀው ፀብ ያገረረው፣ በአምሳገነን አግሯ ምንም በሆነ ሲትነቷ፤ ፍትህ ትረግጣለች፤ ያማረችው በሚስኪኖች እንባ ታጥባ ነው፡፡ ንፅህናዋ ንፁህ ነፍሳትን ትቢያ አድርጋ ነው፡፡ ያውም ራሳቸውን መከላከል የማይችሉ ሚስኪኖችን፡፡ ሸረኛ ናት፡፡ ዙፋን ሸረኛ ናት፡፡ አለቃዬ ሸረኛ ነው፡፡ እዚህ የተሰበሰቡ ወተፈናም ኃላፊ ተብዬዎች ሁሉ ሸረኞች ናቸው፡፡ እና፣

መዝገበ ቃላቱ፣ 'እና' የምትለዋን ቃል ለያያዥ፣ በቻዋን የማትቆም ቁንፀል ይላታል፡፡ በአጭር ምሳሌ 'እና' እኔ ነኝ፡፡ በሸረኞቹ እና በደህነኞቹ መሀል ያለሁ ወይ አልሸርር ወይ አልደህንን "እና" እኔ ነኝ፡፡ ምንም ታሪክ፣ ምንም ትርጉም የለኝም፡፡ሥራዬም ባህሪዬም በሆኑ ነገሮች መሐል መደበቅ ይበዛበታል "እና" ነኝ !! እና ምን ይጠበስ፡፡

ደህና፣ ኢማማ መለኮት መዝገበ ቃላቱ ሳይሆን መዝገበ እግዚሃር "ደህና" ብሎ የሚላቸው አይነት ናቸው፡፡ እማማ መለኮት እድሜያቸው ሃምሳ ሁለት ወይም ሃምሳ ሰባት (እራሳቸው እንደሚሉት)፣ ትሁት፣ በዚህ እድሜያቸው ለሁሉም ሰው ታዛዥ እና የሁላችንም መካሪ፡፡ እማማ መለኮትን የማይወድ ማንም የለም - መስፈሪያው ቢለያይም፡፡ በምንም ይሰፈር በምን፣ እንደኔ የሚወዳቸው ግን የለም፡፡

የዛሬ ዓመት አካባቢ እማማ መለኮት ቢሮዬ መጥተው ከጠረጴዛዬ አንድ ሁለት እርምጃ ራቅ ብለው ቆሙና ከወገባቸው ጎንበስ በማለት ሰላምታ አቀረቡ፡፡ ያረጁ ይመስላሉ፡፡ ፊታቸው በሀዘን እኮፍኩሮ በእድሜ እናቴን ይበልጣሉ፡፡ ከወንበሬ ተነስቼ ለሰላምታ እጄን ዘረጋሁላቸው፤ በሁለት እጆቻቸው አሁንም ጎንበስ ብለው ሰላም አሉኝ፣ እጃቸው ይሻክራል፤ ልክ እንደ እናቴ

እጅ፡፡ እነዚህ ሞረድ እጆች የሰንቶቻችንን ባለ ለስላሳ እጆች ህይወት እንደሞረዱ ፈጣሪ ይወቅ !

እንዴቀመጡ ወደመለከትኳቸው ወንበር ቀስ ብለው ተቀመጡና የመጡበትን ጉዳይ ቀስ ብለው አስረዱኝ፤ "እትዬ አብረሃም (እቤት 'እቶ' በእሳቸው እንደበት እንዴት ክብር እንዳለው !) ያው እንደምታውቀው እዚህ ቤት ነገረ ሥራችው ሁሉ ውስጥ ለውስጥ ነው፡፡ ደከመኝ፤ ሰለቸኝ ባልል በሠራሁ ለትንሽ ትልቁ 'እሺ!' ብዬ ባደርኩ ድንገት ከሥራዬ ነቀሉኝ፡፡" አሉና እንባቸው ተዘረገፈ! እድሜ በሸነተረው የቆዳቸው አጥፋት ሽብሽብ ውስጥ እንባቸው ጎረፈ፡፡ በነጠላቸው ጫፍ አይናቸውን ጠረጉ፡፡ (እዚህች ባልቴት ውስጥ ይሄ ሁሉ እንባ እንዴት ሊኖር ቻለ? እድሜ ልካቸውን ያጠራቀሙት ይሆን??) እማማ መለኮት ከፅዳት የሥራ መደብ ተነስተው በሀያ ዓመት የቢሮክራሲ ባቡር ተጉዘው ፀሃፊ ለመሆን የበቁ ፅኑ ሴት ናቸው፡፡ ከልምድ እንዳየሁት ብዙ ታላላቅ ድርጅቶች ሱፍ ለብሰው በሚኮፈሱት አለቆቻቸው ሳይሆን በሚስኪኖች ትከሻ ላይ ተሞነው ነው የቆሙት፡፡ እማማ መለኮት የድርጅታችን ዋልታ ይሄው ተባረሩ፡፡

ከዘ ባፊት፡ ከመባረራቸው በፊት፤ አሽሙር የሚመስል ስብሰባ ተደረገ፡፡ አንዲት ረዳት የሌላቸው ሚስኪን ባልቴት ለማባረር ቱባ ቱባ ባለስልጣን፤ ከቱባው የተተረተሩ ከር ኢቃጣሪዎች እና "እናዎች" ውሃ ቡና ቀርቦ ስብሰባ ተደረገ፡፡የስብሰባው መሪ፤ "ሽረኛው" እጅጉ፤ ፀሃፊው "ሽረኛው" እለሙ፤ ተላላኪው፤ ወሬ አቀባዩ (እንደ ሰው አልባ አውሮፕላን እያንዣበበ ለላኩት አለቆቹ ወሬ ይቃርማል፡፡ "መታዘዝ ፅድቅ ነው" ሲባል የመታዘዝ ፅድቅነትን የማያመዛዝን አዕምሮ ተሸክሞ የሌሎች ባሪያ መሆን ማለት አይደለም፡፡ ስብዓዊ ትዕዛዝ፤ ሰው መሆን 'ይቅርብህ ተብለህ ሳይሆን፤ 'ለእኔ ማለት ይቆየኝ፤ ቅድሚያ ለሌሎች' ከሚል በጎነት መነሳት ነው፡፡ በጎነት በትዕዛዝ አይመጣም፡፡)

ስብሰባው ተጀመረ፡፡ ለአንዲት ባልቴት ተሰበሰቡ እንዳይባል የማይረባ አርሲ ኩርሲ አጀንዳ ጋር ተደምሮ የእማማ መለኮት መባረር "መቀነስ" የሚል የዳቦ ስም ተሰጥቶት አጀንዳ ሆነ፡፡

"ባንድ ላይ ሲሄዱ" መዝገበ ቃላቱ በአንድ ላይ መሄድን በአንድ ላይ ከመታየት ነጥሎ አለማየቱ ትልቅ ጉድለት ነው፡፡

"ሽረኛ"፣ "እና" ና "ደህና" ስብሰባው ላይ በአንድ ላይ ተገናኙን፤ በማንኛችን በኩል መንገዱ እንደሚናድ ልናይ - ቀድሞ የተናደውን፡፡

"ትናደ"

ስብሰባውን የጀመረው አለቃችን አቶ እጅጉ ነበር፡፡ ኩፍስ ብሎ የኮቱ አጥፋት ሸብዳዳ ትከሻው ላይ ተከምሮ (ከኮቱ ውስጥ ትንሽ የሶፋ ትራስ ያስቀመጠ ይመስለኛል)፡፡ ጩኸዋ ለመሣ"ሰል በሚዳዳው ድምፅ ስብሰባው መጀመሩን አረዳ ('አበሰረ' የሚሉም አሉ "ከሽረኞች ወገን ናቸው") "እ...ያው እንደምታውቁት..." አለ (ምንም በማናውቀው ነገር) "...መሥሪያ ቤታችን ያለውን

መልካም ስምና ዝና ለማስቀጠል (ሂሂሂሂ ጉድ ፈላ በቀን የሚመጣው ባለጉዳይ ሁሉ እዬዬ እያለ ተራግሞ የሚሄድበት መሥሪያ ቤት 'መልካም ስምና ዝና' ይሁና...) ዘመናዊ የአሠራር ሲስተምና ዘመን አፈራሽ መሳሪያዎች እንደሚያስፈልጉ በማመን የተለያዩ ዓለም እቆፍ ተሞክሮዎችን ወስደን እየተንቀሳቀስን 'ያለበት ሁኔታ ነው ያለው'...

እነዚህ ዘመናዊ መሳሪያዎች ደግሞ ብቻቸውን 'ጠብ' የሚል ለውጥ እንደማያመጡ 'እሙን' ነው፤ ስለዚህ ቢሯችንን 'በአመለካከት' 'በእውቀት' 'እና' 'በተግባር' ከመሳሪያዎቹ ጋር አብሮ በሚሄድ 'ወጣት' የሰው ኃይል ማደራጀቱ ለነገ የማይባል አንገብጋቢ ተግባር ነው... !!"

በእማማ መለኮት በኩል መንገዱ "ቀናደ":: ጨዋነትን የሜኑነው መኪና ገደል ገባ:: ትህትና ተሸቀነጠረ:: መንገድ ስለሌለ ወደኋላ ተመለስን:: መንገድ አፍራሽ ሾረኞች ራእይ እንደሀልም ያያሉ:: ከመድረስም ተጣልተዋል:: መንገድ የለማ ...!! ከአባይ ወዲያ ማዶ ያለ ዘመድ ሆነ የእማማ መለኮት ሥራ፤ እንባቸው በአይናቸው የሞላ እለት ዋይ ብለው ቀሩ::

እንዴት በእድሜ የገፉ ሚስኪን አባሮ በየቢሮው እየዞረች ምስጋና የምትቀላውጥ ገልቱ ለመቅጠር ምድረ ጉማሬ ሚስኪኑን ላብ አደር ሰብስቦ አላዘነ:: ደግሞ ስለዘመናዊነት ያወራሉ፤ እግዚኦ አለቆቻችን ስለዘመናዊነት እወሩ::ስልካቸው ባትሪ ሲጨርስ ተበላሽ ብለው ሠራ ቤት የሚሮጡ አለቆቻችን ዘመናዊነትን ሰበኩ:: ከፕሪንተር የሚወጣ ወረቀት ደመና ሰንጥቆ እንደሚወጣ መልአክ በግርምት የሚመለከቱ:: ('እይ ፈረንጅ ነፍስ መፍጠር እኮ ነው የቀረው!' እየተባባሉ::) አለቆቻችን ዘመናዊ እንሁን አሉ::

እማማ መለኮት በጡረታ ስም ተባረሩ:: ('ተቀነሱ በል አቶ አብረሃም' ተብያለሁ::) ዙፋን ተቀጠረች - አሁን ድርጅቱ ዘመናዊ ሆነ:: "እንደምን ዋላችሁ..."፣ "ሃይ ጋይስ" በሚል ሰላምታ በመተካቱ አልልል ቢሯችን ዘመናዊ ሆነ::

ዙፋን የዘመናዊነት ፋና ወጊ፤ አንድ ገፅ ደብዳቤ ስትፅፍ አንድ ከግማሽ ገፅ ስህተት የምትዘራ ጉድ:: ወሬ ብቻ፤መሽኮርመም ብቻ፤ በየስሙ ላይ 'ዬ' መጨመር ብቻ (አብርሽዬ...ቶማስዬ...ጋሽ ሰይድዬ...ተፈራዬ...ሐጎስዬ...ገኒዬ...እግዚያብሄርዬ...ጂሰስዬ...) እንደ 'የ' ፊደል ትልቅ አፍ ብቻ ያላት መርገምት::ደህና ነገር ሲናገር ከንፈሩ እንደደረቀ ሰጡ በየደቂቃው ቻፕስቲክ እየለቀለቀች በየቢሮው ማውራት !! ('ውይ ጥርስ አታስከድንም፤ ተጫዋቹ ምናምን ይሏታል - የሾረኛው መንጋ::)

ቆንጆ ብቻ መሆን እንዴት ይቃፋል:: ሴት ብቻ በመሆን ከወንድ የሚቸር ወሲባዊ ክብር ምንኛ ውድቀት ነው?! ዕድሜ ከፍ ባለ ቁጥር የሚናድ የአንባይ ካብ:: እንዴት ሰውን ያህል ፍጥረት ሙሉ ታወራለች? ስለፀጉር ሁለት ሰአት፣ ስለጥፍር አንድ ሰዓት ስለጥፍር ቀለም ሙሉ ቀን፣ስለ ልብስ...

የመታየት ልክፍት (ኤግዚቢሽኒዚም ይለዋል በሬቻ):: በፋሽን ስም ነጋቸው ላይ ውበት ሊዘሩበት

የሚችሉትን ዛሬ እርሲ ኩርሲ የውበት ኮተት እያወሩ ይፈጁታል:: ይሄ የሴት ውበት ነው የሴት ብክንት:: ስለውበት የሚደሰኩር ሚዲያ ላይ አፍጥጣ የምትውል ዙፋን፣ ቆዳዋን በምናምን አደንድና ፍቅር እንዳይሰርጽት ራሷን ስታቀድድ ትኖራለች:: ሴት ከመልክ የተሻለ መወዳደሪያ ከሌላት ውድድሩ ውስጥም የምትኖረው ቢበዛ ለጥቂት ዓመታት ነው:: ባካና ! ዙፋን ባካና ናት፤ ስሟ ራሱ እሷ ላይ ሲደርስ 'ዙፋን' የሆነ፣ የመወዘፍ አይነት ደውል ነው:: (ውዝፍ ከሚለው ስርወ ቃል የመጣ...)

ከአለቃዬ ጋር በአይኗ ስትዳራ ስንት ጊዜ ታዘብኩ:: እማማ መለኮትን ነቅላ ላትፀድቅ ነገር ራሷን የተከለችበትን ቆሻሻ መንገዷን አይቻለሁ:: ለፀሃፊነት ሥራ ውድድር መሰለፍ የማይችል ባለጩት ጨንቅላቷ ላይ ሰው ሰራሽ ፀጉር ጎዝጉዛ ክቡር ሴትነቷን በየቢሮው ስትጎዘጉዝ ሳናይ አላወራንም፤ "ጭስ ካለ እሳት አለ" ብለንም አይደለም:: ቆይቶ የተደረገ ግምገማ ላይ የተገደደች አስመስላ ቀባጠረችው እንጂ:: ("የሸረኞች መንገድ የተናደች" አለት)

ባለቤት የለሽ ሰጥ ማንም አላፊ አግዳሚ የሚዘማናት:: ወንዶች በምናምናቸው እየተመሩ የሚደርሱባት ጥግ፡፡ የሴትነት ባንዲራ ዝቅ ብሎ የሚውለበለብባት ፀያፍ ምሰሶ:: ለወረደ የሴትነት ባንዲራ ሴሰኛ ወንዶች ሲዘምሩ ምሰሶው እንዴት 'ቴንኪው' እያለ ይሽኮረመማል?

የአድማ ጉዳይ ነው፣ ያች የሴትነት ባንዲራ ትወርዳለች:: ያኔ ዘማሪ ሲጠፋ ሴትነት የተነጠለው "ሰው መሆን ብቻውን" ሲቆም ይሄ ከተማውን የሞላው አላፊ አግዳሚውን በቅናት ግልምጫ የሚገነትል፣ "ምክሩ ላይ ስቆ የመከራ ዱላ መድረሻ ያሳጣው፣ ፍቅር አልባ የሴት ፊት ሁሉ" ዙፋን የተባለች መህበርተኛ ይመረቅለታል::

አቀባበል ይደረግላት ተባለ - ዙፋን:: ሰው እንዴት ምንም ይቀበላል? በግ ታርዶ፣ ቢራ ቀርቦ "አንዲት ፀሃፊ ለመቀበል ይሄ ሁሉ ድግስ" እንዳይባል፣ ለአቀባበሉ ህዝባዊ ስም ወጣለት - "የሩብ ዓመቱ የግምገማ ማጠቃለያ":: ሲበላ፣ ሲጠጣ ሸረኞች የሸረኛ ልዕልታቸውን ከብበው እያውካኩ ጥሬ ከብስል ሲሰለቅጡ እማማ መለኮት ናፈቁኝ:: እንዲህ ዝግጅት ሲኖር እሳቸው ሌሊት ሁሉ እያደሩ ወጥ ይሰሩ ነበር - አምስቱ ሳይከፈላቸው:: ነጭ ልብሳቸውን ለብሰው፣ ምድረ ሆዳም ሲያስተናግዱ ይውሉ ነበር::

መንገዱ...

ከግብዣው ሹልክ ብዬ ወጣሁና፣ አጠያይቄ እማማ መለኮት ቤት ሄድኩ:: በራቸው ላይ ቁጭ ብለው የምስር ክክ እየለቀሙ ነበር:: ሲያዩኝ በድንጋጤና በግርምት ተርበተበቱ:: የምስር ክክ የያዘውን ትሪ ወደቀኛቸው ካለች መደብ ነገር ላይ ሲያስቀምጡ -የተለቀመው ካልተለቀመው ተቀላቀለ...:: እንደእኛ ቢሮ፣ እንደእኛ ሃሳብ፣ እንደእኛ ፖለቲካ፣እንደእኛ እኛነት ተመልሶ መልቀም:: አዲስ እንግዳ ሃሳብ፣ እንግዳ አሰራር፣ እንግዳ ርዕዮተ ዓለም ሲመጣ ያከበርን መስሎን የሰራነውን ማፍረስ::

ከመቀመጫቸው ብድግ ብለው በአክብሮት ቆሙ፤ "ውይ በሞትኩት እዚህ ድረስ ምን አለፋህ

አቶ አብረሃም - እጇ ቆሻሻ ነው ቆይ" ብለው ቀሚሳቸው ጋር ጠራረጉና በተስፋ እያዩኝ ጨበጥኳቸው፣ ምናልባት ወደሥራ ልመልሳቸው የሄድኩ ይመስላቸው ይሆን? ግባ አሉኝ፤ ገባሁ፤ ንጹህና ጠባብ ናት ክፍላቸው:: ወደጓዳ መግቢያ ላይ ባለጥልፍ ነጭ መጋረጃ:: ባለመደገፊያ የቀርከሃ ሶፋ:: ግድግዳ ላይ አንድ ጥቁርና ነጭ የትልቅ ሰው ፎቶ አለ (ባላቸው ይሆኑ?):: ከጎኑ ባለድግሪ ወጣት ባለቀለም ፎቶ:: አማማ መለኮት መጋረጃዋን ገለጥ አድርገው ወደ ጓዳ ገቡ::

*** *** ***

ቡና እንደምወድ ያውቃሉ:: ላፍላልህ ሳይሉ ቡናውን አቀራረቡ:: አወናኝ ስለነበረው፣

"ግራ ገብቶኛል፣ እንቅልፍም አልወሰድሽ ብሎኝ ነው ያደርኩት:: እንግዲህ በዚህ ዕድሜ ሰው ቤት ልብስ ላጥብ ነው ? እንጀራ ልጋግር ? እኔኮ ሌላው አይደለም ያሳዘነኝ፣ ይሄን ያህል ዓመት ያገለገልኩበት ቤት ነው:: ምናለ ለወጉ ጠርተው እንግዲህ በቃሽ ቢሉኝ:: አቶ እጅጉ መጥቶ፣ ስሜን እንኳን አልጠራኝም፣ 'ይሄን ኮምፒተር አፀዳጅው፣ እንግዲህ ጡረታ መውጫሽም እየደረሰ ነው' ቢቃ እንዲህ ነው ያለኝ:: የዛሬን ቀን አያምሽልኝ፣ እንዲሁ አለኝ...ይባላል ? አቶ አብርሃም አስቲ ፍረድ፣ ፍርድ ለራስ ነው መቸም..."

አለቀሱ አማማ መለኮት:: የማደርገው ነገር ጠፋብኝ:: "ብዙ ያየሁ ሰው ነኝ፣ ይከፋኛል፣ ማግኘትም ማጣትም ማጀቴን የጎበኘው ሰው ነኝ::ባሌ የሞተብኝ ሴት ነኝ-እርጅቻለሁ:: ልጄ ምጥ ይግባ ስምጥ የጠፋብኝ ብሉተኛ ነኝ:: ለትንሽ ትልቁ ደፋ ቀና የምለው ቀባሪ የለኝም፣ 'የአገሬ ሰው ነው ቀባሪዬ' ብዬ ነው:: እንዴት እንዲህ ያመንኩት ህዝብ ይተፋኛል? እንዴት ባዕድ እሆናለሁ? አይዞሽ ማንን ገደለ? ፀሃፊነቴን ይተዉት እናትነት ይጠረወራል ? አንድ ሰው በሬ ዝር አይልም ? በሃዘን በደስታው ከሥራዬ አልፎ ተርፎ ለድግሳቸው ጉልበቴን ገብሬ ቤታቸውን አሳቀናሁም ? ፍረድ አቶ አብረሃም - ፍርድ እንደራስ ነው" ስኳር ወደ ስኒዎቹ ጨመሩ:: በዝምታችን ውስጥ ቡናው ሲቀዳ ደስ የሚል ድምፁ ጠባቧን ቤት ሞላት:: አንዲት ከሴት ያለች ጥቁር ድመት ገብታ ረከቦቱ አጠገብ ቆመች:: ለቡና ቁርስ ከተቀራረበው ዳቦ ቆንጥረው ሰጧት::

"እማማ መለኮት!" አልኩ ቀስ ብዬ፣

"ወይዬ!" አሉ ቡናውን እያቀበሉኝ::

"ልጄ ጠፋ ነው ያሉኝ...?" ወይ ወሬ መውደድ አሁን የሰው ብሶት ከመቀስቀስ ውጭ ምንም ላልፈይድ ምን አጠያየቀኝ...::

"አዎ...ይሄ ፎቶ የሱ ነው" አሉ ወደ ባለድግሪው ወጣት እየጠቆሙኝ:: ጭራሽ ተነስተው ፎቶውን ከተሰቀለበት አወረዱና ሰጡኝ:: መልከ መልካም ወጣት ነው፣ ሳቂታ::

"ልጄ ነው - አንድ ልጄ:: ስድስት ኪሎ በድግሪ ተመርቆ ወር ሳይቆይ 'ወደ ውጭ አገር ልሂድ' ብሎ ተነሳ:: 'ኬንያ የሚባል አገር ደረስኩ' ብሎ ደወለልኝ:: ይሄውልህ ከዛ በኋላ ይኑርም ይሙትም ወሬው የለ" ብለው እንባቸውን ዘረገፉት::

"ከሄደ ቆየ ?..." በሃሳቤ ኬንያ ያሉ ጓደኞቼን 'ይሄን ልጅ ካላገኛችሁ ወዮላችሁ!' ልል ተዘጋጅቼ:: "እንግዲህ ወደ አስራ አምስት ዓመት አይሆነውም ብለህ ነው...?" ፎቶው ላይ አፍጥጬ ቀረሁ::

"ቡናው ቀዘቀዘብህ፣ የኔ ነገር" ብለው ፎቶውን ከእጄ ተቀበሉና ቦታው መለሱት::

ስናወራ ቆይተን እንደምጠይቃቸው ነግሬያቸው ስወጣ፣ "አቶ አብረሃም፣ ካላስቸገርኩህ በቀደም ተጣድፌ እኔ መሳቢያ ውስጥ፣ መሃረቤን ረስቼው መጣሁ:: እንደው ላቶ ሽበሩ ብትሰጥልኝ በዚሁ ሲያልፍ ያቀብለኛል" አሉ:: አቶ ሽብሩ የመስሪያ ቤታችን ሹፌር ነው::

ያችን ተዓምረኛ መሃረብ የቢሮው ሰው ያውቃታል:: እማማ መለኮት ፀበል ቤት ይሄዱና ወይም ቤታቸው ዝክር ብጤ ትኖራቸውና ለምንቀርባቸው ባልደረቦቻቸው የፀበሉ ቤት ዳቦ በመሃረባቸው ጠቅልለው ያመጡልናል = በቀይ ክር የሀረግ ጥልፍ ዙሪያውን የተጠለፈበት መሃረብ...::

*** *** ***

በቀጣዩ ቀን ቢሮ ስገባ አቶ እጅጉ ደረጃው ላይ አገኘኝና፣ "አቶ አብረሃም፣ ምነው ድግስ ረግጠህ ወጣህ?" አለኝ:: "እጋሰስ!" አላልኩትም::

የእማማ መለኮትን መሃረብ ለማምጣት ወደ ዙፋን ቢሮ ሄድኩ:: ለመጀመሪያ ጊዜ ነበር እማማ መለኮት ከለቀቁ በኋላ ወደዚህ ቢሮ የመጣሁት:: ዙፋን አፏን ከፈተችው፣ "አ....ንተ በመጨረሻ መጣህ:: ዝም ብለህ ትንቀባረራለህ መምጣትህ ላይቀር" አለች ፊቷ አንበሳ ገዳይ አይነት ቶክራ ሰፍሮበት - ደነዝ!! አትንብሳ እግሯን የሆነ ነገር እያደረገች ነበር የምታወራኝ - ጠረጴዛው እግሯን ጋርዶኛል::

"ምን እዚህ ይሄ መንገዳችሁ አቧራ ብቻ ነው...ኡፏ":: ተሽከርካሪ ወንበሯን ወደእኔ ስታዞረው የተራቆተ ቀኝ ታፋዋ ስለተቀመጠች በጣም ገዝፎ ታየኝ:: አይኔን ወደታች ስልክ ባለተረከዝ ጫማዋን እየወለወለች እንደነበር ገባኝ:: በእጇ፣ በቀይ ክር ሃረግ የተጠለፈበት የእማማ መለኮት መሃረብ በከፊል አቧራ ለብሶ...

# 22 የመደርደሪያው ጫፍ

"አብርሃም !"

"አቤት"

"ስምህ ማነው ?" አለኝ ፊቴ የተቀመጠው ደማ ፖሊስ፡፡ ፊቱን ሳየው ማፏጨት ጀምሮ መሐል ላይ ሲደርስ ሊያፏጭ የፈለገው ዜማ የጠፋበት ጎረምሳ ይመስላል፡፡ ስሜን ጠርቶ 'ስምህ ማነው?' ሲለኝ ቢገርመኝም በትህትና ተናገርኩ፡፡

"አብረሃም"

"አ...ብ...ር...ሃ...ም" ፊደል እየቆጠረ ፃፈ፡፡

"የአባትህ ስም" ነገርኩት - ጻፈ፡፡

"አብረሃም ! ለምንድነው የሰው ባል ጭካኔ በተሞላበት መንገድ በሚዛን ስህን የፈነከትከው?" አለኝ፡፡ አጠያየቁ 'ባትመልስልኝም ግድ የለም' የሚመስል ስሜት ነበረበት፡፡

"እረ ስላበሳጨኝ ነው እንጂ እኔ ሰው ጋር ተሰዳድቤ እንኳን አላውቅም፤ እንኳን በጭካኔ..." ዓረፍተ ነገሬ እየተወለጋገደ መለስኩ፡፡

"እሱማ ታስታውቃለህ፡፡ ጨዋ ልጅ ነህ፡፡ ጨዋ ባትሆን ኖሮ ሰሀኑ ላይ የተቀመጠውን አንድ ኪሎ መመዘኛ ብረት ትተህ በሰሃኑ ብቻ አትፈነክተውም ነበር፡፡ ጎበዝ ! ራስህን መግዛትህ ትልቅ ነገር ነው፡፡ 'ራሱን የሚገዛ አገር ከሚገዛ ይበልጣል' ይባላል፡፡ ቢሆንም ግን አብረሃም ዋስ ትጠራለህ፡፡"

"እሺ !" አልኩና ትዝ ሲለኝ የሚዋስ ሰው የለኝም፡፡

"እንካ ደውልና ጥራ !" ብሎ ቅድም ወደ ማረፊያ ቤት ስገባ የተቀበለኝን ስልኬን ወደ ፊቴ ገፋልኝ::

ወደ አእምሮዬ የመጣችው ሂሉ ነበረች:: ግን ሀሳቡ በራሱ ሳቁን አመጣብኝና ተውኩት:: ባሏን ፈንክቼ ሚስቱን ዋስ ሁነኝ ማለት በእርግጥ ያስቃል:: ዝም ብዬ ዋስ የሚሆነኝ ሰው ሳወጣና ሳወርድ ቆየሁና "ዋስ የለኝም !" አልኩት ለደጉ ፖሊስ::

"እንዴት ዋስ አይኖርህም? ከሰው አልተወለድክም...? ጓደኛ የለህም? ወይም ጎረቤት ?" አለ ፖሊሱ:: እንዲህ ሲለኝ ዘመድም ጓደኛም የምለው ሰው እንደሌለኝ ትዝ አለኝና እንባዬ በዐይኔ ግጥም አለ::

"ደህና እስቲ የአንድ ሰው ስም ንገረኝ!" አለ ለመፃፍ እየተመቻቸ::

"የአንድ ሰው ማለት?"

"በቃ ዝም ብለህ የአንድ ሰው ስም ንገረኝ!" አለ::

"አበራ !" ማረፊያ ቤቷ ውስጥ 'አበራ አንበሳው !' የሚል ስም በተወለጋገደ የእጅ ጽሁፍ አይቼ ስለነበር አፌ ላይ ድንገት መጣልኝ::

"የአባቱ ስም ማነው ?"

"አኔ ንጃ !" ተግርሞ አየኝና ፈገግ ብሎ አጉተመተመ::

"በቃ 'አበራ በለጠ' ብዬዋለሁ - ዋስህ ነው:: አብረሃም አምንሃለሁ፤ ጥሩ ልጅ ነህ፤ ይሄ መቼም የዕለት ግጭት ነው:: ከአሁን በኋላ እዛ ሱቅ አካባቢ ብትደርስ ግን ዋስህን እቀፈድደዋለሁ፤ ንግሬያለሁ!" አለ እየሳቀ::

እዚች ምድር ላይ ይኑር አይኑር በማይታወቅ ዋስ ከእስር የወጣሁ ሚስኪን ሰው፣ ቀበቶዬን ተቀብዬ ከታጠቅኩ በኋላ ወደ ቤቴ አዘገምኩ:: ፖሊሱ ያሳየኝ እምነት በጣም ነው የገረመኝ:: ለምን እንደሆነ ባላውቅም ሰው ከመሬት ተነስቶ ያምነኛል:: ሌባ ብሆን መቼም ባንዴ ሃብታም ነበር የምሆነው፤ ሰዎች እንዲያምኑህ እና እንዲዘናጉ ማድረግ ትልቁ የሌብነት ጥበብ ነውና::

ሰፈሬ ስደርስ ወደ ሀሊና ሱቅ መንገድ ጀመርኩና ትዝ ሲለኝ ደንግጬ መንገዴን ቀየርኩ:: ሱቁ አካባቢ እንዳልደርስ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶኛል:: ወይኔ ከሁሉም ከሁሉም ሀሊናን ሳላይ መዋል እንዴት ያስጠላል?! ሀሊናን እንዳላይ በህግ ተከልክያለሁ:: ያ ፖሊስ በሕግ አላስፈራራኝም፤ ሕጉን ነው አዕምሮዬ ውስጥ ተክሎ በፍቅር ያጠረው::

ሂሉ እስካሁን በዱቄት የተበከለ ጋውኗን ለብሳ ፊቷ በሚነድ ሻማ የሆነ ነገር እያደረገች ይሆናል፤

ወይም የለስላሳ ሳጥን ላይ ቆማ እንደ ነብር ሽንቧ ተመዞ የላይኞቹ መደርደሪያዎች ላይ ሳሙና እየደረደረች ይሆናል፡፡ ስትንጠራራ እኮ ስታምር! ሰማይ ላይ በተቀመጠ ገበታ በሚያማምሩ ጣቶቿ እግዜር ጋር ቼዝ የምትጫወት ነው የሚመስለኝ፡፡ ሂሉ የኔ ውብ ! የኔ ቆንጆ ! የግርማ ሚስት ! ሰው እንዴት ግርማን ያገባል በእግዚአብሔር...!

*** *** ***

ብቸኛ ነኝ ! ሁሉም ነገር የሰለቸኝ የሃያ ሰባት ዓመት ወጣት፡፡ ቤቴ እገባለሁ፤ እወጣለሁ፡፡ ሦስት ዓመት ሙሉ እዚህ ሰፈር ስኖር የማውቃት ህሊናን ብቻ ነው፡፡ መንገዴ ላይ ሱቅ አላት፤ድምቅ ያለ ሱቅ፡፡ የሱቁ ድምቀት ህሊና ራሷ ሳትሆን አትቀርም፡፡

ህሊና ጨዋ ሴት ነበረች፡፡ እኔም ጨዋ ልጅ ነበርኩኝ፡፡ የህሊና ባል ግን ጨዋ ስላልነበረ ሊያሳስተን ሞከረ፡፡ ይሄ አባላች ደስ ይበለው፤ ተሳክቶለት ተሳሳትን፡፡ በዕርግጥ ስህተታችን ጣፋጭ ነበር፡፡

ለሚስቱ ሱቅ ከፍቶ ወንድ ደንበኛ በመጣ ቁጥር ዐይትን ማጉረጥረጥ ተገቢ ነው? ገበያተኛ በመጣ ቁጥር የሚስቱን ፈገግታ መለካት እና ማታ ማታ በልክ ፈገግ በይ እያለ መነትረክ እግዜር ይወደዋል? እሽ ይሄ ይሁን ግዴለም...ግን 'አብረሃም የሚባል ልጅ እዚህ ሱቅ ለምን ይመጣል ለሞላ ሱቅ?!" ብሎ መጠየቅ ከአንድ ባለ ሱቅ ይጠበቃል? ...መንግስት ሳያዳላ ሕዝብ እንዲያገለግልበት በሰጠው ንግድ ፈቃድ እከሌ ይምጣ እከሌ ይሂድ ብሎ ሰው ይመርጣል? እሺ (ሂሂሂሂ...ኧረ ይሄስ ያሳፍራል) ግን ሚስቱ ጋር፣ ቆንጆዬ ሚስቱ ጋር እቅፍቅፍ ብሎ ከመተቃቀፍም አልፎ መርፌና ክር ሆነው ሌላ ዓለም ውስጥ ሲዋኙ ድንገት የማይቋረጥ ነገር አቋርጦ፣ "ለምንድን ነው አብረሃም ቲማቲም የሚገዛው? ማን ሊያበስልለት?" ብሎ ሚስቱን ይጠይቃል፣ እንዲህ ይደረጋል ?

ሂሉዬ ብስጭት ብላ "ራሱ ይሰራላ" ስትለው፡ "ራሱ እንደሚሰራ በምን አወቅሽ ?" ይባላል ? ለጥያቄና መልስ ይሄ ቦታው ነው ? ሰዓቱስ ነው ?

ባሏ ቀልቡ አይወደኝም፣ አቀፈዋለሁ፡፡ እኔ ሱቁ በር ላይ ስቆም ዐይኔን ላለማየት የማያየው ነገር የለም፡፡ የተደረደረውን ሳሙና፣ የተሰቀለውን ሙዝ፡ የተለጠፈውን 'ዱቤ ክልክል ነው' የሚል ማስታወቂያ...ብቻ ማየት የቻለውን ሁሉ ፊቱን አጨፍግጎ ይቃኛል፡፡ እናቴን ሊፈነክተኝ ፈልጎ ደህና መፈንከቻ ያጣ ነው የሚመስለው፡፡ በዛ ላይ ሆን ብሎ ህሊናን በወሬ ያጨናንቃታል፡፡ እንዳናወራ መከላከሉ እኮ ነው፡፡

"እጃከስ አለቀ እንዴ ?" ይላታል፤

"ኧረ አለ!"

"ለስላሳ ዛሬ አላወረድሽም ?"

"ገና ትላንት እኮ ነው ያወረድኩት !"

በቃ የማይቀባጥረው ነገር የለም::

እንግዲህ ስገባና ስወጣ ሰላም የምላት ብቸኛ ሴት ባለ ሱቁ ህሊና ነች:: ሱቋ መንገዴ ላይ ስለሆነች አስቤዛዬም የሚሸመተው ከሷው ነው:: ታዲያ ህሊና ጥሩ ልጅ ስለሆነች ነው መሰል ከደንበኝነት ከፍ ያለ ቅርርብ ነው ያለን::

ዛሬም ልክ ደመወዝ እንደተቀበልኩ ሄድኩ፤ ባሏ የለም:: ሁለታችንም ደስ አለን::

"አንተ!" ትለኛለች፤

በቃ ስሜን ጠርታኝ አታውቅም:: 'አንተ' ነው የምትለኝ:: እውነቱን ለመናገር ህሊና 'አንተ' ስትለኝ ስሜን ያቀናጣችው ነው የሚመስለኝ:: አብርሃም ሲቀናጣ 'አንቱ' ! በእኔ ጆሮ ብትሰሙት በጣም ይገጣጠማል !!

"ሰላም ሂሉ!" ባሏ ከሌለ ሂሉ ነው የምላት፤ በእርግጥ አንዳንዴ እሱም እያለ ያመልጠኛል::

"ምን ሆንህ ነው ዐይንህ የቦዘዘው?" ትላለች በትልልቅ ዐይኗ እያየችኝ:: ዐይኖቿ ዐይኔን ይስሙኛል::

"ዱቤ ልከፍል ስለሆነ ይሆናላ !"

በዚህ ሁኔታ መቀለድ መቻሌ ግዴላችሁም ብርቱ ሰው ብሆን ነው!

"ሂሂሂሂሂሂሂ...ውይ አታስቀኝ ከምሬ ነው!" ትላለች፤ ስቃ ከወጣላት በኋላ እኮ ነው:: ከዛም የወሩ አዳዬን እንተሳሰባለን::

"ዱቤ ከልክል ነው!" ከሚለው ጽሑፍ ስር ያስቀመጠችውን የዱቤ መጻፊያ ደብተር ታወጣና ቁልቁል በአስከርቢቶዋ እየጠቆመች "ካርድ የ100 ብር...ግን ሙቶ ብር ካርድ ምን ያደርግልሃል? ወሬ እንኳን አታበዛ" ትላለች፤

"ዳቦ...

ዳቦ

ዳቦ ...ሰነፍ ስለሆንክ እኮ ነው ዳቦ የምትበላው ! ...ብቻ እንጀትህ እንዳይደርቅ ፤ ምናለ እንደ ወንዶቹ እንቁላል እንኳን ብትጠብስ ?..." ትቀጥላለች::

"...የተፈጩ ቡና...!

ሻይ ቅጠል...!

ኮካ !

እምቦ ውሃ ሂሂሂሂሂሂሂሂ እስኪ. ሰው ዳቦ እየበላ እምቦ ውሃ ሆሆ" ስትስቅ ደስ ስለምትለኝ ዝም ብዬ እያታለሁ፣ ሲታምር !

"እ...እ...እና አንድ ሊትሯን ውሃ በድምሩ...መቶ ሰላሳ ሁለት ብር"

"እምሳ ብሩን ረስተሻል !" እላታለሁ::

"የምን ሃምሳ ብር?" ትለኛለች::

"አንድ ቀን ተበድሬሽ ሌታከሲ እንኳ..."

"እላስታውስም"

"እኔ አስታውሳለሁ" እላትና ሁለት መቶ ብር እዘረጋላታለሁ:: አንዱን ብቻ አንስታ አንዱን እጄ ላይ ትተወዋለች::

"ብር አለህ ግን?" ትለኛለች፤ደግሞ ከልቧ መሆኑን ዐይኗ ያስታውቃል::

"ዛሬማ ሃብታም ነኝ"

"ያንተ ሀብታምነት እንደሁ እድሜው ሦስት ቀን ነው" ታየኛለች፤ በዐይኗ የነካችኝ ነው የሚመስለኝ::

እእምሮዬ ባለትዳር መሆኗን እንዳያምን ጣቷን ሳለማየት እጥራለሁ:: የሆነች ለስላሳ ነገር ነች፤ እንገቷን በዐይኔ ስነካው ይለሰልሰኛል:: ባሏ ግርማ ሲያቅፋት የሚኮሰኩሳት ነው የሚመስለኝ፣ የሆነ ሰውነቷ የሚንደበደብ::

ሂሉን ሱቅ ውስጥ ቆማ ሳያት መደርደሪያው ሁሉ የተሞላው በፍቅር ይመስለኛል:: ማነሽ ሁሉንም በጅምላ ገዝቼዋለሁ፤ ከነመደርደሪያው፣ ከነሚዛኑ፣ ከነመዛኟ !!

በትልቅ ጥቁር ፊስታል ቋጥሮ እእንም እዛው ውስጥ መጨመር፤ ወደ ውጭ ማየት የለ፣ ወደ ውስጥ የሚመለከት የሌ፤ እርፍ !

ኤጭጭ! ከኋላዬ ጥላው ሲከብደኝ ታወቀኝ...ግርማ መጣ...፤ ባሏ መጣ ! የተደገፍኩትን መደርደሪ ከፍቶ ሲገባ ወድቄ ነበር::

"ይቅርታ ልገባ ነው አይባልም ?" ሂሉ በባሷ ብልግና ስትሳቀቅ ይታወቀኛል:: ይሄ ውሻ የሆነ ሰው!...ቢቃ የሂሉም ፊት ኮስተር የእኔም ፊት ኮስተር !! መደርደሪያው ይንኳተትብኛል:: ማካሮኒ፣ ፓስታ፣ ሳሙና፣ ምንትስ...ያ ሁሉ ፍቅር አልም ! ይሄ ስሐራ ባሏ ሲገባ ፍቅር ይተናል::

በለፈው ከስራ ወጥቼ ወደ ቤቴ አዘግማለሁ:: ድከም ብሎኝ ስለነበር ሂሉን ረስቻት ነበር:: ልክ በሱቋ ሳልፍ "አንተ" ብላ ጮኸች:: የሂሉን ድምፅ ሲሰሙ ድካም፣ ድንዛዜ ሁሉ ጠጠር እንደተወረወረበት የወፍ መንጋ 'እኔ' ከምባል ዛፋቸው ላይ ግርር ብለው ሲበሩ ታወቀኝ::ከንፈሬ ላላዘው ግራና ቀኝ ሸሸ፤ ፈገግ አልኩ:: እናም ወደ ሱቋ ሄደኩ፤ ከድካሜ ብዛት ደረጃውን ለወጣ ገድገድ ብዬ ነበር::

"እኔን!" አለች ሂሉ፤

ሱቁ ላይ ስደርስ ግርማ ተቀምጧል:: ድካሞቼ ሁሉ ተጠራርተው ድብርትን ጨምረው ሰፈሩብኝ፤"ሰላም ዋላችሁ!" አልኩ፤

"እግዚያብሄር ይመስገን!" አለች ሂሉ፣ እግዜር ቀኑን የሰጠው ለሷ ብቻ ይመስል:: ያ ጋግርታም ባሏ ዘጋኝ! ይዝጋው !

ምን እንደማወራ ጠፍቶብኝ እንዴ መደርደሪያው ላይ ያሉትን እቃዎች፣ እንዴ ሂሉን ስቃኝ ቆየሁና..."ሳሙና ስጭኝ!" አልኩ:: ሂሉ ሳቋ መጥቷል፤ ድንገት እንደዘባረቅኩ አውቃለች:: ቢሆንም ከመጨረሻው መደርደሪያ ላይ ልታወርድ የለሰላሳ ሳጥኑን አስጠጋችና ጫማዋን አውልቃ ኩርሲዋ ላይ ቆመች:: እግሯ እንዴት ነው የሚያምረው ! ተረከዟ ነጣ ብሏል፤ ተንጠራራች፤ ተመዘዘ ሽንጧ ....!

'ሽንጧ የሚመስለው...የምንትስ ሃረግ..." እያልኩ በሃሳቤ ስዘፍን እና ምራቄን ስውጥ ቆይቼ ዞር ስል ግርማ ዐይኑ ቀልቶ እኔ ላይ አፍጥጧል:: "ነብር አየኝ በል!" አይነት ዛቻ ቀመስ ዕይታ...! የሚጮህ ዐይን ያየሁት ግርማ ላይ ነው:: ዐይኔን ከዚህ ፈጣጣ ላይ ነቅዬ በጥግ በኩል ስልክ የከንዶም ካርቶኑ ላይ አረፈ:: የግርማም ዐይን ዐይኔን ተከትሎ ይሁን ወይም የዐይኑ እግር ጥሎት እዛው ላይ አረፈ፤ ወይም ያረፈ መሰለኝ::

ሂሉ የቆመችበት ኩርሲ ነቅነቅ ሲል "እኔን!" ብዬ በድንጋጤ ጮህኩ፤ አደነጋገጤ ለራሴም ገርሞኛል:: ውሃ ጠገብ ባሷ ምንም ያልመሰለውን እኔን ምን ቆርጦኝ ነው የደነገጥኩት? ምን አስበረገገኝ? "የምጣዱ ሳለ የእንቅቡ ተንጣጣ" አሉ! እንደውም የግርማ አስተያየት 'ምነው ቢፈረጥሽ!' የሚል ያስመስልበታል::

ሳሙናዬን ተቀብዬ ወደ ቤቴ አዘገምኩ:: በቀጣዩ ቀን ቅዳሜ ሂሉ እንባዋ ጠብ እስኪል እየሳቀች ሳሙናውን ገዝቼ ከሄድኩ በኋላ ከግርማ ጋር የተባባሉትን እንዲህ ስትል ነገረችኝ:: እወራሯ

ድራማ ነው የሚመስለኝ፡፡ ሂሉ ሲበዛ ነፃ ነች፡፡

"አንተ !" በሳቅ ፍርስርስ አለች፤

"ምን ያስቅሻል?"

"አይውልህማ...ብታይ...ትላንት ሳሙና ስጭኝ ስትለኝ ሰጥቼህ (ረዥም ሳቅ )...ሰጥቼህ... ከሄድክ በኋላ ግርምሽ ብስጭት ብሎ ሲነዘንዘኝ አላመሽ መሰለህ! ሆሆ!!"

"ምን እነዛነዘው ?"

ነገረችኝ፤ ልክ እኔ እንደወጣሁ ግርማ ሂሉን ጠየቃት፣

"...እኔ የምልሽ! አብረሃም 'ሳሙና ስጭኝ' ነው ያለሽ አይደለም እንዴ?"

"እዎ! እና እኔስ ሌላ ምን ሰጠሁት?"

"ምን እንደሰጠሽውማ አንችው ታውቂያለሽ"

"እንዴ! ግርምሽ ምን ማለትህ ነው?"

"የሳሙናውን ዓይነት አልተናገረም፡፡ እንዴት ዘለሽ እዛ ትንጠላጠያለሽ? እዚህ የገላ ሳሙና አለ፤ እዛጋ እጃክስ አለ፤ አ...ላርጎ ፈሳሽ ሳሙና አለ፤ ምን እንደፈለገ በምን አወቅሽ ?"

ሂሉ ደነገጠች፡፡ ቢሆንም ኮስተር ብላ መለሰችለት፡፡

"ሁልጊዜ የሚወስደው ይሄንን ነዋ!"

"እስኪ እሱን የዱቤ ደብተር አቀብይኝ" አለ፤ አቀበለችው፡፡ የወሰድኩትን ዝርዝር አየና "የቃለ ሳሙና ወስዶ የሚያውቀው?" አላት በብስጭት፡፡

"እየከፈለ ነው የሚወስደው"

"ያሁትን መቼ ከፈለ ?"

"ኤጭ እንግዲህ አትጨቅጭቀኝ ! ወይ 'ሱቋን ዝጊና ቤት ተቀመጪ!' በለኝ" አለች ብስጭት ብላ፤

በዱቤ ደብተሩ ወርውሮ ሳታት፡፡ ከፀያፍ ስድብ ጋር "ሸርሙጣ!"

ይህን ስትነግረኝ ሁለታችንም ከልባችን ሳቅን፡፡ ሲቃ ስቃ ሲወጣላት "አንተ ምናለብህ ላንተ

"ሰውነትህ በሰላም ሰጥ ትላለህ፤ የሰው ትዳር እየበጠበጥክ" ልክ ስሰሌላ ሰው ትዳር የምታወራ ነገር የምትመስለው፡፡

ባሏ ግርማ ከሌለ ወሬያችን መቆሚያ የለውም፡፡ እንደማልወደው ታውቃለች፡፡ እሱም እንደማይወደኝ ታውቃለች፡፡ ይሄ ነገር ሳያስቃት አይቀርም፡፡ "ሰው ከመሬት ተነስቶ ይጠማመዳል ? ሃሆ !!" ትላለች፡፡ ከዛም ልክ የመጀመሪያው ወሬ አካል አስኪመስለኝ ሌላ ርዕስ ውስጥ ትገባለች፡፡

"አንተ...ለች ሸሚዝ አሁንም አለች?" አለችኝ ድንገት የለበስኳትን ሸሚዝ በግርምት እየተመለከተች፡፡

"አዎ የት ትሄዳለች ?"

"መጀመሪያ ቀን እዚህ ሱቅ ስትመጣ እችን ነበር የለበስከው...ፀጉርህ ጨብረር ብሎ እዚች ጋ ቆመህ...ወረፋ ነበር፣ ሰው ሁሉ ኢያለፈህ ገዝቶ ሲሄድ አንተ ዝም ብለህ ቆመህ...ሂሂሂሂ...ሌባ መሰለኸኝ፣ ስልኬን አንስቼ መሳቢያዬ ውስጥ አስቀመጥኩት..ሃሃሃሃ...ከዛ በአንድ ዐይኔ አንተን እያየሁ፣ በአንድ ፀይኔ ደንበኞቼን ሳስተናግድ ነበር፡፡...ሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃ !" አወራሯ ያስቃል፡፡ 'ሌባ ትመስላለህ' ኢያለች እንኳን ታስቀኛለች፡፡...ደግሞ የሚገርመኝ አሳሳቋ 'ሳቁ እንዳይቀር' ዓይነት ግብግብ ነው በቃ !

"...ግርምሽም ሌባ ነበር የምትመስለው...አሁንም ሐሳቡን የቀየረ አይመስለኝም፡፡ ሂሂሂሂሂሂሂሂሂሂሂሂሂ..." ሁለተኛዋን አረፍተ ነገር ስራዬ ብላ እኔን ለማብሸቅ የጨመረቻት ብትሆንም አያውቅኩም ተበሳጨሁ፡፡

"እናትክን በይው እሺ!"

"ሃሃሃሃ አንተ ባለጌ ሰድ...ባሌ እኮ ነው! ሂሂሂሂሂሂ...»

"እኮ ባልሽን እናትክን በይው ! ...ማታ እቅፍ አድርገሽ ጉንጩን እየሳምሽ ! መቼም ይሄ ማቀፍም መሳምም አይገባው...'የኔ ቆንጆ አብርሃም እናትክን ብሎሃል አሽ !' በይው"

"ሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃ" የሚያልፈው ሰው እየዞረ እስኪመለከት ሳቋን ለቀቀችው፤ እየሳቀች አንገቷዋ ሲፈስ ገርሞኝ ነበር፡፡ በቀጥታ እየሳቀች ማልቀስ መጀመሯን ያወቅኩት ወዲያው ነበር፡፡

"እንዴት እንደመረረኝ!" አለችኝ፡፡ ደነገጥኩ፡፡ ብሶቷን ዘረገፈችው፡፡

የሐረር ልጅ ናት፡፡ ዘጠነኛ ክፍል እያለች ይሄ ያሁኑ ባሏ ግርማ ወታደር ሆኖ ሰፈራቸው የነበረ ካምፕ ውስጥ ይኖር ነበር፡፡ ያኔ ተማሪዋች፣ ወንዳወንድ፣ በቃ የሚፈቀር ሰው ነበር፡፡ ለጓደኝነት ሲጠይቃት አላንገራገረችም፡፡ "ይገፎሽ ልጥፉ!" ሲላት አምናዋለች፡፡ ካለ እናት ያሳደጋትን አንድ

ገባች:: እናቱ፣ እህቶቹ፣ ወንድሞቹ
አባቷን ጣጥላ ይሄን መጾሻ ራስ ተከትላ አዲስ አበባ ... በትዳሯ እየገቡ መፈትፈት ጀመሩ:: ነፃ መሆኗን
ሳይቀሩ አተከኗት:: በጉብረት ያገቧት ይመስል በትዳሯ እየገቡ ... እንደ አዲሳባ ሰው በሯንም
አለሴነት፣ ሳቋን የሸርሙጥና ደውል አድርገው ዐይንሽን ላፈር አሏት፣ ብትለውም አልሆነላትም::
ጥርሷንም በልኩ መክፈት ያላደገባትን:: ሚስኪን ! ልለማመድህ ብትለውም አልሆነላትም::

"እጭጭ አበ እንደፈለጉ ይሁኑ!" ብላ ሳቋንም ነፃነቷንም ተያያዘችው:: ይባስ ብሎ ሳቋ ማርከት
እንዳልወደዳት "ሳቅሽን አቁሚ!" አላትና አረፈው!! ብዙ ባሎች የባል ድንበሩ የት ድረስ እንደሆነ
አያውቁም:: ትንሽ ባሎች ደግሞ ድንበራቸው ላይ ሳይደርሱ ይቆማሉ::

እባቷ እሷን ፍለጋ ተንከራትቶ ተንከራትቶ ሲሞት አፈር አላለበሰችውም:: የሐረር ሰው ውሎ
ይግባ አልቅሶ ቀበረው:: በምድር ላይ የነበራት አንድ መሸሻ ዋሻ ተደፈነ:: አሁን ግርማ መድረሻ
የሴላት ከንፏ የተሰበረ ወፍ አደረጋት:: "በየመንገዱ ስታገጭ ነው ያገኘሁሽ" አላት ፤ እንደ
ሚስት ሳይሆን እንደ ሰራተኛ ክፍ ዝቅ አድርጎ ያዝዛት ጀመረ:: ያኔ ካስቀመጠባት መንበር ጎትቶ
አወረዳት:: ለሴት ልጅ ትልቁ ከብሯ ቤተሰቧ መሆኑን አመነች:: ለምን አፈር ጠርጎ የሚተኛ
ደሃ አይሆንም ቤተሰብ አለኝታ ነው ! ፍቅር ይወጣል፣ ይጠልቃል:: አዎ ! የሰው ፍቅር እንደ
ፀሐይ ምስራቅና ምዕራብ አለው:: እየጣፈጠ ወጥቶ፣ እያቃጠለ ይጠልቃል! ቤተሰብ ግን ሰማይ
ነው:: የሕይወት ፀሐይና ጨረቃ ሲፈራረቅ የማይቀያየር፣ የማይጠልቅ፣ የማይጠቀለል በታውንም
የማይቀይር ሰፊ ሰማይ ማለት ቤተሰብ ነው:: ሂሱ ቤተሰብ የላትም:: ሰማይ የለም:: ቀጥ ስትል
እና ነው - ባዶ ነው ! ኮከብ የለም፣ ጨረቃ የለችም፣ ፀሐይም የለችም:: ሰማይ በሌለበት
ምንም የለም:: እግዜር የት ይሆን መቀመጫው ? የት ሆኖ ይሆን ይህን ጉድ የሚመለከተው?!

የአዲስ አበባ ኑሮ አንገሸገሻት:: ለምሬቷ ጣዕም ኮሶ የጨመረው ባሏ ነው:: "ታምናለህ... ከሳመኝ
ስንት ጊዜው !" አለችኝ:: "ግን እወደዋለሁ ! ስድቡ፣ ማቃለሉ እያቃጠለኝ እንኳን እወደዋለሁ !"

"ሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃ አንተ አስለፈለፍከኝ !" አለችና ሳቋን ለቀቀችው:: የኔ ሚስኪን !!

ባለፈው ሐሙስ ደግሞ ሂሱ ወደኔ ጠጋ ብላ ፊት ለፊቴ ቆመች::መሐላችን ላይ ሚዛኑ አለ::
ፊቷ ልክ አልነበረም:: ቶሎ እንድሄድላት መፈለጓ በግልፅ ያስታውቃል::
አንድ ትንሽ ልጅ መጥቶ "ሳሙና ስጪኝ ! ቢጫውን" አላት፤
"የለም !" አለች፣ ግን ፊት ለፊት ተደርድሮ ነበር::
ሌላ ሴት መጣችና "ስኳር ስጪኝ ሕሊና" አለቻት::
"የለም !" ፊት ለፊት ኩንታል ስኳር ተቀምጧል:: ግርምኝ ጠየቅኳት::
"ሂሂሂ...አንተ ካልሄድክልኝ በስተቀር ምንም ነገር አልሸጥም ዛሬ" እየቀለደች መሰሎኝ ነበር::
"ማሪያምን !" ስትለኝ የላጥቶኑ ቦርሳዬን አንስቼ፣ "በይ ቻው !" አልኳት::
"ቻው አብርሽ !" አለችኝ በቅሬታ ፈገግታ:: "አብርሽ" ብላኝ አታውቅም፣ ግራ ገባኝ::

በቀጣዩ ቀን ሂሉ የለችም ነበር፤ ባሏ ተገትሯል::

“ሰላም ግርማ”

“ምን ልስጥህ?” አለኝ ኮስተር ብሎ፤

“ሻሂ”

“የለም”

“እሺ ቀዝቃዛ ስፕራይት አድርገው”

“የለም”

“ትንሿን ውሃ ስጠኝ እሺ !” ውሃውን ሊሰጠኝ ዘወር ሲል ፊት ለፊት ሰማያዊ መደብ ላይ በነጭ የተጻፈ ማስታወቂያ መለጠፉን ተመለከትኩ:: “የኔ ብጤና ዱቤ ፈላጊ እግዜር ይስጥልን” ይላል:: የብልግና ጥግ !! ሂሉዬ ይሄን ለመጋረድ ነበር ትላንት ፊቴ እንደ ጨው አምድ ተገትራ የነበረው::

“ይሄን ብትገነጥይ እገነጥልሻለሁ” ብሎ ፎከረባት:: ግርማ እንደለጠፈው ቆይቶ ሰማሁ:: እኔን ለማኝ! ለማለት ፒያሳ ሂዶ ማስታወቂያ ያጽፋል !?...ጓጉንቸር!!

ሀሊና ከሰዓት ኋላ በስካርቭ ሸፍና ቆማ አገኘኋት::

“ምነው ሂሉ?”

“ትንሽ ጥርሴን አሞኝ !” ፊቷ ሞቶ ነበር:: ዐይኖቿ ባዶ ቀሮ፤ አንድ የሕይወት ምዕራፍ በሆነ ምክንያት የተዘጋ አይነት:: ሀሊና የትላንቷ አልነበረችም:: ባላወቅኩት ምክንያት ተቆጣሁ::

“እስኪ ስካርቭሽን አንሺው” አልኳት::

“ሂድ ቤቃ አብርሽ !” ብላ እንባዋ ተዘረገፈ:: ከዛ በኋላ ሀሊናን ለአንድ ሳምንት አላየኋትም:: ለሁለት ለሦስት...ለስድስት ወር !!

ከአንድ ሳምንት በኋላ ወደ ሱቁ ስሄድ ግርማ ከአንዲት የማልወዳት ሴት ጋር ቆሞ እያወራ ነበር:: በንቀት እያየኝ፡ “አሁን ደግሞ ምን ቀረህ? ከሚስቴ ጋር አጣላኸን !” አለኝ:: ዞር ብዬ ሌላ ሰው መኖሩን ተመለከትኩ፤ እኔን አልመሰለኝም ነበር::

“አንተን ነው ባክህ ምን ታስመስላለህ!” አለኝ እያመናጨቀ:: አንዲት የሀሊናን እግር መጡጣት ተከትላ ግርማን እንደ ጭልፊት ለመንጠቅ ያሰበች የምትመስል ማዲያታም ሴት “ሆሆ...የልብን ስርቆ እንደገና ዐይንን በጨው አጥቦ መምጣት አለ እንዴ?” አለች:: ይህቺ ሴት ካሁንም በፊት ለኔና ሀሊናን ስትመለከት ሀይና ደም የሚለብስ፤ በተሳሳቅን ቁጥር በርሷ እየመሰላት የምትመናቀር፤

ለግርማም ነገር የምታመላልስ ነገረኛ ነበረች፡፡

"በሰላም ነው?" አልኩት፡፡

"ወደዛ ሂድ ባክህ ! ሁለተኛ ሱቁ በር እንዳትደርስ፡፡ እዚህ አካባቢ ባይህ ጥርስህን ነው የማራግፈው!" አለ እያመናጨቀኝ፡፡ አሁን ዩኒፎርሙ ብቻ ሲቀር ወታደርነቱ ተመለሰበት፡፡ አብራው ያለችው ሴት "ግርምዬ በእመቤቴ ተረጋጋ ! የማይረባ ሰው ጋር አትጋጭ ! እጅህ ላይ አንድ ነገር ይሆንብሃል !" አለች፡፡

እንዲህ ስትለው ጭራሽ ለያዥ ለገናዥ አስቸግሮ ቱጭ አለ፡፡ እውነቱን ለመናገር ግርማንም ሆነ ሴትዮዋን ከቁም ነገር አልፃፍኳቸውም፡፡ እንደው ነገሩ ገረመኝ እንጂ !

"አንተ ልክስክስ የሸርሙጣ ልጅ !" ብሎኝ ቁጭ ! ቀኝ እጁን ጌታ ይባርከው !! ከቁጥጥሬ ውጭ ተወንጭፎ ግርማ ጉንጭ ላይ በብርሃን ፍጥነት ሲያርፍ ከመደርደሪያው ስር ተንገዳግዶ ወደቀና ወዲያው እፈፍ ብሎ ተነሳ፡፡ ፊት ለፊቴ የነበረውን የሚዛን ሰሀን አነሳሁት፡፡ በአንድ በኩል አንድ ኪሎ ግራም ብረት ነበር፡፡ እኔ ግን ሰሀኑን እንስቼ በቀጥታ ግርማ ግንባር ላይ በጠርዙ በኩል አሳረፍኩት፡፡ ባባቴ ወንድ ነኝ፡፡

አልወጣልኝም፡፡ እሪታዋን የምታቀልጠውን አቃጣሪ በጥፊ አቃጠልኳት! ከዛ አገር ምድሩ ተሰብስቦ ገላጋይ ሆነ፡፡ ግርማ ደሙን እያዘራ ይፎክራል፡፡ ወደፊት "ደሜን አፍስሼ ባቋምኩት ሱቅ" እያለ ታሪክ ያዛባ ይሆናል፤ ይሄ የማይረባ ! ታሰርኩ፡፡ እናም ደግ ፖሊስ ገጥሞኝ ተፈታሁ፤ "ሂሉ ጋ እንዳትደርስ!" ብባልም ከዛ በኋላ እሷም ራሷ እንደጠፋች ሰማሁ፡፡ ስልክ እንኳን አልነበራትም - ሂሉ፡፡ ከዛ ሰፈር ቤት የቀየርኩበት ምክንያት ያንን የመቃብር ቦታ የመሰለ ሱቅ ላለማየት ነበር፡፡

አንድ ምሽት ከስድስት ወር ይሁን ሰባት ወር በኋላ ስልኬ ሲጮህ አነሳሁት፡፡

"አንተ!"

ዝም...! ደንግጬ ነበር፡፡

"ኢብርሽ !"

"ሂሉ !"

"ሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃ...ተኝተህ ነው ? እንቅልፋም !" ልክ ትላንት የተገናኘን ነበር የሚመስለው አነጋገሯ፡፡ ልታገኘኝ ቀጠረችኝ፡፡ ነገ ቅዳሜ ነው፤ እንኳን የሂሉ ቀጠሮ ተጨምሮበት !

ሂሉዬ አምሮባታል፤ ለወራት፡፡

ቀሀን ጊዜ ግርማ የሚያስጠላ ማስታወቂያ ለጥፎ እንዳትገነጥይ አለኝ፤ እኔ ግን በብስጭት ገንጥዬ ለጥፌው በቦክስ ጥርሴን መታኝ:: ሰማይ ምድሩ ዞሮ የዞረብኝ:: እኔን "ገልምጫ የሚበቃኝ ሂሂሂሂ!" አለች:: በጣቷ ነጭ ጥርሷቿ መሐል በግራ በኩል የተነቃች ሰው ሰራሽ ጥርስ እያሳየችኝ:: እንጋገሯ ልብ ይሰብር ነበር፤ ኢጋዥ የሌለው አቅመቢስ ሰው ዓይነት:: "ብቃ ስካርፍ አድርጌ ያየኸኝ ቀን ማታ በሚኒባስ ተሳፍሬ ወደ ሐረር...ሃሃሃሃሃሃሃሃ" ትንሽ እንደ መተከዝ አለች::

"አባቴ ሲሞት ሐረርም የሞተች መስሎኝ ነበር:: ጓዋደኞቼ፣ የአባቴ ጓደኞች፣ ጎረቤቱ እንደ አዲስ ለቅሶ ተቀምጦ የአባቴን ሞት አዲስ አደረገው:: 'አይዞሽ!' አሉኝ:: ሰው ሁሉ የአባቴን ሞት ያፅናኑ መስሏቸው እኔን ከሞት ቀሰቀሱኝ:: ሐረር ፍቅር ናት ! ሰው ሰው ይሸታሉ ሰዎቹ..." እንባዋና የደስታ ፈገግታዋ ተቀላቀለ:: ሰው በሰው ሲረካ እንደዛን ቀን ተመልክቼ አላውቅም::

"ሂሉ አቤትትትትትት እንዴት ስወድሽ እንደነበር እኮ !" አልኳት::

"አንተ...አንድ ጥርስ አለብህ ላንተ የከፈልኩት ሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃ"

እየተንጠራራን ነበር ከሕይወት መደርደሪያ ላይ አስከፊ ትላንታችንን የምናጥብበት ሳሙና ልናወርድ !!

"ሂሉ ባልሽን በሚዛን ፈነከትኩት እኮ..." አልኳት:: እኒጋገሬ "ተበቀልኩልሽ" ይሁን፣ አልያም "ጀግና ነኝ" ማለት ለራሴም አልገባኝ !!

"ሃሃሃሃሃሃሃ ሰማሁ እኮ...! አቦ ጌታ ይባርከህ...! ሃሃሃሃሃሃ ባሌ ነህ ግን...ገና ሰማኒያችን አልተቀደደም እኮ ! አሁን የመጣሁት ለዛ ነው..."

እየተንጠራራን ነበር:: ከአዲስ አበባ ሐረር፣ ከሐረር አዲስ አበባ መደርደሪያው ቢርቅም የቆምንበት የመፈላለግ ኩርሲ እንደምንም እያደራረሰን:: ሂሉዬ አዲስ አበባ ዘመድ የላትም:: እኔም ሐረር የማውቀው ሰው የለም:: ግ...ን እኔንም ሐረር ! ሂሉንም አዲስ አበባ ደጋግሞ ያስረገጠን ጉዳይ ምንድን ነው ? "ከምር ግን ምንድን ነው ?" የሚሉ ጠያቂዎች ቢከሰቱ መልሳችን አንድ ነው::

"...አቦ አትነዝንዙና !!"

# 23 አለሁላት...!!

እናቴ ሁልጊዜ ሁለት እጆቿን ወደ ሰማይ ዘርግታ እግዜርን እንዲህ ትለዋለች፣

"አብርሽዬ የሚያገባትን ሴት ሳታሳየኝ እንዳትገለኝ።"

.

.

አገባሁ !!

እናቴ ሁለት እጆቿን ወደ ሰማይ ዘርግታ እግዜርን እንዲህ አለችው፣

"ምነው ይቺንንስ ከሚያሳየኝ በገደለኝ..."

ሀና ምንተስኖት ትባላለች የምኮራባት ሚስቴ። እወዳታለሁ፣ አፈቅራታለሁ። ከቶ ነገር በሰፈሯ እንዲያልፍ አልፈልግም። ሀኒዬ የእኔ ጥሩ ሱስ፣ 'ካላየኋት ያዛጋኛል' ስል ሰዎች አያምኑኝም፤ ሀኒ የእኔ ልብ፣ የጠላችው ጠላቴ ነው። "ይሄ ኦባማ የሚባል ሰውዬ በቴሌቪዥን ያደረገው ንግግር አስጠላኝ" ብትለኝ፣ ሲ.አይ.ኤን ሳልፈራ፣ ኤፍ.ቢ.አይን ከቁብም ሳልቆጥረው ኦባማ ላይ የግድያ ሙከራ ባደርግ ደስታዬ ነው። አንቅ አድርጌ አይኑን አፍጥጦ፣ "ኧረ አብርሽ በእናትህ የዛሬን ማረኝ...ሁለተኛ በየትኛውም ሚዲያ ከመቅረቤ በፊት ንግግሬን ለሀና ምንተስኖት አሳውቃታለሁ... ካልፈቀደችልኝ አላደርገውም" ቢለኝ አልምረውም። እማምላከን አልምረውም !!

ሀናዬ የነብሴ ፍራሽ...ሳያት ድሎቴ ናት። ሀና ካዘዘችኝ...እቤት ፍጥነቴ 1 ገና ልትናገር ስትጀምር እኔ ሮጫለሁ። አልጋ ላይ ጋደም ብላ ቴሌቪዥን እያየች እኔ ቆንጆ ቡና እያፈላሁላት...የሆነ ነገር ብትፈልግ...ልትናገር ስትጀምረው ነገሩን አምጥቼዋለሁ ። ለምን ትጨርሰዋለች...ቃሏ ፍቅር ነው...ፊደሎቿ እንደ ረሀብ ቀን እህል ያሳሱኛል።

"አብርሽ..." ስትለኝ 'በቦታህ!' እንዳሉት ፎጭ እዘጋጃለሁ። ወደ መሻቷ ተፈትልኬ በምድር ላይ ያሉ ወንዶች ሁሉ የሚሰቶቻቸውን ፍላጎት ካሟሉበት ሰዓት የተሻለውን ለማስመዝገብ፣

'ድ-' ብላ ስትጀምር ፈትለክ ብዬ ድስት...ድራፍት...ድንች...ድልህ...ድፍድፍ (ከአማማ ፈጠኑ ቤት)...ድመት...ድንጋይ ...ድራማ (በሲዲ) ይገዙላት እያለከለኩ ከተፍ ስል፣ "ውይ አብርሽዬ...በቴቪ ድብ አይቶ 'ድቡን እየው' ልልህ ነበር እኮ" ትለኛለች በፍቅር ዓይን እያየችኝ...!! አይከፋኝም፣ ለምን እከፋለሁ:: እንደገና ድብ ባየችና 'ድ' ብላ ስትጀምር፣ አሁን ባመጣኋቸው ነገሮች ላይ ድብ ጨምሬ ባመጣሁላት...የእኔ ሀኒ...መከሊት ብያታለሁ:: እሷ ናት ቀኝም ግራም ጎኔ::

ሀኒዬን እናቴ አትወዳትም:: "እንዳች አስነክታው ነው ልጄን እቺ የሰው ጉድ!" ትላታለች:: አባቴማ ገና ሲያያት የእናቱ፣ የአባቱ፣ የሁለት እህቶቹና የአንድ አሁቱ ገዳይ ነው የምትመስለው፣ አቤት ሲጠላት:: በወሬ ወሬ "መንገድ ላይ አብረሃም እና..." ቢሉት፣ "በቃ !" ብሎ ይጮሀል:: "አብርሃም ካላችሁ አይበቃም...እናን ምን አመጣው?" ይላል:: ያው ቃል ማንም ጋር እንደማልታይ፣ ሀኒ ጋር ነኝ ቤት ውስጥ - የምትበላውን እየሰራሁላት:: ሀኒ ጋር ነኝ በመንገድ - ቦርሳዋን ይዤላት፣ ጥንጥላዋን ይዤላት፣ ዕቃ ከገዛን እስቤዛም ቢሆን እኔ ይዤላት...ሀኒ ጋር ነኝ የትም !!

ሀኒን እህቴ አትወዳትም:: ከዘመናዊ ጓደኞቿ ጋር ሆና ከሩቅ ካየችኝ በሬ እንዳሯሯጠው ሰው መንገድ አሳብራ የጓደኞቿን እጅ እየጎተተች ትሸሻለች:: "ወንድሜ በሬ እገባ" እያለች ነው የምታወራው እሉ !

ወንድሜ ሀናን አይወዳትም:: "ለስንት ስንጠብቅህ እዚ ሁች አዚፋ ጋር ትወዘፋለህ" ይለኛል፣ አዚፋ ምን እንደሆነ አላውቅም:: ግዴለም ሀኒዬ 'አዚፋ' ከሆንች፣ አዚፋ ይባረክ !! ስድብ ሰውን ካረከሰው፣ ሰው ስድቡን ስለምን አያከብረውም? ሀኒዬ አዚፋን አከበረች...አወዳታለሁ::

ሀ ቆንጆ አይደለችም:: የኔ ቆንጆ፣ ቆንጆ አይደለችም:: "ኪንኪ ፀጉሯ ጠዋት ስትነሳ ያስፈራል" ይላሉ፣ አዎ እውነት ነው:: "አፍንጫዋ በአይኗና በላይኛው ከንፈሯ መካከል ያለ ሁለት የሽንቁር ነጥብ ነው" እያሉ ያሚታል...እውነት ነው !!

ከንፈሯ ወጣ ወጣ ባሉ ጥርሶቿ (በገጣጣ ነው እነሱ የሚሉት) ከርስቱ ተገፍቷል:: በዛ ላይ ብትስቅ ዞሮ ማጅራቷ ላይ ይዘያየራል ይላሉ:: አዎ እውነት ነው !!

"የባቶቿ መደልደም ከዘጠኝ ዓመቷ እስከ አስራ ዘጠኝ ዓመቷ 1000000000000000000000 ኪንታል ገብስ ሳታቋርጥ የወቀጠች ያስመስላታል" ቢሉም (ተጋነነ እንጂ) እውነት ነው !! "እግሯ ከየትኛውም ጫማ ጋር እንዲጣላ ተደርጎ ነው የተፈጠረው" ያሉትም አልዋሹም::

ያዚህ ሁሉ መናቅ፣ በዚህ ሁሉ መገፋት ተገፍታ እኔ የምባል ጥግ ላይ ደረሰች - የሀኒዬ ዓለም መጨረሻ::የት ትሂድላቸው? አለሁላት ወንድሟ ነኝ:: ፍቅረኛዋ ነኝ::ባሏም ነኝ!! አላፍርባትም:: አኮራባታለሁ !! ሀኒዬ የኔ ናት:: ማነው እኔን አልፎ የሚዘልፋት ወንድ ?! የኤሌክትሪክ እጥሯ ጠባቂ ውሻዋ ነኝ:: ከእግሯ ስር የማልጠፋ:: ባለቤቱ ያላከበረው አምሌ፣ ወላ መልኩ ወላ ዘመናዊነቱ አያስከብረውም:: አንዱ የወረወራችው አይደሉ ሌላኛው መኪና ላይ የሚኮፈሱት!

የተናቁ አምሌዎች !! ሀኒዬን አከብራታለሁ !! እግዜር ያውቃል ልቤን !!

"ጥርሰሽ እያምርም" ቢሏት ከሳቅ ተጣላችላቸው:: ሰው ፊት አትስቅም ሀኒ:: የመጻፍ መብታችን፣ የመሰለፍ መብታችን ተነካ የሚሉ ያአገሬ ልጆች፣ የሀኒዬን የመሳቅ መብት በአደባባይ ነጠቁ:: እስካሁን ሻይ ቡና ለማለት ካፍቴሪያ መግባት ያስፈራታል:: ራሷ ቤት ውስጥ ስትቀመጥ እንኳን እግሮቿን ሶፋ ስር ልትደብቅ ይከጅላታል:: በመንገድ ዳር ዘለፋ መሳቀቅን ሸልመዋታል:: ሰላምታ ስትጨብጥ ትሳቀቃለች:: የመዳፏን ሻካራነት በየጭብብጡ የሚጮኽ አዋጅ አድርገው ሰው ልቧ ውስጥ ተከለውባት::

ሀኒዬን "ቆንጆ ካልሆንሽ ሰው ከመሆን መንበር ተንኮታኩተሻል" ብለዋታልና ቆንጆዎች እምላክ ይመስሏታል:: የቤት ልጅ የክብር ጥጉ በየሆቴሉ ወንበር ተጎትቶላት መቀመጧ ነውን ? በአደባባይ መታቀፍስ የፍቅር አሜኬ ሆኖ የታወጀው መቼ ነው ? እየተውረገረጉ የወንድ ጭብጨባ ያደነቆራቸው ሀኒዬን ቃል ሳያወጡ በድርጊት ቀበሯት::

እነሆ ለአንዲት ደሀ...ለአንዲት መልከ ጥፉ ደሀ ተልኬ የምታስተናግድበት ተራ ሻይ ቤት ተከሰትኩ፣ ያውም 'አዩኝ' ብሎ የሚቆሸሽ ነጭ ሸሚዝ ባማረ ጂንስ ሱሪ ለብሼ፣ ጥቁር መነፅሬን ሰክቼ እየተቆነንኩ በረንዳው ላይ ካሉት ወንበሮች በአንዱ ላይ ሰፈርኩ::

"ምን ልታዘዝ!" አለች ሀኒዬ እየተሽቆጠቆጠች:: ሳያት ላማትብ ቃጥቶኝ ነበር:: እግዜር ሰውን የት ድረስ ውብ እንደሚያደርግ አውቃለሁ:: የት ድረስ መልከ ጥፉ እድርጎ እንደሚፈጥር እነሆ የእጁን ውጤት ፊቴ እቁሞ አሳየኝ:: "አቤት ችሎታው ምን ይሳነዋል!" አልኩ ::

ስራዬ በዛው ግድም ነበርና ደጋግሜ ሳያት ከቀን ወደቀን እየባሰ የሚሄድ ይሄ ጎደለው የማይባል ፍፁም የሆነ አስቀያሚነት እንዳሸከማት እየተገረምኩ ታዘብኩ:: ግና የገረመኝ፣ "አቤት ስታሳጠላ" እያልኩ ሳያት መፈለጌ - ደንበኛ ሆንኩ::

"ምን ልታዘዝ!"

"ቡና"

"ምን ላምጣልህ?"

"ቡና"

"ሰላም! ምን ላምጣልህ?"

"ቡና"

"ቡና ነው ዛሬም!" (ፈገግ ለማለት እየሞከረች)

አዎ (በፈገግታ)

ከዛ ሳላዘት ቡና አመጣችልኝ...ቡና...ቡና...ቡና...ስላምታ...ሀና ነው ስሟ፤ አንድ ቀን ጠየቅኳት... ነገረችኝ:: ስራ ከሌላት አጠገቤ ትመጣለች...እናወራለን...እንዴት ደስ እንደምትል:: ትልልቅ ጡቶቿን አልፎ ልቧ ይታያል - ንጹህ ነው !!

አንድ ቀን ከጎኔ የተቀመጡ ተስተናጋጆች "የሰው ጅብ!" ሲሏት ጆሮዬ ጥልቅ አለ - ያዘዝነው ዘገዩብን ብለው !!. በመስደቧ ሳይሆን እኔ ፊት በመሰደቧ የቅስሟ መስተዋት ከፍት እፍ በወረወረው የዘለፋ ጠጠር ሲንኮታኮት ፊቷ ላይ እንዴት እንጀት የሚበላ መሳቀቅ አየሁ:: ተሳዳቢዎቹ ጋር የነበረች እንዲት ሴትም ላንቃዋ እስኪላቀቅ ሳቀች:: አዘንኩ:: ለምን አዘንኩ - እኔንጃ !!

የውበት ጥርሳቸውን ሰለው ወንዱን ሲክረትፉት ከተማውን በቀን የወረሩት ሴቶች...ያውም የጉም ጅቦች ላይ አፋቸውን ለኢድናቁት ሲበረግዱ የሚውሉ ዘመናዊ ተብዬ ቅርፊት የከተማ ወንዶች፣ ለንዲት ደሀ ሚስኪን "የሰው ጅብ!" ብለው ተሳሳቁ::ሰርታ በኖረች...በጅብ አፋቸው ጅብ አሏት::

በቀጣዩ ቀን እንገቷን ደፍታ፣ "ምን ልታዘዝ!" አለችኝ...በመከራ እንገቷን ብቅ ካደረገችበት ግንኙነት በዘለፋ ኩርኩም ወደ ትንሽነት መልሰዋት ከ ሀ አስጀመሯት::

"ስልክ አለሽ?" አልኳት፣

"ቡና" የምል መስሏት ልትመለስ ካለች በኋላ ያልኩትን ባለማመን፣

"እ" አለችኝ

"ስልክ ቁጥርሽን ስጭኝ!"

"የድርጅቱን ነው?" ስትል ጠየቀችኝ፣

"ኖ ! ያንችን የራስሽን!"

ዝም አለች:: ቆይታ...ቆይታ

"09..." አለች

"09..." አልኳት ስልኬ ላይ እየፃፍኩ

"እ...09..." ፈራች:: ማመን ከበዳት ፤ የኔ ሚስኪን! ጆግናው ወገኗ፣ ዘላፊ ወገኗ፣ ሃይማኖተኛ ህዝቧ የገደላት...ሙት መቃብሯን ለመፈንቀል ሁሉም በየአፉ የወረወረባትን ድንጋይ፣ በአሽሙር አካፋው በለበጣ መጋፊያው የመለሰባትን የቀብር አፈር መፈንቀል ከበዳት::

"በዚህ ምልክት አድርጊልኝ አጠብቅሻለሁ" ብዬ ቁጥሬን ያመጣችው ደረሰኝ ላይ ፅፌ ሰጠኋት...

የሴት ክብር መሳም ነው ? መታቀፍ ነው ? ተሰመው የተወረወሩ፣ ታቅፈው የተሸቀነጠሩ የሴት ክብር መሳም ነው ? መታቀፍ ነው ? ተሰመው የተወረወሩ፣ ታቅፈው የተሸቀነጠሩ ይናገሩ፤ ሴት ልጅ ያመነችው ወንድ፣ 'ጣላት!' 'ተዋት!' ከሚል አሽሙር ሲታደጋት፣ ያኔ ነው ክብር ቦታዋ ላይ የምትቀመጠው:: ሴት ልጅ ስታፈቅር እድሜዋን ነው ሸርፋ የምትሰጠው::

ሽራርፈው ሽራርፈው ሴቶቹን ከአድሚያቸውም ከውበታቸውም አግልተው ገሸሽ ያሉ ወንዶች ይስሙ! እኔ ሽቅርቅሩ ሀናን ወደድኳት፣ ወረተኛ አይደለሁም:: ምንም ቢመጣ አልተዋትም:: አገሬ አይደለም:፣ ሰማኋት፣ አይኔን ሳልወድ በግድ አስጨፈነችኝ::

መንገድ ላይ ሀኒዬን በኩራት ሳቅፋት፣ "የሚታቀፍ ጠፍቶ..." ይላሉ ሊታቀፉ ከየቤታቸው የወጡ እቅፍ ናፋቂዎች ሁሉ...

ስሰማት የሚያቅለሸልሻቸው አይናቸውን አዞሩ:: ሀኒዬን አበድኩላት !! ሀና ሴት ናት !! እግዜር "ሴትነትን" መደበቂያ ቢያጣ ባልረባ ስጋ ጠቅልሎ ያኖረበት የክብር መዝገብ:: ወንዶች እግር ላይ ሴትነትን ሲፈልጉ:: ያማረ አፍንጫና ጥርስ ላይ ሴትነትን ሊያጠምዱ መንጠቆ ሲወረውሩ... እግዜር እንቁውን የት እንዳስቀመጠው ተመልከቱ::

አገባታለሁ...ሀናን "አገባታለሁ!" ያልኩ ቀን ሙሾ ባይነት ባይነት ወረደ:: ሀና ራሷ ደነገጠች::ከዛ በፊት "እንዲሁ ከምቀር ፍቅር የሚባለውን ነገር ልሞክረው ቢያንስ ከትዝታው ጋር እኖራለሁ" ብላ እንጂ፣ ያገባኛል ብላ በምን ጠርጥራ(በኋላ እንደነገረችኝ)::

ተወራ በመንደሩ፣ "አብርሀም ቡጡቃ ሻይ ቤት ያለችውን 'ሆረር' ሊያገባ ነው..."

"አትቀልድ ባክህ"

"ማርያምን!"

"ክርስቶስ ምስክሬ..."

"ወላሂ!"

"አበደ እንዴ?!መካሪ የለውም?"

ተቀባበሉ ወሬውን...

ለክብሩ...ለወጉ ለመዓረጉ! "ሀኒን ላገባት ነው ፤ ዳሩኝ!" አልኳ ቤተሰቦቼን፣

"አያገባንም !!" አሉ::

'የራሳችሁ ጉዳይ!' ብያቸው ከሀኒ ጋር አብረን መኖር ጀመርን:: ወላ ቤተሰብ፣ ወላ ጓደኛ ድራሹ ጠፉ:: ሀኒዬን ወደድኳት:: ከዚህ ሁሉ አሰቃቂ መልክ ጥፉነት መሀል የተረፉት ጡቶቿ ወስውሰውኝ በስሜት እንዳይሆን የወደድኳት ብዬ ጀማው ቢንጫጫ ፈራሁ...ኧረ ሀቂቃው ፍቅር ነው !!

አራት ዓመት እሳት በሆነ ፍቅር ኖርን፣ ባለብኝ ወደድኳት:: ደሄው እርጉዝ ናት፣ ያውም የስምንት ወር:: ሀኒ እኔ ጋር ትስቃለች:: እኔ ጋር እግሯን አትደብቅም:: በነበረው ግዝፈት ላይ እርግዝና ያሳበጠው አስቀያሚ እግሯን ጉልበቴ ላይ አስቀምጬ ሳሸሻት እንዴት ደስ እንደሚለኝ.

"አብርሽዬ"

"ዶ..." አላታለሁ

"አንተን ፈልጌ ነበር"

"ምን..." በበታህ እብርሽ! ተዘጋጅ !

"ሊ..." ሂድ...ዲዲዲዲዲዲ ስጋ...ሰዕል (ከሰዓሊ ጓደኛዬ)...ሰስ ፒጃማ...ሰንግ...ሰራስር ነገር(ድንች፣ ቀይ ስር፣ ካሮት) ስእሉት(ለማረያም ሀኔ በሰላም ትገላገል ብዬ)...እያሰከሰኩ ስመለስ፣ "ውይ አብርሽዬ...'ሰልኬን አቀብለኝ!' ለማለት ነበርኮ፣ ሮጥክብኝ....ሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃ"...እኔ ፊት በትሰቅ አትሳቀቅም ሀኒዬ !!

# 24 ትንቢት...

*በዚህች 'ቅድስት' ምድር*

*ትንቢት ነው መሳቡ፣ ትንቢት ነው ሰፈዱ*

*ትንቢት ነው ቡሀቃው፣ ትንቢት ነው ምጣዱ*

*ትንቢት ነው አሳቱ፣ ትንቢት ነው አመዱ...*

*በይበስላል ትንቢት እየተሸወዱ*

*ሚስኪን ድስታቸውን እመድ ላይ የጣዱ*

*ሽሯቸው ሳይፈላ ከአመድ ተዋሀዱ...*

"አመዳም !! በትንቢታችን አሹፌህ ሞተኸል..." (ለጻፍኩት ግጥም የጓደኛዬ አስተያየት)

ሕፃን እንደነበርኩ አማርኛ አስተማሪያችን፣ "ስታድግ ምን መሆን ትፈልጋለህ ?" ብለው ጠየቁኝ፤

"አላድግም !!" አልኳቸው።

ንዝረቱ ሱዳን ድረስ በሚሰማ ኩርኩም አጋጩኙ። ገጭ !! በ'ሬክተር ስኬል' ምናምን ቁጥር የተመዘገበ ኩርኩም በሽመልስ ሐብቴ ትምህርት ቤት ሁለተኛ 'ዲ' ክፍል ስንፍ መደዳ ሶስተኛው ዴስክ ላይ...ጥቁር ሰሌዳው እያደገ እያደገ ሄዶ ግድግዳውን የሸፈነው እስኪመስለኝ ፊት ለፊቴ የሚታየኝ ነገር ሁሉ ጨለማ ብቻ ሆነ። የቀኔ ማብሪያ ማጥፊያ እናቴ ላይ ተገጥሞ በኩርኩም የሚበራና የሚጠፋ ዓይነት...'ገጭ' ሲል እልም !! ቀኑ ጨለመብኝ። ማክሰኞ ቀን ነበር...ማክሰኞ ጨለመ...!!

ይሄ ኩርኩም የሚገባው ለአማማ ዙሪያሽ ነበር...(የሰው ሀቅ ነው የወሰድኩት) እላቸው ናቸው የመለኮታቸውን መስተዋት ለወፍ በወረወርኩት ድንጋይ የሰበርኩባቸው ቀን መንደሩ ሁሉ አየለማ! "ይሄ ያስታው ቃል አያድግም" ያሉኝ:: ደግሞ የባህል መድኃኒት አዋቂ ናቸው:: ትንቢት ቃመስ የሀኪም ትዕዛዝ ብናገር ይሄን የሚያክል ኩርኩም...?

በኩርኩም የሊታድግም!' ትንቢቱን አከሸፈውት ነው መሰል አደግኩ!! ፀረ ትንቢት ኩርኩም:: "ሷጅሀን በኩርኩም አጋጨው ፤ ሲያድግ ዶክተር ለመሆን ይመኛልና::"

ሦስተኛ ክፍል አባቴ፣ "ምን ለመሆን ትመኛለህ?" አለኝ::

ከኩርኩም ቀጠና ነፃ የሆነ በታ ላይ ቆሜ፣ 'ጠቅላይ ሚንስትር' አልኩ

"አዝዝዝዝዝ የኔ ልጅ! ጎሽሽሽሽ!" አለ በጣም ጮሆ:: ጩኸቱ አራት ኪሎ አስኪሰማ !!

"ምናለ ?" አለች እናቴ ጓዳ ሆና የአባቴን 'ጎሽሽሽ' እንጂ የእኔን የ'ጠቅላይ ሚንስትርነት' ምኞት አልሰማችም ነበር::

"ቆይ ራሱ ይንገርሽ... 'ስታድግ ምን ትሆናለህ በይው!'...አፈር ስሆንልሽ ፀሐይዬ ጠይቂው... ሃሃሃሃ ሂድ ንገራት!" አለና ወደ ጓዳው ገፋ አደረገኝ...ወደ ጓዳ እየተገፋ ጠቅላይ ሚንስትር ይሆን ይመስል...::

"ና አስቲ አንተ...ምን ታፍራለህ...ና ወደዚህ...ንገረኝ! ምንድነው የምትሆነው ስታድግ?" አለች 'ምኞቴ' እንዳያመልጣት እቃ ማንኳኳቷን አቁማ::

"ጠቅላይ ሚንስትር"

"ጎሽሽሽሽሽሽሽሽሽ...የኔ ልጅ!" እቅፍ አድርጋ ሳመችኝ:: ፊቷ ሁሉ በፈገግታ ተሞላ::

4ኛ ክፍል እንደኛ ወጣሁና የወላጆች ቀን ላይ፣ "ሳድግ ጠቅላይ ሚንስትር እሆናለሁ" አልኩ፤ ተጨበጨበልኝ:: የጭብጨባው ድምቀት ህዝቡ ከተፈጠረ ጀምሮ ጠቅላይ ሚንስትር አይቶ የማያውቅ እስኪመስለኝ አስገረመኝ::

6ኛ ክፍል... "ምን መሆን ትፈልጋለህ ?" "ጠቅላይ ሚኒስትር" እጅግ በጣም ብልህ...ጎበዝ...!!

7ኛ ክፍል... "ምን መሆን ትፈልጋለህ ?" "ጠቅላይ ሚኒስትር" በጣም ጎበዝ...!! (ብልህን የት ጣሏት)

11ኛ ክፍል... 'ምን መሆን ትፈልጋለህ ?' ሳልባል "ጠቅላይ ሚኒስትር እሆናለሁ" ብዬ ተናገርኩ... "ይሻላል አብርሽ...?" አለች እናቴ ቅር ብሏት፡፡

12ኛ ክፍል... በወሬ ወሬ 'ጠቅላይ ሚንስትር' እንደምሆን ገለፅኩ... ዝብዝ የለ ፤ ሰነፍ የለ (ድምፅ ተአቅቦ)

ዩኒቨርስቲ ልገባ ውጤት መጣልኝ !! እናቷ ላይ 4 ነጥብ !! (አሳት እኮ ነኝ) ማታ አባቴ ጋር እያወራን እናቴ እራት እያቀራረበች ጥያቄው ተነሳ፤ "እ...ሽ ጎረምሳው! ታዲያ ምን ልታጠና ወሰንክ...?" አለኝ በኩራት እያየኝ፡፡

"ያው ፖለቲካል ሳይንስ ነዋ አባባ" አልኩት ልክ እንደሱ ኮራ ብዬ፡፡

"ምን ለመሆን ?" ተገርሞ ጠየቀኝ፡፡

"ጠቅላይ ሚንስትር ነዋ !!" በመገረሙ ተገርሜ መለስኩለት፡፡

እናቴ የያዘችውን ሰሀን በቁጣ ለቀቀችውና እንባ እየተናነቃት አባቴ ላይ ጮኸችበት፤ "ሲያብድ ዝም ብለህ ታየዋለህ እንዴ ? እስከዛሬ 'ልጅ ነው ነብስ ሲያውቅ ይሻለዋል' እያልን ዝም አልን..." አለች ሳግ እየተናነቃት ፤ እንባዋ በአይኗ ሞልቶ ነበር፡፡

አባቴ ሲያስብ ቆየና...ረጋ ብሎ፤

"አብርሃም" አለኝ፤

"አቤት አባባ"

"እርፈህ ዶክተር ሁን !!"

ሕክምና ፋክልቲ ገባሁ፡፡ የሁለተኛ ዓመት የሕክምና ተማሪ እስከምሆን ተስፋ አለኝ (ከተሞከረ)... እያልኩ ሳምሰለስል 'እሳይመንቱም' ምኑም እየያዘኝ አልሞላልህ አለኝና 3...4...5...6...7......እርፌ ዶክተር ሆንኩ !! ጨመርኩበት..."ዶክተር አብርሀም የመሀፀን እስፔሺያሊስት !!"

አገር ከማምራት ሰውን ከመነሻው ወደ መድረሻው መምራት ስራዬ ሆነ፡፡ አገር እቅጣጫውን የሳተ ፖለቲካ ወልዳ ራሷም አቅጣጫዋን እንዳትስት ከመከላከል፤ አቅጣጫውን የሳተ ፅንስ እንዲት ሚስኪን እናት አጥፍቶ ራሱም እንዳይጠፋ መከላከል ስራዬ ሆነ፡፡ የተዛነፈ፤ መቀመጫው ያልተመቸው ኢኮኖሚ በጨነገፈ ቁጥር የጭንገፋውን ምክንያት ለሕዝብ ከማብራራት ስለጨነገፈ ፅንስ ሳይንሳዊ ምክንያት መደርደር ስራዬ ሆነ፡፡ 'ብዙ አልራቅኩም...' እለዋለሁ ለራሴ፡፡

ማን ያውቃል? በእጄ ካዋለድኳቸው አንዱ ጠቅላይ ሚንስትር ቢሆን...ኛኛኛኛአአአአአአ...

ሕፃናት ሃና ተወልደው አጄ ላይ ሲያለቅሱ ከት ከት ብለው የሳቁብኝ ይመስለኛል..."አብርሽ... እዚህ ምን ትሰራለህ...?" የሚሉ ዓይነት...ፈርምልን...እመዳም ሁሉ...!!

ማታ ለዝማሬ ቤት ሄጄ እየጠጣሁ...እላለሁ ተቀበል...

ለየትህልኝ ወይ ይህንን ለንክፍ፤

ሲሪንጅን ወድሮ በአራት ኪሎ ሲያልፍ...

"የተማሩ እኮ ናቸው አቶ አብርሃም..." ሹክሹክታ...

"አሜሪካ...ናሳ...እጃቸውን ስሞ ሊቀጥራቸው ሲል፣ "እንቢ...ህዝቤ...ብለው...ዶላር ከወገኔ አይበልጥም ብለው..." ይባልልኝ ጀመር በመሸተኞቹ...

አሜሪካን በስም ካልሆነ አላውቃትም !! ስንት የጨንገፈ የዲቪ ፎርም አለ መሳቢያዬ ውስጥ...

# 25 ዶክተር አሸብር

ቦምብ እንዲኖረኝ እፈልግ ነበር...!! እንደ እጅ ስልኬ በፈለግኩበት ሰዓት ቁልፎቹን የምጫነው የራሴ፣ የግሌ ቦምብ፡፡ ቦምብ ሲባል ግን ይሄ ሰባት ሰው አቁስሎ፣ ሁለት ሰው ገደለ...መስተዋት ሰባበረ፣ ግድግዳ ደረመሰ የሚባለው ዓይነት ቦንብ ሳይሆን በጅምላ ፊቱን ያጠቆረብንን፣ በጅምላ የበደለንን፣ በጅምላ የገፋንን ሕዝብ በጅምላ ድራሹን የሚያጠፋ ኒውክሌር ቦምብ፡፡

ቡምምምምምምምምምምም ሰፈራችንን የዶግ አመድ...አዲሳባን ከነስሟ ድራሿን የሚያጠፋ...

*ወይ አዲስ አበባ ለወይ ሸገር ሆይ፣*

*ከተማ እንደጤዛ አለም ይባል ወይ...*

እየተባለ አስኪዘፈን ወላሙሾ አስኪወርድ ድረስ ብቻ አዲስ አበባን ባዶ የሚያደርግ...እንጦጦን ሳይቀር ከስሩ ነቅሎ ህንድ ውቅያኖስ የሚጥል...'አዲሳባ የምትባል ከተማ እዚህ ነበረች፡፡ ምክንያቱ ባልታወቀ ፍንዳታ ጠፋች" እንዲሉ ባለታሪኮች፤ ምክንያት ነጋሪ ባለታሪክ አይተርፍማ፡፡

ኒውክሌር ቦምብ እንዲኖረኝ እፈልግ ነበር፡፡ ሰዎች 'የግል ቤትና መኪና ቢኖረን' ብለው እንደሚመኙት ቦምብ ቢኖረኝ እያልኩ እመኝ ነበር፡፡ እዚህ መሐል አዲስ አበባ ሲፈነዳ ንዝረቱ የሩሲያን የበረዶ ግግር የሚሰነጣጥቅ... ካናዳ ሊታጨድ የደረሰውን የስንዴ አዝመራ የሚያረግፍ - ኒውክሌር ቦምብ፡፡

ይሄ የተመኘሁት ቦምብ ቢኖረኝ ለመጥፎ ነገር አልጠቀምበትም፡፡ እንደ ቤት ዕቃ እንደ ፍሪጅ ቆምሳጥን በቀጥታ ወስጄ አቶ ቀለመ ወርቅ ግቢ ውስጥ መሐሉ ላይ አስቀምጠውና እንዲፈነዳ ቁልፉን እጫነዋለሁ፡፡ ቡምምምምምምምምምምም...ከእኛ ሰፈር ጀምሮ አፈር ነሽ ድንጋይ፣ ዛፍ ነሽ ተራራ ነሽ እየጠራረገ...ወደታች ወደ ሜክሲኮ ሕንፃውን ሁሉ አመድ እያደረገ መንገዱን ሁሉ እየገለባበጠ ይወርድና ወደ ጦር ኃይሎች (አቶ ቀለመወርቅ አዛ ወንድም አላቸው)...ከዛ ወደ አየር ጤና፣ ዓለም ባንክ ('አዲስ ቤት እያስገነቡ ነው' ተብሏል ዓለም ባንክ አካባቢ)

በዚህ በኩል ደግሞ በመስቀል አደባባይ አድርጎ ካዛንቺስ ነሽ ሀያ ሁለት፣ መገናኛ፣ መሪ፣ ሲኤምሲን እየጠራረገ በኮተቤ በኩል ሲቪል ሰርቪስ (እዛ የአቶ ቀለመወርቅ ትልቁ ልጃቸው ይማራል...ይሄ ደነዝ ተምሮ ላይገባው የመንግሥት አህል ይፈጃል !) ፍንዳታው ወደ ቦሌ፣ ሊሞናሪያል፣ ገርጂም መሄድ አለበት በቃ...!! ማነው የሚከለክለኝ? የፈለግኩትን ማሰብ መብቴ ነው ! ማንም ሰው በሀሳቡ በአንድ ጀምበር ዓለምን ማጥፋት ይችላል – እንኳን ይህቺን ቢጢቃ ባለቅሟ የምትንጠራራ በውራጅ የምትንደላቀቅ አዲስ አበባን ቀርቶ::

አዲስ አበባ ለቅሶ ደብቃ ጠጅ እያጠጣች ጮማ እያስቆረጠች 'እንቱ' ብላ ባኖረችው፣ 'ቀለመወርቅ' በሚባል ሰው በላ ጭራቅ ሽማግሌ ምክንያት አሸብር የሚባል ቂሙን የማይረሳ ጠላት አፍርታለች:: እኔ የኛ አሸብር:: አዲስ አበባ አዲስነቷን ሳትወድ ተነጥቃ 'አዲስ ፍራሽ' ትሆናታለች የታባቷ !!

መብቴ ነው...በሀሳቤ ሕንፃዎቿን የፍርስራሽ ክምር ማድረግ...ታሪክ ማድረግ:: "እዚህ ላይ እኮ የለበት መንገድ ነበር" እያለ ድሮ የሚያውቃት እስኪያዝንላት(ለወሬ ነጋሪ የሚተርፍ ካለ) እመድ ማድረግ ይህቺን እመዳም፣ የሰው ፊት እያየች የምታዳላን ወረተኛ ከተማ ንፋስ ያየው ዱቄት ማድረግ:: ደግሞ ከሷም ብሶ አዱ ገነት...ኡኡቴ!!

እንዲህ እያልኩ ሳስብ ነፍሴ ትረካለች...ውስጤ ይረጋጋል:: አዲስ አበባን የተበቀልኳት ይመስለኛል...ደስ ይለኛል:: በቁጣ የጋለ ሰውነቴ ይቀዘቅዛል:: አዕምሮዬም ተረጋግቶ ወደ ማሰቡ ይመለሳል፤ አበቦች አበባ ሊመስሉኝ ይጀምራሉ:: አይኔም በጎ በጎውን ማየት ይጀምራል፣ ውርውር የሚለውን ሰው እና መኪና...ቆንጆዎቹን ሴቶች፣ ባጠቃላይ ሕዝቡን ማየት እጀምራለሁ... ግን ሁሉንም እጠላቸዋለሁ፣ አልወዳቸውም::

ጥላቻ የዘወትር ጸሎቴ ነው:: የጥፋት ምኞት አባታችን ሆይ የዕለት ድጋሜ !! ምነው "በደፈናው ጥላቻ" የሚል የአርጎ ዝንብ ቢንጋጋም አዲስ አበባን ከነሕዝቧ አልወዳትም:: ደግሞ "አዲስ... አዱዬ...አዱ ገነት" እያሉ ይመፃደቁላታል:: ኡኡቴ...አዱ ሲኦል !! የአፍሪካ ዋና ጀሀነም፣ የሰይጣን ኅብረት መሰብሰቢያቸውን !!

አልወዳትም አዲስ አበባን:: አልወደውም ሕዝቡን:: እንዲህ ነበር የማስበው ሁልጊዜም:: ጧት የአዲስ አበባ ቅዳሴ  ከአፅናፍ እስከ አፅናፍ ሲናኝ መስጊዶቹ በአዛን የማለዳ እየጮሁ ሲሞሉት፣ 'እናንተ ክፉ ሕዝቦች ደግሞ ነጋላችሁ፣ ለክፋት ተነሱ' የሚሉ ይመስለኝ ነበር:: ማታ ሕዝቡ በየበረንዳው ተኮልኩሎ ድራፍቱን ሲገለብጥ፣ ቢራውን ሲያጋባ ውስጡ የተከለውን ክፋት እንዳይደርቅበት ውኃ የሚያጠጣ ይመስለኝ ነበር:: ሕዝቡ ራሱ ስለራሱ ደግነት፣ ስለራሱ ቸርነት፣ ስለራሱ እንግዳ ተቀባይነትና አማኝነት ለራሱ ሲያወራ ይገርመኛል:: ለእኔ የአዲስ አበባ ህዝብ ብዙ አይደለም፤ አንድ እምሳል አንድ አካል ያለው፣ 'ቀለመወርቅ' የሚባል አንድ ሰው ነው !!

## ክፍል ሁለት

አሸብር ነው ስሜ - ዶክተር አሸብር በእምላክ! 'በእምላክ' አባቴ አይደለም፣ አያቴም አይደለም፣ ማን እንደሆነ አላውቅም...እናቴም አታውቅም:: ልክ ለእኔ አሸብር የሚል ስም እንደወጣልኝ 'አባት' ለሚለውም ቃል በእምላክ የሚል ስም ወጣለት:: የእኔን ስም ያወጣችው ብዙ ላሞች ያሏት ከፋትን እንደ ላም የምታረባ እና ባወራች ቁጥር ከንፈሯን በአውራ ጣቷና በአመልካች ጣቷ በቁንጥ የምትጠርግ ክፉ ባልቴት ነበረች::የአባቴን ስም ያወጣችልኝ ግን እናቴ ናት:: እናቴ አፀደ ! አቲዬ ነው የምላት (በዚህች ምድር ላይ ስሟ ላይ 'ዬ' ጨምሬ አቆላምጬ የምጠራት ብቸኛ ሰው እኔ ልጇ አሸብር ብቻ ነበርኩ::)

አንደኛ ክፍል እስክመዘገብ የአባት ስም አልነበረኝም:: ልክ ትምህርት ቤት አቲዬ ወስዳኝ ለመዘገብ ጉጉት የመሰለው መዝጋቢ እናቴን እያጣደፈ ጠየቃት:: ድሪቶ ቀሚሷ ለዓይኑ ቀፎት እያመናጨቀ የእኔን ስም ጠየቃት:: የንቀት አስተያየቱን፣ እናቴን ዝቅ የሚያደርግ የፊቱን ገፅታ አይቼዋለሁ፣ በዚያው ድሪቶ ቀሚስ ስር በፍርሃት ተከልዬ...አይቼዋለሁ ቅንድብና ቅንድቡ እስኪነካኩ ሲጢጉ እናቴ ላይ ሲኮሳተር:: ሰራሷ ኑሮ የገላመጣት እናቴን ሲገላምጣት አይቼዋለሁ::

አቲዬ እስመዝግባኝ ከፊቱ ዞር ስትል ፊቱን አጨፍግጎ መጥፎ ጠረን እንደሚያባርር ሰው በግራ እጁ አየሩን እያራገበ ሲያባርር አይቼዋለሁ:: በእርግጥ አቲዬ እማማ የብርጓል ቤት እንኩሮ እያነኮረች ነበር:: "ምዝገባው ዛሬ ነው የሚያልቀው" ሲሏት ነው ብድግ ብላ ሳትሊቃለቅ የመጣችው:: ቢሆንስ ልክ ቆሻሻ እንደሸተተው ሰው ሁሉ እንዲያየው አድርጎ እጁን ያራግባል ? የእማማ የብርጓል ቁጥር አንድ የጠላ ደንበኛ እንዳልሆነ ሁሉ፣ 'አሻሮ ሸተተኝ' ብሎ ያዙኝ ልቀቁኝ ይላል ? ኑብር አየው !! እንኳን ይህቺን አይቼ እንዲሁም ጥላቻ ጥላቻ ይለኛል:: ያንን የውሻ ልጅ አስተማሪ እንደ ጠመድኩት ጡረታ ወጣ !! ደግሞኮ አያፍርም መንገድ ላይ ሲያገኘኝ "የእኔ ተማሪ ነው!" እያለ በኩራት ያወራል::

"ስም ?" አላት አቲዬን::

"የእኔን ነው ?" አለች እየፈራች:: ፈሪ ነበረች እናቴ:: ፈሪው የአዲስ አበባ ሕዝብ እንደያቅሙ ደሀ ማስፈራራትን ተክኖበታል:: በትዕቢት ማከላፈቱ፣ በከፋት፣ ስድብና ዘለፋው እናቴን ፈሪ በርጋጊ አድርጓታል::

"አንቺ ነሽ አንደኛ ክፍል የምትመዘገቢው ?" አላት:: አጠገባችን ያሉት ሁሉ ሳቁለት:: አቲዬ ተሳቀቀች:: ሰውነቷ ሽምቅቅ ሲል ቀሚሷን አንቄ ተሰምቶኛል፣ የመሸማቀቋ ንዝረት እንደ ታላቅ የመሬት ርዕደት ለእኔ ለልጇ ተሰምቶኛል:: የሰዎቹ ሳቅ በፍርሀት ሲያንቀጠቅጣት ተሰምቶኛል፣ የአንድን ታዳጊ የፍቅር ሕንፃ የሚያፈርስ የመሬት መንቀጥቀጥ እናት የምትባል ሚስኪን ምድር ላይ ሲነሳ በሳቅ የሚያጅቡ ጅሎች ዙሪያችንን እያላዘኑ ነበር ::

"ሞልድሽን ስም ንገሪኝ ሴትዮ!" አላት ከከበበው ሰው የተበረከተላትን ሳቅ ካጣጣመ በኋላ::
"እ...ኢ..ሽብር.....እሽብር ነው ስሙ" አለች ራሴን እያሻሸች::

"የአባት ስም ?"

"አባ...ት" ብላ ዝም አለች:: አባቴን መንደርተኛው ሁሉ ጠንቅቆ ያውቀዋል:: ወኔ ቢኖረው ኖሮ ሁሉም በኅብረት እንደ መፈክር በአንድ ላይ የአባቴን ስም ሊጠራው ይችል ነበር:: ማን እንደማያውቅ ሁሉ የአቴዬን አፍ በጉጉት ይመለከት ጀመረ::

"የአባቱ ስም ማነው?"

"ቀ..." መጨረስ አልቻለችም... 'ቀለመወርቅ!' ልትል ፈልጋ እንደነበር የገባኝ ካደግኩ በኋላ ነው፤ "የዛሬዎ ደግሞ የጉድ ናት የልጇም አባት የሚጠፋት..." ብሎ እንደገና እንዲስቁለት ሰዎቹን አየ:: ያልደመቀ ሳቅ ተሳቀለት:: "በይ ወደዛ ሁኝ ስታሲታውሽ ትመለሻለሽ ተረኛ ቀጥል!" አለ እስከሪብቶውን እያወናጨፈ:: እናቴ ከእንቅልፉ እንደባነነ ሰው፤ 'በአምላኪ...በአምላክ ነው የአባቱ ስም' አለች:: ጎረቤቱ እርስ በእርሱ ተያየ፤ እንሾካሾከ:: መዝጋቢው ራሱን ግራና ቀኝ በብስጨት እያወዛወዘ መዘገበኝ:: ራስ የሚያስወዘውዝ ስንት ጉዳይ እያለ፤ አቴዬ የእኔን አባት ስም አሰበች ብሎ ይሄን በአድሎዎ የተሞላ ራሱን ይነግጣል:: ብዙ ሰዎች አንድን ነገር በቀላሉ ስለሚያገኙት ማንም ሰው በቀላሉ የሚያገኘው ይመስላቸዋል፤ ለምሳሌ አባት !

ከምዝገባ ስንመለስ አቴዬን ጠየቅኳት፤ "አባቴ ማነው?":: ድንግጣ አየችኝና አጥብቃ በያዘችኝ እጇ ወደ መንገዱ ዳር ሳብ አደረገችኝ:: ከሩቅ የሚመጣ እኛ ካለንበት ነገም የሚደርስ የማይመስል የጭነት መኪና እንዳይገጨኝ:: አቴዬ መኪና መንገድ ላይ ስሄድ መኪናው በአካል ባይደርስ እንኳን ድምፁ የሚገጨኝ ነው የሚመስላት:: ትባባልኛለች !!

"አባትህማ በአምላክ ነው...በአምላክ" አለችኝ:: አነጋገሯ የገጠር ተፅእኖ ይጫነዋል:: 'በአምላክ' የሚለው ስም ለራሷም ሳይገርማት አልቀረም ::

"የት ነው ያለው?"

"ሁሉም ቦታ "

"የታለ ?" ብዬ ዞር ዞር አልኩ::

"አይታይም ...እሱ ግን እኔና አንተን ያየናል፤ ችግር ካጋጠመን ከየት መጣ ሳይባል ከተፍ ይላል"

"ከተፍ"

"አዎ ከተፍ ድንገት!" አለችኝ አቴዬ እልህ በተሞላበት ድምፅ:: እንዲህ ስትለኝ አባቴ ፖሊስ መሰለኝ:: ብዙ ጊዜ ሰዎች ሲያወሩ "ፖሊስ ከተፍ ብሎ" ሲሉ እሰማ ነበር::

"እቴዬ!"

"ወይዬ!"

"አባቴ ልክ እንደ እግዚያብሔር ነው?"

"አዎ ቁርጥ እንደ እግዚያብሄር።" በአባቴ ዝና ትንሽ ልቤ ይሞላል።

"እቴዬ!"

"ወይ" ትንሽ ያሰለቸኋት ትመስላለች።

"ከእግዚያብሔርና ከአባቴ ማን ይበልጣል ?"

"እኩል ናቸው...እኩል" ትለኛለች።

*ክፍል ሦስት*

አሸብር ብላ ስም ያወጣችልኝ ከቤታችን በላይ ብዙ ላም የምታረባ ቅሌታም ባልቴት ናት። ስሙ ከእኔ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። ከእቴዬም ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም። እኔ ልወለድ እቴዬ ምጥ የተያዘች ቀን የዚህች አቃጣሪ ባልቴት የአሜሪካ ላም ያልታወቀ ነገር በልታ ሆዷ ተቆዝሮና እረፋ ደፍቃ እየጓጎረች ነበር አሉ።

የመንደሩ ሰው ከእኔ እናት ምጥ ይልቅ የዚህች የመንደራችን ሀብታም ላም ነፍስ አስጨንቃት አዋላጇ አልማዝ ሳትቀር ወደዛው ሂደው ነበርና እቴዬ ብቻዋን እኔን ተገላገለች። ብቻዋን !! የቀን ሥራ ያጠነከራት ብርቱ ሴት ባትሆን ኖሮ ሟች ነበረች። ብቻዋን ወለደችኝ !!

አንድ የእንስሳት ሀኪም ተጠርቶ የኢቃጣሪዋን ዘርፌ ላም ሆድ አስከረብቶ በሚመስል ነገር ወግቶ ሲያስተነፍስላትና ላሟ መጓጎሯን ስታቆም መንደርተኛው እልልታውን አቀለጠው፤ እልልልልልልልልል... እቴዬ እልልታውን ከሩቅ ስምታለች። በዚህ መሀል አዋላጇ፤ "በምትኩት ያቺ ሚስኪን ምን ደርሳ ይሆን?" ብላ ወደ ቤታችን ተጣደፈች። እቴዬን የተፈለቀቀ ወርቅ የመሰለ ወንድ ልጅ እቅፋ አገኘቻት። ያ የተፈለቀቀ ወርቅ እኔ ነበርኩ ያውም ገና በእሳት ሊፈተን የተዘጋጀ ወርቅ።

ዘርፌ የሚሏት ሀብታም ባለላም የላሟን ደኅንነት ሊጠይቃት ቤቷ ሲጎርፍ የዋለውን ቅቤ እንጓቹ ሁሉ ስታስተናግድ ውላ ወደ ማታ እስር እንጀራና ከከ ወጥ ይዛ ቤታችን መጣችና "መንደርተኛው በእኔ ላም በተሸበረበት ቀን ተወልዷልና 'አሸብር' ብዬዋለሁ" አለች። አሸብር ሆኜ ቀረሁ!! ነገ እድገ ብረብሽ፤ 'ስምን መልዓክ ያወጣዋል' በሚል ሐሳብ 'መልዓክ ነኝ' ልትል። እች...ስድብ የማይገልፃት..!! ለ 'አንቱታ' የደረሰች ሴትዮ ናት፣ 'አንቺ' የምላት ባትሰማኝም ስንቃት ደስ ስለሚለኝ ነው።

እንግዲህ አሸብር የተባልኩት አንዲት ተራ...አጋሰስ...የአሜሪካ ላም ባጋበሰችው ፌስታል ታምጣ መንደርተኛውን ባሸበረችበት ቀን በመወለዴ ነው - ቢቃ !! ደግሞ ምኔም የማያሸብር እንደውም ቅጠል ሲንከሻከሽ አቲዬ አሮጌ ቀሚስ ስር የምደበቅ ፈሪ ነበርኩ...ስሜን ያወጣው መልዓክ አይደለም! ዘርፌ የምትባል ቀንዳም ሰይጣን ናት!!

እኮ የሚያበሳጨኝ...የዛን ጊዜ ዘመኑ ስላልሰለጠነ ነው ብዬ ውስጤ ከተመረዘበት ጥላቻ እንዳይሽር፣ ዛሬም ድረስ ጎረቤቶቻችን ስለዛ ጊዜ ሲያወሩ ፊታቸው የተቀመጠችውን አቲዬን... ብቻዋን መውለዷን ከቁምነገር ሳይቆጥሩት ማሰፋቸው ሳይበቃ፣ ከሞተች የቆየችውን የአሜሪካ ላም ደግነት፣ ባልዲ ሙሉ መታለብ...ፌስታል በልታ ስታቃስት አንጀታቸው መንሰፍሰፉን እየተቀባበሉ ማውራታቸው ነው:: ደግሞ የሚንሰፈሰፍ አንጀት እንዳለው ሰው::ጎማ አንጀት ሁሉ !!

እቤት ስጠላቸው! ልቤ ተሸንቁሮ የቋጠረው ፍቅር ፈሶ ያለቀበት ይመስል የተረፈኝ እፅናፍ የለሽ ጥላቻ ብቻ ነው:: ማንንም አልወድም ሁሉንም እጠላለሁ !! ዘርፌ መልዓክ ብትሆን ጥሩ ነበር - ስሜን እንድሆን፤ ይሄን ከመሬት ተነስቶ የሚሸበርና የሚያሸብር አውሬና ምንዝር ጎረቤት ሁሉ እንዳሸብረው !! ወይ ነዶ...ለምላ በንብ ምናለ እንዲት ኒውክሌር ቦምብ ብትኖረኝ !! ለክፉ ነገር አልጠቀምባትም፣ ቀለመወርቅ ግቢ እወስድና ...!!

## ክፍል አራት

አቲዬ ከገጠር ወደ አዲስ አበባ ስትገባ ገና 14 ዓመት እንኳን አሳምሮ አልሞላትም ነበር:: ገጠር የሚኖሩ ቤተሰቦቿ ምናምኒት የሌላቸው ያጡ የነጡ ድሆች ስለነበሩ ገና በልጅነቷ ነው ልፋት ዕጣ ፋንታዋ የሆነው - ገጠር ስልችት አላት:: ባል አልነበረም የስደቷ መነሻ:: ያላቻ ጋብቻ ምንትስ ብላ አልነበረም ወደ ከተማ መኮብለሏ:: 'የከተማ ሰው ከድህነት የሚያላቅቅ ዓመድሽን የሚያራግፍ ደግ ነው' ብለዋት እንጂ ባል ሽሽት አልነበረም::

ከተሜው ያላቻ ጋብቻ እያለ የሚወተውተው ሲያስመስል እኮ ነው:: በሀብት፣ በዘር፣ በእምነት ለቻ በማሳደድ ሰሉስ ስለተለከፈ፣ የመነፋፈልና የማግለል ንቅዘቱ ነው የሚያስለፈልፈው:: ተራራ ተሻግሮ የሚጮኸው ከተሜ ስንት የነቀዘ ባህል፣ የገማ ዓመል ጉያው ውስጥ ሸጉጧል:: አሱን ብሎ የሙብት ተከራካሪ፣ አሱን ብሎ ታዳጊ:: 'ምን በወጣሽ ካለ አድሜሽ ማግባትሽ' እያለ የገጠሯን ሴት በአዞ እንባ ሙሾ የሚያስወርድ ከተሜ በየጓዳው ከከፉ ባል ይከፋል::

የልጅነት እግሮቿ ወደ አዲስ አበባ መሯት:: ዘርፌ የምትባል ባለ ብዙ ላም ሴት በደሀ መንደር 'ከእኔ ወዲያ ሀብታም ላሳር' የምትል ክብረ ቢስ ባልቴት ላይ ሰዎች አምጥተው ጣሏት:: ሴትዮዋ ብዙ የአሜሪካ ላሞች ስለነበሯት አቲዬን በሰራተኝነት ቀጠረቻት::

ገጠር ትታው የመጣችው አዛባ መዛቅና ላም ማለብ እዚህም መሀል አዲሳባ ጠበቃት:: ባሰው እየመሰለው ይሮጣል እንጂ እጣ ፋንታውን በመሸሽ አያመልጠውም:: እልፍ ሲሉ እልፍ ይገኛል ብሂል ጋር ስንተላለፍ እጣ ፋንታችንም አብሮን እያለፈ ከፊታችን ይጠብቀናል:: እንዲያ ነው እቴዬን የገጠማት፤ ከአበሻ ላም ወደ አሜሪካ ላም!! አዲሳባ ራሷ የአሜሪካ ላም ናት:: ብዙ ላበላት ብዙ የምትታለብ:: አላቢም ታላቢም በጣፍ የሞላባት፣ ውጪዋ አብረቅራቂ ቀለም የተቀባ ሰፈ በረት !!

አንዳንድ የአሜሪካ ላሞች ከሰው ልጆች የበለጠ ክብር ይሰጣቸዋል:: የአሜሪካ ላም ስለሆኑ ወይም ላም ብቻ ስለሆኑ አይደለም - ወተት ስለሚታለቡ:: ስጋቸው ስለሚበላና ሌላ የምትታለብ ላም፣ የሚታረድ በሬ ስለሚወልዱ:: ይሄ የዓለማችን የደነዘ የምጣኔ ሀብት ቀመር ነው - 'የበለጠ የሚታለበውን የበለጠ ተንከባከበው !!' ይልኻል በአደባባይ በክራቫት በታነቀ ተወካዩ:: በተወካዩ መሪነት የሰግብግብነትና የከፋት ኪራላይስ የሚደግም አህዛብ 'ክተሜ' ይባላል::

አገር ይሁን ሰው ምንም ከሌለው ምናምቴ ነው:: ይገፋል፣ ይረገጣል፡፡ ለጠብታ ነዳጅ አንድ አገር ሰው ሲፈጅ ዓለም ጭጭ የሚለው ለዕድቅ የሚሆንን መንገድ በጣፍ ለመቀየስ ነው ካለወት !! 'ሰብዓዊነት ገደል ይግባ!' ብለው ሰው መሆንህን ሊክዱ የሚዳዳቸው ሁሉ፣ በዕድልም ይሁን በችሎታህ አምልጠህ ሰው ስትሆንባቸው ገደል ያስገቧትን ሰብዓዊነት ጎትተው የሚያወጡባትን ገመድ እንድትሰጣቸው ፊትህ ቁመው ጅራታቸውን ይቆላሉ:: ደግነቱ ጭራቅ ለጭራቅ እስከሀላላ አይጨካከንም - የጭራቅ ሕግ አለ፣ የጭራቅ መሀላ በየወንዙ የሚማማሉት ዓይነት:: እንደ እቴዬ አይነት ሚስኪን ለልፋት የፈጠራት እንደ እሀያ ያሻቸውን የሚጭኑባት ፍጥረት የሚማማሉበት ወንዝ ዳር ከተገኘች፣ 'አደፈረሸብን' ከማለት አይመለሱም ::

## ክፍል አምስት

እንደሰው ባልቆጠሯት እናቴ ጉልበት ሰው የሆኑ ብዙዎች 'ሰው ብቻ' እንዳልሆኑ፣ ይልቅ 'በጣም ሰው' እንደሆኑ ሲሰማቸው ('ከጣት ጣት ይበላለጣል' የሚል ተረት ሁሉ አላቸው::) የእቴዬ ወጣት ሰውነት ላይ አይናቸውን ያቁለጨልጩ ጀመረ:: ቀለመወርቅ የሚባል ካፖርትና ከብ ኮፍያ የማይለየው ባለ ትልቅ ቤትና ባለ መኪና ሰው 'ነበር':: እሱስ አሁንም አለ፤ እኔ ውስጥ ከሞተ ቆየ እንጂ ! በውስጤ ሚሊየን ጊዜ ገድየው፣ ሚሊየን ጊዜ ተነስቷል - የከፉ ሰው ነፍስ ጣር ይበዛበታል::

ሁሉም ሰው 'ጋሽ ቀለሙ' ነው የሚለው እና ይሄ ካፖርታም ቤታም እና መኪናም አጋሰስ በእናቴ ቁንጅናና ወጣትነት ቋመጠ:: ትልልቅ ልጆች አሉት:: ሚስቱ ጋር ተፋትቷል (ባይፋታ ነበር የሚገርመው):: ይሄ የአምሳ ምናምን ዓመት 'ሰው' እንዴት ፍሬ ልጅ ሊያጠምድ ዘርፌ የምትባል አቃጣሪ ያረጀች አሮጌ መረብ ሰፈሩ ላይ ወረወረ:: "ዘርፍዬ እንዴት ያለችውን ልጅ አመጣሻት ደሞ! ,, ሲል ይታየኛል በዓይነ ህሊናዬ::

አቲዬ የምትባል ሚስኪን አሳ የህይወትን ዋና ልትለማመድ ስትፍገመገም መረቡ ውስጥ ገባች፤ ዘርፌ የምትባል ቁራጭ የአሳማ ስጋ የከፋት መንጠቆ ላይ ተሰክታ አቲዬን አታለለቻት።፤

"አፀደ!"

"እመት አትዬ!"

"ኤዲያ እንደ ባላገር 'እመት!' አትበይ፣ 'አቤት!' ነው የሚባል፡፡ ነይ እስቲ ሴጋሽ ቀለሙ ወተት አድርጌሽለት!" አለች ዘርፌ።።

"እሺ!" ብላ የወተት ጠርሙሱን እንስታ ልትሄድ መንገድ ጀመረች - የእኔ ታዛዥ አቲዬ። በልቷ ተቆጣች።።

"ጎይ ወዲህ የምን መንኳተት ነው እቴ...ማንም መደዬ ቤት የምትሄድ መሰላት እንዴ...እንዲህ ተንቧተሽ ትልቅ ሰው ቤት ...ምኗ ገልቱ ነሽ አንቺዩ...በይ ፊትሽን ታጠቢ አግርሽንም እዛ ድንጋዩ ላይ ፈግፍገሽ ታጠቢው።።"

አቲዬ ሰውነቷ ነኩዶት የማያውቀውን ልብስ፣ እግሯ ተጫምቶት የማያውቀውን ጫማ ከአመቤቷ ተዋሰችና፡፡ በደስታ ሰከረች፡፡ ስለከተሜ ሰዎች ቸርነት የሰማችው ቃል ሰጋ ለብሶ ፊቷ ሲገተር አየችው፡፡ አበባ መሰለች፡፡ ድሮም አበባ ነበረች !! እንኳን ያኔ አሁንም ውብ ናት የእኔ እናት !!

በዚህ ዓይነት 'ቀለሙ' ለሚባለው ውሻ ወተት አደረሰች፡፡ ደጋገመችው፡፡ ስትመላለስ ቆየች፡፡

የቀለመወርቅ ቤት ቤተመቅደስ መሰላት፣ ካልታጠቡ የማይረግጡት፡፡ አንድ ሌላ ቀን ዘርፌ አቲዬን ጠራቻት፡፡

"አፀደ!"

"እመ...አቤት እትዬ!" ('እመት አትበይ የባላገር ነው' ተብላለቻ፡፡)

"ጋሽ ቀለሙ አመም አድርጎታል፡፡ ቤት ሰውም የለ፣ ሂጂ እስቲ እህል ውሃ ስሪለት፡፡ እኛ እያለን በረሀብ አይሞት መቸስ ጡር ነው፡፡"

"ምን አገኛችው?!" አለች አቲዬ የኔ የዋህ በእባቦች ጨዋታ መሃል ንፁህ ልቧን በአደራ እያስቀመጠች፤

"ምን እንደነካውማ እሱኑ ጠይቂው፣ እኔ ሥራ ሞልቶልኝ አየሁት ብለሽ" አለች ዘርፌ፡፡

አቲዬ ወደ አቶ ቀለሙ ሄደች፣ ዋለች፣ አደረች፡፡ ልታሲታምም ሄዳ አድማ ልቧን ህሊናዋ ውስጥ

ቅስሟ ተሰበረ፣ ፈገግታዋ ጠፋ፣ የሚመረቅዝ በሽታ ይዛ ተመለሰች:: አቲዬ ከዛን ቀን ጀምሮ ቅስሟ ተሰበረ፣ ፈገግታዋ ጠፋ፡ አንገቷን ደፋች:: ቀለመወርቅ ይሉት መኾኮር ግን ወጣትነቷን የመጠጠው ይመስል አማረበት እረማመዱ ሳይቀር እንደወጣት ሆነ:: ግደሌላችሁም አድሜም እንደገንዘብ ይነጠቃል:: ይሄ ሰው የአናቴን እድሜ በግፍ ነጥቋታል::

አቲዬ በዚህ ልክ የሌለው መከፋት፣ መማለጫ አልባ በሆነ ቅስም መሰበር ውስጥ እንዳለች፣ "አፀደ!" አለች አሰሪዋ ዘርፌ::

አቲዬ "አቤት!" እላለችም፣ ዝም ብላ አቃጣሪዋ ፊት ሄዳ ቆመች:: 'አመትን' በስልጣኔ ስም 'አቤትን' ከክብሯ ጋር ቀምተዋት ምኑን አቤት ትበል...:: ዘርፌ ትእዛዟን እንዲህ ስትል ጀመረች፡

"ጋሽ ቀለሙ ቤት ሂጂና..."

"አልሄድም !!" አለች አንብ ተናንቋት::

"ምናልሽ አንች...እከከከከከ ጭቅቅትሽን ሳላቅቅልሽ እንዲህ አፍሽን ምልተሽ ትሰድቢኝ! " ባልቴቷ በያዘችው የኒኬል ሰሀን አቲዬን ፊቷ ላይ ደረገመቻትና፣ "እቺ ደነዝ እጄን አሳመመችኝ" አለች::

ሰሀኑ የሰሚንቶው ወለል ላይ ወድቆ ተቅጨለጨለ:: አቲዬ በቀኝ እጇ ሰሀኑ ያረፈበትን ፊቷን ሸፍና፣ እግሯ እንደመራት ወደ መኪና መንገዱ በረረች:: ትንሽ እንደሄደች እዚህ አሁን ትልቁ ዳቦ ቤት የተሰራበት ቦታ ላይ አንዲት ኪዮስክ ነበረች፣ አንዳንዴ አቲዬ እየተላከች እቃ የምትገዛበት፡ ባለቤቷ የአቲዬን ወጣትነት ስታይ ሁሌ ምራቋን የምትውጥ (ለሰራተኝነት)...ጠራቻት::

"አፀደ...አንችን እኮ ነው!"

ዝም::

"ምን ሆነሻል ?"

ዝም...እርምጃዋን ቀጠለች እየቆመች::

"አንችን እኮ ነው!"

ዝም::

"አንዴ ደማም ፊትሽ ምን ጉድ ነው? ኧረ ጉዴ፣ ምንድነው ይሄ ሁሉ ደም?!"

አቲዬ ደነገጠች:: እጇን ከፊቷ ላይ አንስታ ተመለከተችው፣ በደም ተሸፍኖ ነበር::

አሁን ያፈነችው እንባ ፈነዳ:: ከልጅነቷ ጀምሮ ውስጧ የተጠራቀመው ጩኸት እና እዬዬ፣ መንደሩን የሚያሸብር ዋይታ ሆነ:: መንደርተኛው ተሰበሰበ::

"ምንድን ነው?"

"እንዴ የአትዬ ዘርፌ ሰራተኛ አይደለችም እንዴ ምን አገኛት?"

"ማናባቱ ነው የዘርፍዬን ልጅ እንዲህ ያደረጋት? ...ዘርፌ...ዘርፍዬ...ወይዘሮ ዘርፌ...እሜቴ ዘርፌ"

የዘርፌ ሰራተኛ ሰው በመሆኗ ሳይሆን፣ በዘርፌ ንብረትነቷ መንደሩ ዘራፍ አለ::

እኮ ማናባቱ ነው የነካት?

"ተናገሪ ማነው የመታሽ?"

"ዘርፌ ራሷ !!"

ዝም በሉ !! ዝምምምምምምምምምምምምምምምምምምምምምምም!!

"ምን እየፍተሽ ነው?" አሏት አትዬዎን:: አሏም ዝም !!

"ታስታውቃለች ተንኮለኛ:: ዝም ያለችው ጥፋቷ ቢሆን ነው::"

"እንዲች ዘርፌ...የሴት ወንድ...መች መጨማለቅ ትወድና...አንድ ነገር ስታደርጊ አግኝታሽ ነው::"

መንደርተኛው ዘባረቀ:: ይሄ ዘባራቂ ሁሉ...:: ይሄ ጉዳይ ከሆነ ስንትና ስንት ዓመቱ - ሰፈሩ ግን አሁንም ዘባራቂ ነው !! ባለ ኪዮስኳ ብቻ ለአቲዬ አገዘች:: "የሚመታ ይምታት፣ ምንስ ብታደርግ እንዲህ ደም በደም እስከትሆን ትመታታለች:: እች ጥጋበኛ ባልቴት፣ ምነው እች ስትዋ በመቀረቢያ አድሜዋ አግሯን እንስታ ፏለለች" አለች በብስጭት::

ባለ ኪዮስኳና ዘርፌ ፀበኞች ነበሩ:: ሁለቱም በመንደሩ ውስጥ የተሰሚነት የክብር ጉዳይ ያጋጫቸዋል:: አቲዬ ባለኪዮስኳ ጋር ሰራተኛ ሆና ቀረች:: አጣ ፋንታን በመሸሽ አያመልጡትም ::

ይህች ሴት የምትደገፈው ሁሉ አሾህ፣ የምትረግጠው ሁሉ አረንቋ ይሆንባት ዘንድ ድፍን አዲስአበባን ማነው በአሚኪላ የሞላባት? የአኔ ከርታታ ኩንታል ሙሉ የምስር ክክ፣ ሉቅ ሙሉ ባልትና ማዘጋጀት፣ የሚሸጥ እንጀራ መጠፍጠፍ ነበር የጠበቃት:: ልብሷ ስውነቷ ላይ ተበጣጥቆ ፀጉሯ ላይዋ ላይ ጀልቶ ብልጣ ብልጧ ባለኪዮስክ ጉልበቷን እንደ ምስጥ መጠጠቻት::

ደም መጣጭ ! የደሀ ክብር መጣጭ ! መንደር ሙሉ መዥገር ! እቺ ሚሊየን አዲስአበቤ፣

አምራና ተውባ በየመንገዱ ሰበር ሰካ የምትል ወይዛዝርት፣ የሚንንማለል ሸበላ ሁሉ፣ 'የሰው ላብ ገንዘቤ ውስጥ የለም ብለህ ማል' ቢባል አግሬ አውጭኝ በሚል ሯጭ መንገዱ በተሞላ - ታላቁ የሽሽት ሩጫ !!

## ክፍል ሰድስት

አቲዬ ለስድስት ወር ከሰውነት ተራ እስከትወጣ ለባለኪዮስኳ ስትሰራ ከከረመች በኋላ ከረምት ገባ:: ባለኪዮስኳ አቲዬን በንስር ዓይን ስትከታተላት ነበር:: ከአያንዳንዱ ቀን ጋር እየተሽቀዳደመች ነበር:: አንድ ማለዳ የአቲዬን ድሪቶ ልብሶች በፌስታል ቋጥራ ከድፍን ሃምሳ ብር ጋር ሰጠቻትና፣ "በይ እግዜር ይከተልሽ!" ብላ ከቤቷ አስወጥታ ወረወረቻት:: የአቲዬ ሆድ ገፍቶ ነበር:: የቀለመወርቅ ፅንስ ከውስጥ፣ የመንደሩ ሰው ከውጭ እየገፉ ሰው በሞላው አገር እናቱን ምድረ በዳ ላይ አቆሟት::

አቲዬ ስትረጭ እና ስታንፍስ የዋለችው የምስር ክክ ብናኝ ፊቷና ፀጉሯ ላይ ተነስንሶ ነበር:: ከስድስት ወር በፊት የነበረችው ልጅ አግር ቀንጃ ልጃገረድ ናት ቢባል 'ቀለሙ' ራሱ አያምንም:: መንገድ ዳር ቆመች:: የክረምት ዝናብ ያካፋል:: አንድ የመኪና ዕቃ መለዋወጫ ሱቅ በር ላይ ፍዝዝ ብላ ቆመች:: ምንም አያየች...ምንም ሰው፣ ምንም መኪና ምንም ቤት:: ህይወት ዝም የምትልበት፣ አዕምሮ ዝም የሚልበት፣ የሰው ልጅ ለሆንች ቅፅበት በቁሙ የሚሞትበት ቅፅበት አለ አይደል:: አቲ በቁሟ ሞተች::

አላዛርን ከሞት ያስነሳ ራሱም ከሞት የተነሳ ክርስቶስ 'አቲዬ!' ብሎ ልክ እኔ እንደምጠራት ጠራት:: ዞር አለች ወደ ኋላዋ:: ክርስቶስ ሳይሆን አንዲት ምቾት መድረሻ ያሳጣት ቀንጃ ወጣት ነበረች..."ወደ ውስጥ ግቢ! ዝናብ መታሽ እኮ" አለቻት አቲዬን:: ገና ሲያጉረመርም እግሬ አውጭኝ ብሎ ሰው የሚሸሸው ዝናብ እንኳን፣ እንዳሻው ሰው ላይ ይጨፍር ዘንድ ሰው በቁሙ የሚጠፋበት ቀን አለ:: አቲዬ ጠፍታ ነበር::

ወጣቷ ከፍ ያለ ወንበር ላይ ተቀምጣ እንፋሎቱ ወደ ላይ የሚመዘዝ ትኩስ ሻይ እየጠጣች ነበር::

አቲዬ ወደ ውስጥ ገባችና ኩርምት ብላ አንዱ ጥግ ቆመች:: አንደ ቆመች ዝናቡ አባራ:: ሰዉ በያቅጣጫው ሩጫውን ጀመረ:: አቲዬ ግን አልተንቀሳቀሰችም:: የእርሷ ዝናብ አላባራም፣ መጠገያ ሳጣ ሰው የሕይወት ዶፍ አባርቶ አያውቅም:: ሰው የፍቅር ዣንጥላ፣ የዝምድና ዣንጥላ፣ የጓደኝነት ዣንጥላ፣ የትዳር ዣንጥላ፣ የእውቀት ዣንጥላ፣ የስራ ዣንጥላ፣ የተስፋ ዣንጥላ፣ የእምነት ዣንጥላ ይዞ ስለሚኖር እንጂ ከሕይወት ሰማይ ላይ ነፍስን የሚያበሰብስ መንፈስን እንደ ወረቀት የሚያላሽቅ የብቸኝነት እና የተስፋ መቁረጥ ዝናብ አባርቶ አያውቅም::

የአቲዬ ዝናብ አላባራም:: ይሄን ሁሉ የነፍስ ዣንጥላ ጨላኝ ንፋስ ከእጇ ነጥቋታል:: ንፋሱ ቀሚሷን በግድ ገልቦ ውስጧ ቅዝቃዜ አስቀምጧል:: ንፋሱ የሕይወት እቧራ አንስቶ ፊቷና

ፀሐዩን አልብሷል:: ንፋሱ የተሰፋ ጎጆዋን እፈራርሶ አዚህ አቁሟታል:: አቲዬ የእኔ እናት መሆኛ የለትም ::

ጠለሏት ተንኳኩ:: ቆንጆዋ ልጅ ጃኬቷን ደረበች:: ውጭ የተደረደሩ እቃዎችን አስገባች፤ እናም ጩኸቷን በሚያሟሟሙሩ ጣቶቿ እንዳንጠለጠለች አቲዬን ግራ በመጋባት እየቻት፣ 'ውጪ!' ማለት ብለማኝ ነው:: ቀደሞ ወጥቶ፣ ውጪ ጋር መቆም ግን ያው ውጪ ማለት ነው::

አቲዬ ዝናብ አስኪያባራ ከተጠለለችበት ሱቅ በቀስታ እርምጃ ወጣችና በረንዳው ላይ ቆመች፤ ባለሱቋ ቆንጆ ሴት ሱቋን ቆላለፈች:: የአቲዬ ነገር ሳያሳዝናት አልቀረም፣ "እ...ምን ሆንሽ ነው አትቶዬ?" አለቻት:: አቲዬ ዝም:: ዓይኗ እንባ አቅርሮ ዝም...ወደ ሞቀ ቤቷ አልያም ወደ ሰበሩት ፍቅረኛዋ ልትሄድ ያኮበኮበች ወጣት የአቲዬን የአርባ ቀን ዕጣ ከየት ጀምሮ ቢነገራት ይገባታል? አቲዬ ዝም አለች:: አልለመደባትም 'እንዲህ ሆንኩ' ብሎ ማውራት፣ አልለመደባትም ምሬት መዘብዘብ - ልማዷ አይደለም::

ወጣቷ ጥቂት ብሮች ከቦርሳዋ አውጥታ ለአቲዬ ዘረጋችላትና "አይዞሽ! ይሄን ያዥ በቃ" አለቻት:: አቲዬ ግን ለማትባ ከተዘረጋው የወጣቷ እጅ በድንጋጤ አፈገፈገች:: ልክ ጩቤ እንደተሰነዘረባት ሰው ነበር የበረገገችው:: 'ለማኝ ልሆን?' ብላ በውስጧ አሰበች:: እንባዋን እያዘራች ሸቅብ አግሯን ተከትላ ትጓዝ ጀመር::

ትም የማያደርሱ የሚመስሉ እርምጃዎች አንዳንዴ አዕምሮ አስቦ ከሚደርስበት የተሻለ መፍትሄ ላይ ያደርሳሉ:: ሰዎች የፈጣሪ መንገድ ይሏቸዋል:: አቲዬ ዝም ብላ ብዙ ርቀት ተጓዘች:: መታጠፊያ ስታገኝ እየታጠፈች፣ መንገድ ስታገኝ እየተሻገረች ዝም ብላ ወደፊት:: ከሰጣ ፋንታዋ ትሸሽ ይመስል መንገዱ ባያልቅ ብላ ተመኘች:: በቃ አስከዓለም ጥግ ዝም ብሎ ቀሪ እድሜዋን መጓዝ ::

ቀና ብላ ተመለከተች:: ፀጥ ያለ ቤተክርስቲያን ከነታላቅ ጉልላቱ ፊት ለፊቷ መንገዱን ተሻግሮ ይታያል:: የልብስ ፌስታሏን እንጠልጥላ አሮጌ ሃምሳ ብሯን በእጇ እንደጨበጠች፣ ዓለምን ከመዳፉ የጨበጠ እግዚአብሔር ጋር የተፋጠጠች መሰላት::

ይህ ሁሉ በደል...የዚህ ሁሉ ግፍና ስቃይ ጠንሳሽ 'እግዚአብሔርን' ፊትለፊት ያገኘችው መሰላት:: እግዚአብሔር አይቷት ሳያፈገፍግ፣ የበደላት ሁሉ አሳፍሮት ሳይሸሽ በፊት ልትደርስበት መንገዱን አቋርጣ ወደ ቤተክርስቲያኑ ገሰገሰች::

ግቢው ፊርቷት እግሬ አውጭኝ የማል መሰላት አቲዬ:: መኪናዎች እምባረቁ፣ ሹፌሮች መኪናቸው መስኮት ብቅ ብለው ፀያፍ ስድብ ወረወሩባት:: እንበሳ ጋር ልትፋለም ታላቁን ግቢ 'በላ ልበልሃ' ልትለው በድፍረት የምትገሰግስ ጀግና በውሾዎች ጩኸት የምትበረግግ ማይኳቸው::

አቲዬ ቤተክርስቲያን በር ላይ ደረሰች:: እግዜር ያኔ ለያት:: ከሰማየ ሰማያት ዙፋኑ ላይ እንደተቀመጠ ድምፅ ከወደ ምድር ሰማ:: "ቅዱስ...ቅዱስ..." እያሉ በታላቅ ድምፅ የሚሰግዱና የሚያሸበሽቡ አልፍ አእላፍ መላእክትን "ዝም በሉ አንድ ለየት ያለ ድምፅ ከምድር ሰምቻለሁ" አለ::

"ጌታ ሆይ ሞልቃቆች በስሱ እያማታቡ መኪናቻቸው ውስጥ ሆነው ሸው የሚሉት አይነት ድምፅ ይሆናል" አሉት መላዕክቱ::

"አይደለም" አለ እግዚአብሔር::

"የኮተታሞች የኮተት ጥያቄ ይሆናል" አሉት በምድራዊ ትርኪምርኪ የስጋ ጥያቄ የተማረሩት መላዕክት::

"አይደለም አልኩ እኮ" አለ እግዚአብሔር በታላቅ ድምፅ::

"ጌታ ሆይ! ምናልባት የሀብታሞች 'ከስኳር፣ ከደም ግፊት ከፈወስከኝ መጋረጃ...ዣንጥላ' የሚሉት አይነት የተለመደው ስእለት ይሆን?" ጠየቁ መላዕክቱ::

ዝም አለ እግዚአብሔር !! ዝምታው እንዳች አስፈሪ ነገር አለው:: በዝምታው ውስጥ ፅንፍ የለሽ ሀዘንና ፍቅር ነበር::

ከልጅ ሰጠኝ ንዝንዝ፣ ከስራ ስጠኝ ንትርክም የተለየ ድምፅ ነበር:: ድምፁ ካማረልኝ ብላ የምትዘምር ሴትም አልነበረችም:: 'በታላቅ ግርማ ሞገሰህ በእሳት ሰረገላ ደርሰህ ጠላቴን አፈር ድሜ የምታስበላ የነገስታት ንጉስ:: ከፀሐይ አስራ ዘጠኝ እጅ የምታብራ...' እያለች በተጠና መንፈሳዊ ፉከራ መንፈሳዊ ዘራፍ የምታደነቁር ሴትም አልነበረችም:: ከተሰበረ ልቧ በወጣ ማቃተት ዙፋኑን የነቀነቀችው እዚህ ግቢ የማትባል ሴት ናት:: አንዲት ሴት በሩ ላይ ስትቆም፣ "ማነው የልብሴን ጫፍ በዕምነት የነካው" ብሏል እግዚአብሔር!!

አቲዬ የእኔ ጀግና ማንንም ደጅ አልጠናችም:: በልብሷ መቆሸሸ ይናቋት እንጂ የእኔ እናት ከአዲስ አበባ የሕዝብ ጎርፍ ቁራሽ አልለመነችም:: ለማን ሰሞታ እንደምትናገር እውቃለች:: አጥሩን በድንጋይ ቢያጥር፣ ባማረ መኪና ቢንፈላሰስ፣ ሴቱ በወርቅ ቢሽቆጠቆጥ...የአዲስ አበባ ሰውና አቲዬ ልብ ለልብ ተንቃቅተዋል::

አይታዋለች ሕዝቡን የሀሊናውን ዓይን ጨፍኖ ጎዳና የፈበሱትን የራሱን ጉዶች እንቁልልጭ እያለ በየስጋ ቤቱ በረንዳ ላይ ጥሬ ስጋውን ሲያጋብስ፣ ቢራና ውስኪውን ሲገለብጥ - አይታዋለች::

በረሀብ የተቆራመቱ፣ ልብሳቸው ላያቸው ላይ ያለቀ ሚስኪን ሕፃናት በምኞት ብዛት ገና በሕፃንነታቸው የሲጋ ክምር ከተሸከሙ ብጤዎቻቸው የሚሆኑ ሕፃናት የተረፋቸውን እንዲሰጧቸው እጃቸውን በልመና ሲዘረጉ - አይታለች:: የደሀ ልጆች የሀብታም ልጆችን መኪና እየተከተሉ

ሀም አይታለች:: የተረፈውን ሳንቲም በምፅዋት ሰም ሲወረውር ደግ ይመስላል ሕዝቡ፣ መገባት የደግነት ከበር አያደለቀ 'ደግነት ባህሊ ነው' የሚለው ህዝብ !!

ልብ ፈረሷን ከጎኗ አስቀምጣ በማንበሯ ተደፍታ ስቅስቅ ብላ አለቀሰች:: ቃል አልተነፈሰችም፣ ነት ተነሰታ ቀጥ ብላ ወደ ምፅዋት ማስቀመጫ ሳጥኑ ሄደችና በእጇ የጨበጠችውን ድፍን ሃምሳ ዉ አንጥቶ በጠባቧ የምጽዋት ሽንቁር አስገብታ ፊቷን አዙራ እርምጃዋን ቀጠለች - ባዶዋን !!

ለማለብለር በምድር ላይ ከባዱን ብድር ጥላበት የሄደችውን ቢት እንዲህ አላት::

ሷደሽ አልፍ አጥፍ ብድርሽን እከፍልሻለሁ::" እቴዬ መሀፀን ውስጥ በፅንስነቴ ከተጋባብኝ ሁ በዚህ ቀን መሆን አለበት!! እስከዛሬ ድረስ ትልልቅና ውብ ቤተክርስቲያኖችን ሳይ በእቴዬ ማ ብር የተገነቡ ነው የሚመስለኝ::

ግ ሰትል ፊት ለፊቷ ማንን አገኘች? አባ እስጢፋኖስን !! በተዓምር ማመን የጻዳኝ እቴዬ ደኝን ስትነግረኝ ነው:: አባ እስጢፋኖስ እቴዬን አያዩ፣ "አንች ዘርፌ ቤት የነበርሽው ልጅ ደለሽም እንዴ ?" አሉና ጠየቋት መነፅራቸውን እያስተካከሉ:: አባ እንኳን በዚህ ድንግዝግዝ ሪማ አመሻሽ ቀርቶ በጠራራ ፀሐይ የቤተክርስቲያኑን ዋና በር የሚሰቱ ፅኑ የዐይታ ችግር ለባቸው አባት ነበሩ:: እቴዬን ግን ተመለከቷት_በመነፅራቸው ሳይሆን በእግዚር ዓይኖች !!

ጦ ቀን አባ እስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን ውስጥ እንዷት እናት መነኩሲት የሚኖሩብት የመቃብር ቤት እቴዬን ወስደው አኖሯት:: ሆዷ ውስጥ ወይዚት ምድር ሲቀሳቀል የተዘጋጀ ፅንስ _ከረገጠችው ቢቱ ወለል ሰር ይህቺን ዓለም ጥግብ እስኪል ኖርባት የተሰናበታት የሀብታም ሽማግሌ አፅም.. እቴዬ መሐል ላይ::

## ክፍል ሰባት

እቴዬ ያረፈችባቸው መነኩሲት "የኔ ልጅ አይዞሽ የበላነውን እየበላሽ ልብሽ እስኪፈቅደው ጊዜ ቆዩት ትችያለሽ የእግዜር ቤት ነው..ቤትሽ ነው" አሉና ድርብ የሰሌን ምንጣፍ ብዙ ቦታ ላይ ዘበዙ ዓይነት ከርና መጣፊያ ከተጠቀመ ብርድ ልብስ ጋር ሰጧትና አንዱ ጥግ ላይ ራሳቸው አነጠፉላት::

ኧም ላይ ጭካኔ ሲፈነጭ፣ ማን አሰብኝነት በሀሴት ዋንጫ ልቅሊቃውን ሲያስነካው፣ ሰብዓዊነት ቃብር ቤት ውስጥ በፍፁም ፀጥታ ከእትዬ ጋር ተገኘ:: እቴዬ ከደጓ መነኩሲት ጋር በመቃብር ነት ውስጥ ተቀመጠች:: 'ኑሮ ካሉት መቃብር ይሞቃል' ቢባልም ቅሉ ኑሮው አልሞቃትም:: ሰጓቷ ድረስ ዘልቆ የሚያንዘፈዝፍ የፍርሀት ብርድ ሰላም ነሳት:: 'መሄጃ የለኝም' ከሚል ስጋት ቢሀውም ቢሆን አርፋለች:: ግን መቃብር ቤቱ ውስጥ የነበራት ቆይታ የሲቃይና የፍርሀት ነበር::

ሰው የተቀበረበት ቤት ውስጥ መቶኛቷ ፍርሃት ለቀቀባት:: ከተኛችበት ሰሌን ስር በሰብሰ እፅሙ የቀረ ሬሳ ተኝቷል:: በአፈ ታሪክ እንደሰማችው (አሁንም ድረስ እንደምታምነው) ደግሞ ሙታን አካላቸው ቢጋደምም መንፈሳቸው አርፎ አይቀመጥም...:: መነኩሲቷ ወጣ ካሉ ተከትላ ደጅ ትቆማለች:: እንቅልፍ ሸለብ ሲያደርጋት አንድ ስጋው ሁሉ ረግፎ ጭራሮ የመሰሉ ጣቶቹ ብቻ የቀሩ አጥንታም እጅ የተኛችበትን መሬት ፈንቃቅሎ እንገቷን ሲያንቃት ይታያትና ኡኡታዋን ታቀልጠዋለች...ቅዠት!! መነኩሲቷ አቲዬን ማረጋጋት ለአቲዬ መፀለይ ብቻ ሆነ ስራቸው::

በፍርሀት ሁለት ቀንና ሌሊት እንቅልፍ ሰላልወሰዳት በሦስተኛው ቀን ምሽት እንቅልፍ አሰክሯትና ሰሌኗ ላይ ኩርምት ብላ ተኛች – ዓለም ገፍቶ ገፍቶ የመገነገኛ ሰሌኗ ላይ የጣላት ሚስኪን ቤት፣ መነኩሲቷ በሀዘን ግንባሯን እንደ ትንሽ ልጅ እያሻሹና እተነፋፈሷ የተስተካከለ መሆኑን እያዳመጡ እንደ መልካም ወላጅ ቀስ ብለው ድራቡን አልብሰዋት ወደ ፀሎታቸው ተመለሱ::

ብዙ ሳይቆይ ትንሽዋ የመቃብር ቤት በአሰደንጋጭ ጩኸት ተሞላች:: አቲዬ "ልጄን...ልጄን" እያለች እንደ እብድ ከመኝታዋ በርግጋ በመነሳት ራሷን ይዛ መሮጥ ጀመረች:: አቅመ ደካማዋ መነኩሲት አቲዬን ሊያቆሟት አልቻሉም:: የሷ ባልሆነ ጉልበት ገፈታትራቸው በማገርም ፍጥነት ሰሌኑን ጠቅልላ የቤቱን ወለል በጥፍሯ ትቧጥጥ ጀመረች፣ "ልጄ...ን...ልጄን ወሰዱብኝ..." እያለች በመረገጥ ብዛት የደደረውን አፈር ትመነጭር ጀመረ::

እንባዋ በጉንጮቿ ላይ ለጉድ እየፈሰሰ፣ በላብ ተነክራ እየቃተተች ከትንንሾቹ መቃብር ቤቶች ጩኸቷን ሰምተው የወጡ መነኮሳት ወደ እማሆይ ቤት መጥተው ተረባርበው እስኪያስቆሟት ድረስ አቲዬ በአስሩም ጥፍሯ መሬቱን እየቧጠጠችና እየቆፈረች ኡኡታዋን ማቅለጥ አላቆመችም ነበር::

ከፉ ቅዠት...የዘወትር ቅገሮቷ የሆነው ጭራሮ እጅ ዛሬም ከፈነቀለው መቃብር ውስጥ እጁን ብቻ ሳይሆን ከትከሻው በላይ ነበር ተመዝዞ የወጣው = አፈር እንደለበሰ...!! ከዛም በአስፈሪ ካፖርታው !! "ልጄን እምጪ!" ብሎ አጥንታም እጁን ወደ ሆዷ ላከና በቅፅበት አንድ ቀይ ወደ ውስጥ ወደ መሬት ይዞት ሰረገ...:: ልክ ጫጩት ነጥቆ ወደ ጉድጓዱ እንደሚገባ ሸለምጥማጥ !!መሬቱን ከፍቶ ሲገባ፣ መጋረጃ ገልጦ የገባ ነበር የሚመስለው::

በቀጣዩ ቀን አባ እስጢፋኖስ ሁኔታው ቢነገራቸው ድሮም ለአቲዬ ቋሚ መኖሪያ ሲያፈላልጉ ነበርና ፍለጋውን አፋጥነው ከሁለት ቀን በኋላ በፊት ትኖርበት ወደ ነበረው መንደር ወሰደው አንዲት ከጥናው የቀበሌ አጥር ጋር ተያይዛ የተሰራች የቆርቆሮ ቤት ውስጥ አስገቧት:: የመንደሩ ኢድር እቃ ቀን ፀሐዩ በክፍተቱ ውስጥ እያሰፈ ይገባ ነበር:: አባ እስጢፋኖስ ከንሰሀ ልጆቻቸው ለምነውም ተለማምጠውም ያገኟቸውን አሮጌ ፍራሽ፣ ብርድ ልብስና የውሀ መያዣ ጎማ ለአቲ እያሰሩ

...ዉሮ ለንገዴሀ ለኔ እንደምታውቂው ቤሳ ቤስቱን የሌለኝ የእግዜር እንግዳ ነኝ፡፡ ከዚህ የተሻለ ...ዬ ለላገኙሉሽም፡፡ ባይሆን ጎንሽን ማሳረፊያ ካገኘሽ ሌላው ሌላው በፈጣሪ ፈቃድ ቀስ እያለ ...ማል፡፡ እኔም እየመጣሁ እይሻለሁ፡፡" ብለዋት ሄዱ፡፡

## ክፍል ስምንት

...ሽና ድንኳን፣ እንጨቶች፣ ወንበሮችና ስጋጃ ምንጣፎች በአንድ በኩል ተሰድረው ገባ ብሎ ...ዉ ውስጥ ባለችው ትርፍ ቦታ ላይ ደግሞ የአቲዩ ፍራሽ ተዘርግታለች፡፡ ብዙ ጊዜ ሞት ...ም መርዶ ስለሚኖር የእድሩ እቃ አይኖርም፡፡ ስለዚህ ሰፋ ትላለች ቤቷ፡፡ አንዳንዴ ደግሞ ...ኛው እቃውን ሲመልስ በግዴለሽነት ወንበሩን፣ እንጨቱን ከባባዶቹን ምንጣፎች አቲዩ ...ታ ላይ ጥለውት ይሄዱ ስለነበር ያንን ሁሉ ጓዝ ጎትቶ ቦታ ማስያዙ ለአንዲት ነፍስ ጡር ...ተ ፈተና ነበር፡፡

...ዩ ግን ታደርገዋለች፣ "እንዲህ አታድርጉ" እትል ነገር ሆሆ...ወይ፣ ውጪ ቢሏትስ፡፡

...ባ አስጢፋኖስ ብዙ ቤት ሊያስቀጥሯት ደክመው ነበር፡፡ ይሁንና ቀጣሪዎቹ ነፍስ ጡር ...ዋን ሲሰሙ ሁሉም አቲዩን ቤታቸው ማስገባት አልፈለጉም፡፡ አባ ቢጨንቃቸው የአቲዩ ...ሪ ሰላም ቢነሳቸው አቲዩን ለዚህ ሁሉ መከራ የዳረገቻት ዘርፌ ቤት ሳይቀር ሄዱና፣ "እችን ...ዘ ይቅር በያት ባክሽ" ብለው ተማፀኑ፡፡

"...ይደይይ...አባ ምነው እያወቁት... እንደ ልጆቼ እንከባክቤ በያዝኩ አይደለም እንዴ ጥጋብ ...ቅላት ለመንደሩ ሁሉ ስሜን አጥፍታው የሄደች..." አለች አቃጣሪዋ፡፡ አባን በአፍ መሸንገል ...ግዜርን መሸንገል ይመስል የአቲዩን በደለኝነት ስትዘረዝር ደስ እያላት ነበር፡፡

"...ፍ አይደለችም እንዴ ጠላተማሪያም...ደግሞስ አንች ቤት ከመቼ ወዲህ ነው ይቅርታ የነጠፈው ...ዪ...እንጂ" አሉ አባ፡፡

"...ብኛ አባ በዛብኝ ...ምን በደልኩ እናት በሆንኳት...የበላሁትን ባበላሁ የለበስኩትን ባለበስኩ ...ው ሆኝ! ስልጥኝ!' ባልኩ - ይሄ ይገባኝ ነበር?" እንባ እየተናነቃት አባ ፊት በደሏን ዘረዘረች... ...ች አስመሳይ!!

"...ሄው የትም ስትንዘላዘል ዲቃላዋን ይዛ አረፈችው" አለች ዘርፌ፡፡ "ከእኔ የተጣላ አጣ ፋንታው ...ቃት ነው..." ልትል እየዳዳት...፡፡

...ባ እንደሆኑ የአቲዩን ነፍስ መታደግ ይቅደም ብለው እንጂ የቀለመመርቅንና የዘርፌን ሴራ ...ብጣቸው ያውቁዋል፡፡ አንዳንዴ 'የእግዜር እንግዳ ከመሆን ሸፍታ በሆንኩ፣ ነፍስ ገዳይ ...ሆንኩ' የሚያስብሉ እንደ ዘርፌ ዓይነት ገርፈው የሚያጮሁ ጅራፎች ሲያጋጥሙ የንስሀ አባቶች

ልብ ምን ያህል ይሰበር ይሆን?! ቢቻል ጥምጣምና መስቀልን ላንዴ አስቀምጦ ምንሽር መታጠቅና እንዲህ አይነቶቹን አድሜ ጠገብ አባቦች ማንባር ግንባራቸውን ማለት ነበር፡፡

ዘርፌ ከዚህ ሁሉ ፉከራና ማስመሰል በኋላ አቴዬን ቤቷ እንደማትመልሳትና ከፈለገች በተመላላሽ ላሞቹን የመንከባከብ ልብስ የማጠብ ስራ እንድትሰራ በወር ፲ ብር ልትከፍላት ለአባ ቃል ገባች፡፡

"ያው ለነፍሴ ብዬ እንጂ የደረሰች እርጉዝ ምኗ..." አለቻቸው ለአባ፡፡

"ማይደለም ወለተማሪያም መቼስ ሰው እንዳረገዘ አይኖር...ሁሉ ነገር ሲወለድ ጊዜ አለው፡፡ ደግሞ ይሁን ከፉ ተረግዞ አይቀርም፤ ነገን ነው ማየት" አሉ አባ፡፡ የቄስ ምንሽሩ ቅኔ ነው - ተከሰባት አባ!!

የቅኔ ጥይት ከተኳሹ እስከ ኢላማው ለመድረስ ጊዜ ይወስዳል፡፡ ለዛ ነው ዘርፌ አባ አግር ስር ድፍት ያላለችው - ይድፉትና!! አባ እውነት ነበራቸው፤ እንደ ተረገዘ የሚኖር በደል የለም ይወለዳል አንድ ቀን፡፡

አቴዬ በሁሪያ ገጠም እጣፋንታዋ ዙራ ዘርፌ ቤት ገባች (ዞሮ ዞሮ መግቢያው ጭራሮ አያለ መንደሩ... አውር ቢሸፍት ጓሮ ድረስ ነው እያለ አሽሟጣጨ...) እንደገና ወተት ማለብ፤ እንደገና አዛባ መዛቅ፤ እንደገና ጉልበቷን መገፍገፍ...ያውም ቀጥ ብላ አመቤቷን በማታይበት የሞራል መዳሸቅ ተተብትባ - የበደሏትን ይቅርታ ጠይቃ፡፡ የዘርፌ ደግነት ግን በመንደሩ ተወራ፡፡ "መልሳ ተቀብለቻት እኮ ዘርፌ ሆዷ ቂም አይቋጥር..." እየተባለ፡፡

አቴ አባባ ያገኙላት የቆርቆሮ ቤት ውስጥ እየኖረች፤ ለመንደሩ ሰው ሁሉ የቀን ሥራ እየሰራች ኑሮዋን ጀመረች፡፡ ዘርፌን በድላ በመመለሷ እንደተማረከ ባሪያ ጉልበቷን ትገፈገፍ ጀመር፡፡ የመንደሩ ሰው ሁሉ ዳኛ...ወንጀለኛው ሁሉ ፈራጅ ሆነ እናቴ ላይ!! የማያሰሯት ነገር አልነበረም፡፡

እነዚህ ባሎቻቸው ከየመሸታ ቤቱ እያነሱ፤ ከየመንገዱ እየሲቃቀሙ፤ ከየገጠሩ እያመጡ ሰው ያደረጓቸው...ጊዜ ያነሳቸው ቅሎች ለፍቶ በመኖር፤ አምላክን በማመን በእጆቿ ንፁህ ፍሬ የምትኖር እናቴን ብረት መንፈስ ሰበሩ፡፡

ጊዜ ያነሳው ቅል እንኳን ድንጋይ ብረት ይሰብራል!!

እጠላቸዋለሁ...!!

በባሎቻቸው ገንዘብ እድሚያቸውን የሚገፉ፤ ሰማኒያ በሚባል ህጋዊ ፈቃድ የባሎቻቸውን ዳረጎት እየተቀበሉ የሚዘባነኑ የሰማኒያ ሲማኞች፡፡ ሰማኒያ የሚሉት፤ ፍቅር ሲያልፍ ያልነካው የልመና ንግድ ፈቃዳቸው ቢቀደድ ከአቴዬ የባሰ አዘቅት ውስጥ የሚወድቁ ሁሉ ሚስኪን እናቴ ላይ ተዘባነኑባት፡፡

"ምነው ይሄ ምንጣፍ እንዳልረባ ነገር እዚህ ተጣለ?" ይላል አንዱ ጎረቤት ወደ አንዱ ጥግ የዘመን ቆሻሻውን ተሸክሞ ወደ ተጣለ አሮጌ ምንጣፍ ኢያሳየ::

"አየ...አፈር ተሸክሞ በስብሶ ማን እሱን ይታገላል?" ትላለች ባለቤት ተብዬዋ...ትላንት የከሰል ጆንያ ሳይቀር የምታጥብ የነበረች...ከሰራተኝነት ወደ ሚስትነት በአንድ ሌሊት የአልጋ ወለምታ የተሸጋገረች መሆኗን አገር ኢያውቀ::

"ግድለሽም አፀደ ግማሽ ቀን ብትውልበት አበባ ይመስላል" ይላል መካሪው::

እቴን ይጠሩና ያዟታል:: ግማሽ ቀን ጭቃ ታጥባለች:: እንዳሉትም አበባ ይመስላል ምንጣፉ...፤ "አቤት ቤት አያያዝ ! የምንጣፏ ንጣት ብቻ ለመርገጥ ያሳዝናል እኮ እከሊት ! የእሷ ባል ሚስት አገባሁ ይበል..." ይባልላታል:: ተወዝፋ እቴዬን ቁራሽ በማይገዛ ብር መንደር የሚያለብስ ምንጣፍ ያሳጠበች እከሊትን፤ በእናቴ ጉልበት የምሲጋና ካባ ይደርቡላታል::

"አፀደ በይ እችን ያዥ" ትልና ስስት ብር ትሰጣታለች:: እቴዬ ተቀብላ ወደ ማደሪያዋ ትመለሳለች . እትከራከርም:: ይሄንንም እንደብልጠት ይወስዱታል:: በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ የደሀን ጉልበት ከነፃ በሚጠጋጋ ክፍያ መበዝበዝን እንደብልጠት ያዩታል::

ቀናቸው የተዳረስ እርጉዝ አስሪዎች ሰላሳ ትራስ ደልድለው በረንዳቸው ላይ ይቀመጡና ቀኗ የደረሰ እናቴን፣ "በደንብ እሺው እንጂ" እያሉ ልብስ ያሳጥቧታል:: ለዘመናት በስንፍናቸው ቤታቸው የከመሩትን ቆሻሻ ሲያስፀዷት ይውላሉ:: 'እንኳን ማሪያም ማረችሽ!' የሚል ጠያቂ ቤታቸውን እንዳይታዘብ...የበከተ ቤታቸውን...ከቅዱስ ዮሐንስ እስከ ቅዱስ ዮሐንስ ውሀ ነክቶት የማያውቅ መጋረጃቸውን ያሳጥቧታል !! ወይስ ከእርጉዝ እርጉዝ ይለያል...:: የደሀ እርግዝና ቢጨነግፍም እዳው ገብስ ነው ዓይነት ፍዳዋን ያበሏት ነበር እናቴን...::

ለምን ለፋች አይደለም የምለው ! ግን የለፋችበትን የላቧን ዋጋ ከልከለዋታል:: እፈር ያብላቸውና የደም ገንዘብ የበሉ ናቸው:: ዳሌያቸውን እያገማሸሩ ወንድ የሚያሳድዱ ቤት ልጆቻቸው እቴዬ ከእርግዝና ህመም ጋር እየታገለች ያጠበችውን ልብስ የለበሱ እርኩሳን ናቸው...:: ሕፃናት ልጆቻቸው በየሜዳው ሲንከባለሉ እናቶቹ በሳምንቱ መጨረሻ ስለሚደክመው የእቴዬ ጉልበት ሳይሆን ስለሳሙናቸው ነበር የሚጨነቁት፣ 'አንተ ልጅ ኧረ የሳሙና ጡር አለው' እያሉ:: እቴዬ ቃል ሳትተነፍስ ማንንም ሳታማርር እስከ ወለደችበት ቀን ድረስ ስትሰራ ነበር...::

## ክፍል ዘጠኝ

እኔ የተወለድኩ ቀን ጠዋት እቴዬ 'እቃጣሪዋ ዘርፌ' ቤት ወተት ስታልብ ነበር:: ረፋዱ ላይ የአንዲት ጎረቤት በርበሬ ስትቀነጥስ ዋለች:: ውጋት ሲጀምራትና ምጡ ሲሟናት ከበርበሬ ቅንጠሳው በኋላ ልብስ ወደምታጥብበት ቤት ለመሄድ እየተዘጋጀች ነበር:: ህመሙ ሲጀምራት

ግን መንገዷን ቀይራ ወደ መንደር አዋላጇ አልማዝ ቤት ሄዳ እየፈራች፣ "እትዬ አልማዝ እያመመኝ ነው፡፡ ምጥ ነው መሰለኝ..." አለቻት፡፡

"ውይ በሞትኩት...መጣሁ ሂጂና ቤትሽ አረፍ በይ..." አለቻት፡፡

እቴዬ እንደታዘዘችው አደረገች፡፡ አዛች አሮጌ ፍራሽ ላይ ተኝታ ምጥ እየናጣት በር በሩን ማየት ጀመረች፡፡ አልማዝ ግን ወደ እቴዬ አልሄደችላትም፡፡ ምክንያቱም እቴዬ ምጥ የተያዘች ቀን፣ ዘርፌ የምትባለዋ እቃጣሪ ባልቴት የአሜሪካ ላሟ ያልታወቀ ነገር በልታ ሆዷ ተቆዝሮና አረፋ ደፍቃ እየጓጎረች ስለነበር፣ መንደርተኛው ሁሉ ወደዚያው ሄዶ ነበር፡፡ አዋላጇ አልማዝም ቅድሚያ ለዘርፌ ላም ሰጥታ ነበር፡፡

እንድ ግብርና የሚሰራ የእንስሳት ህክምና ባለሙያ ተጠርቶ እስከራብቶ በሚመስል ነገር የላሟን ሆድ ወግቶ ካስተነፈሳት በኋላ ላሟ ነፍሷ መለሰ በማለቱ የመንደሩ ሰው ደስታውን በእልልታ ገለፀ፡፡

በዚህ መሐል አዋላጇ አልማዝ፣ "በሞትኩት ያች ሚስኪን ምን ደርሳ ይሆን?" ብላ ወደ ቤታችን ተጣድፋ ብትደርስ እቴዬ እኔን አቅፋ አገኘቻት፡፡ 'የወርቅ ፍሊቃቂ' የመሰልኩ እኔ፣ በእሳት የተፈተንኩና የጥላቻ እሳት የምተፋ እኔ፣ እላፊ አግዳሚውን የምራገም እኔ በእናቴ እቅፍ ላይ!!

ታሪክ ይወቀኝም አይወቀኝም፣ እናት የተባለች ታላቅ ሀገር ከስግብግብ፣ ከአስመሳይ፣ ከራስ ወዳድ፣ ከአሽቃባጭ፣ ደሀ ከማይወድ፣ እምነት ከሌለው፣ ሆድ አምላኩ ከሆነ አመንዝራ እና ጨካኝ ጎረቤት ቅኝ ግዛት የወጣሁ ጀግና እኔ ተወለድኩ !! አገሬ እናቴ አፀደ ናት ! ባንዲራዬም የእናቴ ቀለም አልባ አሮጌ ቀሚስ !! ድምጿ መዝሙሬ ነው፣ ትዕዛዟ ሕገ መንግስቴ !! እናቴ አፀደ ወይንም ሞት!! እቴዬ ትቅደም !! እቴዬ ለዘላለም ትኑር!

መዝሙሬ...፣

*ተንቀሽ የኖርሽው ድሮ ከዚህ ቀደም፣*

*ለናቴ አፀደ የደፈረሽ ይውደም !!*

በሰሜን ስግብግብ የደሀ ደም መጣጭ ጎረቤቶች፣ በደቡብ ራስ ወዳድ በደሀ እምባ የሚዋኙ እጋሰሶች፣ በምስራቅ የእናቴን ፀሐይ እንዳትወጣ የሚጋርዱ አስመሳይና ሆዳሞች፣ በምዕራብ ሚስኪን ቤት ደፋሪዎች እና ትውልድ የሚክዱ ካፖርታሞች...፡፡ ከታች በባዶ እግሯ የምትረግጠው ምድር፣ ከላይ እግዚአብሔር (የባህር በሯ) የሚያዋስናት ሀገር አፀደ ትባላለች - የእኔ አገር እሷ ናት !!

አፀደ ከሰማይ ዱብ እንዳለ ጉድ ዘመድ የላትም፡፡ እናት፣ አባት፣ እክስት፣ እኅት የላትም፡፡

ለልተማረችም፤ ገንዘብም የላትም:: ግን ሁሉ በእጁ ሁሉ በደጁ ለሆን ባለፀጋ እግዚያብሔር አንገና ድፍን የኢትዮጲያ ሃምሳ ብር ያበደረች ልበ ሙሉ ሴት ናት:: እግዚያብሔርም የማንም ብድር በእጁ ይቆይ ዘንድ አይወድምና ብድሩን ይከፍል ዘንድ እኔን መንገድ አደረገ:: ለድፍን ሀያ ለምስት ዓመታትም አነፀኝ - ደለደለኝ::

እግዚአብሔር ፈጠነም ዘገየም ወደ እያንዳንዱ ሰው ሕይወት ውስጥ ይመጣል:: ሲመጣ የእግዜርን እርምጃ የሚገሩንም ዳና የሚቋቋም መንገድ የሚሰራው 'መከራ' በሚባል ኮንክሪት ነው :: ዙሪያህን የከበበህን ችግርና እልህ አስጨራሽ የሕይወት ፈተና ስታልፍ፣ የእግዜር የመጀመሪያ እርምጃ ትጀምራለች:: ያኔ ታዲያ ርሀብን ብቻ ሳይሆን ጥጋብንም የምትችል አድርጎ እንዳነፀህ ይገባሀል::

ስራሩ እንደዛ ነው፤ ባይሆንም እኔ እንደዛ ነው እላለሁ:: አንተን ከድሀነት ማውጣት ብቻ ባይሆን መጭውን የጥጋብ ዘመንም የሚሸከም ትከሻ እንዲኖርህ አድርጎ ይሰራሀል:: ካላመንክ እንደየሃይማኖትህ መጽሀፍህን ግለጥ፣ አዱኒያን እንደ ምናምንቴ ንቀው ፈጣሪን ያመኑ፣ የተከተሉ ሁሉ በፈርህ ሕንፃ አቁሞ እንደሚሸልለው እብሪተኛ ሃብታም ባንዴ ሰማይ ጥግ አልደረሱም::

ፈጣሪ ሲሰራህ ቀስ ብሎ ነው፣ ግን መቼም እንዳትፈርስ አድርጎ:: ያኔ ደስ ይልሃል - ወደህ ነው፤ ገንበስ ብለህ ታመሰግናለህ - በግድህ !! አንተ ሳለማመስገን ብትጥር እንኳን ስጋህ ያማረ ፍራሽ ላይ ለሽ ሲል፣ በርሀብ የተንሰፈሰፈ አንጀትህ ውስጥ የጣመ ምግብ ሲንዠቀዠቅ፣ በላዩ ላይ ጥሩ ቡና ስትጨምርበት፣ ከምንም በላይ ደግሞ ራስህን ስትገዛና ልብህ በሰላም ሲሞላ፣ "እግዚያብሔር ይመስገን" ይልብሀል አፍህ ከአንተ ትዕዛዝ ውጭ!!

## ክፍል አስር

አቲዬ እኔን ከወለደች በኋላ ትንሽ ተሰፋ ልቧ ውስጥ አደረ:: 'አባቱ በልጁ አይጨክንም መቼም' ብላ:: ግን አባት በልጁ ጨከነ:: 'ቀለመ ወርቅ' አባት የመሆን ሞራሉም ብቃቱም የሌለው ሴሰኛ ሽማግሌ መሆኑን የአቲዬ ልብ ያወቀው ብዙ ቆይቶ ነበር:: ወንዶች ለአገር ዳር ድንበር ለየፎከሩና እየሸለሉ የመዝመታቸውን ያህል አባትነትን ለመቀበል፣ ትዳርንም 'አሜን!' ብሎ ለመኖር፣ ከነፍሳቸው ጋር የሚገጥሙት ጦርነት ቀላል አይደለም:: ለመውለድ ወንድ መሆን በቂ ነው፣ አባት መሆን ግን ታላቅ ጀግንነትን ይጠይቃል:: ቀለመወርቅ ደግሞ ጀግና አልነበረም:: ስለዚህ እኔን ልጁን ዶሮ ሳይጮህ ሦስቴ ካደኝ::

አቲዬ የእኔ ብርቱ ግን በሰባት ቀኗ ከአራስ ቤቷ ተነስታ ምንም እንዳልተፈጠረ ሁሉ ስራዋን ጀመረች:: "እረ ወገብሽ ይጥና" ያላት አልነበረም:: የበሰበሰ ድሪቷቸውን ከምረው ጠበቃት እንጂ !! 'የምትገርሚ ጠንካራ ልጅ' እያሉ:: አርባ ቀን ሙሉ ተዘፍዝፈው ሲጣቸውን ሲያሸምዱ ኖረው ሲወጡ እንኳን እራስነት ምን ያህል ከባድ መሆኑን እንደማያውቁ ሁሉ፣ አቲዬን በሥራ

ሲያጣድፏት ምንም አልከበዳቸው፡፡

ልጅ ይዛ ሥራ መሥራት ከባድ ነበር ለአቲዬ፡፡ በየቤቱ በረንዳ ላይ እያስተኛች ባለቅበባት እያጠባችኝ(ምናባቴ እንደሚያስለቅሰኝ አንጃ !)፡፡ አቲዬ እናቴ ብርቱ ሰው ከህይወት ጋር ትግሏን ቀጠለች...አንድ...ሁለት...ሦስት...አራት ወር -ለአቃጣሪዋ ዘርፌ አቲ እየፈራች እንዲህ አለቻት፤

"አትዬ...እኔ እንግዲህ እስካሁን ለልጁ አንድ ነገር ያደርጋሉ ብዬ ጠበቅኳቸው እሳቸው ግን..."

"ማናቸው ልጄ..." አለች ዘርፌ አካሄዱ አላምር ብሏት ፊቷን እጨፍግጋ፡፡

"ጋሽ ቀለመወርቅ" አለች አቲ፡፡

"እህ...ደሞ እሱ ምን ቤት ነው ባንች ልጅ..."

"እትዬ...ፈርቼ አልነገርኩትም እንጂ፣ እኔ ሌላም ወንድ ነክቶኝ አያውቅ ተሳቸው ነው..."

"ወዲያ ዝም በይ...ምን ትላለች እቺ...የተከበረ ሰው እናት ዘሎ ፊጥ ማለት ምን ይሉት ብልግና ነው?! ሁለተኛ እንዲህ ያለ ነውር ስትተነፍሽ ብሰማ ውርድ ከራሴ...፡፡ ሂጂ አሁን ወዲያ ያው ደሞዝሽ!"

ብላ አስር ብር ወረወረችላት፡፡ ስራዋ አስደንግጧት እንጂ ሳምንት ነው ገና ደሞዝ ለአቲ ከከፈለቻት፡፡

ቀለመወርቅ ይህችን ጭምጭምታ ሲሰማ ተንኮሉን ጀመረው፡፡ አቲዬን ከመንደሩ ሊነቅል እንቅልፍ አጣ፡፡ አቲዬ ለአባ እስጢፋኖስ ሽምግልና ላከችበት፡፡

"ቀለመወርቅ መቼስ ዘር አይጠላም፡፡ ነገ የት እንደሚደርስ አንድ ፈጣሪ ነው የሚያውቀው፡፡ ሌላው ቢቀር የወተት መግዣ እንኳን ስጣት መቼስ እሷ ጋር እንዲህ ሠራህ፣ እንዲህ አደረግክ ለማለት ባልደፍርም ልጁ ቆርጠው የጣሉት አንተን ነው..."

"ምን ማለተዎ ነው አባ...እኔን በእንዲህ ያለው ቅሌት እንዴት ይገምቱኛል?" ብሎ በአባ ከፋኛ ተቆጣ፡፡ ቀለመወርቅ ሽምጥጥ አድርጎ ካደ !! መቸም ቁርጥ አድርገው የጣሉት ሰይጣን ነው፤ ይባስ ብሎ ከዘርፌ ጀምሮ መንደርተኛው ሁሉ አቲዬን ሥራ ማሠራቱን እንዲያቆም ተንኮል ይሸርብ ጀመረ - ተሳካለት፡፡ አንድ መንደር ሕዝብ እንዴት ደሀ ላይ አመፀ፡፡ ቀለመወርቅ እና ዘርፌ ነበሩ የተንኮል ድሩ ፈታዮች፡፡

"ነገ ባልሽን ስመን ብታጠፋውስ...ሰው እንደሆነ አንች ቤት ልብስ ማጠቧን፣ ገባ ወጣ ማለቷን ነው የሚያየው" ይሏታል ለአንዷ እሰሪ፡፡

"ነውነትዎትን ነው እትዬ ዘርፌ ለአቶ ቀለመወርቅ ያልተመለሰች እች..." ትላለች:: በቃ አቲዬን ወሰበብ አሰባብብ ታባርራታለች፣ "ውይ ትላንት ልጆቹ አጠቡት ልብሱን" በቃ !!

አቲዬ ግራ ገባት:: እኔን እዝላ ስትንከራተት ትውልና የሚሠራ ሥራ አጥታ ማታ ቤት ትመለሳለች:: ቤት ውስጥ የነበረችው ርጋፊ በሶ ብቻ ነበረች:: ወደማታውቀው መንደር እየሄደች፣ "የሚታጠብ ልብስ አላችሁ?" ትላለች::

"የለንም::"

"ወፍጮ የሚሄድ እህል በርበሬ ካለ..."

"የለም...የለም" ይላሉ ያዘለችውን ልጅ እያዩ::

አቲዬ ተንከራተተች:: በመጨረሻም ያላት አማራጭ ልጇ በርሀብ ከሚሞት ቀለመወርቅ እግር ላይ ወድቃ "ይማሩኝ!" ማለት ነው:: ቀለመወርቅ - ቀጣፊው ነብይ እሱ በመንደሩ "ይታሰር" ያለውን ሥራ ሰይጣን በድፍን አዲስአበባ ያስረዋል:: አቲዬ "ይቅር ይበሉኝ ልጄ የአርሰዎ አይደለም ቢቸግረኝ ነው ከፉ የተናገርኩት" ልትል ወደ ቀለመወርቅ ቤት ገሰገሰች::

ለከፋቱ ደግሞ ዓይን የለ አፍንጫ፣ ፀጉር የለ ጆሮ እኔ ቁርጥ ቀለመወርቅን ነበር የምመስለው:: ለክህደት የማልመች ጉድ:: ቀለመወርቅ ብቻውን የወለደኝ ይመስል አቲዬን የሚመስል አንዲት ነገር የለኝም:: የቀለመወርቅን የልጅነት ፎቶ ቁጭ!! ቢሆንም "ይቅር በለኝ ልጅህ አይደለሁም" ልል በእናቴ ጀርባ ላይ ወደ አባቴ እየሄድኩ ነው - አባት ያሳጣውን:: ይሄ የውሸ ልጅ !!

ቀለመወርቅ የእድር ዳኛው ጋር ተነጋግሮ አቲዬን ከማደሪያዋ ሊያፈናቅላት ሲዶልት እንዳመሸ የዘርፌ ሠራተኛ ለአቲዬ ሹክ ብላት ነበር:: ለይቅርታ የባሰ ያሮጣት አንዱ ጉዳይም ይሄ ነው:: ደግነት ጥግ እንደሌለው ሁሉ ከፋትም መጨረሻ የለውም:: ይሄ ከፉ አቲዬን ማሳደዱን በትጋት ተያይዞት ነበር:: እናም አቲዬ ይቅርታ ልትጠይቅ፣ "ማረኝ ጌታዬ" ልትለው ወደ ቤቱ ሄደች::

ወዳጄ...እግዜር ይቅርታ ይወዳል ማለት 'ማንም ጥጋበኛ እግር ስር እየሄድክ እንድትደፋ ይሻል' ማለት አይደለም:: አቲዬ የእኔን የልጇን ነፍስ ለማትረፍ ራሱን በፈጣሪ ቦታ አስቀምጦ ይቅርታ ሊጠየቅ የተዘጋጀው ካ?ርታሙ ቀለመወርቅ ቤት ልክ በሩ ላይ ስትደርስ እና የግቢውን በር ሊታንኳኳ እጇን ስታነሳ፣ እግዜር "ተመለሽ" አላት:: ያው እንግዲህ እግዜር ሲናገር በሰው አይደል...::

የእድር ለፋፊው ጉልማው እሳት ጎርሶ እሳት ለብሶ አቲዬን ከኋላዋ በቁጣ ጠራት:: በስሟ አይደለም፣ "አንቺ...አንቺን እኮ ነው:: ምን ያለችው ናት ጃል" እያለ:: እቲ እየተጣደፈ ወደ እርሷ የሚመጣውን ለፋፊ ቆማ ጠበቀችው:: አጠገቧ ሲደርስ፣ "ምን መሆንሽ ነው አንቺ ሴትዮ የአዙሪት ቅጣል ረግጠሻል እንዴ?" አለ::

"ምነው?" አለች ግራ ገብቷት፡፡

"ምነው ትለኛለች እንዴ፣ በይ ነይ አሁን፡ እቃ ማስቀመጫ ቤቱን ከፈቸላቸው፡፡ ሰው ሞቶ ድንኳን ልናወጣ ብንል ቁልፍ ይዞሽ ጠፋሽ፡፡ አገር ተረፈ እንዴ፣ ያልኳተንኩበት የለም እንቅን ፍለጋ" አለ በማማረር፡፡ አቲዬ ቁልፍ ልትሰጠው እስባ አንድ እቃ ቢጠፋስ ብላ በለፈራች የሰውየውን የማያቋርጥ ድንፋታ እየሰማች ይቅርታው ይቆየኝ ብላ ወደ እድሩ እቃ ማስቀመጫ ቤት ተመለሱ፤ ለፋፊው መንገዱን ሙሉ እየነተረከች ነበር አቲዬን፡፡

"አገር ተረፈኝ እንዴ...ዘርፌ ቤት፡ ከዘርፌ ቤት ጀሚላ ቤት፡ ጀሚላ 'ወደ ላይ ሄደች' ብትለኝ ዝናሽ ቤት፡ ዝናሽ..." አንዳንዱ ሰው አያባራም፡፡ ከእሱ ያነሰ ሰው ያገኘ ሲመስለው ሌሎች ያሉትን ሁሉ ይዘረግፋል፡፡ ሌሎች በናቁት ልክ ሊንቅ ይፍገመገማል፡፡

እቃ ቤቱ ሲደርሱ ብዙ ሰዎች ተሰብስበው ነበር፡፡ ነጭ የእቃ መጫኛ መኪናም ቆማለች፡፡ መኪናዋ ጎን ነጠላዋን ያዘቀዘቀች ሴት፣ ጀርባዋ ላይ ፎጣ ጣል ያደረገች ፀጉሯን በሻሽ አስራ ከቀሚሷ ስር ቱታ ሱሪ፣ የቱታውን ጫፍ ካልሲዋ ውስጥ ጠቅጥቃ ነጭ ሸራ ጫማ የተጫማች ደልደል ያለች ቀይ ወይዘሮ ቆማለች፡፡ (የአዲስ አበባ ሴቶች ሀዘን ማካበድ ይችሉበታል፡፡ ትጥቃቸው ሲታይ ዘመቻ የሚሄዱ እኮ ነው የሚመስሉት፡ የሟችን ነፍስ ሊያስመልሱ ያሰቡ የከተማ አርበኞች...)

እች ከራስ ሻሽዋ እስከ እግር ካልሲዋ የነገርኳችሁ ወይዘሮ እጥፍ ወርቅ ትባላለች፡፡ ዋናው መንገድ ላይ ወደ ግራ ታጥፎ ከሹልቃ ክትፎ ቤት አጠገብ ያለው ባለ ሁለት ፎቅ ሆቴል የእርሷ ነበር፡፡ ጋሪ መቆሚያው አጠገብ ነዳጅ ማደያው ኋላ ያለው ሰፊ ግቢ መኖሪያ ቤቷ ነው፡፡ እና እች ሀብታም ሴት፡ አቲዬ ተጠርታ ከመድረሷ በፊት በወሬ ወሬ፡

"ዘበኛው ነው የጠፋው ?" ትላለች፡፡

"አይ እዚህ የምትኖረው ልጅ ናት" አላት የእድሩ ሊቀመንበር፡፡

"እዚህ መጋዘን ውስጥ ሰው ይኖራል ያውም ሴት ልጅ?" አለች ከልቧ ደንግጣ፡፡

በቆርቆሮ ቤቱ ዙሪያ የሽንት መሽኛ፡ ቆሻሻ መድፊያ ቦታ ሲሆን፣ እዛ አካባቢ ለደቂቃ መቆም እንኳን ከርፋቱ አይጣል ነበር፡፡ በቤቱ ጥግጥግ ሳርና ቅጠላቅጠል አብቅሎበት መቃብር ቤት አስመስሎታል፡፡ ጣሪያውም ላይ ሀረግ ተንዠርግጓል፡፡ በቀንም የሚያስፈራ ቤት ነበር እንኳ በሌሊት፡፡

አቲዬ ስትደርስ የሴትዬዋ ድንጋጤ እና ሀዘን ጨመረ፡፡ ከጎኗ ለቆመው ሰው፣ "ጭራሽ ሕፃ ልጅም ይዛ ነው እዚህ የምትኖረው?" አለችው፡፡

"እዚሁ ነው እኮ የወለደችው" አላት የእድር ሊቀመንበሩ:: ቤትዬዋ አንጀቷ ተንሰፈሰፈ:: ቤቱ ሲከፈት እች ቤት ጉዱን ልየው ብላ ወደ ውስጥ ተራመደች::

"እትዬ እጥፍወርቅ ሽሬ እቧራ ነው ጉንፋን ያስይዝሻል" እያሉ ተንጫጩ የእድሩ ሰዎች:: እፍንጫ ያለት ፍጥረት እች ቤት ብቻ ትመስል:: ወይዘሮ እጥፍወርቅ ግን ወደ ውስጥ ገብታ የእቲዬንና የእኔን መኺታ ተመለከተች:: የተበሳሳውን የቤቱን ግድግዳና ጣሪያ በታላቅ ሀዘን ቃኘች:: በራሷ ዓይን ሳይሆን በእማዜር ዓይን:: እናም ሁለት ጊዜ እስነጠሰችና እቲዬን እንዲህ አለቻት፣

"እሁንኑ የምትፈልጊውን እቃሽን መኪና ላይ ጫኚ:: እኔ ቤት ትኖሪያለሽ:: ማነህ ና አግዛትም" አለቻው የእድሩን ለፋፊ:: ዕቃችን የቆመችው መኪና ላይ ተጫነ:: (ወጉ አይቀር ዕቃ ልበል እንጂ) የእድር ለፋፊው ማውራቱን አላቋረጠም፣ "ያንች ዕጣ ፋንታ እንደ መብራት ሲበራ እኔ ከላምበስት ሳንቲም እንዲህ መኳተን...ነገ ሰው ብትሆኚ አንድ ዋንጫ ጠላ አትይኚም:: አውቀዋለሁ እጄ አመድ አፋሽ ነው:: አገር ቀረኝ እንጂ፣ ዘርፌ ቤት የለችም ሲሉኝ..." እንደ አዲስ ጀመረ...::

## ክፍል አስራ አንድ

እቲዬ ለመርገጥ የሚያስፈራው የወይዘሮ እጥፍወርቅ ግቢ ውስጥ አንዲት ቆንጆ ሠርቪስ ቤት ተሰጣቻት:: ያውም ከነሙሉ ዕቃው::

"ማነው ስምሽ እናቱ?" አለቻት እቲዬን ወይዘሮ እጥፍወርቅ::

"እጠደ"

"ውይ የኔ ድንቡሽቡሽ! ስንት ወሩ ነው?" አለች እኔን እያየች::

"እሁን የፊታችን ገብርኤል መንፈቅ ይሞላዋል" እጇን ወደኔ ዘረጋች:: ፈገግ ብዬ እጇን ለቀምኩ:: 'ሕፃናትን መለይከው ይመራቸዋል' የሚባለው እውነት ሳይሆን አይቀርም:: ወይም ቤትዬዋ እጅ ላይ የተገጠገጠው የወርቅ ቀለበትና ጌጣጌጥ መጫወቻ መስሎኝ:: ወይዘሮ እጥፍወርቅ እቲዬን እንዲህ አለቻት፤

"ላንችና ለልጅሽ ሆድ አታስቢ! እዚህ ተርፎ ለሚደፋ እህል የበላነውን ትበያለሽ:: ብትወጅ እኛ ጋር እየሰራሽ፣ ከፈለግሽም ያሻብሽ እየዋልሽ እዚሁ ኑሪ - ቤትሽ ነው::"

ኑሪ...ኑሪ...ኑሪ...ኑሪ...ኑሪ......በሕይወት ኑሪ:: ሌሊት ኮሽ ባለ ቁጥር ሳትሰጊ ኑሪ:: ልጅሽን እንደፈለግሽ የምታጥቢበት፣ የሽንት ጨርቅ የምታጥቢበት ውሀ ሳያሳስብሽ ኑሪ:: ልጅሽ የሚበላው ነገር ሳይቸግረው ኑሪ...ኑሪ...:: እግዜርም ሲናገር ልክ እንዲህ ነበር፣ "ያውላችሁ ምድር ኑፋብት፤ ውሀው ያው፣ ምግቡ ያው፣ መኖሪያው ያው..." ይሄው ወይዘሮ እጥፍወርቅ ግቢ ዘፍጥረት ራሱን ሲደግም::

"በመጀመሪያ ምድር ባዶ ነበረ:: ባዶው ላይ አንዲት የጨለመባት ሚስኪን ሴት ልጅ አዝላ ቆማ ነበረ:: አግዜር ብርሃን ይሁን አለ:: ቦግ !!" ከአግዜር ብርሃን ጋር ሲወዳደር ቀለመወርቅ አብሪ ትል ማለት ነው:: ዘርፌ ሀይሏን የጨረሰች የኢጅ ባትሪ:: ወይዘሮ አጥፍወርቅ ጫረታ - የእግዜርን ብርሃን የምታንፀባርቅ:: አግዜር ግን ፀሐይ - ከአድማስ እስከ አድማስ በብርሃን የሚያጥለቀልቅ እናም የሚሞቅ !!

አቲዬ በተሰጣት ምርጫ መሠረት እዛው ቤት ልትሰራ ወሰነች:: በዕርግጥም የተሻለ ምርጫ ነበረ:: የማንንም ፊት ከማየት በእጅጉ የተሻለ:: ለእኔ በተለይ ግቢው መቦረቂያዬ፣ የወይዘሮ አጥፍወርቅ ፈገግታ ምቾቴ ሆነልኝ:: በዛ ሰፊ ግቢ ውስጥ ወይዘሮ አጥፍወርቅ፣ ወጣት ተማሪ ልጃቸውና እኛ ብቻ ነበርን የምንኖረው:: የወይዘሮ አጥፍወርቅ አምስት ልጆች ኑሯቸው በውጭ ሀገር ነበር::

ወይዘሮ አጥፍወረቅ አስገራሚ ሴት ነበረች:: እንኳን አቲዬ የድሮ እመቤቷ ዘርፌ ራሷ የማታልመውን ከውጭ ሀገር የመጣ አንድ ሸንጣ ልብስ ለአቲዬ ሰጠቻት:: ለእኔም ቆንጆ ቆንጆ ልብስ ገዛችልኝ - ዘነጥን !! እኔና አቲዬ ቂቅ ብለን ዘነጥን - ደግሞ ሰናምር!!

አቲዬ ከወይዘሮ አጥፍወርቅ የተሰጣትን ልብስ ሉባሳ አበባ መስላ ብቅ ስትል ዘርፌ ዓይኗ ደም ለበሰ፣ ቀለመወርቅ ደም ግፊቱ ከፍ አለ:: ከፉ አሳቢዎች ምን ሀብት ቢተርፋቸው የያዙት ነገር ዓያበደስታቸውም:: ይልቅ የሚጠሉት ሰው ጥቃቅን ለውጥ ያንገበግባቸዋል:: ዘርፌና ቀለመወርቅ የምቀኛ ግንባር ፈጥረው ተንገበገቡ:: የግንባሩ ጸሐፊ ሰይጣን!! እናም ሰይጣን ከቀለመወርቅ እና ዘርፌ ኋላ አግዜርም ከአቲዬ ፊት ቆመው ጦርነቱ ተጀመረ !! አሁን በኑሮ ማስፈራራት በክብር መንጠባረር የለም:: ማንም ሆዱ ከሞላ ጀግና ነው:: ማንም ቢመታ የሚወድቅበት፣ ቢቆስል የሚታከምበት ካለው ጀግና ነው:: ማንም የሚያከብረው ሰው ከጎኑ ካለ በሌሎች ንቀት ሞራሉ እንደደረቀ እንጨት አይሰበርም:: ዋናው ሰንቅና ትጥቅ ግን ማንም አግዚያብሄር ከኋላው እንዳለ ካመነ ልበ ሙሉ ነው !!

አቲዬ ይሄን ሁሉ ሆና ነው ወደ ጦርነቱ የገባችው !! እናም ጦርነቱ በታሪክ 'ወርቃማው ጦርነት' በመባል ይታወቃል በእኔ በንፍሴ ዘገባ !! ወደፊት ልጆቼ "ለምን ወርቃማው ጦርነት ተባለ ?" ብለው ቢጠይቁኝ መልሴ አንድ እና አንድ ነው፣ "በቀለመወርቅ እና በአጥፍወርቅ መካከል በተደረገ ሰብዓዊ ጦርነት በእሳት የተፈተኑ ወርቆች ወደ ምኞት አገር ስለተሰደዱ" እላቸዋለሁ::

## ክፍል አስራ ሁለት

የባርነት አስከፊ ገፅታ ያለው በባርነት መግዛቱ ላይ ሳይሆን በባርነት የተገዙበት መንገድ ላይ ነው:: በፍላጎት ለሌሎች ባሪያ መሆን ለራስ ህሊና የጌትነት ማዕረግ ስለሚያጎናፅፍ፣ ለነፃነት ትግል ሳይሆን ለምስጋና ራስህን እንድታዘጋጅ ነው የሚያደርግህ:: 'አሰይ! እንኳንም ባሪያ

ሆቴሉ' የሚባልለት ባርነት አለኮ:: ሰዎች በፍቅር ለሀገራቸው ባሪያ ይሆናሉ:: ለፈጣሪያቸው ይገዛሉ:: ለሚወዷቸው ያገለግላሉ:: ግን ደስተኞች ናቸው:: ለምን ? መንገዱ ፍቅር ነዋ !!

አቴዬ ዙሪያውን በረንዳም የማንብ አጥር ወደተከበበው ግቢ ገብታ ብትከትምም ዕጣፋንታዋን ግን አላመለጠችውም:: ዕጣፋንታ እኮ ጥላ ነው:: በዙሪያህ ያለውን ችግርና መከራ ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ ብርሃን ሲጠፋ፣ አብሮ የጠፋ ይመስለሃል እንጂ፣ ቀን የሚሉት ፀሐይ ወጋገኑን ሲቀድ ከትላንቱ በላይ ደምቆ ካንተ በላይ ገዝፎ ከፊትህ ይመራሀል - ከኋላህም ይከተልሀል::

አቴዬም ዕጣ ፋንታዋን ስንዝር አላመለጠችውም:: ከባርነት ወደ ፍቅር ባርነት ተቀይሮ በትልቁ ግቢ ውስጥ ጠበቃት እንጂ::ሰው አጥቶ፣ ውርማ ውጡት የነበረውን የወይዘሮ አጥፍወርቅ ግቢ ነፍስ ዘራችበት:: ሰፊውን ግቢ ከጧት እስከ ማታ አፀድታ ትልቁን ቤት ውበት ትደፋበታለች፤ የወይዘሮ አጥፍወርቅን ሆቴልም ቀጥ አድርጋ የያዘችው አቴዬ ራሷ ነበረች::

የሆቴሉን እንጀራ ሙሉ በሙሉ ትጋግራለች:: የአልቤረጎዎቹን አንሶላዎች ታጥባለች:: እንደዛም ሆና በጣም ደስተኛ ነበረች:: ወይዘሮ አጥፍወርቅ ደግ ሴት ነበረችና ምንም ቢደረግላት ይገባታል፤ የአቴዬ ባርነት ጣፋጭ ነበር:: መሀተመ ጋንዲ ወደ ወይዘሮ አጥፍወርቅ ግቢ ጎራ ቢሉ ኖሮ፣ "ነመስቴ...እኛም የታገልነው ለዚህች አይነቷ ባርነት ነበር በርቱ!" ብለው የሚሄዱ ይመስለኛል!!

በእርግጥ ወይዘሮ አጥፍወርቅ አቴዬን እንጀራ 'ጋግሪ' አላሏቻትም:: ራሷ አቴዬ ለሆቴሉ እንጀራ ግዥ እየተባለ በቀን የሚወጣውን ብር ስትመለከት፣ "ምጣድ ግዙልኝ ራሴ እጋግራለሁ" አለች እንጂ:: የሆቴሉን አንሶላ፣ "እጠቢ" ያላት ማንም አልነበረም:: አጣቢዋ ስትጨማለቅ ስታያት አቴዬ የኔ የልብ ሰው፣ "ምነው እቴ ሰው የሚተኛበት አይደለም እንዴ" አለችና እጇን ሰቅሲታ ገባችበት::"አቦ የእጥፍወርቅ ቤርጎ አንሶላው ብትል ፎጣው እንዴት ይጸዳል" እስኪባል:: የወይዘሮ ዕጥፍወርቅ ልብ አቴን በልጅነት መንበር ላይ ወስዶ አስቀመጣት፤ እኔንም በልጅ ልጅነት !!

ግቢው የእኔ ነበር:: እንዳሻኝ የምሆንበት ግዛቴ:: የሳሎኑ ዕቃ የእኔ ነበር:: ጆሮ ጭው የሚያደርግ ዋጋ የተከሰከሰበት ሶፋ ላይ ሸንቼበታለሁ፣ ወተት ደፍቼበታለሁ፣ አቀርሽቼበታለሁ:: ሰዓይን የሚያሳሳውን የቡፌ ዕቃ እንኮታኩቼዋለሁ:: የወይዘሮ አጥፍወርቅን ባለ አልማዝ ፈርጥ የአንገት ሀብል ከአንገቷ ላይ በጣጥሼዋለሁ:: (የዚህ ሀገር ወርቅ አንጥረኛ አይሰራውም ተብሎ ተቀምጦ ቀረ...) የፋናዬን (እህቴ ማለት ናት - የወይዘሮ አጥፍወርቅ ልጅ) ቀይና ውብ ፊት በመጫጭሬዋለሁ፤ ፋኒዬን እንደ ህፃን ልጅ ነበር የማስለቅሳት::

አቴዬ ስትነግረኝ ፋናዬ ከትምህርት ቤት ስትመጣ ቦርሳዋን እንዳዘለች እኔ ላይ ትጠመጠምና ድብድብ ነው:: ሱቅ የተሰቀለ እሻንጉሊት ካየች፣ የሕፃን ልብስና መጫወቻ ዓይኗ ውስጥ ከገባ፣ ለእኔ ለመግዛት ከእናቷ ጋር "ብር ስጭኝ አልሰጥም" ጦርነት ነው::

የእናቱ ንፁህ ልብ እንደስፖንጅ ፍራሽ በሕይወቴ መንገድ ላይ ተነጥፎ በዛች ቅፅበት የነበረ

ልጅነቴን እንከን አልባ አድርጎልኛል፡፡ ጥፋቴን የሳቅ ምንጭ፣ ለቅሶዬ ለማባበል ለሚራወጡ ቤተሰቦቼ፣ "የማባበል ስራ ጀምሩ" የሚል ደወል ነበር፡፡ የፍቅር እና የቤተሰብ ቅንጦት ቶምቦላ በጠዋቱ የወጣልኝ ጨቅላ !!

ሦስተኛ ዓመቴን ልይዝ ሁለት ወራት ብቻ ሲቀሩ በእኔና በአቲዬ ሕይወት ላይ ድንገት ፀሐይ ጠለቀች፡፡ ያች ፍልቅልቅ ፀሐይ ጠለቀች፡፡ ምንም ተራራ በሌለበት፣ ምንም ደመና በማይታይበት ንፁህ ሰማይ ፀሐይ ለወትሮው በአናት ትይዩ በምትሆንበት አኩለ ቀን ድንገት ድርግም አለችና እኔና አቲዬ ድቅድቅ ጨለማ ላይ ቆምን፡፡ ብርሃን ይሁን ያለ አምላክ በቁጣ "ጨለማ ይሁን" ብሎ ያዘዘ ይመስል የዚህን ሁሉ ጊዜ ውብ ብርሃናችን በአንዲት ቅፅበት ድርግም አለ !! እንደማብሪያ ማጥፊያ ቀጭ አድርጎ ድርግም !!

ድቅድቅ ጨለማ ከቀኑ ሰባት ሰዓት ላይ በጠራራ ፀሐይ አይከሰትም ያለው ማን ነው? – የፀሐይ ግርዶሽ፡፡ ማለትም ሳይንሱ ያሻውን ይበል እንጂ፣ እውነታው ወዲህ ነው፡፡ በምንወዳቸው ሰዎችና በእኛ መካከል ሞት የሚባል ግርዶሽ ሲጋረጥ፣ 'የፀሐይ ግርዶሽ' ይባላል !!

ወይዘሮ እጥፍወርቅ ለጓደኛዋ ልጅ ምርቃት ተጠርታ ወደ አዳማ ስትሄድ መንገድ ላይ አንድ ከባድ መኪና ትንሽ ዲኤክስ መኪናዋ ላይ ወጣባት፡፡ ደግ አይበረከትም !! ተረት አውሪዎቹ ደፋሮች ናቸው፡፡ ቀለል አድርገው፣ "ሲኖሩ ሲኖሩ ሞቴ" ይላሉ፡፡ ሞት ከተረትም ከታሪክም፣ ከዛሬና ነገም በላይ የገዘፈ ሰቆቃ መሆኑን ማን በነገራቸው፡፡ "ወይዘሮ እጥፍወርቅ ደግ ሰው ነበረች፣ ስትኖር ስትኖር በተወለደች በምናምን ዓመቷ በድንገተኛ አደጋ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየች" ተባለ፡፡ በቃ!!

ስለ ወይዘሮ እጥፍወርቅ ሞት አቲዬ ለማንም ምንም ስታወራ ሰምቻት አላውቅም፡፡ እግዜር ስትደገፈው የሚወድቅ ምርኩዝ ለአቲዬ በማዋሉ ብዙ ዓመታት ቤተክስቲያን እየሄደች ወቅሳዋለች፣ "ስለምን ደግ ኑሮን እንቁልልጭ ትለኛለህ፣ ለተራበ ውሻ ቁራጭ ስጋ ይዞ ሲያጓጓ እንደቆየ ሰው ከጠላቶቼ ዓይን በላይ ስቅለህ አኖርከኝ፡፡ እንዲበጫጭቁኝ ወይነሱ መልሰህ ጣልከኝ" እያለች፡፡

እኔም ነፍስ ካወቅኩ በኋላ እግዜርን ወቅሼዋለሁ፡፡ "ዘርፌ ለመኪና ሞት ምን ይጎድላታል፣ አዳማ መንገድ ላይ በአሰቃቂ ሁኔታ ተጨፍልቆ ለመሞት ቀለመወርቅ ምን ያንሰው ነበር?"

ዘፋኞቹ እየተቀባበሉ፣

"መንገድ ዓይኑ ይፍሰስ አይባልም ደርሶ፣

የወሰደውን ሰው ያመጣል መልሶ" ይላሉ፡፡

የታለ የአዳማ መንገድ ወይዘሮ እጥፍወርቅን የመለሰው? ቢሆንም እግዜር የለም አላልኩም፡፡ አቲዬ እግዜር አለ ካለች፣ ማንም ፈላስፋ ሀሳቤን ሰንዝሮ አያናውጣትም፡፡ እግዜርን በድፍረት

ልናገረው፣ ልነተርከው፣ ልነዘንዘውና ልነጫነጭበት እችላለሁ:: በምድር ላይ ሰው ሁሉ ከነእናቱ የሞቱኝ እኔ፡ "እግዜር የለም" ብዬ ማን ላይ ልነጫነጭ፣ ማን ላይ ልመናቸክ፣ ማንንስ ልነዘንዝ...፤

ዘወርማፕ አይት ይፍሰስ የተባለው መንገድ ዘርፌንና ቀለመወርቅን ወስዶ ባይመልስም ባልከፋ፣ እግዜርስ ምን ሞኝ እነዚህን ጥራጊ ፍጥረቶች ወደ ሰማይ ቤት የሚጠራ:: እዚሁ ይጨማለቁ እንጂ፣ ይሀ ላይ እፋቸውን ይከፈቱ:: አስመሳይ መንደርተኛ፣ ግፋቸውን በእናቱ፣ ሰማቸውን በምላሉ ተበከሞ ሲኖር እግዜር ለሲኦላቸው የሚሆን ማገዶ ይሰበስቡ ዘንድ እድሜ ይጨምርላቸው:: በሞኝነቱ ልደታቸውን በፌሽታ ያከብሩ !!አንድ ቀን እንደልደት ሻማ 'እፍ!' ተብለው እስኪጠፉ ! የአዳማ መንገድ አበጠላኝ:: የአዳማ መንገድ ላይ ቀለመወርቅ ቀብረር ብሎ ሲራመድ ይታየኛል ልክ እንደቤቱ ኮሪደር:: ቀለመወርቅ የጣረሞትን ገጸ ባህሪ ወክሎ ድራማ የሚሰራ መሰለኝ:: እንዴት ነው የሚቀጣለት::

ደስ የሚለው ነገር አዳማ መንገድ ላይም ባይሆን በመኪና አደጋም ባይሆን ዘርፌና ቀለመወርቅ ይሞታሉ !!!! (ሀሌሉያ) ያች አቃጣሪ ባልቴት ሸንሸን ቀሚሷን ጥላ እርቃኗን ትነነዛታለች:: የአሜሪካ ኣሞቿ አማላጅ ሆነው ገነት ያስገቧት እንደሆነ እናያለን !!

ይሄ ባለጌ ሽማግሌ ቀለመወርቅ ካፖርትና ኮፍያውን መልዐኩት በር ላይ በክብር ይቀበሉትና፣ "እዚህም በክብር ልኖር ነው" እያለ ሲያስብ፣ ማጅራቱን ይዘው ወደ እሳት ጉድጓድ ውስጥ በእርግጫ ይገፈትሩታል:: ታየኝ በአየር ላይ እየተምዘገዘገ ሲወርድና ቦጭረቅ ብሎ ሲያርፍ፣ እሳቱ እንደውሀ ዙሪያውን ሽቅብ ሲረጭ !! ያኔ "አሸብር ልጄ ነው" እያለ ቢቀባጥር እሳቱ ይበርድ እንደሆነ እናያለን !! እንጃ ፈላስፋዎች ምን ነካቸው 'ሲኦል' የለም የሚሉት? ስለቱ ካለ እርቱን እንዴት የለም ይላሉ? ሲኦል መኖር አለበት:: ቀለመወርቅና ዘርፌ እያሉ እንዴት ሲኦል አይኖርም !!

*ክፍል አስራ ሦስት*

ቁጥር ስፍር የሌለው ሕዝብ ለቅሶ ለመድረስ የወይዘሮ እጥፍወርቅን ግቢ እጥለቀለቀው:: ቀስ በቀስ እስተዛዘኙ እየተመናመነ መጥቶ በመጨረሻ ግቢው ወደነበረው ዝምታ ተመለሰ:: ከሀዘኑ በኋላ ነገሮች ሀልም በሚመስል ሁኔታ ተቀያየሩ:: ሀዘኑ ባበቃ በጥቂት ወራት ውስጥ ፋናዬን ወንድሞቿ ስዊዲን ወደሚባል ሀገር ወሰዷት::

ፋኒ የእኔ እህት አቲዬን ስማ በተሰበረ ልብ ግቢውን ለቀቀች:: እቴ በምድር ላይ ያሏትን ሁለት ዘመዶች አጣች:: ዛሬም ይሄን ስታወራኝ ዓይኗ ውስጥ ሀዘም ይንቀለቀላል:: ነፍሷ ይቃትታል፣ እም ብላ ትቆይና፣

"እሹዋ!" ትለኛለች::

"አቤት አቲዬ!"

"ሱዲን የሚሉት ሀገር ወዴት ነው?":: ስዊዲን ሀገር ቤትና ሕዝብ ተቆጥሮ የሕዝቡ ቁጥር ምንትስ ሚሊዮን ደረሰ ቢባል አቲዬ አታምንም:: የስዊዲን ህዝብ ቁጥር 'አንድ' ብቻ ነው. ፋናዬ ብቻ !! አቲዬ የዛችን ደማ ሴትዬ ልጅ ፋናዬን እንደ አየሩሳሌም አንድ ቀን ሲታያት ፀኑ መሻት ፊቷ ላይ ይንቀለቀላል::

እንዲት እድሜዋ አርባ የሚሆን ሸቅርቅር፤ ሲበዛ ቆንጆ የሆነች ሴትዬ (የወይዘሮ አጥፍወርቅ እህት ናት ይላሉ::) ከሁለት ጮምላቃ ሴት ልጆቿ ጋር፤ ወር ሳይሆን ጠብቂ ተብላ እግዜር ይወቅ ብቻ ግቢውን ትኖርበት ጀመረ:: ሆቴሉ ተሸጠ:: እች ሴት እስቴር ትባላለች:: ምንም የማይጨበጥ ተልካሻ ሴት ! ከዕድሜዋ ጋር ጦርነት የገጠመች 'ማዶ' !

እንዳንዴ በተረት የሚታወቀው አስማተኛ መስተዋት መኝታ ቤቷ ውስጥ የተቀመጠ ይመስል ገብታ በወጣች ቁጥር ልብሰ የምትቀይር፤ "የሆነ ቦታ በመልክ የምትበልጥሽ ውብ ሴት አለች" እያላት መስተዋቱ፤ ፊቷ ላይ የትራብ ሰንበር ከሚወጣ ኢትዮጲያ ላይ ከሰሜን እስከ ደቡብ ሜፍ አዲስ ሰምጥ ሸለቆ ቢፈጠር የምትመርጥ የውበት ስስታም !! የዕለት እንጀራዋ የሰው ዓይን የሆነ ከንቱ፤ የእጥፍወርቅን ግቢ በባለቤትነት ታስተዳድር ጀመር::

እቲዬን እንደ ሰራተኛ ስለምታስባት ማመናጨቅ የጀመረቻት ገና የህዘንተኛው እግር ጨርሶ ሳይወጣ ነበር:: እኔንማ ግልገል ሰይጣን አድርጋ ነው የምታየኝ:: በወይዘሮ አጥፍወርቅ የለመድኩትን መዘባነን ታጥቄ ወደ ሳሎን ዘው ስል በቲሸርቴ እንጠልጥላ መሬት ለመሬት እየጎተተች በረንዳው ላይ የመወርወር ያህል ትጎትተኝና፤ "ማነሽ አንች ልጅ ነይ ወደዛ ውሰጅ ይሄን ልጅሽን ! እንዴ የምን መጨማለቅ ነው እሱ...ሁለተኛ እዚህ ምንጣፍ ላይ ሲወጣ እንዳላይ!" ብላ እጇን ታራግፋለች::

እቲዬ ነፍስና ስጋዋ እየተሟገተ መወልወያ ይዛ ትገባና ያበላሸሁት ነገር ካለ ትፈልጋለች:: ብዙ ጊዜ ግን የዚህች ከንቱ ጩኸት ምክንያት አልነበረውም:: ምክንያቷ ሰው አለመፈለግ ነው:: ሰውን በማራቅ ሰላም ይገኝ ይመስል ! ሁካታ ነፍሷን ሀቅ አጉርሳ ዝም እንደማሰባል የቀረባትን ሁሉ ታፍናለች::

በዚያ ከወራት በፊት ምግብ ይልከሰከሰበት በነበረ ግቢ ውስጥ ጣረሞት ረሀብ ያንዣብብ ጀመረ፤ በፊት ወተት የምትገዛልኝ እጥፍወርቅ ነበረች:: መሰቧ መሰባችን፤ ድስቷም ድስታችን ነበረ:: እንዲህ ባጭር ጊዜ ከጓዳችን ቁራሽ ዳቦ፤ ንጣይ እንጀራ ይነጥፋል ብሎ ማን አሰበ !!

እንዳንዴ ምኞት ያዘናጋል:: ምኞት ስትኖርበት ዘላለማዊ ይመስላል:: ሜዳ ላይ ጥሎህ እንደ ጉም ሲተን ነው ፊቱ ላይ ቀዝቃዛ ውሀ እንደቸለሱበት ሰው የምትበረግገው:: ስንቱ ቤተብብ ድንገት ከምኞቱ በችግር ተኮርኩሞ ነቅቷል:: ስንቱ ባለስራ ስራውን ተደግፎ፤ ድጋፉ ሲከዳው ወድቆ ቀርቷል:: ስንቷ ባለትዳር፤ የባሏ እጅ ሲነጥፍ አብሮ ቅስሟ ተሰብሯል:: አግኝቶ ማጣት ብሎ ህዝቡ የሚጠራው ይሄንን አይደል - ተገኝቶ መጥፋት ቢሉት ይሻል ነበር !!

አስቴር አቲየን ታዝዛታለች፣ ታመናጭቃታለች፣ ትልካታለች፣ ግን ብርም ሆነ ምግብ አትሰጣትም፤ የሚገርመው ደግሞ ቤቱ ውስጥ እንጀራ አይጋገርም ወጥም አይሰራም:: እናትና በዘኔ ልጆቿ ይወረውሩታል:: እነዘን ደማቅ ጽሑፍ ያላቸው የቸኮሌት ላስቲኮች በርሀብ እየተንሰፈሰፍኩ ቀድጄ የላስኩባቸው ጊዜያት ብዙ ነበሩ - ዛሬ ቸኮሌት እንደ መርዝ አጠላለሁ !! እነዛ ባዶ የፍራፍሬ ጭማቂ ዕቃዎች ስይት ነበሩ ለኔ:: ዘመናዊነት ያደነዘዛቸው እናትና ልጆች - ምቾት ውስጥ የመነኑ የስንፍናና የከፋት ቆብ የሜኑ ርኩሶች ነበሩ:: እንኳን ግቢያቸው ውስጥ ለተጠጉ ሚስኪኖች፣ እርስ በርሳቸውም የተለያዩ የሰው ክብቶች::

መኻታ ቤታቸውን በየፊናቸው ዘግተው፣ ማንም አራት እግሩን ቢበላ አልሰማንም አላየንም ብሎ የሚረጭህ ጋግርታም የግለኝነት ባሕር ውስጥ የተጠመቁ:: የምዕራባዊያኑን ቆሻሻ ግለኝነት የሰለጣኔ አልፋ፣ የዕውቀት አሚጋ ያደረጉ ፋዞዎች:: በእንግሊዝኛ እየተለፋደዱ፣ በአማርኛ የአዕምሮ መቃወስ ውስጥ የተዘፈቁ የቤት ዕቃዎች:: የሞራልም ይሁን የሀይማኖት፣ አልያም ከነፍስ ስልጣኔ የሚመነጭ ጠንካራ ስብዕና የሌለው ኢትዮጲያዊ፣ ውጭ ሀገር ደርሶ ሲመለስ ምን አይነት አስቃቂ ‘ማቶ’ነት ውስጥ እንደሚነከር የታዘብኩት በእነዚህ ክንቱዎች ነበር:: እናታቸው ሀያ ዓመት፣ ልጆቹ እየሄዱ እየመጡ ከአስር ዓመት በላይ አሜሪካ ኖረዋል:: አስቴር ታዲያ ለዓመታት ከኖረችበት አሜሪካ ምን ይዛ መጣች? ለምቻታለሁ ለመጣ ለሄደው፣

“አበሻ ስራ አይወድም፣ ነፎጬቹ እኮ ለሰዓት ያላቸው ክብር ለስራ ያላቸው...”

“አበሻ የተመጣጠነ ምግብ አያውቅም - ማድፋፋት፣ ጥሬ ክብሰል ማጋበስ...”

“አበሻ ሙች ንፅህና ይወዳል ነፎጬቹ እኮ...”

“ኤዲያ የሀበሻ ወንድ መች ሴት ያከብራል - ነፎጬቹኮ”

“የአበሻ ልጅ አስተዳደግ...”

“የአበሻ ሕክምና ደግሞ ራሱ በሽታ ነው:: ነፎጬቹ እኮ”

“አበሻ ገንዘብ ከመሬት የሚታፈስ ነው የሚመስለው:: ዓይኑን በጨው አጥቦ፣ ‘ዶላር ላኩ ነው’፤ ነፎጬቹ እኮ አስራ ስምንት ዓመት ከሞላቸው...”

ነጭ የባርነት ቀንበር ጫንቃዋ ላይ ተሸክማ የምትደሰኩር ቱልቱላ:: ከየትም የፈለፈለቻቸው ልጆቿ በአስተዳደግ ይሁን በግል ባህሪ ምን ዓይነት እናት እንደሆነች ጮኸው እያወጁ፣ “ዓይናችሁን ጨፍኑ ላሞኛችሁ!” ትለናለች::

የነፎጬቹ ፅንፍ የለሽ ውክቢያ ዕድሜዋን ሙሉ ያጨቀባት የታላቅነት አባዜ አበሻን በበጎ እንዳታይ

እንደ ጋሪ ፈረስ ቀይዷት፣ ለእግዜር ሰላምታ የቀረባት ሁሉ የፈ.ጋቸበትን ዶላር የሚነጥቃት እየመሰላት ስጋዋ ያልቃል:: ልጆቿም በየእጥሩ ጥግ ከሚያናግኙት የአበሻ ወንድ ጋር ሲሳሳሙ እና በየመሸታ ቤቱ ሲዳሩ ከማምሸት ውጭ የፈየዱት ተዓምር የለም:: በነፃይቱ ሀገር ኖረው ለመጡ የሰልጣኔ ጥጎች፣ የከንፈር ዋጋው የዶላሩን ያህል ውድ አይደለም:: እነዛ ወንበር ሰበው በኩብር ሴትን ልጅ የሚያስቀምጡ 'ነጫጭ ወንዶች' የሴትነትን ክብር እየሰበኩ ሰብዓዊነታቸውን ከእግራቸው ስር እንደጨፈላለቁት ለመረዳት የጋረዳቸው ነጭ ደመና አይፈቅድላቸውም !!

ለእነዚህ የሰልጣኔ ርዝራዦች የሰው ልጅ ስለከብሩ መኖር፣ ስለማተቡ ዓለማዊነትን 'በልክ ይሁን!' ማለቱ 'ተራ መኮፈስ' ነው:: በርሳቸውን ከመክፈት፣ ለማንም እላፊ እግዳሚ እግራቸውን መክፈት ይቀላቸዋል:: ምክንያቱም "ዶላር - የተከበሩት የነጮች ውድ ቅርስ" ሲሆን ሰውነታቸው ግን የርካሾቹ፣ የሰነፎቹ፣ ያልተማሩት፣ ሥራ የማይወዱት፣ ብር ከመሬት የሚታፈስ የሚመስላቸው አበሾች ርካሽ ንብረት ነው::

በዚህ ፍልስፍና አገሩን አጥምቀውት አገሬው ፈረንጅ ባል ፍለጋ ሲራኮት ቢታይ ምን ይገርማል !!

አቲዩ አንድ ቀን እየፈራች ሴትየዋን አናገረቻት፤ "እትዬ ወጥቼ አንዳንድ ስራ ልሰራ ነበረ ምናልባት ከፈለጉኝ ብዬ ነው..."

"ስራሽ ምንድን ነው?" አለች ሴትዮዋ አቲዩን ከታች እስከ ላይ እያየቻት::

"እኔ እትዬ እጥፍወርቅ ጋር እንጀራም እጋግራለሁ ያው ለሆቴሉ፣ እዚሁ ነው ስራዬ ሌላ ምን ስራ አለኝ"

"እኔ የማሰራሽ ነገር የለም:: ውጭ ነው የምንበላው:: ልትሄጂ ትችያለሽ::" አቲዩ ደነገጠች::

"ቀን ቀን ስራ ሌላ ሰፍራ እየሠራሁ፣ ለማደሪያዬ እዚሁ ቢፈቅዱልኝ:: መሄጃም የለኝም፣ ከነልጄ ለነፍሴ ብለው እትዬ እጥፍወርቅ እስጠግተውኝ ነው..."

"ኤጭ አበሻ ሲባል 'የነፃ ራት' ካልበላ እንቅልፍ አይወስደውም:: ጤነኛ ነሽ፣ እግር እጅ አለሽ፣ ሰርተሽ ሳትሳቀቂ ቤት ተከራይተሽ መኖር ስትችይ እስጠግተውኝ ቅብርጥሶ ማለት ምን ኦመጣው፣ ነጮቹ ቢሆኑ..." ደሰኮረች:: አቲዩን እዛ መቆየቷ ብዙም ደስ እላላትም:: ቢሆንም አንዳንድ ሥራ ማሠራቱ እንዳለ ልቧ አውቆታል:: 'የነፃ ጉልበት' የማይፈልግ የነጭ አድናቂ ማን አለና:: እናም አቲዩን እንዲህ አለቻት፣ "እንግዲህ ያው ፀባይሽን አሳምረሽ ኑሪ፣ እኔ ጫጫታ ምናምን አልወድም:: ቤቱን ከፈለግኩት በማንኛውም ጊዜ ትለቂያለሽ..."

አቲዩ እኔን እዝላ ወደረሳችው መንከራተት ተመለሰች:: አዲሳባ ውስጥ የምታውቀው መንደር አንድ ነው . እዛም ቀለመወርቅና ዘርፌ አሉ..! እላ ነባሪዎቹ ሦስት ዓመት ፀሐይ ሳይነካት ብርቱካን መስላ የወጣችውን አቲዩን ሲያዩ ጥርሳቸውን አፏጩ:: ቀለመወርቅ ደፋሩ ምራቁን

አየዋጠ እንደገና ተመኘች:: ስላማረባት መንደርተኛው በሙሉ ጠላት:: ዘርፌ የከፋት ልምጪን አዘጋጅታ ነበር የጠበቀቻት::

ከከፍታ እንደመውረድ ውርደት፣ ረግጠው ወዳለፉት ነገር እንደመመለስ ታላቅ ስቆቃ የለም፤ የራስህ ወገኖች መብረር ስትጀምር 'እሰይ' ከማለት ይልቅ ክንፍህ ተሰባብሮ እግራቸው ስር ወድቀህ ስትፈጠፈጥ ለማየት ይጓጓሉ:: እናም ስትወድቅ ይረካሉ:: 'ብዬ ነበር፣ እያቻሁ' እየተባባሉ የምቀኝነት ትንቢታቸው የሰመረላቸው ምቀኛ ኮብያት ይንሜሜሉ:: ብሔራዊ ምቀኝነት የተጠናወተው ሕዝብ እንደኛ ይኖር ይሆን? "ለምን በደፈናው እንሰደባለን?" ይለህል 'ምቀኛ' ስትለው የተዳፈነበት አመክንዮ እየደረደረ፣ 'ሁሉም አንድ አይደለም' ይልሀል፤ ግን ሁሉም አንድ ነው:: ጠጥቶታል እንደ ውሃ፣ በልቶታል እንደ እንጀራና ጥሬ ስጋው !! ቢማርም፣ ቢያገኝም፣ ምቀኝነቱን ያዘምናታል እንጂ ቢሞት አይጥላትም፤ ማተቡ ናት::

ከዚህ በኋላ የሆነውን ዝርዝር ነገር ስናገር ማንንም ሳይሆን ራሴን እጠላለሁ:: እቴዬ በሲጋም በነፍስም የቀለመወርቅ መጫወቻ፣ የዘርፌ ገረድ ሆና ኖረች:: ለስንት ዓመት...:: ዘርፌ ቤት የመደህኒያለም ዝክር፣ አከሊት ቤት የኪዳነምህረት ዝክር፣ አሻሮ፣ የጠላ ቂጣ፣ ድፎ ዳቦ:: የአከሊት ልጅ ልታገባ ነው - ወጥ ሰሪ፣ ጠላ ጠማቂ:: ሲወልዱ - ልደት፣ ክርስትና - እሳት በላት እናቴን::

ውበቷን ጤናዋን ወጣትነቷን እሳት በላው:: እቴዬ እንደብረት ምጣድ እሳት ላይ ተጥዳ እኔ የምባል ጣፋጭ ኬክ በላይዋ ላይ በሰልኩ:: ይሄ ሁሉ ሥራ በዚህች ሚስኪን ሴት ላይ ተጭኖ፣ ማታ ወደ ማደሪያዋ ስትመለስ የአስቴር ጨምላቃ ሴት ልጆች የውስጥ ልብስ ሳይቀር በየቦታው ተወርውሮ ይጠብቃታል:: ቀን እናትና ልጆች ሲወጡ ወንድ የሚራኮትላቸው ዘናጮች፣ ሽቷቸው ከሩቅ የሚጣራ ሽቅርቅሮች፣ የቤታቸውን ጉድ ወላድ አይየው! እነዚህ በየአደባባዩ ሽቅርቅር የሚሉ ሰዎች ቤታቸው የዝርክርክነት ጥግ የሚሆነው ለምንድን ነው ግን ? ብዙ ሰው አየሁ - ብዙ ሽቅርቅር !!

ሴት ልጅ ቢያንስ የውስጥ ልብሷን የራሷን ገመና እንዴት ሌላ ሰው እንዲያጥብላት ትፈልጋለች - ለዛውም በየካፍቴሪያው ተጎልተው ሲገለፍጡ የሚውሉ ስራፈት ሴቶች:: አይቻለሁ በአስቴር ልጆች ! እናታቸውም ያው ናት:: የዘር ነው መቆሸሽ:: ከማን ይማራሉ? ያኔ ነው ረጅም ጫማ አድርጎ ከመቆነን በፊት፣ ፀጉር እየነሰነሱ 'አገር ይያን!' ከማለት በፊት፣ 'ቤት' ሲባል ፊቴ የሚደቀነው ይሄው ፅንፍ አልባ ስንፍና ነው:: የሴት ልጅ ስንፍና እንዴት ይቀፋል? መንገድ ላይ ሰበር ሰካ የሚሉ ሴቶች ሁሉ ከውበታቸው በፊት መታጠቢያ ቤታቸው ነው ዓይኔ ላይ የሚደቀነው::

ድንጉተኛ ፍተሻ ይደረግ ቢባል፣ ከዝርክርኩ ወንደላጤ፣ ካልሲ በየቦታው ከሚጥለው ወንድ የባሰ ሴንት ጉድ ሴቶች አሉ፣ ስንትና ስንት ወር ሙሉ ሰው ሰራሽ ፀጉር አናታቸው ላይ ጀልቶ መሬት አይንካን የሚሉ:: በዛ የልጅነት እድሜዬ ተላላኪነትን በተማርኩባት፣ ለመኖር ስል የመሽቆጥቆጥን እርምጃ ዳዴ ባልኩባት በህይወት ውጣ ውረዴ ነበር "ሴትነት ደራሽ ንፋስ የሚከምረው፣ ደራሽ

ንፋስ የሚበትነው የምድረ በዳ የአሸዋ ክምር ነው" ብዬ በሴት ተስፋ የቆረጥኩት:: የአስቴር ልጆች፣ 'ሴት' መሰለውኝ !! መቼስ በሕይወት ውስጥ ሕይወትን አጠናግረን እንድንመዝናት የሚያደርጉን አባይ ሚዛኖች አይጠፉ::

## ክፍል አስራ አራት

መማርን ጌታ ይባርከው !! 'መማር መቃጠል ነው' ይላሉ ተምሮ ማቃጠል ለእኔ ዓለሜ ሆነች !! ቀደም ብዬ እንደገለፅኩት አንደኛ ክፍል እስከመዘገብ የአባት ስም አልነበረኝም:: አሸብር ብቻ ነበርኩ:: ልክ ትምህርት ቤት አቲዬ ወስዳኝ ስመዘገብ ጉጉት የመሰለው መዝጋቢ የእናቴ ድሪቶ ቀሚስ ለዓይኑ ቀፎት እያመናጨቃት አይቼዋለሁ:: ተመዝግቤ ስንመለስ አቲዬ ከፊቱ ዞር ስትል፣ ፊቱን አጨፍግጎ መጥፎ ጠረን እንደሚያባርር ሰው በግራ እጁ አየሩን እያራገበ ሲያባርር አይቼዋለሁ::

በአርግጥ አቲዬ እማማ የብርጓል ቤት አንኩሮ እያነኮረች ነበር:: "ምዝገባው ዛሬ ነው የሚያልቀው" ሲሏት ብድግ ብላ ነው የመጣችው:: ቢሆንስ ልክ ቆሻሻ እንደሸተተው ሰው ሰው እንዲያየው አድርጎ እጁን ያራግባል እንዴ...:: የእማማ የብርጓል ቁጥር አንድ የጠላ ደንበኛ እንዳልሆነ ሁሉ:: ሊያስተምረን ክፍል ውስጥ ሲገባ እንደባቡር ሀዲድ የረዘመ የጠላ ትንፋግ ተከትሎት እንደማይገባ ሁሉ – ኑብር አየው ያንን የውሻ ልጅ:: አስተማሪውን እንደጠመድኩት ጡረታ ወጣ !! ደግሞኮ እያፍርም መንገድ ላይ ላገኘው ሁሉ፣ "እኔ ነኝ ያስተማርኩት" እያለ በኩራት ያወራል:: በርሱ የትምህርት ዓይነት ብቻ ዶክተር የሆንኩ ይመስል!!

"ስም ?" አላት አቲዬን ድሮ::

"የእኔን ነው ?" አለች እየፈራች::

ፈሪ ነበረች እናቴ:: ፈሪው የአዲስ አበባ ሕዝብ እንደያቅሙ ደሀ ማስፈራራትን ተክኖበታል::

"አንች ነሽ አንደኛ ክፍል የምትመዘገቢው?" አላት:: አጠገባችን ያሉት ሁሉ ሳቁለት:: አቲዬ ተሳቀቀች:: ሰውነቷ ሽምቅቅ ሲል ቀሚሷን አንቄ ተሰምቶኛል መሸማቀቋ::

"የልጅሽን ስም ንገሪኝ ሴትዮ" አላት እያከላፈታት::

"የእሱ አ..ሸብር...አሸብር ነው ስሙ" አለች ራሴን እያሻሸች::

"የአባት ስም ?"

"አባ...ት" ብላ ዝም አለች::

"የአባቱ ስም ማነው..."

ዋ..."መጨረብ አልቻለችም:: ቀለመወርቅ ልትል ፈልጋ እንደነበር የገባኝ ካደግኩ በኋላ ነው:: ካዛሬዋ ደግሞ የጉድ ናት:: የልጁም አባት የሚጠፋት..." ብሎ እንደገና እንዲስቁለት ሰዎቹን አየ:: ያልደመቀ ሳቅ ተሳቀለት::

"በይ ወደዛ ሁኚ! ስታስታውሽ ትመለሻለሽ፤ ተረኛ ቀጥል!" አለ እስክርቢቶውን እያወናጨፈ::

(ለአፈረኝነትም ግማሽ ድረስ ቀለሟ ያለቀ ሰሚያዊ ቢክ እስክርቢቶ::)

እናቴ ከእንቅልፉ እንደባነነ ሰው፤ "በአምላኩ...በአምላክ ነው የአባቱ ስም::" አለች::

መዝጋቢው ራሱን ግራና ቀኝ በብስጭት እያወዛወዘ መዘገበኝ::

የአባት ስም – በአምላክ (በአምላክ አባቴ አይደለም:: አቲዬ ለአምላክ ሰጠችኝ::) የሃምሳ ብሩ ቢገርመው፤ ለእግዜር ሰው አበደረችው አቲዬ:: የእኔ እናት በሕይወት ባንክ ውስጥ ብድር ለሚመልስ ብድር በመስጠት የተካነች ባለሙያ ነበረች – ነገን የምታይ !! እግዜር የተበደረው ትውልድ፤ ወሰዱ የተባረከ ዘር ማንዘር ነው:: "እስከ ሺ ትውልድ ዘርህን አባርካለሁ::" ብሏል ራሱ እግዜር !!

ትምህርት ቤት ገባሁ...!!

ጠፍላችን ልጆች የኑሮ ደረጃ በዳግማዊትና በእኔ መካከል የተወሰነ ነበር:: ዳግማዊት የሚታዘል ባለዚፕ ቦርሳ ያላት ቆንጆ አንደኛ የሀብታም ልጅ ስትሆን፤ እኔ ከሹራብ የተሰራች ኮሮጆ የነበረኝ አንደኛ የደሀ ልጅ:: ይሁን እንጂ በንፅህና አልታማም:: ልብሶቼ ሁልጊዜም ንፁዎች ነበሩ – ንፁህና አርጌ:: ሰኞ ሰኞ ሰልፍ ሜዳ ላይ የእጅ ጥፍሮቻችን ሲታዩ ንፁህ ጥፍሮቼን በኩራት ነበር የምዘረጋው:: የዳግማዊትን ያህል በረጎማታ "ጎበዝ" ባልባልም፤ ከቆሻሻና ከስንፍና የተጣላች ቆራጥ ደሀ እናት አለችኝና ስንፍናና ቆሻሻ እጠገቤ ዝር አይሉም !! (ሰው ወዶ አይደለም ለካ ዘራፍ የሚለው::)

አንድ ቀን ግን በሕይወቴ ስሳቀቅበት የኖርኩበት ነገር ተፈጠረ::

እንግዲህ አስቴር ከዋናው ቤት አሮጌ ፍራሽ (የሆቴሉ አልቤርጎ ውስጥ የነበሩ::) እና ሌሎችም እቃዎችን ከዕቃ ቤቷ አስወጥታ እኔና አቲዬ የምንኖርበት ክፍል ውስጥ አስቀመጠች – እንደዕቃ ቤት:: እናም ቤታችን ውስጥ በታጨቀው ዕቃ ምክንያት ቤቱን እንደ ልብ ማፅዳት ባለመቻሉ ቁንጫ እንደጉድ ይፈነጭ ጀመረ::

ጋሽ መሀሪ አካባቢ ሳይንስ መምህራችን ነበር:: ሲያስተምር ስወደው:: የርሱን ትምህረት እስር ካበር ነው ሁልጊዜም የምደፍነው:: እኔ ስለምወደው፤ የሚወደኝ ይመስለኝ ነበር :: አንድ ቀን

ግን ዘላለማዊ ጠላቴ ያደረገውን የማይረባ ነገር አደረገ ።

ስለ ጓሮ አትክልት ጥቅም እያስተማረ ነበር። ድንገት ዳግማዊት፣ "ዋ...ይ" ብላ ጮኸች። ቦርሳዋ ላይ ሁለት አሳት የመሳሰሉ ቁንጫዎች ዘለውባት ነበር። የክፍሉ ልጅ ሁሉ በድንጋጤ ወደ ዳግማዊት ዞረ። መምህሩ ሁኔታውን ሊያጣራ ከምኔው አጠገባችን እንደደረሰ እንጃለት።

"ምንድን ነው?"

"ቁ..ን...ጫ" አለች ለቅሶ በሚመስል ምልቃቃ ድምፅ።

እኔ ከዳግማዊት ጎን ነበር የምቀመጠው። ባልገባኝ ምክንያት ተቆጣ።

"አስቲ ቦርሳህ" አለኝ። በቃ እንዲህ ነው ያለኝ። ከወንበሩ ስር ከተሰራው የደብተር ማስቀመጫ፣ የሸራብ ኮሮጆዬን አወጣሁ። በዚህች ቅፅበት የተከሰተው ነገር አስደንጋጭ ነገር ነበር። በርካታ ቁንጫዎች ከእኔ ኮሮጆ ላይ ተፈናጠሩ።

መምህር መሀሪ ፊቱን አጨፍግጎ ኮሮጆዬን አንሳና ወደፊት ወደ ጥቁር ሰሌዳው ወረወረው። ደብተሮቼ በአየር ላይ ወረቀታቸውን እያርገበገቡ ተበታተኑ። (እስከዛሬም ደብተሮቼ በአየር ላይ እየተንሳፈፉ ይታዩኛል - አላረፉም።)

"ውጣ ጆሮህን ያዝ!" ብሎ በኩርኩም አፈለሰኝ። ወጥቼ ጆሮዬን ያዝኩ። ከኩርኩሙ በላይ ሀፍረቱ ጠዝጥዞኝ ነበር።

የታፈነ የጓደኞቼ ሳቅ። በትምህርት አልችለኝ ሲሉ እኔን እንደውድቀት፣ እኔን ከእነሱ እንዳነስኩባት አጋጣሚ ሊጠቀሙባት። የኢፉኝት ልጆች...ሰንቱን ትምህርት ሰደፍን ለጭብጨባ በመከራ የሚነሳ እጃቸው፣ ዛሬ ሳቃቸውን ሊያፍን ወደ አፋቸው ተወነጨፈ።

ቡፍ...ቡፍ...ሂሂሂ...

መምህሩ መሀሪ (ስሙን ቄስ ይጥራውና!) ስለጓሮ አትክልት የፃፈውን አጥፍቶ ጥቁር ሰሌዳው ላይ፣

"ተስቦ" ብሎ በትልቁ ፃፈና ከስሩ በድርቡ አሰመረበት። ያውም አረንጓዴ ቀለም ባለውና እንደ ብርቅ በምናየው ጠመኔ !!

ክዛም ስለተስቦ ሙሉ ክፍለጊዜውን ሲለፈልፍ ዋለ።

"እያችሁ...ልክ እናንተ ወደ ትምህርት ቤት ወይም ዘመድ ለመጠየቅ በታክሲ፣ በአውቶብስ ተሳፍራችሁ እንደምትሄዱት፣ ቁንጫዎችም በአይጦች ተሳፍረው ንፅህናው ወዳልተጠበቃ ቤት ይሄዳሉ። አሁን እሱ ደብተር መያዣ ላይ እንዳያችሁት (እኔን እየጠቆመ)፣ ንፅህናው ባልተጠበቀ

የሲብስ ሸንጣ፣ የደብተር መያዣ፣ በሌላም ቁሳቁሶች አማካይነት እየተንጠላጠሉና እየተደበቁ ከቤታ ወደ ቢታ በመንቀሳቀስ፣ እንደ ዳግማዊት ዓይነት ንፁህ ልጆች በተሰበ ይያዛሉ..." በማለት አስተማረ፡፡ ምን ያስተምራል አስተማሪ የሚባለው ነገር የጠላት ስም እንዲመስለኝ አደረገ አንጂ !! ለረጅም ጊዜ 'ተሰቦ' እያሉ ጓደኞቼ ያበሽቁኝ ነበር፡፡ ከአርባው ስንፈተን ግን ስለተሰበ ተጠይቀን የደፈንኩት እኔ ብቻ ነበርኩ፡፡ ሰው ሰድቡን አይረሳማ !! በተለይ እኔ ሰድቤን አልረሳም !! መንፈቴን አልረሳም !!

ለድብና መንፋት እንደ አረማራጊ ሳንቃ ሽቅብ ተኩሰው በቀል የሚባል ጨረቃ ላይ የሚያሳርፉኝ ሮኬቶቼ ነበሩ፡፡ እንዲያ ካልሆነ በቀል መቼ አምሮ !! የሰደበኝን ሁሉ አልለቀውም !! ለምን ዘላለም አይኖርም፣ አልረሳም! የአዲስ አበባ ሕዝብ ሂትለሩን አቅፎ እያሳደገ መሆኑን መች ጠርጥሮ? ለፋሽስቱ እድገት ኩርኩምና እርግማን እያቀጣ እንደሆነ መቼ ቀልቡ ነግሮት? ሬዲዮና ቴሌቪዥኑ አደንቁሮት፣ ፊልምና ድራማው አሳውሮት፣ ሽቅርቅሮቹ ልቡን አጥፍተውት፣ ሕዝቡ ምን እያሳደገ እንደሆነ አያስተውልም !! በእያንዳንዱ መንደር አለ የተገፋ ሕፃን ሂትለር – የሕዝብ ንቀትና ጥላቻ በከፋት ያፈረጠመው፡፡ በቀጥታ ሳይሆን ሳያውቁ ለልጆቻቸው በሚያለብሱት ልብስ! በሚያገምጡት ኬክ፣ እንቅልልጭ እያሉ አርፎ የተኛ ረሀቡን ቀስቅሰው ያስነከሱት – የቆሰለ አበሸማኔ አለ፡፡ ሕዝብ ጠላቱን የሚጠብቀው ድንበሩ ላይ ወታደር አሰልፎ ነው፡፡ አገርና ሕዝብ ንፋስ እንደገረሰሰው ዛፍ ከስራቸው ተነቅለው የሚወድቁት ግን ውስጣቸው ባሳደጉት ጭቆና፣ ባፈረጠሙት የጥላቻ ክንድ በተደቆሱ ግለሰቦች ነው፡፡

ሕዝቤ ያሳረፈብኝን የጥላቻ ኩርኩም ነገ በጅምላ አልቂት እከፍለዋለሁ - ብቻ ልደግ !! ማሪያምን አልለቀውም ይሄን ሕዝብ፡፡ ደግሞ ብቻዬን አይደለሁም - ይሄ ሁሉ ተገፍቶ ጎዳና የሚንከራተት ሕፃን፣ ነገ ተንደላቅው የሚማሩትን ቆንጆ የለበሱትን ልጆችህን ሕይወት ያመሳቅለዋል፡፡ የዘራኸትን የጥላቻ ፍሬ ታፍሳታለህ፡፡ ነገ የበደልከው፣ ያከላፈትከው፣ የረገምከው ሕፃን እጅ ላይ ትወድቃታለህ፡፡ ያኔ በቀሉን በሁለት እጅህ ትቀበላለህ፡፡ ድፍን አገር ይሰማ ተቀምጣችሁ የሰቀላችሁትን ቆማችሁ ማውረድ የሚያቅትባችሁ ቀን ይመጣል፡፡ ...ተ !! አሸብር አይደለሁማ !! እንዲህ ነበር ሁሌም የምለው፡፡

እኔ ዶክተር አሸብር የሚስኪን እናቴን በደል የምከፍልበትን የመጨረሻውን ክፉ በቀል እያሰብኩ ነው ያደኩት፡፡ ኒውክሌር ቦንብ ቢኖረኝ እያልኩ፣ ወስጄ ቀለመወርቅ ግቢ እጥለውና ቁልፉን እጫነዋለሁ፡፡ የቀለመወርቅ ባርኔጣ ከነራስ ቅሉ በርሮ ኬንያ ጠረፍ ቢገኝ ግድ አለኝ? እነዛን የአሜሪካ ላሞች እንደ ኢ.ላማ ፊት ለፊት አቁሜ በመድፍ ነገር ሆዳቸውን ብደረማምሰው፣ ወተታቸው ወደ ሰማይ ጎኖ አዲስአበባ ላይ እንደ ነጭ ዝናብ ቢዘንብ...እችን ያህል ሊሰማኝ ነው?

በአውቶሞቢል፣ በታክሲ፣ በአውቶብስ የሚጓዘውን ሕዝብ አንዳች ኃይል ኖሮኝ እፋፍጬ ቀበና ብከተው አይወጣልኝም፡፡ የእሳት ዲንጋይ እንዲያወርድ እግዚአብሄርን ብዙ ቀን ለምኜዋለሁ፡፡ 'ለእነዚህ ማን ዝም ሲል፣ "እግዚአብሄር ለአዲስ አበባ ህዝብ አዝኖ ሳይሆን ህዝቡን ተፀይፎ፣

አላት ያባክናል?' ብሎ ትቷቸው ነው" እያልኩ አስባለሁ::

ቢሆንም አንድ ቀራፎ አስተማሪ አቃን ከፈተብኝ ብዬ እልተዘናጋሁም:: ብዙ ሰዎች ጎበዝ ተማሪ ነህ ሲሉኝ ይገርመኛል:: እኔ ምንም የተለየ ነገር አላደርግም:: አስተማሪው ሲናገር፣ የፃፍኩትንም ሳነብ፣ ከዚህ በፊት የማውቀውን ታሪክ የምሰማ ነበር የሚመስለኝ:: ፈተናዎችን ሁሉ እኔ ራሴ ያወጣኋቸው እስኪ መሰለኝ ነበር መልሶቻቸውን ጠንቅቄ የማውቀው:: በትምህርት ቤታችን ማንም ጎበዝ ነኝ የሚል ተማሪ ሲያድግ ከእኔ ጋር እኩል ለመሆን ይመኝ ነበር ብል ማጋነን አይሆንም:: እነሱ እስከሚያድጉ ቆሜ እጠብቃቸው ይመስል !! "የዛሬ ምናምን ዓመት አሸብር የደረሰበት እንደርሳለን" የዛሬ ምናምን ዓመት አሸብር የኒውክሌር ቦምብ ባለቤት ይሆናል...

ቡምምምምምምምምምምምምምምምምምምምምጥርግርግ !!

እነዚህ ጉረኛ ሴቶች ሁሉ ሰው ሰራሽ ፀጉራቸው እንደቸቦ አናታቸው ላይ እየነደደ ሰቀላ ጫማቸውን ወርውረው በባዶ እግራቸው ለመዳን ሲሮጡ - ሆዴን ይዤ እስቃለሁ::

ሽማግሌዎች መሸሽ አቅቷቸው ሲንቀጠቀጡ፣ እነዛ ልጆቻቸውን በትልቅነት ያልገሰፁ ሁሉ አላዝንላቸውም:: የቀለመወርቅን በደል ዓይተው እንዳላዩ ያለፉ ዓይኔ እፍንጫዬ ቁርጥ ቀለመወርቅን መምሰሉን እያዩ፣ "በየት ቤት ብሎ! ኧረ ቀለመወርቅ ቀጭን ጌታ ነው:: እዚህ ቋቁቻም ጋር ምኑም አይመሳሰል" እያሉ ያሽቃበጡ ሁሉ 'አባቴ ጣረሞት ነው' ብዬ አልቄት ይዤ ፊታቸው ሰቆም፣ "ቁርጥ ጣረሞትን" ይሏታል - አልምራቸውም ! "ታላላቆቻችሁን አክብሩ፣ ከወንበራችሁ ተነሱላቸው" ሲሉ ይገርመኛል:: ብችል ታላላቆቼን ከነክዘራቸው እያነሳሁ ባፈርጣቸው፣ አልያም ከወንበር መነሳት ሳይሆን ወንበር እንስቼ ጎባጣ ወገባቸው ላይ፣ ሽበታም አናታቸው ላይ ባፈጋባቸው ደስታዬ ነው:: ቅሌታም፣ አስመሳይ ሁሉ:: ነገር ከዛ ከዚህ ሲያቃሉ ስላረጁ ትልቅ የሆኑ ይመስላቸዋል:: ውቤ በረሀ ሴት ሲያሳድዱና አተላ ሲጋፍፉ ያረጁ አስመሳዮች፣ በአባቶቻችን ስም እድዋ የዘሙቱ፣ ማይጨው ላይ አልፍ የመከቱ መስለው ይኮፈሳሉ:: አላከብራቸውም:: የአንዲትን ሴት እንባ ማበሰ ያቃታቸው፣ በጠራራ ፀሐይ እውነትን የሸመጠጡ "እንምከር!" ሲሉ ያቅለሸልሹኛል::

### *ክፍል አስራ ስምንት*

የአስቴር ትልቋ ልጅ ዛጉ ትባላለች:: ትርጉሙ ምን እንደሆነ አላውቅም:: ምናልባትም 'ሰይጣናዊ መዝገበ ቃላት' የሚባል ነገር ካለ፣ ትክክለኛ ትርጉሙ እዛ ላይ ሳይገኝ አይቀርም:: እስከዛው ግን በግምት "ዋጋ ቢስ" ብዬ ተርጉሜዋለሁ::

ዘር ከልጓም ይስባል እንዲሉ ቁርጥ እናቷን (ሰነገሩ አባቷን የት አውቄው?)እኔ ከስምንተኛ ክፍል ወደ ዘጠነኛ ክፍል ሳልፍ እሷ የሀያ አምስት ወይም የሀያ ስድስት ዓመት ወጣት ነበረች፣ ተስፋ እሷ እዚሁ እኛ የነበርንበት ግቢ ውስጥ አንድ ደስ የሚል የተረጋጋ ወጣት ጋር መኖር ጀመረች፣

ምናልባት እዚሁ የቀረችው ልጁን ስለወደደችው ይሆናል::

መጀመሪያ መኪናውን ውጭ ጋር ያቆምና ተያይዘው ይሄዱ ነበር:: ከመሄዳቸው በፊት ዋጋ ቢሷ ትጠራኝና "አሸብር ና እችን መኪና ወልውል!" ትላለች::

ግፒዬ አሁን እኮ ነው ያሳጠብኳት!" ይላታል:: እርሱ የዋጋ ቢሷ መልዕክት ተንቀጥቅጦ የሚታዘዛት ሚስኪን መኖሩን ማሳየት መሆኑን መቼ አውቆ::

ቆይቶ እቤት እየገባ መቆየት ጀመረ::

"አሸብር ና ለስላሳ ግዛ! ና ቢራ ግዛ!" ብታምኑም ባታምኑም ኮንዶም ሁሉ ታስገዛኝ ነበር:: መለላኬ ሳይሆን በዛ እድሜዬ ፋርማሲ ሂዶ ኮንዶም መግዛት ያሳቅቀኝ ነበር:: ፋርማሲስቶቹ በትዝብት ያዩኛል፣ "የተቀደደ ሱሪውን ሳይቀይር..." በሚል ግርምት...ሱሪው የተቀደደ ሰው እንትን እያደረግሽም የተባለ ይመስል::

ከዛ ማደር ጀመሩ:: በጨለማ በዛ በኮረኮንች መንገድ ቢራ ተሸክሜ እጄን የፌስታሉ እጄታ እየከረከረኝ የተላላኩበት ጊዜ መቼም አይረሳኝም (እስከዛሬ እቃ በፌስታል መያዝ አልወድም::)እቴዬ የግቢው በር ላይ ብርድ እያቆራመታት ቆማ ትጠብቀኛለች፤ ገብቼ ቢራውን ስሰጥ ዛፒ ልክ ከፍሪጅ ያወጣችው ያህል ከእጄ ላይ ትወስድና፡

"እንካ ሁለት ፓኬት ሮዝማን ግዛና ና" ትላለች::

በመጨረሻ ጠቅልሎ ገባና አብረው መኖር ጀመሩ:: መኪና ማጠብ ቋሚ ስራዬ ሆነ:: እውነቱን ለመናገር ጥሩ ባል ነበር:: ዋሲሁን ይባላል:: ቤቱ የባለትዳር ቤት እንዲመስል የተቻለውን ሁሉ ይጥር ነበረ:: ዛፒ ግን የሚቋቋማት ዓይነት 'ሚስት' አልነበረችም:: ጉራዋ ፀጉር ያስነጫል፣ በውበቷ ስትመካ ልክ የላትም:: የእናቷ ጫማ ውስጥ ዘላ የገባች ጉረኛ ! እቤት ጉረኛ ሴት እንዴት እንደምትቀፍ:: ከምትናገራቸው አስር ዓረፍተ ነገሮች፣ እስራ አንዱ ስለራሷ ውበት፣ ስለቆዳዋ ጥራት፣ ስለጣቶቿ አለንጋነት፣ ስለልብስና ሽቶዎቿ 'ብራንድ' በቀጥታ አልያም በተዘዋዋሪ ይተርካሉ ::

ዘላ የተዘፈቀችበት ትዳር ከጭፈራ ቤት መዳራት በምን እንደሚለይ ገና ያልገባት እካሲ ብቻ ሀሲናዋን ጥሎ ያደገባት ከንቱ ነበረች:: ዋሲሁን ውጭ መመገብ አይወድም:: የታሸጉ ምግቦችን ገና ሲመለከታቸው ያንገሸግሸዋል:: እንጀራ በሽሮ ወጥ ነፍሱ ነው:: ዛፒ ታዲያ ቤት ውስጥ ለባለቤቷ ምግብ አብስሎ ማቅረብን በሴት ልጅ ላይ የሚፈፀም ታላቅ በደል አድርጋ ነበር የምታየው::

"የአበሻ ወንድ ጓዳለጓዳ ካልተንደፋደፈች ሚስቱ ሚስት አትመስለውም:: ሴት አደባባይ መውጣቷ ያማቅዋል" የምትለው ከእናቷ የወረሰችው ዘይቤ አላት:: በጓዳም በአደባባይም ምንም የማትፈይድ የወሬ ቋት:: ኩኪስ አልያም ጭማቂ ነገር ከፍሪጅ ታወጣና ሶፋዋ ላይ እግሯን እጣጥፋ ቴሌቪዥን

እያየች ትበላለች፣ ትጠጣለች:: ስለፋሽን ሳታቋርጥ ትቀባጥራለች፣ በዓለም ላይ ስላሉ የቅንጦት ሆቴሎችና ጌጣጌጦች "ዋ....ው" እያለች ትቋምጣለች:: ቤቷም የለችም፣ የምትመኘውም ቦታ የለችም:: የትም የሌለች የውሀ ላይ ኩበት ነገር!!

ዋሲሁን ያደገበትን የቤተሰብ ስነስርዓት፣ የኢትዮጵያዊነት ወግ ምሳ ተዘጋጅቶ፣ ቡና ተፈልቶ፣ ቤቱ ሞቅ ብሎ እንደሚጠብቀው በማመን እንደ አባወራ ምሳ ሰዓት ላይ ሲመጣ ዛፒ ጠረጴዛው ላይ እግሯን ሰቅላ ዙሪያዋን የጥፍር ቀለም ጠርሙሶች ከበዋት ቤቱ በአልኮል ሽታ ታፍኖ ስትቆነጃጅ ያገኛታል:: ማታ ሲመጣ ዛፒ ለባብሳ እንዲወጡ ስትጠብቀው ይደርሳል::

"ሃኒ ዮኮ እናድርግ!" ትለዋለች፣ ባል ጋር መታየት እንጂ የባልን መሻት ማየት አልፈጠረባትም፤ የሆሊዉድ ተረቶች ባዶ ጭንቅላቷን ሞልተውት ነበር:: ከንዱን ይዛ መንገድ ላይ ስትውረገረግ ብጤዎቿ፣ "ዋው ምናይነት ጥምረት ነው? ማች ያደርጋል" እያሉ ያወሩላታል::

ሚስኪን ዋሲሁን ሳይወድ በግድ እግሩ አስኪቀጥን ሲዞር አምሽቶ እኩለ ሌሊት ላይ ስልችት ብሎት ይመለሳሉ:: የተሰቀለችበት ባለ ተረከዝ ጫማ ለመራመድ ስለማይመቻት ክንዱ ላይ ተዘፍዝፋ ትወናገራለች::

"ሃኒ ዲጄው 'ሽቶሽ ብራንዱ ምንድን ነው?' ሲለኝ ሰምተኸዋል?"

"አልሰማሁትም" ይላል ትክት ብሎት::

"ሃሃሃሃሃሃ ጠጥተህ ነበር ብ...ዙ...ስካራም ሃሃሃሃ" ትላለች እየተለፋደደች:: እብሯት አይስቅም::

"በናትህ ቀሚሴ ላይ ዋይን ደፋብኝ ያ ወልካፋ አስተናጋጅ" ትላለች ረዥሙ የራት ቀሚሷን እያሳየችው::

"ይታጠባል...ደግሞ አንቺ ስታልፊ እኮ ነው የገጨሽው" ይላታል ስልችት ብሎት::

"እዚህ አገር ምን ላውንደሪ አለ? ሰባት መቶ ዶላር የወጣበት ቀሚስ እንደቀልድ - ምን አይነት አገር ነው?" ብላ ቀሚሷ በአደባባይ ባለመከበሩ አስራ አምስት ቀን ታወራለች:: ስለ ተራ ቀሚስ ሳይሆን ስለ ባንዲራ መደፈር የምታወራ ነው የምትመስለው::

ጧት ተነስቶ በተሰላቸ መንፈስ ወደ ስራ ሲሄድ ዛፒ አትሰማም አትለማም - ተኝታለች:: ምሳ ሰዓት እንደገና ጓደኞቿ ጋር እንደሄደች ትደውልለትና፣ "ምሳህን ውጭ ብላ ሃኒ" ትለዋለች፤ በዛውም 'እያችሁ ባሌን ሳዘው!' እያለች ለከንቱ ጓደኞቿ:: ምሳ፣ ራት፣ ቁርስ በአበሻ ባህል ከምግብ የዘለለ ፋይዳ ያለው ጉዳይ መሆኑ ለዛፒ አልታያትም ነበር::

የቤተሰብ እትብት ከእናት ማዕድ ጋር እንደሚያያዝ ማን ይመክራታል? ዋሲሁን ለአንድ ዓመት እብሯት ቆየና ከቶ ደግ ሳይናገር፣ "አንቺ ጋር እንግዲህ በቃኝ" ብሏት ሄደ...!! መሄድ ብቻ

አይደለም፣ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ድል ባለ ሰርግ ሌላ ቤት አገባ። ዛሮ መጀመሪያ፣ "ጕርግ ይበል! ለሞላ ወንድ!" አለች። ቆይታ፣ "ይሄ ችጋራም ፒዛ እንኳን መብላት ያለማመድኩት ዘሮኩ፣ ጥጋበኛ የደሀ ልጅ!" ማለት ጀመረች። በመጨረሻ ፎቶውን እያየች ማልቀስ ሆነ ስራዋ። እኔ

ዛሮ ሲበዛ ቆንጆ ናት። ልብሶቿ ጌጣጌጦቿ የብዙ ሴቶች የቁም ቅዠት። ግን ዋሲሁን ከሄደ በኋላ ወንድ የሚባል አልቀርብ አላት። ይፈሯታል። የተጋነነ ቁንጅናዋና ውድ ጌጣጌጦቿ የማትደፈር ግዛት ስለሚያስመስላት የሚመኛት እንጂ ደፍሮ የሚቀርባት ጠፋ።

የአበሻ ወንድ' ተመካከሮ ሸሸ...

ዛሮ ታዲያ የለየላት ሰካራም ሆነች። ማታ ማታ ሰክራ ትመጣና፣

'ስቴፒድ፣ ቅቤያም ሴቶቻችሁ ጋር እየሄዳችሁ ተጋደሙ። በርሜም ሴቶቻችሁን እንዘፍዝፉ፣ በምን አባታችሁ ዕድላችሁ ነው እኔን የምትሰሙት!? እዛ የጕራጌ ጫማ ደንቅረው የቻይና ሱሪ ውስጥ የተቆጠሩ ኋላ ቀር ሠራተኛ ሴቶቻችሁ ጋር ኑሩ! 'ጎ ቱ ሄል' ቆሻሾች! በርሜሞች! በ'ጂም' አበገብ እልፋችሁ የማታውቁ" እያለች በረንዳዋ ላይ ቆማ ድፍን የአበሻን ወንድ ትሳደባለች ።

በጣም ስክር ብላ ጨርቅ ሆና ያመጣት ባለታክሲ ግቢ ውስጥ ደግፎ አስገብቷት ሲመለስ ትጠራኛለች፣

"አሸብር ና ጫማዬን አውልቅ!"

ጫማዋን አወልቅላታለሁ። እቾ የውሻ ልጅ! የእግሮቿ ጣቶች የመላዕክትን ጣቶች ይመስላሉ፤ አረዛዘማቸው፣ ጥራታቸው።

"ቀስ በል አንተ ! ሶሉን ልትገነጥለው ነው። የእናትህን ኮንን ጫ...ማ እያረከው። ይሄኮ - አራት መቶ ዶላር የወጣበት ነው። በዚች ችጋራም አገር ወረቀት ሲመነዘር ስንት ይሆናል - አንጀኛ አይደል ከክላስ የወጣኸው" (እያነማጣለሁ። ማን ነገራት? ስለመፈጠሬም የማታስታውስ ሴት ደረጃዬን እውቀችው...።)

"እስኪ አስበዋ፣ እኔ የቻይና ሸራ ጫማ የምደነቅር መሰለሀ?" እየለፈለፈች መኝታ ክፍሏ አስገባታለሁ። አቤት ሽቶዋ! ቆም ብላ አሊጋውን በጥላቻ ታየውና፣ ወደ ሳሎን ትዞሩኛለች። እያንዘፋዘፍኩ ባሎን ሶፋው ላይ አስተኛታለሁ። እየለፈለፈች እንቅልፍ ይወስዳታል።

ቤት ምንም እንዳልተፈጠረ አታናግረኝም፣ መኖሬም ትዝ አይላትም።

"ሮን አጠላታለሁ።ጕረኛ ናት። ሰው ትንቃለች። ግን የማይደበቀው ሀቅ ከእናቷ ትሻላለች። ድካት አቲዬን ትጠራትና፣

"ያውልሽ ይሄን ውብጅ!" ብላ ገና ያልተከፈተ ውድ ሽቶ ትሰጣታለች።

እቴዬ ግን አጇን የሆነ ነገር ሲቆርጣት ብቻ ቁስሉ ላይ ስትረጨው ነው የማያት::

ሌላ ቀን እቴዬን ትጠራትና፤ "እስቲ ቡና አፍይ!" ትላታለች:: እቴዬ ሽር ጉድ ብላ፣ እሚጫሳ ቤቱን ነፍስ ትዘራበታለች:: ዛሮ ግን ቡና አትጠጣም:: እቴዬም ስለምትፈራ አትጠጣም፣ እንሳሰታ ወደ ቤት ትመለሳለች::

ዛሮ አዕምሮዋ ጤነኛ አለመሆኑን መጠራጠር ጀምሬ ነበር::

አንድ ቀን ሰላማዊት የምትባል የሰፈራችን ልጅ አገባችና ሰፈሩ በጭፈራ ቀውጢ ሲሆን ዛሮ ጠራችኝ፤

"ማናት ያገባችው?" አለችኝ::

ነገርኳት::

"ቆንጆ ልጅ ናት እንዴ?"

"አንድ ቀን ጋሽ ዋሲሁን ጋር ሆናችሁ አሟት በመኪና ሆስፒታል የወሰዳችኋት ልጅ ናት እኮ::"

"እና እሷ ልጅ ቆንጆ ናት እንዴ?"

ምን ልበል፤ ጨነቀኝ:: "እኔ እንጃ!" አልኩ::

ዝም ስትል፣ የጨረሰች መስሎኝ ልሄድ ስል፤

"መልኳ ከእኔ ይበልጣል ?" አለችኝ::

"እረ..." ብዬ ሳቅኩ::

"ምን ያስቅሃል? ዝም ብለህ የጠየቅኩህን አትመልስም?" አለች በቁጣ..

ፈገግታዬ ፊቴ ላይ ከስሞ፣ "አንቺ ላይ...ጫፍሽ ላይ አትደርስም፤ አንቺ እኮ በጣም ቆንጆ ነሽ" አልኳት:: ከልቤ ነበር የተናገርኩት::

ትኩር ብላ አየችኝና፤ ወደ መኝታ ክፍሏ ገባች:: የክፍል ደረጃዬን የማታውቀው እንዳስገረመኝ ቁንጅናዋን አይቼው የማላውቅ መስሏት ነበር መሰል::

"ምን አስለፈለፈኝ" እያልኩ ወደ ቤቴ ገባሁ:: ግን ያደነቅኳት ሳይሆን ልኳን የነገርኳት ያህል ውስጤን ደስ ብሎት ነበር::

እየው እንግዲህ፤ "የነገር አመጣጥ እንደ ውሀ አፈሳሰስ ነው" ነው የሚለው መጣፉ:: ይሄን ነው...ጠብ...ጠብጠብ...ፈሰስ፤ ኮለል...ጎረፍ...ዥቅዥቅዥቅ፤ ከዛ ግንድ የለ ድንጋይ ይጠራርገዋል:: ጠብታው መኝታ ቤቱ ነው፣ ግንዱ ሰርቪስ...:: አሰቴር አወቀ ዛሮ መኝታ ቤት ድምጽዋን ከፍ

አድርጋ ትዘፍናለች:: ምን አያለች - አኔንጃ !! ምናልባት እንዴት እንደምትገርፍ፣ እየመከረቻት ይሆናል:: አስቴር እኮ ዘፋኝ አይደለችም መካሪ ናት:: ስንቱ መኝታ ቤት እየገባች በጆሮቸው የሚሆንም የማይሆንም ነገር ሹክ ስትል ከርማለች:: አስቴር ሲረኛ ናት!! የዘፒ ዓይን እንደ እንቴና መዞ ወዲያው አሳድጎኛል፣ ሳድግ የባሰ ፈሪ ሆንኩ::

## ክፍል አስራ ስድስት

ጥቁር አምበሳ፣ ኮከበ ፅባህ፣ ምኒሊክ፣ መነን፣ አዲስ ከተማ፣ ድልበር፣ ቦሌ ከሚማሩ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ሁሉ፣ "አንደኛ ጎበዝ አንተ ነህ" አሉና የምስክር ወረቀት ሸለሙኝ:: እኔ ግን ጥቁር አምበሳ፣ ኮከበ ፅባህ፣ ምኒሊክ፣ መነን፣ አዲስ ከተማ፣ ድልበር፣ ቦሌ ከሚማሩ ሴት ተማሪዎች ሁሉ አንደኛ ቆንጆ የሆነችው ዮርዳኖስ የት ተቀምጣ ይሆን እያልኩ በዓይኔ ከተሰበሰቡት ሰዎች መሀል እየፈለግኳት ነበር::

ዮርዳኖስ ማለት ማንም አይደለችም፤ ለመጀመሪያ ጊዜ ከመሬት ተነስታ ጉንጬን የሳመችኝ ልጅ ናት:: ጉንጬን ሳይሆን በቀኝ በኩል ከከንፈሬ ጥግ ሁለት...ኧረ አንድ ተኩል ሴንቲ ሜትር ርቀት ላይ ነው የሳመችኝ (ለምላ ጉንጬ::)

ዮርዳኖስ ቀይ ልጅ ናት:: ለነገሩ ቀይ ሳትሆን ጠየም ያለች ግን ቀይ ዳማ እንደሚሉት ሳትሆን አትቀርም:: እቦ የራሷ ጉዳይ ገደል ትግባ ብትፈልግ ሌጭጬ!! ይሄው ስንት ጊዜ ሴትም ቀንም ዮርዳኖስ ቀይ ናት ቀይ ዳማ እያልኩ ስዛብር ማደር ከጀመርኩ:: እንኳን ሴት ልጅ፣ ቆንጆ ወጣት ሴት ልጅ፣ ነፍስ ካወቅኩ ጀምሮ ሰው ሲስመኝ የመጀመሪያዬ ስለነበር ዮርዳኖስ ጉንጬን ሳይሆን ልቤ ላይ እንደሳመችኝ አርግጠኛ ነበርኩ:: ማስረጃ ብባል፣ ከዛን ጊዜ ጀምሮ አተነፋፈሴ ልክ አይደለም፤ ሳያት የሆነ ነገር ያፍነኛል:: ሳላያት እንደ ነብር አዳኝ ትንፋሼን ውጬ በጉጉት በዓይኔ እፈልጋታለሁ:: ሳላያት ታፍኜ ሳያትም ታፍኜ ልሞት ሆነ::

"አንቺ ዮርዳኖስ የምትባይ፣ ምን ቆርጦሽ ነው ኧረ ከከንፈሬ አንድ ተኩል ሴንቲሜትር ርቀት ላይ በሚሞቅና በሚለሰልስ አርጥብ ከንፈርሽ የሳምሽኝ?" ብላት ደስታዬ:: ግን ታፍኛለሁ!!

አርብ ቀን ከትምህርት ቤት ወጥቼ ወደ ቤቴ እሄዳለሁ:: ምንም እያስብኩ አልነበረም:: ዝም ብዬ እየተራመድኩና በግዴለሽነት ሁሉንም ከፊቴ ያለውን ነገር እየተመለከትኩ እራመዳለሁ::

"አሸብር!" አለችኝ ከኋላዬ::

ስሜ ሲጠራ የምደነግጠውን ያህል የሰይጣን ስም ቢጠራ እንኳን አልደነግጥም:: ሰዎች ስሜን ሲጠሩኝ ከዝምታዬ ባሕር በምላሳቸው መንጠቆ ጠልፈው ያወጡኝ ይመስለኛል:: ከእኔ ጋር ተታበተብኩ !! ሞራሽ ጠሪዋ ዮርዳኖስ ስትሆን ደግሞ፣ በመንጠቆው ላይ መረብ

ብዙ ሰዎች ወደኋላ አብረው ዞሩ:: ሰዉ ሁሉ ሳይጠራ ሲዞር፣ ጠሪዋን ተመልክቶ ደስ ካሉችው ስሙን 'አሸብር' ሊያስብል ያሰበ ይመስል እኔ ለተጠራሁት መዓት ሰው ዞረ::

ዮርዳኖስን ዞሬ አየኋት:: ጉርድ ቀሚሷ በደንብ አላራምዳት ስላለ በእጇ ሰብሰብ አድርጋ ወደ እኔ ትጣደፋለች:: እግሯ ቀይ ነው:: ባቷ ፍርጥም ያለ ከአድሜዋ በላይ ትልቅ የሚያስመስላት ነው:: ባቷ ብቻውን አስራሁለተኛ ክፍል ይመስለኛል:: ጡቶቿ ደግሞ እዛና እዚህ ይላጋሉ:: ስትጣደፍ፣ በሁለት እጆቿ ከንዶች ገፋ አድርጋ ታረጋጋቸዋለች:: ፀጉርዋ አጭር ነው:: ማንባሯ ትንሽ ወጣ ያለ:: ቀረበችኝና ፈገግ አለች:: ዓይኖቿ እንዴት ያምራሉ::

ኡፍፍፍፍፍፍፍፍፍ አሁን ስትጠራኝ መኪና እየነዳሁ ቢሆን ኖሮ ከዓይኖቿ ለማምለጥ ስል ፊት ለፊት የሚያላዝነው ቦቅ መኪና ጋር አላተም ነበር:: የያዘው ነዳጅ ይዘረገፍና ከዮርዳኖስ ፈገግታ እሳት ለኩሶ ጭስ ፀሐይን ጥቁር ጉልቻ አስከትመስል የሚያጥን:: ሰማይ የሚነካ እሳት ይነሳ ነበር:: በቁሜ ቅዠት ስጀምር ታወቀኝ::

"እንዴት ነው የምትሮጠው ወተት ጥደሃል ቤትህ ?" ቀለደች::

አልሳቅኩላትም:: ስላልሳቅኩላት ግን ራሷ ከመሳቅ አልታቀበችም:: እየሳቀች ወሬዋን ቀጠለች::

"ቤትህ በዚህ በኩል ነው እንዴ ?"

"እዎ"

"እኔ ግን አይቼህ አላውቅም..."

ዝም አልኩ:: ካላየችኝ ምን ይሁን፣ ወሬዋን ቀጠለች::

...፧...

እዎ

...፧...

እዎ

...፧...

እዎ

"እዎ ብቻ ነው እንዴ የምታውቀው ?"

"እይ" አላታለሁ:: እነጋገሬ ሴት የመፍራት ሳይሆን ሰው የመሰለቸት ነበር:: እንዳንዴ የሰዎች ንግግር ይረዝምብኛል::

"ሰላም" ሲሉኝ ይረዝምብኛል:: ሰ..ላ...ም፣ እጃቸውን እንስተው፣ ማንባራቸውን ነቅንቀው፣ ፈገግ

ብለው:: አንዳንዶቹም እጃቸውን ለሰላምታ ዘርግተው፣ ይሄን ሁሉ ነገር አድርገው፣ "ሰላም" ብቻ !! ዝም አለች:: አብረን ሄድን ሄድንና የሆነ መገንጠያ ላይ ስንደርስ ክንዴን ይዛ አቆመችኝና ተንጠራርታ ሳመችኝ:: ምንም አላማ የሌለው፣ ምክንያት የሌለው ወይም "ደፋር ነኝ እዩኝ" የሚል ምናልባትም፣ "ዘመናዊ ነኝ መንገድ ላይ የወንድ ጉንጭ መሳም አልፈራም" አሳሳሟ የሆነ ድምፅ አለው፣ የሚያፏጭ ዓይነት ድምፅ:: የመምጠጥ አይነት ድምፅ:: የበዛ ግለኝነቴን ምጥጥ አድርጋ የሐሳብ ሀይቁን አደረቀችው:: የሰው አለማያ ሆንኩ !! ባደረቀችው የብቸኝነት ኩሬ ራሷን ሞላችው::እዚህ ዮርዳኖስ የምትባል ውሃ የሞላችው ባህር ውስጥ ልቤ አምልጦኝ ገባ:: ይሄው አስባታለሁ፣ የተረገመች ዮርዳኖስ !!

እየጠበቀችኝ ይሁን እየተገጣጠምን ብቻ ከዛን ጊዜ በኋላ በየቀኑ እንገናኝ ጀመረ:: ሲቆይ ግን ጉዳዩ የነፍስ ቀጠሮ ሆነ:: ጠበቅኩሽ ሳለማለት በቀስታ እየተራመድኩ እጓዛለሁ፣ ከየትኛውም ርቀት ላይ አውቃታለሁ::

ፊት ለፊት ሳላያት መንፈሷ እዛ አካባቢ ካረበበ ትካሻዬ ሹክ ይለኛል:: ትከብደኛለች፣ "ሃይ አሹ" የሚል ድምጽ አጠብቃለሁ:: "ሃይ አሹ" ትለኛለች ውስጣችን ያውቃል እንደምንጠባበቅ:: ከዛም ታወራኛለች::

"ዛሬ ይበርዳል!"

"አዎ"

"ሆም ዎርክ ሰራህ ?"

"አዎ"

.

.

"አዎ ብቻ ነው የምታውቀው::"

"እይይ_":: አሁን ግን ምን ማውራት እንዳለብኝ እያሰብኩ ነው...! ችግሩ፣ እስቤ ሳልጨርስ እንደርሳለን::

ስንመለስም እንገናኛለን:: ስንመለስ መለያያችን ላይ ትስመኛለች፣ "ቻው" ከሚል ስርቅርቅ ያለ መለያየቱ ያስከፋው ድምፅ ጋር ከንፈሯ ጆሮዬ ላይ ያፏጫል::

እንዴ መሀል ጉንጬዩ ላይ፣ እንዴ ዝቅ እንዴ ከፍ እያለች ትስመኛለች:: በየቀኑ ትስመኛለች:: ዝም ብዬ እሳማለሁ:: ከንፈሯ ከብ ነው፣ በሃሳቤ ስትስመኝ ከብ ቅርፅ ጉንጬዬ ላይ የታተመ ይመስለኛል፣ የሳምንቱ ከቦች ተቆላልፈው፣ ቅዳሜ የኦሎምፒክ አርማ ጉንጬዬ ላይ ታትሞ በጉልህ ይታየኛል:: አንዱ ከብ እንደ ደቡብ አሞ ሴቶች፣ ከንፈሬን ተልትሎ ከንፈሬ ላይ ተንጠልጥሎ እየሁት - በህልሜ!

ብቸኛ ግጥም ነበር፡፡ ወደፊትም ግጥም አንድ ቀን ግጥም ጻፍኩ፡፡ በህይወት ዘመኔ የጻፍኩት ብቸኛ ግጥም ነበር፡፡ ወደፊትም ግጥም አልጽፍም !! ግጥም ያስጠላኛል፡፡ ሰው ዝም ማለት እያለለት፣ ለማውራት ቃል መጠምዘዝ መድከም ምን ያደርግለታል? – 'ቢፅፍ ባይጠቀም፣ ባይፅፍ ባይጎዳ' ባይ ነኝ፡፡ ደግሞ አዲስ ግጥም ሰምቼ አላውቅም፡፡ ግጥሞች ሁሉ አንድ ናቸው፤ ደራሲያቸው ይለያይ እንጂ ባይ ነኝ፡፡

እኔን የገረመኝ (ርእሱ)

እኔን የገረመኝ፣

እኔ የጠላሁትን፣

እኔነት ሳትጠላ፤

ልጅቱ ስትሰመኝ !!

ቢቃ !! ይሄው ነው ግጥሙ፡፡

ግጥም ማለት ቤት የሚመታ፣ ቀለሙ፣ ስንኙ የሚሉ ሰዎችን ተዋቸውና ግጥም ማለት እስክርቢቶ ሳትጨብጥ ወረቀት ፊትህ ሳይነጠፍ እንደ እፍ ወለምታ ከከንፈርህም፣ ከነፍስህም፣ ከእዕምሮህም የሚያመልጥ እውነት ነው፡፡ ለምሳሌ በዚች ዓለም ላይ ከሰማኋቸው ግጥሞች እሳዛኙ የእቴዬ ግጥም ነው፡፡ ርእሱ፣ "እሺ"፤ ግጥሙም፣ "እሺ" - አበቃ፡፡

ማንም ለጀመረው የትዕዛዝ ስንኝ፣ እቴዬ 'እሺ' የሚል ግጣም እየሰራችለት፣ የማንም ቤት እንዲቆም አድርጋለች፡፡ የእኔ እናት ገጣሚ ናት፡፡

"ቤት ጥረጊ!"

"እሺ!"

"ልብስ እጠቢ!"

"እሺ"

"ሂጂና ሳሙና ግዢ!"

"እሺ"

"እንጀራ ጋግሪ!"

"እሺ"

"ደመወዝሽን ሌላ ቀን ውሰጂ!"

"እሺ"

ግጥም ይሄ ነው !! ከትዕዛዙ እኩል ይሁንታው ዜማ ሲፈጥር:: እናም ያሉትን ሲሆኑ::

ቤት መምታት ይሄ ነው:: መጥፎ ቃል የደሀ ስጋ ለብሶ አዞሽ ቤት ሲያድር፣ በዓመቱ አይኑ በምኞት የሚዛብር 'ገጣሚ' "ውዴ...ዘላለም ልፈጥፈጥልሽ፣ ልቀራመትልሽ" ቢል አይገባኝም:: ግጥም ከቃል ሲጭበረበር ሳይሆን፣ ከነፍስ ሲመዘዝ ከሕይወት ሲቀመም ነው ቤት የሚመታው::

ቢሆንም ግጥም ገጠምኩ:: አላሰብኩም፣ አልደለዝኩም፣ አልሰረዝኩም:: አንድ ደብተሬ ጀርባ ላይ በቀጥታ ጻፍኩት:: ያውም ኬሚስትሪ የሚባል ትምህርት እየተማርን ልክ ስልክ ቁጥር እንደሚጽፍ ሰው ሳላስብ ግጥም ጻፍኩ:: ከብዙ ዓመት በኋላ ይሄን ግጥም ያሳየሁት ገጣሚ፣ "ጭብጡ የላላ ወደታች የተጻፈ ስድ ፅሁፍ ነው የሚመስለው" አለኝ:: ጉዳዩ አልነበረም:: ድርሰቱቼ ግጥም መጻፌ ገረመኝ:: በልጅቱ ጉንጩዋን፣ ያውም አንድ ተኩል ሳንቲሜትር ለከንፈሬ የቀረበ ቦታ ላይ መሳሜ እንጂ !!

ዮርዳኖስ አንድ ቀን ጠራችኝ፣ "እሹ" ብላ !!

"እሹ" ማለት ለካ አሸብር ማለት አይደለም፣ በጭራሽ:: "እሹ" ማለት ከአሸብር ጋር የሚገናኘው ሁለቱም አጠራር ስለሚያስደነግጡኝ ብቻ ነው እንጂ አሸብር "እሹ" አይደለም:: ከየት አመጣቸው ግን እቸ ዮርዳኖስ !! ደግሞ "እሹ" ከአሸብር ይረዝማል:: "እሹ"፣ ሙሉ ቀን ጆሮ ላይ ያቃጭላል - አይገርምም ?

ከተማሪዎች ሁሉ አንደኛ ወጥቼ የተሸለምኩ ቀን ሌሊት ከእንቅልፌ ነቃሁ:: ምን እንዳነቃኝ አላገኘሁም:: ፀጥታው የነቃ ያስተኛል እንጂ የተኛ ሊቀሰቅስ:: ግን ነቃሁ:: ነቃሁና ልክ ዓይኔን ስከፍት፣ ዮርዳኖስ ያንኳኳችውን በር የከፈትኩ ይመስል ምስሏ ፊት ለፊቴ ተደቀነ:: ልትስመኝ ስታምጠሙጥ፣ ስትስቅና "እሹ" ስትለኝ፣ "ፍቅር ይዞኛል" የሚል የማልፈልገው ዓረፍተ ነገር ከምኔ እንዳመለጠ ሳላውቅ ፈነዳ - ...ቡ‹ምምምምምምምምምምምምምምምምም› ፍቅር - እርፍ !!

ልክ እንደ ግጥሙ ያልፈለኩት እንባ ጉንጬ ላይ ተንኳለለ:: በምድር ላይ አለኝ ከምለው አንድ የሆነ እምነት የተካኩዶኩ መሰለኝ:: ለነብስ ጉዳይ የተበደርኩት ብር ከኪሴ የጠፋ ያህል ተሰማኝ::

እንባዬን ጠረግኩና መብራቱን አበራሁት:: ፊት ለፊት ያለው ግድግዳ ላይ በፌስታል የተሰቀለ የአቲዬ ልቃቂት:: ራቅ ብሎ ትንሽ መጋረጃ እንደ ዕቃ ቤት የምንጠቀምባትን ቦታ የከለለች፣ ከመጋረጃዋ ፊት ለፊት አቲዬ ፍራሽ ላይ አሮጌ ብርድ ልብስ ለብሳ ኩርምት ብላ ተኝታለች:: ቤታችን አስጠላኝ:: ሩሴ አስጠላኝ:: አስረኛ ከፍል አስጠላኝ:: ከአሁን በኋላ ስንት ዓመት ተምሬ ነው ስራ የምይዘው? ዝም

አቲዬ ድንገት ባነነችና፣ "አሸብር ምነው አመመህ እንዴ?" አለችኝ፣ ከወገቧ ቀና ብላ:: ፊቷ ላይ ማዲያት ነገር አለ:: ብዬ አየኋት:: አቲዬ እያረጀች ነው:: ደረቷ ከስት ብሷል::

ማንባሯ ላይ ብዙ መስመሮች ተጋድመዋል:: አንገቷ ስር ያለው ቆዳም ተሸብሽቧል:: እስከዛሬ አላየኋትም ወይስ "እውር ያደርጋል" የሚሉት ፍቅር የእኔን ዓይን ገለጠው ? ገመናዬን አላይቶ፤ 'ልክህን እወቅ!' ሲለኝ:: አቲዬን ስራ እስክምይዝ በምን ላፅናናት?

"አቷ ደስ ብሎኝ ነው" አልኳት ፈገግ ለማለት እየሞከርኩ::

"እሰይ፣ ኧረ ደስ ይበልልኝ..." አለች ከእኔ የበለጠ ፈገግ ብላ:: ምኑንም ሳትሰማ፣ 'ምን ተገኘ?' እንኳን አላለችኝም:: በቃ ደስ ካለኝ ደስ ይላታል::

"ከአዲስ አበባ ተማሪዎች ሁሉ አንደኛ ወጥቼ ሰልፍ ሜዳ ተማሪዎች ፊት ተሸለምኩ" አልኳት፤ 'አዲስ አበባ' ያልኩት ሆን ብዬ ነበረ:: 'የገፉሽ ሕዝብ ሰንፍ ነው፣ ያንከራተተሽ ሕዝብ ልጆች በእንቺ በተንከራታቿ፣ በአንቺ ልጅ አፈር ድሜ ግጧል:: ተበልጠዋል:: በእጅ አዙር በልጠሻቸዋል' ለማለት፣ ሌላም ለማለት...

አቲዬ ፊቷ በፍርሀት ተወረረ፣ "ልጄን የሰው ዓይን ውስጥ ሊያስገቡብኝ" አለች::

"አቲዬ ደግሞ፣ ሁልጊዜ እንተያይ የለ" አልኳት:: ዓይን ውስጥ ግን ገብቻለሁ ልክ ነው:: ዮርዳኖስ የምትባል ቡዳ በልታኛለች - በከንፈሯ !!

"በል ጧት ሂድና ማለፍህን ንገራት!" አለችኝ በአገጯ ወደ ዛፒ ቤት እየጠቆመች:: አቲዬ ከሚገርመኝ ባህሪዋ ማንንም በስም አትጠራም:: ተመልከቱ ምን ያህል እንደተበደለች እች ሴት:: የሰውን ስም መጥራት በራሱ መናቅ እንዳይመስልባት ትፈራለች - ትፈራለች !! እናም ለዛፒ ምን ብዬ እንደምነግራት አሰብኩ::

'ዛፒ አንደኛ ወጣሁ'...'ዛፒ አለፍኩ'...ዛፒ ስካራም...ዛፒ ጠብራራ ዮርዳኖስን አፈቀርኳት... ኡፍፍፍፍፍፍ ላብድ መሰለኝ:: መብራቱን አጠፋሁት:: ጨለማው ውስጥ ዮርዳኖስ ገጭ አለች - እች ማንባራም ! አግሯ ቀይ ነው:: ጡቶቿ ትልልቅ ናቸው:: ስትራመድ ይነቃነቃሉ:: ግን ጡት ሴቶችን ይከብዳቸዋል...አይከብዳቸውም? - ታዲያ 'ዮርዲ' ለምንድን ነው ስትራመድ ጎበጥ የምትለው::

"ዮርዲ" ነው ያልኩት ? ሃሃሃሃሃሃሃሃሃ ከአቲዬ ቀጥሎ በዚች ምድር ያቆላመጥኩት ስም እነሆ...

## ክፍል አስራ ሰባት

ጠዋት ዩኒፎርሜን ለብሼ ደብተሮቼን እዘጋጀሁና እየቀፈፈኝ ወደ ትልቁ ቤት ሄጄ አንኳኳሁ::

"ማነው?" አለችኝ ዛፒ:: ደነገጥኩ::

"ኣ...ኔ ነኝ" አልኩ እየፈራሁ::

"ማብ ክፍት ነው":: ገፋ ሳደርገው የሚያብረቀርቀው የጣውላ በር ድምፅ ሳያሰማ ተከፈተ - ክፍቱን ነው ያደረው ማለት ነው:: ዝርክርክ ያለው ሳሎን ጋር ተፋጠጥኩ:: ዛፒ ሰፋው ላይ የሌሊት ልብስ ጣል አድርጋ ተኝታለች:: ፊቷ የተቀመጠው ጠረጴዛ ላይ የሻይ ብርጭቆ፣ የውሃ ጠርሙስ፣ ሩብ ብቻ የተበላ ሰላጣ፣ ምንም ያልተነካ ዳቦ ዝርክርክ ብሏል:: ብዙ ምግብ ማቅረብና ምንም አለመብላት ልማዷ ነው - ይገርመኛል::

"ምንድነው በጧቱ?" አለች እየተነጫነጨች:: ድምጿ የወንድ ይመስላል - ጎርንኗል::

"ኣ...ትምህርት ቤት - ከሁሉም ትምህርት ቤቶች አንደኛ ወጣሁና ...ል...ንገርሽ ብዬ ነው" ድምጼ ተንቀጠቀጠብኝ::

ቀጥ ብላ ግራ በገባው ፊት አየችኝ:: የሌሊት ልብሷን ትከሻዋና ትከሻዋ አካባቢ ይዛ አስተካከለች፣ አቤት ደረቷ ቅላቱ ይንበገበጋል:: ከኋላው ቢጫ መብራት የበራበት መስተዋት ይመስላል::

"እኔ ምናገባኝ ታዲያ?!" የምትል መሰሎኝ ነበር:: ድንገት የሆነ ነገር ትዝ እንዳለው ሰው ፈገግ ብላ፣

"እና ሳመኝ! እንደዚህ ነው እንዴ የምስራች የሚነገረው? መርዶ አስመሰልከው እኮ!" አለችኝና ሁለት እጆቿን እንደ ክንፍ ዘረጋቻቸው፤ ያውም በፈገግታ:: ሁለት ጡቶቿ አፈጠጡብኝ::

ግራ ገብቶኝ እንደቆምኩ፣ "ና እንጂ ሳመኝ!" ብላ ጮኸችብኝ::

በደመነፍስ እየተደነቃቀፍኩ ሄጄ...ሄጄ...ሄጄ..ሄጄ..ሄጄ..ሄጄ እጆቿ ሲጠመጠሙብኝ ሁሉ እርምጃዬን ያቆምኩ አልመሰለኝም:: ጥብቅ አድርጋ አቅፋኝ፣ "ጎበዝ የኔ ወንድም እኮራብሀለሁ!" አለችኝ፤ በለው...!! ከሽ አለ የሻዩ ብርጭቆ ከጠረጴዛው ላይ ወድቆ:: "ይሰበር ተወው!" አለችኝና ጉንጬን ስማ ለቀቀችኝ:: ይሄ ቤት ለካ የወይዘሮ አጥፍወርቅ ቤት ነው !!

ከዛፒ ጋር እንደወጣሁ በደስታ ሰክሬ መንገዱን ሁሉ፣ ሰውን ሁሉ አየሁት:: መቼ ነው ይሄ ትልቅ የመኪና ኪራይ ማስታወቂያ ነዳጅ ማደያው ፊትለፊት የተሰቀለው ? መቼ ነው ይሄንኛው ሕንፃ ተሰርቶ ያለቀው? ወቸ ጉድ አዲስአበባ እንዴት ተለውጣለች? ከሆነ አገር የመጣሁ መሰለኝ:: ደግሞ ደስ የሚል ነገር ይሸተኛል:: አፍንጫዬም ዛሬ ገና የተከፈተ ይመስል...::

ዮርዳኖስ ጋር ስንገናኝ፣ "ምነው?" አለችኝ::

"አ" አልኳት::

"አይ ቆመህ ሳገኝህ ነዋ" አለችኝ:: ለካስ ዮርዳኖስን ቆሜ አልነበረም የምጠብቃት:: ያልጠበቅኳት

ዛፒና ዮርዳኖስ እኔ በምባል ኳስ መስዬ ነበር መጠበቅ የነበረብኝ፡፡ ሳመችኝ ጉንጬን፡፡ "ተስመሀ ትወጣለህ፣ ሰመው በከንፈራቸው እየተቀባበሉ 'ሾሊ ቦል' የሚጫወቱ መሰለኝ፡፡ ድፍን አዲስአበባ እንደ ዳቦ፣ እንደ ይቀበሉሀል" የሚል ትንቢት ከሰማይ የታወጀም መሰለኝ፡፡ (ቀስ ትደርሳላችሁ አትጋፉ...ሂሂሂሂ) ዘይት፣ እንደታከሲ እኔን ለመሳም የተሰለፈ መስሎ ተሰማኝ፡፡

"ደግሞ አሪፍ ሽቶ፣ እፉፉፉፉፉፉ ዮርዳኖስ ፈገግ ብላ አፍንጫዋን በመቀሰር ጠጋ አለችኝና፣ ያደረጋብህ ማነው?" አለችኝ፡፡ አፈርኩ፡፡ ለካ የዛፒ ሽቶ ነው ሲከተለኝ የነበረው፡፡ የዛፒ ሽቱ የዋዛ አልነበረም፡፡ ከዚች ቀን ጀምሮ አድማ ልኬን ሲከተለኝ ነው የኖረው፡፡ ሲያሳድደኝ ሳይሆን ሲከተለኝ፡፡ የሆነ ዞራዩዬን ከብቦ እንደ እናት እቅፎኝ፡፡

ሰው ወደ ውስጥ የሚስበው አየር 'ኦክስጅን'፣ ወደ ውጭ የሚያስወጣው 'ካርቦንዳይኦክሳይድ' እያሉ ያስተማሩን ቅኔ ነበር - ሳይንሳዊ ቅኔ !! አሁን አሸብር ወደ ውስጥ የሚስበው ፍቅር፣ መፈቀር፣ መከበር፣ መፈለግን ነው፡፡ ወደ ውጭ የሚተነፍሰው እርካታ፡፡ የአየር ብክለት ማለት ሌላ ትርጉም የለውም እኮ - የተገፉ፣ የተገለሉ፣ የተናቁ፣ ሕዝቦች ጥላቻን ወደ ውስጣቸው ስበው መልሰው ጥላቻን ወደ መላው ዓለም መተንፈሳቸው ነው፡፡ መፍትሄው የፍቅር ችግኝ በልባቸው መትከል ነው፡፡ እነሆ ዮርዳኖስ የተከለችውን ዝግባ ዛፒ የምትበል ዝናብ ስታረሰርሰው ዘርፈፍ ብሎ በቀለ፡፡ ሕያውነት ከስሩ አረፍ የሚልበት ጥላ ሆነ፡፡

እኔማ ዛፒ ጥቁር ደመና አዝላ እያጉረመረመች ሰማይ ላይ ተንጠልጥላ ሳያት፣ መሽቆጥቆጥና ጥላቻዬን እንደ ዣንጥላ ስዘረጋ ነበር የኖርኩት፡፡ ከፉትም ጉልበት የሚኖረው እንደከፋት ልንቀበለው በተዘጋጀነው መጠን ነው፡፡

*ክፍል አስራ ስምንት*

"አንተ ሴት ነህ እንዴ?" ብላ ዛፒ ሳቀችብኝ፡፡ አፈርኩ፡፡ አንደኛ መውጣቴን ምክንያት በማድረግ ዛፒ ልብስ ልትገዛልኝ ወሰደችኝና 'ምረጥ!' ስትለኝ መጀመሪያ አጄ አንድ ቀሚስ ላይ አረፈ፡፡ ለአቴዬ ልኳ የሚሆን ቀሚስ ነበረ፡፡ ለዛ ነበር የሳቀችው፡፡

ልብስና ጫማ ገዛችልኝ፡፡ የሱሪዬን ቁጥር ስጠየቅ አላውቅም ነበር፡፡ ሱሪ ገዝቼ አላውቅማ፤ የጫማ ቁጥርም አላውቅም፡፡ የሀብታም ልጆች ልብስና ጫማቸው ከሱቅ የተገዛ ሳይሆን እብሪታቸው የሚወስድ ይመስለኝ ነበረ፡፡

ሃሃሃ...ግን ይሄው ሁሉ ነገር ሱቅ ውስጥ አለ - ሸቀጥ ነው፡፡ ያው እዛጋ ቶማስ የሚባለው ሁልጊዜ በሴት የሚከበበው የክፍላችን ልጅ ጫማ - ይሄው የራሄል ቦርሳ - እሪ ጉድ የቴቸር ተስፉ የጥቁር ባለ ብዙ ኪስ ጃኬትም ያውና፡፡ ትንሽ ብቆይ እነዛ 'ውድ ነን' የሚሉ ልጆች እዚህ ተደርድረው ሲሸጡ እገኛቸው ይሆናል፡፡

ቢገርም... - ሁለት ሱሪ፣ አንድ ጫማ፣ ሁለት ሸሚዝና አንድ ሹራብ - ነፍስ ካወቅኩ ለመጀመሪያ ጊዜ አዲስ ልብስ ከሱቅ ገዛሁ:: ለካሁት:: መስተዋቱ ፊት ስቆም ደነገጥኩ:: 'ልብስ ማለት ተራ ድሪቶ ነው' ምናምን የሚሉ ሰዎች እንዴት ጅሎች ናቸው እባካችሁ! ራሴን በመስተዋት ሳየው ታላቅ ፍንዳታ አዕምሮዬ ውስጥ ተፈጠረ::

አወራረዳለሁ ጥቁር አምበሳ፣ ኮከበ ፅባህ፣ ምኒሊክ፣ መነን፣ አዲስ ከተማ፣ ድልበር፣ በሌ ከሚማሩ ተማሪዎች ሁሉ አንደኛ ቆንጆና ወንዳወንድ አቋም ያለኝ ልጅ እኔ ነኝ !! እሮይ! ከቤተክርስቲያን ሃጢያቱን ተናዞ እንደወጣ ሰው ሸከሜ ቀለለኝ -እደግሙ ደግሞ !! የከፍሌን ልጆች በየቤታቸው እየሄድኩ እጄን ኪሴና ኪሴ አስገብቼ "ሃይ!" ማለት አማረኝ::

ዛሬ የለበስኩት አዲስ ሹራቡ ላይ የነበረውን ወረቀት ከኋላ ከሩን በጥርሷ በጥሳ አላቀቀችልኝና፣ "አንተ ልጅ ቆንጆ እኮ ነህ" አለችኝ:: በሙቅ ውሃ በተሞላ ገንዳ ውስጥ የመግባት ያህል ቃሏ ይሞቅ ነበር:: ቆንጆ መሆን ማለት የአፍንጫ መሰልከክ፣ የዓይን መንከባለል፣ የጥርስ መደርደርና ነጣት ማለት አልነበረም:: ለኔ ቆንጆ ማለት በሰው ዓይን መሙላት ማለት ሆነልኝ::

ዝም ብላችሁ የሕይወት መንገዳችሁን ዞሩና ተመልከቱ! አለቀ ያላችሁበት ቦታ ላይ የነበረውንና የሚመጣውን የሚያያይዝ ድልድይ ይኖራል:: ይሄን ድልድይ የሚያምኑ 'ፈጣሪ ነው' ይሉታል፡ ፡ የማያምኑ 'የስነሕይወት መርህ ነው' ይሉታል:: ለእምነቱም ለሳይንሱም ግድ የማይሰጣቸው እድል ይሉታል:: እኔ ግን ይሄ አንዴ በዛ አንዴ በዚህ የሕይወቴን ተራዳ እየደገፈ የሚያቆመው ከአቲዬ ድፍን ሃምሳ ብር የተበደረው እግዚያብሔር ነው እላለሁ::

እንዲያ ነው የመቀጠላችን ስንክሳር ባማረ የሕይወት አትሮኖስ ላይ ተቀምጦ የሚገለጠው:: ዛሬ ልብስ ከገዛችልኝ ከሳምንት በኋላ ትምህርት ቤት ቁጭ ብዬ መቋረጫ የሌለው ሃሳብ ውስጥ ተዘፈቅኩ:: እንደ ቀልድ ነበር ሀሳቡን የጀመርኩት:: ልብሴ የብዙዎች ፊት እንዲበራ አደርጓል፤ መንገድ ላይ ሴቶች ያዩኛል:: አንዳንዴ ማፍጠጣቸው ሲበዛ፣ "እነዚህ ሴቶች ግን ያልለበሰ ሰው፣ ያላብረቀረቀ ነገር 'አብስትራክት' ይሆንባቸዋል - ቶሎ አይታያቸውም" እያልኩ እስባለሁ::

ዮርዳኖስ ከንዴን ጩምድዳ መሄድ ከጀመረች ቆየች:: ጓደኞቿ "'ኤክስሬይ' ነገር ነሽ ይሄ ልጅ ለካ ገና በፊት ውበቱ ታይቶሻል::" እንዳሏት ነገረችኝ:: እግረ መንገዷን፣ "ዛሬ ስለለበስክ ሳይሆን በፊት ከነድሪቶህ ሰው ሳያይህ በፊት ነው የቀረብኩህ" መልዕክት ማስተላለፏም እንደሆነ እንጃ !!

እውነቱን ለመናገር ሰው ራስ ወዳድ ነው:: በዚህ ሁሉ ሃሳቤ ውስጥ አንድ ጊዜ እንኳን ስለ አቲዬ አላሰብኩም:: እኔነት ሲያደክመው የኖረ ሰው ሸክሙን ጣጥሎ ብቻውን የሚቆምበት ቀን አለ አይደለ - ጥፋታችንን ብቻችንን የምንጋፈጥበት፣ ራሳችንን የምንወቅስበት፣ ደስታና ስኬታችንን 'በራሳችን ልፋት ያመጣነው ነው' የምንልበት - በቃ ራሳችንን ብቻ የምንሆንበት፣ የዛን ቀን እንደዛ ሆኜ ነበር::

ታዲያ ውጤት ነበረው:: በውስጤ የተተረማመሱ ሀሳቦች በስርዓት ተሰደሩ:: "ሞተዋል"

ያልኳቸው ጉዳዮች አፈራቸውን እያራገፉ በህሊናዬ አደባባይ በትንሳኤ ቆሙ:: ፍቅር - የሴት ይሁን የእናት አገር ይሁን የፈጣሪ ያልለየለት ባለ ብዙ ዘርፍ ፍቅር ባዶውን የኖረ የልቢ መስቀል ላይ እንደገና የተሰቀለ መሰለኝ:: እንደ ባንዲራ በሕይወት መዝሙር ታጅቦ ወደንፍሴ ከፍታ ቀስ እያለ የሚሳብ ፍቅር::

እንደ ሰው ስንቆጠርና ቤተሰብ፣ ጓደኛ፣ ጎረቤት፣ መንደርተኛ፣ አገሬው ቦታ ሲሰጠን ወይም የሰጠን ሲመስለን ከማሕበረሰብ ያፈነገጠ ውስጣዊም ውጪያዊም ስብዕናችንን ሰልፉን እንዲያሳምር ውስጣችን ራሱን ይመከራል:: እንደዛ ነው የሆንኩት:: እና ደግሞ ፈሪም ሆንኩ፣ የሆነ ነገር መፍራት ጀመርኩ ::

እንደ ሰው ከመቆጠር ስናልፍና እንፋሽ አኩንፋሻችን ሲበዛ የሰልፉ መሪ የሆንን እየመሰለን እንደገና ያገኘንበት እንረግጣለን:: መልካም መካሪ ካገኘን ወደ ሰልፋችን የመመለሳችን ነገር ያውም በጭብጨባ ታጅቦ ይደገማል:: ካልሆነ ግን ማንነት፣ ስም፣ አላማ፣ ስብዕና "እብድ የበላው በሶ" ሆኖ ይቀራል:: የታዋቂ አውቅና መንኮታኮቱ፣ የአገር ፖለቲካ፣ ኢኮኖሚ፣ በልክ እንዳልተሰፋ ቃሚስ መንዘላዘሉ፣ የትውልድ ሽሽት ከመጥበሻው ወደ እሳቱ የመሆኑም ነገር ሁሉ የማንነትን ሰልፍ መሳት ነው:: አጉል ወደድኩ ብሎ ሰልፍ ስትጥስ የሚያጨበጭብልህ፣ ጠላሁ ብሎ ጎትቶ ከሰልፍህ የሚያስወጣህ በምላበት ምድር ጥላቻና ፍቅር እኩል የጥፋት መንገድ መሆናቸው የሚገባህ እንዲህ ራስህ ጋር ሃቅ ሃቁን ስትነጋገር ነው::

እናም ባነንኩ !! እኔ ማነኝ? እኔ አሸብር ነኝ:: እናቴ አፀደ ትባላለች:: በዚህች ምድር ላይ የስጋ ዘመድ የምንለው የለንም:: እናቴ በየሰዉ ቤት እንጀራ ትጋግራለች፣ ልብስ ታጥባለች፣ እንደ ሰው ተከብራ አታውቅም:: ተስፋ የምታደርገው እኔን ብቻ ነው:: ብቸኛ አላማዬ አገር፣ ሕዝብ፣ ወገን አይደለም እናቴ ናት !!

ማንም በፖለቲካ አመለካከት ቢራኮት፣ ማንም ማንንም ቢከተል ስሜት አይሰጠኝም:: የትኛውም አምነት 'ወዮልህ!' ቢል፣ በዚያ በዚህ ቢፈልግ በአምላኩ፣ ቢያሻው በፖለቲካው ተከልሎ ቢቧደን 'እችን ታህል' አይገርመኝም:: እናቴን ነፃ ለማውጣት የሕይወት ጦርነት ውስጥ ያለሁ ታጋይ ነኝ፣ ሆቺ ሚኒ ነኝ ፤ ግዙፉን 'አምባገነን ሕዝብ' ከትንሽ የእናትነት ግዛቴ የማባርር ቼጉቬራ ነኝ፣ በስግብግብና ራስ ወዳዶች ክንድ ስር በፅናት አልፈ የሚስኪን እናቴን ከፍታ በሚያረጋግጥ አብዮት ምድርን የምንጥ - አንጄላ ዴቪስ ነኝ፣ ፋራንዝ ፋኖን ነኝ::

የእናቴ ጠላት ድህነት አይደለም - 'ስለነፃነት የሚቀባጥረው ሕዝብ' እንጂ:: የሕዝብ ልጅ የሚባል ቀልድ አይገባኝም:: የእናቴ ብቻ ልጅ ነኝ:: ፅንፈኛ ነኝ፣ ዘረኛ ነኝ፣ አክራሪ ነኝ - ከእናቴ ጋር በጭፍን የተሰለፍኩ 'ሌላው የተረገመ ነው' ብዬ የማምን ዘረኛ ነኝ:: 'ከእናቴ ወዲያ ታጋሽ፣ ጨዋ፣ ለሰው ልጆች አሳቢ፣ አዋቂ ጀግና ዘር የለም' የምል !! አክራሪ ነኝ፣ ከእኔ እናት ሌላ ሌላ እናት እናት የማይመስለኝ:: እናም ጠላቴ ሕዝብ ነው:: ሕዝብን መበቀል ቀላል ነው:: ምክንያቱም ጠላትህ የትም የሚገኝ እንደ ትቢያ እያፈሰከ የትም የምትበትነው ገለባ ነው:: አስተማሪ ብትሆን

በጠመንጃህ ስር ጠላትህ አለ፡፡ ጥላቻ አዕምሮው ውስጥ እየዘራህ ሰይጣን ታፈራለህ፡፡ ሹፌር ብትሆን የጠላትህ ነፍስ በእጅህ ነው፣ ይዘኸው ገደል ልትገባ ትችላለህ፡፡ ግንበኛ ወላ አናጺ ብትሆን የምትሰራለት ቤት በላዩ ላይ ፈርሶ እንዲቀብረው የማድረግ ስልጣን በእጅህ ነው፡፡ ባለስልጣን ከሆንክማ፣ "አባቡም ከእግርህ፣ ዱላውም ከእጅህ" ብትፈልግ ቀይሽብር፣ ወንጀለኛ፣ ምናምን ታርጋ ብለህ በየመንገዱ ትደፋዋለህ፡፡ ካሻህ እድሜ ልኩን በድህነት እንዲማቅቅ ታደርገዋለህ፡፡

ደግሞ ለበቀልህ 'ማን ይተባበረኛል?' ብለህ አትስጋም፣ ሕዝቡ ራሱ ለመባረክ ስትቆም ነጠላውን አጣፍቶ ከጎንህ ነው፡፡ ለማረድ ስትቆምም ቢለዋውን ስሎ ከጎንህ ነው፡፡ ከሌላ ዓለም ረዳት መጥራት ሳያሻህ፣ ወንድሙ ላይ የሚጨክን 'ፈሪሃ እግዚአብሄር' ያለው ሕዝብ ጠላትህ ከሆን አደግድጎ ለበቀልህ ታዛዥ ነው፡፡

ደነዝ ሕዝብ፣ ደነዝ መሪ እንደሚወልድ እስኪገባው ትጫወትበታለህ፡፡ ጭራቅ ሕዝብ፣ ጭራቅ መሪዎች እንደሚፈለፍል እስኪያውቅ ታሸዋለህ፡፡ አዎ ጠላትህ ሕዝብ ከሆነ በቀልህ ቦታ እና ጊዜ ሳይመርጥ የትም ሊፈፀም ይችላል፡፡ ደግሞ ታዝበህ ከሆነ ከልብህ የሕዝብ ጠላት ከሆንክ ሕዝብ ይወድሃል፡፡ ስላንተ ይዘምራል፡፡ 'ጀግና!' እያለ ሲያወሳህ ይኖራል፡፡ ለምን መሰለህ፣ ውስጡ ያለውን ጭካኔ ነው በአደባባይ ያሳየኸው !!

ወዳጄን እየካደና እየቀረጠፈ ውለታውን ትቢያ የሚያለብስ ሕዝብ የእናቴን ጉልበት እንደምስጥ መጥጦ 'እንጨቷ'ን አስቀረ ብዬ አላዝንም፡፡ ሰው እሆናለሁ፡፡ በእኔ ሰው መሆን ትላንት ፍሬ የምትሰጥ ለምለም ዛፍ የነበረች ሕዝብ ያደረቃት እናት የምትባል 'እንጨት' ከማገዶነት አፋፍ ተመልሳ እንደ አሴይ ብትር ትለመልማለች፡፡

ያኔ በልጅ ልጆቿ ልብ ውስጥ ከቅዱሰቅዱሳኑ ለዘላለም በክብር ትቀመጣለች፡፡ ...ቱ ! አሸብር አይደለሁማ !

አዎ ታጋይ ነኝ !! ታጋይ በሴት አይፈተንም፡፡ ሴቷ ቀይ አግር ቢኖራትም፣ ዐይኗ ቢያምርም፣ ተንጠራርታ ብትስምም፣ ስሟ ዮርዳኖስ ቢሆንም፣ ማታ ማታ ትገዝ ብትልም፣ ከነድሪቶዬ ብትቀርበኝም የጠላት ልጅ ያው ጠላት ነው !! ዮርዳኖስን ርግፍ አድርጌ ተውኳት !

ከባድ አልነበረም፡፡ እንዲያውም ዐይኔን ስገልጥ ዮርዳኖስ ለእኔ ሸክም ነበረች፡፡

በባልጣ ብልጥ ሴትነት ነገን አሻግራ ያየች፣ መረቧን ተሸክማ ግራ በገባው አሳ ዙሪያ የምትሽከረከር ብልጥ ሴት፡፡ እሾሁን አራግፋ ልትቀረጥፈው !! ተውኳት፡፡

"ልብሱን ሲቀይር ተወኝ" አለች ተባለ፤ እሷ የድሮ ልብሴን የሆነች ይመስል፡፡ ብዙ ዖታዊ ግንኙነቶች ላይ አለመፈለግ ክህደት ተደርጎ ይታያል፡፡

## ክፍል አስራ ዘጠኝ

አስራ ሁለተኛ ክፍል ከፍተኛ ውጤት አምጥተው ዩኒቨርስቲ ሊገቡ ከተዘጋጁ ጥቂት ተማሪዎች መካከል አንዱ እኔ ነበርኩ - አራት ነጥብ ! አራት ነጥብ የሚባል አንድ ጠመንጃ ይዤ ለትጥቅ ትግል ዩኒቨርስቲ ወደሚባል ጫካ ልዘምት ተዘጋጀሁ::

ዛጒ አንድ የናጠጠ የሃብታም ልጅ ሊኖረው ከሚችለው በላይ ልብስና ጫማ፣ ሌሎችም ቁሳቁሶችን ከአገር ዉስጥ ብቻ ሳይሆን ከቤተሰቦቿም ጭምር አስመጥታ አምበሻበሸችኝ:: ምርር ያለ ቤተሰባዊ ፍቅር ውስጥ ገብተን ነበር:: ዐይኗ ይወደኝ ነበረ ያስታውቃል:: በተለይ አስራ ሁለተኛ ክፍል ተፈትኜ ውጤት ስጠብቅ ከዛጒ ጋር ያሳለፍነው ጊዜ የማይረሳ ነበረ::

ያልዞርንበት መዝናኛ አልነበረም:: የትም ስትሄድ ከኋኗ አለሁ:: እኔን "ወንድሜ" ብላ ማስተዋወቅ እንዴት እንደሚያኮራት ዐይኟ ራሴን ለወንድምነት አሳልፌ ሰጥቻለሁ:: የእውነትም ደግሞ ወንድሟ እመስል ነበረ:: ዛጒ ለእኔ ብቻ ሳይሆን ለእቲዬም ደግነቷ ተንሰራፍቶ ነበር:: ማታ ማታ ቡና ተፈልቶ በረንዳ ላይ ወይም ሳሎን ደስ የሚል ጊዜ ሦስታችንም እናሳልፋለን::

ዛጒን ከምቾት ጋር ያገለለ ዓለም እኔና እቲዬንም ከጉስቁልና ጋር የተፋ ሕይወት በምን ሂሳብ እንዳቀላቀለን ባይገባኝም ቅልቅሉ ግን ከልብ የሆነ ቤተሰባዊ ትስስርን ፈጥሮ ነበረ::

አንድቀን "እቲዬ!" አልኳት፣

"አቤት!"

"ምን ብሆን ደስ ይልሻል?"

"ኧረ እኔ ምን አውቄ፣ እኔ ትምርት የለኝ አላቀው" ብላ ሳቀች::

"ግዴለሽም ተምሬ እኔ ልጅሽ ምን ብሆንልሽ ደስ ይልሻል?"

"እሷን አማክራት እስቲ" አለችኝ ዛጒን ማለቷ ነበር::

"እቲ ዛሬ ካልነገርሽኝ አልለቅሽም ራስሽ ንገሪኝ!"

ትንሽ አሰበችና፣ "ዶፍተር" አለችኝ በሳቅ:: ሁለታችንም በሳቅ ፍርስስስ አልን::

እነጋገሯ በዕርግጥም ያስቅ ነበር:: ህክምና የመማሬ ብቸኛ ምክንያት ይሄው ነው!! ሕዝቤኝ ወገኔን ከበሽታ ለመታደግ ምናምን ብዬ አልነበረም!! እናቴ፣ የምወዳት እናቴ፣ የአዕምሮዋ ጥግ የታላቅነት መጨረሻ የመሰላትን ነገር ለመሆን እንጂ!!

የዩኒቨርስቲ ቆይታዬ የደስታና የቅንጦት ነበረ:: ዛጒ ውብ ሆና ግቢ ስትመጣ ዐይኑን የማይጥልባት ተማሪ አልነበረም:: ብዙ ሰው እናቴ ያደርጋት ነበረ:: ሴቶቹ የዛጒ ጫማና ልብስ ላይ ዐይናቸው

ይጠቅሳል:: ከዚህ የቆንጆ ዘር በረከቱን ሊካፈሉ የቋመጡ፣ በስልምልም ፀጉሬን፣ በጨዋ መሳይ ፈገግታ ሊቀርቡኝ ሊዞሩኝ ነበር:: 'ፀዳ ያለ ልጅ' ይሉኛል:: ሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃ !! አሳልኳቸውም፣ በድፍን ግምት ወደድን ብለው ከሰልፍ ሊያስወጡ መሞከር ይሄ ነው እኮ::

የወደዱኝን ያከበሩኝን ሁሉ በቁምነገር ባለመቁጠር በቀሌን አንድ ብዬ ጀመርኩ:: ኮተታሞቹ የገጠር ልጆች ራሳቸውን ችለው መቆም ይፈራሉ:: ሴቶቹ ወንድ ታዛ ስር ካልተጠለሉ ሰው የሆኑ አይመስላቸውም:: ወንዶቹ የተፈጥሮን ፆታዊ መፈላለግ ሳይንስ ሊያደርጉት ጅራት ሲቆሉ፣ ግራ የገባቸው የከተማ ልጆች ጭልጥ ወዳለው ማሕበራዊ እንስሳነት ሲወርዱ፣ በግቢያችን ውስጥ እንደሰው መኖርን ያጣጣምኳት እኔ ከፍ ባለ ክብር እየተማርኩ ሁሉንም ተማሪ ፅንፍ በሌለው ጥላቻና ንቀት አመለከት ነበረ::

የኖቀውን የሚወድ ሕዝብ ማን ከጎኔ ነበር ! አሹዬ፣ አሹንት፣ ..ሹ፣ ..ሽቢ፣ ...ሹሹ፣ ከቤተሰቦቻቸው የወረሱት አባብነት የስም ግንድ ላይ ሲጠመጠም ላለመነደፍ ልቤን ቆዳ አልብሼው ነበረ:: ማቆላመጥ የሚወድ ሰው ጤነኛ አይመስለኝም:: እምብርባሪ ነጋዴ ነው የሚመስለኝ:: በየስሙ ላይ 'ዬ' መለደፍ የፍቅር ሃዋሪያ መሆን ይመስላቸዋል::

የቤተሰቦቻቸው መርዝ አልሰራ ሲል፣ (የተመረተበት ጊዜ አልፎ እንዳይሆን ሰግተው) ከፊልምም ከመጽሄትም አዳዲስ መርዝ እየተሸከሙ ብቅ ይላሉ:: በአነጋገር፣ በአለባበስ፣ በአስተያየት፣ በአግር፣ በዳሌ፣ በጣት፣ በፀጉር እናም በመጨረሻ በሃሜት፣ "ይሄ ልጅ ሴት አይመቸውም እንዴ? ማን ያውቃል? ዘመኑ ከፋ ነው እናትዬ፣ እንትን እንዳይሆን"::

እነሱ ጋር ያልሆነ፣ እነሱን ያልፈለገ ጭራ አለው፣ ደብቆት ነው እንጂ:: ቀንድ አለው፣ ጥፍር አለው:: በዚህች ምድር ላይ እንደመናቅ የሚያም ነገር የለም:: ንቀቴ አመማቸው !!

ቡምምምምምምምምም እውነት ፈነዳ !! "ይሄ ቀብራራ እዚህ ይኮፈሳል እናቱ እንጀራ ጋጋሪ፣ ልብስ አጣቢ ነች አሉ":: ጮማ ወሬ ተገኘ:: ዳሌያቸውን እየናጡ ፀጉራቸውን እየነሰነሱ፣ ጅራታቸውን ከሚቆሉላቸው ወንዶቻቸው ጋር አወሩ:: ተሳለቁ:: ሊያሸማቅቁኝ ሞከሩ፣ ራሳቸውን ችለው መቆም ሲፈሩ፣ የአፉኝት ልጆች በልብስ አጣቢ ልጅ ሳቁ:: የቤታቸውን አጠራቅመው ለዘመን መለወጫ ቤታቸውን የሚያፀዱ ሁሉ፣ ሰው ሰራሽ ጠጉራቸው ራሳቸው ላይ ጀልቶ ቢሆም በጸሎት የሚፈታ ሁሉ፣ ተብረቅርቀው 'ሰው ነን' ሊሉ:: ልክ ለልክ ከተዋወቅን ቆየና ይሄም ጥይታቸው ከሸፈ::

ቢሆንም እኔ አሸብር 'ላይፍ' በሚሉት ጋጋታ ውስጥ ከሙታን ጋር ማኅበር አለመጠጣቴ እንዳበገናቸው ወደ 'ዱፍትርናው' ተንደረደርኩ:: ልማዴ ነው ስለኔ የሚንሟፈፈውን ትንሽ እያደረግኩ ማለፍ:: እንከን ፈላጊዎች ሚዛናቸው ከአሉባልታ ሌላ ምን ሊሰፍር...ቡፉፉፉፉ፣ ለማሸነፍ የተጠራሁ መሆኔ ሲገባኝ ተሸናፊ አቆላምጦም ይሁን ሳያቆላምጥ ሲጠራኝ አቤት አልልም:: አቤት ብትላቸው ቃላቸው አንድ ነው፣ "ኑ ና አብረን እንውደቅ!"

## ክፍል ሀያ

የሕክምና ትምህርቴን ከጀመርኩ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ የአንዲት ሴት አስከሬን አየሁ:: እድሜዋ ሃምሳ የነበረ አሁን ግን ዘላለም የሆነ ጠይም ሴት:: አስከሬት ለተማሪዎች የተግባር ልምምድ ትምህርት የሚውል ነበር:: ሁላችንም ለአስከሬን አዲስ ስለነበርን አንዳንዶቹ ደነገጡ፣ አንዳንዶቹ ተንቀጠቀጡ፣ አንዳንዶቹ ሊያስመልሳቸው ሞከረ (አንዲት ልጅ አስመልሷታል) - እኔ ግን እንባዬ መጣ::

ሰው ሞቶ ሲያዩት እንዴት ያሳዝናል - ኢትዮጵያዊ ሞቶ ሲያዩት እንዴት ያሳዝናል:: የአንድ ሚስኪን ኢትዮጵያዊ አስከሬን ማየት ከሞት ከራሱ የበለጠ ያሳዝናል፣ ያስደነግጣል:: ከዛ በኋላ በስራ አጋጣሚ በርካታ የፈረንጅ አስከሬን አይቻለሁ:: ግን የፈረንጅ አስከሬን እንደ ኢትዮጵያዊ አስከሬን አያስደነግጥም:: ባዕድ ምድር ላይ የኢትዮጵያን ባንዲራ ስትመለከቱ የሚሰማችሁ የደመነፍስ ድንጋጤ ዓይነት፣ ግዑዝ ኢትዮጵያዊ አስከሬን ስታዩ ሕይወት ያለው ኢትዮጵያዊነት ሬብበበት ይታያችኋል::

ኢትዮጵያዊት እናት ሞታ ስትታይ እንዴት እንጀት ትበላለች መሰላችሁ:: ዝም ይላል የሞተ ሰው፣ እጅና እግሩን አሳርፎ ዝም !! ሰው እየሮጠ፣ እየተንጫጫ ወደ ዝምታው ነው የሚሮጠው:: እና ይህች ሴትዮ ዝምታዋ ላይ ደርሳ ነበረ:: "ምነው ዘርፌ በሆንች"::

ከፉ ነገር አይቶ ለዘርፌ ያልተመኘሁበት፣ ለቀለመወርቅ ያላጨሁበት ብቸኛ ቀን ነበር:: እንደውም 'ዘርፌንም ከዚህ ይሰውራት' አልኩ:: አንዳንድ ሰው በቁጣ፣ "ዝም በል!" ሲል "አፍህን ዝጋ!" ማለቱ ብቻ አይደለም:: ከዛ ያለፈ እርግማን ነገር አለው:: 'መምራት የምንፈልገው ሬሳን ነው' ካላሉ በስተቀር ለምንድን ነው መሪዎች ህዝባቸውን፣ "ዝም በል!" የሚሉት:: ዝምታ ሰላም ? ዝምታ ኩርፊያ አይደለም:: ይህቺ ሴት አኩርፋለች ? ዝምታ ትዕግስት አይደለም፤ይህች ሴት ታጋሽ ናት ?

በምድርም የተመቻት ዓይነት ሴት ስላልነበረች ነው መሰል በጣም የተጎሳቆለ ሰውነት ነበረ ያላት፤ አስከሬን አንቱ አይባልም የተባለ ይመስል እንቺ ነበር ሁላችንም የምንላት:: እንግዲህ መፅሐፉ፣"የብልሆች እግር ወደ ሀዘን ቤት ነው" የሚለው ለምን እንደሆነ የገባኝ አሁን ነው:: ሕክምና የምማረውም ለምን እንደሆነ የገባኝ አሁን ነው::

"ፍጠን አሸብር ሰዎች ዝምታቸው ላይ ሳይደርሱ" የሚል መልዕክት በውስጤ ያጣድፈኛል::

ሰዎች ከፉም ይሁኑ ደግ፣ የሚጠቅምም ነገር ይናገሩ የማይጠቅም ዝባዝንኬ፣ ብቻ ዝምታቸው ላይ እንዳይወድቁ መሮጥ አለብኝ:: ልቤ ታዲያ ደረቴን ፈጥርቆ የወጣ እስኪመስለኝ ይመታል፤ ታፍኖ የኖረ ሚስኪን ሳያልፍለት እንዳይሞት፣ በደሉን ሳይተነፍስ ዝም እንዳይል፣ የብዙ ብዙ በደል መቃብር እንደሆነ ወደ መቃብር እንዳይወርድ እኔ አሸብር ዶክተር እሆናለሁ:: ሰው ከቀት

እያልፍም ቢባልም ቅሉ፣ ቀኑን እስካላወቅነው ድረስ ቀን ለመጨመር እንሮጣለን - ማምሻም ኢድሜ ነዉ!!

ለእኔ ሰው በሁለት ይከፈላል፤ እናቴ አቲዬ እና ሌላው !! አቲዬ ትኑርልኝ፤ በቃ መኖር ያለባት ሰው ናት:: እኔ ልጇ ባልሆንም አቲዬ መኖር አለባት:: ሌሎችም ይኑሩ፤ አቲዬ መኖርዋን፣ ኖራም ያገን አዘቅት መሻገሯን እንዲመሰክሩ !! እንግዲህ አንድ አስከሬን ነው ይሄን ሁሉ የሚያሳሰበኝ::

እኔኮ አስከሬን ሲባል የሚያብረቀርቅ ልብስ የሚለብስና ለአራት የሚሸከሙት እሌጋ ነበር የሚመስለኝ:: ሞት እንዳለ አወቅኩ፣ ሰማሁ ሳይሆን አየሁት:: ሞት ያፈረሰውን የሕይወት ከተማ አየሁት:: ያውም እናት የምትባል ዋና ከተማ:: መምህራችን ረዳት ፕሮፌሰር ዘሩ ፊታችን ለተጋደመው አስከሬን የሚሰጡትን ትልቅ ክብር እና እንክብካቤ ሳይ ገረመኝ:: አንዳንድ ዶክተሮች በሕይወት ላለ በሽተኛ ከሚያደርጉት እንክብካቤ በጣም የተሻለ ነበር:: ይህ አስከሬን ከዛ በኋላ ያለ ሕይወቴን ቀይሯል:: አስተሳሰቤን ቀይሯል:: ሞት ማለት እርግማን መሆኑን እምኛለሁ (ጎይንቡ ባይልም::) ዝምታ ጤናማ አይደለም፤ ከጭቆና ሁሉ የከፋው ጭቆና "ዝም በሉ!" ማለት መሆኑን አስከሬኑ እየጮኸ ይመሰክራል::

ለሰዎች ማዘን፣ በተለይ ዝም ለሚሉ ሰዎች የጀመርኩትም ያኔ ሳይሆን አይቀርም:: ቢሆንም እስከምመረቅ ሲበዛ ዝምተኛ ነበርኩ:: ውስጤ የሞተ ነገር ነበረ - ትንሳኤ የሚያሻው:: ትንሳኤው በር ድረስ ታደርሰኝ ዘንድ የተሰጠችኝ ደግሞ ዛፒ ነበረች:: የኔ ሚስኪን ዛፒ፣ ግራ የገባት ሙሴ፤ የድህነትን ባህር በፍቅር በትር እየከፈለች እኔና እናቴን ያሻገረች መሪ ነበረች::

ዛፒ ምንም እንኳን በግል ሕይወቷ ደስተኛ ባትሆንም፣ ሙሉ የዩኒቨርስቲ ወጪዬን ልክ በፍርድ ቤት እንደተወሰነበት ሰው ሳታስተጓጉል ትሸፍንልኝ ነበር:: አደረገችልኝ ብዬ አይደለም የማመሰግናት፣ ደግነቷ እያሸማቀቅም፣ ከርሷ ብር መውሰድ ሙብቴ እንዲመስለኝ አድርጋ ነው የምትረዳኝ:: "እሹ ኢስኪ ዛሬ ጥናት ከሌለህ ራት ጋብዘኝ" ትልና ራት ትጋብዘኛለች::

በእኔና በዛፒ መካከል ለቁጥር የሚያዳግት የእድሜ ልዩነት አለ፣ ግን ጓደኛዋ የሆንኩ መስሎ እንዲሰማኝ አድርጋኛለች:: የመጨረሻዋ ውብ ሴት ብትሆን እንኳን ከልሰልትነት ዘሩን ተምዘግዝጋ ታች የምትገኝበት የዝቅታ ዘመን አለ:: ለሴት ልጅ ይሄ ከባድ ነው:: ቢሆንም ሴቶች ከወንዶች በላይ ውድቀትን ዘንብነው እየሳቁ መቀበል ይችሉበታል:: በእርግጥ ዛፒ አንዳንዴ በተጨናነቀ ሁኔታ ውስጥ ባለሁበት ሰዓት ከግቢ ትጠራኛለች፣ እንቢ ማለት አልችልም::
አቤት እሄዳለሁ:: ራሷን ጣል አድርጋ ደብሯት አገኛታለሁ:: ከዚህ ድብርቷ ሳወጣት እሞክራለሁ::
በየቀኑ እደውልላታለሁ፤ ሲመቸኝ ወጣ ብለን እንዝናናለን::
የአዲስአበባ ወንድ እንደፈራ፣ ዛፒም እንደደበራት አምስት ዓመታት ነጉዱ:: በዚህ ብቸኝነትና
ተስፋ መቁረጥ ውስጥ ሆናም ግን ደግነቷ ልክ አልነበረውም::

ተመርቄ እስከምወጣ ሁለት ጊዜ ቤተሰቦቿ ጋር ውጭ ሄዳ ወደ አንድ ዓመት ስትቆይ እንኳን ጠቀም ያለ ገንዘብ ለእኔም ለአቲዬም መላኳን አጽርጣ ኢታውቅም ነበር፡፡ ይፈጥንብኛል ታሪኬ፡፡ በፍጥነት በሚበር መኪና መስኮት የምታየው እስኪመስለኝ ሁሉም ነገር ወደኋላዬ የሚፈተለከው በደንብ እንኳን ሳልመለከተው ነበር፡፡

አቲዬ ቀስ በቀስ የሰው ቤት ሰራዋን እያቆመች የተወሰኑ ቤቶች ብቻ ለዛውም ሰርግ ሲኖር በኮንትራት ወጥ መሥራት የመሳሰለ ሥራ ላይ ብቻ ተወሰነች፡፡ ሰውነቷ ግን በጣም ተጎሳቁሎ ነበር፡፡ ድህነት የማይፋቅ አሻራውን ቆዳዋ ላይ አትሞ ቀርቷል፡፡ እጆቿ 'መሻከር' የሚለው ቃል በማይገልፀው መልኩ ተፍረከርከዋል፡፡ ዐይኗ ለዘመናት በተጋፈጠችው የእሳሮና የማገዶ ጭስ እንዳያገግም ሆኖ ተጎድቷል፡፡ ከዚህ ሁሉ በላይ ግን አቲዬ ልክ በሌለው ፍርሀት ውስጥ ተዘፍቃ ነበር፡፡ ከቀን ወደ ቀን ዝምታዋ እየከበደ ነበር የሚሄደው፡፡ ዝምታ እፈራለሁ፡፡ ዝምታዋና ፍርሃቷ በጣም ይብዛብኛል - በተለይ ፍርሃቷ፡፡

አንዳንዴ በዚህ ባህሪዋ እበሳጭና እጮህባታለሁ፡፡ "ምን ላድርግ ብለህ ነው አሹዬ" ስትለኝ እንባዬ ይመጣል፡፡ የመንደሩ ትንንሽ ልጆች ጋር መንገድ ላይ ስትገናኝ ቆማ ልታሳልፋቸው ትሞክራለች፡፡ ኳሳቸው ወደ ግቢ ቢገባባቸው በሁለት እጇ አንስታ ትሰጣቸዋለች፡፡ የሆነ ቦታ ሄዳ እንደ ትልቅ ሰው ወንበር ላይ ከመቀመጥ ይልቅ እየፈራች ምንጣፍ ላይ ወይም ቁጢጥ ብላ አንድ ጥግ ትቀመጣለች፡፡ ማንም ሲመጣ ወንበር ትለቃለች፡፡ ታክሲ ውስጥ ሳይቀር አንድ ቀን ለአንዷት ልጅ ቦታ ልትለቅ ስትሞክር እጇን ይዤ በብስጭት አስቀምጫታለሁ፡፡ በቃ እዕምሮዋ ውስጥ "ትንሽ ነሽ" የሚል ክፉ መሀተም እትረውባታል፡፡

ድህነት ገንዘብ የሚገዛውን ነገር ብቻ አይደለም የሚያሳጣው፡፡ በነገሮች ሁሉ ሰልፍህን ከኋላ ያደርገዋል፡፡ አንዳንዴ ከአቲዬ በአስተሳሰብም በገንዘብም የሚያንሱ መንደርተኞች አቲዬን ሲያዩ ራሳቸውን ሊቆልሉ ሲሞክሩ እያየሁ ይገርመኛል፡፡ በቃ ይህቺ አዲስ አበባ ዝቅ ሲሉላት ሰው እናት ላይ ቆማ ልትጨፍር ይዳዳታል - ራሷ እናት ላይ ማንም ሲፈነጭባት እትነቃም እንጂ !!

*ክፍል ሀያ አንድ*

ዩኒቨርስቲ ውስጥ የነበረኝ ሕይወት የአንድ መልካም ተረት ፍፃሜ ይመስል ነበር፡፡ ልክ "... ከዛም በሰላምና በደስታ ይኖሩ ጀመር" ተብሎ እንዳለቀ ተረት፡፡ ብር አልቸገርም ነበር - እድሜ ለዛፒ፡፡ ጊዜ ባገኘሁበት ቀን ሁሉ አቲዬን እያታለሁ፡፡ በየቀኑም እደውላለሁ፡፡ አቲዬን በስልክ ማውራት ከባድ ነው፡፡ በቃ ጥያቄዎቿ አንድ ዓይነት ናቸው፤ "እንጀራው ጥሩ ነው...?"፣ "ልብስህ አልቆሸሸም...?"፣ "ንባብ አታብዛ፡ በጊዜ ተኛ፣ ራስህን ያምሀል፤ ማታ ማታ ጋቢ ልበስ፣ አሹ... ደሞ እጅህን ወጣ ወጣ አታድርግ የሰው ፀይን ጥሩ አይደለም" ሁሉንም በጥሞና አዳምጣታለሁ፤

ስለራሷ ስጠይቃት "እኔ ምን አለብኝ ብለህ" ብቻ ነው መልሷ፡፡ አቲዬ የሚያሰቃይ የወገብ ህመም

እንዳለባት እንኳን ያወቅኩት ከተመረቅኩ ከሁለት ዓመት በኋላ ነበር፡፡ እንዳልጨነቅ ደብቃኝ፤
ፍፁም በተረጋጋ ሕይወት ውስጥ ትምህርቴ ላይ ብቻ ሙሉ ሐሳቤን ሰብስቤ እንዳጠና...፡፡
የሰው አፈጣጠሩ እየገረመኝ፣ የበሽታ መከሰቻው ምክንያት ብዛት እና መንገድ እያስደነቀኝ፣
በዛውም የሰው ልጅ ምህረቱ ባይበዛለት በቀናት እድሜ ከምድር ተጠራርጎ የሚጠፋ ትቢያ
መሆኑ እያስደመመኝ፣ ሰው የምጠላው እኔ የሰው ጥላት የሆነ በሽታ ጋር ድብብቆሽ ስጫወት
ወደ መመረቂያዬ ተቃረብኩ፡፡

"ሴት አይቀርብም" ይሉኛል፡፡ ይሄም እንደ ጨዋነት ተቆጥሮልኝ ነበር፡፡ እኔ ባጠቃላይ ሰው
ነው የማልቀርበው፡፡ ለምን ለይተው፣ "ሴት አይቀርብም" እንደሚሉኝ ይገርመኛል፡፡ ሲጀመር
ማንም ጋር በሚያገናኙኝ የትምህርትና መሰል ጉዳዮች ከሴትም ይሁን ከወንድ ርቄ አላውቅም፡፡

ዩኒቨርስቲ ውስጥ ለዛውም የሕክምና ትምህርት ላይ ብቸኛ መሆን ቀላል ነገር አይደለም፡፡
ቢሆንም ከማይረባ መጠባለፍና በሕይወቴ አንድ እርምጃ አልፍ በማያደርገኝ ጉዳይ ውስጥ ገብቼ
የመዳከር ፍላጎቱ አልነበረኝም፡፡ ለምሳሌ ዖታዊ ፍቅር !! ወንድ እና ሴት ቆመው ወይም አንድ
ጥግ ተቀምጠው ያንን ሁሉ ሰዓት ሲቆዩ ምን ጉድ እንደሚያወሩ ይገርመኛል፡፡ ፍቅር ለምን
አይይዘኝም ብዬ ያሰብኩት አንዲት ልጅ እንዳፈቀረችኝ የነገረችኝ ጊዜ ነው፡፡ ማህሌት ነው
ስሟ፣ መጀመሪያ ስታፈጥብኝ አጋጣሚ መስሎኝ ነበር፤ ሲደጋገም የሆነ ነገር ፈልጋ ይሆናል ብዬ
ችላ አልኩት፡፡ ከዛ ከበበችኝ፡፡ አየር ሆነች፡፡ ላይብረሪ ካለሁ፣ አለች፡፡ የሆነ ቦታ ከተቀመጥኩ፣
ከሆነ ቦታው ፊትለፊት፣ ከኋላ ወይም ከጎን አለች፡፡ ባለፍኩበት ታጋጥመኛለች፡፡ ከሰላሳ መንታ
እህቶቿ ጋር ወደ ዩኒቨርስቲው አብራ የገባች እስኪመስለኝ በዛችብኝ፡፡ በመጨረሻ ወደድኩህ
አለችኝና አርፍ !!

እንደው አጋጣሚውን አልለፈው ምንስ አባቴ በ.ከደኝ ባባቱ ወንድ አይደለሁ እልኩና ልሞክር
ወሰንኩ፣ ግን ልጅቱ በቀጣዩ ቀን ሰለቸችኝ !!

ቢቃ ኀግዚአብሔርን ባፈቅር ይሻላል የሴት ፍቅር አያዋጣም' አልኩ፡፡ ሳይቆይ ግን ዓለም እግዜርን
የሚያፈቅርበት አካሄድ እኔ ከማፈቅርበት ጋር አልገጥም አለኝ፡፡ አንድ እግዜርን በስንት መንገድ
እንደሚያፈቅሩት ስመለከት አፈቃቀሬ የተሳሳተ ይሆን እንዴ ብዬ ፈራሁ፡፡

አንድ ቀን ከግቢ ወጥቼ የተማሪው ኪስ ሞላ ሲል የሚያዘወትራት ሬስቶራንት ሄድኩ፡፡ ምሳዬን
አዝዤ ስጠብቅ የዲፓርትመንቴ ልጆች መጡና ፊት ለፊት ተቀመጡ - ሦስት ሴቶች፡፡ ብዙ
ሴቶች ሲሰበሰቡ ኀብረተሰቡ የሚነባቸውን የዖታ ተፅእኖ ቀንበር የሰበሩት ይመስላቸዋል መሰል
ድፍረት ይጨምራሉ - ጮክ ብለው ማውራት መሳቅ ምናምን...፡፡

ያዘዝኩት ምግብ ጭሱን እያግተለተለ መጣ፡፡ አስተናጋጇ ትንትን በሰሀን ይዛልኝ የመጣች ነው
የመሰለኝ፡፡ ርቦኝ ስለነበረ የምግቡ ሽታ የተለየ ሆነብኝ፡፡ እንጎቴን ዝቅ አድርጌ ዐይኖቼን ጨፈንኩ፣
ጸሎት ይመስላል፣ ግን አልነበረም፡፡ በጭራሽ !! መቼ እንደጀመርኩት ባላስታውስም፣ በተለይ

ርቦኝ የሚበላ ነገር ሳገኝ፣ ደስ የሚል ምግብ ሲቀርብልኝ ሁልጊዜም እንዲህ አደርጋለሁ:: ጥልቅ የሆነ ስሜት ውስጤን ይሞላውና የሚያስገርም የእፍታ ዝምታ ውስጥ እገባለሁ:: ለምተው የረሀብ ዘመኔ አጭር የሀሊና ጸሎት !

ቀጥ ስል ሴቶቹ በግርምት አፋቸውን ከፍተው ያዩኛል:: ፊታቸው ላይ ማክበር፣ መቀራረብ መፈለግ ነበር:: ልክ እንደማላውቃቸው ሰዎች ችላ ብያቸው መብላት ጀመርኩ:: በልቼ እንደጨረስኩ ቡና አዘዝኩ:: እንዷ ወደኔ መጣች...ኤጭጭጭጭ !

"ሰላም ላንተ ይሁን፣ አሸብር!"

"ሃይ!" አልኳት ባጭሩ፣ ስናገር ሊያገላኝ ነበር::

"መቀመጥ ይቻላል ?" አለች ለመቀመጥ መንገድ ጀምራ:: ከዛም እንደ እኔ ቡና አዘዘችና ወሬ ጀመረች::

"ስታመሰግን አየንህ ክርስቲያን እንደሆንክ እናውቅም ነበር" አለች ፈገግታዋ ፊቷ ላይ እየተንተገተገ፣ አልመለስኩላትም::

"ፊሎሽፕ አለን ብንጋብዝህ ደስ ይለናል:: ቢቃ አብረን ጌታን ማምለክ ነው አላማው:: ዕሮብና ቅዳሜ ከሰዓት ነው ፕሮግራሙ" የሆነች ወረቀት ሰጠችኝና አመሰግናኝ ቡናዋን ሳታጋምሰው ሄደች:: ከጓደኞቿ ጋር ተያይዘው ወጡ:: ተመራርጠው ጓደኛ የሆኑ ይመስል ሦስቱም በቁመትም በቅጥነትም አንድ ዓይነት ነበሩ::

እንግዲህ ይሄ ምግብ ሲቀርብ ማቀርቀሬ ነው የ"የአብረን እናምልክ!" ግብዣ ያመጣብኝ፣ ወላ ያመጣልኝ:: ዝም ብዬ ሳስብ "እነዚህ ልጆች ጋር እንዴት ነው በጋራ የምናመልከው?" ብዬ ገረመኝ፤ እኔ ለየትኛውም እምነት፣ ለየትኛውም አምልኮ ግድ ያለኝ ሰው አይደለሁም:: በሕይወቴ ሙሉ የፀለይኩበት ቀን ኖሮ አያውቅም:: እግዚአብሔር የእኔ ብቻ ስለሚመስለኝ ሌሎች ጋር በጋራ ማምለኩም፣ መዘመሩም ምኑም ትዝ ብሎኝ አያውቅም::

እግዚአብሔር እኔ ጋር በመተባበር አዲስ አበባን ድራሽዋን ለማጥፋት እስከመረቅ እየጠበቀኝ አልያም እንደ ኖህና ቤተሰቡ እኔና እቷዬ ወደ መርከቡ እንድንገባ ፈልጎ የጥፋት ውሀውን ያዘገየው ስለሚመስለኝ ማንም ጋር ማምለክ ፈልጌ አላውቅም:: ስለዚህ በተጋበዝኩበት ቀን ቀረሁ:: ንዝንዛቸው ግን መቆሚያ መቀመጫ አሳጣኝ:: አንድ ቀን፣ "ይቅርታ የምትሉበት ቦታ መሄድ ስለማልፈልግ ካሁን በኋላ በዚሁ ብናቆም" አልኳት አንዷን በቁጣ::

አዎ ተቆጥቼ ነበር !! እግዚአብሄርን በምኞት የሚያውቁት ሞልቃቆች የቻፕስቲክ መማዣ ቢያጡ፣ "እግዚአብሔር ማነው?" የሚሉ...እግዚአብሄርን እንዲያስተዋውቁኝ አልፈልግም:: አይቻቸዋለሁ በዩኒቨርስቲ ቆይታዬ፣ ዶሮ ሦስት ጊዜ ሳይጮህ ጴጥሮስ ጌታን ሦስት ጊዜ እንደካደው የሚያትት መዝሙር እያንጎራጎሩ እነሱ ራሳቸው የሃብታም መኪና ጡሩንባ ባምባረቀ ቁጥር ከራሳቸው ሰላሳ ጊዜ ሲካካዱ::

አይቻቸዋለሁ የጌታ የማዳን ድንበር አቃቂና ኮተቤ ድረስ ብቻ ይመስል የአዲስ አበባ ልጆች ብቻ ተጠራርተው፣ "በጌታ ፍቅር" ምሳ ሲገባበዙ፣ ቸርች ሲሄዱ - በፅንፍየለሽ ከተሜያዊ ዘረኝነት የሚነበብ ነገር ሲዋዋሱ:: አይቻቸዋለሁ በየእምነቱ ተቧድነው ሲናቆሩ፣ ሲጠዛጠዙ:: አኔ እና እናቴ እግዚአብሄርን ገደል ጫፍ ላይ እንደተንጠለጠለ ገመድ የሙጥኝ ብለን ሕዝብ ከዛ ከዚህ ሲገፉን፣ ድህነት እጃችንን እየቀጠቀጠ የመዳኛ ገመዳችንን ሊያስለቅቀን ሲታገል፣ "አንለቅም" ብለን የተረፍን ሚስኪኖች ነን:: "ሰው አትመልከት እግዜርን እንጂ" ይሉኛል፣ 'አብረን እናምልክ!' ብሎ ጠርቶ 'ሰው አትመልከት!' ማለት ምንድን ነው?

እግዚአብሄርን የማረፊያ ምቹ ሳሎን ሳይሆንን በፊት የውሽንፍርና የማዕበል መሻገሪያ ድልድያችን ሆኖ እናውቀዋለን:: መዝሙር በአፋችን የለም፣ እንጠቅሰው ምዕራፍ፣ እንመዛው ቁጥር የለንም፤ ግን አንድ ነገር እናውቃለን፣ እግዚአብሄር ራሱን ያስተዋወቀን "አደርጋለሁ፣ እሰራለሁ" እያለ በመፎከር ሳይሆን እየሰራና እያደረገ ነው:: ፅኑ ክንዱን እያሳየ:: ያሰጨነቀንን ነገር ሁሉ እንደትቢያ ሲበታትነው እኔና እናቴ የዐይን ምስክሮች ነን:: ሽባ ተተረተረ ቢሉን፣ እውር በራ ቢሉን፣ ሰማይ ቢከፈት፣ ምድር ቢናወጥ፣ ተዓምር ቢነግሩን...መልሳችን አንድ ነው፣

"አልሰሜን ግባ በለው፣ እግዚአብሄር ለእኛ ያደረገውን ነው ለሌሎች ያደረገው":: ከራሱ ከፈጣሪ የተሰበክን ነን - በስራው !!

ምግብ ፊቴ ሲቀርብ ውስጤ በመደነቅ ይሞላል...እነዚህ በመከራ ጩኸት እና በነፍስ ዋይታ ሳይሆን በመዝሙር የተጠሩ ቆንጆዎች ይህን ብነግራቸው ያምናሉ ?...መራር ትዝታ አለኝ:: እንጀራ በቆረስኩ ቁጥር እንደወጥ የማጠቅሰው ፅልመት::

ሕፃን ሆኜ ከአቲዬ ጋር ልብስ የምታጥብበት ቤት እንሄዳለን:: አቲዬ የተቀለለ ቆሻሻ ልብሳቸውን ስታጥብ ባለቤቶቹ አጥንቱ ብቅ ጥልቅ እያለ የሚንተከተክ ቀይ ወጥ በረንዳቸው ላይ በትልቅ ብረት ድስት ጥደው አያለሁ::የሚንተከተክ ሽሮ አያለሁ:: የሚጋገር ትኩስ እንጀራ አያለሁ:: ደማም ሽታው አፌን በምራቅ ይሞላዋል - ያቅለሸልሸኛል::

እኔና አቲዬ ቁርስ ሳንበላ ነው የምንወጣው:: አቤት ምሳ ሰዓት አራራቁ:: የአቲዬ አሰሪዎች ልጆቻቸውን ከሚጫወቱበት ለምሳ ይጠሯቸዋል:: አቧራ የነካ የልጆቻቸውን ልብስ ከላያቸው ላይ ገፍፈው ወደ አቲዬ የልብስ ቁልል ይጥሉና ይዘዋቸው ወደቤት ይገባሉ:: በመቃነሻ ሰሀን ወጡን፣ አጥንቱን ጭምር ጨለፍ አድርገው ቀንሰው ይገባሉ:: ከመጨለፋቸው በፊት በጭልፋው አንድ ሁለቴ ማሰል ማሰል ያደርጉታል፣ አጥንቱና ወጡ ይደበላለቃል :: ይርበኛል !! በጣም ይርበኛል:: ወጡ ሲንተከተክ ድምፁ እስከዛሬ ጆሮዬ ላይ አለ:: የእነዛ ሰዎች ድምፃቸው ይሰማኛል፣ "ብሉ እንጂ አጥንቱን ምነው ፈራችሁት?" እየተባባሉ:: "አልጫው አልጣፈጣችሁም እንዴ?" እየተባባሉ:: ትሪ፣ ጭልፋ ሲንኳኳ ይሰማኛል:: ብቅ ብዬ ባያቸው እወዳለሁ::

አባወራው፣ "እስቲ የአጥንት መቀጥቀጫ አምጪ!" ይላል ሲጋውን የተገፈፈ ነጭ አንቢልታ

የሚያህል ቅልጥም ወድሮ ወደ በረንዳው እየወጣ፡፡ 'ክሽ' ያደርገውና አንጋጥጦ መቅኒውን ይስባል፡፡ ጉሮሮው ወደ ላይ ወደታች ይንቀሳቀሳል፡፡ የእኔም ጉሮሮ ይንቀሳቀሳል፡፡ ምራቄን ደጋግሜ አውጣለሁ፡፡

የቅልጥሙ መርዘም እና ሰውዬው ወደ ሰማይ ወድሮ ጫፉን አፉ ውስጥ አስገብቶ ሲመጠው ሰማይ ላይ ያለውን ደመና በቀሰም የሚመጠው ይመስላል፡፡

"አደይ...ወደቀ" ይላል ወደ መሬት እያየ፡፡ ሚስቱ ጉርሻ ጠቅልላ ወደ በረንዳ ትወጣለች፤ "እችን ብቻ አፈር ስሆን!" እያለች - በወጥ የረሰረሰ ጉርሻ፡፡ 'ውስጡ የተከተፈ ስጋ ወይም እንቁላል ሊኖረው ይችላል' እላለሁ በሆዴ፡፡ እንከርፍፉ ባሏን እንዲጎርስላት ትለምነዋለች፡፡ "ውደ ምኔ ላይ ይቀመጥ ሆዴ እኮ ሞላ" ይላል፤ "ለዚህች ቦታ አይጠፋም በሞቴ"፡፡ አፉን ይከፍትና ጉርሻው እንዳይንጠባጠብ የግራ እጇን መዳፍ ከታችኛው ከንፈሩ ስር ይገድበዋል፡፡ ጉርሻውን በሁለት ጉንጩ ሞልቶ እያላመጠ ተከታትለው ወደ ውስጥ ይገባሉ፡፡

"አሸብር!" ትለኛለች እቴዬ ድንገት፡፡ ማፍጠጤ ሲበዛ፤ "እንካ ብስኩት ግዛና ና!" ብላ እርጎ መሀረቧን ፈትታ አንድ ብር ትሰጠኛለች፡፡ አንድ ብሩን ስታወጣ መሀረቡ ባዶ ይሆናል፡፡ ብስኩት ገዝቼ እመለሳለሁ፡፡ ዛሬ ላይ ሳስበው የሚቆጨኝ ለእቴዬ ብስኩት አልሰጣትም ነበር፡፡ ብቻዬን አበላለሁ፡፡ በሩ ይከፈትና "እፀድ ኣቺን ለቅለቅ አድርጊያት ልጆቹ ሲንቀዠቀዡ ወጥ ደፉበት"፡፡ አንዳች የሚያክል የሰውየውን ኮት ትጨምራለች - ባለቤቷ፡፡ ሁልጊዜም በሩ ሲከፈት ሰሃን ይዛ የምትወጣና "ምሳችሁን ብሉ!" የምትል ይመስለኝ ነበር፤ ግን ብላን አታውቅም፡፡

አንዳንዱ ቤት ደግሞ ቁራሽ እንጀራ (ወጥ የነካካ) በሰሃን ይዘው ይወጡና፤ "እናትዬ እሷን ለቅለቅ አድርገሽ ስትጨርሺ አቺን ብይ" ትላለች አሰሪዋ፡፡ 'እሷን ለቅለቅ' ያለቻት ቢደረደር ሱቅ የሚሞላ ድርቆ ነው፡፡ በነገራችን ላይ በራሴ ገጠመኝ እንዳየሁት ብዙ ሚስቶች ከፉዎች፤ ስስታሞችና ታላቅነታቸውን ለማሳየት ሠራተኛ የሚበድሉ ናቸው፡፡ ባሎቻቸው ይሻላሉ፡፡ እቴዬ ታዲያ፤ "እሹ እችን ብላ" ትልና ፈገግ ብላ ሰሃኑን ለኔ ሰጥታ ስራዋን ትቀጥላለች፡፡ እቴዬ ስትበላ አይቻት አላውቅም፡፡ ይገርመኛል፡፡ እቴዬ ካለምግብ መኖር የምትችል እየመሰለኝ በእርግጥም እገረም ነበር፡፡

ርሃብ እንደ ብርድ፤ እንደሙቀት እንደ ደስታ እንደ ሃዘን ሰውነታችን ውስጥ የሚፈጠር ስሜት ብቻ የሚመስላቸው ምኞች አሉ፡፡ ርሃብ በሽታ ነው ፤ ቆሻሻ የሆነ በሽታ ነው፡፡ ዘመን ተሻግረው ስለ ሰባ ሰባት ድርቁ ሲያወሩ፤ ስለ ስልሳ ስድስት ርሀብ ሲደሰኩሩ፤ እዚሁ በረንዳቸው ስር ከነእናቱ የተቆራመደንበት ሰንት አሰቃቂ ቀን አልፏል፡፡ ሰንት ከፉ ቀናት ወደ ውስጥ አስለቅሰውናል፡፡ መሐል አዲስ አበባ በረሀብ የሚሞት የለም ሲሉኝ፤ 'ጥጋበኞች' የምላቸው ዛሬ ስንቶች ናቸው?

ይሄ ልመናን ስራው ያደረገ ለማኝ ይመስለናል የሚራበው፡፡ እሱ ከብሩንም ይሉኝታውንም ጥሎ ሆዱን ሞልቶ፤ "የአዲሳባ ሕዝብ ወሎ ደግባ" እያለ ያድራል፡፡ መቀመጫዋን እያየሁ

በዐይንህ የምትከተላት ዘናጭ ቆንጆ ሆዷ ቢፈተሽ ማን ማን ያውቃል፣ ሱፉን ሰብሶ ላፕቶፑን እንጠልጥሎ ከሥራ የሚወጣው ጎልማሳ ብትመረምረው ግን ሙሉቀን አህል በአፉ አልዞረም ይሆናል:: 'ራበኝ!' ለማለት ይሉኝታ ያነቀው ባለዲግሪ ረሀብተኛ ነው እለ ስንለው እዚህ ግባ በማይባል በሽታ ከንብል የሚለው:: በስራዬ የገጠሙኝ እልፍ ናቸው:: ዘናጭ ረሀብተኞች:: በምግብ እጥረት እንዲሁ የቀሩ::

ረሀብተኛው ርሃቡ እስኪጥለው የሚንጠራወት፣ በየበረንዳው ጃንበውን ወዝቶ የምታየው ህዝብ የበላውን እንዲያንሸራሽርለት የፈለገ ብቻ እንዳይመስልህ፣ ይሄ ፎርማታው ላይ ያልደረሰ ጅምር ቢራ አራቱ ሊሆን ይችላል:: ወዳጄ ፀጉራሙ በጣ ነው አለ ሲባል የሚሞተው !!

እናም እነዛ የርሃብ ዘመኖች አልፈው፣ ጭሱ የሚመዘዝ ሽፍንፍን ያለ ቋንጣ ፍርፍር ፊቴ ሲቀርብ ሳልወድ በግድ እንባቴን ደፍቼ፣ አንዳንዴም እንባዬ እየመጣ እግዚአብሄርን እንዲህ እለዋለሁ፣ "እቤት ማጥገብ ስትችልበት" በቃ !! ምግብ ሲቀርብ ምንግዜም የምለው ይሄንን ነው:: እንደውም ለእግዚአብሄር አይደለም ለራሴ ነው፣ "ይሄ እግዚአብሄር ማጥገብ ሲችል" የምለው:: ልቤ ታዲያ ያውቃል፣ "ቀላል ይችላል" ይለኛል !! ይሄንን የነፍስ ወግ ያዩት ሞልቃቆች ታዲያ፣

"ጌ...ታ ሆ...ይ ይሄን ምግብ ባርከልን" የምል መስሏቸው፣ "አብረን እናምልክ!" ይሉኛል:: እግዚአብሄርን በእውነትና በመንፈስ ለማምለክ፣ መንፈስህን በደቂቀ የሕይወት ክንድ ስር እያለህ፣ የእውነት መዳን፣ የእውነት ትንሳኤ፣ መኖሩን በመጀመሪያ እመን:: በተመረጠ ቃል፣ በጣፈጠ ዜማ መራር እውነትህን 'ለእግዚአብሄር አብረን እንንገረው' ብትለኝ እዛው የለመድክበት ነው የምልህ ፤ እዛው የለመድክበት !! ያውም ከተረት ጋር፣ "ዱባና ቅል አበቃቀሉ ለየቅል"::

## ክፍል ሀያ ሁለት

አንዳንዱ ሰው ዘመንን ተሻግሮ ታሪክን ተረማምዶ ከዓላማችሁ ሊያደናቅፋችሁ ፊታችሁ ይጋረጣል:: 'ቶሎ ተምሬ ይሄንን ህዝብ የምጠቅምበት መቼ ነው?' እያልኩ ሳስብ፣ 'የምበቀለው እንዴት ነው?' እያልኩ ባምሰለሰል መመረቂያ ቀኔ ደረሰ:: ያስተማሩን የተከበሩ መምህራኖቻችን መድረኩ ላይ በየመዓረግ ልብሳቸው ተተምነዋል:: ወደ በኋላ ዶክተር የሚሉ እምላክ ይነሱና፣ "ተመርቃችኋል ወደ ምድር ሁሉ ሂዱ ይሄንን ሕዝብ ፍዳውን አብሉት" ማለታቸው አይቀርም - ባይሉም ለእኔ ትርጉሙ ያ ነው !! ይሄን ሁሉ ዓመት ስማር የሕክምና ስነምግባር ከሕዝብ ከፋት በልጦ ልቤን ሊያራራው አልቻለም::

እኔ ግራ የገባኝ፣ "ሕዝቡ ማነው ?" የሚለው ጥያቄ ነው::

ሕዝቡ የገፉቸው ብዙ አቲዩዎች አሉ:: ገፊውን ከተገፊው ያልለየ በቀል ያን ያህል አያረካም፣ ሕዝቡ ማነው...? አንዳንዴ ደሃው ከፍ ሲል ሌላ ደሃ እየገፋ፣ የተገፋው ነፃ ሲወጣ የባሰ ገፊ

ሲሆን እያየሁ ሁሉንም በጅምላ ጠራርጌ አገር እንደሳር አዲስ ትውልድ ቢያቆጠቁጥባት ይሻላል እላለሁ::

የዚህ ህዝብ 'ዘርፌ' የምትባል አመልካች ጣቱ፣ 'ቀለመወርቅ' የሚባል አውራጣቱ ብቻ ጋንግሪን እንደለከፈው እግር ተቆርጦ የሚጣል አይደለም:: አገር በሙሉ፣ሙሉ አካሉ ተበላሽቷል፣ በከፋት ደዌ ነፍርቋል::

ምፀዓት፣ "እቃቃው ፈረሰ ዳቦው ተቆረሰ" ዓይነት የምድር እቃቃ ፍፃሜ እስመሆኑ የገባኝ ያኔ ነው:: የኖህ ውሀ፣ የሎጥ እሳት እንደምርቃት ቀኔ ይናፍቀኛል:: በየሆቴሉ ሕዝቡ ሲበላ ሲጠጣ፣ ሆዱን የምላብትን ሰሃን ጓዳ ውስጥ የምትፈትግ የአሱን ወጥ የምትቀቅል የራባት ወጥ ቤት ከኋላው በግፍ እንደምትገረድ እየታየኝ እበሳጫለሁ:: "እና ምን ይጠበስ ይልሀል" ሕዝቡ፤
'አንድ በአንድ ነበር ሜንጦ ላይ እያንጠለጠሉ መጥበስ' እላለሁ እኔ::

ሲፋቀር፣ ሲጋበና ሲወልድ ያበሳጨኛል:: አንዱ ሞቶ ሌሎች ሲቀብሩ ሲሄዱ 'መሞት አልነበረበትም' እይነት ጩኸታቸውና የአዞ እንባቸው ያስጠላኛል:: ሰዎች ታምመው ደፉ ቀና ተብሎላቸው መሞታቸው ይቆጨኛል::

የሎጥ እሳት...እሳት...እሳት...እሳት !! በየመንገዱ ይሄ ጨብራራ ፀጉራቸው በእሳት ተያይዞ ሲጮኹ ማየት እፈልጋለሁ:: ጅምላ ጨራሽ መሳሪያ ሰሙ ራሱ ይማርከኛል:: ይሄን በጅምላ ከፋትን ባህሉ ያደረገ ክፉ ህዝብ በጅምላ ቡምምምምምምምምምም!! ጭጭ!!

ሸክ ብዬ የበቀል ደወል በሚደወልበት ቀን ወደ መመረቂያ አዳራሹ ገባሁ:: ሁሉም ያየኛል - እውቃለሁ:: ምክንያቱም ጎበዝ ነበርኩ፣ ጎበዝ ነኝ...!! እዛጋ የተቀመጠው ዋንጫ የእኔ ነው፣ ይሄን ሕዝብ ኩሶ የማጣጣብት:: ምድረ ኩታራ ሥራ ፈላጊ፣ "የክብር እና የሙያ ስም አሳዳጅ" ሁሉ ዐይናቸው እያየ በፊታቸው እንደምነግስ በመዐረግ ዛሬ እንደምቀባ ያውቃሉ:: ለበቀል እንደምቀባ አያውቁም:: ዩኒቨርስቲ ሰይፏን ስላ ወደ ሕዝብ አንገት በመዓረግ ልታውዘገዝግ ነው-መጣሁልሽ አዲስ አበባ ሃሃሃሃ እያቃሰትሽ ከፊቴ ልትሰለፊ፣ ምጥ እያጣደፈሽ እድነኝ ልትይ፣ ደምሽ እየተንዠቀዠቀ አትርፊኝ ልትይ ሃሃሃ !!

እንኳን ደስ አላችሁ!

እንኳን ደስ አላችሁ!

እንኳን ደስ አላችሁ! እልልልልልልልል!

የበቀል ቀን እንደ'ት ፈጣን ነው፣ ይሄው ደረሰ !!

ተመልከቱ ከኋላ ወንበር ማን እንደተቀመጠ:: ነጭ ፀጉር ጣል ጣል ያደረገበት፣ ያበሻ ቀሚስ የለበሰች፣ ከዘመናት ጉስቁልናዋ አዲስ ልብስና ሹርባዋ ያልታደጋት ሚስኪን እናቴ - አቲዬ... እናቴ !! አቤት ሳያት ሰውነቴ እንዴት እልህ እንደሚሞላው !! አዳራሹ እንደዛሬ ሙሉ ሆኖ አያውቅም፤ እዚህ አዳራሽ ውስጥ ታላላቅ ምሁራን በተገኙበት አራት አምስት ጊዜ ተገኝቼ አውቃለሁ፤ ዛሬ ግን ሙሉ ነው - አቲዬ አለች !!

የሕዝቡ ብዛት ግርግሩ ግራ እንዳጋባት ከዛፒ ጎን ተቀምጣለች:: 'አልመጣም!' ብላ አስቸግራ ነበር ፈርታ:: አቲዬኮ ይሄን ሁሉ ዘመን 'ሰው' የዋለበት ውላ አታውቅም:: እንግዳ እንኳ እነዛፒ ቤት ከመጣ ምግብ አቀራርባ ወደ ጓዳ ነው ሩጫዋ:: ሰውን ፊት ለፊት ቀጥ ብላ አታይም፤ ቀምተዋታል ሰብዓዊነቷን:: 'ሰው ፊት እንዲህ አይቆምም' እያሉ፣ 'ኢቃ እንዲህ አይያዝም' እያሉ፣ 'ምን ትንከረፈፊያለሽ?' እያሉ፣ የእኔን እናት ካላላነሱ ትልቅ መሆን የማይችሉ ይመስል ምድረ ገለባ እስኪበቃው እናቴ ላይ ተጨማልቋል::

ዛፒ እጇን አውለበለበችልኝ ! ደግሞ ፈገግታዋ:: እንዴት ነው ደስ ያላት:: ሳላስበው አፍጥጬባቸው ነበር ለካ:: አቲዬ በስስት እንደምታየኝ ከዚህ ርቀት አውቄያለሁ:: የአርሷ መሲህ ጥቁር መጎናፀፊያ ለብሼ ሰላሳ ስምንት አመት የተኛችበትን የድህነት አልጋ፣ የመገፋት አልጋ፣ የመከላፈትና የመናቅ አልጋ፣ "አንች ሴት ልጅሽ ደርሶልሻል ተሸከመሽ ሂጂ" ልላት ፊቷ ቆሜያለሁ:: ሃሌሉያያያያያያያ እኔ ዶክተር አሸብር ነኝ !! ዶክተር አሸብር በአምላክ !! የተገፋችው የተናቀችው የአፀደ ልጅ!!

*እንኳን ደስ አላችሁ፣*

*እንኳን ደስ አላችሁ፣*

*እንኳን ደስ አላችሁ::*

እንዳንዱ ሰው ዘመንን ተሻግሮ፣ ታሪክን ተረማምዶ ከጓላማችሁ ሊያደናቅፋችሁ ፊታችሁ ይጋረጣል...ለምሳሌ ሂፖክራጥስ:: ይሄ ሰው የዘርፌ የበኩር ልጅ እስኪመስለኝ፣ የቀለመወርቅ የነፍስ ወዳጅ ነው ብዩ እስከጠረጥር ዛሬ ቅጥልልል ነው ያደረገኝ፡፡ በጓጓሁለት የምርቃት ቀኔ ፊቴ ተጋርጦ ማንም ሳያዘው ሽማግሌ ይሆናል ? (ወይስ የአዲስ አበባ ህዝብ ፈርቶ 'ከአሸብር ጋር አስታርቀኝ' ብሎ ልኮት ነው...?)

የሕክምና ዶክተር ሲመረቅ ቃለ መሀላ እንደሚፈፅም ባውቅም ረስቼው ነበር:: በዚህች ቀን ግን የሂፖክራጥስ መሃላ የሚባለውን አስመራቂው ዶክተር ቃል በቃል እያነበቡ ደግመን እንድንናገር ሲያደርጉን፣ ሆን ተብሎ አሻጥር የተፈፀመብኝ እስኪመስለኝ ከፍቶኝ ነበር::

እንዴት ነው፣ 'ሕዝብን ሙያዬን ተገን አድርጌ አልጎዳም' ብዬ የምምለው ?

በምንስ ሂሳብ ነው በጨዋነት የህመምተኛውን ክብርና ስብዕና በሚጎዳ መልኩ ምንም መጥፎ ነገር ሳላደርግ ብዬ የምምል የምገዘተው ? ይሄ ሕዝብ እናቴ ላይ በነፍሰ ሲጋዋ ሲጫወትባት ሂፖክራተስ ከነመሀላው የት ነበረ::

ኸረ ቀልድ፣ ሕዝቡ 'ልጄ አይደለህም' ብሎ የወረወረኝ እኔ፣ ሕዝቡ ከአሜሪካ ላሙ እኩል ሲያየኝ ያልፈለገ እኔ፣ "ሕዝቡን እንደ ቤተሰቤ የሕዝቡን ልጅ እንደራሴ ልጅ ላይ" ብዬ እንድምል ሂፖክራተስ ሽምግልና ፊቴ ቆመ:: ይሄ "ዶክተር" ለመባል የቻኮለ ሁሉ የተባለውን በተመሰጠ ይደግማል::

"በሕክምና ወቅት የምሰማውን የህመምተኛውን ሚስጥርም ሆነ የግል ጉዳይ በታማኝነት ልጠብቅ..." ወቸ ጉድ !

"...ሕዝቤን ከልብ በመነጨ ፍቅር፣ ሰብዓዊነት እና ሙያዊ ስነምግባር ላገለግል..." ካለፍኩበት የትምህርት ውጣ ውረድ ይልቅ ይህን ታላቅ መሃላ ማለፍ ከባድ ነበረ:: ያውም እኮ በእግዚአብሄር ስም፣ በእኔና በአቲዬ እግዚአብሄር ስም::

ግን አንድ እውነት ልንገራችሁ መሃላው ልብን ያርዳል:: ምንድን ነው የተማረን ሰው ፈሪ ማድረግ፣ ከውስጤ የፎከርኩበት በቀል ሲተን፣ እግዚአብሄር የበቀል ብትሬን ከእጄ ላይ ፈልቅቆ ሲወስድ ይሰማኛል:: ሰምል እንባዬ በዐይኔ ሞልቶ ነበር::

ግን ምን አደረገ የአዲስአበባ ሕዝብ ?ሕይወት ሰለሜ ሰለሜ እያጫወተው ከከፉው ኋላ ከፉ ተሰልፎ ማስቂያ በሌለው የከፋት ሰልፍ፣ አንድ አለንጋ ከኋላው እያራወጠው የሚኖር ሚስኪን - ምን አደረገ ?? ልጆቻችን ተመረቁልን ብሎ አልጋው ላይ እያቃሰተ እየጠበቀን ይሆናል:: ውጋቱን ችሎ፣ ቁርጠቱን ችሎ፣ ዘናጩ የአዲስ አበባ ሕዝብ ስንት ዓይነት ጉዳቱን በልብሱ ሸፋፍኗታል - ኢዲያ በቃ 'እፉ' ብዬዋለሁ !!

ኡፍፍፍፍፍፍፍፍፍ ራሴን ቀለለኝ:: ስሜ ከመድረክ ሲጠራ አዳራሹ በጭብጨባ ሲናወጥ መድረክ ላይ ቆሜ ተመለከትኩ:: የማታጨበጭብ ብቸኛ ታዳሚ አቲዬ ነበረች:: "የሰው ዐይን ልጄን..." እያለች እኮ ነው መች አጣሁት:: እናም አልኩ፣ "እህቴ ዛፒ እወድሻለሁ" ሁሉም ወደሷ ዞሮ አጨበጨበ:: እንዴ፣ ዛፒ አለቀሰች !! አቲዬን አየኋት ዛሬ ድረስ ቪዲዮውን ሳየው እልቅስ እልቅስ ይለኛል:: አቲዬን ስሟን ብቻ እንደጠራሁ እንባዬ ተዘረገፈ በቃ!!

ሌሊቱን ሙሉ ምን ብዬ እንደማመሰግናት አጥንቼ ነበር እኮ !!

*** *** ***

ሕይወት እንደ ሰዓት ናት:: በሙላትና በጉድለት መሐል ይዛ የምትነጉድ:: ሁሌጊዜ ትቆጥራለች:: ሩብ ጉዳይ፣ አስር ጉዳይ፣ አምስት ጉዳይ - ትሞላለች ! ከአምስት፣ ከአስር፣ ከሩብ - ትተርፋለች !!

ውስጤ ፍፁም ሰላም ይሻል:: ጥላቻና በቀል በመቀመር ያሳለፍኩትን መራር የውጣትነት ዘመኔን ለማካካስ ስለ ሰላም ብቻ ማሰብ እሻለሁ:: ለዓለም ሕዝብ ሁሉ ሰላም::

እናም እንዲህ አሰብኩ፤ ድንገት የዘገዩ የጸሎት ምላሽ ተልኮ ኒውክሊር በምብ እጇ ቢገባ ወሰጂ ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት፤ "ያውላችሁ ለሰላማዊ ጉዳይ፡ ለኃይል ማመንጫ' ምናምን ማለት የለም፤ 'በሕግ አምላክ ውሰዱልኝ...፡' ይልቅ በጅምላ ሕዝብ የሚፈጁትን ወባና ኢችአይቪ እንዋጋቸው ዘንድ መከላከያውን በገፍ ላኩልንማ"- እላቸዋለሁ !! ፈገግታ ልቤ ውስጥ አለ:: ልቤ ፈገግታን እየተለማመደች ነው::